# የታንጉት

## ምስጢር



ከብርሃኑ ዘሪሁን

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# የታንጉት ምስጢር

ከብርሃኑ ዘሪሁን

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ማውጫ

ምዕራፍ አንድ ........ 4
ምዕራፍ ሁለት ........ 43
ምዕራፍ ሦስት ........ 80
ምዕራፍ አራት ........ 111
ምዕራፍ አምስት ........ 149
ምዕራፍ ስድስት ........ 202
ምዕራፍ ሰባት ........ 240
ድኅረ ታሪክ ........ 292

# ምዕራፍ አንድ

ከፋሲል ዘመነ መንግሥት ጀርሞ የሥልጣን ማዕከል ሆና የኖረችው የጎንደር ከተማ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ፤ ከአዲሱ የቴዎድሮስ ሥርዓት፤ አዲስ የጦር አበጋዞች አዲስ ሠራዊት ጋር ለመስማማት አዲስ ቅኝት ሲከረክር ድንገተኛ ከባድ እንግዳ ወይም ሠርገኛ ደሶበት የቤቱን ዕቃ የሚያተረማምሰ ባለቤት መስሏል። የሚተራመሰው ማኅበራዊ ግንኙነት ግን በወጉ ሊቀመጥ አልቻለም። ሊቀመጥም አይችልም ነበር። ጎንደር ጥንት ከተቆረቆረች፤ ፈጽሞ የተለየ አዲስ ማኅበራዊ ዛፍና ፍሬ ለምቶባት ነበር።

ከተማ እንደ ማሳ ነው። ማኅበራዊ አኗኗር ማኅበራዊ አስተሳሰብ የዘራዉን ማኅበራዊ ሕይወት ያበቅላል፤ ያሽታል፤ ያፈራል፤ ማሳው በወቅቱ ካልታረመ ዝባዝንኬው እስከ ገሰሱ በርክቶ ይገኛል። ማሳው ራሱ በሚገባ ካልተያዘ እንክርዳዱም፤ አረሙም እየበዛ ሔዶ ጠቃሚ ፍሬ የማይሰጥበት ጊዜ ይመጣል። ዕዳሪ ይሆናል። የጎንደር ከተማ ማኅበራዊ ሕይወትም አንድ መቶ ስልሳ ዓመት በሚሆን ጊዜ ውስጥ እየተበላሸና ከመልካም ፍሬ ይልቅ፤ ሙጃ የበዛበት ማሳ እየሆነ ሔዶ ነበር።

ፋሲል፤ ጎንደርን ሲቆረቁር ሠራዊቱ ገና መዝናናት ያልለመደ ለተግባሩ ያልተሰላቸ፤ ምቾት ገና ያላሰናነፈው፤ ትዕዛዝ አቆብቁቦ የሚጠባበቅ ትኩስ አፍለኛ ነበር። አላማም ነበረው። በሃይማኖት ምክንያት ተነሥቶ የነበረው ሁከትና የርስ በርስ ጦርነት ጨርሶ እስኪረጋጋ ከሥፍራ ሥፍራ እየተንቀሳቀሰ አጥፊ ይቀጣል። አስቸጋሪ ይነገራል። ሰላም ያስከብራል። ከጦር መሪዎቹ ሌላ በስብከት፤ በውግዘት፤ በምርቃት መንፈሳዊ ሕይወቱን የሚያንቀሳቅሱና የሚመሩ፤ ከዚያም አልፎ መስቀል ከሰላጢን ይዘው አብረውት የሚሰለፉ፤ አዲሱን የካቶሊክ ሃይማኖት ነበሩ። የነጋሹም፤ የአንጋሹም፤ የዘማቹም የቀዳሹም ማኅበራዊ ሕይወትና አስተሳሰብ በአንዳች ዐይነት የዘመቻና የዘማች መንፈስ የተመራበት ወቅት ነበር። ፋሲል የምድራዊና የሰማያዊ ሥልጣን መግለጫ አድርጎ የቆጠራቸውን የቤተ መንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች ማሠራት የጀመረውንም ምናልባት በዚሁ መንፈስ ነበር። ለሌላ ነገር ቡቃያ፤ ፈር እየቀደዱ መሆኑ ግን በጊዜው አልታየው ይሆናል።

ከሚያማምሩት ሕንፃዎች አካባቢ መሸታ ቤቶች ብቅ ብቅ አሉ። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነጋ ለወሬ፤ መሽ ለዘኬ የሚሉ ጠምጣሚዎች ወጣ ወጣ አሉ። በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ ሴት ሲያጫውት የሚውል ዋልጌ ወታደር እንደ አረም እየበቀለበት ሔደ። በየመንደሩ ሽቶ ተቀብተው፤ ሰንደል ወይዛዝርት መኳንንት

ማስተናገድና ማስደሰት፤ ማጫወት ሥራቸው የሆነ ወይዛዝር ተፈጠሩ። በየዕልፍኙ ከሴት ጋር የሚወዘፉ መኳንንት አቆጠቆጡ።

ከፋሲል የተከተሉት ነገሥታት፤ የየራሳቸው ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ሲያንፁ፤ ጎንደር በሕንፃም በነዋሪ ብዛትም እየለማችና እየደመቀች ስትሔድ እንደ አረጀ ማሳ ማኅበራዊ አራሙጫዋም በዚያው ልክ እየብረከተና እየሰፋ ሔደ። በዘመነ መሳፍንት ደሞ፤ አራሙቻው ደኅናውን ማኅበራዊ ሰብል ጨርሶ የዋጠው ከሚመስልበት ደረጃ ደረሰ።

ግንቦቹ ሳይቀሩ አርጅተው ነበር። አንዳንዶቹ ግድግዳቸው ፈራርሶ፤ መዝጊያዎቻቸው ወላልቀው የሌሊት ወፍ ማደሪያ ሆነዋል። ብዙው መንደር ጠፍ መስሏል። ሁሉ ታክቶ፤ ሰንፎ የተወው ይመልስ ከውጭ በኩል በመልካም ሕይወት እንደውጪ መልኩ ያረጀ፤ የበሰበሰ ዐይነት ነው። መስፍኑ፤ መኮንኑ የባላገር አፍንጫ እየሰነገ የሚያጋፍፈውን በመቀለብ፤ ለሌላ ተግባር የማይባክን ጉልበቱን የሚያውልበት ብዙ ዕቁባት በየጉራንጉሩ አስቀመጠ። እንዳሰኘው፤ እንዳደረሰው እምብርት እስኪያብጥ መብላት፤ ጢንቢራ እስኪዞር መጠጣት፤ በዚያው መዘሞት ነው። ነፍጠኛውና ጭፍራው ከአለቃው የተረፈውን የገበሬ ጎተራና ጎታ እያሚጠጠ እንዳቅሙ ሁለት ሦስት ውሽማ ይዞ ሲተሻሽ መዋልና ማደር ነው። ለተግባር፤ ለዓላማ የሚቀሰቅሰው መንፈስ አርጅቷል። ገርጅፏል። ከፉና በጎ ለይቶ የሚሰነጥቀው ሕሊና ዶልዶሟል። የቀረው ለደስታ፤ ለምቾት ለፍትወት የሚንቀሳቀስ ወደ እንስሳት ስሜት የተቃረበ ሕይወት ነው። ይህም ሕይወት ግን ለመኖር የለመደውን ያለ ማቋረጥ ለማግኘት ይፈልጋል። በዚህ ረገድ ዕቁባቶችና ውሽሞች ሌላም ሚና ነበራቸው።

በየመሳፍንቱ በየመኳንንቱ እልፍኝ፤ ጨለማ የዋጠው ሤራ ሲዶለት ያድራል፤ በዚህም ሤራ ምክንያት ዛሬ የነገሠው በሣልስ ወህኒ አምባ ይጋዛል፤ ወይም የመጨረሻ እስትንፋሱን ውጦ ይገኛል። ሥልታን እንደ ነፋስ ሳይታወቅ አቅጣጫውን በሚለወጥበት፤ ሹመትና ጉልት ከዋለበት በሚያድርበት ሁናቴ መካከል ታማኝነትና መታመንም ቋሚ ሊሆን አይችልም። ፊት አይቶ፤ ሚዛን ገምቶ ይለዋወጣል።

ለዚህም ወይዛዝርቱ፣ ዐይን፣ ጆሮና አፍ ሆነው ይሠራሉ። እንደ ሐረግም መሳሳቢያና መንጠላጠያ ሆነው ያገለግላሉ። እና፣ ይህንን ሚናቸውን በሜባ ይጠቀሙበታል። ራሳቸው ባይሾሙ ለሹመት ያሳጫሉ። ባይቀጡ ጥርስ ያሰባሉ። ባይዋጉ ያጣላሉ። አንዳንዶቹ ከሁለት ባላጋራዎች ጋር ሳይቀር ግንኙነትና ወዳጅነት በመፍጠ፥ ከዚህ ወደዚያ ከዚያ ወደዚህ ነገር እያቀባበሉ፣ ጉልበት እያፈታተሹ፥

አንዱ ቢወድቅ ከሌላው ወደዚህ ነገር እያቀባበሉ፣ ጉበት እያፈታተሹ፤ አንዱ ቢወድቅ ከሌላው ተንጠላጥለው ይቀራሉ። ቆይተው ሌላ መጠባበቂያ ያበጃሉ። ነገራቸው ቢጋለጥ እንደ ብልህ፤ እንደ ብልጥ ይታዩበታል እንጂ አያፍሩበትም ነበር። እንደ ጅል፤ «እንደ ባላገር» የሚታየው የጥንቱን ሥነ ምግባር ልጠብቅ ያለው ግትር ነበር። ነጋዴው ሳይቀር በዚህ የማኅበራዊ ሕይወት ድቀት ውስጥ ገብቷል። በረሃ አቋርጦ፤ ቆላ ወርዶ፤ ደጋ ወጥቶ በሚነግደው ሸቀጥ ሕሊናው በቅንነት የተመነለትን ትፍር በምዝር ከአለቃ መመንተፉ ያስመረረው ጎንደርን ትቶ ሌላ የንግድ ኬላ መምረጥ አለበት። በጎንደር የቀረው ግን በሚዛን ማበል፤ በስፍር መሸፈጥ፥ ያካክሰዋል። በጎንደር ሲኖሩ እንደ «የጊዜው ጎንደር» መሆን ግድ ሆኖበት ነበር። በዘመነ መሳፍንት ፍጻሜ ላይ የጎንደር ማኅበራዊ ኑሮ፣ በሥነ ምግባር የላሸቀ፣ በአስተሳሰብ ያረጀ፣ በሥራ እንቅስቃሴው የደኸዬ ዓላማ የለሽ ነበር።

ቴዎድሮስ የአዲስ ሥርዓት ሰይፍ መዝዞ በድንገት ሲመጣ ወዲያው ቢደናገጥ አይስገርምም። ከድንገተኛ ድንጋጤው መለስ ሲል ደግሞ፣ የህልውና ነገር ነውና፤ መወጣጫው መንገዱን መፈለጉ የማይቀር ነበር።

አዲሱ የቴዎድሮስ ሥርዓታዊ ሰይፍ የጎንደርን ሕይወት እንዳስደነገጠው ሁሉ የጎንደር ሕይወት ያስደነገጣቸው የቴዎድሮስ ወገን ሰዎችም ነበሩ። የገርዬ ሚስት ታንጉት ናት።

ታንጉት የኖረችው በሕፃንነቷ በገጠር፤ በኋላም፣ ባልዋ በዘመተበት፤ ቴዎድሮስ በሰፈረበት በየጫካው ስትዘዋወር ነው። ቀደም ሲል ያየችው ትልቅ የሕዝብ መኖሪያ ሠፈር ቢኖር፤ የጭልጋና የመተማ መንደሮች ነበሩ። እነርሱም በጊዜው አስደንቀዋት ነበር። የደረስጌ ጦርነት እንዳበቃ፤ ገብርዬ ቋራ ድረስ ገሥግሦ በመምጣት ጎንደር ይዘዋት ሲገባ ዐይኗን ማመን አቃታት። ግንቦቹ፤ ሕንፃዎቹ በሰው እጅ የተሠሩ አልመሰላት አሉ። ራስዋ የለበሰችው ጥበብ ኩታና ቀሚስ የማያሳጣ ቢሆንም ከጎንደር ወይዛዝርት አለባበስ፤ ሆነባት። የካህናቱ ጥምጥም ሳይቀር ሌላ ነው። የባለሙያን ሁሉ ትንግርት ሆነባት። የካህናቱ ጥምጥም ሳይቀር ሌላ ነው። የባለሙያን ልቅ ክርክሞሽ ያስንቃል። ድንገት ከሰው መንደር ገብቶ እንደተናገረ የዱር አውሬ አንዳች ዐይነት ፍርሃት ቢጤ ተሰማት።

«አንትዬ እኛ ማናቸው? አቡኑ?» ስትል ገብርዬን ጠየቀችው፤ በጃኖዋቸው ላይ ካባ ደርበው ዝማሜ እንደሚወርዱ መቋሚያቸውን እያወዛወዙ በአጠገባቸው ያለፉትን ካህን በዐይንዋ እያመለከተች። ከኋላቸው ሁለት ደቀ መዛሙርት ይከትተሉዋቸዋል።

«አንድ ቄስ ናቸው!» ገብርዬ በማቃለል ፈገግታ መለሰላት።

«አታውቃቸውም?»

«የጎንደርን ቄስ ሁላ የት አውቀዋለሁ ብለሽኝ!?»

«ኧረ እኚህ ትልቅ ናቸው!» አለች ላለመረታት።

«ግዴለሽም እየቆየሽ ታይዋለሽ።»

«ኧረ አንተዬ» ብላ ሳትጨርስ ተወችው። የሐር ጥላ አሲዛ በሠጋር ግራጫ በቅሎ የምትፈሥሠውን አንዲ ወይዘሮ በአድናቆት ዐይንዋን ትክል አድርጋ ትመለከታለች።

«ምነው?»

«ያች ወይዘሮ ማናት አንተዬ?»

«የጎንደር ሴት?»

«ማለ - ማለቴ የማን ምሽት ናት?»

«የታባቴን አውቃታለሁ ብለሽኝ?»

‹እህ - ጎንደር ተቀምጫለሁ ትላለህ እንጂ እንደኔው ባላገር ነህ። አንዱንም ሰው አታውቀው» አለችው በቀልድ ሽጉጥጫ።

«ምን አታከረሽ። ይኼነ ኮማሪት ትሆናለች።»

«እንደዚህ ያለችው?» ማመን አቃታት፤ ‹ዛዲያ ባሎቻችን እነዚህን እያዩ› የሚል የፍራቻ ሐሳብ ውልብ አለባት።

ማረፊያ ቤታቸውም ቢሆን፣ በመጀመሪያ እንደ ቤተ ክርስቲያን አስፈርቷት ነበር። ከአጣጣሚ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ግቢና የግንቡን ጥግ ይዞ የተሠራ ደርብና ምድር ቤት ነው። ከአካባቢዎቹ ሕንፃዎች ጋር ሲነጻጸር እስከዚህም ትልቅ አይደለም። ደርቡ ሰፋ ያለ አዳራሽ፣ መለስተኛ እልፍኝ፣ በሁለት በኩል አነስ አነስ ያሉ ሁለት ጓዳዎች፣ ከወደኋላው ለብቻ ማድቤትና የዕቃ ቤቶች አሉት። ዱሮ የደጃዝማች ወንድይራድ የነበረው ይህ ቤት፣ ራስ ዐሊ ከነመኳንንታቸውና ከነሠራዊታቸው ጎንደርን ለቀው ከሸሹ በኋላ ወና ሆኖ ቆይቷል።

«ይኸን ሁሉ ምን ልናገረው ነው?» ስት ጠየቀች፣ ገብርዬ አስገብቶ እንዳሳያት። ዕቃ የሌለበት አዳራሽ ከትልቅ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ተሰፋ መስሎ ታያት። «ልጅ የለን ውላጅ የለን» አለች በቅሬታ መልክ።

«እንግዲህስ መቾስ የቋራ ጎጆ ይዘን እንመጣ። እንደሚሆን አሟሙቂው እንጂ፣ እንግዳም መምጣቱ አይቀር። እግዚአብሔር ታለ ደሞ!»

ታንጉት ልጅ አለመወለዷ ሁልጊዜ እንደሚያሳስባት ስለሚያውቅ ከፈገግታ ጋር በማባበል የጉንጩዋን ስርጉዳት በጣቱ ጠቅ አደረጋት።

እንዳለውም ቤቱ ዕቃ ሲገባበት እሳት ሲጤስበት ሰብሰብ ያለ መሰለ። ታንጉትም ቤት ማሰናዳቱ፣ ምግብ ማዘጋጀቱ ጊዜ እያሳለፈላት፣ ፍርሃት ፍርሃት ማለቱ ተዋት። ወደ መጀመሪያ ገደማ አዳዲስ ዕንግዳ ግን ወደ ቢታቸው አልመጣም። ቤተ ክርስቲያን ስትሄድ ገበያ ስትወጣ፣ በቤተ መንግሥት አካባቢ ስትገኝ የሚያጋጥሟት እነዚያ የተሸሞነሞኑ የጎንደር ወይዛዝርት፣ የተኮፈሱ መኳንንት ለወጉ ያህል አንገት ቀልበስ አድርገው በሩቅ ‹ጤና ይስጥልን! እንደምን አደራችሁ? እንደምን ዋላችሁ?› ከማለት በስተቀር አልቀረቧትም። ጎንደሮች ማን ምን እንደሆነ እያጠያየቁ ነበሩ። የዘመነ መሳፍንት የሥልጣን ከዚህም ከዚያም መጓተት ብዙ አስተምራቸዋል። ‹አይተነው ጊዜ ወዳደላበት› እንዲሉ፣ እንዲያው ለመወዳጀት ሲባል ብቻ ዘው ተብሎ ዕውቂያ አይደረግም። በዚህ ላይ የመግደርደሩም ልማድ አለ። አንዳንድ ጊዜ ወደ ማታ ቤታቸው የሚመጡት የገብርዬ ጦር አበጋዞችና አንዳንድ ቀን ወደ ማታ ቤታችው የሚመጡት የገብርዬ ጦር አበጋዞችና የታንጉት ቀደም ሲል የምታውቃቸው ሚስቶቻቸው ብቻ ነበሩ።

ዐልፎ ዐልፎ ቴዎድሮስ ይመጣሉ። መስተንግዶውም፣ ጭውውቱም ከወትሮው የተለየ አይደለም። ስለ ወደ ፊቱ ያወጋሉ፤ ይመካከራሉ፤ ይከራከራሉ፤ በመካከሉ ያለፈ ትዝታ ያወሳሉ። ቀልድ ወይም ተረብ ቢጤ ጣል ጣል የሚያደርግም አለ። አብዛኛው ግን፤ ቁም ነገር ብቻ ነው። ቴዎድሮስ ስለ ዘመቻ በሚያወጉበት ጊዜ ዐይናቸው እንደ ጧፍ የሚበሩ፤ ግድግዳውን አልፈው አድማስ የሚመለከቱ ይመስላሉ።

በእንደዚህ ጊዜ ታንጉት፤ አድናቆት አይሉት አዘኔታ አንዳች ዐይነት ስሜት ገረፍ ያደርጋታል። ከሕፃንነቷ ጀምሮ አብራችወ ኑራለች። አሳድገው ለገብርዬ ድረዋታል። ግን ስለ እርሳቸው ያላት ስሜት ዐልፎ ዐልፎ ግራ ያጋባታል።

ሴቶቹ፤ ለብቻቸው ወደ አንድ ጥግ ሆነው ዝም ብለው ከማዳመጥ ወይም እርስ በርሳቸው የባጥ የቆጡን ከመንሾካሾክ በተቀር በወንዶቹ ጭውውት አይገቡም።

አንድ ቀን እንደዚሁ ራት ተበልቶ ሲጨዋወቱ ለማቆላመጥ ባወጡላት ስም «እንጓች?» ሲሉ ጠሯት። በዚህ ስም ሊጠሯት መጀምሪያ ያወጡላትን ቀን ብዙ ጊዜ

ትዝ ይላታል። በወይኒ መንገድር እናቷ ታማ ቤት ከዋለች በኋላ ነው። ያን ጊዜ ስሙን ባታውቀውም የበፊት ካሣ፤ የአሁኑ ቴዎድሮስ ከአንድ ሦስት ሰዎች ጋር ቤታቸው ይመጣል። ደጅ ተቀምጣ ትጫወት ነበረ። ‹ነይ ሳሚኝ አንቺ› ሲል ይስማትና ቤት ይገባል። ከእናትዋ ጋር ረዘም ያለ ጊዜ ቆይቶ ሲወጣ፤ ከምትጫወትበት ቆርጠጥ ብሎ ይቀመጥና ጉንጭዋን እያሻሸ፤ «ስምሽ ማነው የኔ ድማም?» ሲል ይጠይቃታል፤ ትነግረዋለች። «እኔ ደግሞ አንዳች ነው የምልሽ።» አንዱን ሰውዬ እንዲሰጣት ያዘዋል። ከዚያም ዳቦ ቆሎውን በቀሚሷ ጫፍ እያሲያዘ፤ «ስታድጊ ዳቦ ታነጉችልኛለሽ። እሺ?» አልትና ሔደ።

«አቤት! አባ ታጠቅ» አለች ታንጉት ከትዝታዋ ስትመለስ።

«ጎንደርን ተላመድሽው?»

«ኧረ እኔ እንጃ!» አለች የምትመልሰው ግራ ተጋብቷት።

«አይዞሽ ትለምጅዋለሽ። ጎንደሮች አውሬም ያስለምዳሉ። ግና ዋ! ዋ! እነሱን እንዳትመስይ ወይም ደግሞ ወዬ በነገር እንያደጠምዱሽ! ኋላ ነግሬሻለሁ» አሏት በቀልድ ማስፈራራት።

«እኛ ምንድን ነን አባ ታጠቅ?» ስትል የእንግዳ ምሽት ከጥግ ጠየቀች። እንግዳን ከማግባቷ በፊት ጎንደር ተወልዳ ያደገች የመኳንንት ዘር ነበረች።

«ኧረገኝ!» አሉ ቴዎድሮስ የደነገጡ መስለው እየሣቁ። ሌሎችም ሳቁ። «አንቺና ተዋበችማ እኛን መስላችኋል፤ አጥምቀናችሁ!»

አንዳንዶቹ አንዳንድ ቀልድ ካከሉበት በኋላ ያበቃለትና የተረሳ ይመስል ጭውውታቸው ወደ ቁም ነገሩ ተመለሰ። ድጋሚ አላነሡትም።

ታንጉት ግን ጨዋታው፤ ቀኑም ከዐለፈ በኋላ አንዳንዳች ሟርት፤ እንደ መጥፎ ትንቢት በሐሳብዋ መጉላላቱ አልቀረም። ‹ምን እንዳያደርጉኝ ነው? ምን እንዳላደርግ ነው? ወይስ ምን እንዳልሆን ነው?› የዕለት ሥራዋን ስታከናውን ጥያቄዉን ለራስዋ በሐሳብዋ ጠይቃ መልሱን ታሰላስላለች፤ አይመጣላትም። ግን የጎንደር ወይዛዝርት፣ መኳንንትና ካህን በድንገት ሲያጋጥሟት አንዳች ዐይነት ስሜት ያድርባታል። ጥላቻም አትለውም፤ ፍቅርም አትለውም፤ እየቀፈፋት፤ መጠጋት እየፈራችው ገልጦ የማወቅ ዐይነት ፍላጎት ነው። ስታብላላው፤ እያደርም እየረሳች ስታስታውሰው ሰነባበተች። በቤት ሥራዋ በማተኮር ጨርሶ ልትረሳውም ትሞክራለች። እንደዚያ ሰሞን ፈትላ፤ እንደዚያ ሰሞን ስንት ዐይነት ስፌት ወጥና

አታውቅም። በዚያ የጎንደር ወይዛዝርት መኻል የገብርዬ ጠባይ፤ ለእርሷም ያለው ስሜት ይበልጥ ያማረ እንጅ የተለወጠ ሆኖ አልተሰማትም።

መዋል ማደር መቸም መልካም ነውና ቀናት ሲያልፉ፤ ጊዜዋን በሆነውም ባልሆነውም ሥራ ስታላልፍ፤ ሐሳቧ ደብዘዝ ማለት ሲጀምር፤ መላ ጎንደርን በወሬ ያተራመሰው የሹም ሽር ነገር መጣ።

ቴዎድሮስ፤ ብዙ ጊዜ በውጭ ችሎት ሳይቀመጡ ከውስጥ ብቻውን፤ አንዳንድ ጊዜም ከቤል እየዋሉ መሰንበቻቸውን ታንጉት ቤተ መንግሥት ስትሔድ ብታውቀውም በከተማው የሚነፍሰውን ወሬ የምታመጣላት፤ ከአካባቢው የሙያ መሰሎቿ ጋር በቀላሉ የተለማመደችው ገረድዋ በለጡ ናት። ወጣ ብላ በገባች ቁጥር፤ እንደ አፋራም ሕፃን መዳፍዋን እያፋተገችና ዐይንዋን እያቅለሰለሰች የሰበሰበችውን ወሬ ትነግራታለች።

ጎንደር በወሬና በጥይይቆሽ ሲታመስ ሰንብቷል። ከጎጃም አባይ ባሻገር ድረስ ድፍን በጌምድርን ይዞ፤ ከወሎ እስከ አማራ ሳይንትና እስከ ዋድላድላንታ - እስከ ቦረና አጠቃቅሶ በትግሬ የደጃች ውቤ ግዛት የነበረውን ሁሉ ይዞ፤ በምዕራብ ቆላ ያለውን፤ የጭቆ፤ የቋራ፤ የአዳኝ አገር ማዶ እስከ ገዳሪፍና እስከ ስናር ያለውን ሁሉ አጠቃሎ፤ የሚገዛ፤ ‹ገዥ ነኝ› የሚል፤ ግዛት ለማግኘት የሚመኝ መኳንንትና ጭፍራ ያለው የጎበዝ አለቃ ሁሉ ጎንደር ከተማ እየገባ ተከማችቷል። በቀድሞው ለየብቻው የነበረ የሦስት መስፍን አገር ገብሮ፤ ከትቶ በአንድ ጊዜ ሲገባ አዲስ ነገር ከመሆኑ ሌላ አመጣጡም አዲስ ነገር ሆኖበታል። ዱሮ የስሜኑ ደጃች ውቤ፤ ለመታረቅም ለመስማማትም ጎንደር ሲገቡ ነጋሪታቸውን እያስጎሸሙ ነበር። እነደጃች ማሩ፤ እንደ ደጃች ክንፉ፤ እነ ደጃች ተድላ ጓሉ እንደዚሁ እስከ ፋሲል ግቢ አጠገብ ነጋሪት ያስሙቱ ነበር። አሁን ግን መኳንንቱ ነጋሪት ማስመታት ቀርቶ፤ አብዛኛው ሠራዊቱን በአንገረብና በቀሃ ወንዝ መስከ በድንኳን ሁላ እንደ ሌጣ ከብት ነዳው!› ይባላል።

እንደ ነገ ስብሰባ ተጠርቶ የሹም ሽሩ ሹክሹክታ፤ ሲዛመት አደረ።

‹ሰምተሃል? እገሌ የራስ ወርቅ ሊያስር ነው!› ይላል አንዱ። ‹ደጃዝማች እገሌ ከርብ እስከ መተማ ሊሾም ነው ተባለ!› ይላል ሌላው። ‹አትለኝም! ኧረ በየት ወንድነቱ?› ሲል አድማጩ ይገረማል። ‹ደጃዝማች እገሌ ወህኒ አምባ ተላኩ አሉ?› ሲል አንዱ መርዶ ያሰማል።

‹አይ አበሳ!› ይላል ሌላው በጭንቀት።

እያንዳንዱ የወደደውን ይሾማል፤ የጠላውን ይሽራል፤ ያግዛ፤ በምኞቱ።

አንድ ቀን ሲቀር ታንጉት ስለ ሹመቱ ገብርዬን ጠየቀችው።

«ምን አስጨነቀሽ?» አላት በማቃለል።

«አይ እንዲያው ወሬው ገርሞ ነው አንጂ!» ከተማው ሁሉ ሌላ ነገር የለውም አሉ። ለመሆኑ አንተ ምን ትሾማለህ»

«ወቸው ጉድ! ደግሞ እኔዉ፤ ራሴው ነኝ የምመርጠው! ለሁሉስ ነገ ትደርሽበት የለ?» አለና ጉንጯን ቆንጠጥ አደረጋት።

በነጋው ጧት ገብርዬ ከሐር እጀ ጠባብና ሱሪው ላይ የአንበሳ ለምዱን ደርቦ፤ አንፋሮውን ደፍቶ በግራ ጎኑ ጎራዴውን በቀኝ ጎኑ ሽጉጡን ታጥቆ፤ ታንጉትን በሐር ጥልፍ ቀሚስና ኩታዋ ላይ ጎንደር መጥታ ከሰነበተች በኋላ፤ ‹ኧረ ጎንደሮች የቋራ ቡትቷም ብለው እንዳይሰዱብሽ!› በለው ቴዎድሮስ የሰጧትን ሐር ካባ ወደ ቤተ መንግሥት ተጓዙና ሲገቡ፤ እርሱ ወደ መሰሎቹ እርሷም ወደ መሰሎቿ ተለያዩ።

መኳንንቱ ከነሠራዊቱ ከሠፈሩበት ወይም ከዐረፉበት እየመጡ ወደ ዋናው የፋሲል ግምብ አዳራሽ ቡ። ትርምስ፤ ግርግር፤ ጩኸት የለም። ከፋሲል ግምብ ግቢ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም፤ ብዙም ሳይንቀሳቀሱ ብዙም ሳይነጋገሩ በታዛቢነት የሚያስተውሉ ይመስላሉ።

ሁሉም ገብቶ በአጋፋሪው እየተመራ በየሥፍራው ከተቀመጠ በኋላ፤ ቴዎድሮስና ተዋበች አቡነ ሰላማ ትንሽ ቀደም ብለው፤ ገብርዬ ከገሞ፤ ከዓለሜና ከሌሎችም ጋር ሆነው፤ እንደ ሥርዓቱ እስኪቀመጡ አዳራሹ የነበረው ቆም ብሎ ተቀበላቸው። ታንጉት ይህንን አዳራሽ ቀደም ሲል ደጋግማ ያየችው ቢሆንም፤ ከዚያ በፊት አይታ በማታውቀው ይህንን በመሠለ ሥነ ሥርዓት ከፊትዋ ሲደቀን፤ የመጀሪያ ጊዜዋ ስለነበር የሚስብ የሚማርክ ትርዒት ሆነባት። ከውስጥ በኩል የሚሰናዳውን፣ የሚቀራርበውን ለመርዳት ወጣ ገባ ብትልም ዐይንዋ፣ ጆሮዋ፣ ሐሳብዋ ሁሉ በአዳራሹ እንቅስቃሴ ላይ ነበር። ለምን እንደሆነ ራስዋም ምክንያቱ አልገባትም። ገብርዬ እንደሆነ መሾሙ እንደማይቀር ታውቃለች።

ሊጋባው ከቴዎድሮስ አጠገብ ቁሞ፤ የመኳንንቱን ስም እየጠራ ማዕረጋቸውንና ግዛታቸውን ወይም ሥልጣናቸውን ከፍ ባለ ድምፅ ሲናገር፤ አንድ በአንድ ብድግ እያሉ ለቴዎድሮስ እጅ ይነሡና ተርታ በቆሙት አጋፋሪዎች እየተመሩ የዕቃ ቤቱ ሹም ወደ አለበት ክፍል ይሔዳሉ። ከዚያም ቀሚሳቸውን ለብሰው ሲመለሱ እንደገና እጅ ይነሣሉ።

ሴቶቹ፤ የየራሳቸውን ባል ወይም ወገን ሲሾም ፈንደቅደቅ ሲሉ ታንጉት አብራ ብታጅብም፤ በአብዛኛው የሚሰማት ከተካፋይነት ይልቅ የተመልካችነት ስሜት ነበር። ገብርዬ፤ በፊታውራሪነት ማዕረግ የጦር አዝማች ተብሎ ሲሾም ብቻ ልብዋ ትርትር አለባት። እንግዳ ‹ራስ› ሲባሉ። የገብርዬ ሹመት ቢያስደንቃትም፤ ስሜቷ የደስታ ይሁን የድንጋጤ በትክክል አልታወቃትም።

እያንዳንዱ ሹመት ሲነገር መኳንንቱ እርስ በርሱ ይተያያል። አንዳንዱም ቀሚሱን ለብሶ ወደ ቦታው ሲመለስ ከንፈሩን እንደመንከስ ሲያደርግ ያስታውቃል። እንደ በፊቱ ራስ ወርቁ፣ እንዲያምስ ኢል የጋብቻ መደለያው፤ ሥልታን ባይኖርበትም ሲጠሩት የሚከብድ ግዛት የሚሰጥ የመሰላቸው ብዙዎች ነበሩ። አብዛኛዎቹ ያሰቡትን አላገኙም።

ብዙውን መኳንንት ይባስ ያናደደው ሌላም ሹመት ተከተለ። ሊጋባው ላንዳፍታ ገታ አለና፤ ‹ልጅ ዮሐንስ› ብሎ ሲጣራ ጆን ቤል ተነስቶ እጅ ነሳ። መኳንንቱ ሁሉ የሚሰማውንና የሚያየውን ማመን እስኪያቅተው ድረስ ተደመመ። ሊጋባው ‹ሊቀ መኳስ› ብሎ ሲናገር ቴዎድሮስ የመኳንንቱ ስሜት ገብቷቸው ፈገግ አሉ። ስምምነት የሚጠቅ ይመስልም ወደ አቡነ ሰላማ ዘወር ብለው ተመለከቱ።

ሹመቱና ሽልማቱ አብቅቶ፤ ለስሙ ‹ቁርስ› የተባለ ግን ከምሳ የከበደ የእልፍኝ ግብር ሲቀርብ የብዙው ሆድ ተዘግቶ ነበር። አብዛኛው የፈለገውን አለማግኘቱ ሳይናስ፤ ባሕር አቋርጦ የመጣው የውጭ አገር ሰው ‹ሊቀ መኳስ› መባሉ እንደ ትልቅ ክህደት ቆጠረው። ጆን ቤል ከቴዎድሮስ ዘንድ ባለሟልነቱን ካጠበቀ ወዲህ ተጠምቆ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መቀበሉን ግን ብዙዎች አያውቁም ነበር።

መጠጥ አሳላፊዎች አስቀድመው እንደታዘዙ ያህል መኳንንቱ ምግቡን ችላ ማለት ሲጀምሩ ማሳለፉን ትተው በየጥጉ ቆሙ። ሊጋባው አጨበጨበና፤ ‹እስቲ አንደዜ ዝም በሉ!› ሁሉ ከሐሳቡ ጋር ስለሚነጋገር በፊትም ቢሆን ብዙ ድምፅ አልነበረም። ታንጉትም ተረጋግታ ሁናቴውን ትከታተል ጀመር።

ቴዎድሮስ፤ ዐይናቸውን ተራ በተራ በእያንዳንዱ መኳንንት ላይ አሳረፉት። ሐሳባቸውን ለመገመት ከመሞከራቸው ጋር፣ ‹ሐሳቤን ተረዱልኝ፤ ፍቅራችሁንና ታማኝነታችሁን ስጡኝ› በሚል አስተያየት አንገታቸውን ቀን አደረጉና ፈገግታ አሳዩ። ምናልባት ራሳቸው አይታወቃቸውም እንጂ፤ ከፊታቸው ቀድመው ሞትን የሚጋፈጡ ተከታዮች ካፈራላቸውም የተፈጥሮ ወይም የመሪነት ችሎታ ጋር፤ ስስና ዘርጋ ያሉትን ከንፈሮቻቸውን ሲገልጡ ብቅ የሚለው ፈገግታቸውና ጉድጉድ ብለው እንደቡኸር ዐይን የሚቁለጨለጩት ዐይኖቻቸው አስተያየት፤ አንዳች የመሳብ ኃይል ነበራቸው። ተመልካች፣ በፍቅርና ትህትና እወነተኛነትና ቆራጥነት

አዋሕደው የሚገልጹ መስሎ ይሰማዋል። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህንን ተአምር አልሠራላችሁም። አብረዋቸው ከተነሱት የቅርብ ባላሟሎቻቸው በስተቀር፣ ሹመት በዘር፤ በቀሚስ ለስም የጠበቁት አብዛኞቹ መኳንንት የሕሊናቸው ትዝብት አገጫቸውን ወደታች እንደ ጎተተው ያህል አንገታቸውን አቀረቀሩ። ከዘመቻ በፊት፤ ከድል በኋላ፤ የጦር አበጋዞቻቸውንና ሠራዊታቸውን በዙሪያቸው ሰብስበው መወያየት የሚያዘወትሩት ቴዎድሮስ፤ በአሁኑ አዳራሽ ውስጥ አብዛኛው የቅሬታ ስሜት መታየቱን መገንዘባቸው አልቀረም። በዙሪያቸው ያለውን ያቀረቀረ ፊት ሲያስተውሉ ለሚያቀርቡት ሐሳብ ተስማሚ ጊዜ አለመሆኑ ተሰምቷቸዋል። ነገር ግን፤ የዘመነ መሳፍንት ዝብነና ላስለመደው መኳንንት ቅብጥብጥነት፤ ፊት መስጠት፤ ‹ባለጌን ቢያከብሩት የፈሩት ይመስለዋል› እንደሚባለው የሚሆን መሰላቸው። ከዚህም በቀር ከጆን ቢለ ጋር ብዙ ከተመካከሩና ከተወያዩ ወዲህ፤ ሐሳባቸው ጊዜ እንደማይሰጥ ምጥ ከውጽጥ ይገፋቸው ነበር።

«እህህህ!» ሲሉ ጉሮሮዋቸውን ጠረጉና፣ አሁንም ሰዉን እንደገና ቃኝተው ንግግራቸውን ጀመሩ። «ታሁን በፊትም ቢሆን በዚህ አዳራሽ ሹም ሽር ሲደረግ ቀሚስ ሲሰጥ የኖረ ነው፤ አዲስ አይደለም። እነ ራስ አሊ፣ እነ ራስ ጉግሣ፣ እነ ራስ ይማም፣ እነ ራስ ማርዬ፣ ኧረ ስንቱ ተቆጥሮ! አገሬን ላቀና ወገኔን በመልካም ላስተዳደረ ስለሆነ የምሾመው የምሸልመው ለዚህ ይረዳኛል የምለው እንጂ ሌላውን አይደለም።

በመከፋት አቀርቅሮ የነበረው መኳንንት፣ በማድነቅ ሳይሆን ጉድና መዓት እንደ ሰማ ያህል ቀና ብሎ እየተመለከተ ያዳምጣቸው ጀመር።

«እናንተም ቢሆን ታሁን በፊት ተሹማችሁ የነበረ አላችሁ። ታሁን በፊት አገር ተሹማሁ የማታውቁም አላችሁ። ዛዲያ የዛሬው ሹመት እንደ ድሮው ልትቀማጠሉበት ሳይሆን ሕዝቡን እንድታስተዳደሩበት፣ ዳኝነቱን በሚገባ እንድትፈርዱ ነው። ወንበዴና ወስላታን አጥፍታችሁ አገሩ ሰላም እንዲሆን ታረጋላችሁ። የምትቀበሉት ግብርም የተወሰነ ይሆናል።»

ብዙዎቹ የባሰ በመገረም እርስ በርሳቸው ሲተያዩ፣ አማርኛ በመጠኑ የሚያውቀው ሊቀ መኳስ ዮሐንስና አቶ ሳሙኤል ከኋላው ሆኖ የሚያስተረጉሙለት ቆንስል ፕላውንዴን በአድናቆት ራሳቸውን ያወዛውዛሉ።

«ለዚህ ሁሉ በቅርብ እየተመካከርን የምናወጣው ሕግ አለ። ሕዝቡን የሚበድል፣ ሕግን የሚጥስ ሹም እንደሌላው ሁሉ ይቀጣል። እንዲያውም አይማረኝ አልምረውም፣ በሾምኩት ሰው ላይ ነው ቅጣቴን የባሰ የማከብድበት!!»

ቴዎድሮስ፣ ንግግራቸውን ተግ አድርገው እንደገና ከመቀጠላቸው በፊት መኳንንቱን ሁሉ በዐይናቸው ቃኙት። «ከዚህም በስተቀር ወደ ሀገራችን እንዲገባ የምናስበው አዲስ ነገር አለ። ይኸውም ሀገራችን እንደወትሮዋ ገናና እንድትሆን በማለት ነው። በዚህ ቤተ መንግሥት» አሉ ቴዎድሮስ የአዳራሹን ዙሪያ እየቃኙ፤ «መሳፍንቱ፣ መኳንንቱና፣ ነገሥታቱ ሕይወታቸውን ለጠጅ ለጮማና ለዝሙት አውለው ሲማግጡ ሀገራችን ኢትዮጵያ እየሟማች ሔደች።› ቴዎድሮስ አገጫቸውን እንደ ማሸት አደረጉ። «አገራችንንም እንደ ድሮው፣ ከድሮዋም የበለጠች ገናና ለማድረግ ምን እንደሚበጀን፤ ቆንስል ፕላውዴንና ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በሐሳብም በምክርም ይረዱናል። የሚረዱን ወዳጅጆችን ያፈሩልናል። ሊቀ መኳስ!» አሉ ወደ ጆን ቤል ዘወር ብለው፣ «እስቲ ለኔ ብዙ ጊዜ ያጫወትኸኝን ተዚህ ላሉት ሁሉ ንገርልኝ!»

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ተነስቶ ቁሞአዲስ ከደረበው ቀሚስ በታች ድግድጉን እያስካከለ ቴዎድሮስና ሌላውን ሁሉ እጅ ነሣ። «አባ ታጠቅ መቸም አንድ አገር ትልቅ፤ ገናና የሚሆን ሥልጣኔ ሲያገኝ ነው። ሥልጣኔ የሚገኘው ደግሞ በትምህርት ብቻ ነው። ስለዚህ ከሁሉ በፊት ትምህርት ያስፈልጋል።» ጆን ቤል፤ የሚጠፋውን ቃል ከአቶ ሳሙኤል እየጠየቀ፣ በሚገባ መግለጽ ሲያቅተው እንዲያተረጉምለት በእንግሊዝኛ እየነገረ የራሱ አገር እንግሊዝ፣ በስፋትም በሕዝብ ብዛትም ስነስተኛ ስትሆን በመሠልጠንዋ ምክንያት በእንግሊዝ ግዛት ላይ ፀሐይ አትጠልቅም? እስኪባል ድረስ የዓለምን አብዛኛ ክፍል የምትገዛ መሆንዋን በመተረክ ሥልጣኔ የሚሠራውን ተአምር በሰፊው አስረዳ። በመጨረሻም ትምህርት የሌለው፣ ብሎ ያልሠለጠነ ሕብዝ በጦርነት እስር በርሱ ስለሚፋጅ ደካማ ሆኖ በሠለጠነ አገር መገዛቱ እንዳማይቀር ተናግሮ አበቃ።

ቴዎድሮስ፣ «ዛዲያ ስለዚሁ ጉዳይ ምን ታስባላችሁ?» ሲሉ ለሁሉም በደፈናው ጠየቁ።

በተለይ በነጻድቁ ዮሐንስ ጊዜ ዳኝነትም፣ አስተዳደርም ተዘውትሮ ይሠራበት የነበረው የሸንጎ ውይይትና ትችት በዘመነ መሳፍንት ቀርቶ ወደ መረሳቱ ደርሶ ስለ ነበር፤ በመፍራትና በመፈራራት ሁሉ ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ።

«ሊቀ መኳስ ዮሐንስ እንዳጫወቱኝ የሱም ነገር ነገሥታትና ንግሥታት የሚሠሩት ነገር ሁሉ በመኳንንቱ እየተመከረበት ነው» አሉ። «በኛም አገር፣ ‹አንድ እንጨት አይነድ፣ አንድ ሰው አይፈርድ› እንደሚባለው ትልቅ ያገር ጉዳይ ስለሆነ ተዚሁ ያለነው ሁላችንም ብንመካከርበት መልካም ነው» ሲሉ ቴዎድሮስ በድጋሚ አደፋፈሩ።

ፊታውራሪ ሙጤዩ፣ የኩታውን ጫፍ ጎትቶ እያጣፉ ሁለት ሦስት ጊዜ ለጥ ብሎ እጅ ነሳ። ጥቅሻ የክንድ ጉሽሚያና ሹክሹክታ ባንዴ ተዳርሶ ከኋላ ከፊት፣ ከቀኝ ከግራ፥ ያለው ሰው ሁሉ ወደርሱ ዞረ። በአደባባይ ሳይሾም እንዳመቸው ራሱን ‹ፊታውራሪም ግራዝማችም፣ ደጃዝማችም እያለ ሲሠይም ኑሮ፣ አሁን የፊታውራሪ ቀሚስ በመስጠቱ ይደሰት በትክክል ባይገመትም፣ ከዚያው ከጎንደር ዐለፍ ብሎ የፈንጠር ተወላጅነቱ ከአዳባባይ ስለሚለይና በአነጋገር የሠለጠነ በመሆኑ፣ የሚያውቁት ሁሉ የሚለውን ለመስማት ጓጉ። «ጃንሆይ!» ሲል ጀመረ፣ አሁንም ደግሞ እጅ እየነሣ። «መቸም እኝህ የባህር ማዶ ሊቀ መኳስ ስለ ውቀት ጠቃሚነት የሰጡን ምክር እንዲህ ነው አይባልም። ዕውቀት ጠቃሚ መሆኑን መቸስ ማይ ያብላል?»

ከባህር ማዶ ‹የባህር ማዶ ሊቀ መኳስ› ሲል አሽሙሩ ገብቷቸው በጎሪጥ ተያዩ።

«ዕውቀቱማ መቸም ለሰማዩ ለምድሩም ይበጃል።» አሁንም እጅ ነሣ። «ዛዲያን አሁንም የቅኔ የትርጓሜ፣ ያቋቋም የዝማሬ መዋእሲት፤ ሊቃውንት የሞሉባት አገር ናት። ሌላው ቀርቶ የጎንደር ሊቃውንት ለድፍን ኢትዮጵያ ኸረ እንዲያው ሊቀ መኳስ ዓለም ለሚሏት አይተርፉም? እና ጃንሆይ ዕወቀት ያላቸው ሊቃውንት ካሉን እንዴት ነው ነገሩ ደንቆሮች እንባላላን። ወይ ብዬ ነው!» ሲል በንግግሩ ማሳረጊያ እጅ ነሣ።

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ መልስ መስጠት ቃጣና አቅማማ። የቀለምና የሃይማኖት ትምህርት ብቻውን በቂ ዕውቀት ሊሆን እንደማይችል ለመግለጽ ትክክለኛ ቃል ጠፍቶት ደንቆሮ ማለቱ ትልቅ ስሕተት መሆኑን ተገንዝቧል። «እኔ ደንቆሮ ለማለት -» ብሎ መልስ ሲፈልግ ቴዎድሮስ ቀበል አደረጉለት።

«መቸም ሊቃውንትና ካህናትማ ሞተልተውናል» አሉ ቴዎድሮስ በሽሙጥ ዐይነት ወደ አቡነ ሰላማ እየተመለከቱ። «ፊታውራሪ እንዳለው ሊቃውንት እንዳሉን እውነት ነው። ንግስ፤ የማያውቁትን የግዕዝ ቁንቋ የሚያነቡ፤ የሚያስነቡትን የማይጽፉ፤ ትርጉሙም ምኑም ሳይገባቸው የሚያዜሙ የሚጸልዩ፤ እንዲያው ሲጠይቋቸው የሚያነበንቡት ነገር ርግማን ይሁን ምርቃት፤ ውግዘት ይሁን ምስጋና መናገር የማይችሉት ስንት ናቸው? ውሸት አናንገር ከተባለ አብዛኞቹ አይደሉም ፊታውራሪ?»

ፊታውራሪ በመልሱ ትንሽ አቅማማ። «በመላእክት ቋንቋ መናገር መቸም እኔ ዕውቀት እንጂ ድንቁርና አይመስለኝም» አለ። በሹመቱ የተከፋ መኳንንት መልሱ ቁጭቱን ያወጣለት ይመስላል በአድናቆት ራሱን አወዛወዘለት።

ቴዎድሮስ፣ ነገሩን ፍሬ ፈርስኪ በማድረግ ዐይነት እንደመሣቅ አሉ። «ነገሩስ ያባቶቻችን ቋንቋ ነው። የመላእክት ቋንቋስ ቢሆን ትርጉሙን፣ ምስጢሩን ካላወቁት እንደ ደመ ነፍስ እንስሳት ተንጫጩበት እንጂ መቸ ተነጋገሩበት?» ወደ አቡነ ሰላማ ዘወር ብለው ጠየቋቸው። «ምን ይመስልዎታል አባታችን»

ሳይፈልጉ ጥያቄው የተሰነዘረባቸው አቡነ ሰላማ ከሪዛቸው ጋር ጥቂት አጉተመተሙ። ግዴታ ካልሆነባቸው በተቀር ከቴዎድሮስ ጋር ብዙም መነጋገር አይፈልጉም። ደጃች ውቤም የሚያነጋግሩዋቸው እንደ አባት እያከበሩ፣ እያባበሉ ስለ ነበር ጭውውታቸው ይጥማቸዋል። ቴዎድሮስ የሚያነገግሩባቸውና አንድ ነገር የሚጠይቋቸው ግን በሚያፋጥጥ የክርክር መልክ ነው። «መቸም....መቸም» አሉ ሪዛቸውን ሳብ ሳብ እያደረጉ፣ «የእግዚአብሔርን ቃል ከአጥናፍ አጥናፍ የሚሰብክ ካህናት ሊመሰገኑ እንጂ ሊነቀፉ አይገባም።

ቴዎድሮስ ድንገት ከግራሜ ፈንቅሎ የመጣ ሣቃቸውን ለማመቅ ይምሰል አፉቸውን በግራ እጃቸው ከደን አደረጉ። «እሱንማ መቸ አጣነው፤ አባታችን። ነገር ግናስ እየጠመጠመ ቄስ፤ ካህን ነኝ ባይ፣ ቆብ እየደፋ መነኩሴ ነኝ ባዩ ሁሉ፣ በዚህም ልቆ ርቆ ካገር ማዶ፤ ባሕር ተሻግሮ በሃይማኖት መሪነት የሚመጣው ሁላ፣» ቴዎድሮስ ሆን ብለው ከዚህ ላይ ንግግራቸውን ረገጥ ረገጥ አደረጉት። «የዓለሙን ነገር ሁሉ ትቶ የእግዚአብሔርን የክርስቶስን ቃል ለማዳረስ የዘመተ ነው ብለው ያምናሉ? ሲሉ ከእስክንድርያ ከመነሳታቸው በፊት ብዙ ሺህ ብር እየተከፈላቸው ከመጡም በኋላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በፊት ብዙ ሺህ ብር የተከፈላቸው፣ ከመጡም በኋላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይነታቸው የሚሰበስቡትን ስፍር ቁጥር የሌለው ሀብት ወደ አገራቸው የሚያግዙ መሆናቸውን በሚጠይቅ አስተያየት ተመለከቱዋቸው።

አቡነ ሰላማ፤ የቴዎድሮስን መቅን ዘይቤ በትክክል ባይረዱትም በነገር የተነኩ ወይም የተደፈሩ መሆናቸው ከሰዉ አስተያየት ስለተሰማቸው ያወለወለ ያ ቀይ ፊታቸው የባሰውን የተሰረበ ጉበት መሰለ። ግን መልስ አልሰጡም። ነገሩ የገባው በማዘን ከንፈሩን ሲመጥላቸው፣ ሌላውም ለቅጽበት የራሱን ቅሬታ ረስቶ በወርደታቸው እንደ መሣቅ ሲቃጣው፣ ጸጥ ብሎ የቆየው አዳራሽ ሁካታ አስተጋባበት።

ቴዎድሮስ፣ ሁኔታውን በፈገግታ ለጥቂት ጊዜ ከተመለከቱ በኋላ ዐይናቸውን ወደ ሊጋባው መለስ ሲያደርጉ «እሺሺ----- እሺታ! እሽታ! ሲል አጨበጨበ። ወዲያው አዳራሹ ጸጥ አለ።

«የጳድቁን የኃጥኡን ጉዳይ አሁን ለርሱ ፍርድ ትተን እንለፈውና፣ እስቲ ሊቀ መኳስ ስለ ትምህርትና ስለ ዕውቀት እስታሁን በኛ ነገር ስለሌለው እንመካከርበት» ሲሉ ቴዎድሮስ ቀኝ እጃቸውን እንደ መዘርጋት አደረጉ።

አሁንም ብዙ መኳንንት በማመንታት እርስ በርሱ ሲተያይ፣ ግዙፍ ቁመናው ቂላ ቂል የሚያስመስለው ቀኛአዝማች አሥማረ ብድግ ብሎ እጅ ነሣ። «ጃንሆይ መቸም የዚህ የኛ አገር ትምህርት ርባና የሌለው ተሆነ፣ የባሕር ማዶውን ዕውቀት ያሉትን እንዴት ነው የምናመጣው?» እንደ ገራም አነጋገሩ ጥያቄው አለማወቅ ይመስላል። ቆዳው አሳሳች መሆኑን በቅርብ የሚያውቁት ግን፣ ምክንያት ያለው ጥያቄ እንደሚሆን አላጡትም። ምንም ቢሆን ከደጃች ውቤ ቤት ያደገ ሰው ነው።

ቲዎድሮስ እንደ መሣቅ አለ። «ቀኛዝማች አሥማረ፣ መቸስ በወርቅ ተገዝታ በስልቻ ተቋጽራ፣ በከብት ተጭና የምትመጣ እንዳትመስልህ!»

«እዛዲያ እንዴት ነው ጃንሆይ?» ሲል አሁንም በገራገር አነጋገር ጠየቀ።

«ነፍጥ መድፍ የሚሠራ አናጢነት፣ ግንበኝነት አንጥረኝነት፣ ሌላውም ጠፍ ከመሆን የደረሰች አገራችንን ለማልማት፣ ሕዝብን ለማሰልጠን የሚያበጅ ሙያ የሚያስተምሩ ፈረጆች ለማምጣት አስበናል። በዚህ ረገድ ክርስቲያንዋ የንግሊዝ ንግሥት ግርማዊት ቢክቶሪያ ልትረዳን እንደምትችል....» እያሉ ቴዎድሮስ ወደ ሁለቱ እንግሊዛውያን ዘወር ብለው ተመለከቱ። «ቆንስል ፕላውዴንና ሊቀ መኳስ ዮሐንስ አጫውተውኛል።»

መኳንንቶቹ እርስ በርሳቸው ተያዩ። ‹ፈረንጅ - ፈረንጅ› የሚለውን ቃል በሹክሹከታ ተቀባበሉት።

«አንጥረኛና ግንበኛ ባገራችን መች አጣን፣ ጃንሆይ» የሚል ጥያቄ ከሌላ መኮንን ቀረበ።

«አሄሄ!» አሉ ቴዎድሮስ በቅሬታ መልክ። «ያገሬን ሰው መንቀፍ አይሁንብኝ እንጅ ለጎንደር ወይዛዝርት አምባርና አልቦ ከመሥራት የሚያስፈልገውን እንደ ባለሙያ ቆጠርከው? አሁን ማ - ይሙት ከስንት ስንት ዓመት በፊት ባባቶቻችን ጊዜ የተሠራውን ይህንን የመሰለ ግንብ የሚሠራ ግንበኛና አናጢ ዛሬ አለ? እስቲ አምጡልኝና ላሠራው፣ ልሹመው!» በመጋበዝ ወደ መኮንኑ እጃቸውን ዘረጉ። መረታቱን የተቀበለው መኮንን እጅ ነሥተው ተቀመጠ።

«ጃንሆይ! እንዲያው» ሲል ከቀድሞ ፊታውራሪነት አሁን የግራዝማች ቀሚስ የተሸለመው ወገሬው ጎበና የሚጠይቀው ነገር የጠፋው ይመስል ከአጠገቡ

የተቀመጡትን ሰዎች በዐይኑ ፍለገ። «እንግዲያው እነዚህ ፈረንጆች ያሏቸው ለማስተማር የሚመጡት፣ እስላሞች ናቸው ወይስ አረመኖች?»

ቴዎድሮስ፣ ሐሳብ የሚጠይቁ ይመስል ወደ አቡነ ሰላማ ተመለከቱ። ጳጳሱ ግን እንዳልሰሙ በመምሰል አንገታቸውን ቀርቀር አድርገው ጭጭ አሉ። አብዛኞቹ መኳንንት ነገሩ ገባቸው።

ቴዎድሮስም ጥቂት አሰቡበት። በአቡነ ሰላምና በካቶሊክ በአባ ያዕቆብ እንደዚሁም በእነሱና ‹በፕሮቴስታንት› በሚባሉት ሚስዮናውያን መካከል ያለውን ጥላቻ አሳምረው ያውቁታል። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን እንደ ራሳቸው ስሜት የሚያሳስበው አደጋ ሌላ ነው። ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ጉዳይም ከነዚህ ጠብ ሁሉ በላይ ነው። ግን እዚያ ከፊታቸው የተሰበሰበው መኳንንት ይህንን ነገር አሣምሮ አይረዳውም። ጎጂውንም፣ ጠቃሚውን የሚያውቅ የተማረ የሠለጠነ ቀልበስ አድርገው ላንዳፍታ እንደመቆዘም አሉ። «መቸም አገራችን እንውረር፣ እንግዛ የሚሉት ግብጦች፣ ቱርኮችም ያው እስላሞች ስለሆኑ፣ ከእነሱ ጋርማ እንዴት እንስማማለን ብላችሁ ነው? ከሃይማኖታቸው እንኳን ነገር የለንም በከፋት ስለመጡብን ነው እንጂ አሁን እኛን እንዲያስተምሩን ያሰብናቸው ግን ክርስቲያኖች ናቸው። ግና ክርስቲያንነታቸው እስተዚህ ተኛም ቅባት ጸጋ እንደሚባለው ስለሆነ ተዚህ ምናለን?» አሉና መኳንንቱን በአጠቃላይ ትኩር አድርገው ተመለከቱ። የተቀበላቸው አስተያየት እንደ አለት የጠጠረ ነበር።

«አባታችን፣ አንድ ይበሉኝ እንጂ!» አሉ ቲዎድሮስ ኮስተር ባለ አነጋገር።

አቡነ ሰላማ ሪዛቸውን እየጎተቱ በሐሳብ ስልምልም አሉ። ከየትም ተነሥቶ፤ ራሱን እምሪ አድርጎ እንዳሰብኩት፣ እንደፈለግሁት ልሥራ ከሚል ቴዎድሮስ ጋር ፊት ለፊት መጣላቱንና መጋፋቱን ቀርቶ፣ መከራከሩን ስለ ሚፈሩ ት እያስታመሙ ቆይተዋል። አሁን ግን ከመኳንንቱ በቀረበው ጥያቂ መሠረት፣ አስተያየታቸውን ከተጠየቁ መልሳቸውን መስጠት የተሻለ አጋጣሚ መሆኑ ታያቸው። የአብዛኛው መኳንንት ስሜት ገብቷቸዋል። በዚህም ላይ የቴዎድሮስን ፈቃድ መፈጸማቸው ነው። «መቸስ እሱማ አረመኔና እስላም እስላምና ክርስቲያን አንድ አይደለም፣ ተየት ተቀራርቦ። ግና ደሞ ክርስቲያን በሚባሉት መካከል የማይስማሙበት ብዙ፤ ብዙ፣ አሉና ከዚህ ላይ ራሳቸው ቃላቶችን በመርገጥ፣ እንደ አስተርጓሚ የሚረዳውም ረጂያቸው ጣታቸውን በመቀሰር «ጥልቅ ምስጢር አለ» ሲሉ አስገነዘቡ። «ተዚህም የተነሳ ልክ እኛ የማርቆስ መንበር ሆነን፣ የጴጥሮስ መንበር ነን የሚሉት ብዙ ጉዳት አድርሰውብናል። ይኸ መቸም በመጣፍ ያለ ነው። በጥንቱ የማርቆስ መንበር ትምህርት መናፍቅ ተብለው የተወገዙት ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ሲሆን፣ እርስ

በርሳቸው እንደዚሁ እንደተፋጁ ነው። ዛዲያ በስመ ክርስቲያን ሃይማኖት መቸስ....» ሲሉ ትረካቸውን አቋረጡና ጸሎት የሚያደርሱ ይመስል ወደ አዳራሹ ጣሪያ አንጋጠጡ። አሁንም መለስ ብለው ሪዛቸውን ጎተቱ። እንዳሰቡት የቴዎድሮስ የቅርብ ባለሟሎች ሳይቀሩ መኳንንቱ ሁሉ ዐይኑን በርሳቸው ላይ ተክሎ የሚናገሩት ቃል እንዳያመልጠው ጆሮዉን ለግቷል። ቴዎድሮስ ብቻ የመድረኩን ወለል በቀስታ በእግራቸው ይቆረቁራሉ።

«ክርስቲያን ነኝ የሚለው ሁሉ ክርስቲያን ባለ መሆኑ ብርቱ ጥል እንደሚፈጠር በናንተም አገር መድረሱን መቸም አሳምረው የሚያውቁት ታሪክ ነው።» አቡነ ሰላማ፣ ነገራቸውን ሁሉ እንዲከታተሉ ሪዛቸውን እየሳቡ አሁንም ተግ አሉ። «በአጤ ሱስንዮስ ዘመን እዚያ በመንበረ ማርቆስ ላይ የተነሡት እምነት ተከታዮች መጥተው እንደዚያ በማድረጋቸው ያ ሁሉ እልቂት ደረሰ፣ ያ ሁሉ ሰው አለቀ፣ ያው እንደሚያውቁት ልጃቸው ፋሲል ነግሦ፣ ‹ሃይማኖት እንደ ባቶቻችን የመንበረ ማርቆስ› ሲል ያ ሁሉ በረደ፣ ሰላም ወረደ፣ ይኸው ነው የሃይማኖት ታሪኩ» ሲሉ ደመደሙ።

ብዙ ጦር ሜዳ ላይ ስልት እያወጡና እየሠሩ ያሸነፉት ቴዎድሮስ ጋሻቸውን በአዳጉል አንከርፍፈው እንደ ተመቱ ወዲያው ገባቸው። በአቡኑ መልስ ቆንስለዋል። እንደ ቆስለ እልሃም አውሬም አሁንም ወደፊት ተጋፈጡ።

«ምኑን ከምን አመሳሰሉት አባታችን። ያ ሌላ፣ የአሁኑ ሌላ።» ቴዎድሮስ ወዲያው መልሰው አንደበታቸውን ረገብ ለማድረግ ሞከሩ።

«የእኔ ሐሳብ ለሥራ የሚመጡት ወዲያ ወዲህ ውልፍት ሳይሉ ሥራቸውን ብቻ እንዲሰሩ ነው። አይ ሌላ ነገር ውስጥ እንገባለን ካሉ እኔ የማደርገውን አውቃለሁ። እንኳንስ ከባዕድ አገር የመጡ፤ ተዚህ ካገራችንም ካህን ነኝ እያለ ሲወላገድ የሚውለው ሁሉ አርሶ፣ ቆፍሮ ወይም የሚያውቀኝ በሌላ ነገር ሁሉ ሠርቶ እንዲኖር ነው የሚሆነው። መጽሐፉም ‹ብላዕ በአፈ ገጽከ› ብሏል» አሉ ወደ አቡነ ሰላማ ዘወር ብለው እየተመለከቱ። «አይደለም አባቴ?» ሲሉም ጠየቋቸው።

አቡነ ሰላማ አዎናታ አይሉት አሉታ፣ አሁንም ከንፈራቸውን ውስጥ ከአጉመእመቱ በኋላ፣ «ግና» አሉ ግልጽ በሆነ አነጋገር «አምላካችን ሁሉንም በየሥራው ደልድሎታል። ሙሴ የእሥራኤልን ሕዝብ እንዲመራ ሲመርጠው አሮንን ደግሞ ለቤተ ካህናቱ መድቦታል።»

«እውነትዎን ነው አባታችን» አሉ ቴዎድሮስ፣ በሐሳባቸው ላለው ጉዳይ አሁን ደኅና መንገድ የተከፈተላቸው መሰላቸው። መረጠው። ግና ስንት ዕልፍ ዕማዕላፍ

ለሆነው ለቤተ እስራኤል ሕዝብ ምድሩ ካህን ነው። ዝም ብሎ የሚቀበለው ሁሉ እየሠራ ቢያድር ምን ይመስልዎታል?» ሲሉ ጠየቁ።

አቡነ ሰላማ መልስ መስጠት ባያቅታቸውም ከራሳቸው ይልቅ በዚያ አዳራሽ የተሰበሰበው አብዛኛውን መኳንንት የበለጠ እንደሚቆነጥጠው በመገመት ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ጠበቁ። «መቸስ ቢሆን ቤተ ክርስቲያን ሁላ ይዳፈን አይባል። ዛዲያ፣ ለጧት ኪዳን ለምሽት ቁርባን፣ ለቅዳሴ ለማኅሌት ቤተ ክርስቲያን ያለ አገልጋይ ካህናት እንዴት ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች?» አሉ በመጨረሻ።

«ቤተ ክርስቲያን ይዳፈን አልወጣኝም። ያልታሰበ ነገር አያምጡ» አሉ ቴዎድሮስ ትንሽ የመበሳጨት ቃና ባዘለ አነጋገር፤ «በአንድ ቄስ፣ በሁለት ዲያቆን በሦስት እንደሚቀደስ እናውቃለን። ቢበዛ በሁለት በሦስት ዲያቆን፣ በአምስ ይሁን። ከዚህ በተረፈ ሥራ ፈትቶ እየተለበ የሚንጋጋው ሁሉ ምን ይጠቅመኛል? ደሞስ አንድ ሰንበት ጧት ለመቀደስ ሳምንት ሙሉ ሥራ ፈትቶ መቀመጥ ምን ይባላል? እኔም እኮ ብችል እንደ ጻድቁ ዮሐንስ፣ የሕዝቤን ገንዘብ ባልነካ፣ ሰሌን እየሠራሁ እየሸጥኩ ብተዳደርና ባስተዳድር ደስ ባለኝ ነበር። ይህ ባይሆንልኝ ቢቀርም፣ ሠራዊቴ ግን እንዳለፈው ጊዜ በየጢሱ እየተመራ ወይንም ያገሬን ገብሬ ሞሰብ እየደፋ ሳይኖ በቀለብ ሥራት የሚተዳደርበትን ደንብ ገና አወጣለታለሁ። በሠለጠኑት አገሮች እንደዚህ ነው የሚደረገው አሉ። ስለ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ሌላው ካህን ነኝ ባይ ሁሉ አርሶ ነግዶ፣ ወይም በሌላ ሙያው ሠርቶ እንደሚኖር ነው ያለኝ ሐሳብ።»

ስለ ጻድቁ ዮሐንስ ሰሌን ሥራ ሲነገር በአድናቆት ከንፈሩን እንደመምጠጥ እያደረገ ፈገግታ አሳይቶ የነበረው መኳንንት የምጽአት መዓት እንዲሰማ ያህል በድንጋጤና በግራሜ አተመመ።

«ስንት ባሕታውያን የዘጉበትን ገዳም፣ ስንት የቅኔ፣ ያቋቋም፣ የድጓ መንበር የተዘረጋበት ደብር እንዴት እንዲህ ይሁን ይባላል?» ሲል ጠየቀ አንድ መኮንን።

«መቸም የተቸገረ ጠፍ ደብር ነው በሦስት የሚያስቀድሰው። ስለሆለትማ፣ ሰባትም ዐሥራ ሁለትም፣ አሁን እርስዎ የነገሡበት ደረስጌ ከሰባት ባነሰ ዓመት ባል ተቀድሶበት አያውቅም ሲል ጠቆመ ሌላው በተራው።

«መቸምኮ፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚያገለግለው ካህን ብቻ አይመስለኝም። ከዚህ ከአባታችንና ከጨጌው ጀምሮ ትልልቆቹ ሊቃውንት ያለረድዕ አይሆንላቸውም። እንዲያው እንደ ጨዋ ገበሬ ይንከላወቱ ካልተባለ በስተቀር! አሁንም የሆነ እንደሆነ፣

ቤተክርስቲያንም ከቀዳሹ፣ ካወዳሹ፣ ጋራ ሌላው ቢቀር ገበሬ መበለት አለው፣ ባገራችን» አለ አንዱ ደግሞ በማብራራቱ።

ድንገት ቀፎው እንደተነካበት ንብ፣ ተራ ሳይጠብቁ መኳንንቱ ከዚያም ከዚያም እየተነሳ ጥያቄውንና አስተያየቱን በላይ በላዩ አደራረበው። ቴዎድሮስ ባንድ በኩል ላገር ይበጃል ብለው ያቀረቡትን ሐሳብ መኳንንቱ ለምን በመጥፎ እንደተመለከተው እየገረማቸውና እንደመበሳጨትም እያሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመጨረሻ የሁሉንም አጠቃለው በጥሞና ለማስረዳት ትዕግሥታቸውን እየጨመቁ አዳመጡ። ከሐሳባቸውና ከቃላቸው የማይወጡት የቅርብ ባለሟሎቻቸው በመካከሉ ግራ ተጋብተው አንድ ጊዜ ወደ ቴዎድሮስ በጭንቀት ዐይነት ሲመለከቱ ግራ ተጋብተው አንድ ጊዜ ወደ ጊዮርጊስ በጭንቀት ዐይነት ሲመለከቱ ሌላ ጊዜ ተናጋሪውን በቁጣ ይገለምጣሉ፤ አልተገፋላቸውም።

ቴዎድሮስን ጠቅ የሚያደርግ ጥያቄና አስተያየት በተሰነዘረ ቁጥር አንዱን፣ ‹እሰይ! አበጀህ፣ እንዲያ ነው እንጂ! እያለ በሆዱ ሲቅበጠበጥ በግልጥ ያስታውቃል። በአንድ ጊዜ ብዙዎች ለመናገር ሲነሡ፤ እንደ ቆረፈደ ቆዳ የሚንቋቋ ድምፅ ያለው አንዱ ቀደመ።

«የጦቢያ ሕዝብ ክርስቲያን ነው። ያዕቆብ ካቶሊክ ባገራችን ምን ይሠራል? ተዚህ ላይ ደሞ አሁን አጤ፣ ቤተክርስቲያን ይጻፈን ሲሉ እኔ በውነቱ ለማተቤ፣ ለዚች ለማተቤ ብሞትም ግዴለኝ» አለ እንደ መቁነጥነጥ እንደ መንቀጥቀጥ እየቃጣው። የቴዎድሮስ ዐይን ድንገት እየቀላ ሔደ። «አሁንም የሆነ እንደሆነ አሁን የታሰበው ግን መናፍቅነት» ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ መጨረሻ የተናገረውን ቃላት ሁሉም ሰው በሚገባ ሳያዳምጠው ቴዎድሮስ እመር ብለው ቆሙ።

ስስ ከንፈራቸው እየተንቀጠቀጠ፣ በስስ ከንፈራቸው ጠርዝ ድንገት አረፋ እዬወጣ ተፈናጥረው ተነሥተው ጎራዴያቸውን እስከ ጫፉ አጠገብ ድረስ ላጥ አደረጉት። እፍ እንደተባለ መብራት እርጭ ባለው አዳራሽ ውስጥ «መይሳው ካሣ!» የሚለው ድምፅ እንደ ነጎድጓድ አስተጋባ።

ታንጉት፣ በዚያ ጎራዴ መላ ሰውነቷ የተሰነጠቀ መስሎ ተሰማት። ድንጋጤ ይሁን ፍርሃት አልታወቃትም። ብቻ ካለችበት ደረቀች። በቅጽበት ተዋበች ተፈናጥረው ከቴዎድሮስ ወገብ ሲጠመጠሙ በአጠገብ የነበሩት እነ ገብርዬ እነ ዓለሜ፣ እነ እንግዳ ተረባርበው የተመዘዘው ጎራዴ ጨርሶ ሳይወጣ፣ ቴዎድሮስም ሌላ ቃል ከፍ አርገው ሳይናገሩ፣ በጓደኝነት ገሥጸው ከባብበው ወደ እልፍኝ ሲወዷቸው አላየችም። ዐይኖቿን በመዳፍዋ በመዳፍዋ ሸፍና ሐሳብዋ በተመዘዘው ጎራዴ እንደተተከለ ነበር። ዐይንዋ ግልት፣ አእምሮዋም መለስ ሲል ወደ እልፍኝ

ሔደች። የመጀመሪያዋ ጊዜ ባይሆንም አሁን ግን ለምን እንደሆነ ምክንያቱን አላሰበችውም ነበር። እግርዋ እንደመራት እንዲሁ ሔደች። ሳታስበው ደርሳ ገርበብ ካለው በራፍ ግማሽ አካልዋ እንደገባች ድንገት ቆመች።

ተዋበች፣ ከቴዎድሮስ እግር ሥር ተንበርክከው ሁለት ቋንጃቸውን በማቀፍ ከታፋቸው ላይ ደፋ ብለው በጭንቀትና በፍቅር ይማጠናሉ። «የኔ ጌታ፣ ኧረ ባክህ የኔ ጌታ! ለምን እንደዚህ ትናደዳለህ?» የቴዎድሮስ ቋንጃ ጭምቅ አደረጉት።

የንዴት ትንፋሻቸውን እንደ ነበልባል በአፍንጫቸው ቡል ቡል የሚለው ቴዎድሮስ ጉልበታቸውን ለመገፍተር ቃጣውና መለስ አድርገው፤ «ተሰደብኩ፣ ሰብደበኝ እኮ! ምን ላርግ በለሽ ነው ተዋቡ?» አሉ ምርር ባለ አነጋገር ፊታቸውን በሁለት መዳፋቸውን እየፈተጉ።

«የኔ ጌታ! ዛዲያ እንደዚህ ይኮናል?»

«ስድብ አልወድም!» እንደመራጨት ቃጣቸው።

«እህ! መቸስ ምን ይደረግ?»

«እናቴም! እናቴም ያቺ የምወዳት እናቴም ትመክረኛለች፣ ትገሥጸኛለች፤ ትቆጣኛለች እንጂ የሚዋርድ ነገር ሰድባኝ አታውቅም።»

«አሁን የተናገረውን ምን ስድብ አለበት?»

«መናፍቅ ቅሎኛል።»

«እኔ እንደሰማሁት ‹መናፍቅ ነው› ነው ያለው። እባክህ የኔ ጌታ!»

«ያው ነው!!» ቴዎድሮስ ጥቂት ተወራጩ።

«ኧረ ባክህ የኔ ጌታ! ያው አይደለም። አንተን መች አለህ?»

«አዎ ያው ነው! ሐሳቡን መናፍቅነት ነው ካለው እኔን ሰድቦኛል። አገሬ ትልቅ እንድትሆን ባሰብኩ እኔን የሰደበኝ ደሞ አገሬንም ሰድቧል!»

«ታዲያስ መቸስ እየቻሉ ነው እንጂ!»

«የጭነት ከብት ብቻ ነው ቻይ!»

«ኧረ ባክህ ተው የኔ ጌታ!» አሉ ተዋበች ፊታቸውን፤ ቀና አድርገው ዕንባ ባቆረዘዘ ዐይን ተማጠኗቸው። «ራስህ ምክር፣ ሐሳብ ጠይቀህ እንዲህ ስትሆን ምን ይባላል? ያለ ትዕግሥት አገር ይገዛል?»

«በምክር ላይ ዛዲያ ዘለፋን ምን አመጣው?»

«ምናልባት ደግ አስብኩ መስሎት ይሆናል።»

«ለምን ሐሳቤ አይገባቸውም ተዋቡ?» ከንዴት ይልቅ አጠያየቃቸው የብስጭት ነበር።

«እነሱ የሚያውቁት የለመዱትን። አንተ እንዳልከው፣ አባቴ ዘመንና ተዚያም በፊት አንሥቶ መኳንንቱም፣ ሰዉም ግምኛ ሆኖ ከቆዩ አሁን አንተ ላገርህ ትልቅ ሐሳብ ስታመጣበት ባያውቅልህ ምን ትፈርደብታለህ።»

በተዋበች አነጋገር ተረትተው ቴዎድሮስ በሐሳብ ራሳቸውን አወዛወዙ። «ዛዲያ ምናርግ ትይኛለሽ የኔ መቤት?» ሲሉ በትካዜ አንደበት ጠየቁ። «ያገሬ ነገር ሆኖብኝ ነው እንጂ ለኔና ላንቺ ሆድማ፣ ቋራ አውሬ አድነን ብንበላ ያንሰን ነበርን?»

«እረቴ! ዛዲያ ታጋሽ መሆን ነዋ! በትንሽ በልቁ ቢቆጡ፣ ቢናደዱ፣ አሁን እንዳረከው ብታረግ ሰውን ከማስበርገግ በቀር ፋይዳው የለው!» ተዋበች ከተንበረከኩት ልጥጥ ብለው እንደማስተካከል ዐይነት የአጼ ቴዎድሮስን ቁንደላ ዳበስ ዳበስ ያደርጉት ጀመር። ቴዎድሮስ ዐይናቸውን በሐሳብ ከደን አድርገው፣ የሚሽታቸው ለስላሳ ትንፋሽ ሲያባብላቸው ንዴታቸው በረድ እያለ ሔደ።

«እባክህ ፈጣሪዬ፣ ትዕግሥቱንም አክለህ ስጠኝ!» አሉ በታከተ ኧንጋገር። «አንቺም እስቲ ተዋቡ የመታገሻውን መላ አስተምሪኝ!» በበኩላቸው የሚሽታቸውን ትከሻ ዳሰስ ዳበስ አደረጉት።

«አሁን እስቲ ዐረፍ በል የኔ ጌታ» አሉ ተዋበች፣ ከንብርክካቸው ተነሥተው ዋልባቸውን እየነቀሉና፣ ቀይ የሐር ቀልቢያቸውን እየፈቱ።

«አንቺም እስቲ ዐረፍ በይ የኔ እኅት፣ አንቺንም ጨምሬ መከራ ሥቃይ አሳየሁሽ» ሲሉ የሚሽታቸውን ፊት በትካዜ ፍቅር አተኩረው ተመለከቱ።

«እኔ ግዴለም እስቲ አንተ ዕረፍ» አሉ ተዋበች መቀነታቸውን እየነካኩ። ታንጉት ከበሩ ላይ ቁማ ያዩዋት መዘጋቱን ለማረጋገጥ ዐይናቸውን ወደበሩ በመለሱ ጊዜ ነበር። ታንጉትንም «ምን ሆነሽ ነው ተሱ የቆምሽው?» ሲሉ ጠየቋት። አነጋገራቸው ከግሣጼ ይልቅ የማፈርና የመገረም ቃና ነበረበት። ቴዎድሮስ ዝም ብለው አስተዋሏት። በሌላ ሐሳብ ውስጥ ይመስላሉ።

«እኔማ - እኔማ አባ ታ - ታጠቅ.....» አለች ታንጉት የምትናገረው ጠፍቷት።

«ምንም ነገር የለም! ሲናደድ ታውቂው የለ?» ሲሉ ተዋበች አሰናበቷት።

ታንጉት ‹አላውቅም› ማለት ቃጣት። ስሜቷ የተቀላቀለ ነበር። በሁለቱ ሕይወት ላይ በማጮለጉዋ ኃፍረት ተሰማት። ለጊዜው በሁለቱ መካከል የማትፈልግ መሆንዋ ደግሞ አናደዳት። ‹በፊት የማውቀውስ እኔ ነበርኩ!› አለች በሆድዋ። ደረጃውን እየተንደረደረች ስትወርድ፣ ገብርዬ ከግቢ መውጣቱን አላረጋገጠችም፣ አልተበቀችም፤ ሩጫ በከጀለው አረማመድ ወደ ቤትዋ ሔደች።

ገብርዬ ቤት ሲመጣ፣ ታንጉት የአዘቦት ልብሷን ለውጥ ፊቷን በጣትዋ እየጠቋቆመች ከመስታወቷ ጋር ስትጫወት አገኛት። «እህ?» አለና ከጎንዋ ተምቀምጦ በቀልድ ዓይነት ፊቱን ከመስታወቱ ትይዩ አስተካከለ። ታንጉት፣ ጎንደር እንደሰነበተች ስናር ድረስ ከሚመላለስ አንድ ነጋዴ ዘንድ ካገኘቻቸው ዕቃዎች አንዱ ቁመቱ ወደ ክንድ የሚጠጋ፣ ወርዱ ስንዝር የሚያክል መስታወት ነበር። ዱሮ ፊትዋን በውሃ ውስጥ እያየች በደስታም በቅሬታም ትጫወት እንደ ነበር ሁሉ አሁን መስታወቱ ብርቅዬ ሆኖባታል።ገብርዬም ድንገት ቤት ሲገባ ብዙ ጊዜ ከፊቷ ደቅናው አግኝቷታል። አንዳንድ ጊዜ ከራስዋ ጋር ትሣሣቃለች። ሌላ ጊዜ ከምስሏ ጋር ፊቷን አኮፋትራ የምትሽሟጠጥ ትመስላለች።

ገብርዬ በመጠኑ አጠርና ሰፋ ካለ ፊቱ ዘወትር ከሚያፈጡት ጠባብ ዐይኖቹ፣ አጠር ብሎ ቀዳዳዎቹ ሰፋፊ ከሆኑት አፍንጫው፣ ‹ሰፌድ› አገጭ የሚል ስም ካሰጠው ሰፊና ጠፍጣፋ ቢጤ ከሆነው አገጩ፤ በመጠኑ ከርደድ ብሎ ጥቅጥቅ ደን ከመሰለው ጎፈሬው ጋር ተፋጠጠ። ወዲያውም በጠይምነቱ መኻል እንደ ማሽላ ቆሎ ድንገት የሚፈካውን ጥርሱን በፈገግታ ገለጥ አደረገና ወደ ታንጉት አምሳያ አተኮረ። ቆንጆ እንደሚባሉት በጣም ስልክክ ሳይል ከበብ ያለው የፊት ቅርጽዋና ከእርሡ ገለጥ ብሎ እንደ ውሃ የጠራው ጠይምነቷ፤ ከንፈሮቿን በፈገግታ ሳብ ስታደርግ ከጉንጮቿ ላይ ከሚወጡት ስርጉዶች ጋር የልጅ ውብት፤ የልጅ ለዛ ይሰጣታል። ደስ ያለችው በልቡ፤ የደስ ደስ ያላት ልጅ ናት ያለው፤ ገና ቋራ ከካሣ ጋር ሲገናኝ ያያት ዕለት ነበር። አልተለወጠችም። ዐልፎ ዐልፎ ጣል ጣል ያደረገባት የኩፍኝ ጠቃጠቆ ስንኳን እንደ ማርያም ስሞች አንዳች ዐይነት ውበት ጨመረላት እንጂ አልቀነሰባትም። ሌላ ጊዜ በመስታወቷ ውስጥ ሲፋጠጣት እንደምታደርገው አሁን ግን ስርጉዶቿ በፈገግታ አልወጡም።

«ምን ሁነሻል?» ሲል ጠየቃት።

«እህ? ምን አልኩህ!» አለች ቅዝዝ ባለ አነጋገር።

«በሹመቴ ደስ አላለሽም እንዴ?»

«ለምን ደስ አላለኝም?»

«ዛዲያ ሐሳብ የገባሽ ትመሲያለሽ።»

«ይኸን ነገር የሚያጠፋልኝ ነገር ቢኖር!» አለች ድንገት ችግርዋ የተገለጠላት ይመስል የኩፍኝ ጠቃጠቆዋን በጣቷ እየጠቋቆመች።

«አብሮሽ የኖረውን አሁን አስጨንቀሽ?»

«ሲያስጠላኝስ?»

«ዛዲያ አላሰላብሽ!» አላት የስርጉዱ ቦታዋን ጠቅ እያደረገ። መልስ ሳትሰጠው መስታወቱን አስቀመጠችው።

«እውነት አንድ ነገር ሆነሻል ታንጉት?» ሲል እንደገና ጠየቃት።

«እኔስ ምንም አልሆንኩ። ግና አስፈራኝ?» አለች ታንጉት ከሐሳብ ማመንታት ጋር።

«ማን? አባ ታጠቅ?»

ታንጉት፤ በአዎንታ መልክ ዝም አለች።

«ይህን ያህል ዘመን አብረሽው ኑረሽ አታውቂም?»

«እንደዚህ ሲሆን?» ታንጉት መልሳ ጠየቀችው።

«አንቺ የምታውቂው፣ በቤት በጎረቤት፣ በሠፈር፣ ተሆነ ከሁላችን የበለጠ ታጋሽ ነው። በጦርነት ላገሩ ባለው ሐሳብ ደግሞ ሌላ ይሆናል። ጦር ሜዳ ላይ አላየሽውም?»

«እንደዚህ?» አለች ታንጉት ስቅጥጥ እያላት።

«ምን መሰለሽ ታንጉት» ገብርዬ በማባበል ትከሻዋን በእጁ ጨበጥ አያደረገ «ካሣ እንደ ቀድሞው ካሣ ልበልው ደግነቱ ትልቅ ነው። ዓላማው ትልቅ ነው። በዚያው መጠን ቁጣውም ትልቅ ሊሆን ይችላል።

«እና... እንደዚህ ቅልት ቅንቅፋት ሲያጋጥመው ደሞ፤» ሐሳቧን አቋረጠችና፤ «እኔስ በጣም አስፈራኝ!» ሌላውን ሐሳቧን ሁሉ ትታ።

«ታወቅሽ አትፈሪውም! አሁን ይኸን ተይውና ሰው መምጣቱ አይቀርም። ጉድ ጉድ ብትይ ይሻላል። አባ ታጠቅ እንዳለው ጎንደሮች የሚፈትሹሽ ዛሬ ነው።

ሁለቱም ከደርብ ሆነው በበር በኩል ወደ ውጭ ሲመለከቱ እንኳን ደስ ያለህ ለማለት የሚመጣው የመጀመሪያው እንግዳ ከግቢው በር ደርሶ ነበር።

ገብርዬና ታንጉት፤ ስለ ሹመቱና ስለ ቴዎድሮስ በሚነጋገሩበት ጊዜ ከግንቦች ግቢ በስተምዕራብ ትንሽ ወጣ ብሎ በግምጃ ቤት ማርያም ሠፈር ሁለት ሰዎች እንደእነርሱው ስለ ዘመቱ  ስለ ቴዎድሮስና ስለ ገብርዬ በመነጋገር ላይ ነበሩ። ከጥሞና ጭውውትም ወደ ተጋጋለ ክርክር እያዘበሉ ናቸው።

ደብተራ አክሊሉ፣ ከጋረድ ቤት የመጣው ቀደም ብሎ የሹም ሽሩ ስብሰባና ገና መበተን ሲጀምር ነበር። የጋረድ ቅጥር ሚስት ጋረድ ገና እንዳልተመለሰ ስትነግረው ትንሽ እንደ   ተቅበጠበጠና እንደ ተቁነጠነጠ ቆይቶ እንደ ቤተኛነቱ በምድር በኢቱ ገባና፣ በደርቡ ሰገነት በኩል ሲመለከት የግቢው አካባቢ ጭር ማለት ጀምሯል። ሥነ ሥርዓቱ እንዳበቃ ዐወቀ። «እኮ የት ቆየ?» አለ ከራሱ ጋራ፣ ጥርጣሬም የቸኮላ ብስጭትም ተሰማው። ‹ደጎና ሹመት አግኝቶ ተስማምቶት በዚያው ለምክክር እልፍኝ ገብቶ ከቴዎድሮስ ጋር ቆይቶ ይሆን? ይህማ ተሆነ ስንት የለፋሁበት ነገር ሁሉ ተመልሶ ከንቱ መሆኑ ነዋ! ወይስ ወደዚያች ጋለሞታ ወዳጁ ዘንድ ሔዶ ይሆን? ይህማ ተሆነ ስንት የለፋሁበት ነገር ሁሉ ተመልሶ ከንቱ መሆኑ ነዋ! ወይስ ወደዚያች ጋለሞታ ወዳጁ ዘንድ ሒዶ ይሆን? ነገሩን ማወቅ መሻቴን እንዴት ችላ አለው? ግን ከዚያች ጎንደር ካፋጀች ጋለሞታ ወዳጁ ዘንድ ከሔደ ቢናደድ ነው› ሲል አሰበ። እንዲሁም መጠበቁ አላስቻለው አለና፣ ከዚያው አቅራቢያ ወደ ሚገኘው አንዲት የሚያውቃቸው መሻች ቤት ሔዶ አረቄውን እየደጋገመ ሲጠጣ ቆይቶ ሲመለስ ጋረድ ለጥቂት ቤት እንደገባ ደረሰ።

«የት ጠፋህብኝ ልጅ ጋረድ?» አለ ደብተራ አክሊሉ፤ ከጥያቄ ይልቅ መልክ በሞቅታ ወይም በሌላ የስሜት ሙቀት ጉበት መስሎ ከግንባሩ ላይ ጅማቱን ተገታትረው ነበር።

«አሄሄ! ዐውቄብሃለሁ የት እንደጠፋህ! የአንተ ጉርምስናና ወንድነት መቼ ይሆን የሚበርደው?» አለና በጓደኝነት ትከሻውን እንደመታቀፍ አድርጎ ከአጠገቡ ተቀመጠ።

«እባክህ ምንላርግ ዛዲያ?» አለ ጋረድ ከቁጣ ወደ መኩራራት መለስ ብሎ።

«ኧረ አበጀህ ወንድሜ!» አክሊሉ የጋረድን ትከሻ ጠብ ጠብ አደረገ፤ ቅጥር ሚሽቱ ወደ አለችበት ጉዳ በዐይኑ እያመለከተ፣ «ለመሆኑ ታውቃለች?» አለው በጥያቄ ሳይሆን የአድናቆት ምሥጢር በሚገልጽ ሹክሹክታ። ጋረድ እኔ ምን ቸገረኝ በሚል አኳኋን ትከሻውን ሰበቅ አደረገ። «ብቻ ጠንቀቅ ነው። ገና ብዙ ዕድል የሚጠብቅህ ሰው የቀናተኛ ሴት ነገር አይታወቅም ልጅ ጋረድ!» አሁንም ትከሻውን እንደ ማቀፍ አደረገው።

«እሺ እንዴት ነበር?» ሲል አክሊሉ በጉጉት ጠየቀው።

«ኧረ ተወኝ! ሕዝብ አዳሜ ተፋጀ እንጂ! ካሣ የለየለት!!» አለ ጋረድ በንዴት አነጋገር።

«እንዴት?»

ጋረድ የሆነውን በአጭሩ ተረከለትና «እኔም እኮ ያ -ፈንጠሬ ለጥቂት ቀደመኝ እንጂ ተነሥቼ ልክ ልኩን ልነግረው ነበር» በማለት ፎከረ።

አክሊሉ የደስታ፣ የተስፋ፣ ስሜቱ እየፈካ ሔደ። ጋረድን ቀስ እያለ ከገፋፋው ከአሰበው ድረስ ይሔድለታል። ትንሽ መጠጥ ቢጨመር ደግሞ ሁለቱንም የበለጠ ያደፋፍራቸዋል። «ዛዲያ የሹመት ቀን እኮ ነው። ድግስም የለ ተቤትህ?» አለ በቀልድ መልክ።

«ኧረ -- ኤጭ!» ጋረደ እንደ መወራጨት አለና መለስ አድርጎ፣ «ያንንስ እንተወውና ነገሩ ራሱ ያስጠጣል። አንች ማነሽ! የሚጠጣ ነገር አምጭልን። ምግብ ብጤም ትቀምሳለህ? እኔ እንደሆነ የዚያ ርጉም ግብር ልውጣ እያለ ይተናነቀኛል።

«እኔም አላሰኘኝም! ለመሆኑ ምን ተሸምክ?»

«ምኑን ብዬ ልንገርህ?»

«አህ? መቸም ተሹመሃል!»

ጋረድ በምሬት ከት ብሎ ሣቀ። «አዎ! መንገድ ላይ ትቸው መጣሁ እንጂ ፊታውራሪ ቀሚስና ወገራን!»

«ወገራን! ስሜንንም፣ ወልቃይት ጠገዴንም ሳይጨምር?»

«እንደ ቤት ውሻ ተሥር ተሥሩ ቱስ ቱስ ተሚሉት እንትኖቹ በተቀር ሁሉም እንደዚሁ ነው የደረሰው። የተማሪ ቁራሽ የምታካክል አገር።

«ወገራ? የደጃች ክንፉ ልጅ ወገራን በካሣ ይሾም? ወቸው ጉድ! ዛዲያ አየህልኝ አይደለ የሱን ነገር?»

«ሸቅብ እስቲለኝ ነዋ!»

«በፊትም እኮ ነግሬህ ነበር። ዘመዶቹን ነው ቀድሞ የሚጎዳ በአንተ ወንድሙ ላይ ነው ተቀዳድሞ የሚነሳ ብዬ!»

«ምን በደልኩት? አባቴስ ምን በደሉት?»

«ምንም! ምንም!» አለ አክሊሉ ንግግሩን በመርገጥ። «ደጃች ከንፉ፣ በሰማይ ነፍሳቸውን ይማርና እኛ ደጉ ሰውማ ታንተ ሳይለዩ እንዳንተ እንደ ልጃቸው አቀማጥለው አሳደጉት እንጂ ደሞ ምን በደሉት? በፊትም ነግሬሃለሁ» አለ በድጋሚ አክሊሉ።

ጋረድን በቴዎድሮስ ላይ ለማስነሳት ልቡን ማሻከር የጀመረው ገና ራስ አሊ ድል ከሆኑ ጊዜ አንሥቶ ነበር። መጀመሪያ በአግድሞች አነጋገር ነበር። ከዚያም፣ ቴዎድሮስ ከፋሲል ግንብ ላይ ሆነው ድፍን ጎንደር በንቅስ ወጥቶ የአዲሱን የአስተዳደራቸውን ዐዋጅ ባስነገሩ ጊዜ ሁለቱ ወደ ዳር ሆነው እየተመለከቱ፣ ‹አሁን ማ -- ይሙት አንተ እያለህ እርሱ ተዚያ ላይ ይውጣ?› ሲል በግልጽ ነገረው። የጋረድም ልብ በምኞት ወደ ግንቡ ሰገነት ወጣ። የሙገሳ ማር እየቀባ ዘወትር ተስፋ ሲመግበውም የጋረድ ምኞት በዚያ በሰገነት ላይ እንደ ተንጠለጠለ ቆይቷል። የአክሊሉ ሥጋ ጋረድ ደኅና ግዛት ይሾምና ልቡ ይረካ ይሆናል የሚል ነበር። ሥጋቱ ሳይደርስ ቀረለት።

«ዛዲያ በም ምህኛት ነው?» የሚለው የጋረድ ጥያቄ አክሊሉን ከሐሳብ መለስ አደረገው።

«በምን ምህኛት? ቅናት ነዋ! ምቀኝነት ነዋ! ሰው መቸም በሚበልጠው እንጂ በሚያንሰው እንደማይቀና ታውቃለህ። ትንሽ ሰው ምኑ ይፈራል ምኑስ ይቀናበታል? ዛዲያ አሁንም የሆነ እንደሆነ ካሣ ባንተ ያልቀና ያልተመቀኘ በማን ይመቅኝ? በኔ ሞት! ወንድ ጀግና ነህ። በሰማይ ነፍሳቸው ይማርና፣ የሕዝብ ፍቅር የነበራቸው የደጃች ከንፉ አንድ ልጅ ነህ። ለዚያው ሥልጣን ካንተ የተሻለ ማን አለና? እንዲያውም፤ እንዲያውም» አክሊሉ ንግግሩን አንጠጥልጥሎ ተወውና ወደ አረቄ መለኪያው ዞረ።

« ‹እንዲያውም› ያልከውን ጨርሰው እንጂ!» አረድ በበኩሉ አረቄውን ተጎነጨ።

«እህ?» አክሊሉ ለመናገር ያቅማማ መሰለ።

«ምን ነገር ከምላስህ እያደረስክ መልሰህ ትውጣለህ!» አለ ጋረድ ቆጣ ባለ አነጋገር፣ ሁለቱም የአረቄውን ሞቅታ እየተሰማቸው ሔዶ ነበር።

«ማለቴማ በነፍስህስ ባይመጣ!»

«ሲገለኝ?»

«እህ? ልጃቸውን የዳሩለትን ያንን የመሰለ ጌታ ይኸውና ታገር አጥፍቷቸው የለ? ደጃች ወንዲራድስ ያንን የመሰለ መኮንን ኮሶ ግቶ አልገደለውም?»

«ሰደበኝ ብሎ ነዋ እሱንማ!»

«ቢሆንስ! ለምሳሌ አሁን እነ ገብርዬ እነ ገልሞ እነ ዓለሜ፤ እንዲህ ጣራ ሲነኩ አንተ ወገራን በመሾምህ ደምህ ፈልቶ አንድ ነገር ብትናገረው፣ እንደዚያው መሆንህ አይደል? ኧረ ጨካኝነትና እብሪት ነው!»

ጋረድ በዚህ የፋሲል አዳራሽ እንደ መብረቅ ብልጭ ብሎ የወጣው የቴዎድሮስ ጎርዴም በራሱም አንገት ላይ ሲያንዣብብ ለቅጽበት በሐሳብ ታየውና ፊቱን ጨፍገግ አደረገ። አክሊሉ እንዳያውቅበት ግን ወዲያው ፈገግታ አሳዩ። «ግና ምን ያህል ብትጠላው ነው እባክህ?» አለው አክሊሉን።

«ምን አገናኝቶን እጠላዋለሁ? እርግጥ አልወደውም።»

«ዛዲያ ባትጠላው ነው፣ ፈረስክን ጫን እንጂ እያልክ እንደዚህ የምትቀሰቅሰኝ?»

«በሱ ጥላቻ ሳይሆን ላንተ ፍቅር ስል ነው። በስማይ ነፍሳችውን ይማርና ለዚያ ለደጉ አባትህ ውለታ ስል ነው። አንተ ተሱ በታች ውለህ እያየሁ ብል አጥንታቸውስ አይረግመኝም ጋረድ?» በኃዘን ዕንባው የመጣ ይመስል ዐይኑን ጭምቅ ጭምቅ አደረገ።

«ቢሆንም --- ቢሆንም» አለ ጋረድ በትዝብት መልክ። «ስለኔ ተኔ የበለጠ የምትጨነቅ መቸም አንተም ቂም ቢጤ ብትቋጥር ነው።

«ማን እኔ? የሕይወታችን ጎዳና ለየብቻ፣ እኔ ዓለም ነገሩን ትቼ ለነፍሴና ለእግዜር ያደርኩ። እሱ ጊዜ አንሥቶት መሬት ጠበበኝ ያለ። እኔ እንግዲህ ተዚህ በኋላ» እያለ አክሊሉ ጥምጥሙን ነካ ነካ በማድረግ አመለከተ። «በምድራዊ ሰው ቂም ብይዝ አምላኬስ ይወድልኛል?» ግን ሳይፈልግ ሐሳቡ ስንት ዓመት ወደ ኋላ ተመለሰበት።

ዐሥራ አምስት ይሁን ሃያ ዓመት ገደማ ይሆናል። ትክክለኛው የዓመታት ቁጥር በቁጭት ጭጋግ ተሸፍኖበታል። ድርጊቱ ግን ከሕይወቱ ጨርሶ አይጠፋም፣ ውጤቱም እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ አብሮት ይኖራል።

ካሣ አክሊሉና እርሻ እርሻ የሰለቻቸው፣ ጭቃ ሹምና ምስለኔ ያስመረራቸው ሌሎችም የቅርብና የሩቅ ጎልማሶች ዕድላቸውን በነፍጠኝነትና በአሽከርነት

ለመሞከር ደጃች ከንፉ ቤት በባለሟልነት ገብተ ነበር። ደጃች ከንፉ እናቱም አባቱም ከሞቱ ወዲህ፣ ለካሣ፣ በአባቱ እንደ ተተኩ አሳዳጊው የሚቆጠሩ ቢሆኑም፣ አኗኗሩ ከሌሎች ባለሟሎች እምብዛም የተለየ አልነበረም። ከሌሎቹ ጋር ይበላል፣ አብሮ ይኖራል፤ አብረው አደን ይሔዳሉ፣ ጉግስ ይገጥማሉ፣ ገበጣ ይጫወታሉ፣ አንዱ ከሁሉም ጋር፣ ሁሉም እርስ በርሳቸው የልብ ወዳጅነት ባይኖራቸውም፣ አብረው በመኖራቸው «የከንፉ አሽከር» እያሉ በመፎከራቸው አብረው፣ በመዝመታቸውና ጎን ለጎን በመዋጋታቸው፣ ከሌሎች መኳንንት ባለሟሎች ጋር በአደባባዩ፣ በየመሸታ ቤቱ በመፎከራቸው እንደ ባልንጀራሞች ይተያያሉ። ጠባያቸው ባይስማማ ይቻቻላሉ። በዚህ መካከል ግን፣ የካሣና የአክሊሉ ኮከብ ከመጀመሪያ አንሥቶ የማይገጣጠም ሆነ። ውቃቢው የነገረው ይመስል አክሊሉ፣ ካሣ የሚንቀው ይመስለዋል። በዚህ ላይ፣ የካሣ ኩራትና መንጠራራት ያበሽቀዋል፣ አጉል ድፍረቱ ያናድደዋል። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ደጃች ከንፉ ለአደን በለሳ ወርደው ሲመለሱ የመገጽ ወንዝ ሞልቶ ቆያቸው።

«ማነው እስቲ የሚፈትሽልን ጎበዝ?» ብለው ደጃች ከንፉ ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ካሣ ነጠላውን ወርውሮ ዘሎ ገባ። ወዲያውም ከአረፋው ጋር ይደፍቅ ጀመር። ሰው እየተጯጯኸ፤ ደጃች ከንፉ፤ «ዝም ብላችሁ ታያላችሁ! ኧረ ልጄን ውሃ በላው!» ብለው ሲቆጡ፤ አንድ መቶ ክንድ እንደተወሰደ ሦስት ብርቱ ዋናተኞች እንደምንም አወጡት። ከዚያም ራሱን ዘቅዝቀው ወደ ሆዱ የገባውን ውሃ እንዲወጣ ካደረጉና የተዘፈቀ ልብሱን አውልቀው ሌላ ነጠላ ከአለበሱት በኋላ ትንፋሹ መለስ አለለት።

«አሆሆ! ኧረ እንኳን አተረፈህ ወንድሜ! አፍላ ሙላት እኮ አደገኛ ነው። ቆለኞች የውሃ ጠባይ አታውቁም መሰለኝ! ታዲያ የውሃ ነገር ለእኛ ለደምቤዎች?» ሲል አክሊሉ እንደ ቀልድ ተናገረ- በሆዱ ግን «ይበልህ የቅብጠትህ ዋጋ ሲያንስህ ነው!» ሲል ተመኘ።

«ለደንቤዎቹ? ለጉረኖ ገፊዎቹ? ለአጓት ዛፊዎቹ? ታዲያ ምን ትጠብቅ ነበር? እጅህ በሶ ጨብጦ ነበር? አለው ካሣ በመጠየፍ አኳኋን ከእግር እስከ ራሱ እየተመለከተ።

«አጓትኮ ያፋፋል» በማለት አክሊሉ መለሰ፤ በቀመሰው አሽሙእር መብሸቁን እንደምን ውጦ።

«ገላ ቢያፋፋ፤ ልብ ያሳሳል!» ሲል ካሣ ሌሎቹ ተሣሣቁ። አሽሙሩ ግልጽ ነበር። ልብ የለህም ማለቱ ነው። ከንፉን ባይፈራ አክሊሉ ከዚያው በዚያው ፍልሚያ

ለመጠየቅ ከጅሎት ነበር። ግን «ይህ ምላስህና ቅብጠትህ አንድ ቀን» እያለ በማጉመትመት ዘወር አለ።

ደጃች ክፍኑ በአጉል ድፍረቱ ካሣን በመገሠጽ ፈንታ ሸለሙት። ከዚያም «የመይሳው ልጅ!» እያለ በተጀነነ ቁጥር «ቆማጣ --- ቆመጥማጣ» እያለ ትልቅ ትንሹን በዘነጠለ ቁጥር፣ ብዙው ጎረምሳ «ካሣ ኮስታራው» ሲለው ጊዜ፤ በሸንጎ ከሽማግሌዎቹ ልቆ ሽማግሌ ልሁን ሲል፤ በዘመቻ ከፊቱ እየቀደመ ጥላ በሚጋረድበት ጊዜ አክሊሉ በካሣ ተፈጥሮ የባሰውን እየበሸቀ ሔደ።

የጥምቀት ሰሞን አንድ ቀን፤ የደጃች ክንፉ አሽከሮች ለገና ጨዋታ ጉፋያ መስጫ መስክ ወጡና ካሣና አክሊሉ በተቃራኒ ቡድን ተሰለፉ። ከሠፈር ልጆች በስተቀር በበዓል ጊዜ እንደሚሆን፤ መኳንንት ለመመልከት ያልተገኙበት የአዘቦት ጨዋታ ነበር። አክሊሉ ግን፤ የቡድን አባት ሆኖ ከካሣ ጋር ሲጋጠም የመጀመሪያው ጊዜ ስለ ነበር፤ ቂጭቱን ሁሉ የሚወጣበት አንድ አጋጣሚ ያገኘ መስሎ ተሰማው። በእርግጥም፤ አክሊሉ የቡድን ልጆችን እየመራና እያሠማራ፤ ራሱን ሽንጡን ገትሮ ጥሩ እየተጫወተ ሲረቱ እንደቆዩ፤ ከሎው አጠገብ በድንገት ከካሣ ጋር ተጋጠሙ። «ሚናህን ብያለሁ፤ ውርድ ከራሴ እንዳትለጋ!» አለው ካሣ እሩሩዋን በእጁ ቀልቦ። አክሊሉ፣ ወደ ኋላው ፈንጠር ብሎ ከልጉ ማምለጥ ወይም ደግሞ ወደ ሚናው መግባት ይችል ነበር። ነገር ግን፤ «እስቲ ወንድ!» የሚል ስሜት ላንዳፍታ ከቆመበት ቸኩሎ ያዘው። ሁለቱም ገናቸውን አንሥተው ዐይን - ለዐይን እንደተጋጠሙ፣ አክሊሉ ከመመከቱ በፊት የካሣ ክንድ ውልብ ሲልና ሰማይ ምድሩ ሲጨልምበት አንድ ሆነ። ከዚያም በሳንሳ ተሸክመው ቤት ሲያደርሱት ሁሉ አልታወቀውም ነበር። በሦስተኛው ቀን፤ ካሣ አክሊሉ ቤት መጥቶ በመጠየቅ ክፋት አለማሰቡን ገልጾለታል። አክሊሉ ፈጽሞ አላመነውም። ማ ይሙት ሁለት ክንድ በማይሞላ ርቀት የለጋበት ክፋት ባያስብ ነው? እማዋይሽ የተባለችውን ወዳጁን ከአንድ ወር በፊት ሲወሽምበት ለእርሱ ሲል ደግ መሥራቱ ነበር? አክሊሉ ካሣን ስያነጋግር ፊቱን ወደ ግድግዳው አዙሮ ሸኘው።

አንድ ወር ያህል ተኝቶ ተነሣ። ከቸቸላ እየተመለሠ መኃኒት የሰጠው ስመ ጥሩው የካይላ ዐዋቂ የዳነ መሆኑን ቢያረጋግጥለትም፤ እንደወትሮው ሆኖ አለመዳኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም። በዚያ ጉርምስናው ሆኖ አለመዳኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም። በዚያ ጉርምስናው፤ በዚያ በሚያውቀው ዐመሉ የጎንደርን ቆነጃጅት ሲያይ፤ አንዳችም እንቅስቃሴ የማይሰማው በመሆኑ በመጀመሪያ ጥርጣሬ ብቻ ነበር ያደረበት። አይቶ፤ አይቶ ምናልባት ከሴት ወዝ ተለይቼ ስለቆየሁ ይሆናል ብሎ ገመተና ዱሮ ወደሚያውቃት አንዲት ጋለሞታ

ወዳጁ ዘንድ ሔደ። ምንም አልሆነም። የደጃች ክንፉ ባለሟሎች፤ በተለይም ካሣ እንዳያውቁበት በድብቅ እያጠያየቀ የዐይነ ጥላ ክታብ አሠረ። ጎንድ ተክለ ሃይማኖት ጠበል፤ ዋንዛዬና አለፋ መዋት ሔደ። ሰሚ ሰው ነው ለተባለው ታቦት ሁሉ ተሳለ። መጽሐፍ ገላጭ፤ ቅጠል በጣሽ፤ ሥር ማሽ ዐዋቂ ጠየቀ። አልተሻለውም፤ በመጨረሻ ፍሬው መፍረሱንና መውለድና መክበድ የማይችል መሆኑን ቁርጡን የነገረው አንድ የታወቀ የፈርንጂ ወጌሻ ነበር። ጉዱን ለቅርብ ጓደኛው ስንኳ ሳይናገረው በሆዱ ውስጥ ቀብሮ ያዘው። ሌሎቹ የዕድሜ እኩዮቹ፤ ሲያገቡ ሲወልዱ ውሽማ ሲያበጁ በጎንደር ጋለሞታ ሲደባደቡ የሱ እንዚያም ዝም የማለት ምክንያት እንዳይጠረጠርበት ወደ አንድ የገጠር ደብር ሔዶ፤ ቅኔ ከቆጣጠረና እስከ ጾመ ድጓ ዜማ ካስኬደ በኋላ ጠምጥሞ ወደ ጎንደር ተመለሰ። እንደ ዋዛ «ደብተራ አክሊሉ» የሚለው ስም ወጣለት።

አንድ የገላው ክፍል መሞቱን አክሊሉ ማመን ቢፈልግም፤ መንፈሱ ለአካሉ ጉድለት አልገዛለት አለ። የሴት ወዝ ጥማቱ፤ የሥጋ ፍላጎቱ በተቀሰቀሰ ቁጥር እርሱ ይህን ዋና የሕይወት ክፍል የተነፈገበትን ዓለም ‹አጥፊው› የሚል ስሜት ይገፋፋዋል። ዐቅሙን ገምቶ ሲመራመር ራሱንም ሲቆጣጠር አስተሠቡ ከነገሩ መነሻ ላይ ያተኩራል። በካሣ ላይ። አዎ! ቀደም ሲል ባልቀደም ባይነቱ፤ ምኞቱን ጥላ እንደጋረደበት ሁሉ በዚያ ገና ጨዋታ ደግሞ ወድነቱን ቀጥፎበታል። ዐይነተኛ የሕይወት ጣዕሙን አጥፍቶበታል፤ የወደፊት ዕድሉን አበላሽቶበታል፤ ይህንን በደል እንደሚቀበል ከራሱ ጋር ደግሞ ደጋግሞ ተማምሏል። ሲያስብ፤ መንገድ ሲፈልግ ቆይቶ ወደ ጋረድ የተጠጋበት ዋናው ምክንያት ይኸው ነው።

አክሊሉ፤ በራሱ ሐሳብ ተውጦ ለጥቂት ጊዜ ዝም ማለቱ ጋረድንም፤ በሞቃት ፈረስ በራሱ ሐሳብ እንዲጋልብ ዕድል ሰጥቶት ነበር.....እርሱም ካሣም የአንድ ቅድመ አያት ልጆች ናቸው። ግን ደጃች ክንፉና ልጅ ኃይሉ የትና የት ተገናኝተው። ልጅ ኃይሉ ከቋራ ጎጥ ሳይወጡ ነው ያረፉት። አባቱ ደጃች ክፉን ግን፤ ከርብ እስከ መተማ፤ ሰው ብቻ ሳይሆን ዛፍ ቅጠሉ ሳይቀር የሰገደላቸው መኮንን ነበሩ። ጎንደር የሚገቡት ነጋሪት እያሸጎሸሙ ነበር። አክሊሉ እንዳለው ከትውልድ ትውልድ ሳያንሰው፤ ከጀግንነት ጀግንነት ሳይጎድለው መልክ ከቁመና ጋር ሲኖረው፣ እንደ አዳኝ ውሻ ከፊት እየቀደመ ዕድሉን ምኞቱን የነጠቀው ካሣ ነበር። ገና በአፍላ ጉልምስናው ተዋበችን ማግባቱ የሚከፍትለት የዕድል በር ወለል ብሎ ታይቶት ነበር። ራስ አሊ እየሸመገሉ ሔደዋል። የሚተካ ወንድ ልጅ አልነበራቸውም። ዛዲያ አንዲት ሴት ልጃቸውን ጋረድ ሲያገባ በእግራቸው የማይተካበት ምን ምክንያት አለ? ምንም! ግን ካሣ፤ ቋራና አዳኝ አገር ወርዶ ባኮረፈ፣ ራስ አሊ ተዋበችን በሚስትነት ሰጡት። ተቀደመ፤ ዕድሉን ተነጠቀ፤ ደጃች ክንፉ ሲያርፉ ሲሆን

የጥንቱን «ማሩ ቀመስ» አገር፣ ያም ቢቀር የአባቱን ግዛት ለመሾም ተስፋ አድርጎ ነበር። ግን አሁንም ደጃች ተድላ ጓሉን ሳይቀር ወደ መሃል ጎጃም ገፍቶ ቴዎድሮስ ወሰደበት። በኋላም አፄ በጉበቱ ካሣ እየበረታ እቴጌ መነንና ራስ አሊ ድል ሆነው ከነመኳንንቶቻቸው ቢበታተኑ፣ ምንም ቢሆን ሥጋ ነውና የአንድ ደጃዝማች አገር እንደሚሾመው ገምቶ ነበር። ግን ከባለሟልነት ቁም ነገር ስንኳ ሳያስገባው፤ ከደጃች ውቤ ጋር ለመዋጋት ወገራ ሲዘምት ሳያስከትለው ቀረ። ካሣ ተቀብቶ አልተወለደም፤ ራሱን በራሱ ተቀባ። ወይስ አክሊሉ እንዳለው እኛ እንዲቀባ ተመችነው?.....

«እና አሁንም የሆነ እንደሆነ የዚህ ዓለም ነገር ለኔ እንግዲህ ምኔም አይደለ። አንተ ብቻ....» በማለት ጋረድን ከምኞት ሰመመኑ የቀሰቀሰው፤ ቀደም ብሎ ከሐሳቡ ያነቃአው አክሊሉ ነበር።

«እኮ ምናርግ ትለኛለህ? ተነሥቼ ልሸፍት ነው? በምን ሠራዊቴ ነው የማሸንፈው? ‹አያችሁት ወይ ያንን እብድ፣ አምስት ጋሞች ይዞ ጉራምባ ሲወርድ› ሲባል እሱም ተዘፍኖበት ነበር። እና እንደ እሱ አድርግ ነው የምትለኝ?» የጋረድ አጠያየቅ ብስጭት የሰፈነበት ነበር።

«አላልኩም።»

«ዛዲያስ?»

«ቀስ በቀስ ዕንቁላል በእግሩ ይሔዳል ተብሏል።»

«ሲቆምስ ገምቶ ይቀራል።»

«እንደሱማ እንዳይሆንማ ነው እኔም የምፈልገው።»

«እሺ ዛዲያ ምናርግ ነው የምትለው?»

«እንደዚህ ረጋ ብለህ ስንመካከርበትም መልካም» አለ አክሊሉ፤ የጋረድ ቅምጥ ሚስት ከጓዳ ገባ ወጣ እያለች ለስንተኛ ጊዜ የቀዳችለትን አረቄ እየጨለጠ። «እየህ፤ ልጅ ጋረድ አንተ ጀግንነት አለህ የሰው መውደድ አለህ። እንዳልከውም መኳንንቱ ሁላ ከተከፋእብት ተአሁኑ መንገድ ከፈተልህ ማለት ነው። እሱ ባወቅ። እና አንተ ነገራችንን በሆድህ ይዘህ ውስጥ ውስጡን ተዘጋጅ፤ እየመረጥክ ሠራዊት አሳድር፤ ወገራ መሾምህኮ ለዚህ ይረዳሃል። ከመኳንንቱም ወዳጅ አብጅ፤ አብዛ። ሌላውን ለኔ ተውልኝ። የአንተ ወንድነት የኔ ብልሃት፤ የፈጣሪ ረድኤት አንድነት ሲሆን ግዴለህም» አለ አክሊሉ። የጋረድን ትከሻ በማደፋፈር መታ መታ አረገውና። «ታንተ

ቤት ‹እንኳን ደስ ያለህ› የሚል እንግዳ አልመጣም፤ አሁን እንግዲህ ተገብርዬ ቤት እንሒድ» አለ።

«ምን› እንኳን ደስ አለህ ልለው እኔ ተገብርዬ ቤት?» ጋረድ ድምፁ ተስረቀረቀበት።

«ምናልባት?»

«በቁሜ ሙቻለኋ!»

«አልሞትከም፤ አትሞትም፤ አየህ ጋረድ፤ ‹ንጉሡ አንተን ሲሉ ለመላ አጎነበሱ› ሲባል አልሰማህም። ሙያ በልብ ነው። ሔደህ ሸንገልከውና ራስህ ለራስህ ያለ ክብር አልተቀነሰ። ለራስህ ነገር ስትል ዐውቀህ ነውና ያደረከው።»

«ባልሔድስ?»

«ብትቀር ገብርዬን አትጎዳው። ያሰብነው ነገር ደሞ አትጠመውም።»

«ምህኛቱን አስረዳኝ!» አለ ጋረድ ዐይኑን እያጉረጠረጠ።

«አየህ ገብርዬ ጦር አዝማች ተሹሞ የለ? ‹እሱን ቢያጣ የካሣ ኃይል ምን ይሆናል?› ብለህ አስብ። ስለ ገብርዬ ሐሳብ አለኝ። ያች ምሽቱም ገና ባላገር ገራገር ናት አሉ። ስለርሷም ሐሳብ አለኝ። እንዳልኩህ ብልሃቱን ለኔ ተውልኝ! እምነግርህን ስማኝ! አሁን እንሒድ!» አክሊሉ ጋረድን በጨርቁ ሳብ አድርጎ ሲያስነሳው እንደ ገራም ከብት ተሳበለት።

ከቤት ወጥተው መንገድ ሲጀምሩ፤ አክሊሉ በሞቅታ ውጋገን ከሐሳቡ ቅኔ ፈለቀለት።

«......አያ ጋረድ ጅሌ ከጅልም ጅልሌ፤

አክሊሉ ሲያቀምስህ የምኞት አሞሌ

አጉል ስትጋልብ ወድቀህ ብትሰበር፤

መቸስ ምን ይደረግ እኔ እንደሁ ነገሬ ተዚያ ተከይሲ ጋር» የሚል።

በቅኔው ሥምረት ከራሱ ጋር ፈገግ አለ።

ታንጉት፤ ቀደም ሲል የነበረባትን ሐሳብ ዘንግታ ጭንቀት በሞላበት የደስታና የኩራት ስሜት እንደዚህ ጊዜ ታውካ አታውቅም። የጎንደር መኳንንትና ወይዛዝር፤ ሹመት የሚፈልግ ደጅ ጠኝ ሁሉም አሁን ሚዛኑን አይቶ እንደ ዐቅሙ የሹመት

መጠየቂያውን እያስያዘ መጉረፍ ጀመረ። ከበድ ያልን መኳንንት ነን የሚሉ አንድ ሁለት መኳንንት ሽህር ከብት እያስነዱ መጡ። ከነሱ መለስ ያሉት ሌሎች ብዙዎች መኳንንት ወይዛዝርት ከሙክትና ከሽህር ጋር ማድጋ ጠጅ እያሸከሙ መጡ። አብዛኞቹ ዝቅ ያሉት ደግሞ ዐሥርና ሃያ እንጀራ ከስድት ወጥ ጋር የሆነላቸውም ገምቦ ጠጅና ጠላ አብረው አስገቡ። ባዶዋቸውን እየፎከሩ፣ እዬሸለሉ፤ እልል እያሉ የገቡም ነበሩ።

ገብርዬ፣ ከበር ውች ሰዎችን እየተቀበለ፤ ‹እንኳን ደስ አለህ› ሰላምታቸውን በምስጋና እየመለሱ ሲያስተናግድ፤ ከውስጥ ታንጉት ጉዳ የሚገባውን የበሰለ ነገር ከበለጡ ጋር ከጎረቤት የመጡ የቤት ሠራተኞችን እያመላከተች በየሥፍራው እንዲቀመጥ ታደርጋለች።

ምን የመሰለ ሙክት፤ ማድጋ ጠጅ፤ ሞሰብ እንጀራ፤ ከሁለት ድስት የዶሮ ወጥ ጋር ይዘው የመጡት አንድዋ ወይዘሮ፣ ከሁላ ራሳቸው እንዳስተዋወቁት ወይዘሮ ደብሬ የሚባሉ ነበሩ። ገብርዬን በተገቢው ከበሬታ ‹ሹመው ያዳብር› ካሉት በኋላ ውስጥ የተቀመጠውን ሁሉ እጅ ነሥተው እንደቆሙ፤ ታንጉትን ጥቂት አስተዋሏት። ቁመታቸው ብዙ ወንዶችን ወደ ታች ሊያስመለክታቸው የሚችል ቢሆንም በደኋሣ አጥንትና ይህንን ባለበሰ ሙሉ ሥጋ ተውጧል። ግን ከፊት የቦርጭ ወይም ከሁላ የዳሌ ግርጌ ግፊት አይታይባቸውም። መላ ቁመናቸው ተመጣጥኖ፣ ተስተካክሎ የወጣ ነው። ወደ ቀይ ዳማ የሚያደላው መልካቸው፤ አሁን የዕድሜ መሥመር ቢታይበት፤ በጊዜው ብዙ ወንድ ያፋጅ እንደነበር ያስታውቃል። ዐይኖቻቸው አሁንም እንደ ኮረዳ የሚቁለጨለጩ ብሩህ ናቸው። በዚህ ላይ እንደ ተለመደው የጎንደር ወይዛዝርት ሹርባ ሳይሠሩ፤ ወይም በሻሽ ሳይታሰር በእንዝርት ዛቢያ ነቀስ እንቀስ ተደርጎ የተዘረዘረ የሚመስለውና እንደ መስከረም አደይ አበባ፤ ሽበት በልግሥና ከተበተነበት ጎፈሪያቸው ጋር፣ የለበሱት ሰፊ አረንጓዴ ጠለት ቀሚስና ድርብ ኩታ፤ ደርባባነታቸውን ተጨማሪ ግርማ ሰጥቶታል። «ኧረ ባባጃሌው! አንቺ ነይ እንጂ ሣሚኝ!» አሏት ዓመት ሙሉ ናፍቆት እንደ ከረመ አክስት።

ታንጉት፣ የቴዎድሮስ ማስጠንቀቂያ ትውስ አላትና፣ ድንገት አዳኝ እንደ አየ አውሬ በድንጋጤ ወደ ኋላ በስሜት በረገገች። ወዲያው ትኩር ብላ ስትመለከታቸው ፈገግታቸው ሳባት። ጥርሶቻቸው እንደ ካላቸው ደኋሣ ናቸው። በሌላ ሰው ፊት ላይ ቢሆኑ ፍልጥ ጥርስ ይባሉ ነበር። ነገር ግን፤ በወይዘሮ ደብሬ ላይ ቢሆኑ ትልልቅ አልመሰሏትም። አብረው የሚሥቁ ከሚመስሉት ዐይኖቻቸው ጋር ተቀናጅተው አንዳች የፈካ ማሽላ አበባ፤ ቃሙኝ ቃሙም እያሉ የሚጋብዙ

ዐይነት ናቸው። ዕድሜ የዘረጉባቸው የፊታቸው መሥመሮች ስንኳ የሚስብ አንዳች ውበት ነበራቸው። «ኧረ ባባጃሌው ነይ እንጂ!» ሲሏት ድጋሚ፣ ጠጋ ብላ ጉንጯን እያገላበጠች ሰጠች። ባዳ እንደሚስማት አልቀፈፋትም። በኋላ ቆይታ ስታስበው ራሷም ገርሟታል። ብዙ ጊዜ የተለየችው ሰው የተገናኘች መስሎ ነበር የተሰማት። «በይ ሒጂ ወደ ሥራሽ!» ብለው ወደ ማድቤቱ ገፈተሩዋት።

ታንጉት፤ ጉዳ - ገባና ወጣ እያለች ስትመለከት ወይዘሮ ደብሬ ሁሉንም የሚያውቁ፣ ሁሉም የሚያውቃቸው ይመስል ከሁሉም አቅጣጫ ጨዋታ እየቀረበላቸው ከሁሉም ጋር ተዝናንተው ጭውውታቸውን ቀጠሉ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተከትለዋት ጓዳ ገቡ። «ኧረ ባባጃሌው ምን እያረግሽ ነው አንቺ ልጄ!» አሏት ከልብ የተቆጣ የማይመስል ፊታቸውን አኮሳትረው።

ታንጉት፤ ምን አገባዎት የሚል ቁጣ ከጀላትና አወልጣላት አለ። «ምነው?» አለች በመገረም ጥያቄ።

«እኮ ምን እየሠራሽ ነው?» አሉ ወይዘሮ ደብሬ፣ እንደ ልጅ ለመቆንጠጥ ይመስላል ጣታቸውን ወደ ጉንጭዋ እየዘረጉ።

«ምን ሠራሁ?» ታንጉት አሁንም ጥርጣሬዋና የአቀራረባቸው ድፍረት ያሳደረባት ስሜት ጨርሶ አልጠፋም። ግን አሁንም የቁጣ ፊት ማሳየት አልቻለችም።

«አንቺም፣ እሱም» አሉ ገብርዬ ወደ አለበት ወደ በሩ በዐይናቸው እያመለከቱ፣ «አዬ እናንተ የጫካ ሰዎች ነገር። ዝም ብላችሁ ሰውን ሁሉ ባንድነት በመደዳ ታስቀምጡታላችሁ?»

ታንጉት ነገሩ ስላልገባት በጥያቄ መልክ ተመለከተታቸው።

«አየሽ!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ ጠጋ ብለው በማንሾካሾክ፣ «ሰው እኮ የሚጨዋወተው ከመሰሉ ጋር ሲሆን ነው። ታለ ማዕረጉ ሱጥሉትም አይለውም። መሸስ ይኸው ነው፤ ጎንደሮች፣ ተኔ ጀምሮ የለመድነው ወግ።»

«አሁን ዛዲያ ምን ላርግ?» አለች ታንጉት፣ ሁሉም እንደገባ ባገኘው እንደ ተቀመጠ ገብቷል።

«አሁንማ ምን ታረጊያለሽ። ከተቀመጠበት ተነሡ ማለት የባሰውን ማስቀየም ነው። እንግዲህ የተቀመጠው እየወጣ ሲሔድ አዲስ የሚገነባውን እንደ ምንም ማድረግ ነው። እናንተ መቸም አታውቋቸውም፣ እኔ ላግዛችሁ?» ሲሉ ጠየቋት።

ታንጉት፣ ግራ ከሚያጋባት ከዚህ ሁናቴ ይልቅ ወደ ጓዳ ሥራዋ መመለስዋን አልጠላችውም።

ወይዘሮ ደብሬ የአዳራሹን አስተናባሪና እንደ ባለቤት ይዘው ጥቂት ከቆዩ በኋላ፤ አሁም ጓዳ ገቡና አሁንም በውሸት ቁጥ ዐይናቸውን በታንጉት ላይ አፈጠጡባት።

«ምነው እማማ?» አለች ታንጉት የመጨረሻው ቃል ሳይታወቃት ወጥቶ፣ እንዳጠፋ ሕፃን በሚመስል ጥያቄ።

«ኧረ እንዲያው ምናችሁም አያምረኝ!» የተማረሩ መሰለ።

«እህ! ምን አረግነ አሁን ደሞ?»

«ምን አረግነ? ምግቡን መጠጡን ዝም ብላችሁ እግረ መንገዳችሁ እንዳደረሳችሁ አይደል የምታቀርቡት?» ሲሉ ወደ በለጡ ወደ ሌሎችም የቤት ሠራተኞች ጣታቸውን ቀስረው ጠየቁ። ከታንጉት ጀምሮ ሁሉም ነገራቸው እንዳልገባቸው ከአስተያየታቸው ያስታውቅ ነበር። ለጥቂት ጊዜ ተፋጥጠው ቆዩ።

«ኧረ ባባጃሌው! መቸም የተሰናዳ ምግቡም መጠጥም በቤት አለ!» ሲሉ በመጠየቅ ሳይሆን በማረጋገጥ ዐይነት ጠየቁ።

«አለ እንጂ!»

«ዛዲያ እሱ ብቻ አይደለ ለመጣው ሁሉ የሚቀርብ! ለሁነኛው፤ ለቤተኛውስ ምን ይትረፈው

ብላችሁ ነው። ደግሞስ የመጣው ምግብና መጠጥ ሁሉ አውጥቶ አይጣል! ምን እየሰራችሁ ነው?» ሲሉ አፋጠጡ።

«ተሱምኮ እያቀረብን ነው» አለች በለጡ።

«እሱንማ አይቻለሁ። እግር እንደጣላችሁ፤ ጠላውን ተዚያ፣ ጠጁን ተዚህ ዶሮ ወጡን ለዚያኛው፣ ሥጋውን ለዚህኛው --- የቱ፣ የት እንደሚቀርብ ሳታዩ?»

ከታንጉት ጀምሮ ሁሉም በሐሳብ እንደ ማቀርቀር አሉ። «ቅድም ሰው እንደመለሱ እንዳልኩት ነው። እንዳይበላሽ የመጣው መበላት መጠጣት አለበት። ግን እንደመሰሉም ሲባል፣ አንድ ሰው፣ ያመጣውን ምግብ መልሰሽ አታቅርቢለትም። ይኸ ያመጣውን ለዚያ እየተደረገ ነው።» በጓዳ የተደረደረውን ከወዲያ ወዲህ ቃኙ። «ሞልቷል። ተብለቶ፣ ተጠጥቶም አያልቅ። አሁን እንግዲህ

አሰናዱትና አመለከታችኋለሁ! እሺ?» አዲስ እንግዳ ለማስቀመጥ ወደ አዳራሹ ተመለሱ። ታንጉት፣ «ወቸ ጉድ! ‹ሳይደግስ አይጣላም› አሉ?» እያለች በሐሳብዋ ከሠራተኞቹ ጋር በመገረም ተያየች።

ወደማምሻ አቅራቢያ እንግዳው ጥቂት ቀለል ማለት ሲጀምር፣ ገብርዬ፣ ‹ስቲ አባ ታጠቅን አይቸው ልምጣ። በዚያው ተነ ዓለሜ ብቅ ልበል› ሲላት እንደ መጀመሪያው ቢኖር ኖሮ ታንጉት፣ ‹እኔን ብቻየን ጥለኸኝ› ስትል በተጨነቀች ነበር። አሁን ግን ‹እንዳፈቀደህ!› አለችው።

ከግቢው ትንሽ ፈቀቅ ብሎ ጋረድና አክሊሉ እጆቻቸውን እያወዛወዙ በመከራከር ላይ ነበሩ። ጋረድ፤ የገብርዬን ቤት ብሩቅ ሲመለከት ድንገት ሐሳቡን ቀይሮ አልገባም ብሏል። የሰጠው ምክንያት ባዶ እጃቸውን መምጣቱ ነውር መሆኑን ነው። ትንሽም ይሁን ትልቅ አንዳች ነገር ይዞ ቢመጣ ደግሞ፤ እንደ እጅ መንሻ እንደሚቆጣጠርበት፣ ይህም የባሰውን ቢመጣ ደግሞ፤ እንደ እጅ መንሻ እንደሚቆጠርበት፣ ይህም የባሰውን ለርሱ ውርደት መሆኑን ግን ሕሊናው ይነግረው ነበር።

«ኤዲያ! እኔ ቁም ነገረኛ መስለኸኝ» አለ ደብተራ አክሊሉ በንዴት አነጋገር። «ወትሮውውንስ -- ወትሮውንስ!» ሳይጨርስ ተወው።

«አሃሃ! ይች ባቄላ ያደረች እንደሆነ አትቆረጠምም» አለ ጋረድ በሞቅታ ቁጣ። «ዐቅምህንም የረሳህ መሰለኝ!»

የአክሊሉ አንደበት ወዲያ ለዘብ አለ። «ምናረኩ?»

«እንዲህም ትናገር ጀመር?»

«እኔ መቸስ ላንተ ለአብሮ አደግ ወንድሜ ብዬ ነው እንጂ፤ ደሞ ሰው ተወንድሙ ጋር ሲጫወት እንደ ባዳ አፉን አይቆጥብ!»

ገብርዬ ከአጠገባቸው ሲደርስ ንግግራቸውን አቆሙ።

«ምነው በዛሬው ቀን ብቻችሁን ጎዳና ላይ ቁማችኋል ልጅ ጋረድ? ኧኸ ፊታውራሪ ልበልህ እንጂ!» አለ ገብርዬ የእግዚአብሔር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ።

«እኛማ ወደርስዎ ቤት መመጣችን ነበር» ሲል ደብተራ አክሊሉ ቀድሞ መሰለ። ጋረድ በክፉ ዐይን ገረፍ ቢያደርገውም ሊያስተባብል አልከጀለም።

«ኑዋ ግቡ!» ገብርዬ እጁን በመዘርጋት መራቸውንና የሚተዋወቁበትን ጊዜና ሥፍራ ለማስታወስ የሚሞክር ይመስል አክሊሉን ትኩር ብሎ ተመለከተው። «መሪጌታ አክሊሉ አባታችን ቤት፣ ተኔም ተካሣም ጋራ አብሮ አደጋችን ነው። አሁን ተኛ ተለይቶ የሎዛ ማርያም አልቃ ሆኗል» ሲል ጋረድ አስተዋወቀው። ‹ቴዎድሮስ ብሎ መጥራትም ይቀፈዋል ማለት ነው?› አለ ገብርዬ በሆዱ። ቴዎድሮስና ጋረድ የሥጋ ወንድማማቾች ቢሆኑም የደጃች ክንፉ ልጅ በመሆኑ ብቻ ጋረድ ምኞት እንዳለው በዚህም ምኞቱ ምክንያት ከርሱ ልቀው በሚያያቸው ላይ ሁሉ ምቀኝነት እንደሚያድርበት ሰምቷል።

ቴዎድሮስ ራሳቸው የጋረድ ነገር ሲነሣባቸው ‹ምን ኤዲያ! አይረባም። አጉል መንጠራራት ብቻ ነው። አሁን እሱ የክንፉ ልጅ ነው? ተምናቸውም የለ። እበት ትል ይወልዳል ነው፤ ለነገሩማ ተርሱ የቀረበ ወንድም መቸ ነበረኝ!› ይላሉ። ወገራንም የሾሙት እስቲ ተሞክሮ ይታይ በሚል ሐሳብ ይመስላል። ገብርዬ ስሜቱን በፊቱ ላይ አላሳየም።

የቴዎድሮስ ዘመድ በመሆኑም ይሁን ወይም የኩራት ስሜቱን ስለሚያውቁ፣ ከገብርዬ ቤት የነበሩት ሰዎች ሁሉ ለጋረድ የአክብሮት ሰላምታ አቀረቡለት። ገብርዬ ታንጉትን ጠርቶ አስተዋወቃት። «ልጅ....እህ? ፊታውራሪ ጋረድ ማለት እሱ ነው። መቸም ወሬውን ሰምተሻል።» ታንጉትስ ስለ መልከ መልካምነቱ ሰምታ ነበር። ረጅም፣ ቀይ ጸጉረ ዞማ፤ ከአፍንጫው፤ ከከንፈሩ ከዐይኑ ይህ ጎደለው የማይባል የጎንደር ወይዛዝርት ሁሉ የሚፈዝበት ነው እየተባለ ይነገርለት ነበር። ግን አሁን ስታየው ብዙም አላስደነቃትም። ባትጠላውም አልወደደችውም። ይህ ነው ብላ የአትጠቁመው አንዳች ነገር የሚጎድለው ተሰማት። ምናልባት ከፈገግታው ይሆናል። ጥርሶቹ ውብ ቢሆኑም ከንፈሩን ገለጥ ሲያደርግ የሚያሽሚጥጥ ያስመስለዋል። ደብተራ አክሊሉን ግን ከነአካቴውም በሚገባ አልተመለከተችውም።

«እንደምን ሰነበቱ ወይዘሮ ደብሪቱ?» አላቸው ጋረድ።

«እንዴት ከረምሽ አለኝ እንዴ! ኧረ የት ጠፋህ?! አላደርስህ አለ ማዳረሱ?» አሉት በቀልድ አሽሙር።

«በቀደም መጥቸ አጣሁዎት።»

«እኔን ልትጠይቅ? ወይስ ያችን ሞለፊጥ? ኧረ ባባጃሌው!» አለ ወይዘሮ ደብሪቱ፤ የሚማጡኑ ይመስላል በቤት ያለውን ሰው እየቃኙ። «እኔስ ዲቃላ ማሳደጉ ሰለቸኝ። እሷ ተቤት ተቋጥራ ስትቆየኝ እሱ ተጎረቤት ይዞ ሲመጣ በመሃል ቤት

እኔ.... ብቻ ግዴለም ጻጋ ነው።» አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጆቻቸውን ማለታቸው ነበር። ሰዉ ሁሉ ሣቀ። ታንጉት አብራ ከት አለች። ‹ስለ ልጆቻቸው በሰው ፊት እንዲህ ሲናገሩ አያፍሩም? ወቸው ጉድ!› እያለች በሆድዋ።

በመካከሉ ገብርዬ፣ «በሉ ተጫወቱ» በማለት እንደ ዘበት ወጣ።

«ወይዘሮ ታንጉት፣ አባቴን ያውቁታል?» ሲል ጋረድ ድንገት ጠየቃት ገብርዬ አለመኖሩን ከአረጋገጠ በኋላ።

ለምን እንደ ጠየቃት ምክንያቱ ለጊዜው ሊገባት አልቻለም። ‹ስለኔ የሚያውቀው ነገር ይኖር ይሆን? ታወቀስ በአሽሙር መንካቱ ነው? ወይስ አባቱን ድፍን አገር የሚያውቃቸው መሆኑን ለማስረገጥ? ወይስ እኔን ለማነጋገር የሚያወራው ሲጠፋው?» ከሐሳብ ጥያቄዋ ተመልሳ «ኧረ የታባቱን ዐውቄያቸው?» አለች።

«እጅግ ታላቅ ሰው ነበሩ። በዛ ሲባል» አለ ጋረድ ደረቱን እንደ መንፋት እያደረገ። «ካሣን እንደዚያ አርገው ያሳደጉትና ለዚህ እንዲበቃ ያደረጉት የኔ አባት ናቸው።» ደረቱን በእጁ መታ መታ አደረገ። «የኔ አባት ባይኖሩ ኖሮ ካሣ ይኸኔ፣ ገብርዬም ቢሆን....»

አክሊሉ ጎንተል አደረገው። ጋረድ ከዚህም ከመጣ በኋላ ያከለው ጠጅ የቆየ ሞቅታውን አብሶበት በከፊል ከራሱ ጋር የሚወጋ መስሎት ነበር። «እህ?» ብሎ እንደ መባነን ሲል፤ አክሊሉ ከወይዘሮ ደብሪቱ ጋር ሌላ ጭውውት ለጠቅ አደረገ።

«ወይዘሮ ደብሬ፣ ምነው ሎዛ ማርያምን ረሱዋት?»

«ኧረ ባባጃሌው!! አምና ሁለት ማድጋ መገበሪያ ስንዴ አላመጣሁም መምሬ?»

«መገበሪያ መች አጣና! ባላገር ሁሉ የሚያመጣው ነው። ሲሆን ድባብ፤ ታለበለዚያ የባሕር ማዶውን የሐር ጥላ ነው እንጂ!»

«አዬ መምሬ! ደንቢያን የምገዛ መሰልኩዎት!»

«ማሩ ቀመሰ ደንቢያን ይዞ ያባቴ ግዛት ነበር!» አለ ጋረድ በመካከል ገብቶ።»

ብዙዎች ሰዎች ሞቅታውን ስላወቁ በትዝብት ፈገግታ ይመለከቱታል። አንዳንዶቹም በጥርጣሬ ያስተውሉታል። የቴዎድሮስን የፍቅር ልብ ለማግኘት ሲል በማስመሰል ነገር ሊያወጣቸው እንደሆነስ? ቴዎድሮስ ራሳቸውን አልባቤ ሰው መስለው ከሥፍራ ሥፍራ በመገኘት ስለ አስተዳደራቸው ሕዝብ የሚለውን

ያዳምጣሉ የሚል ሐሜት አለ። መቸም ቢሆን ሥጋቸው ነው። ማን ያውቃል? ማን ይሞኛል?

የጋረድ ስሜት ግን ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ዐይነት ነበር። ከቴዎድሮስ ጋር ከአሁን ተፊት ለፊት ድፍረቱ ለመፈታተን ፈልጎ ሳይሆን የማመዛዘን ችሎታቸውን ደብዘዝ ያደረገበት ሞቅታ እንደ ፈለገ ብቻ ያናግረዋል። «አንቺ ታላጣው ሹመት አንቺንስ ለምን አልሾመሽም እንደኔ?» አለ ጋረድ እጁን ወደ ታንጉት እያጣቀሰ።

«አሆሆ!» ብላ ታንጉት ወደ ጓዳ በር ገብታ ተጋረደች።

«ኧረ ባባጃሌው! ሴት ደሞ ልትሾም? አንተስ ጉደኛ እየሆንክ ሔደሃል። አባትህ ይሄን ጉድ አላዩ» አሉ ወይዘሮ ደብሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ከልብ የተኮሳተሩ መስለው። ግን ይህም በሙሉ አልተዋጣላቸውም። ቁጣቸው ከልባቸው አለመሆኑ የሚያሳጣቸው ከዐይን አገላለጣቸው፣ ከከንፈር መሥመራቸው አንድ ልዩ ምልክት ያለ ይመስላል።

«ለምን አትሾምም ይኸው ተዋበች ተሹማ የለ?» አለ ጋረድ በመጠጡ ኃይል ርግጥ አድርጎ፤ «ያውም የመጨረሻውን!»

«ኧረ ባባጃሌው፤ ያ ሌላ ይኼ ሌላ» አሉ ወይዘሮ ደብሬ ነገሩን በማቃለል።

ብዙ ሰው ግን ግራ ተጋብቶ፣ ተገርሞ ዝም አለ። የጋረድ አሽሙር የታንጉትንም እንደ መርፌ ጠቅ አደረጋት። አዎ፤ እርሷም በአደባባይ ክብርና ማዕረግ ማግኘቱን ትወደው ነበር። ግና አላገኘውም። እርግጥ አባ ታጠቅ እንደልጅ አሳድጎ፤ ከዚያ ባላነሰ ፍቅር እንደሚያመለከታት ይታወቃታል። ከዚህ በተረፈ ግን የፍቅሩ መሠረት ለሰው በግልጽ አይታወቅም። እንዳሳደጋት የቤት በምሥጢር ነው። ዛዲያ ፀሐይ ካላየው ወዳጅና ጠላት ካላወቀው ምን ርባና አለው? ተዋበች ግን ከርሷ በኋላ መጥታ እንሆ ጋረድ እንዳለው በአደባባይ የመጨረሻውን ቀሚስ ለብሳለች። ታንጉት ከዚህ ሐሳብ ላይ ስትደርስ፣ ራሷን ይዛ እግዚኦ ማለት ቃጣት፤ እንደ ትልቅ እህት ትወዳታለች። ለካሣ መንገር የማትደፍረው ግን እንዲሆንላት የምትፈልገውን የምታማክረው ለተዋበች ነበር። ካሣን፣ የአሁኑን ቴዎድሮስ ከራስዋ ይልቅ ተዋበች እንደሚረግፍ አበባ ተንከባክባ እንደምትይዘው ታውቃለች። ‹ታዲያ እኔ በተዋበች ማዕረግ ልቅና?› ስትል ራሷን ጠየቀችና ራሷን በምሬት ለመውቀስ ሞከረች። ወዲያው መልሳ፤ ‹ግና ደግሞስ እኔስ ብሆን› የሚለው ጥያቄ ከጋረድ አነጋገር ጋር አስማማት። ሐሳብዋን ሁሉ ሲማታባት፤ ወደ ጓዳ ገብታ በተደረደረው ምግብና

መጠጥ መካከል ዘፍ አለችና፤ አገጭዋን በመዳፎቿ አስደግፋ ዝም ብላ ተቀመጠች። በአካልም፤ በሐሳብም ደከማት። ከአዳራሹ የሰው ንግግር ይሰማታል።

ጥቂት ቆይቶ ቅልል ሲላት፤ በአንዳች ዐይነት ምሥጢር ያውቁ ይመስላል ወይዘሮ ደብሬ መጡና፤ «ኧረ ባባጃሌው! ነይ እንጂ እንግዳሽን ሸኚ!» አሏት። የድካም ፈገግታ እያሳየች ተከተለቻቸው።

ጋረድ ቀደም ሲል በአክሊሉ ተገፋፍቶ ወጥቶ ስለ ነበር አላገኘችውም። «ያ ቋረኛስ እንደሆነ እየቀባጠረ ሔዷል» አሏት ወይዘሮ ደብሬ ሐሳቧን የተረዱ ይመስል። ሌሎችም አንዳንዱ፤ ከአንገቱ ቀልበስ፤ ሌላው ከትከሻው ሰበር፣ ወይም ከወገቡ አጠፍ እያለ ተሰናብቶ አለቀ።

«በይ እንግዲህ እንዳሻሽ!» አሉና በመጨረሻው ወይዘሮ ደብሬ ተሰናበቷት።

«መሔድዎ ነው!»

«ኧረ ባባጃሌው! ዛዲያ ከዚህ ላድርልሽ ነው?»

እንግዶች ሁሉ ሔደው፤ ሠራተኞች ሁሉ ተሰናብተው ታንጉት ከበለጡ ጋር ብቻቸውን ከቀሩ በኋላ፤ «ጉድ አይደለም?» አለቻት።

«ኧረ! እሜቴ ደስ የሚል ዓለም ነው!» አለች በለጡ በመቅበጥበጥ።

ከዚህም ከዚያም ስታሟላና ስታገላብጥ ቀማምሳ ነበር።

«ዝብርቅርቅ አልሆነብሽም በለጡ?» አለች ታንጉት በአብዛኛው ከራሷ ጋር። የወይዘሮ ደብሬን ከጋረድ ጋር፣ ብዙ ከማይናገረው የሎዛ አለቃ እየፎከረ ለያዥ ለገላጋይ አሰግሮ የተሰኘው አንድ ደጅ ጠጥቶ --- የገብርዬን አሽከር ሲል እየፎከረ ለያዥ ለገላጋይ አስቸግሮ የተሸኘው አንድ ደጅ ጠጅ መሳይ ጋር ሁሉንም አነጻጸረችው።

«ኧረ ቢሆንም ውብ ዓለም ነው» አለች በለጡ በድጋሚ። «ምንም አልቀመሱትም እኮ እትዬ!» ስትል ብርሌ ጠጅ አመጣችላት።

በእውነት ጉሮሮዋ ደርቆ ነበር። በአብዛኛው በሐሳብ። ጎንጨት አደረገችና፣ «ምኑን እናውቃለን ብለሽ። እስቲ መጨረሻውን ያሳምረው» አለች።

# ምዕራፍ ሁለት

ከዐዋጁና ከሹም ሽሩ በኋላ የጎንደር ማኅበራዊ ሕይወት ረጋ ብሎ ቀጠለ። እርጋታው ግን ውሽንፍር ከመነሣቱ በፊት እንደሚሰፍን የነፋስ ጸጥታ አሳሳች ነበር።

‹ሹመት ቀርቶብናል፤ ግዛት ተወስዶብናል› ብለው የተከፉት፣ ከመከፋትም ዐልፎ በንዴት የተቃጠሉት ጥርሳቸውን መንከስ እንጂ መሣሪያ ከመወልወል ገና አልደረሱም። ቁጭታቸውን፤ በሆዳቸው አላምጠው አላምጠው ለፍልሚያ እስኪነሡ ጊዜ ይወስድባቸዋል። ሥርተው እንዲበሉ የተወሰነባቸው ምድረ ካህናትና ጠምጣሚ ሁሉ እንደ አጋጣሚ አዝመራው ሠምሮ፣ ቀማኛና ወንበዴ በመቀነሱ ንግድና ገበያ ደማምቆ፣ በየቤቱ የመንደሩ፣ ግድስ፣ ማኅበርና ዝክር ሞልቶ ስለ ነበር፣ ጉዳቱ ገና አልተሰማቸውም። ቅሬታቸው በዋንጫ አፍ ላይ ከማጉረምረም አላለፈም ነበር። በዚህ ላይ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ስለ ዘመቱ የጎንደር ከተማ የሠራዊት ግርግር ተለይቷት ነበር።

የቅሬታው ቅሬታ በአብዛኛው የሚገለጸው በቴዎድሮስ የሸዋ ዘመቻ ወሬ ነው። ስለ ቴዎድሮስ የሸዋ ዘመቻ በየቤቱ፤ በየመሸታ ቤቱ፣ በየማኅበሩና ዝክሩ የሚወራው በከፊል ምኞት፤ አስተያየት በጣም በጥቂቱ ተባባሪ እውነትና በአብዛኛው ሟርት ነበር።

‹ያ ቋረኛ፣ የተከዜ በረሃ እስከ ሠራዊቱ በላውኮ ተባለ!› ይላል አንዱ።

‹አላንዳች ነገር መቼ እንዲያ አንከወከወው! መቃብሩ ቢጠራው እንጂ› ሲል ሌላው ይለጥቃል።

‹ያቺ ሚሽቱን ምን ዋጣት?›

‹የታደለ የሸዋ መኳንንት ሰቀጣት!›

‹ተወልዳ ካደገችበት ቤተ መንግሥት አውጥቶ ሲያንከራትታት!›

‹እናንተ፣ ሸዌ ዋዛ መስሎ ጉድ ሆነ አሉኮ› ሲል አንዱ ነገር ይለኩሳል።

‹ምን ይሆን?› ይላል ለወሬ የቋመጠ አድማጭ እይተቅበጠበጠ።

‹ውል የያዘ ነገር አንኳን አላገኘሁም። ብቻ፣ ግን......› አንጠልጥሎ ይተወዋል።

‹እኔ ደሞ የሰማሁት ተዚያ አንኮበር ላይ ተማርኳል ነው› ሲል ሌላው ተካ ያደርጋል።

‹ትልልቁን ሰው ሁሉ ሲያስር እንደኖረ የጁን አገኘ በለኘ!› ይላል ሌላው በደስታ መንፈስ ተውጦ።

ወንበዴ የጠፋለት እንዳሻው የሚያስር የሚዘርፍ የሚነዳ የዘመነ መሳፍንት ሹም ይተነሳለት፣ ብዙኃን ሕዝብ ደግሞ በበኩሉ ይህንን ሁሉ ወሬና ሐሜት የሚያስተናግደው በቁጭት ነበር። ቴዎድሮስ ተመልሶ የማይደርስለት የሚመስለው ከንፈሩን በሆዱ ነክሶ በዝምታ ብቻ ይታዘባል። አንዳንዱ ‹ጀግና የማይወድለት የመንደር አውደልዳይ የፈጠረው ነው!» ሲል ደፍሮ ይሚገታ። እረኛ ውሃ ቀጅ ሚርቱን ለማስተባበል ይመስል ለአባ ታጠቅ ሙገሳ በየዕለቱ አዳዲስ ዘፈን ያወጣል።

በዚህ ሁሉ መካከል ታንጉት ዝርዝሩን የመንደር ሚርት ሁሉ ሳይሆን፣ አንዳንዱን መጥፎ ወሬ ስትሰማ ስለ ገብርዬን ስለ ቴዎድሮስ ስለ ተዋበችን ስለ ሌሎችም በደኅና መመለስ ሐሳብ ቢገባትም የጎንደርን ኑሮ እየተላመደችው ሔደች። ከአንዳንዶቹ በስተቀር አብዛኞቹ የቴዎድሮስ የጦር አበጋዞች ሚስቶች እንደ ርሷው ጎንደር ቀርተው ነበር። ‹እስተዛሬ ተኛ ጋር ሲንከራተቱ ኖሩ። እስቲ አሁንስ ትንሽ ዐረፍ ይበሉ እንጂ። ደሞም ከተማውንም ይጠብቁልን ቴዎድሮስ ነበሩ። ተዋበች ግን ተለይቼ አልቀርም ብለው አብረው ሔደዋል እነርሱ ወደ ቤትዋ እየመጡ፤ ታንጉት ወደ እነርሱ እየሔደች በጭውውት በፈትል በስፌትና በሌላም የሴት ሙያ፤ የጥንት ዕውቂያዎቿ ጋር ብዙ ጊዜ እያደገ በመሔድ ላይ ነው። እርግጥ ሌሎችም የጎንደር ወይዛዝርት ሊጠይቋት ይመጣሉ። ከብዙዎቹ ጋር እስከ መወዳጀት ደርሳለች። አንዳንዶቹ አቃቂራቸው አይጥማትም። ሌሎችም አጉል ሲቅበጠበጡላት አንድ ውለታ እንድትሠራላቸው የሚፈልጉ መሆናቸው ይሰማታል። ወይዘሮ ደብሪቱ ግን ከሁለቱም አይደሉም። አነጋገራቸው ለዛ ያለው ቢሆንም በአቃቂር ያልተቀባባ ቀና ነው። እንደ ፊታችወ ፈገግታ ነገራቸው ግልጽ ነው። አንዳንድ ጊዜ ቀልዳቸው ቆማጣ ያስሮጣል። ከነገራቸው ሁሉ በሌለበት ሰው ማማት አይወድላቸው፣ ከተናገሩ በፊት ለፊት ነው።

ታንጉት የወይዘሮ ደብሬን ጨዋታ ስትሰማ ውላ ብታድር የማጠግበው እየሆነች ሔደች። ግማሽ ቀን ሙሉ ከቤቷ ቆይተው ለመሔድ የተነሡ እንደሆነ፣ ‹ይቆዩ እንጅ ምን አጣደፈዎት› ትላቸዋለች። አንድ ሁለት ቀን ሳይመጡ የዋሉ እንደሆነ፣ ‹ምነው በደኅና አይደሉም ወይ?› ስትል በለጥን ትልክባችዋለች። ወይም ራስዋ ሔዳ ከዚያው ስትጭወት ትውላለች።

የሁለቱም ወዳጅነት ገብርዬን ስንኳ አስገርሞት፣ ‹አንቺ እኒህ ሴትዮ ምን አቅምሰውሻል?› ሲል ወደ ሽዋ ከመዝመቱ በፊት እንደ ቀልድ ጠይቋት ነበር።

«ደሞ ምን ሊያቀምሱኝ ኑሮዋል። ተመልካም ሰው ጋር መወዳጀት ነውር ነው እንዴ?» አለችው።

«በዚህ አጭር ጊዜ ከአብሮ አደግ የባሰ ሆናሁብኝ ብዬ ነዋ!»

«ታጉል አብሮ አደግነት፣ አንድ ቀን ልብስ አጠባ ላይ የተዋወቁት ወዳጅ የሚበልጥበት ጊዜ አለ። ‹ዕውቂያና ልደት አንድ ቀን› ተብሏል። አንተስ ቢሆን አባ ታጠቅን የተዋወቅከው አንድ ቀን አይደለም? ብታውቃቸው እንዲህ ያሉ ሰው አይምሰሉህ?› አለች ራስዋን በአድናቆት ነቅነቅ እያደረገች።

«አሆሆ! አንደበትም እያስተማሩሽ መሰለኝ። በሉ ያዝልቅላችኋል!» አለና ነገሩን ተወው። ታንጉት ደስ እስካላትና ጥሩ ሰው ሆነው እስከ አገኘቻቸው ድረስ የሁለቱ ወዳጅነት የሚያስከፋ መስሎ አልታየውም። እርግጥ እንደ አሁኑ ዕድሜ ሳይገታቸው ከአንድ ወንድ አይረጉም ነበር ይባላል። እንዲያውም ገና ኮረዳ ሳሉ፤ በመጀመሪያ ያስቀመጡዋቸው ደጃች ተድላ ስለ ነበሩ በአፍላቸው ጊዜ ‹የተድላ አፋጀሽኝ› የሚል ቅጽል ወጥቶላቸው ነበር። አሁን ግን ምሥጢሩን በትክክል የሚያውቅ ባይኖርም በግልጽ ስማቸው በዚህ አይነሣም። ‹ቢሆንስ፣ እርሷ ሴት እሳቸው ሴት፣ ምን እንዲያደርጓት? አለ በሆዱ። ሌላ ሐሳብ ግን አመልጣበትም።

ታንጉት፣ ወይዘሮ ደብሬን ከወዳጅ ዐልፎ እንደ እናት ያም ሳይሆን እንደምትታመን አክስት እንድትመለከታቸው የሚያደርግ ሁናቴ የደረሰው ደግሞ ገብርዬ ወደ ሸዋ ከዘመቱ በኋላ ነበር።

አንድ ቀን፣ የራስ እንግዳ የደጃች ዓለሜ፣ የደጃች ቢተው፣ የደጃች ቢሠውር ሚስቶች ከታንጉት ቤት ተሰብስበው እህል ውሃ እየቀማመሱ ይጨዋወታሉ። ወይዘሮ ደብሬም አሉ። ማን በምን እንዳነሣው ሳይታወቅ ጨዋታው ወደ ባሎቻቸው ጀግንነትና ማዕረግ ያመራል።

«ታውቁ የለ? ዓለሜ ጉራምባ ላይ የወንዲራድን ጦር እንዴት እንዳተራመሰው። ሲመለሱ እኮ የሽጉጡ መጋል እጅ ያቃጥል ነበር» አለች የዓለሜ ሚስት

«ታልሽስ የቢተው ቶር ሊዶለዱም ምንም አልቀረው ነበር» በማለት ተኩራራች የቢተው ሚስት በበኩሏ።

«ቢሠውርማ ስሜን ላይ የገደለውን የደጃች ውቤ ሰው ቁጥሩንም አያውቀው» ስትል የራሷን አሞጋገሰች የቢሠውር ሚስትም።

«ግና ወንዲራድንም መነንንም ውቤንም የማረካቸው ገብርዬ ነው።»

«ቢሆንስ ተንግዳ ሊስተካከል?» አለች ጎንደሬዋ የራስ እንግዳ ሚስት።

«ተራስ አሊ ስንዋጋ ገብርዬ ቆስሎ አልነበር? ያን ጊዜ አባ ታጠቅ ሊጠይቀው ድንኳናችን መጥቶ፣ ገብርዬ ቀኝ እጄን ላጣ ነበር ነው ያለው። ቀኝ እጄን ላጠ ነበር!» ስትል ታንጉት በማስረገጥ ደገመችው። እርሷም የባሏን ጀብዱ ሳታወሳለት ላለማለፍ ቆርጣ በመነሳት።

«እንግዲህ ቢበልጥ አይደለ ራስ የተባለው? የሁሉም በላይ መሆኑ እኮ ነው አለች የእንግዳ ሚስት አነጋገሩዋን ፍርጥም አድርጋ።

«ፊታውራሪ እኮ ተሁሉ በፊት ማለት ነው። ደሞ የጦሩ ሁላ አዝማች ሆኗል። » ስትል መለሰች ታንጉት ላለመረታት።

ወይዘሮ ደብሬ ነገራቸው አስገርሞዋቸው ዝም ብለው በፈገግታ ሲመለከቱዋቸው ቆዩና፤ «አሁን ምን አከራከራችሁ? ሁሉም ጥሩ ጎበዞች ናቸው ማለቱ አይበቃም?» አሉ በማስማማት መልክ።

አንድ ሁለት ብርሌ ጠጅ የጨረሰችው የእንግዳ ሚስት፤ «ዛዲያ ራስና ፊታውራሪ እኩል ናቸው ለምን ትላለች?» ስትል ዐይንዋን አጉረጠረጠች።

ታንጉት በጀግንነት እንግዳ ከገብርዬ እንደማይስተካከል ስለምታውቅ ንድድ አላት። «ራስ ማለት ምንም ማለት መሰለሽ? የራስ ሚዜ፤ የግር ሚዜ እንደሚባለው ማለት እኮ ነው። አጃቢ ነው እንጂ ሙያው ተሌላ።»

ሌሎቹ ሲሥቁ፤ የእንግዳ ሚስት አሽሙሩ ተሰምቷት ከውስጥ በገነች «የራስ ሚዜምኮ ይሠራል» አለች እንዳይታወቅባት በበኩልዋ በቀልድ ለመሸፈን።

«በሉ በቃችሁ። ሌላ ጨዋታ አምጡ! ኧረ ባባጃሌው» አሉ አዝማሚያው ያልጣማቸውና የእንግዳ ሚስትን ሁናቴ የተገነዘቡት ወይዘሮ ደብሬ።

የእንግዳ ሚስት ግን፤ ሌላ ጨዋታ ከያዙ በኋላም ቢሆን ነገሩ ከሆድዋ አልጠፋም ነበር። ሲከነክናት እንደቆዩ ለመሔድ ሲነሡ፤ «ተዛሬ ነገ እጠይቅሻለሁ እያልኩ፤ ኧረ ለመሆኑ ገልሞ ዘመድሽ ነው፤ ታንጉት?» ስትል ጠየቀቻት። ሌሎቹ ሴቶች በቆሙበት ድርቅ አሉ። ታንጉት መልስ ሳትሰጥ፤ በጥፊ እንደተመታ ሰው ዝም ብላ ተመለከተቻት። «ያንዳገር ሰዎች ስለሆናችሁ፤ ድንገት እንደሆን ብዬ ነው» አለችና ምንም ክፉ ነገር እንዳልተናገረች ተሰነባብታ ወጣች።

ታንጉት፤ እንደ ታከተው ሰው፤ ከጠፍር ወንበሩ ዘፍ አለችና ፈዝዛ በወለሉ ላይ ዐይንዋን ተከለች። ስሜቷ ኀዘን ይሁን ንዴት በሚገባ አለየላትም። የመገረምም

ዐይነት ነው። ‹ምን ማለቷ ነው?› ሲል ሐሳቧ ደጋግሞ ይጠይቃታል። የእንግዳ ሚስት ምን ማለቷ እንደሆነ ግን ተሰምቷታል። ስለ ተሰማትም ታውቋታል። የእንግዳ ሚስ፤ ረስታው እንደቆየችው ነገር ድንገት ትሰንዝረው እንጂ አሽሙሩ ግልጽ ነበር። የምታስበው ጠፍቷት ሐሳብዋ ባዶ ሆኖባት ‹ወቸው ጉድ!› አለች ከራስዋ ጋር። ግን ሳይታወቃት ንግግርዋ ከራስዋ ዐልፎ በአዳራሹ ላለ ሰው የሚሰማ ነበር።

‹አንቺ!› አሉ ወይዘሮ ደብሬ ልጁን እንደሚቀጣ እናት፤ እሷን በእጅዋ ስበው አስነሥተው ራሳቸው ዘርፈጥ ብለው እየተቀመጡና፤ ለቁጣ አይሉት ለቀልድ፤ የሚያሻሙ ዐይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ፤ ‹ቅማንት ነሽ?› አሏት። አነጋገራቸው ያለማወቅ ጥያቄ፤ ወይም እንደ እንግዳ ሚሽት የሚያውቁትን ነገር በአሽሙር መልክ ማቅረብም አልነበረም። በፍልሰታ፤ ጾም ውሎ፤ ቆርቦ ወደ ቤቱ ሲመለስ መንገድ ላይ የሚያገኙትን ሕፃን፤ ‹ቆርበህ ነው?› ብሎ እንደ ማበረታታትም እንደ ማድነቅም ዐይነት ነበር።

ከደበዘዘባት ሐሳብ መለስ አለች። «ለምን ጠየቁኝ?»

«ኧረ ባባጃሌው! መሰሌን ዐውቀዋለኋ!»

«ቅማንት ነዎት?» ስት ጠየቀች፣ ስሜቱና ቅልል እያለው።

«ኧረ ባባጃሌው! አንቺን ነው የጠየኩሽ! ይልቅስ ቁጭ በይ ተፊቴ አትገተሪብኝ!» ሲሉ አዘዞዋት።

ስትቀመጥ እንደገና ጠየቋት። «እኔ እንጃ!» ስትል መለሰች የመደፋፈር ሣቅ በተቀላቀለበት ሙሉ ድምፅ።

»ዛዲያ ምን አስደነገጠሽ?»

«ነገሩ ገርሞኝ ነዋ!»

«ግና ገልሞ ቅማንት እንደሆነ ታውቂያለሽ?»

«ሲባል እሰማለሁ።»

«አገር ያወቀው ነው እንጂ! ያስደነገጠሽ እሱ አይደል? እኔም እንዳንቺ ሳለሁ እንዳንችው ሆኛለሁ።»

«ቅማንት ነዎት ማለት ነዋ!!»

«ኧረ ባባጃሌው! ነኝ አልኩሽ? የተባልኩትን ነው የምልሽ።» ግንባርዋን እያሻሸች ዝም አለች።

«የሆንኩትን መስማት አትፈልጊም?» አሉ ቅር የተሰኙ በመምሰል።

«እየሰማሁዎት እኮ ነው!»

«ይኸውልሽ እንግዲህ፤ ግና ጡቴ እንደዚህ ሎሚ እንደመሰለ ሳለ ነው» በማሳየት ጡታቸውን ነካ ነካ አደረጉት። «እስቲ ጠጅ ስጭኝ፤ አልተጣሁም እኮ» አሉና ቀድታ እስክትሰጣቸው ጠበቋት። «አለፋ ጣቁሳ ነው አገሬ። ዛዲያ እንዳልኩሽ ጎበዝ ሁሉ፤ ላግባት እያለ ሰው በሚልክበት፤ ውሃ ልቀዳ ወንዝ ስወርድ ይኸ ጎረምሳ ሁሉ ‹አንቺ!› እያለ ዐይኑን ተኔ ላይ ጣል በሚያደርግበት ጊዜ፤ ‹ሽፍታ ተነሣ› ተባለና ደጃዝማች ተድላ ተነመላ ሠራዊታቸው ዘመቱብን። ተዚያ ሠፈሩ ሁሉ፤ ሲዘረፍ ሲቃጠል፤ አንዱ ሲገደል ሌላው ሲማረክ ተኛ መንደር ደረሱ። አባቴ ቀደም ሲል፤ እንደ ወጣ የት እንደደረሰ ተማርኮ ይሁን ሞቶ አላውቅም። በመንደሩ በአብዛኛው የቀረውን ሴቶቹ ነበርነ። ዛዲያ ደጃች ተድላ ተፊት ሆነው እኛ ሴቶቹ እንደ ከብት እየተነዳን ስንሔድ ደጎና ሴቶቹን በእጃቸው እያመለከቱ ወደ አንድ በኩል አከማቹን። ተወስድነ ተሰፈራቸው። ኧረ ባባጃሌው! አሁን ሳስበው ይገርመኛል። ስለ ሌሎቹ አላውቅም። እኔን አንድ ቀን አስጠሩኝ፤ እልፍኛቸው! «ተዚያ በፊት ወንድ አልነካኝም ነበር። ምን ልበልሽ! ወደዱኝ! ሰው አይይብኝ አሉ። ዛዲያ እኔ ምን ቸገረኝ፤ ገና ጣሙ አልገባኝም፤ እሳቸውም ሽምግለው ነበር። ዝም ብዬ መሬት ለቀቅኋ፤ ዛዲያ የነሱም አለቆች እኔን መፈለግ! እኔ እምቢ ማለት! አንድ ቀን አንዱ፤ አለቃ ይሆናል፤ ‹አንቺ ደብሬ ቅማን የሚባሉት አንዴት ያሉ ናቸው?› ሲል ቢጠይቀኝ ክው አልኩኝ፤ እኔን መስሎኝ። ኧረ ባባጃሌው! ተመልሶ ሲያስቡት ያሥቃል እኮ! ተዚያም እያለቃቀስኩ ተደጃዝማች እልፍኝ ስገባ ምህኛቱን ጠየቁኝ፤ ነገርኩዋቸው፤ የመከሩትን አልረሳውም። ‹መቸስ፤ እኛማ የአፍ ልማድ ሆኖኮ ነው እንጂ አንቺን ይኸው ወድጄ አቅፌሽ የለም፤ ተሌሎች አብልጬ? አይዞሽ ወደፊትም እንደዚህ ያለ ነገር ስትሰሚ፤ ይኸው ተኔ ጭን ጋር ተሻሽተሽ የለም? በዚህ ስሜት እያቸዋ!› አሉኝ። መቸም የጭናቸውን ነገር ልተወውና - ኧረ ባባጃሌው! ይህን ደሞ ምን አስታወሰኝ አሁን እባካችሁ! ተዚያ ሰውየውን የት እንዳደረሱት አላውቅም፤ ጠፋ። እኔም የልብ ልብ በቃኝ! ተሳቸው ተለይቼ ጎንደር ስኖርም እንደዚያ መኳንንት ይረባረብብኛል እንጂ አንድም ሰው ፊት ለፊት እንዲህ ነሽ ብሎኝ አያውቅም። ይፈራላ! እኔም ብሆን ልኩን እነግረዋለሁ! እኔ ምን ቸገረኝ አገር ምድሩ በየቤቱ ቢንሾካሾክብኝ! አሁን አሁንማ ሲታክታቸው ጨርሰው ትተውት ይሆናል። እና ይኸው ነው እልሻለሁ ልጄ!» አሉና ብርሌያቸውን ዶቅዶቅ አድርገው

አስቀመጡት። ከባድ ቁም ነገር፤ መራራ ትዝታ ስንኳ ሕይወትን በቀልድ የያዘ የሚመስለውን የፊታቸውን ፈገግታ የሚለውጠው አይመስልም።

ታንጉት አፍዋን ከፍታ ስታዳምጣቸው እንደ ቆየች «እንግዲያው ቅማን ነዎት ማለት ነዋ!» አለች ድንገት በገነፈለ የስሜት አነጋገር።

«መባሌን ነው ያልኩሽ መባልሽን ነው ያልኩሽ፤ የቀረው ፍሬ ከርስኪ ነው። ሁሉስ ሰው አይደለ በቁመናውማ? ቴዎድሮስን የወደድኩለት ይህን ዘር ማንዘር ተዉኝ ማለቱን ነው።»

‹ታዲያ የኔንስ ነገር ለምን ግልት አድርጎ አያወጣውም?› ስትል በሆድዋ የቅሬታ ጥያቄ አቀረበች።

«ዛዲያ እንዲህ ነሽ፤ እንዲህ ነህ! ማለትን ምን ያመጣዋል መሰለሽ?» ሲሉ ራሳቸው ጠይቀው መልሱን ቀጠሉ። «ዐቅም ማጣት ነው፤ ሌላ አይምሰልሽ። ደጃች ተድላን ስለፈሩ፤ እኔን ጠየቁኝ አንጂ ‹ነሽ› ብለው አልሰደቡኝ። አንቺንም የእንግዳ ሚት አሁን ‹ገልሞ ዘመድሽ ነው ወይ?› ብላ በተዘዋዋሪ ነካችሽ እንጂ፤ ፊት ለፊት ‹ቅማንት ነሽ› ብላ ለመስደብ አልደፈረች። ገብርዬን ትፈራለቻ! ገልሞንም እንደዚህም አይጠይቁትም። እና፤ አየሽ ልጄ ዐቅም ታለው ሰው፤ ይኸ ደብተሮቹ፤ ጨዋ ነን የሚሉት ሁሉ የሚያወሩት ዋጋ የለውም፤ አይቸዋለሁ። ለመሆኑ ገብርዬ ያውቃል?» ሲሉ ጠይቋት በመጨረሻ።

«ምኑን?» ስትል መልሳ ጠየቀች። ልቧ ቢያውቅም በአንደበትዋ ማረጋገጡ አሁንም አልሆንላት ብሎ።

«ኤጭ ኧረ ባባጃሌው! ‹ተኛ ባላይ ጎራሽ እህል አበላሽ› አሉ! የአባጃሌውን ልጠላሽ ነው።» ለመሔድ የቃጡ መሰሉ።

«ይወቅ ዐይወቅ፤ እኔ ምን አባቴን ዐውቄ ብለውኝ? እኔ አልነገርኩትም፤ ምንምስ ብዬ ልንገረው? እሱም አንሥቶብኝ አያውቅም።»

«ቴዎድሮስስ? እሱም አይደል ያሳደገኝ?»

«እሱማ ሳያውቅ እንዴት ይቀራል?» መጀመሪያ ቴዎድሮስ ከእናቷ ዘንድ ሲመጣ እንዳየችው፤ እናትዋ ከሞተች በኋላ ከእርሱ ዘንድ እንደወሰዳት በአጭሩ አወጋቻቸው።

«በይ እንግዲህ አሁን መንፈስሽን ሳታስጨንቂ ዐረፍ በይ» አሉና በማባበል መልክ ጸጉሩዋን ከምከም ከምከም አደረጉላት።

ታንጉት ከሆድዋ ተቀብሮ የቆየውን ነገር የምታካፍለው ምሥጢረኛ በማግኘቷ አንድ ሸክም እንደወረደላት ያህል ቀለል ቢላትም ከሰዎች ጋር ያላት ግንኙነት ደግሞ በመጠኑ መለወጡ አልቀረም። እርሷ ሳይታወቃት በመቀየም ወደ እነርሱ መሔድዋን ስለቀነሰች ይሁን ወይም እነርሱ በማፈር ወደ እርሷ መምጣታቸውን ስለቆጠቡ፤ ማፈገፈጉ ከየትኛው በኩል እንደተጀመረ በትክክል ሳይለይ እንዲያው በደፈናው ከድሮ ጓደኞቿ፤ ጋር የነበራት ግንኙነትና የምታደርገው ጥይይቆሽ እየቀነሰ ሔደ። እርግጥ በማኅበር በዝክር፤ በሰንበቴ፤ ‹እገሊትን አመም አርጓታል› ሲባልና በሌላም ምክንያት ይገናኛሉ፤ ይጠያየቃሉ፤ በቤተ ክርስቲያ፤ በአደባባይ፤ ሲገናኙ ጥቂት ሳይጨዋወቱ አይለያዩም። ከዚህ በተረፈ ግን፤ ‹ውይ! ሳላይሽ ስንት ቀን ሆነኝ!› ብሎ ወደ አንዳቸው ቤት ጎራ ማለቱ ወይም «ምነው ጠፋሽ?» ብሎ ልጅ መላኩ ያለፈ ታሪክ እየመሰለ ሔደ። ጭውውታቸው ስንኳ ዐይነቱ ቃናውን ቀይሮ ነበር። እንደ ዱሮው ተዝናንተው አይቀላለዱም። ወይም የዱሮ ትዝታቸውን አንሥተው በስሜት አያወጉም። ስለ ጤንነታቸው ይጠያየቃሉ። ስለ ዘመቻው ወሬ ይወያያሉ። ከልባቸው ቢጨዋወቱ ቁስል እንዳይነካኩ የሚጠነቀቁ ይመስላል።

ምናልባት የቀሩት ግንኙነታቸውን እንደ ዱሮው ቀጥለው ይሆናል። ታንጉት አታውቅም፤ ለማወቅም ግድ አልነበራትም። ብቻ አንዳንድ ሳትፈልግ፤ ስሟን ሲያነሡና ሲያሟት በሐሳብዋ ታያቸዋለች። ይህ ሐሳብ ስለ ሌላው ሰው ያላትን አስተሳሰብ አጉል ጥርጣሬ አከለበት። በመንገድ ላይ የሚያጋጥማትና የማታውቀውን ሰው ስለ እርስዋ ዘር የሚያውቅ ይመስላታል። አንድ ሰው ትኩር ብሎ ቢመለከታት በሆዱ፤ ‹ይቺ ቅማንት!› የሚል ይመስላታል። ልጆች በራሳቸው ጨዋታ ሲሣሣቁ እንኳ በእርስዋ የሚያፌዙ መስሎ ይሰማታል። ወይዘሮ ደብሬ ባይኖሩ ኖሮ፤ ይህ ስሜቷ ቤቷን ዘግታ የምትውል ብቸኛ ያደርጋት ነበር። ከሌሎች በራቀች መጠን ደግሞ፤ ከወይዘሮ ደብሬ ጉያ ይበልጥ እየተሸጎጠች ሔደች። ገብርዬ ከሔደ ወዲህ ብዙም እንግዳ ቤቷ አይመጣም ነበር። ወይዛዝርቱ ዐልፎ ዐልፎ ብቅ ብቅ ይላሉ። መኳንንቱ ግን ከስንት አንድ ነው። አብዛኛው ወደ የሹመቱ ወይም ወደ ዘመቻው ሒድዋል። ከተማ የቀረውም ቢሆን አባ ወራው በሌለበት ከሰው ቤት መሔዱ ለሌላ እንዳይመስልበት፤ እምብዛም አይደፍረውም ነበር። ጋረድ አሁንም አክሊሉን አስከትሎ አንድ ሁለት ቀን መጥቷል። ታንጉት የቤቷን በእንግዳ ወይም በሰው አለመዘውተር ግን አልጠላችውም። እንዲያውም ብቻዋን ከቤት ሥራዋ ወይም ከወይዘሮ ደብሬ ጋር መሆኑን እየመረጠችው ሔዳ ነበር።

ይህንን ዝንባሌዋን የተገነዘቡት ወይዘሮ ደብሬ በሚያዉቁበት ዋዘኛ መልክ ሊያስተዋት ጀመሩ።

«ለባብሽና ነይ፤ ተነሽ እንሒድ!» አሏት አንድ ቀን።

«የት፤ ወይዘሮ ደብሬ?»

«የትም! ኧረ ባባጃሌው! እንደ ባሕታዊ ተዘግተሽ ልትሞቺ ነው? ነፋስ ይምታና! መልክሽም ይገረጣል እኮ!»

የዕለቱ ሽርሽራቸውና የጉብኝት ጉዞዋቸው በዚህ ዐይነት ተጀመረ። በመጀመሪያ በእግራቸው ሆነው ሁለቱ ብቻ በአቅራቢያቸው የሚገኙትን እየፈራረሱ የሔዱ ግንቦች አብያተ ክርስቲያናትን ሠፈሮች እያሳዩ ታሪካቸውን ሲነግሩዋት ከመጽሐፍ በቃላቸው ያጠኑት ይመስል ነበር።

«ይኼ ግምጃ ቤት ግንብ የሚባለው ነው። አጤ ፋሲል ናቸው ያሠሩት። ምድር ቤቱ የመጣፍ ማስቀመጫ፤ ደርቡ ደግሞ የጣፊ ትዛዙ መቀመጫ ነበር አሉ። አሁንማ ይኸው ወና ሁኗል። ይህን ደሞ ዱቄት ግንብ ይሉታል። ያጤ ፋሲል ነው። እንጃ እንግዲህ ማቡኪያ ይሁን ወይ የተፈጨ እህል ማስቀመጫ፤ በውል አላወኩትም። ያንን ትልቁን የፋሲል ግንብ መቸም አይተሽዋል እሳቸው ናቸው ብዙ ግንብ ያሠሩል። እሳቸው ጎንደርንስ የቆረቆሩ?..... ይኸም የአንበሳ ግንብ የሚባለው የአጼ ፋሲል ነው። አንበሳ ነበራቸው መሰለኝ። አሁን ቴዎድሮስ እንዳደረገው።

ከአንዱ ሠፈር ወደ ሌላው በሚሔዱበት ጊዜ ሁሉ አንደበታቸው አያቋርጥም። የከተማው ሰው ሁሉ የሚያውቃቸው ይመስል ዐላፊ አግዳሚው፤ «እንዴት አደሩ? እንዴት አረፈዱ? እንዴት ዋሉ?» ሳይላቸው አያልፍም። እርሳቸውም በበኩላቸው፤ ወንዱን ‹አንተ ወስላታ›፤ ሴቷን ‹አንቺ ሞልፋጣ›፤ ብለው በመትራት፤ ሳያሥቁና ሳያጨዋውቱ አይለይም። እርሳቸው የሚሰነዝሩት የነቀፌታ ከማሣሣቅና ከማቀራረብ በስተቀር በሌሎች ላይ ቅሬታ እንደማይፈጥር ሁሉ፤ ሌሎች የቀልድ ቃል ሲጥሉባቸው ከመሣቅ በቀር አያስከፋቸውም። ከውርደት ስሜት ነጻ የወጡ ነው የሚመስሉት። ሌላውም ይህንን ነጻነታቸውን ያውቅላቸው ይመስል በነጻ ያጫውታቸዋል።

እንደዚህ ግራና ቀኝ ያገኙን ሁሉ እያጫወቱ ከሌላው የጉብኝት ሥፍራ ይደርሳሉ። «ይኸ ደሞ የጻድቁ ዮሐንስ ግንብ ነው። ደግሞም የፍቅር ግንብ ይሉታል። ምህኛቱን አልደረስኩበትም። አጤ ዮሐንስ እንደሆኑ፤ ሰሌን ራሳቸው ሠርተው እየሸጡ ይኖሩ ስለ ነበር ስለ ፍቅር ማወቃቸውን እጠራጠራለሁ...... ለዚህ አይደል ጻድቁ የተባሉትስ?» ብለው ሣቅ አሉ።

«የአድያም ሰገድ ኢያሱ ግንብ፤ የአጽራር ሰገድ ዳዊት ግንብ - ዘፈን ይወዱ ነበር ይባላል - የመሲሕ ሰገድ በካፋ ግንብ፤ የቋረኛ ኢያሱ ግንብ፤ የራስ ጊርጊስ

ግንብ.....» እነዚህንና ሌሎችንም አሳይተዋት ሲጨርሱ ደግሞ በከብት ወደ ቀሃ ወንዝ አካባቢ ወሰዱዋት። ታንጉት የቀሃ ወንዝ ተጠልፎ መዋኛ የተሠራበትን የፋሲለደስ ግንብ የዞብልን መቃብርና የዶሮ ግንቡን ስታይ በጣም፤ ገረማት። ሰው ለፈረስ እንደዚያ ያለ ሕንፃ ይገነባል? ‹የሚወዱት ፈረሳቸው ነበር አሉ› ቢወዱት አይደል የመቃብር ቤት የሰሩለት!» ሲሉ ወይዘሮ ደብሬ አስረዱዋት። ስለ ዶሮ ግንቡም ቢሆን የሚናገሩት ራሳቸው «ብልሆችማ እንደዚህ ያለ መልካም ቤት አሠርተው ዶሮዋቸውን ራሳቸው እያረቡ ይኮመኩሙ ነበር። ከሙት ሙቱ ደጃች ውቤ ይሻላሉ። ስንት ጨርቅ እንደሚሰፋበት ዐላውቅም እንጂ አንድ ጋን ሙሉ መርፌ አስቀምጠው ነበር ይባላል፤ ቴዎድሮስ በኋላ የማረከው። በሞቴ እስቲ አንድ ጋን መፌ ይቀብራል ሰው? ቴዎድሮስ እንዲህ ያለው ሁሉ እለውጣለሁ ብሎ የሚለፋው?.... እስቲ እሱ ይሁነዋ!» ንግግራቸው አንዳንድ ጊዜ ካንዱ ወደ ሌላው ይዘላል።

«ቁስቋም ማርያምን የተከተሏትና ይህንን ግንብ የሠሩትማ እቴጌ ምንትዋብ ናቸው።» ዳገቱን ወትተው ከዐፀደ ቤተ ክርስቲያኑ ዐረፍ ብለዋል። «መልካቸው ውብ፤ ጠባያቸው ውብ፤ እንዲያው እጁን ታጥቦ ታለሳንካ የፈጠራቸው ነበሩ ይባላል። እስቲ ይታይሽ! ዛሬ እንኳን ሴቱ ወንዱስ እንዲህ አስቦ ይሠራልን? ዛዲያ ብዙ ጊዜ ሱባኤ እየገቡ ተዚህ ነበር የሚቀመጡት ይባላል።

ታንጉት ለመጀመሪያ ጊዜ ጎንደር ከወደታች በሰፊው ተንጣልሎ ታያት። «ደስ አይልም እማማ ደብሬ? አለቻቸው አጠራርዋ፤ ከወይዘሮ ወደ እማማ ተሻግሮ ነበር። ሳይታውቃት ነበር የጀመረችው።

እርሳቸውም «አሆሆ! አሮጊት አረግሽኝ? ኧረ አሁንም ማደባደብ አያቅተኝም!» ሲሉ ቢቀልዱም ወደውታል። «ሰው ላታማረ ምን ፋይዳ አለው!» ብለው መለሱላት፤ ባልተለመደ የትካዜ መልክ አሻግረው እየተመለከቱ።

ጉብኝታቸው ከንጎንደር ከተማ ክልልም እየወጣ ሔደ። ፋሲል፤ በአንገርብ፤ በመገጭ ወንዝ ላይ ያሠሩዋቸውን ድልድዮች፤ ከዚያም ርቀው ጓዝና አሸከር በማያዝ፤ በጎርጎራ የሱንስዮስን ግንብ፤ የናግራ ሥላሴን ገዳም፤ በእንፍራዝ ባሕሪ ግንብን እንድታይ አደረጉዋት።

ወይዘሮ ደብሬ ታንጉትን በየሥፍራው እያዘዋወሩ ብዙ አስደሳችና አስደናቂ ነገር ሲያሳዩዋት፤ በእውነትም እንዳሰቡት ወደራስዋ ብቸኝነት ማዘንበልዋ እየጠፋ ከመሔዱ በላይ፤ ስለ ቴዎድሮስ ዓላማና ምኞትም ጭላንጭል ይታያት ጀመር.....

....ከዘመቻ መልስ፤ ከወሎ ጉዞ በኋላ ከተሳሚ ሥፍራ ሠፈር ይተከላል። እህል ውሃ ከተባለ በኋላ አባ ታጠቅ ከባለሟሎቻቸው መካከል ተቀምጠው ጨዋታ ይጀመራል። አባ ታጠቅ፤ አንድ ምልክት በሩቅ የሚያዩ ይመስል ዐይናቸውን ከአድማስ ላይ ተክለው ጥንት ታላቅና ገናና ስለነበረችው ኢትዮጵያ አንድ ሰመመን በተመስጦ ትዝታ ይተርካሉ። አሁን ደካማ ሁና፤ ተከፋፍላ ሕዝብዋ ተጎሳቁሎ ስለሚገኝባት በሚያወጉበት ጊዜ ደግሞ፤ ንግግራቸው የትካዜና የቁጭት ቃና ይይዛል።

‹ጎበዝ ዛዲያ አገራችን እንዲህ ሆና ትቅር?› ሲሉ ባለሟሎቻቸውን በማበረታታትም በማፋጠጥም ይጠይቃሉ። እንደገና ትልቅና ገናና መሆን አለባት ብለው ስለሚያስቧት ኢትዮጵያ ሲገልጹ፤ ታንጉት በጊዜው ነገሩ ብዙ ባይገባትም፤ ወደ አንድ ጥግ ሆና ስታደምጣቸውና ሁናቴያቸውን ስትመለከት አብራ ትመሰጣለች። በሕላምቸው የሚያዩዋትን ኢትዮጵያ ለማየት ትሞክራለች። ግን ረቂቅ ሥውር ምስጢር ትሆንባታለች.....

አሁን ግን፤ የደከመ አካልዋን ለማሳረፍ ከአልጋዋ ላይ ጋደም ብላ ስትጎበኛቸው የዋለችውን የሚያስደንቁና፤ ዛሬ እያረጁና እየፈረሱ የሔዱ አብያተ ክርስቲያናት ግንቦች እንደገና በሐሳብ ስታያቸው በሕሊናዋ የሚነሡ፤ ‹እነዚህ ሁሉ አዳዲስ ቢሆኑ ኖሮስ? እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ብዙዎች ቢሠሩስ?› የሚሉ ጥያቄዎች በጣም ግልጽም ሳይሆን ቴዎድሮስ ስለሚያልሟት ኢትዮጵያ መጠነኛ ግምት ይሰጡዋት ነበር።

በጣም ሩቅ ያልሆኑትን የጥንት ቅርሶች አስጎብኝተው ከጨረሱ በኋላ፤ ወይዘሮ ደብሬ አንድ ቀን፤ «ገብርዬ ሲመጣ የማይቆጣሽ ተሆነ አሁን ደግሞ ደልጊ እንሒድ» አሏት።

«እሱማ ምን ያስቆጣዋል። ግና፤ ደልጊ ምን አለ? ስትል ጠየቀቻቸው።

«ዘመዶቼን አሳይሻለኋ!»

«አልቀዋል አላሉኝም?»

«የተረፈ ዘር ተለለኝ እርሜንስ ባወጣ?»

«እስከ ዛሬ የኖሩ ኑረው? ሰውስ ምን ይለዎታል?»

«መሔድ ደስ ታላለሽማ መቸስ......» ብለው እንደ ቅሬታ ነገራቸውን አንጠልጥለው ተዉት።

እለቅሶ ለመድረስ ወይም ዘመድ ለመጠየቅ የስንት ቀን መንገድ መሔድ ታንጉትን በእርግጥ ደስ

አላላትም። ግን ደሞ፤ ከርሳቸው ለእርሳቸው ለእርሷ ሲሉ ያን ያህል ሲደክሙ ልታስቀይማቸው ቀርቶ ለብዙ ጊዜ መለየቱንም አልፈለገችም። «እኔ ምን ቸገረኝ እንሒድ!» አለቻቸው።

ሁለት ቀን ሙሉ ተጉዘው ነው በሦስተኛው ቀን ደልጊ መንደር የደረሱት፤ የሳምንት ቅዳሜ ገብያ ደመቅመቅ ማለት በያዘበት ከረፋዳው ላይ ነበር። እህሉ፤ ቅመማ ቅመሙ ቅጡ፤ ሽማው፤ ከሙተማ የመጣው ጨርቃ ጨርቅ በመደዳው ተዘርግቷል፤ የጋማና የቀንድ ከብቱ በየመኻሉ ተሰግስጓል። ገበያተኛው ይተራመሳል፤ ያውካል፤ ከአንዳንዱ ቦታ ክምችት ብሎ አፍ ላይ የሚነጋገር ይመስላል፤ ሌላው ዘንድ እጁን እያወራጨ ይንጫጫል። የሁሉም ድምፅ ባንድነት ሆኖ ውሃ ሙላት ያተምማል። ከአሸዋ ቀመሱ መሬት የሚነሣው አቧራ አንዳንድ ጊዜ እንደ ጢስ ወይም እንደ መጋረጃ ሰውን ከቅልጥሙ በታች ሸፍን ያደርገዋል። መልሶ ወደታች ይወርዳል።

ወይዘሮ ደብሬ፤ ከጉብታ መሳይ ቁመው አጠቃዩን በዐይናቸው ከቃኙ በኋላ፤ «ድንኳን ተዚያ ትከሉ» ሲሉ አሽከሮችን አዘዙ፤ ደኅና ጥላ ወደ አለው የግራር ዛፍ በእጃቸው እያመላከቱ። እሳቸውም እሷም፤ አንዳንድ ድንኳን ይዘው ስለ ነበር በሁለቱ ቀን ጉዞ እየተጠቀመባቸው መጥተው ነበር።

ታንጉት፤ የጉዞዋቸው መጨረሻ መሆኑን አስባ ምክንያቱ ስላልገባት፤ «ለምና? ገበያ ላይ ድንኳን ተመትከል ቤት ብንገባ አይሻልም?» ስትል ጠየቀቻቸው።

«የምን ቤት?»

«ተዘመዶችዎ ነዋ!»

«ዘመዴን ተገበያ ላይ አላገኘውም መሰለሽ? የተጠፋፋው ሰው የሚገናኝበት እንዲያውም ተገበያ ላይ ልጄ።

«ልቅሶውን ሳይደርሱ?»

«ኧረ ባባጃሌው! እስቲ መጀመሪያ በሕይወት ያሉትን እንያቸው። ይልቅስ ድንኳኑን ቀልጠፍ በሉ ልጆች!» ሲሉ አዘዙ።

ድንኳኖቹ ተተክለው ሁለቱ በአንዱ ድንኳን በር ጥግ በድንኳን ላይ ሲቀመጡ፤ ወይዘሮ ደብሬ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው የገበያውን ትርምስ

ሲያስተውሉ ቆዩ። «እውነትም የቴዎድሮስ ልፋቱ ሁሉ መልካም ነው። ገበያው ቅልጥ ብሎ የለ! የዛሬ ሦስት ዓመት የመጣሁ ጊዜ፤ የአንድ ደብር ሰንበቴ የሚያክሉ ገበያተኞች ብቻ ነበሩበት። አሁንማ የጎንደር ቅዳሜ ገበያ ሊያክል ምን ቀረው!» አሉ በማድነቅ።

ልጅ ልጁ ጨዋታውን፤ ቅልቅ ቅልቁ ገበያውን እየተወ፤ ለመቅረብ የፈራ ይመስል በሩቅ ከብ እየሠራ ይመለከታቸው ጀመረ። የጎንደር ሰው ለገጠሬ ብርቅ ነው። አንዳንዱ እርስ በርሱ ይንሾካሾካል። ሌላው በመገረም በትሩን ተደግፎ ያስተውላል። ቀረብ ብሎ እጅ ለመንሣትና ለመተዋወቅ እየቃጣቸው ፈራ ተባ የሚልም አለ። ቀስ በቀስ ዙሪያውን ገለባ እንደ ተቆለለበት አውድማ ተከበቡ። አሽከሮቻቸው «ወጊዱ እንጂ» እያሉ ለመበተን ሲሞክሩ፤ «ተዋቸው እንጂ ያገሬ ባላገር ሁሉ ብርቁ ድንቁ አይደለ?» ማለታቸው ታንጉት የባሰ አስገረማት። እርሷ ከዚያ ሁሉ ሰው ጋር መፋጠጡ አስጠልቷት ነበር።

ወይዘሮ ደብሬ ግን ዙሪያቸውን ከቆመው ልጅና ትልቅ ሰው ጋር የዐይን ድብብቆሽ መጫወቱ አስደስቷቸዋል።

«ብንሔድ አይሻልም እማማ?» ስትል ታንጉት በማሳዘን ቃና ጠየቀች።

«የት?» አሏት አሁንም።

«ተዘመዶችዎ መንደር ነዋ?»

«ዘመዶቼ እኚሁና!» አለ ዙሪያ ከቆሙት ሰዎች በደፈና እያመለከቱ።

ከወትሮውም ጨዋታና ቀልድ ከማብዛታቸው ጋር አሁን ምኑም የማይገባ ነገራቸው ፍጹም ግራ ሲያጋባት ‹እህ ጤነኛም አይደሉ?› ስትል ራሷን ጠየቀች።

ወይዘሮ ደብሬ፤ የታንጉትን ሐሳብ የገባቸው ይመስል፤ ዘወር ብለው በፈገግታ ተመለከቷትና እጃቸውን ዘርግተው በሌባ ጣታቸው እየጠቆሙ «ነይ አንቺ፤ ኧረ ባባጃሌው ነይ እንጂ!» ሲሉ አንዲን ኮረዳ ጠሯት። ከተርታው ትንሽ ወጣ አለችና መልሳ ተቀላቀለች። «ኧረ ባባጃሌው! ነይ እንጂ የወንዜ ልጅ። ኧረ ባባጃሌው አሁን ምኔ ያስፈራል?» አውራ ጣትዋን በጥርሷ እየበላች አቀርቅራ ቀረበች። «ጠጋ በይ» አሏት። አሁንም እያመነታች ከፊታቸው አጎንብሳ እንደ ቆመች፤ «ቅማንት ነሽ?» ሲሉ በድንገት ጠየቋት።

ታንጉት ጥያቄውን ስትሰማ ክው ስትል፤ ኮረዳዋ ግን እስከዚህም አልደነገጠችም። ለአክብሮትም ይሁን ወይም ፍራቻ ዐይኗን ወደ መሬት አንዳቀረቀረች ዝም ብላ ቆመች። «ኧረ ባባጃሌው! ቅማንት ነሽ ወይ ነው የምልሽ?»

አሏት ወይዘሮ ደብሬ ኮስተር ብለው። ልጅቷ በመገረም አንድ መዳፏን ከጆሮ ግንዷ ላይ አስደግፋ መልስ ሳትሰጥ ወደ ኋላ ልትመለስ ስትል፤ ወይዘሮ ደብሬ ከተቀመጡበት ተፈናጥረው ሌላ እጅዋን ለቀም አደረጓት። ታንጉት በሕልም ውስጥ ያለች፤ ይመስል ከመደናገር ዐልፎ ዞረባት። ግን፤ በአንዳች ዐይነት ሥውር መግነጢስ እንደተያዘች ትኩር ብላ መመልከቷ አልቀረም።

«አይዞሽ አግሪ፤ የወንዝሽ ሰው ነኝ። ምን አሳፈርሽ? ‹ቅማንት ነሽ ወይስ አይደለሽም?› ብዬ ነው የጠየኩሽ።» የከበበው ሰው አብዛኛአው ንግግሩንም በሚገባ ሳይሰማ በሁናቴው ተገርሞ እርስ በርሱ ያውካካል።

ኮረዳዋ የአሉታ ወይም የአዎንታ መልስ ሳትሰጥ ባልተያዘው እጅዋ የሚያለቅስ ዐይኗን እያሸች በኃይል ነጥቃ ማምለጡንም ፈርታ፤ ከቆመችበት መቅላመሙን ቀጠለች።

ወይዘሮ ደብሬ «አትነግሪኝም? አትነግሪኝም? ሒጂ በይ!» ሲሉ ለቀቋት። እንደ ጦር በመወርወር የሰዉን ቀለበት ሰንጥቃ ተፈተለከች። የሰዉ ሁካታ በአንዴ አስተጋባ። ታንጉት አጉል ሕልም ትርዒቱ አፍዝዞ ቢይዛትም ከልጅቷ ስሜት ጋር አብራ ተሠቃይች። ወይዘሮ ደብሬ ሁካታው ጋብ እስኪል ጠበቁና ዙሪያውን ሰው ፈለጉ። ጥርሱን መንቀል ከጀመረ ተራ ልጅ ላይ ዐይናቸው ዐረፈ። «ና እስቲ የኔ ድንቡሽ» አሉና እንደሚታቀፍ ሁለት እንጃቸውን ዘረጉለት። በልጅ ድፍረት መጣና ከፊታቸው ቆመ። በቁልምጫ ጉንጩን ቆንጠጥ አድርገው ጠየቁት። «አንተስ ምንድነህ?»

«የናኔ ልጅ ነኛ!» አለ ባለማመንታት።

«ናኔስ ምንድናት?»

«የኔ እናት ናታ!»

«ቅማንት ናችሁ?»

ልጁ በጥያቄያቸው እንደ ጅል የቆጠራቸው ይመስል፤ በመገረም ተመልክቷቸው እየሣቀ ወደ ኋላ ተመለሰ። አሁንም ሁካታው አስተጋባ። አሁን የከበባቸው አብዛኛው ሰው ነገሩን እንደ ጨዋታ እየቆጠረው ሔዶ ነበር። ወይዘሮ ደብሬ፤ አሁንም እንደገና ዐይናቸውን ከዳር እስከ ዳር አዞሩና አፍንጫቸውን በነጠላው ዳርቻ ሸፍኖ፤ በትሩን ተደግፎ ከቆመ ጎረምሳ ላይ አተኮረ። «አንተ ጎበዝ! አንተ ጎበዝ!» ብለው ተጣሩ። ባጠገቡ ያሉት እርስ በርሳቸው ተያዩ።

«እኔን ነው?»

«አዎ፤ እስቲ ና!»

ነጠላውን ካፍጫቸው ላይ አውርደው ቀረበ።

«አንተስ ምንድነህ?»

በመናደድ ሳይሆን በመገረም ኮስተር ብሎ ተመለከታቸው፤ «እህ?»

«ዘር የለህም?»

«እህ! ዘር አለኝ እንጂ!»

«ዛዲያስ ዘርህ ምንድነው? ወይጦ ነው?»

«ኧረ!»

«ቅማንት ነህ?»

«ኧረ!»

«አማራ ነህ?»

«አወና!» አለ እርግጥ አድርጎ። ሰው ሁሉ ሲሥቅለት አብሮ እየሣቀ ወደ ሥፍራው ተመለሰ......

«አየሽ አይደል እንግዲህ ጉዳችንን!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ በአንድ እጃቸው የሚበሉትን ምግብ እያሰናዱ፤ አንድ እጃቸውን በማመልከት አኳኋን ወደ ገበያው አቅጣጫ ዘርግተው። ወይዘሮ ደብሬ የመጡበትን ጉዳይ ከጨረሱ በኋላ ገበያው ትርምስ ለመራቅ፤ ድንኳን አስነቅለው፤ ከመደሩ ጀርባ ሠዋራ ሥፍራ ላይ ሠፍረው ነበር። «አይገርምሽም?!» አሏት ዐይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ። ታንጉት መግረውሙን ገርሟት፤ አገጯን በመድፏ አስደግፋ የሌለ ነገር የምታይ ትመስል ነበር። ግን የምትሰጠው መልስ አልነበራትም።

«ኧረ ባባጃሌው! ምን አፈዘዘሽ? ነቃ እንድትይ ነበርኮ ያመጣሁሽ።»

«ይህንን እንዳይና እንድሰማ?»

«አወና! አየሽ፤ ቅማንቱም፤ ወይጦውም፤ አማራውም ሁሉ እግዜር የፈጠራቸው ሰዎች ናቸው። መልካቸው አይለይ! ወይ እነዚያ ጅራትና ቀንድ የላቸው። በሥራም፤ በሙያም የሆነ እንደሆነ፤ አይተናነሱ። እኩል ሠርተው ያድራሉ። እንዲያውም፤ ውይጦቹና ቅማንቶቹ ይበልጣሉ በሥራ። ዛዲያ ይችልጅ እንደየሻት፤ ‹ቅማንት ነሽ ወይ› ብዬ ስጠይቃት ‹አይደለሁም› እንዳትል መሆንዋን

ታውቃለች። ‹ነኝ› እንዳትል ደግሞ አፈረችበት። ዝም ብላ መቅለስለስ! ኃፍረትነቱን ገና ያላወቅው ትንሹ ልጅ ይሻላል። ሥቆብኝ ሔደ! ያኛው ግን፤ ‹ቅማንት ነህ ወይ?› ብየ ስጠይቀው አስተባበለኝ። አማረ ነህ ወይ ስለው ደሞ ‹አዎና!› አለኝ ተኩራርቶ። ይኸን ሁላ ዛዲያ ምን አመጣው? እነዚያ ለምን ያፍሩበታል? እንዲያውም ለነገሩ እኔስ አንቺን ብንሆን ለምን እናፍርበታለን? አያስገርምም?» ውሃ እየርከፈከፉ በሰውን ማሸት ቀጠሉ።

«ግን ምን አሳሰበዎትና ይዘውኝ መጡ?» ስትል ታንጉት ጠየቀች። መገረሙ ዐልፎላት፤ በወይዘሮ ደብሬ አመለካከት ነገሩን ስታስበው እወነትም ‹ለምን› የሚል ጥያቄ አሳደረባት።

«እኔም ራሴ ታሁን ቀደም መጥቸ ነበራ!»

«እንዳሁኑ ለመጠየቅ?»

«አወና!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ፤ ነገሩን ለማስታወስ ይመስል ዐይናቸውን ሰለምለም አደረጉ። «ነግሬሽ የለም አንድ ወታደር እንደ ሰደበኝ? በኋላ ቅጣቱን ሊያገኝ! ዛዲያ ነገሩ ሲከነክነኝ ይኖር ነበር። ደጃች ተድላ ይወዱኛል። ሌላውም፤ መኳንንቱም ወታደሩም፤ ዕድል ታገኝ ልጋደልብሽ ይላል። ‹ዘሬ ዛዲያ እንደነውር የሚታየው ለምድን ነው?› እያልኩ። ሀብትም፤ ከበሬታም ታገኘሁ በኋላ ምን እንዳሳሰበኝ አላውቅም፤ ‹እስቲ የተሰደብኩበትን የወገኖቼን ጉድ ልይ› ብዬ ወደዚህ መጣሁ። እንደዛሬው የገበያ ቀን ነበር፤ የምገዛ መስዬ አንዋን ባለ ቅቤ አስጠራኋት። እንዲያው ውብ መልከ መልካም ናት። ላዩን ሸተት አረኩና ‹ውስጡ ሁሉ ጥሩ ነው?› ብዬ ጠየኳት። ገንቦ ምሙሉ ነው። ‹አወን አለችና። ለመጠይቅ ሰበብ ፈልጌ፤ ‹የቅማንቶች ቅቤ ጥሩ ነው ይባላል። የቅማንቶች ቅቤ ነው?› ብዬ ጠየኳት። ‹ይሆን ይሆናል› አለችኝ። ‹ምን ይሆን ይሆናል፤ ያንቺ ቅቤ አይደለም እንዴ?› ብዬ አፋጠጥኳት። ጥቂት አቅማማችና ‹ነው እንጂ› አለችኝ። ‹ዛዲያ አንቺ ቅማንት ነሽ፤ አይደለሽም፤?› ተዚያ በኋላ ዝም። ባረጋት ብሠራት ልትመልስልኝ መሰለሽ? ታለፋሁት አይቀር ብዬ ገዛኋትና ሌላዋ ዘንድ ተጠጋሁ። ማር በትልቅ ቅል የያዘች ናት። ላዩን በጣቴ ጠንቆል አደረኩና፤ ‹ውስጡ በሙሉ ነጭ ነው፤ እንደ ላዩ?› ብዬ ጠየኳት። ‹አወና አለችኝ። አሁንም ቀጠል አረኩና፤ ‹የቅማንት ማር ውሃ ያነሣል ይባልላ። የቅማን አገር ማር ነው?› ማለት።» ነገሩ እንደ አዲስ ሣቅ ያመጣባቸው መሰሉ። «ትኩር ብላ አየችኝና ‹ቅማንት ንብ ታለ ተኛ መንደርስ የለም?› አትለኝም መሰለሽ? ‹አማራ ነኝ› ማለቷ ነዋ! እንደ በገንኩ ሙብገን ምን ብዬ ልንገርሽ። ተዚያ ምን እንዳሳሰበኝ አላውቅም ብቻዬን ወደ አንድ ሠዋራ ሥፍራ ሔድኩና መዓት ጊዜ ይሆናል፤ ለራሴ በራሴ፤ ‹እኔ ቅማንት ነው!› እያልኩ ጮህኩ። እውነትም ወጣልኝ፤

ቀለለኝ፤ ተዚያ በኋላማ ሰው ቢያማኝ፤ በአሽሙር ቢነካኝ ተመጤፍ የማይሰማኝ እየሆነ ሔደልኛ!»

«እና፤ ‹አንቺም አሁን ጫካ ሄደሽ ተራስሽ ጋር ጩሂ ነው› የሚሉኝ እማማ ደብሬ» አለች ከት ብላ እየሣቀች። አንዳች ሸክም የወረደላት የሚመስል ስሜት ድንገት ሠርጾባት ነበር።

«ታሰኘሽ ምናልባት! ግና ቁም ነገሩ» አሉ ወይዘሮ ደብሬ ንግግራቸውን ለማስረገጥ ራሳቸውን ነቅነቅ እያደረጉ፤ «ችግሩ ያለው ራሳችን መሆኑ ነው። የዘር ውርደታችን በኛው በራሳችን ውስጥ ተተሰማን፤ እሣቅ ቅጠሉ ሁላ፤ የሚዘባበትብን፤ የሚሰድበን፤ የሚያሽኳጥጠን፤ የሚያማን ይመስለናል። ቅማንትም ሆነን ወይጦ፤ እኛው ራሳችን ተውስጣችን ብንሆንሳ ምንተዳየ! ብለን ታመንበት፤ ሲሆንም ተኮራንበት ግና፤ ውጭ ሰው የሚለን አያስጨንቀንም። አያሥቃየንም። እንዲያውም ፋይዳ አንሰጠውም። ዐቅም፤ ማለቴ ሀብትም፤ ከበሬታም ታለን ደሞ ፊት ለፊት ደፍሮ ‹እንዲህ ነህ፤ እንዲህ ነሽ› የሚለን የለም። በሆንደ የሚለንንም እየቆየ ሲታከተው ይረስዋል። አሁን ገልሞን ተፊቱ ማን የሚናገረው አለ? ራሱ ውስጥ ውስጡን የሚያመው ታልሆነ በቀር። አንቺንም ቢሆን፤ ገብርዬ እስታለልሽ፤ አባ ታጠቅ እስታለልሽ ደፍሮ ፊት ለፊት የሚናገርሽ የለም። ቢበዛ፤ እንደዚያች የእንግዳ ሚሽት በሥውር ዘዬ ነው። ያን ጊዜ ‹አወ!› ብትያት ኖሮስ? ራስዋ ነበር የምታፍረው። እና አሁንም የሆነ እንደሆነ፤ ተዚህ ድረስ አምጥቸሽ ጉድ ያሳየሁሽ ለዚህ ብዬ ነው። እንግዲህ ራስሽ ለራስሽ ዕወቂበት። ለመሆኑ፤ በነገር ነዘነዝኩሽ አይደል?»

«ለኔ ብለው ነዋ!» አለች ታንጉት ዐቅፋ መሳም እየከጀላት።

«እንግዲህ ይብቃን። ‹የሰማነውን በልቦናችን ያስድርብን› ነው የሚሉት ቄሶቹ? አሁንስ እህል እንቅመስ።»

ወይዘሮ ደብሬ ከስንት ዓመት በፊት እንደሆኑት ሁሉ ታንጉት የሐሳብ መቅለል ይሁን የመንፈስ ነጻነት፤ ከውስጥ አንዳች ለውጥ ተሰምቷት ወደ ጎንደር ተመለሰች።

ገብርዬ፤ ከሸዋ ዘመቻ እንደተመለሰ በታንጉት ላይ የደረሰውን አንዳች ዐይነት ለውጥ የተገነዘበው ወዲያውኑ ነበር።

እግሩን ክፉኛ ቆስሎ፤ ቁስሉም አመርቅዞበት ጎንደር ድረስ የመጣው በቃሬዛ ቢሆንም፤ ብዙዎቹ የጦር አዝማቾች በዚያ ሲቀሩ እርሱ በሕይወት በመመለሱ ከተሰማት ደስታ ጋር፤ ሳያስፈልግ አንዴ ትራሱን፤ ሌላ ጊዜ የመኝታ ጋቢውን እያስካከለች፤ ከዚያ በፊት አይቶት በማያውቀው ሁናቴ ስታቆላምጠውና፤ የባጣ

የቆጡን ስታጫውተው በመገረም ተመለከታት። ወትሮም ቢሆን አንደበተ ዝግ አልነበረችም። ነገር ግን ምናልባት ከሴት ጓደኞቿ ጋር ካልሆነ በስተቀር፤ ከእርሱም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስትጨዋወት፤ በማፈርም ይሁን ልማድ ሆኖባት፤ አንገቷን ቀልበስ፤ ዐይኗን ሰበር ታደርግ ነበር። ብዙውን ጊዜም ከጨዋታ አፍላቂ ይልቅ ተቀባይና ሲያስፈልግም በዚያው ላይ አከታታይ ናት። ቃላት የምትቆጥብ ይምስል ነገርዋ የተመጠነ ነው። አሁን፤ በአስተያየቷም በአንደበቷም ተዝናንታ ጨዋታዋ እንደ ምንጭ ውሃ ኮለል ብሎ ይወርዳል።

«ታንጉት አዲስ ሰው መሰልሽኝ! እነኝህ ጎንደሮች ለወጡብኝ መሰለኝ» አላት ገብርዬ ጨዋታዋን ሲያዳምጥ ቆይቶ። አመለካከቱ ግን የፍቅር ነበር።

«መጥፎ ነገር አየህብኝ?»

«ደስ ደስ የሚል ነገር እንጂ!»

«ዋ! አባ ታጠቅ እንዳስጠነቀቀሽ እንዳያሰየጥኑሽ ኋላ!» የቀልድ ማስጠንቀቅ ነበር።

«ላንተ ደስ ደስ ታሰኘሁህ ምን ቸገረኝ! ስቀልድህ ነው ባክህ» አለች መለስ አድርጋ። «አንተ ተሔድክ ተብዙም ሰው ጋር አልተገናኘሁም። አዲስም ወዳጅ የለኝ! ወይዘሮ ደብሬ ብቻ አልተለዩኝም።»

«እሳቸውን ሴትዮ ሙጥኝ ብለሽ ይዘሻቸዋል?»

«ብቻዬን ስሆን እሳቸው ናቸው ያካረሙኝ ልጂ!» አለችና፤ ጊዜውን እንዴት በጉብኝት ያሳልፉት እንደነበር አጫወተችው። የደልጌውን ግን አልነገረችውም። ምክንያቱን መግለጽ ነበረባት። ለዚህ ደግሞ ገብርዬ ምን እንደሚሰማው አላወቀችም። ጋይንቶች በዘር ጉዳይ ጥብቅ እንደሆኑ ሰምታለች። ከፈለገ ቴዎድሮስ ራሱ ይንገረውና መላ ይፈልግበት ብላ ወስና ነበር።

«እሺ በጄ!» አለና ገብርዬ በእጅዋ ወደ አልጋ ሳብ አረጋት።

«ዋ! እኔ ኋላ የለሁበትም ቁስልህን!» አለች፤ እጅዋን ለማስለቀቅ ወይም ለመራቅ ስትሞክር።

«ለምን ተቆርጦ አይወድቅም!»

«አሆ! አንተ ጉደኛ ነህ! ባንድ እግር ልትዋጋ?»

«ፈረሰኛ እሆናለኋ!» አለና ደረቷ ትከሻውን እስኪነካ ድረስ ጎትቶ አስጠጋት።

«ዛዲያ ቆይ እንጂ የእልፍኙን በር ልዝጋው።» ተመልሳ ከጎኑ እንደተጋደመች፤

«አሁን ማ - ይሙት ድፍን ሸዋን ስታዳርስ፤ እኔ ነኝ እንጂ ተዚህ ተኮራምቼ የከረምኩት!»

አለሽ በውሸት ቅሬታ።

«አንቺማ እንዲያውም፤ የከተማው አውደልዳይ ሣር ቅጠል በሆነበት......»

«እኔ ታንጉት!»

«እኔ ገብርዬ!»

«እስቲ እንማማል!» ገብርዬ ዝም ብሎ ሲደባብሳት፤ «ፈራህ አይደል?» ስትል ጠየቀችው።

«ምን አስፈራኝ!»

ክርክሩዋን አልቀጠለችም። ሁለቱም ወዲያው ረሱት።

በኋላ ሁለቱም በረካ መንፈስ ክንድ ለክንድ በመንተራሰስ ተጋድመው እንዳሉ፤ ገብርዬ ዐይኖቹን ስልምልም በማድረግ የተመሰጠ የሚመስል ፊቱን ተመለከተችና፤ «ምን እያሰብክ ነው?» ስትል ጠየቀችው።

«ዕድሌ ነዋ!»

«የምን ዕድል?»

«አንቺን ለሚሽትነት፤ አባ ታጠቅን ለመሪነት የሰጠኝን መልካም ዕድሌን ነዋ!» ሲል መለሰላት። ይህ አባባሉ የልቡ እውነት ቢሆንም፤ እርሷን በሐሳብ ላይ ላለመጣል ብሎ ነው እንጂ አእምሮው ሌላም ዕድል እያሰላሰለ ነበር፤ የልጅ ዕድል።

ታንጉት መንፈሷን ቅልል ብሎት እንደ ቆየ ሁሉ፤ ከሸዋው ዘመቻ መልስ የዕለት ተዕለት ኑሮዋ፤ ከወትሮው ሞቅ ደመቅ ባለ መልክ ቀጠለ። በነጋው ጧት ጀምሮ ጠያቂው ይጎርፍ ጀመር። የሚመጣው ምግብና መጠት ጉዳ ጠበበው። ከብቱ ግቢውን በረት አስመሰለው። ገብርዬ፤ በአዳራሹ ለቁስለኛ በሚያመች ድንክ አልጋ ላይ ዐረፍ ብሎ፤ ጠያቂዎቹን እያመሰገነ ሲቀበል፤ ታንጉት እንደ ፊተኛ ማስተናገዱ አላደናገራትም። አሁን የገብርዬን የወዳጅነት ቡራኬ ያገኙት ወይዘሮ ደብሬም በቤቱ አድራጊ ፈጣሪ ሆኑበት። ‹ቴዎድሮስን ጦር የመንዝ ገደል በላው› እያለ ሲያሟርት የነበረው ሁሉ ለምን ጊዜው ተለውጦ ሥርገኛ ተቀባይ መምሰሉ ቢያስገርማትም፤ በራሷ ደስታ ተውጣ ስለ ነበር ግራሜዋን ዋጋ አልሰጠችውም።

ሌላው ቀርቶ በእንግዳ ሚሽት ላይ የነበራት ቅሬታ ለጊዜው ከሐሳብዋ ጠፍቶ ነበር። አዲስ ሁናቴዋን የተገነዘቡት የዱሮ ጓደኞቿም፤ በመገረም እንደ መጠቃቀስ እያሉ ዐሥር ጊዜ እርስ በርሳቸው ተያይተዋል.......

ማምሻውን ቴዎድሮስ፤ ገብርዬን ሊጠይቁ መጡ። ተከታትሎ፤ መሔድ ያቃታቸው ሽህር ላሞች፤ እየተነዱ ገቡ።

ገብርዬ ተነሥቶ ለምቆም ሲሞክር፤ «ኧረ ኤዲያ! ምን እያልክ ነው? ዐርፈህ ተቀመጥ ይልቅስ!» አሉት በጉደኛ ግሣጼ። «ለመሆኑ እንዴት ነህ አሁን?»

«ደህና ነኝ፤ በጣም ደኅና ነኝ አባ ታጠቅ።»

መምጣታቸውን ቀደም ብሎ መልከተኛ ሲነግር፤ ብዙው ራሱ ዐውቆ፤ ሌላዉም ወይዘሮ ደብሬ፤ «ደከመህ እኮ ፊታውራሪ፤ ሕመምተኛ ቁስለኛ ነህ፤ ግባና ጋደም በል» ሲሉ ባለቤት ከሌለበት ቤት እንግዳ አይቀመጥምና ነገሩ እየገባው ተነሥቶ ስለሔደ፤ በኢቱ ጭር ባይልም ቀለል ብሎ ነበር። ቴዎድሮስም የመጡት ጥቂት ራሳቸውን ነው።

«ይቆያል እንጂ እሱማ የት ይቀራል! ነገ ወጌሻው ጨርቁን ይፍታና አጥቦ አዲስ መድኃኒት እንዲያደርግልህ። ቆይቷል። አንቺ ደሞ» አሉ ቴዎድሮስ ወደ ታንጉት እያመለከቱ፤ «ተሣው ጋር ሽኮናውን፣ ቅልጥሙንም እየቀቀልሽ ጠግኚው። ማብሰሉ ታቃተሽማ ለጉድ ነው። ወዮ ነግሬሻለሁ!»

«እሱ እሺ ብሎ ተበላ ለመሥራቱ መች ይገዳል አባ ታጠቅ?» አለች ታንጉት፤ ውሽትነቱና ቀልድነቱ በሚያሳውቅ ማሳጣት።

«እኔ ምን ቸገረኝ። ተቤት ተወዝፎ ይኖራታል!» አሉ ቴዎድሮስ በተመሳሳይ ዛቻ። «ታሁኑ ዘመቻ የሚቀረውም ቢት ዋይ ቢሆን ነው!»

«የምን ዘመቻ አባ ታጠቅ!» ገብርዬ እንደመፍናጠር ቃጣው።

«ዘመቻችን ተጀመረእንጂ መቸ አለቀ ብለህ ገብርዬ? አሁን ግና ይች ወርቂት ‹ወሎን ይዛ እንደገና ሽፍታለች› የሚል ወሬ መጥቷል። ያን ያህል ምላ ተገዝታ፤ በሱዋው አልፈን በሸዋ ዞረን እግራችን ሳይገባ ከምንጊዜው?» ቴዎድሮስ አንድ ነገር ትዝ ያላቸው ይመስል ፈገግ አሉ። ወርቂት በጦር የሚያሸንፉትን በሌላ እንደምትገራቸው የሚነገርላት ቆንጆ ነበረ። «አሁንስ አይማረኝ አልምርም። ያገኘዋል ተጁ።» ቅጣቱ ይታያቸው ይመስል ኮስተር አሉ።

«መቼ ልትሔድ ነው? እኔም እኮ እንደምንም መሔድ እችላለሁ» አለ ገብርዬ እግሩን እያሳየ።

«እንኳን አንተ ቁስለኛው ጤነኛው ሠራዊትም ጥቂት ጊዜ ዐረፍ ብሎ ነው የሚነሣው። እስቲ መጀመሪያ ድነህ ቆየኝ። ለሌላው ትደርስበታለህ» ብለው ቴዎድሮስ ግራና ቀኝ በቤት ያሉትን ሰዎች እንደመገምገም ካደረጉ በኋላ፤ «ለመሆኑ እንዴት እንደቆሰለ ነግሮሻል?» አሏት ታንጉትን።

«ኧረቴ!»

«አፍሮ ነዋ!» ከገብርዬ ጋር ቁልጭልጮ የሚጫወቱ መስለው እየሣቁ። «ጀግናው ገብርዬ፤ ጅሌ ሆዬ፤ በነፍጥ በጦር በጎራዴ የመጣውን ፊት ለፊት፤ ግንባር ለግንባር እየተጋፈጠ መሬት አየበቃኝ ሲል ብልጥ መንዜ ሆዬ ከቁጥቋጦ ሥር ተሸጉጦ መርግ መልቀቅ። ቅልጥም አደረገዋ! እንዲያውም ዝንጀሮ ሳይሆን ይቀራል መርጉን የለቀቀው? አገሩ ሁሉ ዝንጀሮ ብቻ ነው!» አሉና ቴዎድሮስ እንደ ወንድም በፍቅር እየተመለከቱት ከት ብለው ሲሥቁ ሌላውም ለቀቀው። ታንጉት ከልብ አንፈራፈራት። ወይዘሮ ደብሬም አፋቸውን በእጃቸው ከድነው በቆሙበት እንደ ቅጠል ተንዘፈዘፉ።

«ሲሮጥ አይቸዋለኋ! ሰው መሆን አለበት!» አለ ገብርዬ አብሮ እየተንከተከተ።

«አዬ ገብርዬ! ሰዉ በጨርቅ ፈንታ፤ ያን ባናውንና ደበሎውን ለብሶ፤ በሩቅ ከዝንጀሮ አይለይ! ዝንጀሮምኮ ይሮጣል። እንዲያውም ተሰው አብልጦ!» ሲሉ ቴዎድሮስ፤ ሣቁ እንደገና ቀለጠ።

«አንጓች!» አሉ ቴዎድሮስ ለመሔድ ሲነሡ። ቀረብ አለች። «ነገ ብቅ በይና ተዋቡን ጠይቂያት እንጂ!» አሏት። አነጋገራቸው መሳሰብ ወይም መለመን ይመስል እንጂ፤ ውስጠ ትእዛዝ ጭምር መሆኑን ታውቃለች። ቴዎድሮስ ‹እባክህ፤ እባክሽ› ያሉትም ጉዳይ መፈጸም አለበት።

ራሳቸው ያሰቡትን ከመፈጸም እንደማይመለሱ ሁሉ፤ ከሌላውም እንደዚሁ ይጠብቃሉ።

«እሺ አባ ታጠቅ!» ስትል መለሰች፤ ለምን ይሆን የሚል ሐሳብ ግን እየመጣባት። ምክንያቱም ትናንትናውኑ ገብርዬን ከአልጋ ላይ እንዳሳረፈች፤ ወዲያውኑ ወደ ቤተ መንግሥት ሔዳ ከሁሉም ጋር ተገናኝታ ተመልሳለች። ስለዚህም ተዋበችን የመጠየቅ ብቻ ሊሆን አይችልም። አንዳንድ ጊዜ ግን፤ ቴዎድሮስም ቢሆኑ ሊያይዋት ሲፈልጉ ያለ ምክንያት የሚያስጠሩዋት ጊዜ አለ።

በአንዳች ዐይነት ሐሳብ ፊት ፊቷን አይተው፤ ደኅንነቷን ደግመው ደጋግመው ጠይቀው ያሰናብቷታል። ከእርሳቸው ጋር ያላት ግንኙነት ይበልጥ የሚያሠቅቃትና ግራ የሚያጋባት በእንደዚህ ያለ ጊዜ ነው። እንደሚወዱዋት፤ እንደሚያስቡላት፤ በጣም ይሰማታል። ‹ነገ ሲደርስ ለማየው አሁን ምን አሳሰበኝ› ስትል ለጊዜው ከአእምሮዋ ፋቀችው።

ታንጉት፤ ቴዎድሮስን እስከ ግቢው በር ሸኝታ ስትመለስ ሣቋን ለቀቀችው። ወይዘሮ ደብሬ ቴዎድሮስን እጅ ነሥተው ከተሰናበቱበት እንደቆሙ ነበሩ።

«ኧረ ባባጃሌው! መንነካሽ ልጄ!» አሉ እንደቀድሞው የቀልድና የዋዛ መልክ ሳይታባቸው እንደተኮሳተሩ።

«እርስዎ ነዎታ እማማ ደብሬ!» ታንጉት ሣቋን መግታት አቃታት።

«ኧረ ባባጃሌው! ምን ሆንኩ እኔ?»

«ዛሬ ምነው እንደዚህ ዝግት አደረገዎት። አይተህልኛል ገብርዬ? ተዚያ ተበሩ ጥግ የተደግፈው ነው እኮ የዋሉት። እጃቸውን አጣፍተው።»

«ዛዲያ ምን ላድርግ?»

«አይናገሩም? አይንቀሳቀሱም?»

«ኧረ ባባጃሌው! ልቅለብለብ ነው የምትይኝ?»

«እንደ ወትሮው ማለቴ ነው!»

«አይ! ቦታ ቦታ አለው። ተማንም ጋር አፌን የተካፈትኩ እንደሆነ ተትልቅ ሰው ጋር እንደዚያ መሆን አለብኝ? ቴዎድሮስ ትልቅ ሐሳብ ያለው ትልቅ ሰው ነው። አክብሮት አደርግለታለሁ። አይገባም ፈታውራሪ?» ሲሉ ገብርዬን ጠየቁት።

በከፍተኛ አድናቆት እየተመለከታቸው ራሱን ብቻ በአወንታ አወዛወዘ። እንደ ታንጉት እየማረኩት ሔደዋል።

«በሉ እናንተም ዕረፉ እንጂ! ኧረ ባባጃሌው! ወይስ አልተነፋፈ.ቃችሁም ልበል?» አሉ ወይዘሮ ደብሬ ተሰናብተዋቸው ሲወጡ፤ ፊታቸው በተለመደ ፈገግታቸው ፈክቶ። የሁለቱ ሣቅ ተከተላቸው።

ታንጉት፤ ከተዋበች ጋር ስለ ሸዋው ዘመቻ፤ ስለ ጎንደሩ ኑሮ በሁለቱም በኩል ያጋጠማቸውን ነገር፤ ሌላ ሌላውንም በቀላሉ እንደዋዛ ሲጨዋወቱ ቆይተው፤ ያሁኑ ቴዎድሮስ የዚያን ጊዜው ካሣ፤ ከተዋበች ጋር ሲያገናኝዋት ‹ተኔ ቀጥላ እናትሽም፤

እኅትሽም ናት፤ እታልም በያት፣ ካሏት ጀምሮ በምትጠራት፤ «እታለም ልሒድ እንግዲህ» ብላ ስትነሣ ተዋበች፤ «ታጠቅም ሊያይሽ ይፈልጋል መሰለኝ፤ ግን ተልፍኝ አይደለም። ታዲሱ ቤት ነው» አሏት።

ቴዎድሮስ፤ በጎንደር ቤተ መንግሥት ውስጥ ካመጡት አዲስ ነገር ለራሳቸው የተለየ የሥራ ክፍል መመደባቸው ነበር።

ከእርሳቸው በፊት የነበሩት መሳፍንት፤ ከእነዚያም በፊት የነበሩት ነገሥታት በአደባባይ ችሎት ይቀመጣሉ። በሰፊ አዳራሽ ይሾማሉ ይሽራሉ፤ ግብር ያበላሉ፤ ጥብቅ ምሥጢር የሌለበት ጉዳይ በዚሁ አዳራሽ ይመክራሉ። ያከናውናሉ። ራሳቸውን ወይም የቅርብ ታማኞች ባለሟሎቻቸውን ብቻ የሚመለከተው ምሥጢር ቀመስ ውሳኔና፤ ወይም በዘመነ መሳፍንት ሳያቋርጥ እንደተደረገው ሁሉ፤ ሤራውና ሌላውም ተግባር በእልፍኝ ውስጥ ይካሔዳል። ቀላጤ ወይም ደብዳቤ የሚያስፈልገው ጉዳይ ሲሆን፤ ጸሐፌ ትእዛዙ በቃል የተቀብለውን ትእዛዝ በራሱ ክፍል ወይም ጽሕፈት ቤት ውስጥ አዘጋጅቶ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤ ቴዎድሮስ ግን ከዚህ በተጨማሪ የራሳቸው የሥራ ክፍል እንዲደራጅ አደረጉ።

ሐሳቡን ያገኙት በኋላ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ከተባለው ከጆን ቤል ነበር። ጆን ቤል፤ የቴዎድሮስን ትልቅ ሐሳብ፤ የቴዎድሮስን ትልቅ ዓላማ ከተረዱት ጥቂት ሰዎች አንዱ ነው። እንዲያውም ከሠለጠነው አውሮፓ ከመምጣቱ ጋር በቅን አስተሳሰቡ ከሁሉም ተረድቶላቸዋል። ከደጃች ውቤ ዘንድ ረዘም ላለ ጊዜ የጌታ አድሮ፤ ደጃች ውቤ ሲሸነፉ ማርከው ካሰሩት ቴዎድሮስ ጋር በመተሳሰብ ፍቅር ያቀራረበውም ይኸው ነበር።

ስለ ሥልጣኔ፤ ስለ ዕውቀት፤ ስለ አስተዳደር፤ በተለይም አንድ ሕዝብን ሀብታምና ኃያል ስለሚያደርጉ የሙያ ሥራ በሰፊው ሲያስረዳቸው በመመሰጥ እንደሚከታተሉ ሁሉ፤ በበኩሉ ሥራቸው እንዲቃና ብዙ መንገደ ሲፈልግ፤ የሠለጠኑ አገሮች መሪዎች ከተለመደው አንድ አዳራሽ፤ ችሎት፤ ከመሳሰለው ይፋ የሥርዓት ባሕል መድረክ ሌላ፤ የዕለት ሥራቸውን በጥሞና የሚያከናውኑበት ልዩ ክፍል እንዳላቸው አንድ ቀን ነገራቸው። ቴዎድሮስ የአዳራሹ ጋጋታ፤ እርሳቸው እንደሚሉት የቅምጥል ጫጉላ የመሰለው እልፍኝ ሽብርቃት አስጠልቷቸው ነበርና ሐሳቡ ወዲያው ማረካቸው። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ አስተያየት እየሰጠ፤ ከሚስዮኖችና በጊዜው ከነበሩት ከውጭ አገር ሰዎች ችሎታ ያላቸው፤ የሚያስፈልገውን ዕቃ ሥራ አጣድፈውት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሰናዳ። ከዚህ በኋላ ቴዎድሮስ ከችሎት ሲነሡ ወይም በእልፍኝ የሚቀበሉት እንግዳ ከሌላቸው፤ የሥራ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ወይም ብቻቸውን፤ ወይ ከሊቀ መኳስ ዮሐንስ ጋር ዐልፎ ዐልፎም ከቅርብ

ባለሚሎቻቸው ጋር በዚህ ክፍል ነበር። ገብርዬ ስለዚህ የቴዎድሮስ አዲስ ጓዳ ብዙ ጊዜ ነግሮዋታል። ራስዋ ግን ካሁን ቀደም አላየችውም ነበር።

በመቃብር ሥፍራ እንደማሠረግ ሁሉ በሠርግ ዳስ ውስጥ እንደማይለቀስ ሁሉ፤ ከለመደችው ከአዳራሹና ከእልፍኝ ውጭ ለመጀመሪያ ጊዜ ቴዎድሮስ በዚህ አዲስ ክፍል ለምን እንደጠብቋት ታንጉት ግራ ገብቷት፤ ‹ለጥሩ ነው ለመጥፎ?› እያለ ልብዋ በፈራ ተባ ዳንኪራ መታባት። ሳንቃውን ፈርቀቅ ስታደርግ «ማነው?» አሉና ቀና ብለው በመመልከት፤ «አንጓች አንቺ ነሽ? ግቢ? አሏት።

«ቁጭ በይ አንጓች!» አሏት። ተቀምጣም ዐይንዋ በመገረም ዙሪያውን ሲንከራተት አይተው፤ «ምነው አንጓች?» ሲሉ ጠየቋት። ስሜቷ ግን ገብቷቸዋል።

ወዲያው ነገራቸውን ለወጥ አደረጉና፤ «ለመሆኑ አንቺ ደኅና ነሽ፤ ጤንነትሽ?» ሲሉ ጠይቋት።

«በጣም ደኅና ነኝ።»

«ሐሳም የለብሽም?»

«ምን ሐሳብ አለብኝ አባ ታጠቅ?»

«ምናውቃለሁ ብለሽኝ? የሰው ሐሳብ ብዙ ነው። እኔ እንደሆነ እንግዲህ፤ ባራቱ ማዕዘን ሳስብ ብዙ አላጫውትሽ፤ አላዋይሽ! እንዲያው ድንገት ብዬ ነዋ!» ራሳቸው ጥቂት ያሰቡ መሰሉና «ገብርዬም አያስከፋሽም?» ሲሉ ጠየቋት።

«ኧረ ጭራሽ! የእግዚአብሔርን ሰው!» አለች ታንጉት ደመቅ ባለ አነጋገር ከገብርዬ ጋር የትናንቱ ሁናቴያቸው ታውሷት።

«እንደማያስከፋሽ አውቃለሁ። እንዲያው ለነገሩ ብዬ ነው እንጂ። እንደምወድሽ ታውቂያለሽ? አዎ ባልወልድሽም ልጅጄ ነሽ።

ታንጉት የምትመልሰው ጠፍቷት ዝም አለች።

«አዎ! ታንቺና ተተዋበች የሚቀርበኝ የለም።»

«ለምን ነገሩን ለየትህ፤ ግልጽ አርገህ አትናገርም?» የሚል ሐሳብ ታንጉት ድንገት መጣባትና የአፍቅሮት ፊታቸውን ስታይ ወዲያው ከአእምሮዋ ተሰረዘ።

«እና ጎንደር፤ ሲያወራብም ሲያሚርትብ፤ ሲሸርብብኝ፤ ከርሚል ማለትን እሰማለሁ። ለምን አልነገርሽኝም አንጓች? ወይስ አልሰማሽም?» ትዝብትም፤ ግሣጼም ሳይሆን የመማጠን ዐይነት ነበር።

«ምኑን ልንገርህ አባ ታጠቅ? ወሬ ብቻ እኮ ነው!» አለች ታንጉት አነጋገርዋ የጭንቀት ሪ ነበረበት።

«ተወሬ ተሤራ እኮ ነው ሁሉም ነገር የሚጀምረው። አታውቂም? ‹ዘመቻ ተፈታው ወሬ የፈታው› ሲባል አልሰማሽም? ተዚያ ደሞ ሌላው ይመጣል። ያለፈው ዐልፏል። አሁን የወደፊቱን ልለምንሽ እሺ ትይኛለሽ?»

«እህ! ላንተ እምቢ የምልህ ነገር አለ?» ታንጉት ሳይታወቃት በመጨነቅ ተወራጨች። የተናገረችው ከልብዋ ነበር። ቴዎድሮስ በፍቅሩም፣ በፍቃዱም በቁጣውም ስቦ የሚይዝ አንዳች የተፈጥሮ ኃይል እንዳለው አብራ በኖረችበት ሁሉ ተሰምቷታል። ይህንን ኃይልም ኑራዋለች። ገና ልጅ ሆና ከፉኛ በቀጣት ጊዜ ስንኳ እንዳቀላመጣትና በስጦታ እንዳባበላት ያህል ጥምጥም ትልበት ነበር፤ እንደዛሬው ሌላው ሌላው ሐሳብ ሳይመጣባት።

«አዎ ዐውቃለሁ። አንቺም ታውቅሽኝ እምቢ እንደማይትይኝ ዐውቃለሁ፤ እሺ እንግዲያው ዐይንሽንም፣ ጆሮሽንም ነቃ አድርገሽ የምታይውን፣ የምትሰሚውን እንዲይው አርቲ ቡርቲውን ሳይሆን እህ? የምትይውን ባውቀው መልካም ነው። አሁን እኛ ዘመቻ ሔደን ሲወራ ሲዶለት እንደከረመው ዐይነት።፡፡»

ታንጉት የነገሩን ዳርዳርታ በመጠኑ ገባት። ነገር ግን ያልገመተችው አዲስ ነገር ስለሆነባት በትክክል ለማረጋገጥ ዝም ብላ ጠበቀች።

«ቀፈፈሽ? አስጠላሽ አይደል አንጓች?» በቅሬታ መኮስተር ትክ ብለው ተመለከቷት። «ነገሩ መሰለል ነው። አዎ በመሳፍንቱ ዘመን አንዱ መስፍን በሌላው ላይ ሲያሤርና ሲዶልት፣ እገሌ የእገሌ ሰላይ ነው ሲባል ከሚጠላት ዐልፎ ምን ልበልሽ ተሰውነት ወጥቶ ተውሻ፣ ተልክስክስ ውሻ መባስ ነው። ግን ደሞ አንድ ሰው አዝመራውን ይሰልላል፣ ደኅና አምሮለት እንደሆነ። ከብቱንም ይሰልልላ፣ አውሬ ወይም ሌባ እንዳይነጥቅበት። እርሱ ክፉ ሳይስብ በክፉ የሚነሣበትን ጠላት ሁናቴም ይሰልላ። ዛዲያ ይኸ ሁላ ምን መጥፎ ነገር አለበት? ለበጎ ነዋ ሐሳቡ። ዛዲያ አገራችን አዝመራችንን አይደለችም? ናት እንጂ! አብቅላ፣ አፍርታ የምትመግበን። ዛዲያ፤ ጠላት፣ አውሬ ጠላት አድክሟት ኖረ። አሁን ደግሞ እኛ እንደገና እንደ ጥንቷ ሀብታም ጠንካራ እንድትሆን ስንፈልግ፣ ቱርኮችም፣ ፈረንጆችም ሊያደክሟት፣ አድክመውም ጨርሰው ሊወስዷት ውስጥ ውስጡን እየሰለሉ የሚሠሩትን ይሠራሉ። ይኸ ተንኮል ያልገባው የእኛ ሰውም ተነሱ ጋር አብሮ ለማፍረስ ይቆፍራታል። ሌላው ደግሞ፣ ይኸ የዘመነ መሳፍንት ጨምላቃ ኑሮውን እንደ ትልቅ ነገር ቆጥሮት ያ ለምን ተነካብኝ ብሎ በዚህም በዚያም ይዶልታል። ዛዲያ፤ ይህ እንዳይደርስ፣ ተዚህም ዐልፎ በጠላቶቿ ላይ መሰለል ምን

ክፋት አለበት? በጎ ነገር ነው እንጂ! የጽድቅ ሥራ ነው እንጂ! ተሆነልኝ፤ እኔ ላገሬ ታገር አገር፤ ታጥናፍ አጥናፍ እየተንከራተትኩ እሰልላት ነበር። ለኔው ለራሴማ ምን ፈልጌ! የምበላው አንድ እንጀራ የምለብሰው አንድ ጨርቅ! ለኔስ ላንቺስ፤ ለተዋበችስ ባባታችን አገር አርሼ፤ አድኜ ሳንጎርስ ሳንበላ፤ ሳንለብስ ማደር ያቅተናል? እንዲያውም ሐሳብ የሌለበት የሰላም እንቅልፍ እየተኛን! መቀለብ፤ በምቾት መድለብ ቢያምረኝ ኖሮስ የአማቼ የራስ አሊ አዳራሽ ተከፍቶልኝ አልነበረም? ያገርሽ፤ ያገሬ ዕዳ ሆኖብኝ ነው እንጂ! ሰው ላገሩ.....»

ታንጉት፤ የቴዎድሮስ የዓላማ ሸክም ተጫናት። ወይዘሮ ደብሬ እያዘሩ ባሳይዋት የጥንታዊት የኢትዮጵያ ፍርስራሽ ሕልማቸው እንደገና ተደቀነባት። «እሺ አባ ታጠቅ! ምን አርጊ ነው የምትለኝ? እሺ አልኩህ ንገረኝ!» አለች የሚታያት ሕልማቸውን መሸከም ያቃታት ይመስል ንግግራቸውን እያቋረጠቻቸው።

ቴዎድሮስ፤ ከአስጨናቂ የሕልም ዓለም ተጉዘው ድንገት እንደተመለሱ ያህል በሰፊው ተነፈሱ። «እንዳልኩሽ ዓላማዬን ለማጨናገፍ ብዙ ሰዎች እየዶለቱ መሆናቸውን ሰምቻለሁ። በተለይም ካህን ነን ባይ ጠምጣሚዎች። ለመሆኑ ብዙ ሰው ዐውቀሻል ጎንደር?» ሲሉ በመካከሉ ጠየቋት።

«ኧረ እቴ! አንድ ጥሩ ወዳጅ ብቻ አፍርቻለሁ። ወይዘሮ ደብሬ የሚባሉ።» ቴዎድሮስ ጥቂት እንደ ማሰብ አሉና ራሳቸውን ነቀነቁ። «አናውቃትም።»

«ኧረ ድፍን ጎንደር ያውቃቸዋል።»

«ኸኸ!» አሉ ቴዎድሮስ በማስታወስ ነቃ ብለው። «ይች የደጃች ተድላ የነበረችው?»

«ኧረ በዕድሜ ጠና ያሉ ትልቅ ሴትዮ ናቸው!» አለች ታንጉት ‹አንቺ› በመባላቸው የተዋረዱባት ይመስል።

«ጎንደር ሳለሁ ይወራላት እሰማ ነበር እንጂ እኔ የት ዐውቃት ብለሽ! ግን ምን አጋጠማችሁ ልጄ?» አሉ ቴዎድሮስ እንደ ዋዛ።

ታንጉት ግን፤ ነገሩ እንደ መርፌ ጠቅ አደረጋት። ‹እሱም እንደሌሎቹ በነገር መንካቱ ነው?› አለች በሆድዋ። የቴዎድሮስ አስተያየት ግን አንዳችም የአሽሙር ምልክት አልነበረበትም።

«አንዱ ዋና የዱለታው ጎንጓኝ እኒያ ግብጻዊ የቱርክ አሽከር ናቸው ይባላል» አሉ ቴዎድሮስ ወደ ጉዳያቸው ተመልሰው። ታንጉት በጥየቃ ዐይነት ትኩር ብላ ተመለከተታቸው። «አዎ! አቡን ተብየው!» ሲሉ መለሱላት። «ተዋውቀሻቸዋል?»

«አንድ ጊዜ ቤታችን መጥተዋል። ቤተ ክስያንም ዐልፎ ዐልፎ መስቀል ያሳልሙኛል።

«እስቲ እሳቸውንም ቀረብ በያቸው። እና፤ ለሁሉም የሚሆነውን እያደማመጥሽ ንገሪኝ።»

ጉዳያቸው ያለቀ መስሏት ታንጉት ለመሔድ ስትነሣ፤ «ኧኸ! ልረሳው ነበር» አሉ ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት እየተነሡ። ከዚያም ከአንድ ጥግ ዝተት የሚለብሱት። ባና ይመስሉታል። ገብርዬ ብቻሽን ጥሎሽ በዘመቻ ሲንከራተት ይሞቅሻል!» በቀልድ ሣቅ ፈገግ አሉ።

ታንጉት፤ በተሰጣት አዲስ ተግባር ብዙ ሳትጨነቅ፤ ከአቡኑ ጋር እንዴት እንደምትቀራረብ እያሰላሰለች ወደ ቤቷ ተመለሰች።

ጋረድ፤ ከጎንደር አደባባይ ተሰውሮ ሰንብቶ፤ ገብርዬን ሊጠይቀው የመጣው ቴዎድሮስ እንደገና ወደ ወሎ ዘመቻ ከሔዱ በኋላ ነበር። አሁንም የመጣው ከደብተራ አክሊሉ ጋር ነው።

«ይህንን ያህል ምን አስቸገረህ ልጅ አረድ?» አለው ገብርዬ ከምስጋናው ጋር በመገረም። በእርግጥም በጣም ገርሞት ነበር። በደርቡ በር በኩል እንዳያቸው፤ ጋረድ አንዲት ምን የመሰለች ሽህር፤ አንድ ዐሥር የሚሆኑ በጎች አስከትሏል። «ግቢውስ እይት ይበቃል!» አለ በቀልድ መልክ።

«እህ! እንደ ካሣም ባልሆን ይኸ ይብዛብኝ?» ሲል ጋረድ እንደዋዛ መለሰ። የማወዳደሩ አሽሙር ገብርዬ ቢገባውም ሊጠይቅ የመጣን ሰው ማስከፋት ነውር ስለመሰለው ቅሬታውን አላሳየም። ወዲያው ሌላ ሌላው ጭውውት ቀጠለና ረሳው።

ታንጉት፤ በበኩልዋ በጋረድ ላይ ከፊተኛው የተለየ ሁናቴ ያየችበት መሰላት። ጉራው ተቅንሷል። የንቀት አመለካከቱ መለስ ብሏል። ከመጠጡም ተቆጥቧል። ‹ያን ለት ሞቅ ስላለው ነው ወይስ ዐይኔ ነበር!› አለች በሆድዋ።

ከዚህ ቀን ጀምሮ አዘውትረው መምጣት ያዙ። ሲመጡም፤ ሲሔዱም ሁለቱ ተለያይተው አያውቁም። ታንጉትን የሚያስገርማት ይህ ነበር። ‹ምን ዐይነት ፍርቅ ነው?› ትላለች ለራስዋ። አንዳንድ ጊዜም ከእርስዋና ከወይዘሮ ደብሬ ወዳጅነት ጋር ታመሳስለዋለች።

ገብርዬ መጀመሪያ ላይ፤ ‹ተመቸ ወዲህ ነው?› የሚል ጥርጣሬ ቢያድርበትም እያደር ጉብኝታቸውን እየለመደው ሔደ። የቅርብ ጓደኞቹ ሁሉ ዘምተው፤ ሌላው

ጠያቂም እየቀዘቀዘ ሔዶ ስለነበር፤ እየመጡ ማጫወታቸውን አልጠላውም። እንደ ማንኛውም መቀራረብ፤ ገበጣ እየተጫወቱ ከአደንና ከዘመቻ እስከ ዋዛ ፈዛዛ እያወጉ ብዙ ጊዜ አብረው ሲያሳልፉ፤ መተራረብ መቀላለድና ከሚሸት የሚደበቅ የፍቅር ምሥጢር መለዋወጥ ጀመሩ። ይበልጥ እየተላመዱ ሔዱ።

ነገሩ የከነከናቸው ወይዘሮ ደብሬ ነበሩ። «እኔ አላማረኝም» አሏት አንድ ቀን ታንጉትን ለብቻ። ጋረድና አክሊሉ ጧት ገደማ እየመጡ ሲጫወቱ ውለው መሔዳቸውን ነበር።

«ምኑ?» ስትል ጠየቀቻቸው።

«እግር አበዙብም እነዚህ ሰዎች። ኤዲያ፤ ዝምድናም ተሁነኛ ሰው ጋር ሲሆን ነው» አሉ ወይዘሮ ደብሬ አነጋገራቸውን ፍርጥም አድርገው።

«ወይ እማማ ደብሬ! አለ ሰው ክፉ ሲናገሩ ዛሬ ገና ሰማሁዎት!!»

«እኔ ምን ክፉ አናገረኝ። እንዲያው ውቃቢዬም እንደሆነ እያዘወተሩ መምጣታቸው ቢያስገርመኝ ነው እንጂ!»

«ጋረድም እንደሆነ የአባ ታጠቅ ወንድም ማለት ነው። ዛዲያ ተወንድሙ የጦር አለቃ ጋር ወዳጅነት ቢፈልግ ምን አለበት!»

«ያስገረመኝስ እሱ አይደለ? ደግሞ ጋረድ የደጃች ክንፉ ልጅ ቢሆን በአባቱ አልወጣ! ቴዎድሮስንም እንደ ወንድሙ አያየው!»

«ኧረ እንደዚህ አያስቡ!» አለች ታንጉት ነገራቸውን በማጣጣል።

«አንቺን ተመሰለሽማ» አሉና ወይዘሮ ደብሬም ነገሩን ችላ አደረጉት። ከእርሳቸው ሌላ ወዳጅ በማፍራታቸው ምቀኝነት እንዳይመስልባቸው።

ታንጉት፤ በበኩልዋ የእነልጅ ጋረድ ዝምድና ከልብ ባያስጨንቃትም ጉብኝታቸውን የምትፈልግበት ሌላ ምክንያት ነበራት።

ገብርዬ ከወትሮውም ልጅ በጣም ይወዳል። ከመንገድ ላይ ልጅ ካጋጠመው ይወቀውም አይወቀውም ዝም ብሎ አያልፍም። እንደ ቤተ ክርስቲያን ጎንበስ ብሎ ግንባሩን ይስመዋል። ወይም ደግሞ ብድግ አድርጎ በማቀፍ፤ ‹ስምህ ማነው? የማን ልጅ ነህ? ጎበዝ ነህ ፈሪ?› እያለ ላንዳፍታ ያጫውተዋል። ዘመቻ ወይም አደን ሔዶ ሥራዬ ብሎ ለመንደር ልጆች የዱር ፍሬ በጨርቅ ቋጥሮ የሚመጣው ብዙ ጊዜ ነበር። ልጆችም የሚወዱት የዚያኑ ያህል ነበር። ታንጉት እንደምታውቀው ጎንደር እስከ መጡ ድረስ በየቆዩበት የሠፈር ልጆች ከወላጆቻቸው ቀጥሎ የሚቀርቡትና

የሚያቀርባቸው ገብርዬ ነበር። እንደ ዕድል ሆኖ፤ እርሷም እንደ ተዋበች እስከ አሁን ልጆች አልወለደችም። ልጅ የሚያፈቅሩትና የሚያፈራቸው ገብርዬና ቴዎድሮስም የሚያጫውቱት የራሳቸው ልጅ አላገኙም። እርሷና ገብርዬ ከተጋቡ ሰባት ዓመት ዐልፏቸዋል።

ምናልባት ጊዜው እየገፋ ሲሔድ፤ ያለመውለድዋ ሐሳብ አመለካከቷን አጉልቶባት ሊሆን ይችላል። ገብርዬ ከሸዋ ዘመቻ ከተመለሰ ወዲህ ደግሞ ስለ ልጅ ያለው ስሜት ከበፊቱ እጅግ የበረታ እየሆነ ታያት፤ ተሰማት የሚያነጋግረው ወንድ እንግዳ ከሌለ ድንክ አልጋውን ከድርቡ በር ደረጃ ላይ እንዲያወጡለት ያስደርግና በአቅራቢያው የሚዘዋወሩትን ወይም የሚጫወቱትን ልጆች በተመስጦ ያስተውላል። ከእንቅስቃሴያቸው ጋር ዐይኑ ይንከራተታል። አመለካከቱ የፍቅር ብቻ ሳይሆን የስስት ዐይነት ጭምር ነው። የሐሳብ እጁን ዘርግቶ የሚያቅፋቸው የሚደባብሳቸው ይመስላል። በፊቱ ላይም አንዳች ትካዜ ጥላ ይደረብበታል። ታንጉት ፍላጎቱ እየገባት ስሜቱ እየተሰማት፤ ትሠቀቃለች። ትጨነቃለች። እያደርም ሰቀቀን እየሆነባት ሔደ። እነጋረድ እየመጡ ገብርዬን ማጫወታቸውን የወደደችውም፤ የውስጥ ሐሳቡም ባይሆን፤ ዐይኑ ከልጆች ጋር መንከራተቱን በመጠኑ ይቀንስለታል በማለት ነበር። በዚያውም የእርሷንም ሠቀቀን።

በኋላም ‹እሾህ በእሾህ› እንዲሉ ቴዎድሮስ ለሰጣት ሥራ፤ አክሊሉ ከአቡነ ሰላማ ጋር የበለጠ አቀራርቧት፤ እህል ውሃ እየያዘች መንበራቸው ዘንድ ብዙ ጊዜ በመሔድ፤ እምብዛም የተጨበጠ ነገር አላገኘችም እንጂ ታንጉት አንዳንድ ነገሮች ለመታዘብ ችላለች። ብዙ ካህናት በአቡኑ አዳራሽ እየተሰበሰቡ ሲወያዩ ሲከራከሩ ይውላሉ። ታንጉት ብዙው ነገራቸው አይገባትም። ስለ ምሥጢረ ሥላሴ፤ ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ፤ ስለ ክርስቶስ ባሕርይ ነው። በመካከሉም አዲሱ የቴዎድሮስ ውሳኔ በሀገሪቱ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ስለ አስከተለው ጉዳት ይነሣና የብዙው ካህናት ስሜት በንዴት ይግላል። ‹እኮ አባታችን፤ ቤተ ክርስቲያን ጨርሳ እስክትዘጋ ዝም ብለን አንይ?› እስከ ማለት የሚደርሱ ነበሩ። የገብርዬ ሚስት መሆንዋን የሚያውቁ ቢኖሩም፤ በነገራቸው የሚፈሩባት አይመስሉም። ‹አሁን ተፊቱ እንደዚህ ደፈረው ይናገሩ ይሆን?› የሚል ሐሳብ ይመጣበታል፤ ታንጉት። አክሊሉ የሎዛ ማርያም አለቃ ብቻ ቢሆንም፤ በካህናቱ ዘንድ ከፍተኛ ተሰሚነት ያለው ይመስላል። ግን፤ የቴዎድሮስን ውሳኔ በግልጽ ተቃውሞ ሲናገር ሰምታው አታውቅም። ነገሩን እንደዋዛ አንሥቶ ለሌሎቹ ይተወዋል።

ባልንጀርነታቸው በጣም የሠመረ በመሰለበት፤ ገብርዬ ተሽሎት በምርኩዝ በግቢው ውስጥ መረማመድ በጀመረበት ወቅ፤ እነጋረድ ድንገት መምጣታቸውን

አቆሙ፤ ብዙ ቀናት ዐለፉ፤ ሳምንት ሞላ። ገብርዬ በመቅረታቸው ቅር የተሰኘ ወይም የተገረመ ሳይመስል፤ ከግቢው ወጣ እያለ ከመንደሩ ልጆች ጋር በመጫወት ጊዜውን ያሳልፍ ጀመር። እንዲያውም አንድ ሐሳብ የወረደለት መሰለ። ታንጉት ግን ከነከናት። ከልጆች ጋር የሚያሳልፈው ጊዜም ሠቀቀንዋን እንደገና እየቀሰቀሰባት ሔደ። ሁለተኛው ሳምንት እንደ ተገባደደ፤ አልስችል አላትና ጠየቀችው። «ምን ሁነው ነው ኧረ የጠፉት?»

«ወረታቸው ቢያልቅ ነዋ!» ሲል በማቃለል መለሰላት።

«አንድ ነገር ቢሆኑ ነው?»

«ቢሆኑ እንሰማ ነበር።»

»ተቀያማችኋል?»

«ምን አቀያየመን?»

«ማለቴ አንድ ነገር ተናግረውህ፤ ወይም ተናግረሃቸው እንደሆነ ብዬ ነዋ!»

«አንቺ ምን አስጨነቀሽ?»

«ባይጨንቀኝም መቸስ ይከነክናል!»

ደግማ ደጋግማ ካነሣችበትና ‹እኔ እነሱንም ቢሆን አጠይቃቸዋለሁ እንጂ!....› ካለችው በኋላ ነበር ምክንያቱን የነገራት።

የምሳ ገበታ ተነሥቶ ሁለቱ ብቻቸውን ቡና እየጠጡ ነበር። «እይው እንግዲህ፤ የነሱ ነገር ተሆድሽ አልጠፋ ታለ» ሲል ጀመረና የሆነውን በአጭሩ ተረከላት። አንዳች ምሥጢር የሚፈልግበት ይመስል፤ የጠጣበትን ፍንጃል ከእጁ ላይ እያገላበጠ፤ አእምሮው ግን ዝርዝር ሁናቴውን እንደገና እንደ ፈትል ያጠነጥን ነበር።

ገብርዬ ምርኩዝ ይዞ ትንሽ መንቀሳቀስ እንደ ጀመረ አንድ ቀን ምሽት፤ ሦስቱ ወደ ጓሮ ወጥተው ራት እስኪደርስ ከየድንጋይ ላይ ዐረፍ ብለው ነበር። ሙሉ ጨረቃ ወጥታለች፤ የሚበርድ ሳይሆን ቀለልና ቀዝቀዝ ያለ አየር ይነፍሳል፤ እንቁራሪቶቹ ቋ! ቋ! ቋ! ይላሉ። ዐልፎ ዐልፎ የሰዎች ጥሪና የከብቶች ጩኸት ይሰማል። ከማዶ በቁስቋምና በአባ እንጦንዮስ፤ እሳት ብልጭ ብልጭ ሲል ይታያል። ጎንደር ከተማ ከናካቴው ችር ባትልም የሚያስደስት ጸጥታ ሰፍኖባታል። የዜማ ተማሪ ቀስ ብሎ ድምፁን የሚያሽበት፤ ከብቶቹን ያስገባ እረኛ ዋሽንት

የሚጫወትበት፤ ጎልማሳ ለእጮኛው ወይም ለወዳጁ የፍቅር ዜማ የሚያንጎራጉርበት ምሽት ዐይነት ነበር።

በአካባቢው ላይ የሰፈነው ጸጥታ፤ ከእነርሱም መንፈስ ውስጥ የሠረጸ ይመስል ሦስቱም ጭውውቱን ትተው፤ በየራሳቸው ሐሳብ ተውጠው ዝም ብለው ቆዩ። ገብርዬ የሚያስበው፤ ድንገት ባላሰበው ሁናቴ መቁሰሉ፤ ‹ለካንስ ድንገት መሞትም አለ ለካ?› የሚል ሥጋት ከአሳደረበት ወዲህ ዐልፎ ዐልፎ በአእምሮው የሚመጣበትን ጉዳይ ነበር። ልጅ አለመውለዱ። ከታንጉት ጋር እስከዛሬ ሁለት ሦስት ልጅ የሚያደርሱበት ጊዜ ነበር። ግን የአንዱም እርግዝና አልሞከራትም። ‹እኔ ነኝ መኻን እርሷ?› ሲል በሐሳቡ ይጠቅና በታንጉት እንዳያመካኝ ከጋብቻው በፊትም ሆነ በኋላ ዐልፎ ዐልፎ ከሔደባቸው ሴቶች የልጅ ወይም የርግዝና ነገር ካላጋጠመው የወንድ ልጅን መኻንነት ማመን እያዳገተው ግራ ይገባዋል። ዛዲያ መቸም ሰው ቁሞ አይኖርምና ስሙ የሚጠራበት፤ ዘር ሳያስተርፍ ሊያልፍ ነው? ጉዳዩን ከታንጉት ጋር አንሥቶት ባያውቅም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየከነከነህ አስቸግሮታል።

«በእንደዚህ ያለ ጊዜ ወንድ ልጅ ይሸፍታል!» አለ አክሊሉ እንደመጣላቸው በድንገት የሚናገሩትን በመስማት የሚያስቡትን ለማወቅ።

«የሴት ልጅ ደምጎ ተኝቶ ያንኮራፋል» ሲል ጋረድ ለጠቅ አደረገ።

«ስለ ሽፈታና ስለ ሕልም ስትናገሩ የትናንት ሌሊቱ ሕልሜ ትዝ አለኝ» አለ ገብርዬ ድንገት ከቅንቅልፉ እንድ ባነነ ሰው።

«አንተም ታልማለህ?»

«እኔ ምንድነኛ?» ጥያቄው አድናቆት ይሁን አሽሙር ስላልገባው ገብርዬ ግንባሩ ቋጠርጠር አደረገ።

«አየህ ሰው በእንቅልፉ ሕልም የሚያልምበት፤ በውኑ ብዙ የሚጨነቅ፤ የሚደነግጥ፤ ብዙ ሐሳብ የሚይዘውና በሕይወቱ ብዙ የሚመኝ ሲሆን ነው ይባላል» አለ አክሊሉ አለሳልሶ።

ገብርዬ፤ አንተም የነገሩ ትርጓሜ በትክክል አልገባውም። «ዛዲያስ?»

«ዛዲያማ አንተ የምትመስለኝ ሞት እንኳን ዐይኑን አፍጦ ቢመጣብህ ፍንክች የማትል፤ ለማንም የማትበገር ቆራጥ! በዚህ ላይ የቴዎድሮስ ጦር አዛዥ ሆነህ የምትመኘውን አግኝተህ ተሆነ፤ ምን ሕልም ይታይሃል ብዬ ነዋ!»

«አቤት - አቤት! ‹ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሉዋት› አሉ። አንተምኮ በውዳሴ ነገርህ አንገቴን ገዘገዝከው። ተዚህ ሁላ፤ ጉባኤ ቃና ነው ዘ - ሥላሴ የምትሉት

ቅኔ ብትዘፍልኝ አይሻልም» አለና ገብርዬ በነገሩ ከት ከት ብሎ ሣቀ። ግን በቆራጥነት መወደሱን አልጠላውም።

«ሙት - ሙት! ጻድቁን እልሃለሁ እውነት ነው።»

«ዛዲያ ሕልሙን ንገረና!»

«አታልምም ብለኸኝ።»

«ታለምክስ?»

«ተውኩታ!»

«ሕልምህን ለመንገር ፈራሃ!»

«ምን አስፈራኝ።»

«ዛዲያ ንገረና!»

«ግም ሕልምኮ ነው» አለ ገብርዬ በማጥላላት ትከሻውን ነቅነቅ እያደረገ።

«ሕልም ‹እንደ ፈቺው ነው› ተብሏል። መጥፎም ደግ የለውም» አለ ጋረድ።

«አይ - እንደሱ አትበል። እንደ ገሃዱ የሚቆጠር እውነተኛ ራዕይ ደሞ አለ» ሲል አክሊሉ አረመው።

‹እሺ ሕልምም ሆነ ራዕይ ለሁሉም እንስማው› በማለት ገብርዬን በውትወታ አስጨነቁት።

ገብርዬ ነገሩን በማንሣቱ ትንሽ ጸጸተው። «የሸፈትን ይመስለኛል» አለ ነገሩን ያቀለለ በመምሰል ትከሻውን ሰበቅ አድርጎ።

«እነማን?» ሲል ጋረድ ጠየቀ።

«በማን ላይ?» ሲል አክሊሉ ለጠቀ።

በገብርዬ የታማኝነት ስሜት በሕልም እንኳን መሸፈት ራሱ እንደ ክህደት የሚቆጠር ነበር። ይህንን ክህደት እንደ ደኅና ነገር ለሰው ማውራት ደግሞ ከትዝብት ያለፈ ዓመፅ መስሎ ተሰማው። ሰው በሚጠላው ላይ ይሸፍታል። የተበደለ ሰውም

ቢያምፅ አይፈረድበትም። በሚወዱትና በሚታመኑት ላይ እንዴት ሊደረግ ይታሰባል? ገብርዬ መልስ የሚያገኝበት ይምሰል ቀና ብሎ ሰማዩን ተመለከተ። ጸጥ ያለ፤ የረጋ ነው። ዘለዓለማዊ ሥርዓት መከተል እንደሚገባው ይሰማዋል። በጦር ሜዳ ደረቱን አስጥቶ፤ ልቡን ሰጥቶ የሚዋጋን ያህል አገር ለመበጥበጥ፤ መንደር ለማመስ፤ ለመዝረፍ ወይም ለመፍራትና ለመታወቅ የሚደረግ ሽፍትነትን በጣም ይጠላል፤ ይጠየፋል፤ ቴዎድሮስን ያመነበት በቴዎድሮስ የታመነበት ዋናው ምክንያት ይኸው ነበር። ቴዎድሮስ፤ ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና አዲስ ዐይነት አስተዳደር ባላቸው ከፍተኛ ዓላማ ያገሩ ሥርዓትና ዕድገት አርአያ ሆነው ይታዩታል። ዛዲያ የመሸፈቱን ሕልም ምን አመጣው? እርግጥ ወዲያው የቆሰለ ሰሞን ከትኩሳቱ ጋር ብዙ አቃዥቶት ነበር። የዚህ ዐይነቱ ሕልም ግን ለእንቅልፍ ዓለሙ እንግዳ ነበር። አልመዋለሁ ብሎ የማይገምተው ስለሆነ ሕሊናውን ሡቅቆት ነበር አሁን ለሰው መንገሩ ደግሞ የሐፍረት ሡቀቀን አሳደረበት።

«እስተዚህምኮ አይደለ!» አለ ገብርዬ ከጠራው ሰማይ ላይ ዐይኑን እንደ ተከለ። «ዝርዝሩንም በትክክለኛ አላስታውሰውም። ዝብርቅርቅ ያለ ነበር። ከዚህ ላይ እውነቱን ነበር የተናገረው። ጠቅላላው ትርዒት ጎልቶ ቢታየውም የጊዜ፤ የቦታና የሰዎች መታወቂያ ከእውነተኛው ሕይወት ጋር የተመሳሰለ አልነበረም። ጊዜው፤ ቀንና ሌሊት ሥፍራው ቆላና ደጋ ተራራና ሸለቆ፤ አንዳንዶቹ ሰዎች ጭራቅ የመሳሰሉ፤ መላቅጡ የጠፋ ነበር። «እንዳልኩት በትክክል አላስታውሰውም። ድንብርብሩ የወጣ ዐይነት ነው» አለ ገብርዬ ችላ ብለው እንዲተዉት ነገሩን በማቃለል አሁንም ወደ ጠራው ሰማይ እንዳንጋጠጠ።

«ይሁና ዛዲያ፤ ምናለ!»

«ሕልም የተዘበራረቀን ያህል ምሥጢሩ በዚያው ልክ ነው ረቂቅ መጢቅ የሚሆነው፤ ስለይህ ንገረን» ሲል አክሊሉ አፍጥጦ ያዘው።

መንገር እንዳልቀረለት ሲረዳ አምጦ የሚያአወጣው ይመስል ገብርዬ በሰፊው ተነፈሰ። «ለነገሩማ ቢረቀቅ ቢጎላ እኔ ምንተዳዬ! ዐይነቱ ግን አስገርሞኛል» በጉጉት እየጠበቁት ላንዳፍታ ዝም ብሎ ቆየና ቀጠለላቸው «ባንድ ትልቅ መስክ ሕዝብ ተሰብስቦ የጋማና የቀንድ ከብት ሳይለይ እየታረደ የሚበላ ይመስለኛል። የጥብሱ ጢስ እንደ ሐምሌ ዳመና አየሩን አፍኖታል፤ አጠይሞታል፤ ከአንዳንድ ሥፍራ ሰው እርስ በርሱ ይብላላል።» ገብርዬ የሁናቴው ቀፋፊነት ያሳከከው ይመስል ማኮኮውን አውጥቶ ጀሮውን በየተራ ሰቀሰቀ። «በሌላ ሥፍራ በአንድ ትልቅ ዋርካ ዙሪያ ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን የሆኑ ሴቶች እየተንጋለሉና እየተደፉ ምሕላ

የሚያደርሱ ይመስለኛል። መልሶ ቁርባንም ይመስለኛል። በዚህ መካከል አምስት የምንሆን ሰዎች እንደ ሽፍታ በገመድ ተጠፍረን ከንጉሥ ፊት እንቀርባለን።

«እነማን? ንጉሡስ ማነው?» አለ አክሊሉ፤ በዚህ ሕልም በኩል የገብርዬን ጥላቻና ፍቅር የደረሰበት መሰለው። ቅዠትም ይሁን ትንቢት የሰው ሐሳብ ፍላጎትና ምኞት በሕልሙ ይመጣበታል። በይሉኝታ በግብዝነት፤ በፍርሃት የተዳፈነ ስሜት በሕልሙ አማካይነት እየገነፈለ፤ የሥውር ሕሊናን ጓዳ እየበረገደ ይወጣል። ስለ ሰው ስሜትና ዝንባሌ ከእውን ሕይወት የላቀ የሕልም ዓለም የተሻለ ግላጭ ሳይሆን ይቀራል? አክሊሉ በምሽቱ ጨለማ ዐይኖቹን ብልጥጥ አድርጎ የገብርዬን ገጽታ ለማንበብ ሞከረ።

«ተኔ ጋር የተያዙት እነማን እንደሆኑ አይለዩኝም። ጢም የለውም፤ ሹርባ አልተሠራም እንጂ ንጉሡ ቴዎድሮስ ይመስለኛል።

«እሺ ተዚያ በኋላስ?» በማለት ጋረድ እንደ መቅበጥበጥ ቃጣው።

«ተዚያ ንጉሡ እኛን ሲመለከት ፊቱ በርበሬ ይመስለናል ወደ ፍም እየተለወጠ ሔዶ የሚቀለቀል እሳት ይሆናል። ወላፈኑ ሲገርፈን ጊዜ የኋሊት እንደ መሸሽ ስንል ወታደሮች ወደፊት ይገፈትሩናል። እንዲህ ሲል - በነበልባሉ መካከል የንጉሡ ቁመና እንደገና ቅርጽ ያወጣና በትረ መንግሥቱን ቀና አድርጎ ወደኔ እየጠቆመ፤ ‹አንተም ደሞ ገብርዬ! አንተም!› ሲል እንደ ነጎድጓድ ይጮህብኛል። ‹ኧረ እኔ ምንም አላጠፋሁ› ለማለት እሞክርና ድምፄ ሰልሎ ያቅተኛል።»

«የሚገርም ነው። የደብረ ሲናው ቋጥቋጦ። አንተ እንደ ሙሴ፤ እሱ እንደ ኤሎሄ!»

«አክሊሉ አንተ ቅቀልድብኛለህ ልበል!»

«ሙት የምሬን ነው። የነበልባል ሁናቴና ከነበልባሉ ድምፅ መውጣቱ አይመሳሰልም ነው የምትሉትን? ይልቅስ ጨርስልን።»

«ይኸው ነው። ‹ደሞ ይከዳል!› በሚል የቁታ ድምጥ በበትረ መንግሥቱ ዐይኔን ሊሸነቁረኝ ሲቃጣ ብንን ብዬ ነቃሁ፤ ላብ አጥምቆኝ።»

«በቃ ይኸው ነው እንደኢህ የዘገነነህ?»

«ከዚህ የባሰ ምን ሊመጣ ኑሮዋል?» አለ ገብርዬ ስቅጥጥ በማለት አኳኋን ራሱን እየነቀነቀ።

«ሕልም እኮ ነው!» አለው ጋረድ።

«ሕልም መሆኑ ብቻ በጀ! ለዚህ አይደለ ደፍሬስ ያወራሁላችሁ!»

«እውነት ቢሆን ኑሮሳ?»

«ምኑ?» ሲል ገብርዬ በመገረም ጠየቀ።

«ሕምልሙ ነዋ!»

«እንዴት አርጎ ሕልም እውነት ይሆናል?»

«ማለቴ - ማለቴ» ሲል አክሊሉ ድንገት ዘባርቆ ነገሩ እንዳይበላሽበት ላፍታ ገታ ብሎ ከአፉ የሚወጡትን ቃላት መዘናቸው። ገመገማቸው። ደፈር አለና ሐሳቡን ተፋው። «መሸፈትህ ሕልምሳይሆን እውነት ቢሆንስ? ምን ትሆናለህ? ጨርሰህ ጥለህ ልታብድ?»

ገብርዬ አሁንም ነገሩን ትክክል አልተረዳውም። «እንዴት አርጎ ሕልም እውነት ይሆናል? ምናልባት በጊዜው እንደ ትርጓሜው ይደርስ ይሆናል እንጂ።»

አክሊሉ፤ የመናገር ድፍረቱን ጨምቆ የሚያወጣ ይመስል በጨለማው ፊቱን ጭፍግግ አድርጎ ምንጋጋውን አጣበቀ። «እኔኮ ያልኩት በሕልም መሸፈት እንዲህ ያረገህ በውንህ ብትሸፍት ማለቴ ነው።»

«መሸፈት? እህ መሸፈትማ ማንስ ይሸፍት የለ! ዋናው ነገር መሸፈቱ ሳይሆን በማን ላይ መሸፈቱ ይመስለኛል።»

አክሊሉና ጋረድ፤ በጨለማው በዐይን ተፈላለጉ፤ ሳይነጋገሩ ሐሳብ ለሐሳብ ተገናኙ። ነገሩ የሚታወቀው የሚለየው አሁን ነው የሚል ስሜት በሁለቱም ላይ አደረ፤ ፍንጭ ተገኝቷል፤ ገርበብ ያለውን የአእምሮ በር በርግደው ገብተው አስተሳሰቡን ማወቅ አለባቸው። አክሊሉ እጁን ነጠቅ አድርጎ በመመለስ ምልክት አሳየው። ጋረድ ጭንቅላቱን ወደ ኋላ ቀልበስ አድርጎ መስማማቱን ገለጸለት። ጥቅቅሳቸውን እንደ ዋዛ ቢያይም ለጊዜው ምሥጢሩ አልገባውም ነበር።

አክሊሉ፤ ነገሩን ለማለስለስ ጉሮሮውን በትንፋሹ ደግሞ ደጋግሞ ጠራረገ። «የምልህ፤ የምትሸፍተው አንተ፤ የምትሸፍትበትም በሕልምህ ያየኸው ቢሆንስ?» አለ አክሊሉ፤ ጥያቄውን በተቻለ መጠን እንደ ቀላል ነገር ጣል ያደረገው ይምሰል እንጂ አካሉ ከተቀመጠበት እየተናጠ፤ ስሜቱ እየተናወጠ ነበር።

«ምን? እኔ ቴዎድሮስ ላይ ልሸፍት?» ጥያቄው ሳይሆን ቁጣው አይሎ ገብርዬ ከተቀመጠበት ተወርውሮ ተነሣ።

«እህ? እኔ በቴዎድሮስ ላይ ልሸፍት?» ጥያቄው ሳይሆን ቁጣው አይሎ ገብርዬ ከተቀመጠበት ተወርውሮ ተነሣ።

«እህ? መቸስ... መቸስ» በማለት አክሊሉ ጥቂት እንደ ማቅማማት አለ። «ለጊዜው ከቴዎድሮስ በቀር ሌላ ንጉሥ የለን።»

«ሳሊለነ ቅድስት - ሳሊለነ ቅድስት!» ሲል ገብርዬ እንደ መሐይም አማተበና በሁለት እጁ ጭንቅላቱን ያዘ። «ምነዋ! ምነው ወንድሜ ነውርም አይደለ?»

«ምኑ ነው ነውር?» ሲል ጠየቀው።

«ምንስ ቢሆን እንዲህ ታስብልኛለህ?»

«ተከፋህ እንዴ!» ሲል ጋረድ በማባበል መልክ ጠየቀው።

«ክፉኛ እንጂ!» አሁንም ገብርዬ በመገረም ራሱን ነቀነቀ።

«ምነው አዲስ ነገር አረከው?»

«ኧረ ከአዲስም አዲስ ትንግርት ነው እንጂ!»

«አንተ ራስህ በራስ አሊ ላይ አልሸፈትክም? እሱስ በሚሸቱ ኢያትና አባቷ ላይ አልሸፈተም?»

« ‹ያ ሌላ ይኸ ሌላ› ይላል ሸማኔ! ምን አገናኝቶት?»

«ምን ሊያይቶት?»

ገብርዬ ንዴትና ቁጣ ቢተናነቀው ራሱን ለመግታት ሞከረ። «እኔ በደል ጥቃት ቢደርስብኝ ጫካ ገባሁ። ቴዎድሮስ የሆነ እንደሆነ ለአማቱ ከመታመን ላገሩ አንድነት ላገሩ ትልቅነት ያለው ዓላማ ቢበልጥበት ነው የሸፈተው። የሱ ሽፍትነት አይባልም። ፈጥሞ! አገሩን በጎዱ ወንበዴዎች ላይ ነው የተነሣው። ልፋቱና ጥረቱ ሁላ እኔንም ይሰማኝል። በዚህ ላይ ከልብ የሚያምነኝ፤ ከልብ የምታመነው የልብ ወዳጄ ነው። ለነገሩ ይህንን ሁሉ አሁን ምን አስለፈለፈኝ?» አለና ተወው።

«ጨርሰው እንጂ!» ሲል የአክሊሉ አነጋገር የውትወታ ቃና ነበረበት። «ወዳጅህ ሆኖ ምን አደረገልህ?»

«አሆሆ! ምን ያላደረልኝ አለና?»

«እንግዲያውስ በራስ አሊ ላይ የሸፈትከው ምን ስላላደረጉልህ ተመቅኝተህ ነዋ?» «ቢመረኝ ዝም ብዬ ነው በረሃ ገብቸ የተቀመጥኩት።»

«በኋላ ግና ከካሣ ጋር ሆነህ ወግተሃቸዋል፡፡»

«በሀገራችን ምህኛት ጠላቶች ከሆንን በኋላ ነዋ!»

«ዛዲያ ከቴዎድሮስ ጋርስ አንድ ቀን ጠላቶች የማትሆኑበት ምን ምህኛት አለ?»

«ያለ ምህኛት?» ሲል ገብርዬ በመገረም ጠየቀ፡፡ «ከመሬት ተነሥቶ እንደዚሁ ጠላት መኳኳን የለም፡፡ ምህኛት ያሻዋል፡፡ እስቲ ቴዎድሮስን በምን ልጥላው? በምን ልመቅኘው? አልበደለኝ? በጥቅም በምቾት፤ በሀብት አልበለጠኝ! ተቀምጦ፤ በዚህ ውጡ በዚህ ውረዱ ብሎ አያዝ! ከኛው ጋር ይዘምታል፡፡ አንደኛው ይዋጋል፡፡ እንዲያውም ከኛ ቀድሞ! ያለውን አብረን እንበላለን! አብረን እንጠጣለን! ሐሳቡን ዓላማውን አብረን እንማከራለን! መሪ ተመሆን በቀር እሱ ተኛ የተለየ ምን ነገር ያለው መሰላቸው?!» አነጋገሩ ጥያቄ ሳይሆን የማረጋገጥ ዐይነት ነበር፡፡

«እኛስ የገረመን ይኸው አይደል! ከኛ የተለየ ሳይኖረው በዚያ መከረኛ ዙፋን ላይ....» በማለት አክሊሉ ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው፤ እንዴት እንደሚጨርስ የተቸገረ ይመስል፡፡

አክሊሉ ንግግሩን ባይጨርስም፤ ገብርዬ የሰማው በቅቶት ነበር፡፡ ሁለቱንም ተራ በተራ በዚያ ጨለማ ሊያያቸው፤ ሊያፈጥባቸው ሞከረ፡፡ ወዳጅነቱን ስለ መፈለጋቸው ሕሊናውን ሲከነክነው ለቆየው እንቆቅልሽ አሁን ፍንጭ አገኘ፡፡ ‹አዎ! እንደዚያ መሆን አለበት› አለ በሐሳቡ፡፡

«ኧረ ይኸ ሁላ የንገር ዳርዳርታ ምን ብታስቡ ነው? ከኔስ የምትፈልጉት ጉዳይ ምንድን ነው?» ሲል ጠየቃቸው በንዴት ይብገን እንጂ የገብርዬ አነጋገር ፍርጥም ያለ ሆኖ የለዘብታ ነበር፡፡

«ኧረ አንዳችም!» አለ አክሊሉ፡፡

«ወዳጅነትከን እንጂ!» ሲል ቀጠለ ጋረድም ፋታ ሳይሰጡት የተማከሩ ይመስል መልሳቸውን በጥድፊያ ተቀባበሉት፡፡

«ዛዲያ እንደዚህ ያለ ነገር ለምን ታነሣሣላችሁ?» አሁንም አጠያየቁ ለዘብ ያለ ነበር፡፡

«ጨዋታ በጨዋታ ይነሣል - እንዳመጣጡ፡፡ ምን ከፋት አለበት?»

«ከሆነማ እሺ፡፡ እንዳፋችሁ ያርገዋ!» አለ ገብርዬ፡፡ የጥርጣሬ አሽሙር ጣል ያደረገው እንደ ዘበት ነበር፡፡ ነገር ግን፤ ለዐይን ያዝ ባደረገው ምሽት፤ በኃፍረትም

ይሁን በሐሳብ ላመል ያህል አንገታቸውን ሰብር ሰበር ሲያድርጉ እንደ ጠረጠራቸው መገንዘባቸን ዐወቀ።

ራት ሲበላ እንደ ሰሞኑ ተዝናንተው አልተጨዋወቱም። ለራትም ቢሆን የቆዩት፤ ነገሩን ያዘናጉ ሥለ መሰላቸው ወይም ለምን ተፍረት መሆኑ ለገብርዬ ተሰምቶታል። የተሰነባበቱት በሙሉ ዐይን ለዐይን ሳይተያዩ ነበር.......

«ዛዲያ ምን አሰብክ?» ስትል ታንጉት ጠየቀችው፤ ከተረከላት በኋላ።

«ደሞ ምን አስባለሁ ብለሽ! እንደዚህ ያሉትን ያው በሩቅ ነው እንጂ!»

«ማለቴ ለአባ ታጠቅ ትነግረዋለህ?» ታንጉት ቴዎድሮስ የጣሉባት አድራ ድንገት ትውስ አላት።

«ምን ብዬ? ጥርጣሬ እንጂ የጨበጥኩት ነገር የለ! ‹ሸፍት› ብለው አልመከሩኝ። ወይ ‹አብረን እንሸፍት› ብለው አልጠየቁኝ። ‹ቢሆን› ብሎ ነገር ይዞ እንዴት ተሰው ይቀረባል? ደሞስ የራሴን ሕልምስ ቢሆን እንዴት ብዬ አወራለታለሁ? አሆሆሆ!» አለ ገብርዬ በመገረም እንደ መሣቅ እየሞከረው።

«እና፤ ለጊዜው መተፋፈር ይሆን? ወይንስ ተናካቴው ቁርጥ ያለ አለመደራረስ መሆኑ ነው?» የታንጉት ጥያቄ ለራስዋ ጭምር ነበር።

«ወደ ፊት እናያለና!»

«የወደፊት ሕይወታቸው እንደገና መጋጨት ግን በሰላምና በበጎ ሳዮን ነው።»

# ምዕራፍ ሦስት

ገብርዬ፤ ምናልባት ከተፈጥሮውም ባይሆን፤ በኋላ ከአኗኗሩ ወርሶ እንደ ተዋሐደው ሰውን በቀላሉ የማይቀርብ ነው። ጋይንት ዙራምባ ማርያም፤ የአባቱን መሬት ደብረ ታቦር ላይ እየተንሰራፉ የሔዱት የራስ አሊ ዘመዶች ነጥቀው፤ ጉልት አድርገውበት በረሃ ከገባ በኋላ፤ አዳኝ እንደሚሠጋ የዱር አውሬ ሰው በሩቅ እንደሚያስተውል፤ ሲገመግም ነበር የኖረው። በመጀመሪያ የሚያውቀው ልቡን ከፈቶ እንደ ልቡ የሆነበት፤ አባቱ ‹የራስ አሊ ዘመዶች ናቸው› በሚባሉ ሰዎች ከመገደላቸው በፊት ከሠፈሩ ልጆች ጋር የፍቅር፤ የጨዋታ የወዳጅነት የመሠረተበት የልጅነት ዘመኑ ነበር። ከዚያም ጦር ለመወርወር ጋሻ፤ ለመመከት ሲችል አንድ ቀን ወደ ቆላው ወርዶ ከመሰሎቹ ጋር ተቀላቀለ። ግን ገብርዬ እየቆየ እንደ ተረዳው፤

በጅምላ በረሃ የገባው ሁሉ ተመሳሳይ ሐሳብ፤ ተመሳሳይ ፍላጎት፤ ተመሳሳይ ጠባይና ተግባር አልነበረውም። በየትም እየዘረፈና እየቀማ መኖር የሚፈልግ አለ። እንደ መነነ ባሕታዊ ነገር ዓለሙን ትቶ ከዱር ፍሬ፤ ከአውድማ እንደተገኘ ጥራጥሬ ያገኘውን እየቀማመሰ ሕይወቱን የሚገፋ አለ። አርሶም፤ ነግዶም ከራሱ የተደላደለና የተሻለ ኑሮ ያለውን ሁሉ አኗኗሩንም ሕይወቱንም ያለ ምክንያት የሚያጠፋው ደግሞ አለ። በበደል ምሬት ከኅብረተሰብ ሸሽቶ ምክንያቱን እስኪያውቅ፤ መፍትሔውን እስኪያገኝ የሚንከራተተው እንደ ገብርዬ ያለው ደግሞ አለ። ሁሉም አምሳያውን እየተመራመረ ያሰባስባል። እምነት፤ ፍቅር በጥቂቶቹ መካከል እየጠበበ ይሔዳል። ይህ በስንት ፍለጋ የሚገኝ ፍቅርና መተማመን ግን ከብረት የጠነከረ ነው። ሲበጠስም የዚያኑ ያህል በቀላሉ አይቀጠልም። እንዲያውም ብዙ ጊዜ ከነአካቴው ሊቀጠል አይችልም። እንደ ልጅ ልብ ሲከፈት በሙሉ ይቀበላል፤ ሲዘጋ ጨርሶ ያርቃል፤ መሐል መንገድ፤ ግማሽ ስሜት የለውም፤ ገብርዬ በዚህ ዐይነት መንፈስ ያደገና የኖረ ሰው ነው።

ገብርዬ፤ ከመጀመሪያውም እያመነታ ከነጋረድ ጋር የሞከረው ጓደኝነት እምነቱን ካቆሰለበት በኋላ ደግሞ የዕድሜ እኩዮቹ በሞሉበት በጎንደር ከተማ ቅርበቱንና ውሎውን ከነአካቴው ከልጆቹ ጋር አደረገ። ጧት ቁርሱን እንደ ቀመሰ ሥራዬ ብሎ እያዘገመ ይወጣና ለምሳ የሚመለስበት፤ ከዚያም እንደገና ሔዶ ምሽት የሚገባበት ጊዜ አለ። እንደ አካንዱራ፤ ገበጣ የመሳሰለውን፤ እንቅስቃሴ የማይጠይቀውን ከልጆች ጋር አብሮ ይጫወታል።

ታንጉት፤ የገብርዬ ፍቅር እንዳልተነቀነሰባት ብታውቅም፤ በበኩልዋ ወይዘሮ ደብሬ ስላሉላት ከእርሷ ጋር የበለጠ ጊዜ እንዲያሳልፍ አስፈላጊ መስሎ ባይታያትም፤ ሁናቴው ሐሳብ እያሳደረባት ሔደ። ‹ሕይወቱን ሙሉ መንቀሳቀስ ለምዶ አሁን ከቤት ሲውል መንፈሱ አልረጋለት እያለ ነው? ወይንስ ባለመውለዳቸው የልጅ ፍላጎት እየበረታበት መጥቶ?› ከግቢ መውጣት ሳይጀምር እርሱ ያደርገው እንደ ነበረ ሁሉ፤ ኋላ፤ ታንጉት ከደርቡ በፍራ ላይ ሆና፤ ከመንደሩ ልጆች ጋር ሲጫወት ዝም ብላ ትመለከተውና አንዳች ዐይነት የሐሳብ ትካዜ ይጫናታል።

«ኧረ አንተ ሰው ልጅ መሆንህ ነው?» ስትል ጠየቀችው። «አንድ ቀን እግርህን አንፈራጥጠህ ቁሊዋን ሣቄ መጥቶ ነበር።» አነጋገርዋን ቀልድ ታስመስለው እንጂ ሐሳብዋ ከቀልድ የራቀ ነበር።

«ተገኝቶ ነው!» አለ ገብርዬ በአንድ እጁ የማታ ልብሳቸውን ሲደራርብላት፤ በሌላ ታፋውን እንደ መቆንጠጥ እያደረገ።

«ልጅ ነው? ልጅነት?»

«በሁለቱም።»

«ባለመውለዳችን እያዘንክ ነው መሰለኝ?»

«ምን አሳዘነኝ። እሱ ባለው ጊዜ ይሆናል።» አነጋገሩ ግን የቆዘመ ቃና ነበረበት።

«ልጅ ግን በጣም ትፈልጋለህ?»

አልመለሰላትም። ሐሳብ እንዳይገባት ብሎ መሆን ተሰማት።

«መቸስ እኔ እምቢ ታለኝ ለምን ተሌላ አትወልድም ገብርዬ? አንተ ደስ ታለህ እኔ እንደሆነ አይከፋኝም።» ከውስጥ ሐሳብዋ ግን የተናገረችውን በማስተባበል ጮኸባት። እርሱ ልጅ ቢፈልግ እርሷ ካልወለደችለት፤ የሁለቱ የፍቅር ውጤት፤ የሁለቱ የዐይን ማረፊያ ካልሆነ የሁለቱ ግንኙነት አነሰም በዛ መለወጡ ይቀራል? መቸም ሰው ነውና ዐይኑም ልቡም ወደ ውጭ ወደ ልጁ፤ ወደ ልጅ እናቱ ሊከፈልበት ይችላል። በዚያው ልክ በሁለቱ መካከል የነበረው ስሜት ተቀነሰ፤ ሳንካ ገባበት ማለት ነው። ‹ካላንቺ ከሌላስ አላደርገውም! በል ገብርዬ› ስትል በሐሳብዋ ተማጠነችው።

ገብርዬ ሐሳብዋን የደረሰበት ይመስል፤ «የሁለታችን ልጅ ቢሆን ነበር እንጂ» አለ በቅሬታ መልክ። ግን ሌላውንም በእርግጠኝነት፤ የተቃወመ አለመሰለም።

ታንጉት ሥቀቀን እንደ ወስፌ ወጋት። «በተለይ ደሞ ተሸዋ ተተመለስክ ወዲህ ነው ዐይንህን ተልጅ ጋር በጣም የሚንከራተት የሆነው!» ከመሱ አንዳች ዐይነት መጽናኛ መፈለጉዋ ነበር።

«ይሆናል!» አለ ገብርዬ በደፈናው።

«ያጋጠመህ ነገር ነበር?»

ገብርዬ በድንገት ከቅንቅልፉ እንደ ተቀሰቀሰ ዐይነት ‹እእ?› የሚል ድምፅ አሰማ።

«አንድ ነገር ደርሶብሃል!» አለች፤ አንድ ነገር እንደ ተሰማው እየተሰማት።

«ለምን ተአእምሮዬ አይጠፋም ልጄ!» አነጋገሩ ከራሱ ጋር ይመስል ነበር።

«ምንድን ነው እሱ ንገረኝ እስቲ! ወይስ ተኔ የሚሸሽግ ነው?» ታንጉት ላንዳፍታ ተመልሳ አጳናኝ ሆነች።

«ምን የሚሸሽግ ጉዳይ አለበት፤ የአንድ ልጅ ሁናቴ እኮ ነው!» ሲል ገብርዬ ጀመረ። የትዝታውን ትርዒት አጥርቶ ለማየት ይመስል በእጁ ፊቱን ጠረግ አደረገ። «ተመቁሰሌ በፊት ነው። አንኮበር ተሚሉት የእነሱ ከተማ አጠገብ ትልቅ ጦርነት ገጠሙንና ተጧት ጀምረን ስንከሳከስ ጀምበር ዘቅዘቅ ማለት ስትጀምር አጠቃናቸው። ፊታቸውን መልሰው ሲበታተኑ ተከተልናቸው። ሰዎቹ የዋዛ ሰዎች አይደሉም፤ ጨርሶ የተሸነፉ መስለው ይበተኑና እንደገና አድፍጠው መጥተው አደጋ ይጥላሉ። መጠጊያን እህል ውሃ ድንናጣ መንደሩን ጎተራውን ክምሩን፤ ሁሉ ያቃጥሉታል። ተዚያ በፊት ብዙ ጊዜ እንደዚህ ሠርተውን ነበርና አባ ታጠቅ እንዳያሞኝዋችሁ ብሎናል። ዛዲያ እኔም የእነሱ የጦር አለቃ የሚመስለውን ተከተልኩት፤ ልማርከው። አለቆቻቸውን ‹አቤቶ ገሌ ወይም የአቤቶ ገሌ ልጅ› ኢያሱ እያሉ የሚጠሩዋቸው። እድኒህ አይምሰልሽ ዙሪያውን ሰብስበው በለው ነው የሚይዙዋቸው።

«ዛዲያ ለይቼ አይቼው ነበር። አነጣጥሬ ጦር ስወረውር ትከሻው ላይ ወጋሁት። ግን ተፈረሱ አልወደቀም። አንዴ ነጠቅ እንደ ማለት አረገውና ተኮርቻው ላይ ተደፍቶ ግልቢያውን ቀጠለ። እኔም አለቅም ብዬ ተከተልኩት። የኛ ከብቶች በመንገድ ብዛት ተዳከመው ነበርና እንደፈለኩት አልደረስኩበትም። ብቻ ትንሽ ነው የራቀኝ። ተዚያም ተመንደር ደርሰን ተትልቁ ቤት ወርዶ ሲገባ በሩቅ ታየኝ። በመንደሩ ሰው አይታይም።

ይደበቃሏ! ተከብቴ ላይ ወረድኩና ባንድ እጄ ጦሬን ሰብቄ ይዤ፤ ባንድ እጄ ሽጉጤን ደግኘ በመጠንቀቅ ቀስ ብዬ ገባሁ። ዛዲያ ምን አየሁ መሰለሽ? ሰውየው ተመደቡ ላይ ተጋድሞ ደሙ በደረቱ ይወርዳል። ዕድሜው ታሥር ዓመት የማይበልጥ አንድ ልጅ ታጠገቡ ተንበርክኮ ይለዋል፤ ልጁ መሆኑ ነው። እንደ ልጅ ፈርቶ ደንግጦ ማልቀስ የወግ ነው። ፍጡም! የተገላቢጦሽ የቆሰለ አባቱን ያበረታታል። ገርሞኝ ገብቼ ቆም ስል ጥላዬ ከበደው መሰል ዞር ሲል አየኝ። ተዚያ ለምን ጊዜው ተአንድ ጥግ አጭር ዱላ መዘዝ አደረገና አባቱን በመከለል፤ ‹እኔ እያለሁ እስቲ አባቴን ትነካዋለህ!› ብሎ አያፈጥብኝም መሰለሽ? እንዳልሥቅ የልጁ ተልቡ እንዲያ መሆን በጣም አስገረመኝ፤ ልቤን ነካው፤ አብሮ ወዲያ ወዲህ በማለት ተፊቴ እየተጋረጠ ሊያሳልፈኝ ነው? አይነኩት ነገር ገና ተራ ሕፃን? ቢቸግረኝ እሺ አልነካብህም የምጠጣው ውሃ ስጠኝ› አልኩት። ምኑ ሞኝ ሆነና! ላባቱ ዘብ እንደ ቆመ፤ ‹ተንሥራው አለሉዎት› አለኛ! ገንቦውን እንሥራ ነው የሚሉት። አንቱታው ደግሞ እንጂ! ውሃዬን ጠጥቼ ዝም ብዬ ወጣሁና ተመለስኳ! በፊት አቤቶውን ስከታተለው አባ ታጠቅ አይቶኝ ኖሮ፤ በግዳዬ ጥሎሽ ጊዜ፤ ‹ገብርዬ፤ ምነው ዛሬስ

ባዶ እጅህን መጣህ?› ሲል ጠየቀኝ። ‹ገደል ገባ መሰለኝ ጠፋብኝ› አልኩት። አገሩ ገደልማ ነው። ዛዲያ ምን ብዬ ልንገረው?»

ገብርዬ፤ ታሪኩን እንደ ጨረሰ ታንጉት ብታውቅም እርሱ በታሪኩ እንደ ተመሰጠ ሁሉ፤ እሷም የምትናገረው ወይም የምትሰጠው መልስ ጠፍቶባት ዝም አለች።

«አይገርምሽም?» ሲል ገብርዬ ጠየቃት፤ ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላ።

«ምኑ?» በማለት መልሳ ጠየቀች። ልጅ ካለመውለዳቸው ጋር ያለውን ግንኙነት ያቃለለች መስሏት ነው እንጂ፤ ታርኩ የእርሷንም ስሜት ነክቶት ነበር።

የገብርዬ መልስ ግን የባሰውን አናወጣት። «እህ! ዐሥር ዓመት የማይበልጥ ልጅ ለአባቱ እንደዚህ ዘብ መቆም! እንደዚያ ያለ ልጅ ተተኩ ቢሞቱስ ምናለበት! ያንን ልጅ ታየሁ በኋላ ሳይወልዱ መሞት የሞት ሞት መስሎ ነው የተሰማኝ! ምንጊዜም ተሐሳቤ አልጠፋም ነው ያለው።

ታንጉት፤ መላ ሰውነቷን ጭምቅ የሚያደርግ አንድ ዐይነት ምጥ የያዛት መሰላት። ቀስ አለችና ፊቷን አዙራ ተጋደመች። በማባበል ፊቷን ሲደባብስ እጁን እርጥበት አቀዘቀዘው። «ምንድን ነው?» አላት ፊቷን ወደ እርሱ እየመለሰ።

«አንተ ልጅ ትፈልጋለህ እኔ ደግሞ እምቢ አለኝ!» አለች መላ ሰውነቷ በሠቀቀን እየተሰበቀ።

«ብትጠይቂኝ ታሪኩን ነገርኩሽ እንጂ አሁን ጠፍጥፈሽ አድርሺልኝ አልኩሽ?» በማለት ዕንባዋን እየጠራረገ፤ እየደባበሰ እያሻሸ ሊያጽናናት ሞከረ። ሁናቴው በዚሁ አላበቃም። ወደ ሚቀጥለው ተሸጋገረ።

ታንጉት፤ ግን፤ ፍላጎቱ በሙሉ ፈቃድ ታስተናግድ እንጂ፤ ስሜቱና ከስሜቱ ለማዋሐድ ትሞክር እንጂ ‹.....እባክህ ፈጣሪዬ ለዘር ብታበቃን! እባክህ! እያለች ባልተለመደ ጊዜና ሁናቴ መካከል የሕሊና ጸሎት ይዛ ነበር።

ወይዘሮ ደብሬ ታንጉት አዲስ ሐሳብና ትካዜ ያደረባት መሆኑ ለመገንዘብ ረጅም ጊዜ አልወሰደባቸውም። እንደ ወትሮው ትጫወታለች፤ ትሥቃለች የዕለት ሥራ ታከናውናለች፤ በመካከሉ ግን ኤሊ በድንገት በራስዋ ድንጋይ ገላ እንደምትገባ፤ ታንጉትም አንድ ነገር እንደ ረሳች ድንገት ቅዝዝ፤ ፍዝዝ ስትል የአካባቢዋን የውጭ ዓለምና ሕይወት ትታ ወደ ራስዋ የውስጥ ዓለም የገባች ትመስላለች። እንደ ልጅ አሁንም አሁንም ትኩር ብለው ለሚመለከቷት ወይዘሮ ደብሬ፤ በተለይ የሚያስውቁባት ዐይኖቿ ናቸው። ሕይወት የሚፈነጥቁትን ያህል፤

ተፊት ለፊት ከአንዳች ነገር ላይ አፍጥጠው እፍ! እንደ ተባለ መቅረዝ በድን ይሆናሉ። ወይዘሮ ደብሬ ይህንን ብዙ ጊዜ ታዝበዋል። የሚያውቁበት ምክንያት አልነበራቸውም። እንጂ፥ የዐይኖቿ ጸዳል መጥፋት እያዘወተረ የሔደው ከገብርዬ ጋር ተኻታ በሕሊናዋ ብትፀልይም በውኑ ያው የተለመደው የሴቶ፤ ‹የሔዋን እርግማን› የሚሉት ከቀጠለባት በኋላ ነበር።

ወይዘሮ ደብሬ ‹እንዴ ጭንሽ ይሻከራል፤ ሌላ ጊዜ ጣትሽ ይጎርባል እያሉ የሁለታቸውን ሥራ እንደ መሰላቸው ከዕለት ዕለት ይለዋውጡታል። አንዳንድ ቀን ‹እማማ ደብሬ ዛሬ እኔ ይህን ልሥራው› ስትላቸው ውሳኔ የዕለቱ ሥራቸውን ይመድባሉ። አንድ ቀን እንደተለመደው ገብርዬ ወደ ልጆች ጨዋታ ሒዶ፤ ሁለቱ ብቻ አዳራሹን ይዘው ወይዘሮ ደብሬ በዕለቱ የሥራ ምድባቸው ጥጡን ነድፈው በሰፌድ አቀረቡላት እርሷ ግን የእንዝርቱን ዛቢያ ከባቷ ላይ አሽከርክራ መኻል መንገድ ላይ ስትተው ወይም የከረረውን ፈትል ከእንዝርቱ ላይ አጠንጥና ስትጨርስ ጣቶቿ ቀጥ ሲሉ፤ በዚህ መኻል ዐይንዋ እንደዚሁ ቦዘዝ ሲል ሲያስተውሉ ከቆዩ በኋላ፤ «ኤዲያ ተይው!» አሉና ንድፍ ጥጥ የተቆለለበትን ሰፌድ ፈቀቅ አደረጉት። «አንቺ ልጅ ምን አግኝቶሻል?»

«ምን ሆንኩ?»

«ኧረ ኤዲያልኝ! የሰው ዐይነ ውሃው ሲቀየር መቸ አጣሁትና! ተገብርዬ ጋር ስላምም አይደላችሁም?»

«ኧረ ደኅና ነን!»

«እዛዲያስ?»

ለነገሩ ከርሳቸው የምትደብቀው ነገር የላትም። እንዝርቱን ጣል አደረገችና «እማማ ደብሬ ልጅ እምቢ አለኝ። ገርብዬ ደግሞ ለልጅ እጅግ እየሳሳ ሔደ» አለች በምሬት ፊቷን ጭፍግግ አድርጋ። የነገራትን ታሪክ ነገረቻቸው።

«ወይ የግዜር ነገር! የኔዋን መንቃራ በያመቱ ያስታቅፋታል። ተማን አባቱ እንደሆነ አሁን ደሞ አምስተኛዋን ቋጥራለች። በዚያው ሰውሞን እኔ እግሬ ወጣ ሲል ልጅ ጋረድ ሲያንዣብብ አይቸዋለሁ። ተዚህስ ምን ሆኖ ቀረ ልጄ? ሲሉ በመካከል ጠየቋት።

በገብርዬና በእነሱ መካከል የደረሰውን መንገር አልፈለገችም። «እኔ ምናባቴ ዐውቄ?» አለቻቸው።

«ወትሮውንስ የወረት አልነበረ!....ስለ ልጅ መወለድማ እኔዋ ጉድ እንዴት እንደሚሆንላት ትነግርሻለች!»

ታንጉት ከንፈርዋን መጠጠች። «እኔ አንጀቴ እርር ብሷል። እርስዎ ደሞ!»

«አይዞሽ እንጂ! በማዘን ብቻ የሚሆን ነገር የለ።»

«ምን ላርግ ብለውኝ!»

«ለመሆኑ ውርዴነት አለባችሁ? አንቺም እሱም?»

«ምናባቴ አውቄ!»

«የሕግ ባልሽ ነው። አንቺማ ተየት ታመጭዋለሽ! እናትሽም የሆኑ እንደሆነ አንቺን በደኅና አወልደዋል። ውርዴነት ቢሆን ደሞ ይመታሽ ነበር እንጂ እንደዚሁ አይተውሽ! ለመሆኑ ጠበሉን ምናምኑን ሞክረሻል?»

«በቋራም በአዳኝ አገርም በጫቆም ሰሚ ነው የተባለውን ታቦትና የታወቀውን ጠበል ሞክሬ ነበረ። ማኅበረ ሥላሴም ቸንከር ተክለ ሃይማኖትም አልቀረልኝም።»

«የዚህን አገር ደሞ መሞከር ነዋ!»

«ተሆነልኝማ ለምን ኢየሩሳሌም አይሆንም!»

«እሱንስ ቴዎድሮስ ሲዘምቱ ትደርሽበታለሽ።»

በዚህ ዐይነት ከሰሜን እስከ አቸፈር፤ ከጋይንት እስከ አርማጭሆ ቀዝቃዛውንና ፍል ውሃውን ጠበል፤ የታወቀውን ገዳም፤ የበቃ የተባለውን ባሕታዊ ያዳርሱ ጀመር። አሁን ያለ ምርኩዝ መራመድ የቻለውን ገብርዬም ብዙ ሥፍራ አብሯቸው ይሔድ ነበር። ታንጉትና ወይዘሮ ደብሬ ‹ጎንደር ከተማ ከመወዘፍ አገር ማየት አይሻልም!› ከማለት በስተቀር የጉዞዋቸውን ዋና ምክንያት በግልጽ ባይነግሩትም ጠርጥሯል። ሙከራቸውን አልጠላውም።

ከሩቅ ጉዞ ተመልሰው ጎንደር በሚሰነበቱበት ጊዜም፤ የዐርባ አራቱን ታቦት በዓል እየቆጠሩ እምነትና ቅብዓ ቅዱስ መቀባቷን፤ ማየቆረር መቅመሷን አልተወችም።

ታንጉት፤ በተስፋ እጅግ ከመጓጓቷ የተነሳ ቡራኬ በተቀበለች፤ ጠበል በቀመሰች ማግሥት የእርግዝና ምልክት እንደሆነ ግን አታውቅም። ‹ሲያረግዙ ብዙ ነገር ያምራል አሉ። እኔን ምን ይሆን ከቶ የሚያምረኝ› ትላቸዋለች ወይዘሮ ደብሬን።

‹ሲደርስ ታገኚው የለ!› ሲሉ ይመልሱላታል ጉጉትዋ ልባቸውን እየነካው። ለእርሷ ሳይነግሩ ለታቦት ተሳሉላት።

የወር አበባዋ አንድ ሁለት ቀን እንዳለፈ እንደሆነ፤ ‹እማማ ደብሬ አሁንስ ሊቀር ነው መሰለኝ!› ትላለች ፊቷ በተስፋ እየበራ። ሲመጣ መልሳ ቅዝዝ ትላለች።

ብዙ ወራት ዐለፈ። ብዙ አገር አዳረሱ። ግን አልሆነላትም። ገብርዬ አብሮዋቸው ብዙ ከተዟዟረ በኋላ ባይሰለችም ከንቱ ልፋት መሆኑ እየተሰማው ሔደና፤ ‹እህ! እንግዲህ መቸስ ስንንከወከው አንኖር። ባ ታጠቅም መመለሻው ሳይቃረብ አይቀርም። ጎንደር ብቆየው ይሻለኛል። ታላለው መቸስ ምን ይደረግ!› አላቸው አንድ ቀን ለሁለተኛ ጊዜ ጎንደር ተክለ ሃይማኖት አንድ ሰባት ሲያበቁ።

‹ምኑዋ! ሲሉ ወይዘሮ ደብሬ ያላወቁ መስለው ጠየቁት።

‹አሄሄ! ምህኛታችሁ ሳይገባኝ ቀርቶ ነው አብሬያችሁ የምከራተተው? ተሆነልንማ በማን ዕድሌ ነበር።›

ታንጉት የቀድሞው ትካዜ እንደገና ተጫናት። ፊቷ የሠቀቀን ጥውልጋት ሰፈነባት።

«እውነቱን ነው ገብርዬ!» አሏት ወይዘሮ ደብሬ፤ ታንጉትን ለብቻዋ። «ይኸ ሁሉ ታቦት ታልሰማ!»

«ምን ብበድለው ነው ፈጣሪዬ እንደዚህ የረገመኝ!» አለች ታንጉት፤ የምሬት ሲቃ እየተናነቃት።

እንደገና ረግተው ጎንደር ሲቀመጡ ገብርዬ፤ ተስፋ በመቁረጥም ይሁን ታንጉትን እንደሚያሣቅቃት በሚገንዘብ ስለ ልጅ ማንሣቱን ተወው። ከመንደር ልጆች ጋር መጫወቱንም ቀነሰ። በተቻለ መጠንም የደስተኝነት ሁናቴ ያሳይ ነበር። ይህ ግን ለታንጉት አልበጃትም። ውስጥ ውስጡን እንደበላው ለእርሷ ሲል ስሜቱን እንደ ደበቀ በመገመት፤ የባሰውን እሳት ላይ እንደ ተጣለ ቋንጣ አንጀትዋ በኅዘን እርር ድብን ይል ገባ። ሙጥኝ እንደ ማለት ያህል ወዳጅነታቸውን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ብትፈልገውም፤ ያ ውብ ጨዋታቸውና ቀልዳቸው ጥርሷን የሚያስገልጣት በስለት እየመሰለ ሔደ። ዐልፎ ዐልፎ የምታሰማው የሣቅ ድምፅም ቢሆን፤ እንደ ቅል ኳኳቴ የደስታ ሕይወት የሌለው፤ ከአንገት በላይ መሆን በግልጽ ያስታውቅባታል። ወይም የትዝብት ዐይነት ነው።

የሐሳብ በሽታዋን በምንም ዐይነት ማጽናናት ሊያቃሉላት እንደማይችሉ ወይዘሮ ደብሬ ሞክረው - ሞክረው ሲገነዘቡ፤ «ግንኮ ተገብርዬ ይሆን? ይሆናል ምክንያቱ!» የሚል ሐሳብ አቀረቡላት።

«ኧረ እሱ አንዳች ጉድለትም የለበት እቴ!» አለች ታንጉት በግራሚ ማስተባበል።

«እህ! ምን ጉድለት አለበት ያልኩሽ መሰለሽ። ቢሆንማ አልመነኮሽ! መች አብረው ትኖሪ ነበር። ግና ያም ዘሩ መካን እንደሆነስ? አለዉ እኮ የወንድ መካን። ስለዚህ እኮ ነው፤ ውርዴነት አለበት ወይ ብዬ ተመጀመሪያው ጠይቄሽ የነበረው?»

«መካንነቱ ተሱም ሆነ ተኔ ያው ነው!» አለች በተስፋ መቁረጥ እጅዋን እያወራጨች።

«መችም ተሱ የሆነ.....» ንግግራቸውን አንጠልጥለው ተዉት።

«እህ ተሱ ተሆነሳ?» ታንጉት ሲቃ ያዛት።

«አይ! ተይው የማይሆን ነው። ጭንቀትሽ ቢያስጨንቀኝ ነው እንጂ!»

«የሚሆን ተሆነ ምናልባት።»

«ኧረ ባባጃሌው ይዥዎታለሁ። ልጄ የሚያስወልድ መላ ታለ ይንገሩኝ!» ከጉልበታቸው ላይ ተደፍታ ለመለመን የከጀላት ትመስላለች።

«ይልቅስ ያውራ ዶሮውን ታሪክ ነግሬሻለሁ?»

«እኔ የዶሮ ታሪክ ምን ይሠራልኛል። ያመጡትን ይንገሩኝ ነው ያልኩት እንጂ» ስትል ተማጠነች ታንጉት ብስክስክ እያለች።

«እሱም እኮ የልጅ ጉዳይ ነው! አንድዋ አንዳቸው ልጅ እምቢ አላትና ተቀሚሷ ሥር መዓት ጨርቅ ጎዝጉዛ ባሏን አርግዣለሁ እያለች ስትዋሽለት መከረም!»

«እህ! ማታ ሲተኙ አያያትም?» ስትል ታንጉት ጠየቀች፤ ድንገት ነገሩ አስገርሟት።

«ያመኛል እያለች ለብቻዋ እየተኛች ነዋ! ዘጠኝ ወር ተሞላት በኋላ ምን ታርገው። አውራ ዶሮዋን አርዳ ደሙን ታልጋው ላይ አፈሰሰችና ‹አስወረደኝ› አለችው ይባላል። ዛዲያ ምን ተብሎ ተዘፈነላት መሰለሽ። ጌጤ ነው ስሟ እንግዲህ። ‹የጌጤ አውራ ዶሮ ዘንድሮ ከበረ፤ ዘጠኝ ወር ተረግዞ አልጋ ላይ ሠፈረ›።» ወይዘሮ ደብሬ ይህንን ጨዋታ ያመጡት የፊተኛውን ለማረሳሳት ነበር።

ታንጉት ግን ጨዋታው ቅንጣት እንዳላሣቃት ሁሉ ጥያቄዋን አላስረሳትም። «እኔ ይንገሩኝ የምለው ገብርዬ መካን ቢሆንስ ብለው የጀመሩት ነው። ምናለ የልጅ ልጅ አይተዋል። የኔ ጭንቀት መቸ.....» ስትል በመከፋት አንገቷን አቀረቀረች።

«ተይ እንጂ፤ እንደዚህ አትሁኝ!»

«ዛዲያ ይንገሩኝ!»

«አይሆንሽም አትስማሚም ይሆናል ብዬ ነው!»

«መጀመሪያ ልስማው።»

«ታልሽ ምን ቸገረኝ። አየሽ፤ አንድ ልጅ እናቱ ናት እንጂ አባቱኮ በርግጠኝነት የሚታወቅ አይደለም። አባቱ ማን መሆኑን ምናልባት በርግጠኝነት የምታውቅለት እናቱ ብቻ ናት። አሁን ለምሳሌ እኔ ልጆቼን ለአባታቸው ልጆችህ ናቸው አልኩት እንጂ ተሌላ አርግዤያቸው ቢሆን በምን ያውቅ ነበር? እና አሁንም የሆነ እንደሆነ.......» መጨረሱ የከበዳቸው ይመስል ተዉት።

ወይዘሮ ደብሬ እንደሠጉት ሐሳቡ ታንጉትን በጣም አላስደነገጣትም። «እና ለገብርዬ ልጅ ተሌላ ወንድ ላርግዝለት ማለትዎ ነው?» ስትል ከመገረም ጋር ጠየቀች።

«አንቺን አርጊው አላልኩሽም፤ ንገሪኝ ስላልሽ ነው፤ ባላቸው መካን ተሆነ የሚያደርጉ ሴቶች ግን አሉ። ወንዱስ ቢሆን የጨነቀው እርጉዝ ያገባል ሲባል አልሰማሽም?»

«ግና ኃጢያት አይሆንም?»

«የልብን ጭንቀት አይቶ ባወቀ ይፍረዳ! ለነገሩማ እንደዚሁስ ይወሰለት የለ!»

«እኔ እንጃ! ተዚያ በኋላ የገብርዬን ዐይን ደፍሬ ማየት የምችል አይመስለኝም። »

«እሱማ የት ያውቅና!»

«ቢሆንም ሕሊናዬ መውቀሱን መች ይተወኝና!»

«እሱማ እንደየሰዉ ሆድ ነው፤ የማይችልለት አለ።»

«ኧረ እኔ እንጃ!» ስትል ታንጉት ራሷን ነቀነቀች። የሚቀፍ ነገር እንዳየች ፊቷን ጭፍግግ ታድርግ እንጂ አነጋገርዋ የተረጋገጠ የመጨረሻ እምቢታ አልነበረም።

ታንጉት በአብዛኛው በራስዋ ሐሳብ ብትዋጥም ቴዎድሮስ የጣለባትን አደራ ደግሞ ችላ አላለችውም። ነበር። የገብርዬ ፍላቶ እንዲሚላለት ከልብ የምትጨነቀው ያህል ቴዎድሮስ ቅር እንዲሰኝባት አትፈልግም። ‹ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ› እንደሚባለው ነው ትላለች በሐሳብዋ። ከሁለቱም በኩል ግልጽ ሆኖ አለመውጣቱ ቢከነክናትም፤ በተለየ መንገድ ለቴዎድሮስ ያላትን ፍቅርና አሳቢነት ብትፈልግም ከልብዋ ልትፍቀው አትችልም። ሌላው ቢቀር ‹አንጓች› ብሎ በዚያ አስተያየቱ ሲመለከታት፤ በተለየ ልቡን በእጁ ይዞ የሰጣት ይመስላትና ገና ላልጠየቃት ነገር በሆድዋ ‹እሺ!› የሚል ስሜት ያድርባታል። ከዚህም ጋር ቴዎድሮስ ለእርሷ ያለው አስተያየት ከገብርዬ ጋር የምትመራውን የጋራ ሕይወትም ይመለከታል። ቴዎድሮስ ለእርስዋ በጎ ሐሳብ እስካለው ድረስ ገብርዬ ሊያስከፋት እንደ ማይፈቅድ ይታወቃታል። የቴዎድሮስ በጎ አሳቢነት እንዳይቀንስባት ደግሞ ከአቡነ ሰላማ አካባቢ ከወይዘሮ ደብሬ፤ ከሌሎችም ያገኘችውን ይዛለት መቆየት ይገባታል።

ከአቡነ ሰላማ መንበር፤ የካህናቱ ስብሰባና ምክክር መቀጠል ብቻ ሳይሆን፤ የቴዎድሮስን አድርጎት በግልጽ ወደ መቃወም እያመራ መሆኑን ተገነዘበች። ካህናቱ ለብቻ ከአቡኑ ጋር ከሚዶልቱበት አዳራሽ መቆየት ባትችልም መስቀል ለመሳለም ስትገባ ብዛታቸውን ታያለች። ከቤት ሠራተኞቹም አንዳንድ ወሬዎች ትሰማለች። ታንጉት የተገነዘበችው አዲስ ነገር፤ አክሊሉ ከእነርሱ ቤት እንደቀየረ ሁሉ በአቡኑ ግቢም አለመታየቱን ነው። ሁለቱም ሆነ ብለው የተደበቁ ይመስላል። ሌላው በጎንደር ከተማ የሚወራው አገው ንጉሤ የሚባል ሽፍታ በስሜን መነሣቱ ነበር። ብዙ ሠራዊት እንዳለው ይነገርለታል። ጎንደር ውስጥም ሰዎች አሉት። ካካህናቱ ጋር ይላላካል ይባላል።

ቴዎድሮስ ገና እብለሳን ሳይሻገሩ ‹አጤ ቴዎድርሶ እጅግ ተዋረዱ የወሎን ሰው ሁሉ እጅ ነሥተው ሔዱ› ከሚለው ግጥም አንሥቶ፤ «ግምቤንስ ታጉርሰኝ ምሽቴ። አቦ አቦ እንትኔንስ በም አባቴ» አለ አንድ ወሎዬ ተብሎ እስከ ተነገረው ቀልድ ድረስ በወሎ የፈጸሙት አስፈሪ ወሬ ጎንደር ገባ። ጎንደር በፍርሃትም በወሬም እየታመሰ ሰነበተ። ቴዎድሮስ አካላቸውና መንፈሳቸው የታከተው የሚያስመስል የጠወለገ ገጽታ ይዘውለት መጡ። እንደ ወትሮ ግብር አላስገቡም።

ምናልባት ከእርዋ ባገኙት መረጃ ብቻም ባይሆን ታንጉት ያየችውን የሰማችውን የተገነዘበችውን እንዲሁም የመሰላትን በነገረቻቸው በሁለተኛው ቀን ቴዎድሮስ ካህናቱን ጉባኤ ጠሩ። ዙፋን ተዘርግቶ በአዳራሹ ውስጥ ሳይሆን

ወይዛዝርቱም፤ ጨዋውም ወንድ፤ በተመልካችነት ወይም በወሬ አድማቂነት የተገኘበት የመስክ ስብሰባ ነበር።

ካህናቱ ግብር እንደተጠራ የክት ልብሳቸውን እየለበሱ፤ ጥምጥማቸውን እየከሸኑ፤ መቋሚያቸውን እያዘመሙ፤ አቡነ ሰላማን አጅበው ጃን ተክለ በር ላይ ተሰበሰቡ። ቴዎድሮስ የጦር አለቆቻቸውን አስከትለው ከቤተ መንግሥቱ ወጡና ከነጭ ልብሱና ከነጭ ጥምጥሙ ጋር በረዶ መስሎ የፈሰሰውን ምድረ ካህን ሲመለከቱ፤ ‹ይቺ ቆማጣ ቆመጥማጣ ራስዋን ጠምጣሚ ወገቧን ሰባቂ ሁላ አስቸገረኝ አይደል?› አሉ ከአጠገባቸው ለነበሩ የጦር አለቆቻቸው። አቡነ ሰላማ መንበር ተቀምጦላቸዋል፤ ድባብ ተዘርግቶላቸዋል። ቴዎድሮስ ግን፤ ትሕትና ይሁን መከፋታቸውን ለማሳየት ከአሸዋው ላይ ተቀመጡ።

«አባቶቼ ምን በደልኋችሁና ነው ጀርባችሁን የሰጣችሁኝ» ወገኔ እንዲጠላኝ የምትመክሩብኝ፤ በክፉ የምታነሡኝ፤ ክፉ የምታስቡብኝ? የግዜር ሰዎች ነን ትላላችሁ፤ ዛዲያ ይህን እግዜር ይወደዋል?» ሲሉ በርጋታ ጠይቁ።

«እንደ ጥንቱ፤ እንደ ጧቱ እንደ ቀደምቱ ነገሥታት ያኑሩን» አለ አንዱ ተጠሪ ደብተራ።

«እኩሌታውን የመስቀል መሬት፤ እኩሌታውን ሪም፤ ገዳም እያላችሁ ከወሰዳችሁ፤ እኔ ምን ልብላ? ሠራዊቱንስ ምን ላብላው?» ሲሉ ጠየቁ ቴዎድሮስ፤ ንዴታቸውን እንደ ምንም ገትተው።

ሌላው ካህን ቀበል አደረገ። «አራት ወር በጎንደር ተቀምጠው አርማጭሆን፤ ፀገዴን፤ ወልቃይትን ስሜንን ይብሉ» አላቸው።

«ተዚያስ?»

«አራት ወር በዓራንጎ ተቀምጠው በጌምድርን፤ ላስታ፤ የጁን፤ ወረይመኑን፤ ወሎን፤ ሸዋን ይብሉ።»

«የተቀረውንሳ?» የቴዎድሮስ አጠያየቅ የትዝብት ዐይነት ነበር።

«ይባባ ላይ ተቀምጠው ጫጫን፤ አገውን፤ ዳሞትን፤ ጎጃምን መብላት ነዋ!»

ቴዎድሮስ በምሬትና በፌዝ ከት ብለው ሣቁ። «ብልጤ፤ ብልጣ ብልጤ! ሕዝቤ ሲጠላኝ፤ ሠራዊቴ ሲከዳኝ፤ ብቻዬን በሆንሁልሽ ጊዜ እንዳጤ ኢያሱ በሻሽ አንቀሽ ልትገይኝ!»

ክርክሩ ከተከፈተ በኋላ፤ ከካህናቱ በኩል ብዙው እየተደፋፈረ መነሣት ጀመረ።

«ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም ብሏል ዳዊት።»

«እንግዲያው አሮንን ለክህነት ሙሴን ለመሪነት ለምን መረጠው? ልጠይቃችሁ!»

«ሁሉም በየተመረጠበት፤ በየተመደበበት እንዲሠራ ካህኑ በካህንነቱ።»

«ሠራዊቱ በሠራዊነቱ» አሉ ቴዎድሮስ ኮስተር ብለው።

«ዛዲያስ?»

«ዛዲያማ እናንተ በሥራት የነበረ አሁን ምን ቀረባችሁ? ወንጌል ይፋረደኝ» አሉ ቴዎድሮስ። ማፋረድ ወይም መፍረድ ሳይሆን እንደ ተራ ተሚጋች እየተነሡ የሚከራከሩት ራሳቸው ነበሩ። ሠራዊቱና የጦር አበጋዞቻቸው ግን አልወደዱላቸውም።

«ከሁለቱም ሥልጣናቸውንና ድርሻቸውን ወስኖላቸዋላ!» አለ አንድ ካህን ተነሥቶ በድፍረት።

ቴዎድሮስ አንገታቸውን ደፋ አድርገው በቅሬታ ጥቂት አሰቡ። ‹አንድም እያለ ነገር ሲበልት፤ ሲሰነጥቅ፤ ሲከፋፍል፤ ሥራ ፈትቶ ተረብ ሲያወጣ ሲያወርድ የሚውል ደብተራ ማን ይችለዋል?› የሚል ይመስላል አስተያየታቸው። «ክርስቶስ ዳኛችን ይሁን» አሉና የሚደግሙበት የጃቸው ወንጌል እንዲቀርብላቸው አዘዙ።

«በፍትሐ ነገሥት ነው የምንፋረደው» አለ ሌላው ደብተራ እጁን ቀስሮ።

«ይምጣ! ፍትሐ ነገሥቱስ ቢሆን ማን ይፈራዋል!»

ፍትሐ ነገሥቱ መጣና፤ በፍትሐ ነገሥት ለታወቁት ለደብረ ብርሃን ሥላሴው ዓለቃ ተሰጠ። የደብረ ብርሃን ሥላሴ አለቃ ትልቁን የብራና መጽሐፍ ገለጥ ገልበጥ - ገልበጥ አደረጉና የሚፈልጉትን አንቀጽ ሲያገኙ፤ ሌባ ጣታቸውን ከብራናው ላይ ጠንቁለው ጉሮሮዋቸውን ጠራረጉ። «ከመቅደስ የገባ አይወጣም» ይላል አሉ።

«ዛዲያስ?» ቴዎድሮስ ነገሩ ቢገባቸውም ያላወቁ መሰሉ።

«ዛዲያማ፤» ሲሉ የአደባባይ ኢየሱስ የፍትሐ ነገሥት መምህር ተተኩ። «መቅደስ የገባ ሲባል፤ በየሱስ ሥጋ ደም የሚሠየመው ‹ኅብስቱ ወይኑ ብቻ

አይደለም› እንደ ጥንቱ፤ እንደ ጧቱ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለካህናት ሁሉ የዋለው አይቀነስም፤ አይነካም። እንደ ኅብስቱ እንደ ወይኑ ማንም ምድራዊ ሥልጣን አያዝበትም ሲል ነው፡!»

«አንድሽ አንባቢ፤ አንድሽ ተርጓሚ።» ቴዎድሮስ የቁጣቸው ግንፍላት እየተናነቃቸው እንደ መወራጨት አሉ።

«እንግዲህ መቸስ ፍትሐ ነገሥቱ እንደሚለውና ያገርዎ ሊቃውንት እንደ ተረጎሙት ነው።» አሉ አቡነ ሰላማ በማቅማማት ሪዛቸውን እየነተቱ።

ቴዎድሮስ አምቀው የያዙት ንዴት ትንሽ ፍልቅ ብሎ ወጣባቸው። «ብልጤ ብልጣ ብልጤ! ለነገርማ ማን ብሎሽ? እርስ በርስሽ ትተካኪያለሽ። እና ማን ይፈረዳል?» ሲሉ በመወራጨት ተነሥተው የተሰበሰበውን ካህን ሁሉ ጠየቁ።

«እስዎ ይፍረዱት» የሚል መልስ አስተጋባ።

ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርጉት ሁለት ክንዳቸውን ከወገባቸው አስደግፈው ያንን ካህን ሁሉ በትዝብት ቃኙት። በክርክር እንደተረቱ ተሰምቷቸው። «ዛዲያ ምን ላርገው?» ሲሉ ራሳቸውን ጠየቁ። ከዚያ በፊት እንደሚያደርጉት ከሆነ አልሆን ከአላቸው ደግሞ መምታት ወደ ጥሎ መሔድ። ከነራስ አሊ ጋብቻ ሆነው ሲያዋርዷቸው ለጊዜው ዐቅማቸውን ገምተው ገሸሽ ብለዋል። በኋላም የዐቅማቸውን ጥንካሬ ሲያረጋግጡ ተጋጥመው ሁሉንም ተራ በተራ መትተዋል። ነገር ግን ነፍጥ ቀርቶ የረባ ዱላ ካልያዘ ካህን ጋር ያዋጣልን ማለት በጣም መቅለል ሆነባቸው። አይንን ዕብሪተኛ ካህን ቢቀጡ ራሳቸው እንደ ዕብሪተኛ ይታያሉ እንጂ ከጀግንነት አይቆጠርላቸውም። የነገሩ አጉልነት የባሰውን አበሸቃቸው። ግራ እጃቸውን ከወገባቸው ላይ እንዳስደገፉ በቀኝ እጃቸው የጎራዴያቸን ሰደፍ እንደ መነቅነቅ እያደረጉ፤ «አንተው ፍረድ! እኔማ ምኑን እፈርደዋለሁ? እናንተው ጨርሳችሁት የለ! እናንተ ከጠላችሁኝ፤ እናንተው የወደዳችሁትን አስቀምጡበት። እኔ እንደሆነ እንደ ወትሮዬ እየዘረፍኩ እያደንኩ መኖር አያቅተኝም» አሉና በመወራጨት ወደ አዳራሻቸው እንደ መሔድ ሲቃጡ፤ ዙሪያውን ሆኖ ሲያዳምጥ የነበረው ሠራዊት ማዕበለ እንደነካው ባሕር አብሮ ተናጋ። አብዛኛው ካህንም በሁናቴው መልሶ ተደናገጠ። የፈለጉት ቴዎድሮስ፤ ‹አባቶቼ እንዳላችሁ፤ እሽ ከፈቃዳችሁ አልወጣም› እንዲሉ ነበር። ‹የፈለጋችሁትን አስቀምጡበት። እኔ አድኘ፤ ዘርፌ እበላለሁ› ሲሉ ግን እምቢታ እንጂ እሺታ አለመሆኑ ግልጽ ነበር። የሚዘረፉትስ ያው እነሱው አይደሉ የሚሆኑት? ገበሬና የእጅ ባለሙያንማ አትንኩብኝ ብለዋል። ቴዎድሮስ ከነሠራዊታቸው ልቅ ሆነው በአልጋው ላይ ደፍሮ የሚቀመጥ የት ይገኛል? እነ ራስ አሊ እንደሆኑ ደብዛቸው ጠፍቷል።

‹ይለመኑን! ይቅር ይበሉን!› የሚል ድምፅ እንደ ምሕላ ባንድነት አስተጋባ።

ቴዎድሮስ ተመልሰው ተቀመጡ። ግን እጅግ የሚጠሉትና የሚጠየፉት ነገር ቢኖር ፍርሃትና ፈሪን ስለሆነ፤ ከካህናቱ የፊተኛው ድፍረት ይልቅ የአሁኑ መርበትበታቸው የባሰ አናደዳቸው። ‹ፈሪ ክብር አይገባውም› ባይ ናቸውና በውርደት ሊቀጡዋቸው ፈለጉ። «ጠምጥማችሁ ከፊቴ እንዳትቀርቡ ከልክዬ አልነበረም? ይኸስ ድፍረት አይደለም? ሲሉ ዐይናቸውን አፈጠጡባቸው።

ደፍሮ መልስ የሚሰጥ ጠፋ።

«በሉ እንጂ ተናገሩ!» አሏቸው። እንደገና ሁሉም እርስ በርስ እየተያየ ጭጭ አለ።

«አንተ ፍትሐ ነገሥት ተርጓሚው። ስለ ቅሽር ጥምጥማችሁ መጽሐፉ ምን ይላል? መስል ስጥ» አሉዋቸው የአደባባይ ኢየሱስን መምህር። «እኮ በል!»

«መቾስ መቾስ» የአደባባይ ኢየሱስ መምህር በመቋሚያቸው ጫፍ ዐይናቸውን መሬት ላይ ተክለው እንደ ማመንታት አሉ። «ጥምጥም ክብራችን፤ መለያችን ነው። እንደ ቸሮታዎ ይበይኑልን።»

«ዛዲያ መለያችሁ፤ ክብራችሁ ተሆነ ከታቦት በገባችሁ ጊዜ ለምን ጥምጥማችሁን ታወልቃላችሁ?»

«እሱማ እግዚአብሔር አድሮበታል ብለን ነው!»

«በኔስ ላይ አላደረም!»

ማንም አላስተባበለም።

በጃቸው ወደ አቡነ ሰላማ እያመለከቱ፤ «አባታችን፤ የለም፤ በኔ ላይ ያደረው ይበልጣል ብለው የሚከራከሩኝ ተሆነ መቾስ እሰጥ እገባ አልሚገትዎም። ግን ያንድ ሀገር መሪ ደግሞ ያገሩ ‹ተምሳሌት ነው። እኔም ያገሬ ተምሳሌ ስለሆንኩ፤ ጥንታዊቷ፤ ባለታሪካዊቷ ኢትዮጵያ ሀገሬ በኔ ላይ ታድራለችና፤ ፍቅርዋ ጰራቅሊጦስ በልቤ ውስጥ ሥርጿልና ለኔ አይምሰላችሁ፤ ከበሬታው ለርሷ ነው።»

«በሉ እንጂ!» አሉ ቴዎድሮስ ጥቂት ከጠበቁ በኋላ መከራከሪያ የሚያቀርብ እንደሌለ ሲገነዘቡ። ብዙው ካህን ነገራቸው አልገባውም። ጥምጥምህን አውልቅ የተባለ መሰለውና ሥራዊቱ ተለቆ በዱላ ሳይዠልጠው ወይም በጎራዴ ሳያወራርደው፤ አንዳንዱ ውሉን እየፈታ ይተረትር፤ ሌላው እንዳለ ከጭንቅላቱ ላይ እየመዘዘ በጉያው ይሸጉጥ ጀመር። መላጣ ሽበታም፤ ከምከሞ፤ ዐልፎ ዐልፎም

ለምጥና በሽታ የወረሰው ራስ መጋለጡ እየበረከተ መሔዱን ቴዎድሮስ ሲመለከቱ ቅር አላቸው። ‹ጥምጥም ስንቱን ጉድ ሸፍኗል› አሉ በሆዳቸው።

«እኔማ ሥራ ላስተምራችሁ ብዬ ነው እንጂ ተሆድ ያልሆነ ከበሬታ ምን ሊጠቅመኝ? ጥምጥማችሁ ምን ሊጎዳኝ? ራሳችሁ ተገለጠና ምን ሊረባኝ? እንደፈቀዳችሁ ሁኑበት» አሉ በመታከት መልክ እጃቸውን እያወዛወዙ።

ካህኑ ሁሉ እንደገና ጥምጥሙን እያስተካከለ ለመበተን ሲል ለወረደው ዕርቀ ሰላም ማሳረጊያ ግብር ታደመ።

ማምሻውን በሥራ ክፍላቸው ለማናገር ሲያስጠሩዋት ለፊተኛው ዐይነት ጉዳይ መሰላትና ታንጉት የተለየ ሐሳብ መጣባት። ‹ሊያመሰግነኝ ነው? ወይንስ ለወደፊቱም አደራሽን ሊለኝ? የእነ ጋረድን የገብርዬን ነገር ሰምቶ ለምን ደበቅሽኝ ብሎ ይጠይቀን ይሆን? በምን ያውቃል? ማን ይነግረዋል? ገብርዬ እንደሆነ አልነግረውም ብሏል። ዛዲያ እኔስ ብሆን ገብርዬ እንደዚህ ያለ ሕልም አየብህ ብዬ መንገር ነበረብኝ?»

«ቁጭ በይ አንጓች» አሏትና ኀዘን ይሁን ቅሬታ በሰፈነበት አስተያየት ተመለከቷት። «ይኸውልሽ ተንከራተት ብሎኝ ነገ ደግሞ ወደ ጎጃም መዝመቴ ነው! ገብርዬን ይጌብሽ!»

«ወትሮስ ቢሆን ተኔ ጋር ቁጭ ብሎ መኖር አለመደ» ስት መለሰች። ለዚህ ኖሯል የጠራኝ እያለች በሆድዋ።

«ተመነሣቴ በፊት ግን፤ ነገ ጧት ተተዋበች ጋር ልንቆርብ ነው!» አሏት በድንገት።

ታንጉት፤ የምትናገረው ጠፍቷት በመገረም ብቻ አፍዋን ያዘች። የቴዎድሮስና የተዋበች ፍቅር፤ እንኳን እርሷ፤ የቅርቧ ቀርታ አገሩ ሁሉ የሚደነቅበት ቢሆንም፤ ይቆርባሉ የሚል ግምት በሐሳብዋ መጥቶ አያውቅም።

«አዎ! ተዋበች ተኔ ጋር ስትንከራተት ጤናም እያጣች ሔዳለች። በዚህ ላይ ልጅ የላት!»

‹እኔስ ብሆን ያታለም!› ሲል ሆድዋ የጮኸ መስሎ ተሰማት።

«እና ባንድ በኩል ትንሽ መጽናኛ ቢሆናት ብዬ ነው» ሲሉ ቴዎድሮስ ቀጠሉ። «ዕድሜዋን ታረዘመልኝ እንኔ እንግዲህ ተሷ ሌላ አልመኝ! በሌላ በኩል ደግሞ፤ ለሌላው ምሳሌ የሆንኩ መስሎኝ ነው። በምግባርም፤ በጠባይም፤ በጭዋነትም፤

በትዳሩም ሆነ በሥራ እንዲያው በማንኛውም ነገር እኛ ሆነን ታላሳየነው፤ ሌላውን ‹ይህን አታድርግ፤ ይህን አትሥራ› ብለን ብንመከረው ብንገሥጸው ምን ብሎ ይሠማናል? ለምንስ እንፈርድበታለን? ስለዚህ እስቲ ተኔው ልጀምር ብዬ ነው። ገልሞ መቸም ያው ዐይኑ የሚያሳርፍባትን አላገኘም። ታንጉት፤ ‹ወይስ በዘሩ ምክንያት እሺ የምትለው አማራ አላገኘም?› የሚል ጥያቄ በሐሳብዋ መጣባት። ‹ዓለሜና ሌሎች ግን፤ ነገ ተኛው ጋር ሊቆርቡ ነው። ‹እኔ እንደሆነ አግኝቸው ነው! በኋላ እሳቸው ተኮንነው እንዳይስኮንኑኝ እንጂ!› እያለች ትንሽ እንዲያ እንዲህ ያለችው የጎንደሬ ጠባይዋ ገና ያለቀቃት የእንግዳ ሚሽት ናት። ተሁለቱ የትኛቸው እውነተኞች ይሁኑ እኔ ዐላውቅም። ለሁሉም እነሱም ነገር እንቆርጣለን ብለዋል።» ቴዎድሮስ በማሰብ ዐይነት ንግግራቸውን ገታ አደረጉ።

ታንጉት፤ የሚቀጥለውን ለማወቅ ከመጓጓት የተነሣ ከመቀመጫዋ እስከ መነሳት ቃጣት። ለቅጽበት ስሜቷን ያነጠረው እና አሁንም ‹አንቺና ገብርዬ አንደኛና እደሌሎቹ ሁኑ› የሚለውን ጥያቄ ለመስማት ነው። እሽታዋን ከእልልታ ባላነሰ ስሜት ለመመለስ መላ ሰውነቷ እንደ ጦር ተሰበቀ፤ እንደ ቀስት ተወጠረ፤ በሐሳብ ሊያስጨንቃት ለኖረው የልጅ ጉዳይ አንድ የማቃለያ ተስፋ ብልጭ ብሎባት። ገብርዬ ከርስዋ ልጅ አለማስወለዱ እሱንም እሷንም የሚያሳዝን ቢሆንም፤ ጋብቻቸው ፍቅራቸው በቁርባን ከታሰረ በቃው። አንዳቸው ካልሞቱ እንደ ታሰረ ይቀራል። ገብርዬ በጎን ከሌላ ሴት የመውለድ ሐሳብ ከነበረበት አከተመ። ወይዘሮ ደብሬ እንዳሉት ራሱ መካን ካልሆነ በስተቀር። ግን መሆኑን በምን ያውቀዋል? ከእርስዋም ቢሆን እያደረ ተስፋ ቆርጦ ከጊዜ በኋላ ይረሳው ይሆናል። የቆረቡ ባልና ሚስቶች በዓመት በዓሉም በጾሙም ሌላውን ነገር እንደሚተዉት ሰምታለች። ወይ ደግሞ ከጊዜ በኋላ ከቁርባናቸው ጋር ጾም ጸሎቱን ካጠናከሩት እሱ ባወቀ መርቆ ዘር ይሰጣቸው ይሆናል፤ ማን ያውቃል!

«አንቺና ገብርዬ» የሚሉት ቃላት ከቴዎድሮስ ሲወጡ በአንዳች ዐይነት ስሜት መጥቃ፤ ‹ግን› የሚለው ተከታይ ቃል እንደ መብረቅ መታት። ቴዎድሮስ ዐረፍተ ነገራቸውን እስኪጨርሱ መጠበቅ አላስፈለጋትም። ‹ግን› የሚለው አንድ ዐይነት ቃል እንደ ጦር ተሰካባት። ቴዎድሮስም በዚያው ቅጽበት የሁናቴዋን መለወጥ ተገንዝበው ንግግራቸውን አቋረጡና በመገረም አተኮሩ። «ምነው ተጓደኞችሽ ላለመለየት መቁረብ ትፈልጊ ነበር?» ሲሉ ጠየቋት፤ ስሜቷ የቅሬታ መሆኑ ወዲያው ገብቷቸው።

«ኧረቴ! አንተ እንደ መሰለህ!» ስትል መለሰች ድምፅዋም፤ ገጽታዋም የምትናገረውን በግልጽ እያስተባበለባት።

ቴዎድሮስ ፊታቸውን በመዳፋቸው እየፈተጉ ቁንዳላቸውን እዬነተቱ አሰቡ። ስለ እርሷ እንደ እርሷ በመጨነቅ ፊታቸው ተጨፈገገ። «ምን መስለሽ አንጓች» አሉ በሚያባብል ድምፅ። «እንደእውነቱ ተሆነ እኔ ተገብርዬ የቀረበ እንድም የለኝ። አንቺም ተሱ የሚሻል ባል አታገኝም። እናንተ ያልቆረባችሁ ማን ይቆርብ ነበር። ዛዲያ እንደምታውቂው ገብርዬ የጦር አዝማች በመሆኑ፤ ታንቺ እየተለየ ተብዙ አገር ተብዙ ዘመቻ መሔዱ የማይቀር ነው። ወንድ ልጅ ለረጅም ጊዜ ተቤቱ ሲለይ ደግሞ መቸስ። እና በዚህ ላይ ደግሞ አንቺም እንደ ተዋበች እስተ ዛሬ ለልጅ አላደለሽም። እኔ መቸም እንዳልኩሽ ተዋበች ልጅ ብትሰጠኝ ደስታውን አልችለውም ነበር። ታልሆነ ግን፤ የወገኔ ልጅ ህሉ ልጄ ነው ብዬ እጽናናለሁ። ገብርዬን ግን እንደኔ ሁን ማለቱ ይከብደኛል። ልጅ እንደሚወድ ዐውቃለሁ። ለኔ ሲል እየተጋደለ በዚህ ላይ ታለ ዘር ቅር ማለቱ ዐጉል መጨከን መስሎ ይታየኛል። ስለዚህ የሁለታችሁ መቁረብ ቢቆይ የተሻለ መስሎኛል።

ታንጉት ‹እ!› የሚል ድምፅ ብቻ አሰማች። አጥንት የተሰነቀረባት ያህል ጉሮሮዋን ተናነቃት። አነጋገራቸውን ምክር ያስመሰሉት እንጂ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ መሆኑ ገብቷታል።

«አንቺም ብትሆኝ ገና ልጅ ነሽ፤ ይቆይሽ!» አሉ ጉዳዩን ለማቃለል በመቀለድ መልክ።

ታንጉት የምትናገረው አልነበራትም። የምታስበው ሳይቀር ጠፋባት። አእምሮዋ ድንገት ባዶ ሆነባት። በደመ ነፍስ እጅ ነሥታ ወጣች።

በበነጋው ጧት፤ በደብረ ብርሃን ሥላሴ የቅዳሴውና የቁርባኑ ሥነ ሥርዓት ተካሔደ። ከጨለማው ጋር ተፋጥጣ አብዛኛውን ሌሊት እንቅልፍ ሳይወስዳት ያደረገችው ታንጉት ወትሮ ይመስጣት፤ መንፈስዋን ወደ ተረጋጋ ዓለም ይስብላት የነበረው ቅዳሴ አሁን የሚያስጠላ ልቅሶ ሆነባት። ከዜማው እስከ ቃጭሉ፤ ከጧፍ እስከ መንጦዕላቱ ሁሉም ነገር አስጠላት። ሥነ ሥርዓቱ እንደ አንድ ዓመት መከራ ረዘመባት። ከሁሉም ያሠቃያት፤ የውስጥ ስሜቷን፤ ሌሎች በተለየ የሚቆርቡት መሰሎቿ እንዳያውቁባት ለመደበቅ የምታደርገው መጨነቅና መጠበብ ነበር። ገንፍሎ ለመውጣት የሚተናነቃትን ልቅሶ አምቃ ይዛ በሹክሹክታ ሲያነጋግሩዋት መመለስ፤ ፈገግ ሲሉ አብራ ጥርሷን መገልፈጥ ነበረባት። ድርብ ሥቃይ ነበር።

እንዳያልቅ የለም ሥነ ሥርዓቱ አለቀ። የታንጉት መከራ ግን አላለቀላትም። ገብርዬና ታንጉት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ከከብቶቻቸው ወርደው በመሳለም ሰዎቻቸውን አስቀድመው ታንጉት ከአንድ ነገር የምትሸሽ ይመስል፤ ከአረማመድዋ ፈጠን ፈጠን እያለች ገብርዬ የመንገድ ጓዙን ለማዘጋጀት የተጣደፈች

መስሎት፤ ስለ ጉዞው እያሰበ በእግራቸው ትንሽ እልፍ እንዳሉ ከጋረድና ከአክሊሉ ጋር ድንገት ተገናኙ። እነ ጋረድ እንደ አጋጣሚ ያስመስሉት እንጂ፤ ትክክለኛውን ሁናቴ ለማወቅ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቆይተው ሥጋ ወደሙ እንደ ወረደ ቀደም ብለው በመውጣት፤ ሆነ ብለው መገጣጠሚያ ላይ ጠብቀዋቸው ነበር።

በግልጽ እንዳልተጣሉ ባላጋራዎች የመተፋፈር ሰላምታ ተለዋወጡ። ታንጉት ተለይታ ወደ ፊት ቀደም አለች።

«ምነው ጠፋችሁ? ባገር አላችሁ እንዴ?» አለ ገብርዬ የመጨረሻ ቀን ጭውውታቸውን የሚያስታውስ በሚመስል ትዝብት።

«የሹመት አገሩን ልናይ ወደ ወገራ ወጥተን ነበር» ሲል አክሊሉ መለሰለት።

«ኧረ! አልሰማሁም ነበር» ብሎ ገብርዬ ተሰናብቷቸው መንገዱን ሊቀጥል ሲል፤ እርሱም ወደ እርሱው አቅጣጫ ታጠፉ።

«ምነው ተለይታችሁ ቀራችሁ?» ሲል አክሊሉ በፌዝ ዐይነት ዐይኑን አጨንቁሮ እየተመለከተ ጠየቀው።

«ተምኑ?» ገብርዬ ያላወቀ መሰለ።

«በተክሊል ተመታሰሩ ነዋ! ‹ተከተል አለቃህን› ተብሎ የለ?»

«በመታሰር ማን ደስ ይለዋል?» አለ ገብርዬ ነገሩን አቃልሎ እንደ መተው በማድረግ።

«አንተነህ እሷ እስራቱን የፈራችሁት? ደፍራችሁ በምትገቡበት ጊዜ ግን እኔ ደብር ሎዛ ማርያም ነው የማቆርባችሁ።»

»ለዚያ ያብቃን» አለ ገብርዬ። አንድ ዐይነት ሥውር አሽሙር ያለበት ጨዋታቸው አልጥም ብሎት ለመለየት አረማመዱን አፍጠነ።

«ምን ታውራለህ ተነሱ ጋር ደሞ?» ስትል ታንጉት ኮስተር ብላ ጠየቀችው፤ አድሮ ያረፈደ እምቅ ስሜቷ ምክንያት አፋጠነ።

«ሰላም ሲሉኝ ዛዲያ ዝም ብያቸው ልለፍ?»

«ዛዲያ የግዜር ሰላምታ የሚያሣሥቅ ነገር አለበት?» ሆን ብለው መንገዱ ላይ እንደ ተጠባባቁዋቸው ከገብርዬ ይልቅ ታንጉት ጠርጥራ ነበር።

«አይ! ለምን በቁርባን አልታሰራችሁም ብለው ቀላለዱ።»

«እና፤ ምናልካቸው?» ካለወትሮዋ አጠያየቅዋ የማፋጠን ዐይነት ነበር።

«መታሰር ማን ይፈልጋል ነዋ!»

ውጋት ንዝር እንዳደረጋት ያህል፤ ‹እእ!› ብላ እንደ ዕውር እየተደናበረች ወደ ቤትዋ ገሠገሠች። አሁን የገብርዬ አንድ ቃል ሰበብ ሆኖ ያስገነፈለባትን፤ ሲተናነቃት የቆየውን ሠቀቀን ብቻዋን ሆና እስከታወጣው መድኃኒት እንደ ቀመሰ ሰው አጣደፋት።

ገብርዬ፤ ለጊዜው ታንጉት ያበሳጫትን ትክክለኛ ምክንያት ይገምት እንጂ፤ የሠቀቀንዋን ጥልቀት፤ የሥቃይዋን ክብደት አልተገነዘበም። ሊገነዘብ የሚችልበት መንገድም አልነበረም። ሌሎቹ እንዲቀርቡ መጠየቃቸው፤ እነርሱ ግን እንዲቆዩ ለታንጉት የተነገራት መሆኑን ፈጽሞ አያውቅም ነበር። ሌሎቹ መቁረባቸውን ያወቀው ጧት ሲቆርቡ ነው። ቴዎድሮስን ለማስደሰት ወይም ሥነ ሥርዓቱን ለማድመቅ ሲሉ ለየራሳቸው አስበው በፈቃዳቸው ያደረጉት መሰለው። አብሮ መሰለፉን ባይጠላውም፤ ተለይተው መቅረታቸውም ደግሞ ከባድ ግምት ውስጥ አላስገባውም። ቢፈልግም ደግሞ እዚያው ተነሥተው መቁረብ አይችሉም ነበር። ታንጉትን እንደ ልጃቸው የዳሩለት ቴዎድሮስ ናቸው። አስቀድሞ ማማከር፤ የሚስማሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዳለበት ያውቀዋል።

ገብርዬ ተከታትሎ ቤት እንደ ደረሰ እንደ ዋዛ ታንጉትን ደጋግሞ ቢጣራ ጓዳ አድፍጣ ዝም አለችው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሚጠፋ ጊዜያዊ ቅሬታ እንደሆነ አድርጎ በመገመት፤ ‹እስቲ ይለፍላት!› አለና በሆዱ፤ ለጊዜ አስረሽነት ተወው። ከዚያም የኮርቻ ከብቱን ደኅንነት መራምሮ የሚይዘውን ጓዝ ሲፈታትሽ ከቆየ በኋላ ቤተ መንግሥት ሔደ።

ታንጉት፤ ብርቱ ቁርጠት እንዳመመው ሰው ከሥር በእጅዋ ጭብጥ አድርጋ ይዛ፤ ከአልጋው ላይ በሆድዋ ተኝታ ነበር ወይዘሮ ደብሬ ያገኙዋት። በጨርቅና በትራስ መኻል የተቀበረ ፊቷን በአገጭዋ መለስ አደረጉና ትኩር ብለው ተመለከቷት። ቀደም ሲል መላ ሰውነቷን እንደ ጦር እየሰበቀ ያንሰቀሰቃት ልቅሶ፤ በኃይል ተነፍቶ እየተነፈሰ መሟሸሽ እንደ ጀመረ ፊኛ ጋብ ብሏል። ዕንባዋም ቢሆን እንዳባራ ዝናብ ጠፈፍ ማለት ይዟል። የፈሰሰው ዕንባዋ አሥምሮ ከተወው የጉንጭ ፈር ጋር ጠቅላላ ፊቷ እሳት እንደ ገረፈው ብራና ተኮማትሯል። ዐይኖቿ በርበሬ መስለዋል። የጉንጮቿ ስርጉዶች ጠፍተዋል። ያ ሙሉ ጉንጭ ተንገርግቦ እንደ ቆየ ጥሬ ወደ ውስጥ ተመጥጧል። «ኤጭ! ምን እየሆንሽ ነው፤ ኧረ ባባጃሌው!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ በእናት ዐይነት ቁጣ መንጨቅ ማድረግ እየቃጡ። ጥያቄ አልነበረም። የቁርባኑንና የቆራቢዎችን ወሬ እንደ ሰሙ ተጠራጥረው ነበር የመጡት።

«እሺ አደርገዋለሁ!» አለች ታንጉት የኮሶ መድኃኒት ድንገት ለመጨለጥ እንደ ደፈረ ሰው ዐይነት ድንገት ተወራጭታ።

«ምኑን የእኔ ልጅ?» ሲሉ ወይዘሮ ደብሬ፤ ምን ማለቷ ነው እንደሆነ እያወቁ ትከሻዋን ዕቅፍ አድርገው በማባበል።

«ስለ ልጅ መውለድ ያሉትን!» አለች አሁንም በኃይለ ቃል።

«እሺ! እሺ የኔ ልጅ!» አሉ እንደ ሕፃን ትከሻዋን ዕቅፍ አድርገው እንደ ዐቀፏት።

«እሺ እኮ አልኩሽ» አሉ ወይዘሮ ደብሬ፤ አሁንም በማባበል ትከሻዋን በመዳፋቸው መታ መታ አደረጉ።

«እሺ መቸ!»

«ኧረ ባባጃሌው! ዛዲያ ቀስ ብሎ ረጋ ብሎ ነው እንጂ!»

«አንድ ጊዜ! አንድ ጊዜ!» ታንጉት እንደ እንቆቆ አንድ ጊዜ ጭልጥ አድርጋ ስትውጠው ታያት።

«ዛዲያ አንድ ጊዜ ቢሆንስ? ደግሞ ባይሆንስ? ለሁሉስ ቴዎድሮስ ዛሬ መዝመቱ አይደለም? ገብርዬስ አብሮ ሒያጅ አይደለም?»

«እሱማ ማነው እንግዲህ።»

»ኧረ ባባጃሌው! ልጅ፤ ጅላ ጅል ነሽ ልበል!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ ከግሣጼ ይልቅ በመገረም።

«ምነው?»

«እህ ዛዲያ አርግዘሽ ልትቆይው ኖሯል? አንድያውን ባዋጅ ጉዴን ዕወቁልኝ ማለት አይሻልም?»

ታንጉት ገባት። «እሺ ሲመለስ!»

ታንጉት፤ እንቆቆዋን ለመጨለጥ አንድ ጊዜ ብትወስንም፤ የገብርዬን ከጎጃም ዘመቻ መመለስ ሲጠብቁ፤ ጉቶው ሁሉ አውሬ እንደሚመስለው የጨለማ መንገደኛ ብዙ ዐይነት ጥያቄ እየተደቀነባት ሐሳብዋ መለስ ቀለስ ማለቱ አልቀረም ነበር።

«ኧረ እማማ ደብሬ! አባትየው በኋላ ምሥጢር ቢያወጣሉ?» ትላቸዋለች።

«በምናባቱ ዐውቆ?» ሲሉ ይመልሱላታል።

«በምናባቱ ዐውቆ?» ሲሉ ይመልሱላታል።

«ገብርዬ እኔን አይመስልም ብሎ ቢጠራጠርስ?» ስትል ትጠይቃቸዋለች።

«ልጅ ሁላ አባቴን ይመስላል ያለሽ ማነው? ‹ማጅራቱ አባቱን ይመስላል› እየተባለ ሲተረት አልሰማሽም?» የሚል መልስ ታገኛለሽ።

«እንዲያው ለመሆኑ ያደረግነው ሰውየው ቢያወራልሽስ?»

«ግዴለሽም። ለኔ ተይልኝ መላውን። እንኳን እሱ አንቺም ማን መሆኑን እንዳታውቂው እናረጋለን» ያልሆነልኝ እንደሆነስ? ዳግመኛስ የምሞክረው አይመስለኝም!»

«የሱ ፈቃድ ተሆነ ዘርና ዕውቂያ አንድ ቀን ተብሏል።»

«ውይ እማማ ደብሬ፤ እኔኮ የሌላ ወንድ ጠረን አላውቅም!»

«ላንዳፍታ እንደ ምንም መቻል ነዋ!»

ገብርዬ፤ ከሁለት ወር ያህል በኋላ ተመልሶ ጎንደር እስኪመጣ፤ ወይዘሮ ደብሬና ታንጉት ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ጥያቄዎች በመካከላቸው በማንሣት መልሱን ተነጋግረውበት ነበር። ገብርዬ ከመጣ በኋላ፤ «ሐሳብሽን ታልቀየርሽና ይሁን ታልሽ እንግዲህ መዘጋጀት ነው» ሲሉ ወይዘሮ ደብሬ የመጨረሻ ውሳኔዋን ጠየቋት።

«እሱማ ጨርሰን የለ!»

«እንግዲያው በጠራሽ በሳምንቱ ሲሆን ነው የማይስተው» ሲሉ ተስማሚውን ጊዜ ገለጹላት። የወር አበባዋን ማለታቸው ነበር።

«ለመሆኑ ሰውዬው ማነው የሚሆነው?» ታንጉት ማወቅ ባትፈልግም ማንነቱ ከነከናት።

«ኧረ ባባጃሌው! እንዳትተዋወቁ ነው የሚሆነው ብየሽ! ለሕሊናሽም፤ በኋላ ለልጁም ጥሩ አይሆንም» በማለት መለሱላት።

በተስማሙበት የቀጠሮ ቀን ቡን እየተጠጣ በዋዛ ፈዛዛው ጨዋታ መካከል ወይዘሮ ደብሬ፤ «ነገ የጊዮርጊስ ዋዜማ ነው። የአምባ ጊዮርጊስ የሚነግሥበት እና ለመሳለምም፤ ዘመድ ለመጠየቅ ስለምሔድ የምትፈቅድ ተሆነ ታንጉትን ተኔ ጋራ ልውሰዳት» ሲሉ ገብርዬን ጠየቁት።

«ኧረ በመድኃኔ ዓለም! አሁን ማን ይሙት የትም ስትዞር እኔን ጠይቃችኋል?» አለ ገብርዬ ነገሩን በማቃለል።

«ድንገት ያደርንም እንደሆነ እንዳታስብ ብዬ ነዋ!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ፤ በተመሳሳይ የማቃለል አነጋገር።

ታንጉት፤ ወደ ጎንደር ተመልሳ በአምባ ጊዮርጊስ የሆነው ሁሉ እንደገና ስታስበው የሚታያት እንደ ሕልም ነው።

......አምባ ጊዮርጊስ ሲደርሱ ከመንደሩ ዳርቻ ላይ አንድ ትልቅ ሁለት ትናንሽ የሣር ቤቶች ወደ አሉበት አንድ አጥር ግቢ አመሩ። አስቀድመው የወሰኑ ወይም የተሰናዱበት ይመስል፤ ታንጉትን ከአንደኛው አነስተኛ ጎጆ አስገቡዋት። ወይዘሮ ደብሬ ወደ ትልቁ ቤት ሔደው ከጥቂት ጊዜ በኋላ የገብስ ቆሎና ኮረፌ ጠላ ራሳቸው ይዘው ተመለሱ። «እንግዲህ ከዚሁ ቆይ፤ ማንም አያስቸግርሽ፤ እኔ ቤተ ክርስቲያን ተሳልሜ ልምጣ!» በማልት ብቻዋን ተዋት። ጊዜው አልገፋ ብሏት ጣራና ግድግዳ ስትቆጥር፤ የኩታዋን ጫፍ እየተረተረች እንደገና መልሳ ስትቋጭ ቆየች። ውሎ መሰላት። እንደዚሁ ከመጠበቅ በስተቀር የፍርሃትም ይሁን የጉጉት አንዳችም የለየለት ሐሳብ አይሰማትም ነበር። ወደ ማታ ገደማ ወይዘሮ ደብሬ እንደገና ሲመጡ፤ እንጀራ በክክ ወጥና አረቄ ይዘው ነበር። «አይዞሽ» አሏት ያመጡትን እያቀረቡ። «ኮረፌው ብቻ ሆድሽን ይነፋዋል፤ አረቄውን ጠጭበት፤ ደሞም ፍርሃትሽን ያጠፋልሻል።» ሲመሽ፤ «በይ እንግዲህ ዐረፍ በይ» አሉና በጨለማው ውስጥ ብቻዋን ጥለዋት ሔዱ። አሁን ልብዋ ከፉኛ ይመታ ጀመር። ካለ ዐመልዋ አረቄውን አንድ ሦስት መለኪያ ስትጠጣለት ሞቅታ ተሰማት። ‹ምናለበት!› ስትል ራሷን አደፋፈረች። ከትልቁ ቤት ጠበል ጣዲቅ መኖሩን የሚያበሥረው የሰዉ ሁካታ እየቀነሰ ሔዶ ጨርሶ ሲጠፋ ታንጉት መቀነቷን ፈታችና ከጠፍር አልጋው ላይ ተጋደመች። መጀመሪያ የሰው ድምፅ በሩቅ ሰማች። ጀሮዋን አንቅታ ስታዳምጥ ዲክ፤ ዲክ፤ የሚለው ኮቴ እየቀረበ መጣ። ገርበብ ብሎ የነበረው በፍራ ሲከፈት በውጭው ደብዛዛ የከዋክብት ውጋጋን የሰውዬው ቅርጽ ጥላ መስሎ ታያት። ትንፋሽዋን ያዝ አደረገችው። ልብዋ ደረትዋን ተርትሮ የሚወጣ መስሏት ነበር። ከአልጋው ጠርዝ ተቀምጦ ልብሱን ሲያወላልቅ፤ ‹ምነው ዛሬ ይህንን አረቄ ዝም ብላ ጋተችኝ እባካችሁ?› አለ ሰውዬው ከራሱ ጋር፤ መጠጥ ትንሽ ባሰረው አንደበት። ‹እህ!› አለ በመገረም በመደንገጥም። ታንጉት እንቅልፍ የወሰዳት መስላ ዝም አለች። ለማረጋገጥ በእጁ ዳበስ ዳበስ አድርጎ ቁንዳላዋን ሲነካ እንደገና ‹እህ!› አለ። ‹ተነሥቶ ይሔድ ይሆን?› የሚል ሐሳብ መጣባት። ግን አልሔድም፤ ዶሮ ሊጮህ አቅራቢያም ሁለተኛ ጊዜ እንደዚሁ። ታንጉት ባትደስትበትም እንደ

ፈራችው አላስፈራትም፤ ሲጀምር ተነሥቶ ሔደ። ቀይ ይሁን ጥቁር አላየችውም፤ እሱም ያላያትም፤ ከረፋዱ ላይ ወደ ጎንደር ተመለሱ.......

ከጥቂት ሳምንታ በኋላ «እማማ ደብሬ መሆኑ ነው መሰለኝ!» አለቻቸው፤ የደስታ ፈገግታ እያሳየች።

«እሰየው! እሰየው! ስለቱን አስገባለኋ!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ እንደ ልጅ መፈንደቅ ቃጣቸው።

«ይኸው አራት ቀን ዐለፈኝ እንግዲህ። ለገብርዬ ልንገረው!» ስትል በጥርጣሬ መልክ ጠየቀች።

«ትንሽ ቆይ፤ ያደርስሻል!»

«ግን እንዲያው አንዳችም ፍንጭ አይወጣም ብለው ነው?»

«በምን መንገድ። እኔን እንጂ አንቺን አላየሽ! ማን መሆንሽን ዐያውቅ! ደፍሮም አይናገረው እንጂ!» በጥያቄ አስተያየት ተመለከተታቸው። «ዲያቆን ነበራ!»

«ምን?» ታንጉት በመብረቅ እንደ ተመታ ክው አለች።

«አይዞሽ አትደንግጭ! ማፍረሱም የማይቀር ነበር። « ታሪኩን ነገሩዋት። «ሦስት ልጆች የወለደችለት ሚስቱ ከሞተች ሁለት ዓመት ሊሆናት ነው። እኅቱ ሌላ ሚሽት እንዲያገባ ትፈልጋለች። በዚህ ዕድሜው ምን በወጣው! አይቀስስ! አይመነኩስ ባይ ናት።»

«ግን እኅቲቱን ምን ብለው አማከሯት?»

«ወንድ የማያስጠጋ ዐይነ ጥላ ያስቸገራት አንዷት እኅቴ ነበረች፤ ዐዋቂ ብንጠይቅ ምሽቱ የሞተችበት ካህን ይገፍላታል አለን አልኳት፤ ወትሮውንም የወንድሟ ነገር ሲከነክናት ቆይቶ ኖሮ ደስታውንም አልቻለችው።»

«እንዴት መጣልዎ እንደዚህ ያለው መላ እቴ!» በመገረም ራስዋን እያወዛወዘች.....

በዚያው ሰሞን ግን፤ ጋረድና አክሊሉ የተጨዋወቱት ስለ አምባ ጊዮርጊስ ነበር።

ከጋረድ ቤት ጠጅ እየኮመኮሙ በመጠጥ ኃይል ተኩራርቶ፤ «ራስ ታልኩት መቸ አነሰውና» እያለ ከአገው ንጉሤ ጋር ስለሚያደጉት ስምምነት፤ ስለ ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር ላይ መክተም ሲያወጉ ነገሩን በመኻል ያነሣው አክሊሉ ነበር።

«ኧረ እንዲያው እንደነገሩ ሰምቸ!» አለ አክሊሉ መገረሙን ለማሳወቅ ዐይኑን ጨንቆር አድርጎ።

«ምን?»

«የአምባ ጊዮርጊሱን አለቃ መንክር ታውቃቸዋለህ?» ጋረድ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ። «ወዳጄ ናቸው። ዛዲያ በቀደምለታ በጨዋታ ጨዋታ አንድ የሚያስደንቅ ወሬ ነገሩኝ። ሚሽቱ የሞተችበት አንድ ካህን ነበር፤ በጣም የሚያቀርቡት። እንዲያውም እሳቸው ትልቅ ገዳም የተሾሙ እንደሆነ አለቅነቱ ይይዛል ብለው ያመኑበት። ዛዲያ የጊዮርጊስ ማግሥት ድንገት አፈረስኩ አይላቸው መሰለህ!»

«ሲሽፍት መቸስ ምን ያድርግ?» አለ ጋረድ፡

«መሸነፉስ ይሸነፍ። ሳያስበው እኮ አንዲት ሴት አሳተችኝ ነው የሚለው። የሚገርመው ደግሞ ሴትየዋን አያውቃትም።

«ታላወቃት እንዴት?» ጋረድ ጥያቄውን አንጠልጥሎ ተወው።

«ጠበል ጠዲቅ ሲል መሽቶበት ተእነቱ ቤት አድሮ ታልጋ ላይ አገኘሁዋት ነው የሚለው!»

«በዕንጨት ለቀማ፤ በልስብ አጠባ፤ በውሃ ቅዳት ጊዜ ዐልፎ ዐልፎ የሚያስትም ያጋጥማል» አለ ጋረድ ነገሩን በማቃለል መልክ።

«ዛዲያ ተመንደሩ ማን እንዳደረ ታውቃለህ?» ሲል አክሊሉ ጉጉት በሚቀሰቅስ አነጋገር ጠየቀውና መልሱን ወዲያው ሰጠው። «ወይዘሮ ደብሬ!»

«ኧረ! በዚህ ዕድሜያቸው?» ጋረድ የግራሜ ሣቅ መጣበት።

«እሳቸውማ አይደሉም። ሌላ ነው ነገሩ። እሳቸውን ጥቂት ጥቂት ያውቃቸዋል። በዚህ ላይ ሴትየዋ ቁንዳላ መሆንዋን ዐውቋል። ገምት እስቲ!» ሲል አክሊሉን ጠበቀው።

ጋረድ ጥቂት እንደ ማሰብ አደረገ። «ታንጉት ናት እንዳትለኝ!»

«ሌላ ማን ሊሆን ይችላል? ሁለቱ እንደሆነ አይለያዩ። መቁረቡንስ የጠላችው ዐመሏን ስለምታውቅ ሳይሆን ይቀራል?»

«እንከፍ!» ጋረድ ገብርዬን በሌለበት ሰደበው። «ይህንን እናውጣውና እናፋጀቸው! እሱ እንደሆነ እንዳሰብነው ተወጥመዳችን አልገባልነ። እውነትም እንከፍ!»

«ቆይ እንደሱም አይደል! አትቸኩል ልጅ ጋረድ። ነገርን አስቦ ነው። እነሱ ቢጣሉ እኛን ምን ይጠቅመናል አሁን!»

«አሳድጌያታለሁ፤ ልጄ ማለት ናት ይል የለ! ቴዎድሮስና ገብርዬም በዚሁ ምህኛት ይቀያየሟሏ!»

«አይመስለኝም። ጥፋቱ የሷ ተሆነ ቴዎድሮስ ለገብዬ ነው የሚያደላው። ትክክለኛ ፍርድ እያለ የሚመጻደቅባት ነገር አለ አይደል!»

«እና፤ ዝም እንበል ነው የምትለው?»

«ለጊዜው! ለጊዜው! ይህንን ጉድ የምንጠቀምበት መንገድ እስትናገኝ በምሥጢር እናቆየዋለን።»

ታንጉት፤ እርግጠኛ ከሆነች በኋላ አንድ ቀን የምሥራቹን ለገብርዬ ስትነግረው፤ «አሁን ለሱ ቸርነት ምን ዋጋ ይከፈለዋል!» እያለ ዐሥር ጊዜ ከማመስገን በቀር ደስታውን የሚገልጥበት ሌላ ቋንቋ አጣ። ደብረ ታቦር ሔዶ ለቴዎድሮስ እስኪነግራቸው ድረስም ተቻኮለ። ከእርሱ ያላነሰ ደስ እንደሚላቸው ይሰማዋል፡ ነገር ግን፤ ታንጉት ጧት ጧት እያጥወለወላት ያስታውካት ስለ ጀመረ ወይዘሮ ደብሬ ብዙ ጊዜ ባይለዩዋትም በእንደዚህ ያለ ወቅት ከባለቤት የሚቀርብ አይገኝምና ትቷት ከመሔዱ ይልቅ፤ ሲባል እንደ ሰማው ሽሉ እስኪረጋ መቆየቱ የተሻለ መስሎ ታየው። የጧት ሕመምዋ እያደረ ቀለል ሲልላት ደግሞ ታንጉት አዲስ ሁናቴ ተፈጠረባት።

ምናልባት በማሕፀንዋ ያለው ፅንስ የራስዋን የልጅነት ዘመን ስላስታወሳት ይሁን፤ ወይም ደግሞ እርግዝናዋ በዐጸደ ነፍስ ለሚገኙት እናትዋ ለማሳየት አንዳች ሥውር ፍላጎት አድሮባት፤ ብዙ ጊዜ ሐሳብዋና ትዝታዋ ዐፈር ውሃ ተራጭታ ወደ አደገችበት ትውልድ ሀገርዋ ጭልጥ ብሎ ይሔድባታል። በዚህ ጊዜ ፈጽሞ ያላሰበችው አምሮት ይይዛታል። «ወቸው ጉድ» ትላለች በመገረም ከራስዋ ጋር። ይህ አዲስ አምሮት እየበረታባት ሲሔድ ለወይዘሮ ደብሬ አማከረቻቸው።

«ዛዲያ ችግሩ ምንድን ነው?» አሏት።

«እህ! ገብርዬ እሺ አይል እንደሆነ ብዬ ነዋ!»

«እህ! ሁለት ወዶ አይሆንም።»

ይሥቅብኛል እያለች ስታቅማማ ሰንብታ፤ «ምነው ሆድሽ አላደገም ልጄ!» ብሎ አንድ ቀን ሲዳብሳት ነበር ደፍራ የጠየቀችው። የውስጥ ጉጉቷ ከፊቷ ላይ

ይነበባል። «አንድ ነገር እያማረኝ አስቸግሮኛል፤ እሺ ትለኛለህ?» አለችና ጠየቀችው።

«እምቢ እንዳልልሽ ነው ዛዲያ! ወገኛ ነሽ!»

«አገሩ ሩቅ ቢሆንሳ!»

«ተቅርብ ተለለ! እነኢ ምንተዳዩ!»

«ዋልካ አማረኝ!» አለች ታንጉት የመጨነቅ ሣቅ እየመጣባት።

«ዋልካ! ዋልካ ዛዲያ ጉራንባ ወረድ ሲል ምን የመሰለ ዋልካ ተፍሮ የለ! ብቻ ልጅጄን ጥቁር እንዳታደርጊው እንጂ!»

«እኔን ያማረኝ ደሞ የወይኒ ዋልካ ነው። ልጅ ሆኜ የነበርኩበት ተወይኒ ወንዝ ዳር አንድ ገርገብም አለ፤ ልጆች ሆነን የምንጫወትበት። ዛዲያ ሲርበን ይሁን እየጣመን የዚህን ገረገምብ ዋልካ እንበላዋለን፤ አንዳንድ ቀን ሆዳችን እስቲነፋ ድረስ። ተዚያ በኋላማ እ! እያሉ ማማጥ ነዋ! ድርቅ ብሎ የሚወጣው። እና ምን ቸግሮን! ነገም እንበላዋለን። አሁንም ባይኔ ላይ የሚንከራተተው የዚያ ዋልካ አምሮት ነው።»

«ሌላ ዋልካ ቢሆን አምሮትሽን?......» ጥያቄውን እንዴት እንደሚጨርሰው ገብርዬ ጠፋበት።

«ፈጥሞ! ለዚያ - ለዚያማ አንተን ተማስቸገር ብዬ በዚያው ሰሞን አንገረብ ወደ ታች በኩል ዋልካ ታለበት ሔደን ቀምሼ ነበር። ሊያስታውከኝ ደረሰ።

«ሌላው ታልሆነማ መቸስ እንሔዳለና!» የገብርዬ አነጋገር ትንሽ የቅሬታ ቃና ነበረበት። በደብረ ታቦር ሳይመለስ እስከ አሁን የቆየው ሳያንስ አሁን ሲጨመርበት ደግሞ ቴዎድሮስ ምን ይሰማዋል? ለዘመቻ ይፈልገው ይሆናል። በመልክተኛ እንዳያሳውቅ ምክንያቱ የሚያስቅበት ወይም አጉል ሆኖ የሚታይበት መሰለው። በኋላ እንዲያው መረዳቱ የሚሻል መሰለው። «እንግዲህ ስንቅሽን አሰናጂ!» አለ በመጨረሻ።

ከወይዘሮ ደብሬ በቀር ማንም ሳያውቅ ከሠራተኛ በለጡን ብቻ ይዘው አንድ ቀን ጧት በሳሙና በር ከጎንደር ወጡ።

እነ ገብርዬ፤ የት እንደ ሔዱ ሳይረጋገጥ ከጎንደር መጥፋታቸውን ጋረድና አክሊሉ ሲሰሙ ትንሽ እንቆቅልሽ ሆነባቸው። ወደ ደብረ ታቦር ከሆነ አንድያውን ጓዙን ነቅሎ መሔድ ነበረበት። ባለሟሎቹን ስንኳ አላስከተለም።

«እንግዲያው ደብረ ታቦር እንሔዳለን!» የሚል ሐሳብ አክሊሉ አቀረበ። ጋረድ በጥያቄ መልክ ትኩር ብሎ አየው።

«አዎ በቶሎ ደብረ ታቦር መሔድ አለብን!»

ጋረድ አሁንም ያልገባው እንደ መሰለ ቀረ።

«አየህ ገብርዬ ደብረ ታቦር ተሊለ፤ ተነሚሸቱ የት አባቱ እንደጠፋ ማወቅ አለብን። ደብረ ታቦርም ሔዶ እንደሆነ አንዱ ብልሃት ጠላትን ተዐይን አለማራቅ ነው። ከዐይን ተጠፋ፤ ተጀሮ ተራቀ መምጫው አይታወቅም ይባላል። ገብርዬ፤ ድንገት ተነሥቶ የሔደው ለነገር ቸኩሎ ተሆነ፤ እኛ ደሞ አገራችንን ማዘጋጀት ነው።

ሁለቱም ድንገት የመርካት ስሜት አድሮባቸው እየተያዩ ተሣሣቁ።

ለጊዜው ያሰባሰቡትን መጠነኛ ሠራዊት ይዘው ጋረድና አክሊሉ ደብረ ታቦር ሲደርሱ፤ ከተረጋጋ ከተማ ይልቅ በመንቀል፤ ወይም በመትከል ላይ ያለ የሚተረማመስ ጦር ሠፈር መስሎ አገኙት። ከመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ጥግ አንሥቶ፤ የጠቢቦች መንደር እየተባለ ወደሚጠራው ወደ ጋፋት በሚወስደው ረባዳ መሬት ላይ ብዙ ድንኳን ተገጥግጧል። ዳር ዳሩን ይዞ ቤቶች ይሠራሉ። በዚህ መካከል ከዥጉንጉርጉር የሕንድ ሐር የተሠራውን በወርቀ ዘቦ የተከፈፈው የቴዎድሮስ ድንኳን እንደ ድባብ ጉብ ብሏል።

በየድንኳኑ ውስጥና በየድኳኑ መካከል ሴቶችና ሎሌዎች የዕለቱን ሥራቸውን ያከናውናሉ። አብዛኛው ሠራዊት ግን በሠፈሩ አልነበረም። በርከት ያሉ ወታደሮች ተሰብስበው የሚታዩት ከቴዎድሮስ ድንኳን አካባቢ ነው። ጋረድና አክሊሉ ድንኳናቸው እስኪተከል ሰው ጠያይቀው ምክንያቱን ዐወቁ። ደጃች ዓለሜ፤ ወረኢሉ እንደገና ሸፍቶ፤ ዘመቻ ሔደዋል። ራስ እንግዳ ወደ አገው ምድርና ወደ አቸፈር ወርደዋል። ገልሞ ደሞ ብቸኛ ተልኳል። ሌሎች ጦር አበጋዞች በዚህም በዚያም የተነሣ ወንበዴ ለመምታት፤ የሸፈተ አገር ለመቅጣት በየሥፍራው ተበታትነዋል። የቀረው ግን፤ ጧት ጧት ቴዎድሮስን ተከትሎ ወደ ጋፋት እየሔደ አብሮ የሚመለሰው ማምሻውን ነው። ተዋበች ታመው ከአልጋ ላይ ከዋሉ ስነብተዋል።

ጥንት የጠቢቦች መንደር እየተባለች የእጅ ባለሙያዎች ይኖሩባት የነበረችው መንደር፤ በኋላ ከውጭ አገር የመጡ የወንጌል ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ተሰብስበው ሠፍረውበታል። ቴዎድሮስ፤ ጋፋት የፈረንጆች መንደር እንድትሆን ያደረጉት ጥንትም ማረሻው፤ ወገሉ፤ ካራው፤ ሌላውም ብረታ ብረት ይሠራበት እንደ ነበር ሁሉ አሁን ለሀገራቸው የሚመኙት የእጅ ጥበብ ማፍለቂያና ምሳሌ

እንድትሆን ነበር። ብዙዎቹ የውጭ አገር የእጅ ጥበብ ማፍለቂያና ምሳሌ እንድትሆን ነበር። ብዙዎች የውጭ አገር ሰዎች የሃይማኖትና የቀለም እንጂ ጥበብ ሙያ የለንም ብለው ለጊዜው ቢያጉረመርሙ በቴዎድሮስ ውትወታ፤ በውሃ ግፊት የሚሠራ የዕንጨት መሰንጠቂያ መንኮራኩር፤ የእህል ወፍጮ፤ የብረታ ብረት ማቅለጫ፤ የኖራ መሥሪያ፤ በያይነቱ አቋቁመውበት ከዚያ በፊት ሌላም ሌላም የእጅ ሥራ ማከናወኛ መሣሪያ፤ በያይነቱ አቋቁመውበት ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ ታይቶ የማያውቅ የሥራ እንቅስቃሴ የሚካሔድባት መንደር ሆናለች። መዘውሩ ሺሽከረከር፤ ብረት ማቅለጫው ምድጃ ሲንቀለቀል፤ ወናፉ፤ አሸንዳው ሲንፎለፎል፤ ብረት ከብረት ሲፋጭ፤ ቴዎድሮስ ይህንና ሌላውንም እንቅስቃሴ ሲመለከቱ፤ በሚደርስባቸው እንደ እውን ፍንትው ብሎ ይታያቸዋል። ቅልል ይለዋል። ሕልማችው እንድ እውን ፍንትው ብሎ ይታያቸዋል። ‹ፊታቸው እንደ ተኰላ ወርቅ ይፈካል› ይላሉ የሚያስተውሏቸው ሰዎች። እንደ ሁናቴያችው በዚህ እንደ ዋሉ ቢያድሩ የሚወዱ ይመስላል። ግን፤ ከታመሙት ሚሽታቸው አጠገብ ለመሆን ማምሻውን ወደ ሠፈር ይመለሳሉ።

ጋረድና አክሊሉ ሌላም ወሬ አገኙ። ገብርዬ ደብረ ታቦር አልመጣም ነበር። ‹የት አባቱ ተሠወረ? መንገድ ላይ ሰዎች ሰዎች አደጋ ጥለው ድራሹን አጠፉት? ምናልባት የሚሽቱን ጉድ ሰምቶ ጫካ ውስጥ አንቋት እንደ ተራ ሰው ተሠውሮ ለመቀመጥ ታገር ጠፋ? ወይንስ እንዳየው ሕልም ሸፈተ?› እያሉ ተጠያየቁበት።

ገብርዬ ከጎንደር ስንኳ መነሣቱን ቴዎድሮስ እንዳልሰሙ በበነጋው ካረጋገጡ በኋላ፤ ጭር ሲል ወደ ጓሮ ወጣ እያሉ ብዙ ተመካከሩበት፤ ተወያዩበት፤ ተከራከሩበት።

በመገድ ላይ ወንበዴ ገድሏቸው ከሆነ ምን ይጠቅማቸዋል? ምንስ ይጎዳቸዋል? በጠቀሜታ ረገድ አንደኛ እነሱን የጠረጠረበትን ምሥጢር ከቴዎድሮስ ጆሮ እንዳይደርስ ይቀራል። ሁለተኛ፤ ቴዎድሮስ አንድ ጎበዝ ጦር አዝማቹን ያጣል። በሌላ በኩል ግን፤ የገብርዬ ሠራዊት በሌላ ጦር አዝማች ሥር ከቴዎድሮስ ጋር ስለሚቀር፤ የሠራዊቱ ኃይል የሚቀነስበት አይሆንም። ተራ ሰው ሆኖ ለመኖር ተሠውሮ ከሆነ ውጤቱ ያው የሞተ ያህል ነው። በቴዎድሮስ ላይ ሸፍቶ ከሆነ ግን ነገሩ ድብልቅ መልክ ይኖረዋል። አንደኛ፤ የቴዎድሮስን ኃይል ይቀናንስባቸዋል። ገብርዬ ከንባሮቹም ሆነ አዲስ ከሚመለምላቸው ብዙ የሚከተለው ሠራዊት አያጣም። ቴዎድሮስን በቀላሉ ማሸነፍ ባይችልም፤ በእርግጥ ያዳክምላቸዋል። ግንኮ ገብርዬ በሸፍትነቱ እየበረታ ከሔደ የጋረድንም ዕድል ሊያውክ ይችል ይሆናል። ይህን ሲደርስ ያዩታል። አሁን አያስጨንቃቸውም።

«አሁንም የሆነ እንደሆነ ይሙትም በሕይወትም ይኑር፤ ይሸፍት ወይም ዐውቆ ይጥፋ፤ ጥቂት ጊዜ ካገኘን.... ጥቂት ጊዜ ካገኘን......ጥቂት ጊዜ ካገኘን» አክሊሉ መቋጠሪያው ግሥ እንደጠፋበት የቅኔ ተማሪ የመጨረሻውን ቃላት ደግሞ ደጋግሞ ወዝፎ ተወው......

ቴዎድሮስ፤ ከጋፋት ሲመለሱ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፉት ተዋበችን በማስታመም ስለሆነ አጋፋሪው ጋረድ ሊያቀርበው የቻለ ደብረ ታቦር በመጡ በአራተኛው ቀን ነበር። በሰንበት ቀን ወደ ጋፋት አይሄዱም። ከቤተ ክርስቲያን መልስ ቁርስ ከቀማመሱና ተዋበችን ከአጨዋወቱ በኋላ፤ ድንኳኑ በራፍ ላይ አቤቱታ ይሰማሉ። ባለ ጉዳይ ይቀበላሉ፤ እጅ ያስነሣሉ፤ አክሊሉን ወደ ኋላ በመተው ጋረድ ቀርቦ እጅ ሲነሣ የተቀየሙብትም የተቆጡትም ወይም የተደሰቱ ሳይመሉ፤ ወገብ ሰበር ላደረገ እጅ አነሣሡ፤ አንገታቸውን ቀልበስ በማድረግ አጸፋውን መለሱለትና የወገራ ግዛቱ እንዴት እንደሆነ ጠየቁት። ከተሾመ ጊዜ አንሥቶ ወገራን የረገጠው አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆንም፤ ከዚያው እንደ ቆዩ አገሩን ሰላም እንደሆነ አስመስሎ ተናገረ። ግን፤ እስከዚህም በጥሞና አላዳመጡትም። ከድንክ ወንበር ላይ ተቀምጠው ከጎናቸው የቆመው የሸዋውን ምርኮኛ ምኒልክን እየደባበሱ ሐሳባቸው ወደ ሌላ ርቆ የሔደ ይመስል ዐልፎ ዐልፎ በሹክሹክታ ያናግሩታል። ባጠገባቸው ያሉት ሊቀ መኳስ ዮሐንስ፤ ቆንስል ፕላውዴንና ሌሎች ጥቂት ሰዎች የቴዎድሮስን ሁኔታ የሚያንጸባርቁ ይመስላሉ። የወትሮው የሞቀ ጭውውት አልነበረም። ‹የሚሸቱ ሕመም እንደሆነ ለምን ድፍት ብላ አብሮዋት አይደፋም ለኔ ብሎ!› አለና በሆዱ ከአባቱ ጋር ወደ ራስ አሊ ግቢ ሲመላለስ፤ እሱም ለተዋበች አልተሰማውም። እንዲያውም ካሣ የአባቱን የደጃች ክንፉን ፈቃድ እየፈጸመ እንዳይቀየሙት ብሎም ይሁን፤ ከልቡ ለጋረድም በከበሬታ እየሰጠ አብረው ማደጋቸውን አክሊሉ ባሳደረበት የምኞት ዐይን፤ ከአሁን ደጅ ጥናቱን እጅ አነሣሡ በአጸፋው ከተደረገለት የንቀት አቀባበል ጋር ሲያስተያየው ቁጭት እንደ ሬት መርሮ ተሰማው.......

«ጊዜ? ጊዜ አልከኝ?» አለ ጋረድ ሁናቴውን ለአክሊሉ ከነገረው በኋላ ዐይነ ልቦናው ከቴዎድሮስ ፊት ትርዕይት ተተክሎ ቆይቶ ነበርና ድንገት ከሐሳቡ ነቅቶ።

«አዎ፤ የጥቂት ሳምንት ጊዜ» ሲል አክሊሉ ራሱን እየነቀነቀ መለሰለት።

«ለምኑ?»

«ለሁሉም ነገር ጊዜ ይበጃል። አየህ፤ ‹ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል› ነው። አሁንም የሆነ እንደሆነ የገብርዬ የት እንደ ደረሰ፤ ወይም ምን እንደነካው

አጥርተን ማወቅ አለብን። ከዚያ በኋላ ደሞ ባወቅነው ነገር መሠረት የሚያስፈልገን ለማድረግ......»

ጥቂት ከተጓዙ በኋላ፤ «ጊዜ? ጊዜ አልከኝ» ሲል ጋረድ በሕልም ዐይነት ተናገረ።

«አዎ! አዎ» አለ አክሊሉ መልሱን ከመሬት አፍርጦ የሚያወጣ ይመስል ደቅ ደቅ እያደረገ በመርገጥ። « ‹ቦ ጊዜ ለኵሉ› ብሏል መጽሐፉ።» ድንገት የመጣለት ጥቅስ ከጉዳያቸው ጋር ያለውን ግንኙነት ባይረዳውም፤ በግዕዝ በመነገሩ ብቻ አንድ ዐይነት ምሥጢራዊ እምነት እንድሚያሳድርበት ተሰማው። «አዎ! ‹ቦ ጊዜ ለኵሉ!› ለሁሉም ጊዜ አለው ሲል ነው። ለመሾም፤ ለመሻር ለሁሉም ጊዜ አለው። ሰው ጊዜ ካገኘ በጊዜው የፈለገውን ያደርጋል፤ ያገኛል ሲል ነው። ለመሆኑ በጥሩ ከብት ሽመጥጠህ ጎንደር ደርሰህ ለመምጣት ስንት ቀን ይፈጅብሃል?»

ጋረድ ጥቂት አሰላ። «ከብቱ ታልደከመብኝ አራት አምስት ቀን።»

«መንገዱ ላይ ተዘመድ ዘንዳ እየቀርየርክም ቢሆን። ድፍን ፎገራ እንፍራንዝ እንደሆነ ያንተው ነው።»

«ምህኛት አለ የምሔድበት?»

«ገብርዬ የሔደበትን ለማወቅ ነዋ! የሚያውቅ ቢኖር ወይዘሮ ደብሬ ናቸው።»

«ዛዲያ እሳቸው ጠባያቸው እንደምታውቀው ነው። አትንገሩብን ተተባሉ መቸ ትንፍሽ ይሉና!»

«ያች ባዝራ ልጃቸው ታውጣጣልሃ! ወዳጅህ አልነበረችም? አሁንም ቆንጠጥ ታደረካት ያው ነው።»

«እሷስ አታቅተኝም!» አለ ጋረድ በኩራት።

«ተዚያ በኋላ እናያለን፤ ጀግንነቱን ላንተ መላውን ለኔ ተውልኝ ልጅ ጋረድ!» አለው አክሊሉ በአረማመዱ እየተኮፈሰ።

ለረጅም ጊዜ ሳይነጋገሩ ዝም ብለው ወደ ድንኳናቸው ተጓዙ። እያንዳንዳቸው በየራሳቸው፤ ቂም ቂማቸውን በሚወጡበት በየራሳቸው የሐሳብ ባሕር ሰጥመው ነበር።

# ምዕራፍ አራት

ቴዎድሮስ፤ ማመን የሚያቅተው መርዶ የተነገራቸው ከራት ላይ እንደ ተቀመጡ ነበር። ራቱ ከዘወትሩ የተለየ ድግስ ባይኖርበትም፤ ተዋበች ትንሽ ሻል ብሏቸው እንደ ምንም ከአልጋ በመነሣት ገበታ ላይ ቀርበው ስለ ነበር የእጅ ሥራ ዕውቀት ለማስፋፋት የማዕድን ሥራ ለማቋቋም ስለሚመጡት የእንግሊዝ ዐዋቂዎች ከቆንስ ፐላውዴንና ከሊቀ መኳስ ዮሐንስ ጋር ያደረጉት ውይይት ትልቅ ተስፋ አሳድሮባቸዋል።

ቴዎድሮስ በዚሁ ሁሉ እንደ መርካት ብለው፤ ‹በካሣ ሞት አንዴ ሳሚኝ› እያለው ወዳጁን ስላቆላመጠው ወታደር ሲቀልዱ፤ ብዙ ጊዜ የማይለያቸው የእልፍኝ አሽከራቸው ገብቶ አፉን በመዳፉ ጋርዶ በጆሮዋቸው ሹክ አለ።

እንደገና እንዲነግራቸው በማለት አንገታቸውን ወደ ርሱ ሰበር አደረጉ። አሁንም በሹክሹክታ ነገራቸው።

«ለምን ጮህ ብለህ አትነግረኝም። ወይስ ከባድ ምሥጢር ነው?» ፊታቸው ባንዴ ተለዋወጠ። አሽከርዬው እንደ መደናገጥ እንደ መደናገር ብሎት ቆመ።

«ምንድን ነው የምትለኝ?» ሲሉ መልሰው ጠየቁት፤ የተናገረውን የሰሙ ቢሆንም ጆሮአቸውን ተጠራጥረው። ላመል ያህል ድምፁን ከፍ አድርጎ ለሦስተኛ ጊዜ ነገራቸው።

«ኧረ አንድ በሉኝ ይህን ሰው! ጤናም አልያዘው?» የቴዎድሮስ አነጋገር የጥያቄ ሳይሆን የተግሣጽ ዐይነት ነበር። ሁሉም እንደ ሚዳቋ ጆሮውን አቆመ። መጠጡም ምግቡም ላንዳፍታ ተረሳ። መዝናናቱ፤ ጭውውቱ በነፋስ እፍ ተብሎ የጠፋ መሰለ።

«ምንድን ነው አባ ታጠቅ?» በማለት ከአጠገባቸው ከሁለተኛው መሶብ የተቀመጠው ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ጠየቀ።

«ይቀኘብራል!» አሉ ቴዎድሮስ እጃቸውን በማወራጨት።

«ኧረ እውነት ነው ጃንሆይ!» አለና አሽከርየው በመጨነቅ እጁን አፋተገ።

«ገብርዬ!» የቴዎድሮስ አነጋገር የጥያቄ ሳይሆን የመረገም አጋኖ ነበር።

የእልፍኝ አሽከሩ በማረጋገጥ ራሱን ላይና ታች አወዛወዘ።

ጸጥ ባለው ድንኳን ውስጥ የተዋበች ድምፅ ጎልቶ አስተጋባ። «ምን ሆነ ገብርዬ?»

«አሆሆ! ጆሮ አይሰማው የለ!» ቴዎድሮስ ከመገረም ሌላ፤ የሰሙት ነገር ከጆሮዋቸው እንዳይገባ ለመከላከል ይመስል ሁለት ጆሮግንዳቸወን በመዳቸው ደገፉ።

ተዋበች ዘንበል አሉና ዳበስ አደረጉዋቸው። «ምንድን ነው፤ የኔ ጌታ?»

«አሆሆ! ገብርዬ ሸፈተኮ ነው የሚለኝ!» አሉ ቴዎድሮስ ድንገት እንደ መወራጨት እየሞከራቸው። እንደ መነሳት ቃጡና መልሰው ተቀመጡ። በድንኳኑ ውስጥ ንግግር አይሉት ትንፋሽ አንድ ዐይነት መስገምገም አስተጋባና መልሶ እርጭ፤ ጸጥ አለ። ላንዳፍታ ዝምብ ሲበር የሚሰማው መሰለ። አንገቶች በያሉበት በመሶብ ላይ አቀረቀሩ።

ተዋበች ማባበልም መጨነቅም በሚገልጽ አኳኋን የባላቸውውን ክድን ጨበጥ አደረጉ።

«አንተ ደሞ እያደር የምትሠራውን አታውቅም! ስንት ጊዜ እንገርኩህም ሲሉ አስከርዬውን ተቆጡ። ቴዎድሮስን ሊያስቆጣ የሚችል ጉዳይ ሲሆን፤ አስቀድሞ እርሳቸውን እንደሚያማክር ደጋግመው ነግረውት ነበር።አለዝበው የሚያቀርቡበት መንገድ ያውቁታል።

«መቸ አጣሁት!» አለ አሽከርዬው በይቅርታ አጠያየቅ ወገቡን ሰብሮ፤ አንገቱን ደፍቶ። «ቢጨንቀኝ ነው፤ እጅግ የሚያጥድፍ ከባድ ጉዳይ ስለመሰለኝ።

«ደግ አረገ! እውነቱን ነው» የቴዎድሮስ ሰውነት በመኮሳተር ፍርጥምጥም አለ። «በመጥፎ ወሬ መበርገግ ከያዝኩማ፤ ምኑን ሰው ሆንኩት! እንኳን ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ እንኳን ትልቅ ማድረግ ቀርቶ ለራሴውም ርባና የለኝም ማለት ነው። ብቻ ነገሩ አስገረመኝ፤ የማይታመን ሆነብኝ እንጂ!» መልሰው ትክዝ አሉ። «ግን፤ ገብርዬ ለመሆኑ ተረጋግጧል?»

«አዎ! አዎ!» አለ አሽከርዬው፤ አሁንም መዳፉን እያፋተገ። «ወሬውን ያመጣው መልክተኛ አሁንም ተውጭ አለ። ተርሱም በኋላ ሌላ ሰው መጥቶ ገብርዬ መሸፈቱን ላባ ታጠቅ ንገር ብሎ ሔደ። ሰውዬው እንደ ተናገረው ነጋሪትም እያስመታ ነው አሉ።

«ለመሆኑ የት ላይ ነው?»

«ጭልጋን ዐልፎ ወይኒ ላይ።»

«እህ! ተሚሽቱ አገር መግባቱ ነው?» ቴዎድሮስ በመገረም እንደ መንከትከት ከቃጣቸው በኋላ በትካዜ ተዋጡ። አገጫቸውን በቀኝ መዳፋቸው ላይ አስደግፈው፤ በማመንና ባለማመን መካከል የሚሟገቱ ይመስል ላመል ራሳቸውን እያወዛወዙ ቆይተው፤ «አሆሆሆ! ገብርዬም? ገብርዬም?» የተነጋገሩት ከራሳቸው ጋር ነበር። ድምፃቸው ለሌሎቹ መሰማቱ አልታወቃቸውም። በራሳቸው በትዝብት ባሕር ሰጥመው ነበር። ድንገት መንጥቆ ያወጣአቸው የደጃዝማች ቢሆነኝ ድንፋታ ነበር።

«እኔ ያንተ አሽከር፤ ያንተ ቡችላ! ያንን ያህያ፤ መጅ አሽክሜ አምጥቼ ከፊትህ ባላንበረክከው እኔ ቢሆነኝ ሱሪ አላጠለኩም! ሒዲ በለኝ! ላከኝ አሁኑኑ!» እያሉ ቆመው መፎካከር ሲጀምሩ በድንኳኑ ውስጥ የፌዝ ሁካታ ተነሣ።

ቴዎድሮስ እንደማይልኩዋቸው፤ ቢዘምቱም ገብርዬ ድል አድርገው እንደማይመለሱ ሁሉም ያወቁት ነበር። ደጃዝማች ቢሆነኝ፤ በጎልማሳነታቸው ጎበዝ የነበሩ ቢሆንም፤ አሁን ዘመቻው፤ ወደ ሰባ ዓመቱ ጊዜ የተጠጋቸው ሽማግሌ ናቸው። ሰውነታቸው ደካክሟል፤ የተንዠረገገ ገብስማ ጺማችውን እያሻሹ በአደባባይ በሰው መካከል ሲገኙ፤ ለሽምግልናና ለምክር የተሠየሙ ይመስላሉ። ግን በቅርብ የሚያውቋቸው ብዙ ሰዎች ለጨዋታ እንጂ እስከዚህም ለቁም ነገር አይመድቧቸውም። እንዲያውም፤ በነገራቸው ላይ ውሸት ስለሚጨምሩ ተረብና ፉከራ ስለሚያበዙ፤ በትንሹ በትልቁ «እኔ የካሣ አሽከር» ማለትን ፈሊጥ ስላደረጉት፤ «የሽማግሌ ቀላል» እያሉ የሚያሚቸው አሉ። ብቻ በክፋት የሚያስባቸው የለም።

ቴዎድሮስም ቢሆኑ፤ ደካማ ጠባያቸውን በማወቅ ቁም ነገር ላይ ባያውሏቸውም፤ ቋራ በሸፍትነት ሳሉ የሠሩላቸውን ውለታ በማስታወስ ሽምግልናቸውንም በማሰብ፤ ፍሬ ፈርስኪ ጨዋታቸውን ዐልፎ ዐልፎ እየተዝናኑበት ለስሙ ያህል የደጃዝማች ቀሚስ ሰጥተው እንደ ፈለጉ በአጠገባቸው እንዲገኙ ፈቅደውላችዋል።

ቴዎድሮስ፤ በደጃች ቢሆነኝ ሁናቴ ትንሽ ፈገግ አሉ። «ባትነግረንም ስላንተ ታማኝነት እናውቃለን። ግን ገብርዬን አንተ ነህ.......?» ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ራሳቸውን ነቀነቁ።

«እኔ ቢሆነኝ! እኔ ያባ ታጠቅ አሽከር! ያንን ፈ ፈ......» እየተንቆራጠጡ ቃሉን ለመጨረስ ሲቃጡ፤ ቴዎድሮስ በድንገት አቋረጧቸው። የቃሉ መጨረሻ ገብቷቸው ነበር።

«ተው! ተው በል በቃህ!» አፈጠጡባቸው። «አሁን ምንም ጠላት ቢሆን ገብርዬ በማንም አፍ የሚሰደብ ሰው አይደለም። ከፊቱ ላይ የማትተነፈውን ለም ትወሽከታለህ?»

«እኔ ያንተ አሽከር?» አሉ ደጃች ቢሆነም፤ ዐመል ሆነባቸው አሁንም እንደሚፈክር ሰው ከተቀመጡበት እንደገና ብድግ አለ።

«እኮ በቃህ!» በማለት ቴዎድሮስ ከፍ ባለ ድምፅ ተቆጡ። «ደግሞስ ዘር ቆጥሮ መሳደቡ ምን ዋጋ አለው መሰላችሁ?» አሉ ድምፃቸውን መለስ አድርገው። «እኛ ጥቁ፤ ወይም የቀይ ዳማ፤ ቀይ እያልን የጨዋ ዘር፤ የምንቴስ ልጅ እያልን እንለያለን። ፈረንጆች ደግሞ ሁላችንንም በመደዳ አንድ አድርገው ነው የሚቆጥሩን!»

‹ደጃዝማች ቢሆነኝ፤ መጫወቻቸው እንደ ተወሰደበት ሕፃን አቀርቅረው የስርቆሽ እያዩ ዝም ብለው ተቀመጡ። ድንኳኑ ጸጥ፤ ረጭ አለ። ቴዎድሮስ በየገበታቸው ዙሪያ የተቀመጡትን ባለሟሎቻቸውን ተራ በተራ በዐይናቸው ቃኙ። ከዚያም ለጥቂት ጊዜ ትክዝ ብለው ከቆዩ በኋላ፤ በታከተ ስሜት ከተቀመጡበት እየተነሡ «ተናንተ ደሞ ማን ይሆን የሚከደኝ?» አሉና ወደ እልፍኛቸው አመሩ። ተዋበች ሲከተሉዋቸው፤ ሌሎችም መኳንንት ገበታውን እየተዉ ወጡ።

ተዋበእች የባላችውን የንዴት፤ የደስታ፤ የሐሳብም ሆነ የትካዜ ስሜት እንዴት ማለዘብ እንደሚችሉ ከብዙ ዓመታት አብሮ መኖርና ማስተዋል ዐውቀውታል። ለምሳሊ፤ በሽፍትነት በነበሩበት ጊዜ በኃይል ሲናደዱ፤ ከምንጭ ይሁን ከእንስራ እንደ ምንም ከአቅራቢያ ባገኙት ውሃ ፊታቸውን ረጫጭተው፤ አፋቸውን ተጎማምጠውና ትንሽ ተጎንጭተው፤ «እፎይ! እፎይ!» ይሉና ቀለል ይላቸዋል። ከውስጣቸውም የሚቃጠለን እሳት ጨርሶ ባያጠፋውም በረድ የሚያደርጋቸው ይመስላል። ይህንን የተገነዘቡት ተዋበች የባላቸው ቁጣ በገነፈለ ጊዜ ከሰው መካከል ገለል አድርገው ይወስዱና ፊታቸውን በውሃ ለቅልቀው የሚጎነጩት ይሰጧቸዋል። ከዚያም መቀነታቸውን እያላሉ ጨርሶ የሚያበርዱበት ሌላ አቀራረብ አላቸው..... ትካዜ በተጫናቸው ጊዜ ደግሞ፤ ሊያቃልሉላቸው የሚሞክሩበት መንገድ ከዚህ የተለየ ነው። በመጽሀፍ ቅዱስ እንደ ተጠቀሰው እንደ ሳምሶን፤ የስሜት ኃይላቸው ከጸጉራቸው ላይ ያለ ይመስል፤ ወይም ጋማውን ሲደባብሱት ገራም እየሆነ እንደሚሔድ አንበሳ በለዘብታ በሹክሹክታ እያጨዋወቱ፤ ሹርባውን ፈትተው እንደገና ይሠሩላቸዋል። ወይም መፈታታት የጀመረውን ያስተካክሉላቸዋል።

ቴዎድሮስም ትካዜያቸው መለስ እያለ «ኧረ ተይ! ነጨሽኝ እኮ» እያሉ በመቀለድ ብድራቸውን መቆንጠጥ ይጀምራሉ።

አሁን ግን አልሠራም። ተዋበች የባላቸውን ሹርባ አስተካክለው ከጨረሱ በኋላ፤ በሐሳብ እንደ ተዋጡ መቅረታቸውን ሲመለከቱ፤ «ኤጭ እቴ! ምን መጨነቅ ነው! የሽፈተ እንደሆነስ ዛዲያ!» አሉ ‹እባክህ ፈጥሪ የዓላማውን የምኞቱን ቅንነት አይተህ እርዳው። ተማለደው፤ አትጣለው፤ ሐሳቡን ላልተረዱት አንተው በጥበብህ ከሥትላቸው› እያሉ።

«ማን? እኔ ነኝ የምጨነቀው? አላወቅሽኝም ልበል ተዋቡ? ወይስ እያደር ደሞ ዘነጋሽኝ? ለምን ሞት ራሱ ሥጋ ለብሶ አይመጣም? እኔ የመይሳው ልጅ!» አነጋገራቸው ግን፤ የጉራ ዐይነት ሳይሆን የቁርጠኝነት ርጋታ ነበረት። «ብቻ ነገሩ አስገረመኝ እንጂ!» አሉ እራሳቸውን እየነቀነቁ።

«ምኑ ነገር የኔ ጌታ?»

«እህ! የገብርዬ መሸፈት ነዋ! መላ መኳንንቴና ሠራዊቴ ቢከዳኝ አይደንቀኝም ነበር። ግና እንደራሴው የማምነው ገብርዬ? ራሴ በራሴ ላይ የሸፈትኩ ነው የመሰለኝ። ምን አረገኝ ብሎ ይሆን?» ሲሉ ራሳቸውን ጠየቁና መልሱን አሰላሰሉ። «እንደ እንግዳ ራስ ስላልኩት ተቀይሞ ይሆን? ግን ተስሙ ምን አለው? የጦር አዝማች ያረኩት እሱን ወይንስ ታንጉትን ምክንያቱ ሳልገልጽለት አሳድጌ ስለ ዳርኩለት፤ ለብቻም ስለማነጋግራት ሌላ ነገር መስሎት? እንዲህማ ታሰበ በጣም የዋህ ነው።»

ለሁሉም የገብርዬ ጠባይ እንደሚያውቁት ፊት ለፊት ይጠይቃቸው ነበር እንጂ አኩርፎ ሹልክ የሚል ሰው አልነበረም። ከጀመሪያው ያመኑትም በዚህ ግልጽነቱ ነበር። ዕድሉን ከእርሳቸው ዕድል ለማቆራኘት መጥቶ የመጀመሪያ የተገናኛቸው ጊዜ ትዝ አላቸው.....

በራስ አሊ ላይ ሸፍተው፤ መላውን ቋራ፤ ጫዎን፤ አዳኝ አገርን እስከ አለፋ ጣቁሳ ድረስ ይዘዋል። አንድ ቀን ማምሻ ላይ ወታደሮች አንድ ሰው ያቀርቡና እጅ ይነሣል። ‹ለምን በዚህ ሠፈር መጣህ?› አሉት በጥርጣሬ መልክ።

‹ዝናህን ሰምቸ ታንተ ዘንድ ለማድር!› ሲል ደፈር ባለ አነጋገር መለሰላቸው።

‹አገርህ የት ነው?›

‹ዙራምባ!›

‹ጋይንት?›

‹አዎ! ደብረ ታቦርም እወለዳለሁ!›

‹ዛዲያ ተጋይንት ነው እዚህ ድረው የመጣኸው? ወራዬንስ እንዴት ሰማህ?› ትኩር ብለው ተመልከቱት። ‹ደብረ ታቦርም፤ ጋይንትም እነራስ አሊ ግዛት ነው። ተነሡ ተልከው?....› እንደ ዋዛ ነበረ። ሰውዬውን ግን ከቆመበት ያነጠረው መሰለ።

‹እኔ ገብረ ሕይወት ነኝ፤ ለነ አሊ የምሰልለው፤ ጎበዝ አገኘሁ መስሎኝ ነው እንጂ!› አለና ዙሪያውን ያለውን ወታደር ሁሉ ከምንም ሳይቆጥር ጣጥሶ ለመሔድ ወደ ኋላ ዞረ።

‹ቆይ እስቲ!› አሉት በመገረም። በሐቀኝነት የሚፈታተኑ ይመስል ላንዳፍታ ተፋጥጠው ተያዩ። ‹አምኜሃለሁ፤ ገብረ ሕይወት ነው ስሜ አልከኝ? እኔ ደሞ ተዛሬ ጀምሮ ‹ገብርዬ ብየሃለሁ።›

ከዚያስ ቀን ጀምሮ ሐቅንና እምነት አንድም ቀን ቅንጣት ሳያጓድል የኖረ ሰው ነበር......

«አሆሆ! ጉድኮ ነው!» አሉ ቴዎድሮስ ከሐሳባቸው እንደ ተመለሱ፤ ሳይታወቃቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው።

«አሁን እስቲ ዐረፍ በለ የኔ ጌታ። ማንኛውንም ነገር ነገ እንደርስበታለን፤ ጧት መኳንንቱ እንዲሰባሰቡ ላድርግ?» ሲሉ ተዋበች ጠየቋቸው።

ቴዎድሮስ በአወንታ ራሳቸውን ነቀነቁ። አሁንም ከሐሳብ ትካዜ መወጣት አልቻሉም።

በበነጋው ጧት፤ በደብረ ታቦር የሚገኙት ጦር አበጋዞች ተሰብስበው ጉባኤ ተደረገ። ቴዎድሮስ ፊታቸው ጠውልጎ አስተያየታቸው ታክቶ በዐይኖቻቸው ዙሪያ ቀጫጭን መሥመሮች ወጥተው፤ ዕረፍትና ዕንቅልፍ አጥተው ማደራቸው ያስታውቅ ነበር። አሁንም ቢሆን በገብርዬ ላይ ስለሚደረገው ዘመቻ ጉባኤ መሰብሰብ ራሱ የባሰውን አሳዝኗቸዋል፤ አስጠልቷቸዋል። «በገብርዬ ላይ ከሌላው ሰው ጋር ልምከር?» ሲሉ ከራሳቸው ጋር ተገረሙ። ነገር ግን፤ የመጨረሻው ውሳኔ የራሳችው ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስለ ማንኛውም ከፍተኛ ጉዳይ ከሌሎች ጋር መመካከር ተገቢና አስፈላጊ መሆኑን እየተገነዘቡት ሔደው ነበር።

በአብዛኛው የሊቀ መኳስ ዮሐንስ ሐሳብና ምክር ነው። ስለ እንግሊዝ ምክር ቤት ተርኮላቸው ነበር። የፓርላማ አሠራርና የዲሞራሲ ፍልስፍና እምብዛም በጥልቀት ባይገባቸውም የመመካርን ጠቃሚነት ተገንዝበውታል። መሠረተ ሐሳቡ ለኢትዮጵያም አዲስ አይደለም። ‹ከአንድ ፈጣሪ ብዙ መካሪ›፤ ‹አንድ አይነድ፤ አንድ

አይፈርድ› የሚሉት ምሳሌዎች የሚያረጋግጡት ይኸንኑ ነው። የሚጎድለው ሥርዓትና መልክ ማሲያዝ ነው።

ሁሉም ከንፈሩን የሚነክስ መስሎ ቢታይም፤ በጉባኤ ላይ ከተቀመጡት መኳንንት ምናልባት በልባቸው የተደሰቱ ይኖራሉ። ጀግንነቱና የቴዎድሮስ በጣም ቅርብ መሆኑም ያስቀናቸው ብዙ ናቸው። መውደቁን አይጠሉትም። ከዚህም የገብርዬ መወገድ ክፍት የሹመት ቦታ ስለሚፈጥር፤ የእርሱንም ባይሆን፤ በእርሱ የሚተካውን ሰው ሹመት የሚመኝና ለማግኘትም ተስፋ የሚያደርገው ብዙ ነው።

የምክክሩ ዋና ጉዳይ በገብርዬ ላይ ስለሚዘምተው ጦር መሪ ነበር። ቴዎድሮስ፤ ራሳቸው እንዲያዘምቱ የቀረበውን ሐሳብ ብዙዎቹ አልተስማሙበትም። ቴዎድሮስ ሐሳቡን ለመነሻ ያህል አቀረቡት እንጂ፤ ሌላ የመጨረሻ ምርጫ ከሌላቸው በስተቀር ቆርጠው እንደማይዘምቱ ይሰማቸው ነበር። በገብርዬ ላይ መዝመቱን እንዳንድ ነገር ተጸየፉት።

‹ደጃች ብርዬ እንዲዘምት› የሚል ሐሳብ ቀረበ። «አንተስ ምን ይመስልሃል? ብርዬ» ሲሉ ቴዎድሮስ መለሱ።

«ጌታዬ እንዳለ» ሲል መለሰ። ግን እምቢ ላለማለት እንጂ የሚጓጓለት ዘመቻ አለመሆኑን ከአነጋገሩ ያስታውቅ ነበር። ቴዎድሮስም ቢሆኑ፤ ስለ ተጠቀሰ ጠየቁት እንጂ የደጃች ብርዬን መዝመት ከልባቸው የሚደግፉት አልነበረም፤ በሁለቱ ምክንያት። አንደኛ፤ ሁለቱን የቅርብና የልብ ጓደኛሞች እንዲዋጉ ማድረግ በደል መስሎ ታያቸው። በሌላ በኩል፤ ከገብርዬ ወዲያ የሚያምኑት ካልነበራቸው ብርዬ በዚያው ከጓደኛው ጋር ቢቀላቀልስ የሚል ቅንጣት ጥርጣሬ ተሰማቸው።

«የለም አንተ እንዲያውም ወሎ ዘምተህ፤ መሐመድ በሽርን አይቀጡ ቅጣት ብትቀጣልኝ ነው የሚሻለው» አሉ ቴዎድሮስ።

የሌሎችም መኳንንት ስም በየተራ ተጠቀሰ። ግን በሚጠቀሱት ሰዎች ላይ ጉባኤው በቀላሉ ከስምምነቱ ለመድረስ አልቻለም። አንዳንዶቹ ራሳቸው ለመዝመት በመፎካከር የሌላ ስም ሲጠራ ልዩ ልዩ ምክንያት እየሰጡ ይከራከራሉ። ሌሎች፤ የሚጠሉት ሰው ከገብርዬ ጋር ሲዋጋ እንዲሞትላቸው፤ ደጃዝማች እገሌ ቢያዘምት እያሉ አስተያየት ይሰነዝራሉ። ሌላው በሌላ ምክንያት ይቃወማቸዋል። እንዲህ እያለ የብዙ መኳንንት ስም ተነሥቶ ከተጣለ በኋላ የጋረድ ስም እንደ ዋዛ ተጠቀሰ።

ጋረድ፤ እንደ ሌሎቹ ለጉባኤው ይታደም እኒ ወደ ዳር ጥግ ይዞ ነበር የተቀመጠው። ሌሎች ሲናኮሩ፤ በሆዱ እያፌዘባቸው በትዝብት ይመለከት በስተቀር

አንዳችም አስተያየት አላቀረበም። በስብሰባ ደረጃ ከእነርሱ ጋር መከራከሩን እንደ ውርደት በመቁጠር ብቻ ሳይሆን አንደበቱን አዳልጦት ነበር እንዳይስት በመሥጋት ጭምር ነበር። ስሙ ሲጠቀስ ሁሉ በዐይኑ ይፈልገው ጀመር። ቴዎድሮስም አንገታቸውን ሰገግ አድርገው ዙሪያውን ቃኙ። ሳይስበው ከተቀመጠበት ተነሣ። ‹ማን ያውቃል? ምናልባት አንተ ዝመትበት ትባል ይሆናል› ሲል አክሊሉ ቀደም ሲል የገምተ ቢሆንም፤ ጋረድ በበኩሉ እስከዚህም ተስፋ አድርጎ ስላልነበረ በሁኔታው ድንገተኝነት ትንሽ ተደናገረ።

ጋረድ፤ የቴዎድሮስንና የሌሎችን መካሪዎች ፊት ሲመለከት፤ ክርክራቸው ከእርሱ ላይ እንደሚያበቃ ታወቀው።

ቴዎድሮስ፤ ለምን በጋረድ ላይ እንደ ወሰኑ ምክንያቱ ለራሳቸው ግልጽ አልነበረም። ምናልባትም አማራጭ ስላጡ ይሆናል። ምናልባትም የደጃች ክንፉ ውለታ ሳይታወቃቸው ተሰምቷቸው ሌላ የተሻለ ሹመት ለመስጠት መፈተናቸው ይሆናል። ወይም ደግሞ፤ ያመኑትን ከዳተኛ በሚጠረጥሩት ዘመድ ማጋጠሙ ልዩ የስሜት ትርጉም ሰጥቷቸው ይሆናል። በገብርዬ መክዳት ሕሊናቸው በጣ ተነክሮ ስለ ነበር፤ ስለ ምርጫቸው የምክንያት ምርምር ለማድረግ አላስቻላቸውም።

«በል እንግዲህ ተዘጋጅ!» ብለው ጉባኤውን በተኑ።

በሰፈሩ ለጋረድ የሚደረገው አመለካከት በአንድ ጊዜ ተየቀረ። መኳንንት ሥራዬን ብለው ሰላምታ ይሰጡታል፤ ያነጋግሩታል፤ ተራው ወታደርና ነፍጠኛ ብድግ እያለ እጅ ይነሣዋል፤ ወይዛዝርት አንገታቸውን አቀርቅረው የጎሪጥ እያዩ ስለ እርሱ ይንሾካሾካሉ። ከቴዎድሮስ ቀጥሎ የሁሉ ዐይን የሚያስተኩበት ሆነ። ከዚህም የበለጠ እንደሚሆን ተሰማውና ትከሻውን ገልበጥ፤ ደረቱን ነፋ ቋንጃውን ሳብ እያደረገ መራመድ ያዘ።

ድንኳን ብዙ መኳንንት ያዘወትረው ገባ። እንኳን ደስ አለህ። ለማለት ምክርና አስተያየት ለመስጠት፤ ለመሸኘት፤ ጎራ የሚለው በዛ። እንግዶቹን የሚጋብዝበት ግን አልቸገረውም። ከዚህም ከዚያም የተውጣጣ የአንድ ፊታውራሪ ሠራዊት ተሰጥቶት ስለነበር፤ ዘመቻ ከመነሳቱ በፊት የሚያስገባበት ፍሪዳው፤ እንጀራው፤ ጠጅ ጠላውና አረቂው ከቴዎድሮስ ተልኮለታል። በተጨማሪም በከረጢት የተቋጠረ ጠገራ ብር የግምጃ ቤቱ ሹም ራስ አምጥቶ ሰጥቶታል። ይህም ምኞቱን ሰማይ አደረሰበትና፤ ‹እኔም ጉርሻ የምልክበት ቀን ይመጣል› ሲል አሰበ። የራሱ መከበር ብቻ ሳይሆን ሌሎቹን ለክብር ሲያበቃ ታየው።

«እንዲያው ግን፤ ነገሩ ሁሉ እንዲህ መሳካቱ ደንቆኛል» አለው ጋረድ አክሊሉን። በበነጋው ጧት ሊዘምት እንደ ዛሬ፤ የተመደበለትን ሠራዊት ግብር አብልቶና ጥቂት መኳንንት በድንኳኑ ውስጥ ሲጋብዝ አምሽቶ ከሸኘ በኋላ፤ ይዞዋት ከሚዘምተው የጭን ገረዱ ጋር ሦስቱ ብቻቸውን ነበሩ። ጋረድ በዕድሉ የመደሰቱን ያህል በመጠጡም ሞቅታ ተሰምቶት በአስቾኳይ አፈላልጎ ያስመጣትን የጋሜ ቆንጆ አክሊሉን ሳያፍር እየደባበሰ ያሽኮረምማታል። ሌላ ጊዜ እንደዚህ ያለ ሁናቴ ሲመለከት አክሊሉ ብርቱ ሠቀቀን የሚሰማው ቢሆንም አሁን ግን ደንታ አልሰጠውም። እሱም በበኩሉ ሞቅ ብሎት በራሱ ርካታ ተዝናንቶ እንደ ዋዛ ይመለከታቸዋል።

«እመነኝ አላልኩህም?» አለ አክሊሉ በመኩራራት።

«አልተጠራጠርኩም ነበር። ግን ዋና ቡዳ ነህ አክሊሉ!»

«ተአምረኛ ማለቱ አይሻልም?» አለው አክሊሉ። በሐሳቡ ግን ምንም ዐይነት ተአምር እንደሌለበት ያውቀው ነበር። ቅኔ እንደ መድረስ በማሰብ፤ በማሰላሰል፤ ለክፉም ሆነ ለደግ አእምሮ በማስጨነቅ፤ በማስጠበብ የተገኘ ውጤት ነው።

ስለ ገብርዬ መሠወር የአክሊሉ ምርምር መጀመሪያ ያተኮረው፤ ሸፍቷል በሚለው ጥያቄ ላይ ነበር። በጥሞና ሲይስበው የገብርዬ መሸፈት እውነት አልመስለው አለ። ሰዎች እንደ ጠባያቸው የአሸፋፈት ዐይነት አላቸው። አንዳንዱ አንገረብና ቀሃ ወንዝ እንዳለፈ ገና ምኑንም ሳይዘው፤ ድል አድርጎ እንደ ማረከ ያህል ነጋሪት እያስጎሰመና እያስፎከረ ጉራውን ይለቀዋል። አንዳንዱ በሥውር ይወጣና አመቺ እስኪመስለው ድረስ ረጅም ጊዜ አድፍጦ ይቆያል። እንዲያውም ካልተመቸው፤ ማምለጫ ራሱን ማዳኛ እንዲሆነው ‹ገዳም ገባ፤ መነነ› እያለ ያስወራል።

ገብርዬ፤ እንደ መጀመሪያው ዐይነት አጉል ጉረኛ፤ እንደ ሁለተኛው ዐይነት ፈራ ተባ ባይ ባይሆንም፤ አክሊሉ ጠባዩን እንደ ገመተው መሸፈቱ ወይም አኩርፎ በረሃ መግባቱ እንዲታወቅበት ማድረጉ የማይቀር ነበር። በሽፍትነት ጊዜ አጋር የሚገኘው፤ ከቅርብ ባልንጀራ ብቻ ሳይሆን ከባላ ጋራ- ባላጋራ ነውና፤ ቀድሞ የሚያማክረው፤ ያም ቢቀር በረሃ ከገባ በሁላ በመላክተኛ የሚያስጠይቀው ሰው ቢኖር፤ በሹመቱ ምክንያት በቴዎድሮስ ላይ የተከፋው ጋረድ በሆነ ነበር። ዛዲያ ካልሸፈተ፤ ምን በላው? ምን ዋጠው? የት ደረሰ?

አክሊሉ፤ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ አእምሮውን ሲያስጨንቅ ቆይቶ ጋረድ ከወይዘሮ ደብሬ ልጅ ፍንጩን ካመጣለት በኋላ፤ ወሬ ማዛመቱ መልእክተኛ

በገንዘብ ገዝቶ እንዲናገር ማድረጉ ቀላል ነበር። ከዚያ በኋላ ለሚሆነው በጣም እርግጠኛ አልነበረም። ብቻ፤ ገብርዬ በጀግንነቱ ስለሚፈራ፤ እንዲወጋው የሚላክበት አዝማች ነገሩን ሳያጣራ ተሽቀዳድሞ አደጋ ይጥልበታል ብሎ ነበር ተስፋ ያደረገው። አሁን ግን ነገሩ የበለጠ ሠመረ።

«ቡዳም እኮ በሥውርና በረቂቅ ኃይል ያሰበውን የሚሠራ ተአምረኛ ማለት ነው!» አለ ጋረድ አሁንም እንደገና በአድናቆት። የገብርዬ መሸፈት በሠፈሩ እንዲወራ ለቴዎድሮስ እንዲነገር ከመመካከራቸው በስተቀር የአክሊሉ ብልሃት እንደዚሁ ግልጽ ሆኖ አልታየውም ነበር።

«ለአንተ ለወዳጄ እንኳንስ ቡዳ ሰይጣን ብሆን ምንተዳዬ!» አለው አክሊሉ በሞቃት መኩራራትና መዝናናት እንደ መንጠራራት እየቃጣው።

«ሲኦል ትወርዳለሃ!»

«ፈረሴን ይገፍ ነዋ!» እንደ ፈረስ የመሰለ፤ እርሱን ራሱን መሆን ጋረድ አልገባውም።

«ብቻ ውጊያው የሚያሠጋን ይመስልሃል!» ሲል አክሊሉን ጠየቀው።

«የምን ውጊያ አመጣህብኝ? ከኮረዳው ጋር ተቃቅፎ ሲያንቀላፋ ነው የምንደርስበት። እንዲያውም እሱን ለኔ ተውልኝ እስቲ። ኮረዳውን ሽልሜሃለሁ፤ ለዚፍ ድላል» አለ አክሊሉ፤ ጋረድ በሚያሻሻት ልጅ ላይ ዐይኑን በቀልድ እያጉረጠረጠ።

«ችግሩ ገብርዬ ላንተም ሆነ ለኔ አልተተወም።»

«እንዴት?»

«ተነሕይወቱ አምጣልኝ ተብያለሁ።»

«ተነሕይወቱ? እህ - እህ - እህ» አክሊሉ በማሾፍ እንደ መንከትከት አለ። «እኛ ገብርዬን በሕይወት ስናስረክበው፤ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ የኛን ጭንቅላት ደሞ በሰፌድ ልናቀርብለት! እንደዚህ ያለውን ጅል ነገር ለጅላጅሎቹ ይንገረው።»

«ዛዲያ ምን እናግር ትላለህ?»

«ወቸው ጉድ! ቀላል ነው። እጁን አልሰጥም ብሎ ሲዋጋ ሞተ።»

«ሲዋጋ ሞተ!» ጋረድ ራሱን እየነቀነቀ ተቀበለው።

«ሲዋጋ ሞተ!» አሉ እንደ ዝማሬ ሁለቱም ባንድነት።

በበነጋው ጧት፤ ጋረድ ሺህ ሠራዊት አሰልፎ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጋሪት እያስጎሰመ ከደብረ ታቦር ሲነሣ፤ ፈረሱን ባንድ ጊዜ መውጣት አቅቶት እርካቡን እንደ ረገጠ ሁለት ሦስት ጊዜ ያህል፤ ላይ ታች ሲል አክሊሉ ተመለከተውና ከት ከት ብሎ ሣቀበት።

«ምነው?» አለ እሱም ሳይታወቅበት እየሣቀ።

«ምን ያህል ወገብህ ደቆ ቢያድር ነው ወንድሜ?» አለው። የአክሊሉ አነጋገር የቅናት ቃና አልነበረበትም። የበቀል ዕቅዱ እየተቃረበለት ሲመጣ ወትሮ በእንደዚህ ያለው አጋጣሚ ያቃጥለው የነበረው ሠቀቀን እየጠፋለት፤ በምትኩ አንድ ልዩ የሆነ ሥነ ልቡናዊ የወሲብ እርካታ እየተሰማው ሔዶ ነበር። ጋረድም ቢሆን እንኳን በእንደዚህ ያለው ቀልድ በምር ቢሾፍበት፤ እንኳን ሙሉ ቅሬታ፤ የቅሬታ ጫፍ ከማይደርስበት የመኩራራት ጣሪያ ላይ ወጥቶ ነበር።

ለገብርዬ ወይኒ ኪዳነ ምሕረት ቆይታ ከብዙ ዓመታት ወዲሃ አግኝቶት የማያውቀውን የዕረፍት የመዝናናት ዕድል ሰጠው። ቤተ መንግሥት ለመሔድ ወይም በሌላ ጉዳይ ለማነጋገር፤ ጠያቂ እንግዳ ለመቀበል፤ ሠራዊቱ ለመጎበኘት ወይም በሌላ ጉዳይ በጧት መነሣት፤ የዕለት ውሎውን በዓቃቤ ሰዓት መመደብ አልነበረበትም። ቢፈልግ ቀኑን ሙሉ ተኝቶ መዋል ይችል ነበር። ነገር ግን ተኝቶ ማርፈድ ያልለመደበት ሆኖ በጧት መንቃቱ አልቀረም።

ከሣልስት አንድ ቀን ገብርዬ፤ ከፀሐይዋ ቀድሞ ከጎጆው ይወጣና ቁልቁለቱን ወርዶ ከፈፋው ጎን ከሚገኘው መዋት ሲታጠብ ቆይቶ ይመለሳል። ሌላ ቀናት ከጎጆው ታዛ ይቀመጥና የጧትዋ ጀንበር በወይኒ ጋራ የደቡብ ጎን ብቅ እያለች ጨረርዋ በረባዳው መሬት ላይ ስትዘረጋ፤ ሴቶች እስንራቸውን አዝለው ወደ ወንዝ ሲወርዱ፤ ወንዶች እርፋቸውን ተሸክመው በሬዎቻቸውን አስቀድመው ወደየማሳቸው ሲያመሩ፤ ልጆች እየተጩዋጩሁ፤ እየዘፈኑና እያፏጩ ከብቶችን ወደ ጨፌ - ቀመሱ መስክ ሲነዱ በአንክሮ ይመለከታል በነፋሻው ዓየር፤ በጸጥታው፤ በአካባቢው ግርማ ሞገስ ይመሰጣል። ይማረካል። ከዚህ፤ የቤተ መንግሥት ግርግር ሁካታና ነጋሪት የለም። ከዚህ፤ የግድያና የጦርነት ዜና የለም። የሚያድምና የሚያሤር የለም። ሁሉም የዕለት ተግባሩን ብቻ ያከናውናል። የጅራፉ ጩኸት ከኮረብታ ጋር ሲያስተጋባ እንደ ጥይት ተኩስ ሞትን አያረዳም። የዐራሹ ሸለላ፤ የቁጣ፤ የንዴትና የግዳይ መግለጫ ሳይሆን በሬውን ማባበሉ ነው። የወፎች ዝማሬ፤ ከአዝማሪ ቁልምጫ የበለጠ ለጆሮ ይጣፍጣል። ዕድሉ ከቴዎድሮስ ዕድል ጋር ባይጋጠም ኖሮ ሕይወቱ ይህንን መሳይ ሆኖ በቀረ ነበር። ጥቁር ዐፈር የሚገፋው ትሑት ገበሬ ሕይወት ሳይሻል ይቀራል? የሚል ሐሳብም ይመጣበታል።

የራሱ ሕይወት የሚያውቀው፤ ሰልፍ ፤ ትጥቅ፤ ዘመቻ፤ ግድያ፤ ምርኮ፤ ነው። በገደሉ ቁጥር መሳቀቅ አለ። ሲሸነፉ ደግሞ መጨነቅ ነው። ችግር ድካምና ልፋት ቢኖርበትም፤ ከጥቁር አፈር ጋር ሲታገል የሻከረ መዳፍ ሰይፍና ጠመንጃ እንዲጨብጥ እጅ የሰው ደም የለበትም። ሐሳብ ቢኖር፤ ጠሉ እንዲለግስ፤ አድባር፤ አውድማውን እንድትባርክ ነው። ዛዲያ ይኸ ሳይሻለኝ ይቀር ኑሯል? ይልና ገበርዬ በወጣትነት ጀምሮት የነበረው የግብርና ሕይወቱ ትዝታ ይመጣበታል።

በዙራምባ ማርያም ደብር የታወቁትን አባቱን የሚተካ ደጎና ዐራሽ መሆን እንደ ጀመረ፤ በሰው አፈላልገው ከምር ድንጋይ ከሚኖሩ ቤተሰቦቹ አንዲት ቆንጆ ልጅ ያጨለታል። ገና ሲያያት ውክክል ያለላት ስልክክ ያለች ቀይ ናት። የሠርጉ ዕለት፤ የሕግ ሚስቱን ተረክቦ ወደ ዙራምባ ሲመለስ ራስ አሊ በደብረ ታቦር ላይ የሾሙዋቸው ደጃዝማች አሽከሮች ከመንገ ላይ መንጠቅ አምባጓሮ ያስነሳሉ። ተኩስ ይከፈታል፤ ከሁለቱም በኩል ሰዎች ይጎዳሉ። እንደ ምንም ጠው ሠፈራቸው ይደርሳሉ። በበነጋው በዳስ ውስጥ እንዳሉ፤ መዓት ሠራዊት ድንገት ይደርስና ድብልቅልቁን ያወጣዋል። ከአባቱ ጋር ብዙ ሰዎች ይገደላሉ። መንበሩ በሙሉ ይቃጠላል። ገብረ ሕይወት በፍጅት መካከል እንዴት እንደ ወጣ ሳይታወቅ ያመልጥና፤ የሕግ ሚስቱንና ከብቶቻቸውን ዘርፈው ሲሔዱ በሩቁ ይመለከታል። ጥርሱን ነክሶ፤ ደግሞ ደጋግሞ፤ በራስ አሊና በሰዎቻችወ ላይ በቀል ይምልና ወደ አሞራ ገደል ይወርዳል።

ከዚያ በኋላ ወደ ግብርናው ሕይወት አልተመለሰም። እጁ ከዕርፍ ይልቅ ለጐራዴና ለነፍጥ የታደለ ሆነ።

ከራሱ የጥንት ትዝታ ጋር አሁን የወይኒ ገበሬዎችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በእርጋታ ሲያስተውል፤ ዕርፍ የመጨበጥ፤ ከበሬ ጋር የመነጋገር ፍላጎት እንደ መሳብ አደረገው። ጊዜውን የሚያሳልፍበት ሌላ ሥራ ደግሞ አልነበረውም።

የዕለት ኑሮዋቸው በጣም ቀላልና የተወሰነ ሆነ። ከረፋዱ ላይ ታንጉት ኪዳነ ምሕረት ቀዝቃዛ ጠበል በመጀመሪያ አቅምሳው ቁስ ታቀርብለታለች። ከዚያም፤ ከገረገምብ ዋልካ አምሮቷን ለመወጣት ብቻዋን ትሔዳለች። በመገረም ፈዝዞ ያያት የመጀመሪያው ቀን ብቻ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን አፍራ አስከትላው አታውቅም። ትዝታዋን ሌላ እንዲጋራት የማትፈልግ ይመስል፤ በልጅነቷ የምታውቀውን ሥፍራ ሁሉ የምትጎበኘው ብቻዋን ነው። ይህ ገብርዬን አላስገረመውም ዐሥር ዓመት እስኪሆናት ድረስ የኖረችው በዚህ መንደር ነው። ራሷም ቢሆን የሥጋ ዘመድ እንዳላት ለማጠያየቅ የምትፈልግ አይመስልም። ገብርዬ፤ ነገሩ ትንሽ ከንክኖት ሊጠይቃት አሰበና፤ «የሥጋ ዘመዶቼ ሁሉ በድንገት አልቀው ታጠቅ ወስዶ

አሳደገኝ» ብላ ነግራው ስለ ነበር፤ አሠቃቂ ትዝታዋን እንዳይቀሰቅስባት በማለት ተወው።

ከሳምንት ያህል በኋላ፤ ከቤቱ ያረፈበት ገበሬ ማሳ ወደ ሚገኝበት አብሮ ወረደ። ለጥቂት ጊዜ አየ። «እስቲ!» አለና ዕርፉንም፤ ጅራፉንም ተቀበለው። ግን ሰው ኑሮውን ይመስላል እንደሚባለው ከግብርናው ሕይወት ምን ያህል ተለያይቶ እንደ ነበር፤ ወዲያው ሲያየው ከመገረም ዐልፎ ተናደደ። አንድ ጊዜ፤ ምንም ያህል ጅራፍ ቢያጮህና ቢያላጋ ጥማድ በሮቹ የማያውቁት ባዳ ከኋላቸው መኖሩን እየተማከሩ ይመስል ከቀንበራቸው ሥር አንገታቸውን ላመል ያህል እያንቀሳቀሱ ግትር ይላሉ። ሌላ ጊዜ ማረሻው ይቸከልበታል። በስንት መዓት ሲነቅለው ደግሞ ላይ ላዩን ይጭርበታል። ወይ ደግሞ ትልሙ እንደ ሰካራም ኮቴ ተወዲያ ተወዲህ ይወላገድበታል። እንደ ጦር ሜዳ ወኔው እልህ ተጋብቶ በየዕለቱ ሲጋተረው፤ እየተለማመደው፤ እየነቀለው ሔደ።

የዕለት ሥራ አልቆ ሁሉ ወደ ሠፈሩ ሲመለስ፤ ብዙዎቹ የጎረቤት ሰዎች እነ ገብርዬ ወደ ዐረፉበት ቤት ይመጡና ከደጅ ተሰብስበው አብረውት ሲያወጉ ያመሻሉ። ከአባ ታጠቅ ካሣ ጋር ስለ አደረጋችወ ዘመቻዎች፤ ስለ ጎንደር ከተማና ስለ ቤተ መንግሥት ሕይወት ያለ መታከት ይጠይቁታል፤ ያወጋቸዋል፤ ያለ መሰልቸት ያዳምጡታል። ከወንዶቹ ጥቂት ፈቀቅ ብሎ ታንጕት ከጠፍር ድኳ ላይ ተቀምጣ ትፈትላለች። ወይም ጥጥ ትባዝታለች። ወይኒ ኪዳነ ምሕረት ከመጡ አንሥቶ ከታንጕት አጠገብ የማትለየው የገበሬው ሴት ልጅ ከሥርዋ ተሸጕጣ፤ ወይ ቅልሞሽ ትጫወታለች፤ ወይ ተረት ስታጫውታት አፍዋን ከፈታ የሚያማምሩ ዐይኖቿን በአድናቆት እያቁለጨለጨች ትሰማለች።

ገብርዬና ታንጕት፤ ከገበሬው ቤት ያረፉት በዚችው ልጅ ምክንያት ነበር። ከጎንደር በተነሡ በአራተኛው ቀን ወይኒ ኪዳነ ምሕረት ደርሰው፤ ድንኳናቸውን ተክለው ከደብሩ ጥቂት ራቅ ብሎ ከሚገኘው ገላጣና ደልዳላ ሥፍራ ላይ ነበር። ድንኳኑ የማን መሆኑ እንደታወቀ፤ የታጠቅ ጦር አዝማች ገብርዬ መጣ የሚለው ወሬ እንደ ቋያ እሳት ሦስት አራት ሰበካ የሚሆን አዳርሶ አድሮ ኖሮ፤ ጧት ቤተ ክርስቲያን የመጣው ሕዝብ ብዛት ታቦት የሚነግሥበት ዓመት በዓል ያህል ሆነ። ቅድስቱና ቅኔ ማኅሌቱ በተሳላሚ ብዛት ቢጨናነቅም፤ ለገብርዬ በስሜን በኩል፤ ለታንጕት በደቡብ በኩል ከቅድስቱ ሥፍራ ተሰጥቷቸው ሰዉን ከአጠገባቸው ገለል የሚያደርግ አስተባባሪ ተመድቦላቸው ነበር። የደብሩ ገበዝ ግን ጨርሶ አይሞከርም ብለው ስላስቸገሩ ፈቃዳቸውን መፈጸም ግን ሆነበት። ሙሉ ማኅሌት ተቆመ። የክቱ ልብሰ - ተክህኖ ወጥቶ በሰባት ተቀደሰ። በዚህ ሁሉ መካከል የሰው ዐይንና ሐሳብ

ያተኮረው ግን፤ ከቅዳሴውና ከጸሎቱ ይልቅ ከሁለቱ እንግዶች ላይ ነበር። ቅዳሴው አልቆ፤ «ሐሩ በሰላም» እንደ ተባለ ገብርዬና ታንጉት ወደ ድንኳናቸው ሲመልሱ፤ ብዙው ሰው እንደ አጃቢ ግር ብሎ ተከተላቸው። ከዚያም የተነሣ ከብ ሥርቶ በመቆም ይመለከታቸው ጀመር። ገሚሱ እጅ ነሥቶ፤ ዐይኑ እስቲጠግብ አይቶ፤ በሆዱ የታንጉትን ውበት፤ የገብርዬን ጉብዝና አድንቆ ሲሔድ ሌላው ይተካል። ረዘም ላለ ጊዜ ቁሞ የሚቆየው አብዛኛው ለጌታ የማደር ሐሳብ ያለው ጎረምሳ ነበር። ገብርዬና ታንጉት ከሌሎቹ ነጥለው አላስተዋሉትም እንጂ፤ አንድ መካከለኛ ዕድሜ ያለው ገበሬ ዘጠኝ ዓመት የሚሆናት ሴት ልጅ ይዞ በመቅረብ እጅ ከነሳ በኋላ እሱ ለመሔድ ሲል እሷ እጅዋን እየጎተተች እምቢ ስትለው ረዘም ላለ ጊዜ ቆይቶ ነበር።

በሰው በመከባቸው ገብርዬን ትንሽ አስጨነቀው። ተዝናንቶ ማረፍ አልቻለም። በሕዝብ ዐይን የታፈነ መሰለው። ገርነታቸው ደግሞ ደነቀው። በእነሱ ቤት እኔን ከሰው የተለየሁ፤ ከሰው በላይ የሆንኩ ማድረጋቸው ነው እኮ አለ በሆዱ።

ወደ ማምሻው ገደማ፤ የወይኒ ኪዳነ ምሕረት ሰበካና የአካባቢው ሰው እጅ መንሣቱ፤ በአድናቆት መመልከቱ ተዳርሶት ጎልማሳው ከብት ልማስገባት፤ ሴቱ ራስ ለማሰናዳት ወደ የመንደሩ ሲበተን ሠፈሩ ጭር አለ። ለመጀመሪያ ጊዜም ገብርዬና ታንጉት ከድንኳናቸው ውጭ ምንጣፍ አዘርግተው በመዝናናት ተቀመጡ። ባይሠሩም ድካም ተሰምቷቸው ነበር። ጃኖ ጋቢ ያደገደገ አንድ ሰው ከአንዲት ልጅ ጋር ድንገት ከፊት ለፊታቸው መቆሙን ያስተዋሉት በዚህ ሁናቴ ሳሉ ነበር። ገብርዬና ታንጉት፤ ትንሽ ግራ ገብቷቸው እርስ በርሳቸው ተያዩ። ዕርዳታ ጠያቂ ደሃ ቢጤ ነው እንዳይባል አለባበሱና ግርማ ሞገሱ ያስተባብላል። እጅ አነሳሱም የትሕትናና የአክብሮት እንጂ እንደ ለማኝ የመለማመጥና የመሽቆጥቆጥ ዐይነት አይደለም። ቀኑን ሙሉ ሲንጋጋ እንደ ዋለው ጎልማሳ ሁሉ ለማየት ብቻ የመጡም አይመስሉም። ጉዳይ እንዳላቸው አቀራረባቸው ያስታውቃል። ለአዛውንቱ ሰላምታ አጸፋውን በመመለስ ገብርዬና ታንጉት ከአቅማመጣቸው ቀና አሉ።

ሰውዬው ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠራርገና፤ «ከድፍረት አትቁጠሩብኝና! ላስቸግራችሁ። ለልምናችሁ ጌታየ፤ እመቤቴ!» አለ በረጋ ጨዋ አንደበቱ ከወገቡ እየታጠፈ። ልጅቷ የተጨነቀች ይመስል ትንንሽ መዳፎቿን እያፋተገች ዐይንዋን በሰውየው፤ በታንጉትና በገብርዬ መካከል ታንከራትታለች፤ አብዛኛው ጊዜ የሚያርፈው ግን በታንጉት ላይ ነበር ጉዳዩን እስኪናገር ጠበቁት።

«አሽከር የያዛችሁ አልመሰለኝም። ፈቃዳችሁ ቢሆን ተኔ ቤት ዕረፉ። እልፍኝ አዳራሽም ባይሆን ለመጠለያነት አይገድም።

‹ሰውየው በራሱ ሙሉ እምነት የሚሰማው፤ የሰውነት ዋጋን ያወቀ መሆን አለበት› ሲል ገብርዬ አሰበ።

«ዛዲያ እኛ ታንተ ቤት ባረፍን፤ አንተን እናስቸግራለን እንጂ መች እንቸገራለን?» አለው።

«ለኔ ደስታና ክብር ነው ጌታዬ» አለ ገበሬው ድግድጉን እያስተካከለ።

«አይ! ሰውን ማስቸገር ምንም አያስፈልግ። ተዚሁ መሰንበቱን ነው የምንመርጠው። ስላሳብህ እግዜር ይስጥህ።»

«አይሆንም። እንደማመጣችሁ ላይኔ አበባ ቃል ገብቼላታለሁ።» አለማመኑ የልመና ሳይሆን የማረጋገጫ ዐይነት ነበር።

«የተዘባነነው መጣ! ምንናት ያይኔ አበባ?» ሲል ገብርዬ ጠየቀ፤ በመገረም ንግግሩን ትንሽ ስለት ሰጥቶ።

«ይቺ የኔ ልጅ ናታ!» ቁልቁል እየተመለከተ ራሷን በእጁ ያሻሻት ጀመር።

ልጅቷም በማባበልና በመለመን አኳኋን በሁለቱ እንግዶች ላይ የሚያምሩ ዐይኖቿን አቁለጨለጨች። ሁለቱም የመገረም ሣቅ እንደ መጣባቸው ተገንዝቦ፤ «ምናልባት ታሪኳን ብነግራችሁ ነው የሚሻለው» አለና ሳይጋበዝ ከአጠገባቸው ተቀመጠ። ልጁንም በክንዱ ሳብ አድርጎ ከጎኑ አስቀመጣት። ከዚያም በእርጋታ አጫወታቸው።

ያይኔ አበባ አንዲት ልጁ ናት። ገና ከአራስ በኢት ሳትወታ እናታዋ ከሞተች እነሆ ዘጠኝ ዓመት ሊሆናት ነው። ሌላ ሚስት አላገባም። የሴት ፍርቅ ምንጩ ስለ ደረቀበት፤ ልጁን የእንጀራ እናት እጅ ማሳየት ስለማይፈልግ፤ ሌላ ሚስት የማግባት ሐሳብ ጨርሶ የለውም። እግዜር ይመስገን፤ አገልጋይም ሀብትም አለው። ግን ዕድሜ የሚለምነው ለልጁ ሲል ብቻ ነው። የርሷን አበባ፤ ወግ ማዕረግ ለማየት እንዲበቃ ብቻ! ለሌላውስ ግድ አልነበረውም። ዛዲያ ጧቱን ቤተ ክርስቲያን ይዟት መጥቶ ነበር። ከቤተ ክርስቲያን ሲወጡ በእመቤት ታንኰት ላይ ዐይኗ እንዳረፈ መላ ሰውነቷ ይለዋወጣል። በጣም ትደሰትና፤ «ያች ሴትዮ ማናት?» ብላ ትጠይቀዋለች። ከነገራት በኋላ፤ «እናቴ መሰለችኝ። ወይ እናቴ ብትሆንልኝ» ትልና ትካዜ ይገባታል። ይቀላት እንደሆነ በማለት ከሰዎቹ ጋር ወደ ድንኳኑ በመምጣት በድጋሚ እንድታይ አድርጎ ወደ ቤት ይመለሳሉ። ግን ትካዜው ብሶባት እየቆዘመች እያለቀሰች ምሳ ሳትበላ ዋለች። እንደ ምንም አባብሎ ምክንያቱን ቢጠይቃት፤ ከሴትዬዋ ዘንዳ ሒዳ ካደረች ወይም ሴትዬዋ ከቤታችን ካልመጣች ሙቼ እገኛለሁ ብላ ትንሰቀሰቅ

ገባች። ነገሩ እንግዳ ቢሆንበትም መቸም አንድ ልጁ ናትና እንደሚያመጣቸው ቃል ገብቶላታል፤ እህል ቀምሳ እነሆ ሊጠይቃቸው መጣ። ታሪኩን ሲጨርስ ለጥቂት ጊዜ ያህል ሦስቱም ዝም አሉ። ዐይኔ አበባ መልሱን የምትጠብቅ ይመስል ዐይኗን በታንጉት ላይ ትክል አድርጋ ቆየች።

«ነይ እስቲ!» አለችና ታንጉት በማቀፍ አኳኋን እጅዋን ዘረጋች።

«ለመሆኑ እናቷ እኔን ትመስል ነበር?» ስትል ጠየቀች። ያይኔ አበባ በከንፈርዋ ላይ የማፈር ፈገግታ እየተጫወተ ተነሥታ ተጠጋች።

«ኧረ እስተዚህም አትመስልም። ግና እርሷም መልከ መልካም ነበረች። ሰውዬው የሚስቱን ፊት በሩቅ የሚያይ ይመስል፤ ዐይኖቹን ወደ ማዶው የወይኒ ተራራ አነጣጠረ።

«አስቀድመህ ለልጅ ቃል መስጠህ ደግ አልነበረም። አይመስልህም?» አለ ገብርዬ። ጥያቄም ምክርም ነበር።

«ምን ችግር አለው? ተወደችን ተኔው ጋር ተዚህ ትሰነብታለች፤ ሁለትችሁ ተተስማማችሁ ደሞ በኋላ ይዘናት እንሔዳለን» አለች ታንጉት ለጠቅ አድርጋ።

ሰውዬው የታንጉትን የመጨረሻ መስል ዘሎ፤ «አየ መቸም እመቤቴ የዚሁ የእኛው አገር ናቸው ስለሚባል እምቢ አትሉኝም ብዬ ነው። ደሞም አባ ታጠቅ ካሣ፤ ገበሬ ባላገር ይወዳል። ተነሱ ጋር ይበላል፤ ይጠጣል፤ ተቤታቸውም ይውላል፤ ሲባል ስለምንሰማ ነው። ዛዲያ ምን አለበት፤ እኔም እንደ ዐቅሜ ቤት አለኝ ብዬ ነው የደፈርኩት» ሲል ተናገረ።

«ኧረ ቀላል ነው!» አለ ገብርዬ፤ እጁን በማወዛወዝ። «ታንጉት እንዳለችው ልጅቱ ተኛ ጋር ትሰንብት።»

«አይ እሱማ እንዴት ተደርጎ» ከልጁ መለየት ሞት መስሎት መንፈሱን እንዳሸማቀቀው ከፊቱ ላይ ይታወቅ ነበር።

«ዛዲያ እንዴት ይሁን?» ተብሎ ተጠየቀ።

ሰውየው ግን፤ ታሪኩ ልባቸውን እንደ ነካው በመረዳት የእሽታ ቃል ካቸው ሳይወጣ፤ «እንዳልኩት አዳራሽም ባይሆን፤ ለብቻችሁ የምትሆን ገለልተኛ ማረፊያ አለችኝ» የሚል መልስ ሰጣቸው።

የአባትዬውን ጭንቀት፤ በጉጉትና በተስፋ የሚቁለጨለጨውን የልጅቷን ዐይን ሲመለከቱ እምቢ ማለት አልቻሉም። ድንኳናቸውን ልጆች እንዲጠብቁ አድርገው አብረውት ሔዱ።

በመሔዳቸው ቅር አልተሰኙም። ማረፊያው ጎጆ ከድንኳናቸው የተሻለ ምቾት ነበረው። ከበለጡ ሌላ አንድ አገልጋይ ተመደበላቸው። በምግብም በመጠጥም የሚጎድል ነገር አልነበረም። የታንጉትና ያይኔ አበባ ፍቅርም የእናትና ልጅ ዐይነት ሆነ። ታንጉት ጧት ተነሥታ ቤተ ክርስቲያን ስትሔድ፤ በጉዳ አንዳንድ ነገር ስታዘጋጅ፤ ወይ ጥጥ ስትፈትል ሁሉ ያይኔ አበባ ከአጠገብዋ አትለይም። የባጥ የቆጡን የልጅ ተረት ታጫውታታለች። ወይም ደሞ «ትዬ ታንጉት የላሜ ቦራን ተረት ንገሪኝ» ብላ ለንስተኛ ጊዜ እንደ አዲስ በጉጉት ታዳምጣታለች። የምትለያት አምሽታ ማታ ለመኝታ ወደ አባትዋ ስትሔድ፤ ሌላ መንደር ስትላክ፤ በአንድ ድንገተኛ ስጦታ ልታስደስታት ስታስብ ብቻ ነው። ተደብቃ ወደ ጫካ ትሔድና የሚያምር የመሰላትን አበባ የሚጣፍጥ የመስላትን ፍራፍሬ ይዛላት ትመጣና፤ «እትዬ ታንጉት ይች አበባ አንቺን ስለምትመስል አመታሁልሽ» ትላታለች። ከስጦታው ሌላ ያይኔ አበባ ኮልታፋ አነጋገር እንደ ግሩም ዜማ ይጥማታል። የእናትነትን ጣዕም፤ የእናትነት ተስፋ ይበልጥ ያሳድርባታል።

በዚህ የሚያዝናና ደስ የሚያሰኝ ቆይታቸው መካከል፤ ገብርዬ ለአባ ታጠቅ ያለማሳወቁ ጉዳይ በመጀመሪያ ሳምንት አላሳሰበውም ነበር። እንዲያው ጊዜው ሳይታወቅ ነው የበረረበት። በሁለተኛው ሳምንት ላይ ዐልፎ ዐልፎ ከነከነው። በሦስተኛው ሳምንት ኪዳነ ምሕረት የምትውልበት ሰሞን ስለ ነበር፤ ምናልባት ታንጉት ማስቀደስ ብትፈልግ ከዚያ በኋላ እንነሣለን ብሎ በመገመት ለጊዜው ችላ አለው። በኪዳነ ምሕረት ማግሥት፤ «እንግዲህ አምሮትሽም ሳይበቃው አይቀርም፤ ታስፈለገም ለስንቅ ያህል እንይዛለን፤ እንነሣ እንጂ» ቢላት የሰጠችው መልስ፤ ተዚህ ድረስ መጥቼ ስለት ሳላስገባላት፤ ዝክር ቢጤ ሳላደርግ ልሔድ ነው? እህ!» የሚል ነበር።

«.....ዛዲያ የዚህ የዚህ መጀመሪያ ደብረ ታቦር ደርሰን ብንመጣ አይሻልም ነበር? ምን አቻኮለን! አባ ታጠቅስ ምን ይላል?» ገብርዬ ጥቂት እንደመበሳጨት አለ።

«ምን እንዳይል ነው አባ ታጠቅ? ተሚሽትህ ጋር ለምን ጠበል ሔድክ? ለጠበል ይዤህ መምጣቴን ተምሥራቹ ጋር ስነግረው ደስታውንም አይችለውም። ስለ ቀደምከው እንዳይቀና እንጂ!» ስትል በቀልድ መልክ ሕሊናዋ ከውስጥ ቆንጠጥ አደረጋት።

«መጀመሪያ፤ ደብረ ታቦር ብንሔድም ትርፉ መንገድ መመታት ነበር። ቀደም ብለን መምጣታችንስ ምን ጎዳን? ላንተም ዕረፍት ሆነልህ። ጠበሉ ተስማማህ። የረሳኸውንም እርሻ ይኸው እየለመድከው ሒድክ።

ታንጉት፤ እስከ ኪዳነ ምሕረት ንግሥ ለመቆየት መፈለግዋ ከልብዋ ቢሆንም፤ ለይታ ልታውቀው ያልቻለችው፤ ከወይኒ እንዳትወጣ እንደ እናት ጉያ ምቾትና ሙቀት የሚስብ አንዳች ውስብስብ ስሜት ደግሞ እያደረባት ሔዶ ነበር። እንደ እናት ከምታያት ከዐይኔ አበባ ጋር መሆን በማኅፀንዋ ውስጥ ላለው የራስዋ ልጅ የደኅንነት እንደ ክታብ የሚበጅ፤ ወይም ለእናትነት ለመብቃቷ የተምሳሌት ማረጋገጫ መስሎ ይሰማታል። ሌላው ደግሞ፤ የሕሊናዋን ወቀሳ ለመከላከል የተፈጠረ ስሜትም ይሁን፤ ስለ ገርብዬ የልጁ አባትነት የሚመላለስባት አጉል ተስፋ ነው። ከአምባ ጊዮርጊስ ተመልሳ ከገብርዬ ጋር ግንኙነት በምትፈጽምበት ጊዜ ስንኳ፤ «ማን ያውቃል? ከተለመደው የቤተ መንግሥትና የጦር ሠፈር ግርግር ተለየው ሁለቱ ብቻቸውን ስለ እርስ በርሳቸው ብቻ በመተሳሰብ፤ በወይኒ መቆየታቸው በአንዳች ተአምር ልጁን የገብርዬ ያደርገዋል የሚለው ተስፋ በውስጠ ሕሊና ይሰማታል። ምክንያት አታገኝለትም። ብቻ እንደዚሁ ይሰማታል። ስለዚህም የተቻለውን ጊዜ ያህል ወይኒ መቆየት ትፈልጋለች። እንደማይሆን ታውቃለች እንጂ፤ እንደርሷው ሁሉ የልጅዋም እትብት ወይኒ ቢቀበርላት ትወድ ነበር፤ የእናቷ ዘመዶች ሁሉ እትብት በተቀበረበት።

«እና ምናለበት ትንሽ ብንቆይ?» አለችው የፊቱን ቅሬታ ተመልክታ። «ታለአሁን እንኳ እስተዚህ አስቸግሬህ አላውቅ!» እወነቷን ነበር። ታንጉት ባሏን የምታስቸግር ሚስት አልነበረችም። እርሱው እራሱ አስቦ ካሆነ በቀር፤ ጥምቀት መጣ፤ ፋሲካ ደረሰ፤ ቅዱስ ዮሐንስ ተቃረበ፤ የባሕር ማዶ ሐር ቀሚስ ግዛልኝ፤ ሽቶ አምጣልኝ፤ የወርቅ ጌጥ አሠራልኝ ብላ ጠይቃው አታውቅም። እንደ አንዳንድዋ ሚስት ዘወትር ዘመቻ የሚሔድ ቀንታ የምትጨቀጭቅ፤ አስቀንታ የምታቃጥል ሴት አይደለችም። አባ ታጠቅ ሲድሩዋት፤ «ተዋበች ለነኢ እንደ ሆነችው፤ ሚሽትም እኅትም፤ ሁኚለት እንጂ፤ ወንድሜን ብታስቸግሪው፤ ብታስከፊው ወዮልሽ!» ሲሉ የመከሩዋትን እንዳላጓደለች ገብርዬ ያውቃል።

«እሺ እንዳልሽ እንቆያለን!» አላት በማቆላመጥ ሰርጉዳቷ ላይ ቆንጠጥ እያደረገ። መልኳ የእርግዝና ውበት እየደረበ ሔዶ ነበር።

በዚህ አኳኋን፤ አንድ ሳምንት፤ ሁለት ሳምንት፤ ብዙ ሳምንታት ዐለፉ። ገብርዬ ወደ ደብረ ታቦር ሰው ለመላክም ቢሆን ነገ ሣልስት ሲል የአባ ታጠቅ የቅጣት መልክተኛ ቀድሞ ወይኒ ኪዳነ ምሕረት ደረሰ።

በኅዳር ኻያ አራት ሰበካው የወይኒ ኪዳነ ምሕረት አዋሳኝ የሆነው የተክለ ሃይማኖት ታቦት የሚነግሥበት ዓመት በዓል ስለሆነ፤ በሁለቱም ሰበካዎች የሥራ እንቅስቃሴ አይታይም። አብዛኛው ሰው ወደ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሔዶ በዚያው በየማኅበሩና በየዝክሩ ታድሞ ስለዋለ፤ የወይኒ ኪዳነ ምሕረት መንደሮች በአብዛኛው ጭር ብለዋል። ገብርዬና ታንጉትም በአካባቢው የታወቁ ሦስት አራት ሰዎች መጥተው ጠበል እንዲቀምሱላቸው ጠይቀዋቸው ነበር። አክብረው የሚጠሩዋቸውን ሰዎች ለማስደሰት ስትል ታንጉት መሔዱን ባትጠላውም፤ እንዲያውም ብትወደውም፤ ገብርዬ ግን ስንኳን በዓመት ንግሥ በየሰንበቱ እንደ ትንግርት መታየቱ ስለሚቀፈው፤ ብቻዋን መሔዱም ጥሩ ስላልመሰላት አብረው ከቤት ውለዋል። ታንጉትና ያይኔ አበባ፤ ከሚያዘወትሩት ታዛ ሥር ተቀምጠው ቡን ከማሽላ ቆሎ የቡና ቁርስ ጋር ቀርቦ ተዝናንተው ይጫወታሉ። ያይኔ አበባ አሁን ገብርዬንም እየቀረበችና እየተለማመደች ስለ ሔደች ተረት እንዲነግራት መጠየቅ ጀምራለች። ገብርዬ በሕፃንነቱ የሰማውን ተረት ከዚያ በተራው መልሶ ያጫወተው ልጅ ስላልነበረ፤ ሐሳቡም በአብዛኛው፤ ሰይፍ ከሰይፍ የሚፋጭበት፤ ሕይወት ከሕይወት የሚጋጭበት፤ ጀግንነትና ሞት በሰፈነበት የጦር ሜዳ ትዝታ የተሞላ ስለሆነ፤ ለልጅ የሚሆን ገራ ገርና አስደናቂ ተረት አልመጣለት እያለ ይቸገራል። «እኔ ጥሩ ተረት አላውቅም ያይኔ አበባ» ይላታል። «ግዴለም ያንተ ተራ ነው» ብላ ትጠይቀዋለች። ፈጣጥሮ፤ አንዱን ከሌላው ቀጣጥሎ ያጫውታታል። በዚህም ወቅት፤ «አሁን ማ ይሙት እንደዚህ ያለ ተረት አለ?? ስትል ታንጉት እያፌዘችበት ስለ አንድ ሰነፍ ጅብ የፈጠረውን ተረት ለአይኔ አበባ በማውጋት ላይ ነበር።

ፀሐይ ዘቅዘቅ ብላ ቀዝቃዛ አየር ይነፍሳል። ከቤት ጓሮ የዋሉና የናታቸውን ጡት ለመጉረስ የተቻኮሉ እምቦሳዎች ጥሪ ያሰማሉ። ተባራሪ መልክ ከዚህም ከዚያም ይሰማል። የተረጋጋና የተፈጥሮ ክንዋኔ መካከል ከሩቅ የዳገቱን ጥግ ይዞ አንድ ነጭ ነገር የሚበር ወይም የሚሽከረከር ነቁጥ መስሎ ወደ እነርሱ አግጣጫ ሲመጣ ተመለከቱ። እየቀረበ ሲሔድ የሚንቀሳቀሰው አካሉ ለየ። የሚሮጥ ሰው ነበር። ከመደራቸው ዳገት ስር ሲደርስ ከጫካው ውስጥ ገብቶ ጠፋ። ገብርዬ ጨዋታውን ባያቋርጥም፤ የአዳኝ ጠረን ከሩቅ እንደሚሰማው አውሬ፤ የዘወትር ዘመቻ ባሳደረበት የጥንቃቄ ልምድ ጆሮውን አቅንቶ ዐይኑን ከወዲያ ወዲህ ወርወር እያደረገ ይጠባበቅ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባለቤቱ በሩጫ እያለኸለኸ ከተፍ አለ። ሁሉም ክው አሉ። በደኅና አለመሆኑ ግልጽ ነበር። ጫን ጫን ይተነፍሣል።

ያይኔ አበባ «አባባዬ» ስትል ተወርውራ ከወገቡ ላይ ተጠመጠመች። በዝክር ወይም በማኅበር ላይ አምባጓሮ ተነሥቶ ከሰው ጋር የተጋጨ ወይም አደጋ የደረሰበት መሰላቸው።

«ጌታዬ! ጌታዬ! ቶሎ ቢነሱ ይሻላል!» አለ ገበሬው ካለወትሮው ከሚቆራረጥ ትንፋሹ ጋር አካላቱ እየተወራጨ።

ገብርዬ፤ ግራ ገብቶት ዝም ብሎ አስተዋለ።

«የአስተናጋጅ ይሁዳ ስም አያሳጡኝ። በአምላክ ፊትም አያስጠይቁኝ ነው የምሎት! ቶሎ ይሒዱልኝ ተዚህ!» የገበሬው አነጋገር የቁጣ ትዕዛዝ የመሰለ ነበር።

«ምን?» ገብርዬም ሳይታወቀው በቁጣ ዐይነት ጮህ ብሎ ጠየቀ።

‹ለምኖን ነው እንጂ ለምነነው አልመጣን› የሚል ትዝብት እየተሰማው።

«ይነሱና ይሒዱልኝ ነው የምሎት!»

«ምን ተፈጠረ?» ገብርዬ የሚጠይቀውና የሚናገረው ጠፍቶት፤ ሰውየው አብዷል፤ በሚል አመለካከት ገበሬውን ከላይ እስከ ታች ገላመጠው።

«ተፈጥሮዋል! አዎ ጦር ዘምቶብዎታል!» አለ ገበሬው በንዴትም በጸጸትም።

«የምን ጦር?» ገብርዬ አነጋገር ከጥያቄ ይልቅ የመገረም ነበር።

«የንጉሥ ጦር! እንደሚባለው ወደዚህ የመጣችሁ በቴዎድሮስ ላይ ሸፍታችሁ ነው አሉ። በመሸፈትዎ ባልስማማም እንግድነታችሁን አከብራለሁ። እኔው ለምኛችሁ፤ እኔን አምናችሁ ባረፋችሁበት ቤቴ ውስጥ አትያዙም።»

ገብርዬ አልመለሰለትም። በሥውር እጅ ድንገት እንደ ተኮረኮረ ያህል ከት ብሎ ሣቀ። ያሣቀው መሸፈቱ ነበር። ራሱ ሳይታወቀው ሸፍቶ ይሆን? የቁም ቅዠት ነው? ወይስ ሕልም? ይህ የዋህ ገበሬ የዝከር ጠላ ከራሱ ላይ ወጥቶ እያስቀባዠረው ይሆን? ሁናቴው ግን አይመስልም። መልሱን የሚያገኝበት ይመስል ዐይኑን ከሰውየው ወደ አይኔ አበባ፤ ከዐይኔ አበባ ወደ ታንጉት፤ ከታንጉት መልሶ ወደ ሰውየው አንከራተተና፤ «እርግጠኛ ነህ?» ሲል ጠየቀ። «ያው!» አለ ሰውየው እጁን በማወራጨት እያመለከተ፤ «ሽፍታ አሳዳሪ ነህ? በማለት ፊታቸው ያገኙትን መንደር ሁሉ እንደ ቋያ እሳት እየለበለቡ በመገሥገሥ ላይ ናቸው።

ገብርዬ፤ ከተቀመጠበት ሳይነሣ አንገቱን ሰገግ አድርጎ በሩቅ ተመለከተ። በርግጥም ወደ ጭልጋ በሚወስደው አግጣጫ ሦስት አራት ላይ ጢስ ወደ ሰማይ ሲወጣ ይታያል። ስካርም፤ ቅዠትም ሕልምም አልነበረም። ገብርዬ ከመገረሙ የተነሣ፤ «ለመሆኑ አዝማቹ ማነው አሉ?» ሲል በትዝብት አኳኋን ጠየቀ።

«የቴዎድሮስ የአጎታቸው የደጃች ክንፉ ልጅ፤ ልጅ ጋረድ የሚባለው ነው አሉ።

«አሃ! ነው?» አለ ገብርዬ በምፀት፤ ድምፁን ከፍ አድርጎ። ተጨማሪ ማብራሪያ አላስፈለገውም። የጋረድ ስም መጠቀሱ ብቻ ነገሩን ከሡተለት ቴዎድሮስን በሜራ አወናብደው በሐሰት አሳምነውታል። ግን እንዴት በቀላሉ ሊታለልላቸው ቻለ? ቢጠረጥረውስ ሳያረጋግጥ እንዴት ሡራዊት አዘመተበት? ደግሞስ ወይኒ መምጣቱን በምን ዐወቁ? እሱ ራሱ የሚሔድበትን የነገረው ሰው የለም። ምናልባት ታንጉት የነገረችው ቢኖር ወይዘሮ ደብሬ ናቸው። እሳቸው ነገሩዋቸው? ወይስ በሌላ መንገድ ደረሱበት? እነ ጋረድ ለሜራቸው ሲሉ እስከ ጓዳ ያነፈንፉሉ ማለት ነው? አበስኩ ገበርኩ! በሕሊናው አማተበ። ጠቅላላው ክንውን እንዴት እንደ ተቀነባበረ ለመገመት ሲያሰላስል፤ ታንጉትን ስንኳ ሳያናግር ዝም ብሎ ፈዝዞ ተቀመጠ። እሷም ነገሩ ዱብ ዕዳ ሆነባት አንደበቷ እንደ ተዘጋ ያህል ማዶ ማዶውን አፍጥጣ እየተመለከተች ከተቀመጠችበት አልተንቀሳቀሰችም።

«ጌታው ቁጭ ብለው ነገር ለማስላት ጊዜ የለዎትም። የዘመተብዎ ሡራዊት እየተቃረበ ነው፤ በኋላ በኔ እንዳያማርሩ!»

የሰውየው ኮስተር ያለ አነጋገር፤ ገብርዬን ከሐሳብ ሰመመን አነቃው። የመጀመሪያ ቅጽበታዊ ስሜቱ ወደ ድንኳኑ ለመገሥገሥ ቃጣው። ቀድሞውንም ቢሆን ወደ ድንኳኑ መቆየት ወይ ድንኳኑን መንቀል እንደ ነበረበት አሁን ተሰማው። በገበሬው ማረፊያ ለመቆየት ከሔዱ በኋላ ድንኳኑን መንቀል አስቦ ነበር። ግን ገበሬውና ሌሎችም የመደሩ ሰዎች፤ «የአባ ታጠቅ ጦር አዝማች ድንኳን ለሡፈራችን ክብር ሞገስ ነውና ይቆይልን፤ ልጆች በየተራ ይጠብቁታል» ብለው ስለ ለመኑት ተወው። አሁንም ከአንድ ገበሬ ጎጆ ተደብቆ የተገኘ ከሚመስልበት በራሱ ድንኳን፤ የጣለውን ጥሎ መውደቁ የተሻለ መሰለውና፤ በድንገት ተወራጭቶ በመነሣት አሻግሮ ተመለከተ። ድንኳኑ የተተከለበት ገላጣ ሥፍራ በግልጽ ይታያል። ገና ዐይኑን እንደ ተከለ በአካቢው ጢስ ተነሣ።

«አቃጠሉት እንኳኔን!» አለ ገብርዬ ከራሱ ጋር የሚነጋገር በሚመስል አኳኋን። ዕንባ ተናነቀው። ፊቱን በመዳፉ ሸፍኖ አንገቱን ደፋ። ታንጉት ደፋ አለችና በትከሻው ዕቅፍ አደረገችው። ሰውነቱ በንዴት እንደ መንቀጥቀጥ ሲል ይሰማት ነበር። ይህ ሁሉ የመጣው በርሷ ምክንያት መሆኑ በማወቅ የምታሰበው፤ የምትናገረው፤ የምትይዘው ነገር ጠፍቷታል። ለማጽናናት ለማደፋፈር ስንኳ አንደበቷ ተዘጋባት። ገብርዬ ግን፤ የቁጣ ስሜቱ ሁሉ የተሰበቀው በጋረድና በአክሊሉ ተንኮል ላይ ስለ ነበር፤ በታንጉት ምክንያት የመሆኑ ጉዳይ ለጊዜው በሐሳቡ አልመጣም። ባልና ሚስት በዚህ ዐይነት እንደ ቆሙ፤ ሰውየው ወደ ጓሮ ሔደና ከጥቂት ጊዜ በኋላ በቅሎ እየሳበ መጣ።

«ለጊዜው በጋጥ ያለችው የኮርቻ በቅሎ ይህች ብቻ ናት። ተታች ከመስኩ አንድ የጭነት ከብት ነበረኝ። ግና እንደምታዩት ፈልጌ እስታመጣው ድረስ የሚያቆይን አልመሰለኝም። በዚችው እንደ ምንም ተቸገሩና ባመቻችሁ ጊዜ ትልኩልኛላችሁ» አለ ገበሬው በመቸር ፈንታ፤ ያስቸገራቸው ይመስል ይቅርታ በመጠየቅ መልክ።

የልብስ ከረጢታቸውን ሳይዙ ገብርዬ ከበቅሎው፤ ሲወጣና ታንጉትን ከኋላው ሲያፈናጥጥ በንዴት ከመኮማተሩ የተነሣ እንደ ደመነፍስ ነበር። ሌላው ቀርቶ በቅሎዋን ከደብረ ታቦር በሰው ከመላክ እነ ጋረድ አልዘረፉዋቸው እንደሆነ ሰውዬው በምትኩ የእርሱን መውሰድ፤ ወይም ደግሞ በትንሽ ኮረጆ ገንዘብ ዋጋዋን በብር መክፈል እንደሚቻል አልታሰበውም። በቅሎዋን በኃይል መጭ አላትና ስትሸመጥጥ ሁለት ሦስት ጊዜ ወደ ገበሬው ተገላመጠ። ታንጉት፤ በሁለት እጅዋ ወገቡን እንደ ያዘች ወደ ኋላ ዞራ የዐይኔ አበባን ዐይንዋን ለመሰነባበት ሞከረች። ማልቀስ ስትጀምር አባቷ ዐቅፎ ይዟት ገብቶ ስለ ነበር ከቆመችበት ቦታ አጣቻት።

እነ ገብርዬ ወደ ምዕራብ ከታጠፉ በኋላ፤ የጋረድ ሠራዊት አልደረሰበትም ብለው በገመቱት ቁጥቋጦ በበዛበት ፈፋ ለፈፋ ከተጓዙ በኋላ፤ እንደገና ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ መልሰው ከጋረድ ሠራዊት ጀርባ ወደ ጭልጋ ከሚወስደው መንገድ ገቡ። ሥፍራው ለጊዜው የሚያሠጋ መሆኑን ሲያረገግጡ፤ ገብርዬ በቅሎውና ወደ ኋላ አዞረና በሰላም የሰነበተበትን መንደር ለጥቂት ጊዜ በትካዜ ቃኘው። በየሥፍራው የሚኮለኮለው ቃጠሎ አሁንብ እየተበራከተ የወይኒ ኪዳነ ምሕረት ሰበካን በማዳረስ ላይ ነው። ቀደም ብሎ የተለኮሰው ተቃጥሎ እያበቃ ጥቂት ጥቂት የሚተን ጢስ እየቀረው ሲሔስ አዲሱ የሚነሣው ትኩስ ነበልባል፤ እያዘቀዘቀች ከሔደችው ጀንበር ጋር ይንጸባረቃል።

«እኔስ ሸፈተ ልባል! አገሬው ምን በደለ?» አለ ገብርዬ ከራሱ ጋር ዐይኑን ወደ ገበሬው ቤት አግጣጫ፤ ሲያማትር። በመጀመሪያ እንደ ባዘቶ ሳሳ ያለ ጢስ በቀጭን ሲነሣ፤ ቀጥሎ እየሰፋና እየጠቆረ ሔዶ ከውስጥ እሳት ቡልቅ ሲል አየ። አንጀቱ አብሮ የተቃጠለ መሰለው። በቅርብ ሆኖ ከዚያ ቃጠሎ አጠገብ የተፈጸመው ቢመልከት ኖሮማ ምን እንደሚሰማው እንጃ!

ጋረድ፤ ከሠራዊቱ ጋር፤ በየሠፈሩ እየተርመሰመሰ ሲዘርፍና ሲያቃጥል ቆይቶ የገብርዬ ድንኳን ካለበት ሲደርስ፤ ውስጡንና ዙሪያውን እየፈተሸና ሳይመልጥ የቀረውን አንድ ጠባቂው አስጥሎ በጅራፍና በትርኳሽ ተያያዘው። ጠባቂው ግን፤ ታማኝነቱም ይሁን ድንጋጤው መዓቱ እየወረደበት መልስ ከመስጠት ዘገየበት። በዚህ ጊዜ ጋረድ እግሩን አንፈራጦ ቁሞ አፉ አረፋ ቢጤ እየደፈቀ ጎራዴውን ላጥ

አደረገ። «በሕይወት መኖር አትፈልግም!» በማለት ሲያንባርቅበት ጠባቂው ድንገት የባነነ መሰለ።

«እ እ እ! አለ ሰመመንና ጣዕር በሚመስል ድምፅ።

«ገብሬ የት አባቱ ሔደ? ሕይወትህ እንዲተርፍ ከፈለግህ ብትናገር ይሻልሃል?» ለንገት ሽሚያ ዙሪያው ያሰፈሰፈውን ጎራዴ ሲመለከት፤ «እዚያ እዚያ ማዶ» አለ በደመ ነፍስ አንድ እጁን ወደ ገበሬው ቤት እያመለከተ። «ታን - ታንድ ሰው ቤት ነው ያረፉት» የዘረጋውን እጅ ሳያጥፈው የጋረድ ጎራዴ አንገቱን ቀለበውና መትረፉንም ሆነ የፈራውን ሞት መቀበሉን ላያውቀው ተገላገለ።

ገበሬው ለመፍለጫያ ከሚያገለግለው የንግድ ጉማጅ ላይ ተቀምጦ ያይኔ አበባን እያባበለ ጠበቃቸው። እድንኳናቸው ሲያጧቸው የት እንደ ሔዱ ጠይቀው እንደሚረዱ ገምቷል። ከመድረሳቸው በፊት ሸሽቶ ማምለት ይችል ነበር፤ ምን እንደ ያዘው ራሱም በትክክል አልተረዳውም። ባንድ ፊት ከቤቱ ደግሞ ማነው የሚያባርረኝ? የሚል እልህ ነው። በሌላ በኩል እኔ መሸፈቱን ዐላውቅሁ። የእግዜር እንግዳ በአሳረፍኩ ምን አጠፋሁ? በሚል ሐሳብ ምንም ጉዳት እንደማይደርስበት በመገመት ነው። ሌላው ቀርቶ የሚፈልገውን ሰው ያላስተናገዱ ቤቶች ሁሉ መቃጠላቸውን ግን አላስተዋለውም ነበር።

ብዙም ሳይቆዩ ደረሱ። ጋረድ ከበቅሎው ዱብ ብሎ ወረደና ወደ ፊት ቀደመ። እንዳቃጠለው ቤትና ድንኳን እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ነበር። የደረቀው የምራቅ አረፋ በከንፈሩ መጋጠሚያ ነጭ መሥመር አብጅቷል። ዐይኑ ጉርሽጥ መስሏል። ተከታዮችም የእርሱን ስሜት የሚያስተጋቡ ይመስላል። ከፊሉ ጎራዴውን እየነቀነቀ ይንቆራጠጣል። ከፊሉ እዲሰማለት አድርጎ ጥርሱን ያፋጫል። ሌላው ፊቱን አኮሳትሮ ይገላምጣል። የተለየ እርጋታ የሚታይበት ደብተራ አክሊሉ ብቻ ነበር።

ከዚህ በፊት መንደሮቹ በእሳት ሲለኮሱ፤ የገብርዬ ድንኳን ሲቃጠልና ጠባቂው ሲገደል እንዳደረገው ሁሉ፤ ከበቅሎው ሳይወርድ እየኮለኮለ ወደ ዳር በኩል አቁሞ ጠቅላላውን ትርዒት ያስተውል ጀመር። የሰጠው ፍርድ ሲፈጸም የሚመለከት ዳኛ ዐይነት ነበር። እርሱ፤ የቅጣትን፤ የቁጣን የበቀልንና የጥፋትን ኃይል የሚፈጥር ብልሃት ነው። ይህ የፈጠረው ኃይል እንዴት እንደሚሠራ በሚገባ ማወቅ አለበት። ሊቆጣጠረው፤ ሊመራመረው የሚችለው ሲያውቀው ብቻ ነው። አንዳንድ ጊዜ ጋረድ እንደ ዕብድ መወራጨት እያስገረመው ከንፈሩ በፌዝ ፈገግታ ወደ አንድ ጎን ጠመም ይላል።

«የዚህ ቤት ባለቤት አንተ ነህ?» አለ ጋረድ። ጥያቄ ሳይሆን የደነፋ ቁጣ ነበር።

«አዎና ጌቶች!» ሲል መለሰ። ከተቀመጠበት ተነሥቶ ሳይነቃነቅ።

«ኧረ የማን አባቱ ጀለንፎ ባለጌ ነው! ደሞ እጅ አይነሳም?» በማለት ጋረድ ጎራዴውን እየነቀነቀ ጮኸበት።

ገበሬው፤ ክንዱን ላይ ተንጠልጥላ የነበረችውን ያይኔ አበባን ገፋ አድርጎ ለጥ ብሎ ሰገደ።

«ገብሬ የት ያለው?»

«ገብሬ? ገብሬ?» የተጠየቀው ማንን እንደሆነ ቢያውቅም ያላወቀ መሰለ። የስሙን አጠራር አልወደደውም ነበር።

«ገብርዬ ነዋ! ገብሬ ገብርዬ ያው ነው።»

«የታባቱ ዐውቄው ጌታው» ጋረድ ሲጦ የሰውየው አንድበት ርጋታ አልተቀይረም።

«እንዴት? ከቤትህ አልሰነበተም?»

«እሱማ መቸስ ቤት ለእግዜር እንግዳ ነው!»

«ድንቄም እንግዳ!» ሲል ጋረድ በፌዝ አንባረቀና አሽከሮቹን በዐይኑና አንገቱን ሰበቅ በማድረግ ሲያመለክታቸው፤ ለመፈተሽ እየተሯሯጡ ወደ ሁሉቱ ቤቶች ገቡ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በማስተባበል ራሳቸውን እየነቀነቁ ተመለሱ።

«እኮ የት አባቱ ሔደ ነው የምልህ?» ጋረድ የአፉ አረፋ በከንፈሩ መጋጠምሚያ መፍለቅ ጀመረ።

ሰውየው መልስ አልሰጠም።

«ምን ይዘጋዋል? አትናገርም!» ጋረድ እድነገና ጮኸበት።

«በእውነቱ እኔ አላውቅም ጌታዬ።»

ከገብርዬ መጥፋት፤ የሰውዬው እህልና ታብዮ ጋረደን ይበልጥ በንዴት አንጨረጨረው። መላ ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ገባ፤ ጥሩስን አፋጨ፤ ገብርዬ ካመለጠ ነገር ተበላሸ ማለት ነው።

እየተንደረደረ ሔዶ ሰውዬውን በቃሪ ጥፊ ሲያጮኸው ነፍሱን አያውቅም ነበር። ሰውዬውም «ይህን ይወዳል መሬ!» ብሎ በዚያ በገበሬ መዳፉ ሰማይና ምድሩን ሲያደባልቅበት እንደዘሁ አልታወቀውም። ወዲያው በቅጽበት ደግሞ

አንድ የጋረድ ባለሚል ፍክሮ ጎራዴውን ሲሰነዝርና የሰውየውን ጭንቅላት ከመሬት ወድቆ ሲንከባለል አንድ ሆነ። ያይኔ አበባ ከድንጋጤዋ የተነሳ የሆነውን በትክክል ባትገነዘብም እሪታዋን ለቀቀችው።

«ልጅትዋን ብትይዟት አይከፋም። ስታድግ መልካም አገልጋይ ይወጣታል። ወይም ደኅና ዋጋ ታወጣለች» ሲል አሁንም ድርጊቱን እንደ ታዛቢ በርጋታ የሚመለከተው አክሊሉ ምክር ሰጠ። እሪ እያለችና ትናንሽ እጆችዋን እግሮችዋን እያፈራገጠች ስታለቅስ ወዲያው ቀለቡና ከአንዱ አጋሰስ ላይ አስረው ጫኑዋት። ከዚያም ሁለቱን ቤት በእሳት ለኩሰው አሰሳቸውን ለመቀጠል ወደ ሌላ መንደር አመሩ።

ከወጣትነት አንሥቶ ብዙ መንገድና ዘመቻ የሔደው፤ ብዙ ውጊያ ላይ የዋለው ገብርዬ፤ ከተዋጊ ኮብላይ፤ ከፈራጅ፤ ተፈራጅ የሆነበት የአሁነኛ ጉዞው ራሱን ፈትኖና ተፈታትኖት ራሱን የታዘበበት፤ የዓለምንና የሕይወትን ተለዋዋጭነት የተገነዘበበት ነበር። የውሃ ዋናና አደን ማዘውተሩን ያልተወ ቢሆንም በረጅም፤ ጉዞ ገረድ የከብት ጀርባ የለመደ መሆኑን ያወቀው በዚህ ጊዜ ነው። በተለይ ቋራ ላይ ከካሣ ጋር ከተገናኘበት ጊዜ አንሥቶ ለመንገድ ሰጋር በቅሎ ለግልቢያ ሽመጣጭ ፈረስ ተለይቶት የማያውቅ ስለ ነበር፤ አሁን ለሁለት የተፈናጠጣት በቅሎ እከሥር መብረክረክ ስትጀምርና ወርዶ በእግሩ ማኮብኮብ ግድ ሲሆንበት፤ አካላቱ እንደ ዱሮው እንደማያስመካው ተረዳ። አንድ ቀን በእግሩ እንደ ተጓዘ ጡንቻው ይተሳሰር ጉልበቱ ይብረከረክ፤ አንጓው እንደ ደረቅ ዕንጨት የሚሰበር መስሎ ይሰማው ጀመር። በዚህ ላይ ሰውነታቸውን ትንሽ ገባ ብለው እህል ውሃ እንዳይጠይቁ ከቴዎድሮስ ፊት ቀርበው ከማስረዳታቸው በፊት፤ ወሬውን የሰማ «አረመኔ» ተቀዳድሞ መሾሚያ መሸለሚያ እንዳያደርጋቸው ወይም የጋረድ ሰው እንዳያገኛቸው ሠጋ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሥጋና ጠጅ የለመደውን ሆዳቸውን በዱር ፍራፍሬና ሥር እያስታገሡ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። አብዛኛውን ጊዜ የሚጓዙት መንገድ እያሳበሩ ነበር፤ መንገደኛ እንዳያጋጥማቸው ነው። ግን ይህ ደግሞ ጨርቃቸው ከላያቸው ላይ እሲቦጫጨቅ እግርና እጃቸው የተተለተለ እስኪመስል ድረስ የቆንጥርና የሾህ ሲሳይ አደረጋቸው።

የአካል ዳካሙ፤ የመንፈስ ቁስሉ የተሰማት ታንጉት እርስዋ ወርዳ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በበቅሎ እንዲጓዝ በመወትወት፤ «አንገላታሁህ የኔ ጌታ?» ትለዋለች።

«ደኅና ነኝ!» ይላል በልህ ጥርሱን ነክሶ። ‹ይልቅስ ድካሙ አንቺን ነው የሚጎዳው› ይላል፤ እርግዝናዋን ሲያመለክት ነው።

«አንተ ታልወጣህ እኔ ሁለተኛ አልወጣትም። ሌጣዋን ትሔዳለች እንጂ!» ታንጉት በእግርዋ እያዘገመች ገብርዬ በበቅሎዋ ጥቂት ይጓዛል። ግን ስሜቱ ክብደት፤ ከእግር ጉዞ ድካሙ ይብስበታል።

«ደብረ ታቦር ተደረሰነ በኋላ ብታባርረኝ አባ ታጠቅም አይፈርድብህም!» ትለዋለች ሌላ ጊዜ።

‹አንቺ ምናረግሽ? ነገሩ ሌላ› ይላታል።

‹የማይሆን ነገር ባያምረኝ ኖሮ፤ ስለት ላስገባ፤ ጠበል ልዘክር ባልል ኖሮ መቸ ይኸ ሁላ› በራስዋ ላይ በመፍረድ በትካዜ ባሕር ውስጥ ትሰጥማለች።

‹ያለፈው ዐለፈ። ብቻ በደኅና እንድረስ› ሲል ያጽናናታል።

በሦስተኛው ቀን፤ ቆላውን ወጥተው ከደጋው አገር እንደ ደረሱ፤ «አውርደኝ! አውርደኝ!» አለች ታንጉት በጣዕር ድምፅ። ገብርዬ ተፊት ሲጓዝ እንደ ነበር ዘወር ሲል፤ ለመውደቅ ወደ ጎን ዘምማለች። ከንብል ከማለቷ በፊት ተንደርድሮ ደገፋት።

ምን ሆንሽ? ምን ነካሽ?» ከድንጋጤው የተነሣ የገብርዬም ድምፅ የማቃሰ ቃና ያዘ።

«ደም - ደም መታኝ መሰለኝ! እስቲ ወደ ጥላ ቢጤ ውሰደኝ!» አለች፤ እያቃሰተችና እንደ ማማጥ እየቃጣት።

ከቁጥቋጦ ሥር ነጠላ ጋርዶላ ዐርፋ ከቆየችና እርሱም ወደ ምንጭ ወረድ ብሎ የተበላሸውን ጨርቅ ለቃልቆ ከተመለሰ በኋላ ነበር ሐሳቡ በመጠኑ የተሰበሰበለት። እንደ ዋዛ ወርወር ያደረገው ዐይኑን ትክል አድርጎት ቀረ። መልሶ ግራና ቀኝ ተመለከተ። ተነሥቶ ዙሪያውን ቃኘ። ማመን ቢያቅተውም መንገድ ዳር ትተዋት የነበረችው በቅሎ በአካባቢው ጨርሶ የለችም። ተዘዋውሮ ከፈለገ በኋላ ዕድላቸው ገርሞት ቁጭ ብሎ አሰበ። አንዳንድ ልማደኛ ከብቶች እንደሚያደርጉት የቆላውን አየር እያሸተተ ወደ አገርዋ ተመልሳ ከሆነ አይደርስባትም። ታንጉት ውርጃው የመጣባት ከረፋዱ ላይ ሲሆን፤ አሁን ፀሐይ ወደ ምዕራብ በኩል አዘንብላ ነበር። ታንጉት፤ ትንሽ ጠና እስክትል ለምኖ ከአንድ ቤት ለማስጠጋት አሰበና ከአካባቢው አንድ ጊዜ «ክንፉ ቀመስ» ስለነበር ምናልባት ልጃቸውን ጋረድን ከሚደግፉ ሰዎች ቤት እንዳይወድቅ ሠጋ። የሚያጣሩበት መንገድ አልነበረም። የበቅሎዋን መጥፋት ለታንጉት ከነገራ በኋላ፤ «እስቲ ምናልባት ካህናቱ ለመታመን ቢሻሉ ተዚያ ማዶ ቤተ ክርስቲያን ደጀ ሰላም እንጠጋ» አላት፤ እብሩቅ ከጉብታ ላይ የተተከለችውን ቤተ ክርስቲያን እየተመለከተ።

ታንጉት በክንድዋ ትከሻውን ተደግፋ፤ እያረፉ እየተነሡ ሲያዘግሙ የሲራራ ነጋዴ ከኋላቸው ደረሰ። የጭነት ከብቱ እያለከለከ፤ ጫኑ እንደ ዋዛ እያያቸው ዐለፈ። በግራጫ በቅሎ ላይ ተቀምጦ በኋላ ይከተል የነበረው ቱጃር ነጋዴ ከአጠገባቸው ሲደርስ ቆም ብሎ አስተዋላቸው። «እንደምን ዋላችሁ? ደኅናም አይደላችሁ? ምን አገኛችሁ?» ሲል ጠየቀ።

«አሞብም ድንገት» ገብርዬ ዐቅመ ቢስ መሆኑ አስተሳሰቡንም አነጋገሩንም ባላገር መሰል አደረገበት።

«ዛዲያ ወደ መንደር መውሰዱ አይሻልም ነበር?»

ነጋዴው ዐልፏቸው እንደ መሔድ ሲል ገብርዬ የመጣው ይምጣ ብሎ ወሰነ። «ጌታው!» አጠራሩ ከምላሱ ላይ አዲስ ሆነበት። «አንድ ነገር ልለምንዎት?»

«የምችለው ነገር ተሆነ። ምንድነው?»

«መጀመሪያ ደብረ ታቦር እስትደር ምሥጢሬን ላያወጡ ይማሉልኝ።»

«እኔ ስለ ምሥጢርህ ምን ቸገረኝ ወንድሜ» ጉዞውን ለመቀጠል፤ በቅሎውን በርካቡ ነካ አደረገ።

«በእግዜር ይዤዎታለሁ» ሲል ገብርዬ እንደ ገና አስቆመው።

«እንደዛሬው ሰው ለምኜ አላውቅም። የሷ ነፍስ ነገር ሆኖብኝ ነው» አለ ታንጉትን በዐይኑ እየተመለከተ።

«ችግርህን ንገረኝ?»

«ይማሉልኝ» አለ ገብርዬ፤ ታንጉትን ከመገዱ ዳር አሳርፎ የመሐላውን ዐይነት በጥሶ እያሳየ።

ነጋዴው ነገሩን እንደ ቀልድ እንዳይመለከተው ገብርዬ በጭንቅ ላይ መሆኑ ያስታውቅ ነበር። እንቆቅልሽነቱ ሳበው። ከበቅሎው ወረደና፤ የነጨውን ሣር፤ «ይኸውልህ!» ሲል ደጋግሞ በጠሰለት። ገብርዬ ምንነቱን ሲነግረው፤ ነጋዴው ሲጥለው የነበረውን ሣር እንደ ያዘ ፈዝዞ ቀረ። «ድፍን ወይኒ የተቃጠለው አንተ ሸፍተህ ነው አልተባለም?»

«መባልማ ተብሏል። ታሪኩ ረጅም ነው። ወደፊት አጫውትዎት ይሆናል። የምለምንዎት። ግን ይህች በሽተኛ ሲሆን ደብረ ታቦር፤ ታለበለዚያ ከሚታመን

ሠፈር እስክደርስ፤ የጋረድ ሰዎችም ቢያገኙን የርስዎ ሰዎች እያስመሰሉ ለማድረስ እንዲረዱን ነው» አለ ገብርዬ።

በእርግጥ በቴዎድሮስ ላይ የሸፈተ ሰው ካላበደ በስተቀር ተመልሶ መግባት እንደማይፈልግ ነጋዴው በመገመት «መናኸሪያችን ስንኳ ይፋግ ድረስ ነው። ለሁሉም መጀመሪያ ተዚያ እንድረስ» አለው።

ነጋዴው የኮርቻ በቅሎውን ለታንጉት ሰጥቶ ገብርዬና ራሱ ጭነት በተጋባላቸው ሁለት አጋሰሶች ላይ በድብዳብ ተቀምጠው በሰላም ይፋግ ሲደርሱ ነጋዴው አዲስ ሐሳብ አመጣ። በገብርዬ ላይ የተፈጸመውን ተንኮል ከማመኑ ሌላ፤ በመገድ ላይ ስለ ቴዎድሮስ ያወጋለት ሁሉ አስደንቆት ነበር። «ፍቃደኛ ሆናችሁ ታቀረባችሁኝ፤ አብሬያችሁ ደብረ ታቦር ልውጣና የዚያን ታምረኛ ሰው ፊት ልየው። በየደረስኩበት ለወሬም ይመቸኛል» ሲል ጠየቀ።

«ምን ቸግሮኝ!» አለው ገብርዬ።

ከአንድ ቀን ዕረፍት በኋላ፤ ሦስት በቅሎ ተጭኖ ሦስቱም ወደ ደብረ ታቦር ጉዞ ቀጠሉ።

የደብረ ታቦር ከተማ፤ ከፊት ለፊታቸው ብቅ ሲል ቀኑ ገፍቶ ጀምበር በምዕራብ በኩል ሩብ ያህል ተደፍታለች። በሩቅ ከፊት ለፊታቸው የጉና ተራራ ጭጋግ ለብሶ የሰማይ ጣሪያ ጥሶ የገባ ይመስላል። ከግራቸው እንደዚሁ በሩቅ የደጋ መልዛ ተራራ ሰማይን እንደ ተሸከመ ግድግዳ በርዝማኔ ተገትሯል። ከቀኝ በኩል፤ እንደ መልካም የጤፍ ክምር መስሎ ከወጣው ተራራ ላይ ከተተከለው የየሱስ ደብር መሳለሚያ ላይ ሲደርሱ የቴዎድሮስ ሠፈርና የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ወደ ታች ተንጣሎ ታያቸው። ገብርዬ ክንዱን ከበቅሎዋ ጀርባ ላይ ደገፍ አድርጎ ቆመና በጣም ተከዘ። ከአካል ድካሙ ይልቅ የመንፈስ ሠቀቀኑ ከብዶ ተሰማው። እንደዚህ ያለ ጉዞ እንኳን በውኑ በሕልሙም አልታየው ነበር።

አሁንም ቢሆን እውን መሆኑን ማመን ያስቸግረዋል። ወይኔ ገብርዬ! እንደ ተራ ወንበዴ ዱር ለዱር ልሽሎክሎክ ብሎ ራሱን ነቀነቀ።

ገብርዬ፤ ከአባ ታጠቅ ጋር ለመገናኘት በጣም ቸኩሎ ነበር። ግን አደጋው ደግሞ ግልጽ ሆኖ ታየው። ‹የወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል› እንዲሉ፤ ዐፀደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ውሻ እንደሚቀጠቀጠው ሁሉ፤ እርሱም የባልንጀራ አለቃውን አባ ታጠቅን የከዳ ይሁዳ ነው ተብሎ ተወርቶበታል፤ ሰው ሁሉ ፍቅሩንና አክብሮቱን ሊገልጥለት በተሽቀዳደመበት ሰፈር ከሰላምታ በፊት ሰይፍ መዝዞ እውነቱን ከመጠየቅ በፊት አድብቶ አንገቱን በመቀንጠስ ወደ ቤተ መንግሥት የሚሮጥ

የትናንት ዕውቂያ ወይም ጓደኛ ቢያጋጥም አያስገርምም። በስምና በመልክ ብቻ የሚያውቀውም ቢሆን፤ በመጀመሪያ አንገት ቀንጥሶ በኋላ መመራመሩን ይመርጣል። ችግሩ የተቀነጠሰ ጭንቅላት አይቀጠልም። ሌላው ቢቀር፤ እውነቱ ሳይታወቅ መሞቱ ድርብ ውርደት መስሎ ተሰማው።

መሸትሸት እስኪል ከአንድ ችፍርግ ቁጥቋጦ ሥር ተከልለው ዐረፉ። ገብርዬ፤ ብዚያ ድካሙና የሐሳብ ስመመኑ፤ ከኮርቻው ላይ ደገፍ እንዳለ ወዲያውኑ እንቅልፍ ይዞት ሔደ። ታንጉት ጡንቻው በመጠኑ እንዲለሳለስ ቀስ አድርጋ ቋንጃውንና ቁርጭምጭሚቱን ስታሻሽለት እንደ ቆየች በመጥፎ ቅዠት ባንኖ ሲነቃ ጀንበር በምዕራብ አድማስ ጠልቃ ነበር። ከላይ ጨረርዋን ገና የሚቀበለው ሰማይ ግን ፍም መስሎ ነበር። የደም ምልክት ነው ይባላል። የማን ደም? የኔ ደም? የጋረድና የአክሊሉ ደም? ወይስ ሌላ ጥፋት ሊመጣ ነው? ያም ሆነ ይህ የሚፈጸም ነገር ቢኖር በሐሳብ ቀስ በቀስ ከሚጨርሰኝ አንድያውኑ ዛሬ ይለይልኝ ሲል ቆረጠ።

ከዋና ከተማው እስኪገቡ ሙሉ ጨለማ እንደሚሆንና ሰውም ወደየቤቱ እንደሚከተት ገመተ። ግብዣ ከሌለ የቤተ መንግሥቱ ድንኳን አካባቢም ጭር እንደሚል ገመተ። ራት ተበልቶ አባ ታጠቅ ካሣ ከሊቀ መኳስ ዮሐንስና ከሌሎችም የቅርብ አማካሪዎቻቸው ጋር በእልፍኝ ወይም በቤተ መጻሕፍታቸው፤ ስለ ዓላማቸውና ስለ ዕቅዳቸው የሚወያዩበት ጊዜ ነው። ምናልባት አንዳንዶቹ ተሽቀዳድመው ሰይፍ ለመምዘዝ የሚራወጡ ቢሆንም፤ አንዴ ከፊታቸው ከቀረበ እወነቱን ለመንገር ዕድል አያጣም። መቸም ፍትሐ ለመስጠት የሁለት ወገኖችን ጉዳይ ማዳመጥ ያስፈልጋል። ቴዎድሮስ ደግሞ በፍትሐ ያምናል። ለመናገር እንዴት ዕድል ይነፍገዋል። ችግሩ፤ ድንገት የሚፈነዳው ቁጣው ነው። ቢሆንም፤ ተዋበች በአጠገቡ ካለች ደግሞ እሳት ቁጣውን ውሃ ሆኖ በቅጽበት ታቀዘቅዘዋለች።

ገብርዬ ታንጉትን አገላብጦ ጉንጭዋን ሳማትና ደግፎ ከበቅሎዋ ላይ አወጣት። «እናንተ እንግዲህ የሚያስጠጋ ዘመድ ፈልጉና......» ሲል «እስከመለስ» የሚለውን ቃል የተጠራጠረ ይመስላል ሳይጨርስ ተወው።

«ኧረ ምን ዘመድ ይጠፋል? የነጋድራስ ይማም ቤት፤ ቤቱ ማለት ነው!» አለ ነጋዴው።

«ስለኔስ ሰው የጠየቀሽ እንደሆነ ግን የት እንደ ደረሰ አላውቅም፤ ብቻየን ነው የመጣሁት በያቸው፤ ነገሩ እስቲለይ!» ሲል ተሰናበታትና መች ብሎ በቅሎዋን መንገድ አሳያት። ከዚህም ጸሎት እንደሚያደርስ ክንዶቹን ከደረቱ ላይ አመሳቅሎ ሳይንቀሳቀስ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆመ። ዐይኖቹ ዕንባ ቋጥረው ነበር። ምናልባት ነገ ጧት ከታንጉት ጋር በሰልማ አይገናኙ ይሆናል። ወይም ደግሞ ለመጨረሻ ጊዜ

መሰነባበታቸው ይሆናል። ከንፈሩን ነክሶ ወደ ፊት ተራመደ። መሞቱ ካልቀረ በጭልጋ ዱር የጅብ ራት ከሚሆን ከቴዎድሮስ ፊት መውደቁ ይሻለዋል።

አንደኛውን የዘብ ክልል ያለ ችግር ሰተት ብሎ ዐለፈ። የጠየቀው አልነበረም፤ ዘብ አንቀላፍቷል፤ ወይም ሌላ መኮንን መስሎታል። ከሁለተኛው ዘብ ክልል ሲደርስ፤ «ቁም! ማነህ! ሃ! ሃ!» የሚል ድምፅ ጸጥታ በሰፈነበት ጨለማ ውስጥ አስተጋባ።

ገብርዬ ስቅጥጥ አለው። የመጀመሪያ ስሜቱ በጎራዴው ስለት ጸጥ ማሰኘት ነበር። ነገር ግን የታዘዘውን ብቻ የሚፈጸም ሰው ሕይወት ማጥፋት ከባድ በደል መስሎ ተሰማው። ባይሆን ሌላ መንገድ ካጣ መቸስ ምን ይደረጋል። ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠራረገና ቢያዋጣ ያዋጣ ሲል እንደ ራስ እንግዳ፤ ድምፁን ጎርነን አደረገና፤ «ጎበዝ እንደዚህ ነቃ ብሎ መጠበቅ ነው» እያለ መንገዱን ቀጠለ።

«ተመልሰው መጡ እንዴ ጌታዬ?» የሚል ድምፅ ከወደ ጀርባው መጣ። እየቃጣ፤ ራሱን በመጋበዝ እየገታ፤ እንደ ሠጋር በቅሎ በማኮብኮብ ገሠገሠ።

ገብርዬ የሰው ደም እንደ ውሃ በጨቀየበት፤ ሬሣ ተነባብሮ መረማመጃ ባሳጣበት የጦር ሜዳ ላይ ውሏል። ግን እንደ አሁኑ መንፈሱ ታውኮ አያውቅም። ልቡ ደረቱን ሰብሮ የሚወጣ እስኪመስል ድረስ መታ። በዚያ ቀዝቃዛ ምሽት ሰውነቱ በላብ ውረዛበት። ከቴዎድሮስ ፊት መቅረቡ ነው? ወይስ የሞት ፍራቻ ነው እንዲህ የሚያረገኝ? ብሎ ራሱን በመጠየቅ ራሱን በጣም ታዘበው። አዲስ በሆነ ፈተና ወቅት ተፈጥሮው እንዴት እንደሚለወጥ እስከ አሁን ባለመገንዘቡ ተገረመ። ከዚህ በኋላ ግን ወደ ኋላ መመለስ የለም። እየተንደረደረ ከቴዎድሮስ ዋና ድንኳን ደረሰና በሩን ወደ ላይ ገለጥ አድርጎ ተመለከተ። ጧፍ በየመቅረዙ በርቶ አዳራሹ ፍንትው ብሎ ይታያል። ግን፤ ዕቃም ሰውም ድምፅም የለም። ድግሱ የተከተተለት ዳስ መስሏል። የልቡ ምት አካባቢውን የሚቀሰቅስ እየመሰለው ዙሪያውን ሲመለከት ከአንድ ጥግ በኩል ከጥቂት ጓዝ መካከል የሰው ቅርጽ የለየ መሰለው። ከአንዱ መቅረዝ ላይ ሻማውን አነሣና ይዞ ወደዚያ ሔደ። ራሱ መሰለው። አንድ ዋንጫ ተንከባሎ ወድቆ ከውስጡ የፈሰሰው መጠጥ ዕፊሩን አርሶታል። ከአጠገቡ አንድ ቅምጫና አግጣጫ እንደ ዘረጋ የተጋደመው የራሱ ሻለቃ አዛዥ ነበር። ማመን አቅቶት ጭልጥ አድርጎ ወስዶታል። ገርበብ ሳብ - ቡልቅ ሳብ - ቡልቅ ይላል። የራሱ መንፈስ በሰቀቀን ተወጥሮ ሳለ፤ ሻለቃው፤ ነገር ዓለሙን ችላ ብሎ በመስከሩ ገብርዬ ይህ ነው የማይባል ንዴት ብልጭ አለበት። በጥፊ አቃጥለው አሰኘው የቃጣበትን እጁን እንደ ምንም መለሰው።

«ሰንደቄ! ስንደቄ! አንተ ሰንደቄ!» ገብርዬ የወታደሩን ትከሻ በኃይል አንገጫገጨው።

«እ! እ! ማነው እሱ ሰውን አላስተኛ የሚል?» አለ ወታደሩ ለጥቂት ጊዜ ያህል ዝም ብሎ እንደ በድን ከተዝለፈለፈ በኋላ ዐይኑን ገለጥ ክድን እያደረገ።

«እንፈፍ! ተነሥ! ተነሥ! ነው የምልህ!» እያለ ገብርዬ እንደገና በኃይል ነቀነቀስ።

«እኮ ቀስ!»

«ተነሥ ነው የምልህ!» በማለት ገብርዬ ከዛፍ ፍሬ እንደሚያራግፍ ዐይነት ሁለት ትከሻውን ፈጥርቆ አንገፈገፈው።

ሻለቃው እየነቃ ሔደ። «ምንድነው ጥድፊያው? ድንኳን ጠብቅ እንጂ ዘመቻ ተነሣ አልተባልኩ! ድንኳን እየጠበቅሁ ነው። በተረፈ ግን አለቃ እንደሆነ የለኝም።»

«አለቃህ ነኝ!»

«ማን?» ወታደሩ በመገረም አኳኋን ዐይኑን ብልጥጥ አደረገ።

«እኔ ገብርዬ።»

«ገብርዬ? ገብርየማ......»

«አዎ ገብርዬ ነኝ» በማለት ገብርዬ ወታደሩ በሜባ እንዲያየው ሻማውን ከፊት ለፊቱ ድቅን አደረገው። «እየኝ! ገብርዬ ነኝ።»

ወታደሩ በመጠራጠርና በመገረም አስተዋለው። «ብትሆንም ተቀይሜሃለሁ፤ አንተ አለመንከኝም፤ ታጠቅም ባንተ ጠረጠረኝ፤ ተሁለት ያጣ ጎመን ነው የሆንኩት። ስለይህ፤ ለዚህ ተጅ ነው መድኃኒቱ!» እጁን ወደ ቅምጫናው ዘረጋ።

ገብርዬ ክንዱን ጨበጥ አደረገው። «ይኸ መድኃኒት አይደለም። አንተም የምትቀባጥረው አይገባኝም።»

«ዛዲያ ለምን አልወሰድከኝም?»

«የት?»

«ጽት...እህ.....ስትሼ......»

«አልሸፈትኩም!» ገብዬ ሳይወቀው ጮኸ።

«እህ? ሽፍተህማ ሠራዊት ዘምቶህ!»

«ሐሰት ነው!» ገብርዬ እጁን አወራጨ።

ወታደሩም እኔ ምናውቃለሁ በሚል ስሜት ትከሻውን ነቀነቀ።

«አታምነኝም?»

«ባምንህማ ነበር አብሬህ ስዘምት የኖርኩት።»

«አሁም እመነኝ።»

«እኔ ማመን አለማመን ምን ዋጋ አለው? አባ ታጠቅን አሳምን እንጂ!!»

«ለሱ አይደለ! በረሃ ለበረሃ ስኳትን የመጣሁት። ለመሆኑ የት ሒዶ ነው፤ ድንኳኑ እንደዚህ ወና የሆነው። ዘመቻ ነው እንዳልል ሰንደቅ ድንኳኑን ሳይነቅል አይነሣም።»

የተዋበች ሕመም እየጠናባቸው ስለ ሔደ ለማንኛውም ነገር ከድንኳን፤ ቤት ይሻላል ተብሎ፤ የተጀመረው ቤት እስኪያልቅ ለጊዜው ወደ ራስ ጉግሣ አዳራሽ መዛወራቸውን ሰንደቁ ነገረው።

የተፈጸመበት ሤራ፤ የጉዞውንም ሁናቴ ከተረከለት በኋላ አብረው ሔደው ስንደቁ ተጠግቶ በመሰለል እንዳረጋገጠው፤ ገብርዬ ማን መሆኑ ሳይታወቅ ከአዳራሹ ለመግባት እንደ ድንኳኑ ቀላል አይሆንም። ግቢው ዙሪያውን የታጠረ ሆኖ መግቢያው በር አንድ ብቻ ነው። ከበሩ ላይ በርከት ብለው የተኮለኮሉት ዘበኞች አንድደው የሚሞቁት እሳትም በአጠገባቸው የሚያስፈልገውን ሰው ማንነት በቀላሉ ለመለየት ያስችላቸዋል። በዚህ ላይ ቴዎድሮስ ከሰዎች ጋር በቆይታ ላይ ስለሆኑ፤ ያልተፈለገ ወይም አስቀድሞ ያልተፈቀደለት ሰው እንዳይገኝ ተብሎ ታዟል።

አልቃና ጭፍራ አዳራሹን በሩቅ እየተመለከቱ ዘዴ ተመካከሩ።

«ገብርዬ መጥቷል ብለው ለምን ገብተው አይነግሩልንም?» ሲል ሻለቃው ሐሳብ አቀረበ፤ ቴዎድሮስ ወዲያው እንደሚያስጠሩት በማመን።

ገብርዬ ራሱን ነቀነቀ። መልእክቱ በእርግጥ ከደረሰ ለክፉም ሆነ ለደግ ወዲያው መጠራቱ አይቀርም። ግን ‹እባብ ያየ በልጥ ይበረግጋል› እንዲሉ፤ በእነጋረድ ሤራ ማንን አምኖ ማንን እንደሚጠረጥር እርግጠኛ ሊሆን አልቻለም። ቴዎድሮስን ማሳመን ከቻሉ፤ ከእልፍኝ አስከልካይ አንሥቶ እስከ ዘበኞቹ ድረስ የራሳቸውን

ሰው አዘጋጅተው እንደሆነስ? ቴዎድሮስ ፊት በሕይወት መቅረቡ፤ ሤራቸውን የሚያጋልጥባቸው ስለሚሆን ፊት በሕይወት መቅረቡ፤ ሤራቸውን የሚያጋልጥባቸው ስለሚሆን አስቀድመው ከማጥፋት አይመለሱም። ጉዳያቸውን ሸፋፍነው የሚያስቀሩበት ሌላ ምንም መንገድ የላቸውም። ከገደሉት በኋላ ምክንያት መስጠት ቀላል ነው። በቴዎድሮስ ላይ አደጋ ለመጣል አድብቶ ሲገባ ያመሰግናቸዋል፤ ይሸልማቸዋል።

«ይህማ እንደሳት ራስ በርረን ወጥመዳቸው ውስጥ ገባንላቸ ማለት ነው። የለም የሚያዋጣን እንደ ምንም ሾልኮ ማለፍ ነው። ይልቅስ አንድ ሐሳብ መጣልኝ። ካልገባህ ብለህ ወይስ ሰካራም መስለህ፤ ነገሩማ አሁም እንደ ሰከርክ ነህ.....ከበሩ ላይ ጭቅጭቅና ግርግር ፍጠር። ዛዲያ ሁሉም ባንተ ላይ ሲረባረቡና ሲያተኩሩ እኔ በአጥሩ ዘልዬ ልግባ። አጠር ያለ ስለሆነ የሚያቅተኝ አይመስለኝም።

ሰንደቁ በሞቃት ስሜቱ ለአምባጓሮ የጓጓ ይመስል፤ ገብርዬ ንግግሩን ሳይጨርስ «ምን ቸገረኝ!» አለና እንደ መራመድ ቃጣ።

«ቆይ!» ሲል ገብርዬ በክንዱ ሳብ አደረገው። «ዐውቀህ ግባበት።»

«ምኑን?»

«አደጋ ሊያደርሱብህ ይችላሉ።»

«አንተን ይቅናህ እንጂ ለኔ አታስብ። ጦር ሜዳ ውዬ የማላውቅ አደረከኝ እንዴ?»

«ያ ሌላ ይኸ ሌላ።»

«እሳት ካየው ምን ለየው?»

ገብርዬ ምክንያቱን ያላወቀ ቅሬታና ኀዘን ድንገት እየተሰማው የጭፍራውን ትከሻ በእጁ ጠብ ጠብ አደረገው። «በላ እንግዲያው ውለታ ከፋይ ያርገኝ።»

«ባትረሳው!» አለ ወታደሩ በቀልድ አኳኋን። «በሰሜን በኩል ያለው አጥር ይሻላል። እሾህ ቀለል ያለ ነው።»

«ባትረሳው!» አለ ወታደሩ በቀልድ አኳኋን። «በሰሜን በኩል ያለው አጥር ይሻላል። እሾሁ ቀለል ያለ ነው።»

ገብርዬ ወደ ተባለው አግጣጫ እስኪቃረብ ድረስ ወታደሩ ጥቂት ጠበቀው።

የበሩ ጫጫታና አምባጓሮ ሲፋፋም፤ ገብርዬ አጥሩን ዘሎ ግራና ቀኝ ተገላመጠና ተወርውሮ ከአዳራሹ በራፍ ደረሰ። የልቡ ትርታ ግቢውን የሚቀሰቅስ መሰለው። ገርበብ ብሎ የተዘጋውን በር ቀስ አድርጎ ከፈተውና አንገቱን ብቻ ሰገግ አድርጎ አስገባ። አቶ መላኩ ግራና ቀኝ ሁለት ሻማ ተተክሎለት ለአትሮኖስ ላይ ተደፍቶ ይጽፋል። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ከአጠገቡ ቁሞ መላኩ የሚጽፈውን ይመለከታል። ቆንስል ፐላውዴዎን ከአዳራሹ ጥግ በድንክ ወንበር ላይ ተቀምጧል። ቴዎድሮስ አንድ ጊዜ ወደ ፐላውዴን እየሔዱ ሌላ ጊዜ ወደ መላኩ እየቀረቡ፤ ከወዲያ ወዲህ እየተንጎራደዱ፤ ጣታቸውን እየቀሰሩ በአእምሮዋቸው የሚጉላላውን ሐሳብ የሚያወጡ ይመስል፤ አንገታቸውን ሰበር መለስ እያደረጉ የሚጻፈውን ይናገራሉ። ገብርዬ እንደ ነፋሱና እንደ ፊታቸው አቅጣጫ የሚናገሩት በከፊል ተሰማው። «ሊቀ መኳስ ዮሐንስ እንደ ልጄ፤ ቆንስል?...... እንደ ወንድሜ.....በማክበር.......በማፍቀር.......ይኸውም ....በመፍራት ሳይሆን.......ከቧታል......ትልቅ እንድትሆን ወገኔ እንዲሠለጥን.....ሳይሆን.....ወዳጅነትዎን በመፈለግ እንድትሆን ወገኔ በመሳፍንቶች......አሁንም ጠላት ከቧታል......ትልቅ እንድትሆን ወገኔ እንዲሠለጥን.....ዐዋቂዎች፤ ባለሙያዎች......ውለታውን አልረሳም። እመልሳለሁ.....» ቴዎድሮስ ለንግሥት ቢክቶሪያ የሚላክ ደብዳቤ እያጻፉ መሆናቸውን ገብርዬ ወዲያው ተገነዘበ። ሁናቴያቸው አሳዘነው። ባለፉት ጥቂት ወራት ብዙ ዓመታት ያረጁ ይመስላሉ። የግንባራቸው መሥመሮች የበለጠ ተቀርሰው ወጥተዋል። የዐይኖቻቸው ዙሪያ ወደ ጥቁረቱ መቀለሙ በጧፉ ብርሃን ወጥተዋል። የዐይኖቻቸው ዙሪያ ወደ ጥቁረቱ መቀለሙ በጧፉ ብርሃን ለይቶ ያስታውቃል። እንቅልፍ አጥቶ የመሰንበት ምልክት ነው።

‹የኔው ጣጣ ይሆን? ወይስ የተዋበች ሕመም? ወይንስ ደሞ ሌላ ችግር አጋጥሟቸዋል?› ሲል ገብርዬ አሰበና፤ አንድ ሥውር ኃይል እንደ ሳበው ያህል ሳይታወቀው ወደ ፊት ተራመደ። አሁንም እየተንጎራደዱ ንግግራቸውን እንደ ቀጠሉ ወደ በሩ አቅጣጫ ዘወር ሲሉ ድንገት አዩት። ግን አልለዩትም። «ብርቱ ጉዳይ ይዣለሁ ሰው አይግባ አላልኩም ነበር?» አሉ ትንሽ የታከተ የሚመስል ቁጣ። ገብርዬ ቀጥ ብሎ ቆመ። በመጠራጠርም፤ በመመራመርም ትኩር ብለው አስተዋሉት።

«ገብርዬ? ገብርዬ ነህ ወይስ ምትሃት ነው የሚታየኝ?» ሲሉ ጠየቁ። የምሥጢር ውይይት ይመስል በጣም በለሰለሰ ድምፅ።

«ኧረ እኔው ገብርዬ ነኝ አባ ታጠቅ» አለና መለሰ፤ አሁንም አንድ ኃይል የሳበው በሚመስል ስሜት እየቀረበ። ቴዎድሮስም እንደዚሁ አቅፈው ለመቀበል የከጀሉ ይመስል፤ ሁለት ክንዳቸውን ዘርግተው ወደ ገብርዬ ተራመዱ። ግን የገብርዬ መሸፈት ድንገት የተገለጠላቸው ወይም የታወሳቸው ይመስል መላ አካላታቸው ኩምትርትር አለና ቀጥ አሉ። አቶ መላኩና ቆንስል ፕላውዴን ከተቀመጡበት ተነሥተው ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በቆሙበት ሁሉም በመገረም ድርቅ አሉ።

«ጥፋ! ጥፋልኝ ቶሎ ተፌቴ! ሕይወትህ ሳትጠፋ! እኔ እንዳንተ አይደለሁም። ሕይወትህንስ አላጠፋትም። ብዙ ጊዜ ለሕይወቴ አዳረግሃት ናትና! እና በፈጠረህ ጥፋልኝ!» ሲሉ ቴዎድሮስ ጮሁና ሕይወቱን ሊያድን ሲወጣ ለማየት ያልፈለጉ ይመስል፤ ፊታቸውን በመዳፋቸው ሸፍነው ወደ ታች አቀረቀሩ።

ገብርዬ ተንደርድሮ ከጉልበታቸው ሥር ተደፋ። «እንግዲያውማ እንደ ተባለብኝ ባጠፋም ኖሮ ትምረኝ ነበር ማለት ነው? ዛዲያ ያጠፋ ሲማር ባላጠፋስ ደሞ ልትምረኝ አትችልም? አባ ታጠቅ፤ ቁጣህን ከአፎቷ ከማውጣህ በፊት ነገሬን ስማኝ። አንተ እንደምትለው፤ ትክክለኛ ፍርድ ለመበየን የከሳሽንም፤ የተከሳሽንም ቃል ማጣራት ይገባል እና ከቁጣህ በፊት......»

«እኮ በል ተነሥ! ማነን ጡረኛ ለማረግ ነው? ቁጣ አልከኝ? ግና ምን የተረፈ ቁጣ አለኝና! አልቋል። ተሚጦ አልቋል። ይልቅስ የምትናገረው ነገር ታለ ልስማው!» ፊታቸውን በመዳፋቸው እንደ ሸፈኑ፤ በመታከት ከወንበራቸው ላይ እንዘፍ አሉ።

«የት ልጀምር አባ ታጠቅ?»

«የትም ጀመረው፤ ብቻ ልስማው» አሉ ፊቱን ሳያዩ።

ነገራቸው። ቆስሎ ጎንደር እንደ ተመለሰ ጋረድና አክሊሉ ሙከት አሲያዘው እንደ ጠየቁት ከዚያም እየተመላለሱ እንደ ተወዳጁት ስለ ሕልሙና ስለ ፌዛቸው፤ ስለ ጥርጣሬው፤ በመጨረሻም ስለ ታንጉት እርግዝናና አምሮት ምንም ሳያስቀር ተረከላቸው። ከታሪኩ ግማሽ ላይ እንደደረሰ ከሩቅ የሐሳብ ዓለም የሚመጣ በሚመስል ድምፅ ተቀምጦ እንዲያወጋቸው አዘዙት። ከአንድ ጥግ የሚገኘውን ወንበር አምጥቶ ከአጠጋባቸው ተቀመጠና ታሪኩን ቀጠለ። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ፤ ቆንስል ፕላውዴንና አቶ መላኩም ዙሪያውን ከበው ቆመው በመገረም አዳመጡት። ከወይኒ ኪዳነ ምሕረት ደብረ ታቦር እንዴት እንደ ደረሰ ከተናገረ በኋላ «ይኸው ነው፤ አባ ታጠቅ» ሲል አበቃ።

ቴዎድሮስ አንገታቸውን ደፍተው ሲያዳምጡ እንደ ነበር በራሱ አካል ላይ ተጠምጥሞ የሚወረወር የቆላ እባብ ከመቀመጫቸው ተፈናጠሩ። ከንፈራቸውን፤

በቀኝ እጃቸው ቁንዳላቸውን እየጎተቱ። ሪዛቸውን እየሳቡ የአዳራሹን ወለል አምስት ጊዜ ያህል ተመላለሱበት። አንዳንድ ጊዜ እንደቆመ ግንድ ባሉበት ድርቅ ይላሉ። ምንም ነገር የማያዩ፤ የማይሰሙ፤ በውጣቸው የሕይወት እንቅስቃሴ የሌለባቸው ይመስላል። ነገር ግን፤ በዚያች ቅጽበት በዚያ ድርቅ ባለ አካል ውስጥ ይህ ነው የማይባል አንድ ዐይነት እሳት የሚንቀለቀል አንድ ዐይነት እሳተ ገሞራ ለመፈንዳት የሚፈላ መሆኑን በቅርብ የሚያውቁት ጥግ ጥግ ይዘው በመቆም ረጅም ጊዜ አብሮ ከመኖር ተገንዝበውት ነበር። በምክር በቃል ይኸ መሆኑን ረጅም ጊዜ አብሮ ከመኖር ተገንዝበውት ነበር። በምክር በቃል መልስ ሊያስረጉዋቸው የሚችሉት ተዋበች ብቻ ናቸው። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በአዘኔታ ታስፈልገዋለች፤ ‹ይህ ሰው ዓላማአውን እንዲፈጽም፤ ተዋበች የግድ ታስፈልገዋለች፤ ታለበለዚያ ግን› የሚል ሥጋት በሐሳቡ መጣበት። የዲፕሎማትና የታላቋን ብሪታንያ ክብር ለመጠበቅ ተረጋግቶ የቀረበ ቆንስል ፕላውዴን ብቻ ነበር።

ከጊዜ በኋላ ቴዎድሮስ ከወለሉ መኻል ላይ እግራቸውን እንደ ማቧተር አድርገው፤ ግራ እጃቸውን ከጎራዴያቸው ሰገባ ላይ አስደግፈው፤ በቀኝ እጃቸው ጺማቸውን እየጎተቱ ቆሙ። እሳቱ በረድ ማለት ጀምሮ ሐሳብ ሲተካበት ነው እንደዚህ የሚሆኑት።

«አሆሆ! እኔን የሚገርመኝ የኔው የራሴ ጅልነት። ሁለቱ የማይለያዩ ጓደኛሞች መሆናቸውን፤ ሁለቱም አብረው የዚያን ጳጳስ ነኝ ባይ ግብጽ ቤት እንደሚያዘወትሩ ከሰማሁ ቆይቻለሁ።» ቀደም ሲል የነገረቻቸው ታንጉት ብትሆንም የት፤ እንዴት እንደሰሙት አልገለጹም። «ዛዲያ፤ ጋረድ ዐቅሙንም ችሎታውንም ሳይመጥን ታለኔ ሰው የለም ብሎ የሚንጠራራ አጉል መሆኑን ሳውቅ፤ ያ አክሊሉ፤ ገና ከልጅነቱ ተንኮለኛና መሠሪ መሆኑን ሳውቀው፤ ሁለቱን ምን አቆራኛቸው ብዬ ማመዛዘንና ነገር ማያያዝ እንዴት ተሳነኝ?» ራሳቸውን በቅሬታ ነቀነቁ።

«እኔም እኮ አጥፍቻለሁ፤ ጥርጣሬው እንዳደረብኝ አለመንገሬ» አለ ገብርዬ።

«ጥፋት ነው፤ ጥፋቱም አይደለ። ማለቴ፤ ጥርጣሬህን ከመጀመሪያው እነሱን መስለህ ሐሳባቸውን ብታጣራው መልካም ነበር። ታለበለዚያማ፤ ‹ሳያጣሩ ወሬ ሳይገድሉ ጎፈሬ› እንደሚባለው ባልተጨበጠ አጉል ጥርጣሬ ነገር ማወሻከቱን ብትጠላው መንፈስህ ኩሩ በመሆኑ ስለሆነ አላጠፋህም ባይ ነኝ።» ንዴታቸው መልሶ ተቀሰቀሰ። «ጥራልኝ ታከለን! የተጣራ፤ የተረጋገጠ ነው ብሎ የነገረን ያ ቀልማዳ ነው!» አሉ ከንፈራቸውን እየነከሱ።

ታከለ አልተገኘም። ቴዎድሮስ በራሳቸው ሐሳብ ተውጠው ልብ አላሉትም እንጂ ከቀትር ጀምሮ በአካባቢ እልነበረም። ከመሠረቱ እነጋረድ ከሄራቸው

ምሥጢር ሳያስገቡት በስሕተት የፈጸመው ነገር ቢሆንም፤ እንዲቀላቀላቸው ሲሉ የቴዎድሮስ ሰይፍ በአንገቱ ላይ ሳያርፍ ራሱን እንዲያድን መልእክት ስለ ላኩበት ነፍሴ አውጭኝ ብሏል። ቴዎድሮስ፤ በታከለ መጥፋት ከማዘንና የባሰውን ከመናደድ ይልቅ በመገረም ከትከት በለው ሣቁ። የቤተ መንግሥት ኮረዳ መጫወት እንጂ ከወንዶች ጋር ይውላል ሲሉ ገምተውት አያውቁም ነበር። ያቀረቡት፤ ከወንዶች ቦታ ይውላል ሲሉ ገምተው አያውቁም ነበር። ያቀረቡትን፤ የደጃች ጎሹ ዲቃላ ልጅ ስለሆነ የሀገሬው ሕዝብ እንዲደሰትና እንዲተባበራቸው ነበር። አንድ ዕዳ እንደ ተገላገሉ ቆጠሩት።

«እሱም ሰው ሆኖ! ምንተዳዬ መይሳው! ‹ባቄላ አለቀ ቢሉ ፈስ ቀለለ እንጂ» በማለት የፌዝ ሣቃቸውን ሳይጨርሱ ከበሩ በኩል አዲስ ግርግር መጣ። ወዲያው የግቢው ዘብ ኃላፊ እየተንደረደረ ገባና እንደ መደፋትም እጅ እንደ መንሳትም አለ። ሰውነቱ በድንጋጤ ይርበደበዳል፤ ገብርዬን ሲያይ ባሰበት።

«ደሞ ምን ጉድ ተፈጠረ! ጆሮዬ ደግ ነገር ላይሰማ መከልከሉ ነው ልበል?»

«ሰንደቁ - ሰንደቁ» አለ የዘብ ኃላፊው ትንፋሹ እየተቆራረጠ።

«እኮ ሰንደቁ ምን ሆነ? ወይም ምናረገ?»

«ተጎድቷል - ሙ - ሙ» የዘቡ ኃላፊ መጨረስ አቃተው።

ባይጨርሰውም ቴዎድሮስ ገባቸው። ገብርዬ ስቅጥጥ አለው። «እኮ ምን አገኘው?» ሲሉ ጠየቁ።

ዐረፍተ ነገሩ እየተቆራረጠበት የዘቡ ኃላፊ የሆነውን ለማስረዳት ሞከረ። «መጣና አዳራሽ ካልገባሁ ታባ ታጠቅ ዘንዳ አለ። ሰክሮዋል መሰለኝ፤ ይንገዳገዳል። የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥራል። እኛ ግን አንድም ሰው እንዳይገባ በታዘዝነው መሠረት ክልክል ነው አልነው። እሱ ግን ካልገባችሁ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ አስቸገረ። ጭቅጭቅም ፈጠረ። ኧረ ተው! ብንለውም አልመለስም አለ። ሰክሮ ነው ብለን ልናባብለው፤ ልናበርደውም ሞከርን። ጭራሹን ጥሼ ካልገባሁ ብሎ ጎራዴውን መዘ ሁላችንንም እያወከ ወደኔ ሲመጣ፤ ሲመጣ አንደኛው ዘብ - አንደኛው ዘብ እኔን ለማዳን ብሎ

«.....ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው።

«ወጋው አትልም። ከሆነ በኋላ ቃሉን ምን ትፈራዋለህ? አሉት ቴዎድሮስ፤ «ግን ምን ነካው እባካችሁ?»

«እኔ እንጃ ብቻ የሰከረ ይመስለኛል» ሲል መለስ የዘቡ አለቃ፤ የሠጋው ቁጣ ባለመጣቱ ቀለል ብሎት።

«እርግጥ ጠጥቶ ነበር» ሲል ገብርዬ ለጠቀ። «ግን በርዶለት ስለ ነበር የሰካር አይደለም።»

ቴዎድሮስ በመገረም ትኩር ብለው ተመለከቱት።

«አዎ! በኔው ጦስ ምክንያት ነው።»

ነገሩ እንቆቅልሽ እንደ ሆነባቸው ቴዎድሮስ አሁንም በአስተያየታቸው ገለጹት።

«እኔ ነኝ አባ ታጠቅ፤ ማንም ሳያውቅ ባጥር ዘልዬ ገብቼ ካንተ ጋር እንድገናኝ ከበሩ ዘበኞች ጋር ግርግር እንዲያነሣ ያደረኩት። እኔው ነኝ ለሞት የዳረኩት ሰንደቄን።» ገብርዬ የተናነቀውን ዕናባ ለመግታት ከንፈሩን ነከስ አደረገ።

«አይፈረድብህም። አንተማ ምንታረግ? በማንከበት፤ በታመንከበት ግቢ የምታምነው ብታጣ ሰውን ሁሉ መጠርጠር መች ይነስህ?»

ቴዎድሮስ፤ በትካዜና በሐሳብ ተውጠው ለረጅም ጊዜ ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ፤ ታፍኖ እንደቆየ ያህል በሰፊው ተነፈሱና፤ «ለመሆኑ ወይኒ አገርዋ መሆኑን አንዳች ነግራሃለች?» ሲሉ ገብርዬን በድንገት ጠየቁት።

«አዎ አባ ታጠቅ! የልጅነቴ አማረኝ ስላለች እኮ ነው እኔም የሔድኩት።»

«አዎ! የልጅነቷ!» ቴዎድሮስ አንድ ዐይነት የትካዜ ናዳ የተጫናቸው ይመስል፤ ጭንቅላታቸውን በጃቸው ደገፉ። «ሌላስ? ዘመድስ አገኘች?»

«አይ! አይመስለኝም። እኔ አላወኩም» አለ ገብርዬ እይኒ እንደ ገባ ሰሞን የከነከነው ነገር እንደገና ትዝ ብሎት።

«ወቸው ጉድ!» ሲሉ ከራሳቸው ጋር፤ ከንፈራቸውን በአዘኔታ መጠጡና ጉዳዩን ወዲያው ለወጡት። «እስቲ ለሁሉም የአንተ የወንድሜንና የልጄን ሕይወት በደኅና ተዚህ ያደረሰልኝን ነግዴ ነገ ይዘኸው ናና ላመስግነው። በተረፈ እንግዲህ ጆሮየ ሌላ ጉድ ሳይሰማ በሉ ወደየማረፊያችን እስቲ» ሲሉ ተሰናብተው ወደ እልፍኝ ፊታቸውን መለሱ።

«መልክቱ አባ ታጠቅ?» ሲል ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ጠየቃቸው።

«መልክቱ?» ሲሉ ጠየቁ ጨርሶ እንደ ተረሳ ጉዳይ፤ «ከፍተኛ የቁም ነገር መልክት የሚጻፈው ሐሳብ በተሰበሰበት፤ መንፈስ በተረጋጋበት ጊዜ እንጂ በንዲህ

ያለ ሁኔታ ሊቀ መኳስ? ያድርሰን፤ ረጋ በለን እንጨረሰዋለን። ገብርዬ ግን ተዋበችን ጠይቃት እንጂ» ብለው ወደ እልፍኙ አመሩ።

ገብርዬ ለማልቀስ ይሁን ለመሣቅ፤ ያለየለት ሲቃ እየተናነቀው ተከተላቸው።

# ሁለተኛ መጽሐፍ

## ሮዜንታል

.......የምትሔድበትን ሳታውቀው ጨርሳ
እውሩዋን የምትሮጥ እንዲያው በዳበሳ
ሳትፈራ ሳትሰጋ ሳታስተውል አስባ
እያቅነዘነዛት ገደት የምትገባ.....

ከበደ ሚካኤል
(የቅኔ ውበት)

# ምዕራፍ አምስት

## የተዋበች ሕመም እየጠናባቸው ሔደ።

በሽታቸው ምን እንደሆነ በትክክል ሊታወቅ አልቻለም። አንዳንዱ ሥራይ ነው ይላል። ሌላው የአባታአቸው ወገኖች ወዳጃ ገብተው ረግመዋቸው ነው የሚል ወሬ ያናፍሳል። ስለቀረቡ፤ ሥር የሰደደ ንዳድ፤ ለመውለድ ሲሉ ከጠጡት መድኅኒት አንዱ መርዝዋቸው፤ ሌላም ሌላም ይባላል። ቴዎድሮስ በበኩላቸው ‹እሷ ምን በሽታ ነበራት፤ እኔ ነኝ እንጂ አገር ላገር፤ በረሃ ለበረሃ እያንከራተትኳት፤ እያንገላታኋት ለዚህ ያደረስኳት፤ በማለት ራሳቸውን ተጠያቂ ያደርጋሉ። ሊቀ መኳስ ዮሐንስን ጨምሮ፤ ስለ በሽታ ምናልባት የተሻለ ግምት ሊኖራቸው ይችላል የሚባሉት የውጭ አገር ሰዎች ስንኳ፤ ምንም ፍንጭ ሊያገኙለት አልቻሉም። በየዕለቱ እየሰለሉ፤

እየደከሙ ሲሔዱ ብቻ ይታያሉ። ቴዎድሮስ ‹ተዋቡ ምንሽን ነው የሚሰማሽ?› ብለው ሲጠይቋቸው የሚያገኙት መልስ፤ ‹ምናባቴን ዐውቄው!› የሚል ነው። ጸሎት፤ ጠበሉ መድኃኒቱ አላሻላቸውም።

ከወይኒ ተመልሰው ታንጉት ልትጠይቅ ከተዋበች አልጋ እንደተጠጋች ቴዎድሮስ መደንገጧን አይተው፤ ‹ይኸውልሽ እኅትሽ እንዲህ ሆነች› ካሏት ጊዜ ጀምሮ የተዋበች ሕመም ከራሷ ሥቀቀን ጋር ተጨምሮ የደብረ ታቦር ኑሮዋን ጭጋግ አለበሳት። አንዳንዱ ጊዜ፤ ስለ እርሱ የማትፈልገው ብስጭት ቢመጣባትም ታንጉት ቴዎድሮስን ትወደዋለች። እንደምትወደውም ደኅንነቱን ትመኛለሽ። ተዋበች ደግምፐ፤ ለቴዎድሮስ ምትክ የማይገኝላት ምሽት መሆንዋን አሳምራ ታውቃለች። ልታስደስተው የምትችል፤ አንበሳ ተፈጥሮዋን አሳምራ የምትችል እርሷ ብቻ ትመስላለች። ለምን እንደሆነ ግን አይገባትም። ለራሷም ቢሆን እርሷ የመጣው ልዩነት፤ ከእርሱም ጋር የመጣው የቤተ መንግሥት ወግና የዕለት ተዕለት ሥራ በመጠኑ ቢያራርቃቸውም፤ ከተዋበች የሚቀርባት አልነበረም። እንደ ልጅ ያይዋታል። እንደ እናትም ሳይሆን እንደ ትልቅ እኅት ታያቸዋለች። ታንጉት እንደምትጠራጠረው፤ ምናልባት ከቴዎድሮስ ጋር ብቻቸውን ካልሆኑ በስተቀር ቀልድና ጨዋታ የሚያዘወትሩ ተዋበች፤ ጋር ብቻቸውን ካልሆኑ በስተቀር ቀልድና ጨዋታ የሚያዘወትሩት ተዋበችና በዝምታቸው የሚያጫውቱ፤ በቁጣቸው የሚያባብሉ የሚያስመስላቸው አንዳች ዐይነት ተፈጥሮ አላቸው። አሁን ከአልጋ ላይ ውለው ስታይ ለእርሳቸውም፤ ለቴዎድሮስም አዘነች፤ ለራሷም ጭምር።

ታንጉት ደብረ ታቦር ሰንብታ፤ የመንገዱ ድካም ወጥቶላት ድንጋጤው ዐልፎላት የሆነውን ሁሉ እንደገና ስታስበው ከደሮው የባሰ ትካዜ ይሰማት ጀመር። ትካዜ ብቻ ሳይሆን አሁን ጸጸትም ታከለበት። ገብርዬስ ደስ እንዲለው፤ ትዳርዋ እንዲጸና ብላ፤ እንደ ትልቅ ኃጢአት በሚቆጠር መንደር ልጅ ለማግኘት የሠራችውን ሠራች። ሆነ፤ ተስፋ አደረባት። ግን በአጭር ጊዜ ተመልሳ ወደ ቀድሞ ዕድልዋ ገባች። ‹ኃጢአት ስለሆነ ወትሮውንስ ቢሆን ባይባርከው ነው እንጂ ትላለች› ከራስዋ ጋር። ለዚህም ደግሞ ገብርዬንም ራስዋንም ለሞት አብቅታ ነበር። ለእርሷ ሲል ገብርዬ፤ ከቴዎድሮስ ፊት ለረጅም ጊዜ ባይርቅ ኖሮ እነጋረድ መች ሰበብ ያገኙ ነበር? ቴዎድሮስ ከወሎ እንደ ተመለሰ፤ ሌላ ሌላውን ስትነግረው፤ የእነጋረድና የነገብርዬን ጭውውት ደብቃ ባታስቀር ኖሮ ይህ ሁሉ መች ይደርስ ነበር? ገብርዬ፤ ከቴዎድሮስ ጋር ጋፋት ወይም ጦር ሠፈር ሔዶ ታንጉት ብቻዋን ተቀምጣ ከጸጸት ጋር ይህንን ሁሉ ስታስብ፤ የምታዋየው፤ የልብዋን ቁስል የምታሳየው ሁነኛ ሰው ትፈልጋለች። ከአጠገብዋ የምታገኘው ይመስል፤ አንዳንድ ጊዜ ሳይታወቃት ዙሪያዋን ትመለከታለች። ማንም የለም። ወይዘሮ ደብሬ ጎንደር ናቸው። ከዱሮ

ጓደኞቿ ጋር፤ አንድ ጊዜ የነቃ ብርሌ መስለው ቀርተዋል። ከአገሬው። ሰው የምትቀርበው ወዳጅ አላፈራችም። የምታፈራም አይመስላትም ከወይዘሮ ደብሬ በቀር። ያውስ በዘርዋ ምክንያት ሳይሆን ይቀራል? ጎንደሮችን መጠጋት እንዳቃታት ሁሉ፤ የዚህ አገር ሰዎች ደግሞ የባሰውን የተለዩ ሆነውባታል። የምታምናቸው፤ የምትተማመንባቸውና በቅርብ የሚገኙ ተዋበች ብቻ ናቸው። ከሥቃይ፤ ከሞት ጋር ሲታገሉ፤ ራሳቸው ማጽናናትን፤ ማስታመምን የሚፈልጉ እንጂ የሌላ ችንቅን የሚካፈሉ አልሆኑም። ከገጽታቸው እንደ ተመለከተችው፤ ሞትን የሚጠብቁ ለሚመስል ሰው እንደዚህ ያለ ነገር ማዋየቱስ መች ይገባል? በዚህ ላይ የሰው ሁላ ገጽታ የሚጨፈግግ ነው። ከትልቁ ራስ አሊ ጀምሮ ደብረ ታቦር የኖረው ዘመድ አዝማድና ጀሌ፤ ዘወትር የሚታየው፤ አፍንጫውን ነፍቶ ግንባሩን አኮሳትሮ ነው። ሚሽቱም፤ ወዳጁም እንደዚሁ ናት። ሌላ በሌላ በኩል መርዶ የሚቀበላቸው እየመሰላቸው መላ ሰውነታቸው በጭንቀት እየተኮማተረ ስለሚቆይ፤ የባለሟሎቻቸውና የሠራዊታቸውም፤ ፊት በጭንቀት የሚያንጸባርቅ ሆኗል። ሌላው ቀርቶ ጠጅ በበዛበት የማር አገር፤ እንደ ጎንደር የአዝማሪ ዘፈን አለመስማቷ ታንጉትን ገርሟታል።

በአዝማሪ ፈንታ ግን፤ አንዲት ሴት ቴዎድሮስን እየወረፈች፤ እየረገመች ደብረ ታቦርን ስታዳርሰው ትውላለች። ታንጉት የመጀመሪያ የሰማቻት ቀን ባለችበት ድርቅ ብላ ነበር። ቴዎድሮስን እንደዚያ ብሎ ማን ቁሞ ይሔዳል? ከቁስሉ ድኖ በመጨረሻ በዘመተበት የደረሰ ታሪክ ስለሆነ ገብርዬ እንደ ነገራት የጎጃም ሴት ናት። አባቷ፤ የደጃች ተድላ ጦር አበጋዝ፤ ወንድሟና ባሏ እንደዚሁ የጦር ሻለቆች ነበሩ። ባልዋ በውጊያ ላይ ይሞታል። አባቷና ወንድሟ ተማርከው በገበያ ላይ ይሰቀሉባታል። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ ባሉበት አካባቢ ሳይቀር አጥንት የሚሰብር ልቅሶዋን ታወርዳለች። አገር ምድሩ ይሰማዋል።

«ጠጅ እንዳያምረኝ ድሮ ጠጥቻለሁ።

ሥጋም እንዳያምረኝ ቋንጣ ሰቅያለሁ

ቢሻኝ ከወንድሜ ከአባቴ እበላለሁ።

«አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ

እንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ይፍጃችሁ።

«ሺ ፈረስ ከኋላው ሺ ፈረስ ከፊቱ

ሺ ብረት ከኋላው ሺ ብረት ከፊቱ

ይህን ሳይት ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ።

«ይህንን ሲሰማ ያጓራል ላመሉ

ማናትም ቢላችሁ ምንትዋብ ናት በሉ!»

እያለች ታወርዳለች።

ተይዛ ከቴዎድሮስ ፊት ትቀርባለች። ከቁጣ ጋር በመገረም፤ «በየደረሽበት ተነናቴ ታብጠለጥይኛለሽ አሉ?» ሲሉ ይጠይቋታል።

«አዎና!» ስትል በድርቅና ትመልሳለች። ምክንያቱን ይጠይቋታል፤ ትነግራቸዋለች።

ቴዎድሮስ በዙሪያቸው ለነበሩት ሰዎች፤ «እህ? ዛዲያ እንዲህ ሁና ታመስግነኝ ነው የምትሉት?» ይሉና የሴትዮዋን ምረው ድርጎ ያዙላታል። ምንትዋብ ግን ድርጎዋንም እየተቀበለች፤ ከጎጃም ደብረ ታቦር ድረስ ተከትላቸው በየዕለቱ አዳዲስ ግጥም እያወጣች፤ አሁንም መዓቱን ታወርድባቸዋለች።

‹ስሟ ከምሽታቸው ስም ጋር ስለ ተመሳሰለ ነው! የተዋበች ዋና ስማቸው ምንትዋብ ነበር። በኋላ ተለውጦ ነው የተለመደው!› እያሉ የሚቀልዱ አሉ።

ሌሎች ምንትዋብን አእምሮ በኀዘን እንደ ተነካ ዕብድ በመቁጠር ነገርዋን እስከዚህ ዋጋ ባይሰጡትም፤ ታንጉት ግጥሟም ሆነ እንደ ቅባት የሚሰረስር ዜማዋ ሚርት መስሎ ይሰማታል። ስቅጥጥ ያደርጋታል። እንደ ጉና ተራራ እናት ጭጋግ ከማይለየው ከዚህ የራሷም ሆነ የውጭው አካባቢ ስሜት ለመራቅ አስፈቅዳ እደ ጎንደር የምትሔድበትን አመቺ ጊዜ ስትጠብቅ፤ አንድ ቀን ገብርዬ ከጋፋት እንደ ዋለ ሲመለስ፤ «አባ ታጠቅ ይፈልግሻል» አላት።

«አሁን?» ታንጉት መደንገጥ አለች።

«አዎ!»

«ተዳከሙች እንዴ?» ስትል ጠየቀች ኩታዋን እየደረበች።

«እሱ ነው እንጂ የባሰ የተዳከመው» አለ ገብርዬ።

ስትደርስ ቴዎድሮስ ከአልጋው ራስጌ ቋንጣ ወንበር ላይ ተቀምጠው፤ ሕፃን እንደሚያቆላምጥ አባት የተዋበችን እጅ ይዘው ሲያሻሹ፤ ሲያገላልጡ፤ ሲያስተውሉ አገኘቻቸው።

«ላስቸግርሽ ነው አንጓች!» ንግግራቸውን እስኪጨርሱ ዝም ብሎ ጠበቃቸው። «ወረይሉ አንድ ጥሩ ጠበል አለ ይላሉ። ይዣት መሔድ ነው። ዛዲያ አገር ሁላ ሽፍታ ሆኖ ስላስቸገረ ወዲያ ወዲህ ማለቴ ስለማይቀር፤ ታጠገብዋ እንድትሆኝላት አብረን እንሒድ ብዬ ነው። በዚያውም ያው ተገብርዬ አትለዩም ማለት ነው!» አሉ ትካዜያቸውን ሊደብቅ ያልቻለ የቀልድ ፈገግታ ለማሳየት እየሞከሩ።

በዚህ ዐይነት፤ ከዚያ ደርሶባትና አይታው የማታውቀውን አስጨናቂ ጉዞ በበነጋው ጧት ጀመሩ።

መጀመሪያ ለተነሡበት ዓላማ ከጉዞዋቸው ፍጻሜ የደረሱት ከሰጠኝ ወር በኋላ ነበር።

የተዋበች አስክሬን በግሼን ማርያም ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያርፍ ተደርጎ፤ ሠራዊቱ በቅጽር ግቢው ወጣ ብሎ ከሚገኝ ደልዳላ መሬት ላይ ሠፍሯል። ቴዎድሮስ ጸልየው የማይበቃቸው ይመስል ከቤተ ክርስቲያን ቅድስት ውስጥ ቀርተው፤ ገብርዬና ሌሎች የቅርብ ባለሟሎቻቸው ከቅኔ ማኅሌቱ ይጠብቋቸዋል። ተዋበችን በሚመለከት ዝም ብሎ የሚሠሩትንና የሚሆኑትን ከማየት በተቀር ደፍሮ ምክር የሚሠጥ አልነበረም።

ታንጉት፤ ለጊዜው የምትሠራው ነገር ስላልነበረ፤ ከአሳለፉት የሕይወት ማዕበል ትንሽ ያረፈች መስሏት፤ በምሥራቅ በኩል ከዐጸደ ቤተ ክርስቲያን ዳርቻ ከጥድ ዛፍ ሥር ተቀምጣ ዙሪያውን ትቃኛለች። ከአንድ በኩል የእግዚአብሔር አብ ሜዳ መስሎ ይታያል። አዝመራው፤ ከብቱ፤ ሸንተረሩ ዙሪያውን ያለው ትርዒት ትርዒት ሁሉ ውብ ነው። ታንጉት ግን ዐይንዋ እንጂ ዐይነ ልቡናው ይህንን ሁሉ ውብ ትርዒት አያስተውልም ነበር። ሐሳብዋ አሁንም በአንዳች ዐይነት ማዕበል ውስጥ ነበር። ስሜቷ ምን እንደሆነ በትክክል ለይቶ አይታወቃትም። ኀዘን ይሰማታል። ተገላልገልኩ የሚል ዐይነት እፎይታም ይመጣባታል። ሰው፤ ሰውን የማትፈልግ አንድ ስሜት ይቆነጥጣታል። ይህ ሁሉ ስሜት ሲፈራረቅባት፤ መነሻ የሆነ የጉዞዋቸው ሁናቴ፤ ከፊቷ እንደ ተዘረጋው የእግዚአብሔር አብ ሜዳ በሐሳብዋ ተንጣልሎ ይታያት ጀመር.....

ተዋበች ያረፉት፤ ቴዎድሮስ፤ ለሚሽታቸው ተስማሚ አየርና ጠበል እየፈለጉ፤ እግረ መንገዳቸውንም በጊዜው ሽፍቶባቸው የነበረውን የዐመዴ በሽርን ተከታዮች ግራና ቀኝ በማሰስ ከሥፍራ ሥፍራ እየተዘዋወሩ፤ ግራኝ ሜዳ ከተባለው ሥፍራ ላይ ነበር። በጊዜው ታንጉት ድንኳን ውስጥ አልነበረችም። የተዋበች ደንገጡ፤ ሠፈሩን በእሪታ ስታደባልቀው፤ ታንጉትና ሌሎችም ባለሟሎች ተሯሩጠው ገቡ። ቴዎድሮስ ክንዳቸውን እንዳንተራሱት የተዋበች ሬሳ፤ ራሳቸው በድን ሆነው፤

አንዳችም ነገር ሳያዩ ዐይናቸውን ከፊት ለፊታቸው ከምንም ላይ ተክለው እንደ ጨው ዓምድ ድርቅ ብለዋል። ድምፅ አውጥተው አያለቅሱም። ለጊዜው ዕንባም አይፈሳቸውም። ዐልፎ ዐልፎ ብቻ በጥቂቱ ሲወዛወዙ የታቀፉትን ሬሳ እሹሩሩ የሚሉ ይመስላሉ። ድንገት ዙሪያቸው የቆሙትን ሰዎች በእንቅልፍ ልብ ዐይነት ሲመለከቱ። ድንገት ዙሪያቸው የቆሙትን ሰዎች በእንቅልፍ ልብ ዐይነት ሲመለከቱ፤ ‹በመጨረሻ፤ በመጨረሻ - ታታ -አለችኝ፤ ታጠቅ ልትለኝ ኑሮዋል? ወይስ ታገሥ? ሲሉ በእንቅልፍ ልብ አነጋገር ጠየቁ። ሬሳውን ከክንዳቸው ላይ አንሥተው አንሥተው ደጋግፈው ድንገት እንደ ተሰበረ ብርሌ፤ ስቅስቅታቸውም ባንዴ ለቀቁት።

በበነጋው፤ የቆላው፤ የደጋው፤ የስሜንኛው፤ የበጌምድሬው፤ የጎንደሮች መረግዶ ልቅሶ በየዘርፉ በየተራው እየወረዱ የግራኝ ሜዳና ሌሊቱን ተጉዘው ሊደርሱ የቻሉት የአካባቢው አድባራት ካህናት ጸሎት ፍትሐት ሲያደርሱ ዋሉ። በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስ በለቀስተኛው መኻል እየተዘዋወሩ፤ እየየውን ሲለቁት፤ ግጥሙን ሲደረድሩት፤ ከነግጥሙ የልቅሶውን ዜማ ሲያወርዱት የሕዝቡ አንጀት ተበላ። በሰቆቃው ተብላላ።

«እጅግ ሥራ ዐዋቂ ታበላኝ ነበረ» ብለው፤ ቀረርቶ በገራው ድምፅ ልቅሶውን ሲያወርዱት፤ በዚያ የነበረው ሁሉ ተንፈቅፍቆ የሚሟሸሽ አልነበሩም። ቴዎድሮስን የሚፈሩ፤ ከዚያም ዐልፎ የሚጠሉ ሰዎች ስንኳ፤ ቁጣቸውን የሚያበርድላቸው፤ ቅንጣታቸውን የሚያስምርላቸው በማጣታቸው አብረው ሳያለቅሱ አልቀሩም።

ተዋበች፤ በጠና ከታመሙ ጊዜ አንሥቶ የሽምብራ ቆሎና ንፍሮ እየተመገቡ የከረሙት ቴዎድሮስ፤

«እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሔድ፤

የሴት ወንድ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ?»

ብለው በግጥም እንዳወረዱ ከአጎበሩ ላይ ተደፍተው ተንዘፈዘፉ። እነሊቀ መኳስ ዮሐንና እነ ራስ እንግዳ ከአጎበሩ ላይ አስነሱዋቸው።

በዚህ ዐይነት ሲለቀስና ሕዝብ ሲላቀስ እንደ ዋለ ቀብር ባለመፈጸሙ፤ እንዲያውም መቃብር ስንኳ ባለመቆፈሩ፤ ለማሳረግ ግራኝ ሜዳ ደብር አለቃ ቀስ ብለው፤ ራስ እንግዳን አማከሩ። በጥቂት ቅያሜ ለአጭር ጊዜ ታስረው ቆይተው በቅርቡ የተፈቱት ራስ እንግዳ በበኩላቸው ፊት ለፊት ቴዎድሮስ መጠየቁን ስላልደፈሩ ሊቀ መኳስ ዮሐንስን አማከሩት።

ባዶ ሆዱን ሲያለቅስ የዋለው ኀዘንተኛ ተደካክሞ፤ በዳሱም በያለበትም፤ የተቀመጠው ተቀምጦ፤ የቆመው ቆሞ፤ ለየብቻው እየቆዘመ ዐረፍ ብሏል። ቴዎድሮስ ከኀዘንተኛው መኻል ወጣ ብለው፤ ከወደ ዳር በኩል ከአንድ ቋጥኛ ላይ ብቻቸውን ተቀምጠዋል። ሐሳባቸውም ዐይናቸውም በዚያ ቦታ የለም። ይመልከትም፤ አይመልከት ከማዶው አድማስ ላይ ተተክሏል። የተዋበችን ሬሳ እንደታቀፉበት ወቅት፤ በዚያ ሥፍራ አሉ.... በዚያም ሥፍራ የሉም። ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቀስ ብሎ ቀረበና፤ «አባ ታጠቅ ይህን ያህል መሆንም አያስፈልግም» አላቸው።

መልስ አልስጡትም። የሰሙትም አልመሰለውም። ሐሳባቸውም፤ ዐይናቸውም አዳምስ ላይ ከሩቅ ባዶ ላይ እንደ ተተከለ ቀረ።

«አባ ታጠቅ!»

ቴዎድሮስ፤ ከእንቅልፍ በድንገት እንደባነነ ሰው ዘውር ብለው፤ ‹አቤት› የሚል መልስ የሰጡት የሰጡት ሦስት ጊዜ ከተጣራ በኋላ ነበር። በጩኸት ልቅሶ የማይወጣው፤ በቃላትና በንግግር የማይገለጸው የዝምታ ሰቀቀናቸው አስጨንቆአቸው ሲያይ መጠየቅ ከበደው። «የቀብሩ ነገር እንዴት ነው?» አለ ከብዙ ማመንታት በኋላ።

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ፤ በኋላ ለእነገብርዬና ታንጉት እንደ ነገራቸው ወዲያው መልስ ስላልሰጡት በጉዳዩ አልገፋበትም። አንዳንድ ጉዳዮች ሕይወት ውስጥ ዘልቀው ከመግባታቸው የተነሣ፤ ባለቤቱ ራሱ አምጦ በጊዜው ካልወለዳቸው በስተቀር በሌላ ምክርና ማሳሰቢያ እልባት እንደሚያገኙ ያውቃል። ቴዎድሮስንም አሁን ይህንን የመሰለ ሁናቴ ገጥሟቸዋል። የባሰውን ከማበሳጨትና ከማወራጨት በስተቀር በምክርና በሐሳብ ሊረዳቸው እንደማይችል ተሰማውና ከሐሳባቸውና ከሠቀቀናቸው ጋር ተዋቸው፡

ቴዎድሮስ፤ ሐሳባቸውን ለብቻቸው አምጠው ውሳኔያቸውን ወልደው ያደሩ ይመስል በበነጋው፤ የተዋበችን አስክሬን በሣጥን አስከትተው በመቅደላ አግጣጫ ወደ መኻል ውሎ ጉዞው ተጀመረ።

ከላይ የነሐሴው ዝናም እምብዛም ሳያቋርጥ ይወርዳል። ከታች መሬቱ እንዳለ ጭቃ ነው። አቀበት ሲወጡ ወደ ኋላ ያንሸራትታል። ቁልቁለት ሲወርዱ ወደ ፊት ያዳልጣል። ችግሩ ግን ይህ ብቻ አልነበረም። ቴዎድሮስ፤ ተዋበች በቃሬዛ ስትሔድ እኔ በከብት ላይ ፍጹም አልቀመጥም ስላሉ፤ የኮርቻ ከብት የያዘው ሁሉ እንደርሳቸው በእግሩ መጓዝ ነበረበት።

በየሥፍራው አደጋ ከሚጥሉ ሽቶች ጋር እየተዋጉ፤ የቆሰለ እስኪታከም፤ የሞት እስኪቀበር የውሎና የአዳር ዕረፍት እየተደረገ ጉዞው ቀጥሎ ከብዙ ቀናት በኋላ በሽሎ ወንዝ ደረሱ። ከዚህም ጥቂት ተደረገና አስከሬኑን የተሸከሙት ሰዎችና አብዛኛው ሠራዊት ወንዙን ለመሻገር ቀድሞ ተነሣ። መሻገሪያው የበሽሎ ወንዝ በስፋት የተንጣለለበትና ረጋ ብሎ የሚወርድበት ሜዳ ቀመስ ቢሆንም የነሐሴው ክረምት ውሃ መጠን እስከ ወገብ ይደርስ ነበር። ብዙው ሰው፤ ቃሬዛ የተሸከሙትን ሰዎች ከፊትም ከኋላም ከጎንም ከቦ እየተጠባበቀ ዋና የሚችለው የማይችለውን እያደፋፈርና እየረዳ፤ ቀደም ያለው እያቋረጠ መውጣት ሲጀምር ትርምስና ሁካታ ተነሣ። ደራሽ ሙላት ድንገት ከወንዙ አናት በኩል ሲጀምር ትርምስ ሁካታ ተነሣ። ከቦ እየተጠባበቀ ዋና የሚችለው የማይችለው እያደፋፈረና እየረዳ፤ ቀደም ያለው እያቋረጠ መውጣት ሲጀምር ትርምስና ሁካታ ተነሣ። ደራሽ ሙላት ድንገት ከወንዙ አናት በኩል መጥቶ ገና በመሻገር ላይ ያለውን ሠራዊት ያላጋውና ያዳፋው ጀመር። ዋናተኛውና ሸክም የሌለበት እንደ ምንም መዝለቅ ሲችል፤ ቃሬዛ ከተሸከሙት መካከል ሁለቱ ዋና የማይችሉ ኖሮ ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ሲወራጩ ለቀቁት። የቀሩት ብቻቸውን መሸከም አቅቷቸው ከእጃቸው አፈተለከ። በዚህ ጊዜ፤ ከወንዝ ወዲህ ማዶም፤ ከወንዝ ወዲያ መዶም፤ «ኧረ ቃሬዛው! ኧረ ቃሬዛው!» የሚል ጩኸት ሲያስተጋባና ቴዎድሮስ እንድ ጦር ተወርውረው ወንዙ ውስጥ ሲገቡ አንድ ሆነ። ሌላውም እየተሯሯጡና እየተጯጯኸ ተከተላቸው። በቅጽበት በሽሎ ወንዝ በሰው ተሞልቶ፤ ዋና የማይችለው ብቅ ጥልቅ እያለ ሲደፈቅ፤ የሚችለው የሙላት ግፊት ለመመከት ሲወራጭ፤ ቃሬዛውን ተከትሎና በውሃም እየተገፉ ሁሉም ወንዙ ወደሚወርድበት አግጣጫ ሲነዱ፤ የበሽሎ ወንዝ ብርብራ የተጨመረበት ባሕር መሰለ። በመጨረሻ ቃሬዛው አንድ ሁለት መቶ ክንድ ርቀት ላይ በወደቀ ግንድ ታግዶ ከወንዙ ጥግ ተገኘ። በመካከሉ ብዙ ሰዎች በሙላት ተወሰዱ።

ሁሉም በሁናቴው ስለ ተደናገጠና መንፈሱ ስለ ተነካ፤ የዕለቱ ጉዞ ፍጹም ዝምታና ጸጥታ የሰፈረበት ነበር። ዐልፎ ዐልፎ በለሆሳስ ከመንሾካሾክ በስተቀር ስለ ደረሰው አደጋ ስንኳ ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚነጋገር አልነበረም።

ወደማታ ገደማ በደን በተሸፈተ ዳገት ጥግ ሠፈር ሆነ። ምሽቱ ገፍቶ፤ አብዛኛው ሰው የሚቀምሰውን ቀማምሶ በየማደሪያው እንደ ተሠማራ ቴዎድሮስ በኋላ እንደ ነገሩዋቸው ቀስ በለው ብቻቸውን ወደ ዳገቱ አናት ወጡ፤ ብቻቸውን ከሐሳባቸው ጋር ለመወያየት። ዐልፎ ዐልፎ በሚገኝ ቀዳዳ ብልጭ ስልም ከሚሉት አንዳንድ ከዋክብት በስተቀር በነሐሴ ዳመና ከተሸፈነው ሰማይ ሥር ድቅድቅ ጨለማ ሰፍኗል። ከቀኑ አደጋ በኋላ እሳት ማቀጣጠል እንደ ወንጀል የተቆጠረ

ይመስል፤ በሠራዊቱ ሠፈር ስንኳ አንዳችም የሳት ምልክት አይታም። ቴዎድሮስ ከአንድ ቁጥቋጦ ጥግ ድንጋይ ላይ ከዚህ ጨለማ ጋር ተፋጥጠው ተቀመጡ። ከዚህ ዐይነት ለረጅም ጊዜ ተቀምጠው እንደ ቆዩ ከታች ከዳገቱ ጎን የሰው ድምፅ እንደ ነፋስ ሽውታ መጣባቸው። ድምፁ እየቀረበ ሲመጣ የሁለት ሰዎች ጭውውት መሆኑ ለየ። የባሰውን ሽምቅቅ፤ ድርቅ አሉ። ሁለቱ ሰዎች በአጠገባቸው ለማለፍ ተቃርበው ነበር። ግን ከቁጥቋጦው ጥግ የተቀመጠውን ሰው አላዩም። ማንም እንዳልሰማቸውና እንደማይሰማቸው የሐሜት ጭውውታቸውን ቀጠሉ።

«ኧረ ምን ያህል ቢወዳት ነው እባክህ?»

«ይኸን መውደድ አልለውም። ልክፍት እንጂ! ለመሆኑ ስንት የሚሆን ይመስልሃል በውሃ የተወሰደው ሰው?»

«ምኑ ታውቆ፤ አለቆቹም ቴዎድሮስ የባሰውን እንዳያዝን ብለው ነው መሰለኝ፤ ተቆጥሮ እንዲታወቅ አልፈለጉም።»

«ኤዲያ! ምን ያዝናል በልህ ነው?»

«ለምን አያዝንም ሠራዊቱ በውሃ ሲወስድበት?»

«ቢያዝንማ ኖሮ፤ ተመሥረቱ የበሰበሰ ሬሣ ተሸክሞ አገር ታገር እያንከራተተ በውሃ ሙላት ሊያስጨርሰን ይነሣ ነበር?»

ቴዎድሮስ፤ የሰውየውን ንግግር መጨረሻ አልሰሙትም። መላ ሰውነታቸው ነዝሮ እሳት ውስጥ እንደ ተጨመረ የጥጥ ጓል እርር ያለው፤ ‹የበሰበሰ ሬሣ› የሚለውን ቃል ሲሰሙ ነበር። ጆሮዋቸውን ማመን አቃታቸው። ተዋበች የበሰበሰው ሬሣ ለመባል በቃች? ሰዎቹ የተፈጥሮ ግዴታውን አሟልተው እስኪመለሱ ድረስ ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት እንደ በድን ደርቀው ቆዩ። ከዚያ ሰዎቹ ወደ ማደሪያቸው ሲመለሱ በአንድ ሥውር ኃይል እንደሚሳብ ኮቴያቸው አጥፍተው ተከተሉዋቸው።

ቴዎድሮስ፤ ‹የበሰበሰ ሬሣ› የሚለው ቃል በዕዝነ ልቦናቸው እንደነጎድጓድ እያስተጋባባቸው፤ ከንፈራቸውን እየነከሱ፤ አንጀታቸውን በአንጀታቸው እየበሉ በዐይናቸው እንቅልፍ ዝር ሳይል ነጋ።

ጧት ሁለቱ ሰዎች ተይዘው መጥተው ችሎት ተሠየመ። ከሁለቱ ሰዎች በተዋበች ላይ ያንን ጠያፍ ቃል የትኛው እንደተናገረው ቴዎድሮስ በድምፃቸው መለየት አላቃታቸውም።

ለችሎት የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ሲገረም፤ ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት ተነሡና ከተከሳሹ ጎን ቆሙ። ግን ከዚያ በፊትም አንድ ጊዜ አድርገውት ስለ ነበር ለብዙዎቹ ፍጹም አዲስ ነገር አልሆነባቸውም።

«ፍረዱ፤ ወይ ፍረዱልኝ፤ ወይ ፍረዱብኝ» አሉ ቴዎድሮስ በችሎት ለተሰበሰበው ሰው።

«እኔን የሰደበ ምን ይሆናል?» ሲሉ ጠየቁ።

«ይቀጣል» የሚል የብዙ ሰው ድምፅ አስተጋባ።

«በምን ይቀጣል?» ቴዎድሮስ እንደገና ጠየቁ።

«በሞት።»

«ባልና ሚስት ሁለት አካል ይሁን እንጂ አንድ አምሳል ናቸው ተብሏል። ነውም አይደል?» ቴዎድሮስ ከውስጣቸው በንዴትና በቁጣ መቃጠላቸው ቢያስታውቅም ረጋ ብለው ለመታየት ሞከሩ።

«ነው እንጂ!»

«ስለዚህ እኔን የሰደበ ተዋበች ሰደበ፤ ተዋበችንም የሰደበ እኔን ሰደበ ማለት ነው። ነውም አይደል?»

«ነው።»

«ኧረ ነው።»

«ምን ጥርጥር አለው?»

«እንግዲያው ይህ ሰው» አሉ ወደ ከሰሱት ሰው እጃቸውን ዘርግተው እያመለከቱ። «ትናንት ማታ ተዋበችን ያልሆነ ከባድ ስድብ ሰድቧታል፤ ሰድቦኛል፤ ወይስ ትክዳለህ?» ሲሉ በሰውየው ላይ አፈጠጡበት።

በዚህ ወቅት፤ በድካምና በድንጋጤ ስሜት የተናገረው እንጂ ከልቡ አለመሆኑ ገጹ ጥፋቱን አምኖ ምሕረት ቢጠይቅ፤ ቴዎድሮስ ምን ግን ጨርሶ ተስፋ በመቁረጥ ይሁን በመታበይ ሳያስተባብልም፤ አምኖ ይቅርታ ሳይጠይቅም ዝም ብሎ ቆመ።

ይህ ሁኔታ ቴዎድሮስን የባሰ አብግኖዋቸው፤ ሰይፋቸውን መዝዘው ለመሰንዘር የከጀሉ ከመሰሉ በኋላ ጥርሳቸውን ነክሰው ገቱት። አንድ ጊዜ ፍርድ ከጠየቁ በዚያው ማለቅ አለበት።

«እንግዲህ ፍርድ ስጡኝ» አሉ።

«ምን ጥያቄ አለው! ይቀጣል።

«በሞት ይቀጣል።

«ሞት ይገባዋል።»

«በስቅላት፣»

«በድንጋይ ተወግሮ ሲገደል ይታየኛል።»

ፍትሕ ለመስጠት ያሰበውም ቴዎድሮስን ለማስደሰት የፈለገውም እየተነሣ ብያኔውን አሰማ።

ቴዎድሮስ፤ ከዚህም ከዚያም የቀረቡትን ትችቶች ከአዳመጠ በኋላ፤ «ፍርዳችሁን ከሰጣችሁ» በሞት እንዲቀጣ ከፈረዳችሁበት የአገዳደሉን ዐይነት እኔው እወስናለሁ» አሉ፤ ሰውዬው አሁንም አንዳችም ዐይነት ፍርሃትና መርበትበት ባለማሳየቱ በንዴታቸው ላይ እየተገረሙ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ አንዳችም አስተያየት አላቀረቡም ነበር። ቴዎድሮስ ከሌሎቹ ይልቅ የርሱን ምክር እንደሚያዳምጡ ቢያቅም፤ በራሳቸው ባለማሳየቱ በንዴታቸው ላይ እየተገረሙ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ አንዳችም አስተያየት አላቀረቡም ነበር። ቴዎድሮስ ከሌሎቹ ይልቅ የርሱን ምክር እንደሚያዳምጡ ቢያውቅም፤ በራሳቸው ሐሳብ የሚመሩበት ጊዜ ደግሞ አለ። በሰውየው ላይ ሞት ለማስፈረድ ወስነዋል። የፈለጉትን ፍርድ ካገኙ በኋላ፤ ምናልባት በመጨረሻ ምሕረት ያደርጉለት ይሆናል የሚል ግምት ነበረው። አሁን ሰውየው በሁለት ወታደሮች የፊጥኝ ተይዞ እየተዳፋ ቴዎድሮስ ቀድመው እየመሩ ከሠፈሩ ወጣ ብሎ ወደ ሚገኘው ጫካ ሲወስድ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ፊቱ በርበሬ መሰለ። ከንፈሩን እንደ መንከስ አደረገ። ከጫካው ውስጥ እስኪሰወሩ ድረስ በዐይኑ ተከተላቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቴዎድሮስና ሁለቱ ወታደሮች ተመለሱ።

የሆነው ሁሉ ሳይነገረው ዐወቀ።

ቴዎድሮስ፤ ከሃምሳ ያልበለጡ ሰዎች ይዘው በቋራ ከሸፈቱ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ፤ በዚህ ቀን ጉዞ፤ ከሠራዊታቸው መካከል ከመቶ የሚበልጡ ከድተዋቸው መዋላቸው ማታ ሠፈር ሲደረግ ታወቀ። ቴዎድሮስ ግን፤ በነገሩ የመታከትና የማዘን እንጂ የቁጣ ስሜት አላሳዩም።

ይህ የሠራዊታቸው መከዳት የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው አልሆነም። የሠራዊቱ መከዳትና ጉዞውም ቀጠለ።

አንድ ቀን ማምሻውን ከሸፈተው አገር እየተነዳ ከመጣው ከብት ታርዶ ሠራዊቱ ጥብሱንም፤ ጥሬ ሥጋውን ሲመገብ ቴዎድሮስ የሽምብራ ቆሎ በውሃ ሲያወርዱ፤ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በኅዘኔታ እንደሚያስተውላቸው ተመልክተው፤ «መቸም በጣም እንዳዘንከብኝና እንደ ታዘብከኝ፤ አንድና ሁለት የለውም» አሉት።

«በምኑ አባ ታጠቅ?» ሲል ጠየቃቸው።

«አሄሄ! አሁን ማን ይሙት አጥተኸው ነው የምትጠይቀኝ፤ እንግሊዞች በነገር ቁጥቦች ናቸው እንደሚባለው መቸም አንተ ሀገራችንን ወዲህ፤ ኢትዮጵያዊ መሆንህ ባያጠያይቅም፤ የዘር ጠባይህ አለቅህ ብሎ ነው እንጂ» አሉት ቴዎድሮስን፤ ላመል ያህል የትካዜ ፈገግታ እየታየባቸው። «ሌላው ቢቀር ሰውየውን ስቀጣ ቀይ ፊትህ ምን ያህል በርበሬ እንደ መስለ ተገንዝቤያለሁ። ተዚያምወዲህ እንደ ወትሮህ ለኔ ምክርና አስተያየት ያልከጀልከው ያለምክኛት አይደለም።የሠራሁት ሥራ ስሕተት ቢመስልህ ነው፤ ይታወቀኛል፤ ግን አትፍረድብኝ ወድጀን አይደለም» ሲሉ ቴዎድሮስ በቅሬታ ራሳቸውን እየነቀነቁ።

«መቸም ‹ከሰው ስሕተት ከብረት ዝገት አይጠፉም› ተብሏል አባ ታጠቅ። እንግሊዞችም፤ ‹የማይሳሳት የማይሠራ ብቻ ነው› የሚል አነጋገር አላቸው። አለ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በማጽናናት አኳኋን።

«እሱማ ነው። ግን ስሕተት እኮ ሳያውቁት የሚሠራ ነው። እኔ ግን ታውቆኛል። ዛዲያ ምን ላድርግ? የተዋቡ ነገር ሆኖነብኝና አላስችል አለኝ። እህ፤ ስለ እኔና ስለ ተዋቡ ከሁለታችን በቀር ማንም በሚገባ ሊገነዘብ የሚችል የለም። በቃልም ማስረዳት በጣም ያስቸግራል። ተዋበች ለኔ ሚስት ብቻ አልነበረችም፤ ሁሉ ነገር ናት» አሉና ቴዎድሮስ የትዝታ ሰመመን እንደ መውሰድ አደረጋቸው። «ንጹሕ፤ ቀና ፍጡር ነበረች። በአሳቢነቷ፤ በፍቅርዋ፤ በርኅራኄዋ፤ የእናቴና የእናት ሀገሬ ምሳሌ ናት። ሲከፋኝ የምታጽናናኝ ጋሻዬ፤ ሳጠፋ የምትመክረኝ መምህሬ ናት። ዐመሌን፤ ጉዴን የምትሸፍንልኝ፤ የምትደብቅልኝ የምሥጢር ሙዳዬ ናት። ኧረ ምኑን ልንገርህ?» ቡና አቅርባ ከአጠገብ የተቀመጠችው ታንጉት ጭውውታቸውን እንደምታዳምጥ ተመለከቱና፤ «እውነቴን አይደለም አንጓች?» ብለው ንግግራቸው ቀጠሉ። «ዛዲያ እንደዚህ ያለችውን ፍጡር ሳያውቃት ሳትበድለው ለአፍ በሚከብድ፤ ለጆሮ በሚቀፍ ቃልት ሲያነሣት መታገሥ አቃተኝ። ምሕረት ማድረግ አልሆንልህ አለኝ። እና አትፍረድብኝ ሊቀ መኳስ።

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ መልስ ወይም አስተያየት አልሰጠም፤።

«በክረምት ሙላት ባንድ ፊት የተዋቡን አስክሬን አሸክሜ፤ በሌላ ፊት ያገሬን ጥፋቷን እንጂ ልማቷን የማይወድ ወንበዴ እያሳደድኩ፤ ሠራዊቴን አገር ላገር እያንከራተትኩ ማጉላላቴ ብዙውን ሰው ደስ እንዳላሰኘው ይታወቀኛል። ታለበለዚያማ፤ ሠራዊት ከሌላ እየከዳ ወደኔ ይገባ ነበር እንጂ መች ከድቶኝ ያውቅ ነበር? ዛዲያ አሁንም ቢሆን ወደን አይደለም። በሰማይ ነፍሷን ይማርና ተዋቡ በሕይወትዋ ዋና ምኞቷ ኢየሩሳሌምን መሳለም ነበር። እኔም ብሆን በሕይወቷ ያልተሳካላትን፤ ባይሆን አስክሬንዋን ኢየሩሳሌም ወስጄ በዴር ሡልጣን ገዳም ባሳርፈው እወድ ነበር። ግን ኢየሩሳሌም በቱርክ ተይዞ የማይቻል ተሆነ ሌላው፤ ቢቀር አስከሬንዋን ከኢየሩሳሌም የመጣው ግማደ መስቀል በተቀመጠበት በግሸን ማርያም እንዲያርፍ ማድረግ፤ ልፈጽምላት፤ ላደርግላት ላሟላላት፤ የሚገባኝ ትንሹ ነገር መስሎ ስለታየኝ ነው።

«አዎ አባ ታጠቅ፤ ሰው ለሚያፈቅረው ከዚህም የበለጠ ከዚህም የከበደ ያደርጋል። ሌላው ስሕተት መስሎ ቢታይ፤ ለሌላው ችግር ቢመስለው ለእርስዎ ትክክል ነው» አለ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በማጽናናትና የኀዘን ተካፋይ በመሆን አኳኋን፤ «ግን ደግሞ ኀዘንን በልኩ ማድረግ ተገቢ ነው» አለ መልሶ በምክር መልክ፤ «በኀዘን መኮማተር ራስን መጉዳት ብቻ እንጂ ሟችን አይመልሰውም። መቸም ሰው ሆኖ መሞት አይቀርም። ብቻ አንዱ ሲቀድም፤ ካለጊዜው ሲቀጭ ሰቀቀን ላይ ይጥላል። ዛዲያ ከሆነ በኋላ እየተበረታቱ እየተጽናኑ መሔድ በሕይወት ያሉ ሰዎች ተግባር ነው። ታለበለዚያማ ሕይወት ትርጉም አይኖረውም።»

«ታልክስ ሕይወቴ ከፊል ትርጉሙን አጥቷል። ለሕይወት ሁለት ትርጉሞች ይዤ ነበር። አንድ ለሀገሬ ያለኝ ዓላማ፤ ሌላው ተዋቡ ነበረች። አንዱዋን አጥቻለሁ። በአንደኛው እስከሆነልኝ አዘግማለሁ። ምክንያቱም ዋናውን ዓላማዬን የምታግዘኝ እርሷ ነበረች!»

«ቢሆንም፤ መፈስን አለማወክ፤ አለማስጨነቅ ነው። ጤንነትን ከመጉዳት በስተቀር ምንም አይጠቅም።

«ግዴለህም፤ አታስብ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ። ተዋቡ ተዘላለም ቤትዋ እንድታርፍ ታደረግሁ፤ የኔም መንፈስ እንደ ምንም ዐረፍ ይልልኝ ይሆናል።» አሉ ቴዎድሮስ።

ቴዎድሮስ በወሎ ሽፍቷል የሚባለውን እየቀጡ፤ የዐመዴ በሽር ቀንደኞች ናቸው የሚባሉትን እየተከታተሉና እየወጉ፤ የተዋበችን አስከሬን እንደያዙ ብዙ

ወራት ከተንከራተቱ በኋላ ግሸን፤ ሲደርሱ በሺህ የሚቆጠር ሠራዊት በየቦታው እየከዳ ቀርቶባቸው ነበር።

በግሸን ማርያም፤ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት በሰባት ጉዞ ፍታት የተከናወነ ቢሆንም፤ ሠራዊቱ በመንገድ ብዛት የተዳከመ፤ የወሎ ሕዝብም እየበረገገ ከአቅራቢያቸው የሚሸሽ ስለ ነበር፤ እስከዚህ የደመቀ አልነበረም። ቴዎድሮስ ግን፤ እንደ ነገሩ ከባድ ሸክም የወረደላቸው መስለው ነበር።

ታንጉት እንደ ሕልም የሚመስለውን የተዋበችና የቴዎድሮስ፤ «የፍቅር መጨረሻ ጉዞ» - ሌላ ትርጓሜ ስላጣችለት፤ አንድ ጊዜ ይህ ቃል መጥቶላቸው ነበር - በሐሳብዋ ተጉዛ ሳጥጨርስ ከዚህ በኋላስ፤ የሚለው ጥያቄ መጣባት። የምታግዘኝ እርሷ ነበረች ብሏል? እኔስ እንዳግዘው መቸ ጠየቀችኝ? እንደሚያሳድጋት ልጅ ዐይነት ከመቁጠር በስተቀር። አጋዥ አጥቶ አንዳነከሰ ይቀር ይሆን? ወይስ ተዋበችን ወይስ የተዋበችን ፍቅር የሚተካለት ያገኛል? ቢያገኝ ደስ ይላታል? ይከፋታል፤ ስሜቷ አለየለትም። በእነዚህ ኮቴ የቀሰቀሳት። ቴዎድሮስና የቅርብ ባለሚሎቻቸው እርሷ ወደ ተቀመጠችበት አግጣጫ በመምጣት ላይ ነበሩ።

ቴዎድሮስ፤ ፊታቸውን ወደ ደብረ ታቦር ካዞሩበት ከግሸን የብዙ ሳምንታት መንገድ ርቆ፤ በጎንደር ከተማ፤ ጠጉረ ልውጥ፤ ቀለመ ልሙጥ፤ በተለየ ስሜት፤ ለተለየ ዓላማ ስለ ተዋበች ሞትና፤ ስለ ወደፊቱ የቴዎድሮስ የፍቅር ዕድል እንደዚሁ ታስባለች። እሷም ሚስስ ሮዜንታል ናት።

ቴዎድሮስ፤ ሥልጣን ከመያዛቸው በፊት ሆነ በኋላ ክርስትና እንሰብካለን በማለት፤ በሃይማኖት ስምና ልዩ ልዩ ጥናት ለማድረግ ከመጡት መካከል፤ ሚስተር እስተር እና ሚስስ ሮዜንታል የተባሉት የስኮትሽ ሚስዮናዊ ማኅበር አባላት ይገኙበታል። ሚስተር እስተርን ቀደም ሲል መጥቶ ከሔደ በኋላ ሁለቱን ሌሎች ባልና ሚስት ያመጣቸው በሁለተኛው ጉዞው ነበር።

ቴዎድሮስ፤ ገና አሊ ቤተ መንግሥት ከነበሩትበት ጊዜ አንሥቶ ስለ ውጭ አገር ሚስዮናዊን የጥርጣሬ አመለካከት ነበራቸው። ምክንያታችው፤ ሃይማኖትም፤ ሀገርም የሚመለከት ነበር። ራሳቸው አጥብቀው የሚያምኑትን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በሚመለከት ረገድ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፤ ከኤፌሶን ጉባኤና ከቅዱስ ቄርስሎስ ጋር በመተባበር፤ ሥጋና ከመለኮት ነጥሎ አካልና ባሕርይን ከፋፍሎ፤ የስበከ ንስጥሮስንና ተከታዮቹን መርታቱና፤ በኋላም በመርቅያን፤ በበርክልያን፤ በሮማው ፓፓ ያምናሉ። ያምኑበታል። የሀገርን ሰላምና ደኅንነት በሚመለከት ረገድ፤ በአጼ ዮሐንስ ዘመነ ምንግሥት ጴጥሮስ ፐኤዝ የተባለው ሚስዮናዊ ባሰራጨው የካቶሊክ እምነት ምክንያት የተነሳ የእርስ እብርስ ጦርነት፤

በጎጃም በቤገምድር፤ በትግሬና በላስታ ብዙ ሺህ ሕዝብ ያስፈጀ መሆኑን፤ በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የብዙ ሰው ደም ማፋሰሱን፤ አንድ ጊዜ አዘዞ በተባለው የዕጨጌው መኖሪያ ሥፍራ ላይ ብቻ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ለመጨፍጨፋቸው ምክንያት መሆኑን አሳምረው ያውቃሉ። የደከመች ኢትዮጵያን ለማንሳት ዓላማ አይተው ሥልጣን በያዙበት ወቅትም ቢሆን፤ ጥንት ዘተው የሔዱት፤ በኋላ የመጡት ሚስዮናውያን፤ ገዳም ከገዳም በማጋጨት፤ ክርስቲያን ከክርስቲያን በማጣላት የሚያደሱትን ጉዳት እንደ ቀጠለ ነበር። ይህን ሁሉ በሚገባ በመገንዘባቸው ቴዎድሮስ ሚስዮናውያንን ሁሉ የሚመለከቱት በጥላቻም ባይሆን ከፍ ሲል በሥጋት፤ ዝቅ ሲልም በንቀት ነበር። አንድ ጊዜ ቆንስል ፕላውዴን ምክንያት ቢጠይቃቸው ሃይማኖት ምክንያት በየዘመናቱ የደረሰውን ጥፋት ከተረኩለት በኋላ፤ «ዛዲያ አሁንም የሆነ እንደሆነ፤ ይኸ ሁሉ አልበቃነ ብሎ ነው፤ ተመልሰን ታጥቦ ጭቃ የምሆነው? አሁንም ቢሆን ለማመሱ፤ ለማተራመሱ፤ እነ አራት ዐይና ጎዙ መቸ አነሱኝና ነው ተጨማሪ በጥባጭ ከባሕር ማዶ የማስመጣውም?» ብለውት ነበር።

የታወቁት የቅኔ መምህር አራት ዐይና ጎሹ፤ የቅባቶች አፈ ጉባኤ ነበሩ። በወቅቱም ከሞላ ጎደል በአንድ ፊት በቅባቶችና በጸጎች፤ በሌላ በኩል ወገን በተዋሕዶች መካከል በየገዳምቱና በየደብሩ በየሃይማኖት ትምህርት ከፍተኛ ክርክር እየተካሔደ ነበር። በዚህ ላይ ‹እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ› እንደሚባለው፤ የሀገር አንድነት ገና ሳይጸና፤ የሽፍታውና የጸጥታው ችግር ሳያንስ፤ ባዕዳን ያመጡት የሃይማኖት ሁከት እንዲጨመር ቴዎድሮስ አይፈልጉም። ‹ሳይቸግር ጤፍ ብድር› መሆኑ ያውቁታል።

ያም ሆኖ፤ ክርስቲያኑን እንደገና ቄደር እናጥምቅ እስካላሉ ድረስ በሕዝበ - ክርስቲያኑ መኻል ገብተው ባዕድ መሠረተ - እምነት እንሰብክ እስካላሉ ድረስ፤ ወይም በሀገርና በመንግሥት ጉዳይ ላይ ልባቸው ለቂም ሐሳባቸውን ለተንኮል፤ አንደበታቸውን ለበደል እስካላነሡ ድረስ፤ ቴዎድሮስ ሚስዮኖች በግልጽ አይቃወሙም ነበር። እንዲያውም የቱርክን የወረራ ሥጋት ከእስከምና ሃይማኖት መስፋፋት ጋር የተያያዘ አድርገው ስለሚገምቱት ለዚህም ከግራኝ ጀምሮ ብዙ ታሪክ ምክንያት አላቸው በተወሰነው አካባቢ የእስልምንና እስላሞችንና አረመኔዎችን እያስተማሩ ክርስትና እንዲጠምቁ ፈቅደውላቸዋል።

እነ ሚስተር እስተርን የመጡት የአሪት አማንያን የተባሉትን ፈላሾን ለማጥመቅ ነበር። ቴዎድሮስም፤ ሀገርና መንግሥትን በሚመለከት ረገድ ፈላሾችን እስከዚህ አሳሳቢ አድረው ባይቆጥሩዋቸውም፤ ከኦሪትነታቸው አንዳችም ዐይነት

ክርስቲያንነት ሳይሻላቸው አይቀርም በማለት እስተርን በጀንዳ፤ በትክል ድንጋይ፤ በቸቸላ የጀመረውን ሥራ እንዲቀትል ፈቀዱለት።

ቄስ ሄንሪ እስተርን ግን በተወሰኑ ሥፍራዎች፤ በሃይማኖት ተግባር ብቻ የሚወሰን ሰው አልነበረም። በሃይማኖትና በሃይማኖታዊነቱ ፍጹማዊ አማኝ ነበር። ከዚህም የተነሳ ራሱን ፍጹም ትክክለኛ፤ ፍጹም ጻድቅ፤ ፍጹም ትክክለኛ፤ ፍጹም ጻድቅ፤ ፍጹም የሚፈጸመው ተግባር ትክክለኛ፤ የርሱን ትክክለኛነት መቃወም ግን ኃጢአት መስሎ ይሰማዋል።

ለዚህ ስሜቱ መነሻ ነበረው። በእስኮትላንድ የድንች ረሃብ እልቂት ከቤተሰቦቹ መካከል ተርፎ የወጣ ነበር። ይህንንም እግዚአብሔር ለትልቅ ሥራ መርጦ እንደ ፈጸመው ተአምር ይቆጥረዋል። ከዚያም በሚስዮን ትምሕርት ቤት በኩል ዐልፎ የቅስና እምንጦላዕት ሲደርብ፤ ከልጅነት ትዝታ ከወረሰው ምሬቱ ጋር አጣምሮ የያዘውን የእስኮትሽ ግልፍተኝነቱን አላወለቀም ነበር። ራሱን ከሰው በላይ አድርጎ በሚገምትበት የሐዋርያዊነት ስሜት ወደ የመን አገር ተጉዞ በዐረቦች እስልምና ሥር የነበሩትን አይሁዶች በእምነት። የታሰረው በዘላኖች፤ ሠፈር ነበር። በቴምር ተክል አካባቢ በተተከለ ድንኳን፤ ደመራ የመሰለ እሳት እየተንቀለቀለ፤ ጐራዴ እየተመዘዘ ሲቃጣበት፤ ሲፎክርበት፤ አሁን ከአሁን አንገቴ ተቀነጠሰ እያለ ዐይኑን ከድኖ ሲጠብቅ፤ ጭፋሮውና ፉከራው ጋብ እያለ ይሔዳል። አብዛኞቹ ተዳክመው፤ ዝለው በየአሉበት ተጋድመዋል፤ ተዝለፍልፈዋል፤ ጎራዴያቸውን፤ ጅራፋቸውን በተዘረጋ ክንድ እንደ ጨበጡ። እስተርን ብድግ ብሎ ነፍሴን አውጭኝ ይፈተለካል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ደማስቆ የሚሔድ የነጋዴ ቡድን አግኝቶ፤ ለህገሩ እንደገና በሌላ አገር ሥራውን ለመቀጠል ይበቃል።

ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ሌሎችንም አመጣ። ነገር ግን በዐረብ አገር የሕይወቱን መትረፍ፤ እንደ ተአምር ስለሚቆጥረው፤ የሌሎችን ነፍስ ከማዳን ይልቅ ስለ ራሱ ከመቃብር መውጣት፤ ጎልቶ ይሰማዋል። ብዙ ጊዜ የሚወራውም ስለዚሁ ነው። ለእንደዚህ ያለው ተአምራዊ ታሪክ አድናቂ የሚገኘው በከተማ ስለሆነም፤ ከተመደበለትና ከአቋቋማቸው የሚስዮን መንደሮች ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ የሚቀመጠው በጎንደር ነበር። ቴዎድሮስ ደግሞ፤ ስንኳን አውሮፓዊ ሚስዮን ቀርቶ፤ ኢትዮጵያዊ መኳንንቱም ቢሆን ያለ ምክንያት ጎንደር የሚቀመጥ ሰው አይወዱም። ‹ወይ ጋለሞታ ሲያጫውት ነው፤ ወይ ተንኮል ሲያደራ ነው› የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው። ሚስተር እስተርን አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፈው ከአቡነ ሰላማ ጋር ለመሆን ወሬ ደርሷቸዋል። የጋፋት ሰዎች ስለ እነእስተርን የነገሩዋቸው ምናልባት የተጋነነ ሊሆን ቢችልም ልብ የሚነከንኩ ነጥቦች ነበሩበት። ነገር ግን፤ ከስንቱ ጋር

ተጣልቶ በሚል ስሜት ዐልፎ ዐልፎ እየገሠጹና እየተቆጡ እንደምንም ችለውት፤ ታግሠውት ኖረዋል።

ሚስስ ሮዜንታል ደግሞ ሕይወቷ ከእነእስተርን ሚስዮናዊ ሕይወት ጋር የተቀናጀው፤ በሃይማኖታዊ ስሜት፤ ወይም በሐዋርያዊ መንፈስ አልነበረም። ሕፃን ሆና ስንኳ፤ እንደ መሰሎቿ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አይመርካትም ነበር። ሌሎች ልጆች እሑድ መጥቶ የክት ልብሳቸውን ለብሰው ቤተ ክርስቲያን የሚሔዱበትን ጊዜ በጉጉት ሲጠብቁ ሮዜንታል ስለ እሑድ የምታልመው፤ ከቲአትር ቤት ጋር በተያያዘ መንገድ ነበር። ግን የሚስባትና የሚማርካት ተውኔት ሳይሆን በተለይ ለሴቷ ተዋናይ ተመልካች የሚሰጠው አድናቆት ነበር። ከዚህም የተነሳ፤ ወጣትዋ ሮዜንታል ኻያ ዓመት እስኪሞላት ድረስ እየተራፈቀ ካደረባት ብዙ ዐይነት ምኞት ዋናው፤ በድፍን አውሮፓ ስሟ እየጠራ ተዋናይ መሆን ነበር። ተውኔት ትምህርት ቤት ገብታ ሞከረች፤ አልሆነላትም። አስተማሪው አንድ ሳምንት ከፈተናት በኋላ፤ ‹ያንቺ ችግር ምን መሰለሽ? ቲአትር ከመጫወት ይልቅ በሐሳብሽና በስሜትሽ ለራስሽ ነው የምታጨበጭቢው› ሲል አሰናበታት። ከዚህም አንድ ልዑል አግብታ ልዕልት ለመሆን ተመኘች። ስንኳን ልዑል ደኅና ከበርቴ ባል አላጋጥማት አለ። ያልተሳካ ምኞት፤ ወደ እውን ያልተለወጠ ሕልም፤ ብስጭትጭት፤ ቅብጥብጥ እያደረጋት በሔደበት ወቅት ነበር ከሚስተር ሮዜንታል ጋር የተገናኘችው። በውበቱም ሆነ በቁመናው ይማርከኛል በፍቅር ‹ይወድቅልኛል› ብላ ያሰበችው ወንድ ዐይነት አይደለም። አፉ የጉጉት የመሰለ ነው። ስብከት የሚያሰማበት ድምፁ ሳይቀር ያለልክ እንደተወጠረ ጅማት ሲጢጥ የሚል ይመስላል። ሚስዮኑ ከሚካፈለው አበል በቀር ሌላ ሀብት የለውም። ነገር ግን፤ ለስብከተ ወንጌል ኢትዮጵያ ወደሚባ የጥቁር ሕዝቦች አገር እንደሚሔድ ሲነግራት፤ ለተቀጨ ምኞቷ መካሻ ዕድል የቀረበላት ሆኖ ተሰማት። ነጭ ልዑል ልታገባ ባትችል በደንቆሮ ጥቁር ሕዝብ መካከል እንደ ልዕልት ትከበራለች። በግሩም ተዋናይነቷ የሚያጨብጭቡላት፤ የሚያደንቃት፤ ‹ፊርማዋን የሚለምናት› ተመልካች በአውሮፓ ባታገኝ፤ በአክብሮት የሚሰግድላት ጥቁር ሕዝብ ይኖራታል። ብዙ ዓመታት ቆይታ እንደገና ወደ ሀገርዋ ስትመለስም፤ እስከ ዓለም ዳርቻ ተጉዛ ስለ ፈጸመችው ገድል፤ ስለ አዳነችው ነፍስ ስትተርክ ሰው ሁሉ በአድናቆት ያዳምጣታል። ሚስተር ሮዜንታልን አግብታ ወደ ኢትዮጵያ የመጣችው ለዚህ ስትል ነበር።

ወደ ኢትዮጵያ ከመጣች በኋላ ያጋጠማት ሁናቴ ግን እንደ ገል ፍርክስክሱን አወጣባት። ጭርንቁስ ከለበሰ ደሃ ገበሬ አንሥቶ የሚያደንቃትን፤ የሚሰግድላትን ቀርቶ አንዳችም የተለየ ግምት የሚሰጣት ሰው አላገኘችም። በንጣትዋ፤ በአለባበስዋ እንደ ጉድ አይተዋት፤ ተቀላልደው፤ ተሣሥቀው ገልመጥ ገልመጥ ብለው

ተመልክተው ያልፉዋታል። መጀመሪያ ላይ ምናልባት ቀደም ሲል ዐረቦችንና ቱርኮችን በማየታቸው በቆዳ ፍካት አንድ መስያቸው ቢሆን ነው ስትል ራስዋን አጽናናች። ከየት አገር እንደመጣች፤ ማን እንደሆነች ለምን ከፍተኛ ተግባር እንደመጣች ቀደም ሲል ከሚስዮኖች ጋር ቆይተው አንዳንድ እንግሊዝኛ ቃላት በሚሞክሩ አስተርጓሚዎች አማካይነት ማስረዳት ባዳ በመሆንዋ ያዘኑላት ይመስል ብቻ ከንፈራቸውን ይመጡላታል። ከራሳቸው ዝቅ አድርገውም ባይሆን ከራሳቸው ቅንጣት ያህል ከፍ አድርገው እድነማይመለከቱዋት ሲታወቃት ትበሽቃለች። ትበግናለች። ግን ሕልሟ ሁሉ እንደ ጉም በንኖ መቅረቱን መቀበል ስለማትፈልግ ምርጥ ቀሚሷን ከነመደረቢያ ካባዋ ትለብስና፤ እንደ ምኞትዋ ልዕልት፤ ቀጥ፤ ጅንን፤ ኮስተር ብላ መሔድ ስትጀምር፤ ጉምጉምታው ሣቅን ለማፈን ይመስ አፍን በመዳፍ መከደኑ ይበዛል።

በንዴት ምክንያት ትጠይቃለ። «ምን ነካት ሴትዮዋ? የሙቀጫ ልጅ ውጣለች እንዴ እንደዚህ የደረቀችው?» ብለው እንደሚቀልዱ ይነገራታል እርር ትላለች።

ተስፋ ባለመቁረጥ የምትፈልገውን ከበሬታ ለማግኘት ስትል ወደ ሌላው ጫፍ አቀራረብ ትሔዳለች። መናኛ ለብሳ፤ ራስዋን ሸፍና ጎንበስ ብላ አንገቷን በመድፋት፤ የጥቁር ሕዝብ ነፍስ ለማዳን ሕይወትዋንና የድሎት ኑሮዋን የሠዋች ለመምሰል ትሞክራለች። ውጤቱ ካሰበችው የተገላቢጦሽ ይሆንባታል። ‹ኧረ ይች የውጭ አገር እንግዳ አንጀትዋ ታጥሮ ልትወድቅ ምንም አልቀራት!› ከጥራጥሬ እስከ ሙክት ድረስ ምግብና መጠጥ ይላክላቸዋል። ከዚያኛው ያላነሰ ያናድዳታል።

‹ደደቦች፤ ምንም የማይገባቸው ፍጹም ደደቦች› ትላለች፤ ከራስዋ ጋር። ከሙብሽቅዋ የተነሣ፤ እርሷ የሚሰማትን የበላይነት ሊረዱት አለመቻላቸውን ከድንቁርና ዐልፎ እንደ ወንጀልም ልትቆጥረው ይቃጣታል። ሌላው ቀርቶ፤ ብዙ ጊዜ አብራቸው በመገኘት እንዲከተሉዋትና እንዲያጅቡዋት የምትፈልገው፤ በክርስቲያኖች ዘንድ ዝቅ ተብለው የሚታዩት ፈላሾች እንኳ የተለየ አክብሮት አያደርጉላትም። ልታስተምራቸው፤ ልታስረዳቸው የምትፈልገውን ነገር በትሕትናና በጥሞና አዳምጠው፤ ዐልፎ ዐልፎም ፈገግታ እያሳዩ ያለ አንዳች መርበድበድ ወደ የግል ሥራቸው ይበተናሉ። የፈረንጁን ጥልፍ ሥራ ስታሳያቸው በበኩላቸው ፈትል ይዘውላት ይቀርባሉ - ሊያሳዩዋት፤ ሊያስተምሩዋት። ሹራብ ሥራ አሳይታቸው ስትጨርስ እየመሩ ወደ መንደሩ ሸማኔ ይወስዱዋታል፤ እኛም አለን የማለት ዐይነት። ከርስዋ ችሎታ ጋር ውድድር መያቸው ያበግናታል።

በዚህ ሁሉ የመንፈስና የስሜት ቁስለት ላይ፤ ሮዜንታል ከባልዋ ጋር ያላት የግብረ ሥጋ ግንኙእንት አስደሳችና አርኪ አልነበረም።

ሚስተር ሮዜንታል፤ ዱሮውንም ከተፈጥሮው ደመ ሞቃት አፍቃሪ አልነበረም። ለአንድ ሚስት የሚሆን ኃይል ባያጣም፤ ጉንፋን የሚያዘወትረው፤ ብዙ ጊዜ ስለሆድ ሕመሙ የሚያወራ፤ አካሉ ኮሰስ ያለ ሰው ነው። ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ ወዲህ ደግሞ ሐሳቡና ስሜቱ፤ በመንፈሳዊና በፖለቲካዊ ተልዕኮው ላይ ስለ ተጠመደ፤ ከሚስቱ ጋር ለፍቅር የሚሰጠው ጊዜ እያነሰ እየተራራራቀ ሔደ። የተፈጥሮ ፍላጎት ጨርሶ አይጠፋምና ዐልፎ ዐልፎ እርሱ ሲያሰኘው ደግሞ እንዳጋጣሚ ሚስስ ሮዜንታል ተበሳጭታ፤ ተብሰክስካ የዋለችበት ጊዜ ይሆናል። በመደሰትና በማደሰት ፈንታ፤ ሌላ በሽቀቷን እርሱን በማመናጨቅ ትወጣዋለች። ደግነቱ ስሜቱን የሚገታ ሰው ስለሆነ እስከዚህም አይማረርም። ችግሩ እርሷ ባሰኛት ጊዜ ደግሞ እርሱ ደክሞታል፤ ሌላ ሐሳብ ይዞታል፤ ወይም የሆድ ሕመሙ ተነሥቶበታል። እንደ ተቃጠለች ታድራለች። በዚህ ዐይነት በሐሳብዋና በስሜቷ ውስጥ አንዳንድ ነገር መምጣቱ የማይቀር ነበር።

ከአንድ ወንዝ ወይም ኩሬ ትደርሳለች። ጎልማሶች፤ ልብሳቸውን አጥበው አስጥተው እየተጫወቱ ገላቸውን ሲታጠቡ ታገኛለች። ከሩቅ ሆና ትመለከታለች - ከውሃው ጋር እንደ ዓሣ የሚያንጸባርቅ ጠይም ቆዳ፤ ስብሰባ ፍርጥም ያለ ገላ። ሲደፋፈቁ ውሃ ሲራጩ ወይም ሲሯሯጡ ሰው ይያቸው አይያቸው ግድ የላቸውም አይመስሉም። በገላቸው አይፍሩእብትም። ከፍ ብለው ውሃ ከሚቀዱት፤ ቅዝ ብለው እንደዚሁ ልብስ ከሚያጥቡት ሴቶች ጋር ስንኳ አይተፋፈሩም። እንዲያውም በሩቅ እየተጠራሩ ይቀላለዳሉ። ሮዜንታል መቀላቀል ያሰኛታል። ያ ጠይም የሚያብረቀርቅ የጎልማሳ ገላ፤ ከርስዋ ነጭ ገላ ጋር ሲጠጋጋ እንደ አበባ ጎብር ቀለም ውበት ሰጥቶ በሐሳብዋ ይታያታል። ከንፈርዋን እየበላች ፈዝዛ ለረጅም ጊዜ ትቆማለች።

ወይም ደግሞ በሠርግ፤ በድግስ፤ እንደ መስቀልና ጥምቅት በመሳሰሉት ዓመት በዓላት ላይ ትገኛለች። ዘፈኑ እንደ ማዕበል ይወርዳል። እስክስታውና ጭፋሮው ይቀልጣል። በኮረዶችና በጎልማዶስ መካከል መሣሣቁ መጠቃቀሱ፤ መሽኮርመሙ፤ መዳራቱ፤ በአበባና በቄጤማ በቀልድ መመታታቱ ይስባታል። አውሮፓ ሳለች እንደ ሰማችውና እንደ ገመተችው ከከብቶች ሥሪያ የማይሻል የአረመኔዎች ሩካቤ ሥጋ አፈጻጸም አይደለም። ወግና ባሕል፤ ፍቅርና መተሳሰብ ያለበት የሕይወት ውበት ነው። የሕይወት ጣዕም የሕይወት፤ ጸጋ ነው። በዚህ የሕይወት እየቀጠለና ውስጥ እርሷም ተካፋይ መሆን ያሰኛታል። ሁኔታው እየቀጠለና እየተደጋገመ ሲሔድ፤ በመጨረሻ ራስዋን መግታት እስኪያቅጣት በአእምሮዋ ውስጥ ቅዠት መሰል ልዩ ልዩ ትርዒት እየፈጠረ ይበጠብጣታል።

መስከረም ወር የኢትዮጵያ ደጋንና ወይና ደጋውን ይዞ ተፈጥሮ ሰው፤ ፈካ የሚሉበት ጊዜ ነው። እንደ መልካም የጥጥ ቁልል፤ ባለሙያ ሴት እንደዋለችበት ንድፍ ጥጥ መስሎ ከሚንጠባጠብ ደመና በስተቀር ሰማዩ ገልጧል። ዐልፎ ዐልፎ ዝናም ይጥላል፤ ብርቱ ዝናም ሊሆን ይችላል። ግን የመስከረምን ዝናም ማንም አይጠላውም። ማንም አያማርረውም። አዝመራ አፋፍቶ ወዲያው ዐላፊ ስለሆነ። እንዲያውም ልጆች ከቤት እየወጡ በፍንደቃ የቀበታሉ። መሬቱ በእሸት አዝመራ አበባና በለመለመ ዕፅዋት ፈክቷል። ወንዙ፤ ምንጩ፤ እየጠራ፤ መሔድ ይዟል። የሰውም ፊት ከተፈጥሮ ጋር ፈክቷል። የዓውደ ዓመት ዕለት ‹የጎመን ምንቸት ውጣ የገንፎ ምንቸት ግባ› ተቦ እንደተጨፈረው ሁሉ፤ ልጅም ዐዋቂውም በእሸት ምግብ ወዛዝቷል። ሥራ በጣም የማይበዛበት፤ የመዝናኛም ጊዜ ነው። የአረም ሥር በአብዛኛው ሥራ በልጅጆች የሚከናወን ሰብልን ከአዕዋፍና ከአራዊት መጠበቅ ነው።

በኢትዮጵያ መስከረም፤ የወበት፤ የተስፋና የደስታ ወር ነው። ለድግስ የሚሆነው ሰብል ገና ተሰብስቦ ስላልገባ፤ በመሰከረም ወር ብዙ ሠርግ ባይደረግም የቅዱስ ዮሐንስና የመስቀል ድግስ አለ። ከሌሎቹ ወራት ይልቅ በመስከረም በርከት ብሎ የሚታይ ሌላም የደስታ ምክንያት አለ። ከታኅሣሥ ወር ጀምሮ አዝመራ ተሰብስቦ እየገባ በሥራ ፈንታ የፍቅር ጨዋታ ስለሚተካ፤ በጥር ወር ሠርግ ስለሚበዛም ይሁን በሌላ ምሥጢራዊ ምክንያት ከሌሎች ወራት ይልቅ የሚወለዱት ሕፃናት በርከት ይላሉ። የማርረሻው ድግስና የዐራስ ጥሪው በዚያው መጠን በመስከረም ወር ተረፍረፍ ይላል። ከዚህ ከሕፃናት ልደት ጋር ተያይዞ በተለይ በፈላሾች ዘንድ በመስከረም ወር የሚበዛ ሌላ በዓል አለ - የግዝረት በዓል።

ግዝረት በፈሳሾች ዘንድ፤ እንደ ክርስትና ሁሉ ድግስና መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት የያዘ ባሕል በመሆኑ፤ እያንዳንዱ ቤተሰብና መንደሩ ጭምር በከፍተኛ ስሜት ያከብረዋል፤ ይፈጽመዋል። እነ ሚስተር እስተርን ወደ በሰባት ቀን መግዘር ሕፃኑን አደገኛ ቁስል ሲያመጣበት የሚችል ከመሆኑ በቀር፤ በክርስትና ሃይማኖት እንደሚያስፈልግ ሲነግሩዋቸው፤ «የኛዎቹ አገር የጥንቱ ክርስቲያኖችስ ይገዝሩ የለ?» የሚል መልስ ይሰጣሉ። ሚስዮኖች አሳምነው ማስቀረት እንደማይችሉ ሲገነዘቡ፤ የግዝረት ባሕላቸውን እንዳሻቸው እንዲቀጥሉ ተውዋቸው። እንዲያውም ከጊዜ በኋላ ወደ ክርስትና ከመለሱዋቸው የፈላሽ ቤተሰብ ግዝረት በዓል ላይ ራሳቸው እየተጠሩ ይገኙ ጀመር። ሚስስ ሮዜንታል፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንድ ጋር የተገናኘችው በእንደዚህ ያለ የግዝረት በዓል ላይ ነበረ።

ሌሎቹ ቀርተው እርሷ ብቻዋን የተገኘችበት ምክንያት አሁን በትክክል ትዝ አይላትም። የሰወየውንም ስም ረስታዋለች። ሌላውን ሁናቴ ግን በሚገባ ታስታውሰዋለች።

የግዝረቱ ሥርዓት ተፈጽሞ፤ ድግሱ ተበልቶና ተጠጥቶ፤ ጊዜው መሸትሸት ብሎ አብዛኛው ተጋባዥ እየተመረቀ ከሔደ በኋላ፤ በጣም ቀራቢ የሆኑ ሴቶች ብቻ ቀሩ። እነሱም ምሽቱ ለዐይን ያዝ ሲያደርግ አራሷን ደጋግፈው ይዘው ወደ ሌላው ትንሽ ጎጆ ሔዱ። ግብር ውሃ መውጫ ጊዜ ነው። ሌሎቹ የዕለት ተግባራቸውን ከውጭ በጓሮ ቢፈጽሙም፤ አራሷን የሚያጸዱት ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ጎጆ ውስጥ ነው። በዚያም ሲያወሩና ምኑንም ምኑንም ሲያደርጉ፤ ረዘም ላለ ጊዜ እንደሚቆዩ ሮዜንታል ታውቃለች። ያን ጊዜ ተሰናብታ መሔድ ትችል ነበር። ግን ከመጠጡ ሞቅታና ከወርቃዊው የስሜት ዑደት ጋር፤ የሚሰዮን ሠፈር ቅርብ ስለሆነ ምን ጊዜም የሚያሠጋ ነገር የለም በሚል ሰበበ ተቀምጣ ቀረች፤ ከልጁ አባት ጋር በጎጆው ውስጥ ብቻቸውን።

ከውጭ በሙሉ ጨረቃ የተንጣለለው ብርሃን ገበብ ባለው በር በኩል ሰፊ አራት ማዕዘን ፈጥሮ በመግባት ከጧፉ መብራትና ከምድጃው እሳት ጋር ተቀላቅሎ የፈጠረው አጠቃላይ ኅብረ ብርሃን በአውሮፓ የቲያትር መድረክ ላይ ትርዒት ምሥጥራዊ የሚመስልና በምሥጥራዊነቱም የሚስብ አንዳች ዐይነት ትርዒት አስፍኗል። የልጁ አባት እንደ ባለቤትነቱ በድግሱ ላይ አቀማመጡ ከበሩ ትይዩ ስለሆነና ጧፎቹም በዚያው አካባኢ ስለ ተቀመጡ፤ አጠቃላዩ ብርሃን እንደ ድባብ ክብ ሠርቶ ዐርፎበታል። ከበሩ ጥቂት ፈቀቅ ብላ የተቀመጠችው ሚስስ ሮዜንታል ሁሉም ከወጡ በኋላ፤ ዐይንዋ በዚያ ድባብ ውስጥ ተተክሎ ቀየ። የሕፃኑ አባት ግድግዳውን እንደተደገፈ ቋንጃውን ወደፊት ዘርግቶ ተቀምጧል። ዐልፎ ዐልፎ ዐይኑን ወደ ሚስስ ሮዜንታል ጣል ከማድርግ በስተቀር አብዛኛውን ጊዜ ዝም ብሎ ወደ በሩ ነበር የሚመለከተው። ግን በተለይ አንዳች የተወሰነ ነገር የሚያይ ደግሞ አይመስልም። ‹ምናልባት የሚጠብቀውን እያሰበ?› ስትል ሚስስ ሮዜንታል በሐሳብዋ። በፈላሾች ባሕል መሠረት ሴት ነፍሰ ጡር ከሆነች፤ ወይም አደፍ ስትሆን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነውርና ክልክል መሆኑን ታውቃለች። ከወለደች በኋላም የግዝረቱ ሥነ ሥርዓት እስኪፈጸምና እናቲቱም ለተወሰነ ቀን እስክትጸዳ ድረስ እንደዚሁ ነው። ዛሬ ይሆናል እንግዲህ የመጀመሪያ ቀናቸው የሚል ሐሳብ መጣባትና ልብዋ በኃይል ይመታ ጀመር። በጣም የተራበ መሆን አለበት። ቀን፤ እጅ ጠባቡንና ሱሪውን ጠቅለል ጠቅለል አድርጎ ጠቦቱን ሲያርድ ያየችው ፈርጠምጠም ያለ መልካም አካሉ በአእምሮዋ መጣ። ገና ሁለት የወለደ ለሚስስ ሮዜንታል የሚታያት መልኩ እልነበረም። ረጅም ጊዜው ነው። ‹ምን ያህል ተርቦ

ይሆን?› የደረት አጥንቷን የሚሰብር እስኪመስል ድረስ ልብዋ እየደለቀ ሳይታወቃት እንደ ደመ ነፍስ ተነሥታ ከጎኑ ተቀመጠች።

«አባት መሆን እንዴት ነው?» አለችው የምትናገርው ጠፍቷት፤ ከራዋ የወጣ ባይመስል ድምፅ።

«እህ?» ሲል መልሶ ጠየቃት፤ ጥያቄዋ አደንጋሮት። ግን ከሁናቴዋና ቀደም ሲል ከተገነዘበው አመለካከቷ አዝማሚያዋ ተሰምቶታል። ስሜቷ ወደ እሱም መጋባቱ የማይቀር ነበር።

«ማለቴ - ማለቴ» ቃላቱም ድምፅዋም ጠፉባት።

«እህ?» ቋንጃውን እንደ መሰብሰብ አደረገ።

ሊነሣ የፈለገ በማስመሰል፤ «የለም - የለም ቁጭ በል» ስትል እጁዋን ከጭኑ ላይ ጣል አደረገች።

ሊፈነዳ ደርሶ ነበር።

ሴቶቹ ሲመለሱ ያገኙዋቸው በዚያው ሥፍራ ላይ በሌላ ዓለም ውስጥ እንደ ሆኑ ነበር። ደግነቱ ጸጉር መናጨት ቀርቶ እምብዛም ግርግር አልተነሣም። በምን ተፍረት ቀሚሷን እያስተካከለች ከቤት ስትወጣ በመገረም በትዝብት ብቻ ተመለከቷት።

ለወንዶቹ ሚስዮናውያን ይነግሩብኛል፤ ወይም ባልና ሚስት ይፋቱና ጉዳዩ ይፋ ይወጣል በማለት ሰሞኑን ጥቂት ሥጋት አድሮባት ነበር። ግን ምንም ነገር አልደረሰም። ባልዋና ሚስተር እስተርን ወይም ሌሎች ሚስዮናውያን ምናልባት ነገሩን ሰምተው ቢሆን ያልሰሙ ነበር የመሰሉት። እሷም ቢሆን በሆነው ነገር አልተቆጨችበትም። ለአጭር ጊዜም ቢሆን ይህ ነው ወደ ማይባል የደስታ ዓለም ደርሳ ተመልሳበታለች። ታዲያ ይኸ ምን ያስቆጫል? እንዲያውም፤ ከዚያው የሕፃን አባት ጎልማሳ ጋር እንዳለፈው ጊዜ እጅ ተፍንጅ እንዳይያዙ ጠንቀቅ በማለት ብትደጋግመው አትጠላም፤ ነበር። ለክፋቱ ሆን ብሎ የሚሸሻት ይመስል ድጋሚ ዕድል አላጋጠማትም አለ። አዳዲስ ዕድል ግን እየቆየ መጣላት።

ስለ እርሷ ሲወራ ወይም ስትታማ አልሰማችም። ግን ወንዶች ስለ እርሷ ያላቸው አመለካከት አዲስ ዐይነት መሆኑ ግልጽ ነበር። ዐይናቸውን የሚተክሉባት፤ በማባበል በፈገግታ፤ በግምገማ መልክ ሆነ። ብዙ ጊዜም አስተያየታቸው በጥቅሻ የታጀበ ነበር። አድፍጦ የሚጠባበቃት ይመስል፤ ድንገት ብቅ ብሎ ፈገግታ የተመላበት ሰላምታ ያቀርብላታል። ጭውውት ይቀጥላል። ፍላጎቱ ከሁናቴው

ያስታውቃል። ሚስስ ሮዜንታል ይህንን ሁሉ ወደደችው እንጂ አልጠላችውም። እንዳፈረሰ ዲያቆን፤ ዐይነ ጥላዋ ድንገት እንደ ተገፈፈላት ኮረዳ፤ አንዴ የጀመረችውን ቀጠለችበት።

ይህ ሁሉ የተወሰነ ወሲባዊ፤ ርካታ ሰጣት። ሌላው ምኞቷ ግን እንደ ተንሳፈፈ የማይጨበጥ፤ ደመና እንደሆነ ቀረባት። ‹ንግሥት ባትሆን፤ ልዕልትም ባትሆን፤› በቤተ መንግሥት አካባቢ ከሚታዩት ወይዛዝርት ልቃ፤ ደምቃ መከበር ትፈልጋለች። አገርዋ ስትመለስ ምን ትተርካለች? ከአንድ ገበሬ ጎልማሳ ጋር በፍቅር ተገናኘሁ ብላ? መኳንንቱ፤ ወሬዋን ሰምተው ንቀዋትም ይሁን ጠጉረ ልውጥ እልፍኝ የማስግባቱን ሐሜት ፈርተው ፍላጎታቸውን በግልጽ አያሳዩም። የራሳቸውን አገር ሴት ሲፈልጉ ጎተት ጎንተል ያደርጋሉ። ከእርሷ ላይ ግን ከቀልድና ከፈገግታ፤ እንዲያም ሲል ሌላ በማይታይበት ጊዜ ከጥቅሻ አያልፍም። ሮዜንታል ከፈልገችና ከልብ ካሰበችበት፤ ደመቅ ያለ ግብዣ ተደርጎ ብዙው መኳንንት፤ ከሞቅታ ዐልፎ ጥንብዝ በሚልበት ጊዜ እንደ መጀመሪያው ፈላሻ ስሜቱ የሚያሸንፈው መኮንን እንደማታጣ አሳምራ ታውቀዋለች። ውጤቱስ? ለወሲብ ርካታ የሚፈጸም አንድ ነገር ነው። ለሌላ ዓላማ የሚሆን ደግሞ ሌላ ነው። እንዲያውም ከተራው ሰው ጋር መነካቷ በመኳንንቱ ዘንድ አንዳች ዐይነት የባሕል ልጓም እንዳደረገባቸው ሁሉ ከመኳንንቱ ጋር መነካካቷ ደግሞ፤ ትልቁን ምኞቷን ሊበጥስባት እንደሚችል ይሰማታል። አትፈልግም።

ሮዜንታል፤ አባ ታጠቅ ስለሚባል ጀግና የሰማችው ገና ተዋበችን ይዞ በቋራ እንደ ሸፈተ ነበር። ታሪኩ ራሱ፤ በእንግሊዝ ልብ ወለዶች መጻሕፍት ያነበበችው ዐይነት ሆኖ ተሰማት። ደሃው ጀግና ልዕልቲቷን ከቤተ መንግሥቱ መንጥቆ ወሰዳት። ልዕልቲቷም በጀግንነቱ ትወደው ነበርና ደስ አላት። ከዚያም በእንግሊዝ ልብ ወለድ ታሪክ እንዳነበበችው «ሮቢን ሁድ» አገሬው ገበሬው ወደደው። ሮዜንታል ስለ አባ ታጠቅ ካሣ አስደናቂ ጀብዱ ከዚያም ከዚያም ስትሰማ፤ ያደረባት አስተሳሰብ ጥንት ያለመችውን ልዑል ብቻ ሳይሆን፤ ከልዑል ጋር የጀግና ፍቅር አብሮ የሚሰጣትን ስሜት ነበር። ከዚያም ሥልጣን ይዘው ጎንደር ላይ የመገናኘት ዕድል አጋጠማት።

ሚስስ ሮዚንታል፤ ከሌሎቹ የውጭ አገር ሰዎች ጋር በእልፍኝ አስከልካይ ጎንደር ቤተ መንግሥት ገብታ ቴዎድሮስን በቅርብ ከተዋወቀች ጊዜ አንሥታ ያላት አመለካከትና ስሜት፤ ልትለየውና ልትገልጸው የማትችል ዝብርቅርቅና ውስብስብ ዐይነት ሆነባት። የምታደንቃቸውን ያህል ትፈራቻቸዋለች። ፈገግታቸው የሚያስደስታትን፣ የሚማርካትን ያህል እዚያው በዚያው መልሶ ያናድዳታል። ይህ

ንዴትም፤ ጥላቻ ወይም በቀል ወደሚመስላት ስሜት ሊቃረብ ይቃጣዋል። ቴዎድሮስን በሚመለከት ረገድ፤ እርሷን በቀጥታ የማይነካ በሚመስል ጉዳይ ስንኳ ስሜቷ ይነካል። ይለዋወጣል። ስለ ቴዎድሮስ ያላት የሐሳብ ሕልም፤ በእንቅልፍ ሕልሟ የኖረችበት ጊዜ አለ። በእውን ግን አልሆነም። ዘወትር የምትሰማው ስለ ቴዎድሮስና ስለ ተዋበች የማይታመን ፍቅር ነው፤ በልብ ወለድ መጽሐፍ እንዳነበበችው ዐይነት። ከዚያም ቆይታ ሚስቱ አንዳቸው በሞት ካልተለዩ በስተቀር፤ ሦስተኛ ሰው ጋር የፍቅር ግንኙነት የማያደርጉበት ቃል ኪዳን መሆኑን ሲያስረዷት ማመን አቃታት። የሮማ ካቶሊኮች ምንኩስና ይገባታል። አፍሪካ ውስጥ በጥቁር ሕዝቦች መካከል ሊኖርና ሊፈጸም መቻሉን ማመን ግን አቃታት። ልታምነው ብትችልም አበሸቃት፤ አናደዳት። ነገር ግን የምኞተኛ ሕይወት እስካለ ድረስ ምኞት አይሞትም። ስሜትና ልብ እስካለ ድረስ ስሜት አይሞትም። ሮዜንታል ሁለቱም ነበሯት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ ቆየች ድረስ በተስፋ የሚያኖራት በመካከሉ ግን ሁለቱንም የሚያጠፋ የሚስተር እስተርን ውሳኔ መጣ።

ከመሠረቱ የሚስተር እስተርን ውሳኔ ብቻ አይደለም። የቴዎድሮስም ጭምር ነው።

‹ወገኔ ተድህነት እንዲላቀቅ ተተፈለገ ተጸሎቱ ቀነስ፤ ተሥራው በዛ፤ ተስብከቱ ቆጠብ፤ ተሙያው በርከት ማድረግ ነው የሚበጀው የሚሉት ቴዎድሮስ በጋፋት መድፍና የብረታ ብረት ሥራ እንዲረዱዋቸው አነእተርንን ይጠይቋቸዋል። እነ እስተርን ግን፤ ከጤንነት ጉድለት እስከ ችሎታ እጥረት ድረስ ድረስ ልዩ ልዩ ምክንያቶች በመደርደር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ይቀራሉ። ሚስስ ሮዜንታል ስንኳ ከቴዎድሮስ አካባቢ ላለመለየት ጋፋት መቀመጡን ባልጠላችውም ነበር። ግን ከሌሎቹ ሚስዮናውያን መለየት አትችልም። በብዙ ጉዳዮች ላይ ቢመካከሩም ኃላፊ ስለሆነ፤ በመጨረሻ ለእስተርን ውሳኔ መገዛት አለባቸው። ቴዎድሮስ፤ በእስተርን ፈቃደኛ አለመሆን ግልጽ ቁጣ ባያሳዩም፤ ቅያሜታቸውን በሆዳቸው ችለው፤ ‹እናንተ ተመንፈሳዊ ሥራችን አናወጣም፤ ታልችሁ፤ እንግዲያው ወደኔ ሥራም ቅንጣት አትግቡብኝ› ብለው ስብከታቸውም ሆነ የማስተማር እንቅስቃሴያቸው፤ ከተፈቀደላቸው የፈሳሾች መንደር ክልል እንዳይወጣ አዘዙ። እስተርን የፖለቲካና የሌላው ሥራው መልክ በዚህ እንዳይወጣ ሲጠብበት፤ የሃይማኖት ሥራውም እየሰለቸው ሒደ መሰል፤ ትእዛዝ የሮዜንታል ቤተሰብ ወደ ባሕር ጠረፍ እንዲመለሱ በመልእክተኛ አማካይነት ፈቃድና ስንብት ጠየቀ። ቴዎድሮስ፤ ‹መሔዱን ሒዱ፤ አልከክላችሁም። ግን ብዙ ጊዜ አብረን ኑረናል። ተቻላችሁ ደብረ ታቦር መጥታችሁ ተሰናበቱኝ፤ ታለዚያ ጎንደር እስከመጣ ቆዩኝ!› የሚል መልስ ላኩባቸው። ትእዛዝም ባይሆን፤ እነ እስተርን ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ከቴዎድሮስ ፊት ቀርበው

መሰናበት እንዳለባቸው ግልጽ ነበር። ወዲያው ቀጥሎ ተዋበች ታመው፤ ቴዎድሮስ ከደብረ ታቦር የመነሣታቸው፤ ከዚያም የተዋበች መሞት ወሬ በተከታታይ ደረሰ።

ሚስስ ሮዜንታል፤ የተለመደው ምክንያት በማይፈልግ ምኞቷ፤ የተዋበች ሞት የእርሷን ዕድል የሚነካ መስሎ ተሰማት። በሕይወት ብቻ ሳይሆን በሞትም ቴዎድሮስ የተዋበችን አስከሬን ይዘው አገር ላገር እንዴት እንደ ተንከራተቱ፤ በሠቀቀን እንዴት እንደ ተኮማተሩ፤ ሚስስ ሮዜንታል ታሪኩን ስትሰማ፤ ቅናት አይሉት ኀዘን የራስዋንም መንፈስ የሚያኮማትር ብስጭት ለቀቀባት። ‹እንዳይመነኩስ ገና ሙሉ ሰው ናቸው። ዛዲያ የተዋበችን ፍቅር የምትተካው ሴት ማን ትሆን?› እያለች ሮዜንታል ከሐሳብዋ ጋር ያለ ማቋረጥ ትወያያለች። አውጥታ አውርዳ፤ ከራስዋ ጋር ፈገግ ትላለች።

የዓላማቸው መደናቀፍ ነው፤ የቴዎድሮስን ቁጣ ማጉላት የጀመረው? ወይንስ ቁጣቸው ነው ዓላማቸውን የማደናቀፍ የያዘው? ታንጉት ቅደም ተከተሉን ልትለየው አልቻለችም። ብቻ ከተዋብች ሞት በኋላ ሁለቱም የቴዎድሮስ ዕጣ ፈንታ ሆኑ። ሽፍታው በየሥፍራው ይነሣባቸዋል። ቁጣቸው በየአቅጣጫው ቅጣቱን ያሰራጫል። ዱሮም ቁጣቸው እንደሚያስፈራ ታውቃለች። አሁን ግን በተከታታይ የሚያሸማቅቅ የሚያኮማትር እየሆነ ሔደባት። በተለይ ከደባርቅ ጦርነት በኋላ ጠቅላላው የአካባቢያቸው ሁናቴ የሚዘገንን መልክ ያዘባት።

ቴዎድሮስ፤ ‹ብታርፊ አይሻልም አንጓች?› ቢሏት፤ ገብርዬ ‹ምን ትሠሪያለሽ› ሲል ቢመክራት ‹አልቀርም› ብላ ያስቸገረችው ራስዋ ነበረች። በስንት መከራ ልታገኝ የነበረውን ልጅ እስከ ማጣት ድረስ ጋረድና አክሊሉ የፈጸሙባቸውን ተንኮል፤ በወይኒ የደረሰውን እልቂት በማስታወስ፤ መጨረሻቸውን ለማየት ከፍተኛ ፍላጎት አደረባት። እንዲያውም፤ የዘመቻው ነገር ሲነሣ፤ ራሷ ፊት ለፊት የምትፋለመው ይመስል፤ መላ ሰውነቷ አንዳች ዐይነት ትኩሳት ይሰማታል። ሆኖ ካየችው በኋላ፤ ምነው ባልመጣሁ ልትል።

ቴዎድሮስ፤ ወትሮም የዘመቻ ጉዞ ሲጀምሩ ማዝገም አይወዱም ነበር። የአሁኑ ጉዞ ግን፤ እንደ ሽምጥ ግልቢያ የሚቆጠር ነበር። እንደተለመደው ፀሐይ በርታ ሲል ጥላ ፈልጎ ማረፍ ፀሐይ ዘቅዘቅ ስትል መስፈርና እህል ማበሳሰል፤ ጧት እንደዚሁ እህል ቀማምሶ ጤዛ እስኪረግፍ መጠባበቅ አልነበረም። ሌሊቱ ገና ለዐይን ከፌት ሲል ተነሥቶ ቀኑን ሙሉ ሱዳዙ መዋል ነው። ሠራዊቱ የያዘውን ደረቃ ደረቅ ስንቅ በመንገድ ላይ እየቀማመሰ፤ ከየደረሰበት ወንዝና ምንጭ ውሃ እየተጎነጨ ቀኑን ሙሉ ሲኬድ ተውሎ፤ ጨለማው ለዐይን ጥቅጥቅ አድርጎ ሲይዝ የግድ ሠፈር ይደረጋል። ንጋቱ ላይ እንደገና ተነሡ፤ ተንቀሳቀሱ ይባላል። በዚህ ዐይነት ከደብረ

ታቦር በተነሡ ሳምንት ሳይሞላ ጋረድ ነጋሪት እያስመታ ከሚገኝበት ወገራ ደርሱ። ጉዞው እጅግ አድካሚኢ ቢሆንም፤ በጋረድ መሸፈት ሠራዊቱ ሙሉ በሙሉ ተናድዶ ስለነበር፤ የከዳ ቀርቶ ቅሬታ ያሰማ አልነበረም። በዚህ ድካሙ ላይ ባላገር እየዘረፈ ዐርፎ ሲቀለብ ከከረመው የጋረድ ሠራዊት ጋር እንደ ደረሰ ለመፋጨት ያሰፈሰፈ ነበር።

ቴዎድሮስ፤ ለጦር አለቆቻቸው አንዳችሁ ትበቁታላችሁ ሲል እንዳቃለሉት ሳይሆን፤ ወገራ ላይ የጠበቃቸው ቀላል ውጊያ አልነበረውም። ቴዎድሮስ፤ ገና ልጅ ካሣ ሲባሉ ሳለ፤ ጥቂት ወታደር አሰልፈው እንደ ሣር ቅጠል የተትረፈረፈውን የእቴጌ መነንና የራስ ዓሊን ሠራዊት ድል ነሥተዋል። እብሪተኛውን ደጃች ውቤን ማርከው፤ አገሩንና ሰዉን ፈጽሞ ሳያውቁት ሰዉም፤ ምድሩም እጅግ አስቸጋሪ የሆነውን ሸዋን አስገብሬው ተመልሰዋል። ጋረድ ደባርቅ ላይ ያደረገው ውጊያ በአሠቃቂነቱ፤ በእልቂቱ ከእነዚህ ቢበልጥ እንጂ የሚያንስ አልነበረም። የውጊያው ጊዜ ምናልባት ከሁለት ሦስት ሰዓት ያልበለጠ በጣም አጭር ነበር።

በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ግን፤ ከእቴጌ መነንና ከዳጅች ውቤ ዘመቻዎች ድምር የሚበልጥ ሰው አለቀ።

መጀመሪያ እንደተስማሙት ሳይሆን፤ አገው ንጉሤ፤ ብቻውን ትቶት ወደ ተከዜ ቢወርድም ጋረድ የመጨረሻውን ጀግንነትና ቆራጥነት አሳይቶ ለማለፍ ቆርጦ የተነሳ ይመስል፤ ደኅና ቦታ ይዞ በማዋጋትና ጦሩን በመምራት ፈንታ፤ በነጭ ፈርሱ ላይ ተቀምጦ ወደ ቴዎድሮስ ሠፈር እንደ ጦር እየተወረወሩ አንገት በጥሶ፤ ደረት በስቶ ይመለሳል። ከጦሩ ተቀላቅሎ፤ ትጥቁን አስተካክሎ፤ እንደገና ወኔውን ደግሶ፤ ፈርሱን ኮልኩሎ አሁንም ይወረውራል። በጆሮ ግንዱ እያፏጨ የሚያልፈውን ጦር፤ የሚንጣጣውን የጥይት ጩኸት፤ በዙሪያው የሚያጸባርቀውን የሰይፍ ስለት ከምንም የቆጠረው አይመስልም። እንዲያውም በዘፈንና በሆታ መካከል እንደሚጨፍር፤ ወይም የተፈጥሮን ውበት እደሚያደንቅ ዐይነት ሆነ። ብዙው ወታደሩም የእሱን ምሳሌ እያየ፤ አንዱ ከሌላው እንዴት አንሼ እያለ፤ አጅቦ እየተከተለው ይጨፋጨፍ ገባ። እየቆየ ጩኸቱ፤ እንቅስቃሴው፤ ደሙ፤ ሞቱ፤ ፍጅቱ እንደ ስካር በብዙው ራስ ላይ የወጣ መሰለ። ጋረድ እንደ ወገሼ አውሬ በሬ ሆኖ፤ የወገራ ሜዳ የበረት ያህል ጠበበው።

የጋረድ ሠፈር ከጀርባው የተደገፈው የስሜን ተራራ አዳፋች ስለሆነ፤ የሚያጠቃው ቁልቁል እየተወረወረ ከመሆኑ ሌላ፤ የቴዎድሮስ ሠፈር ከታች ተዘርግቶ ይታየዋል። ቴዎድሮስ ደግሞ፤ ከአምባ ጊዮርጊስና ደዳባት እንደ ዘለቁ በዚያ የወገራ ሜዳ ላይ ድንኳናቸውን በትንሽ ጉብታ ላይ አስተክለው በቦታ

አቀማመጥ ምክንያት ጋረድን ቁልቁል እንደ ማየት አሻቅበው እየተመለከቱት ጦርነቱን ይመራሉ። ‹አንቺ ልጅ እስቲ ወደ ኋላ ሁኚ› እያሉ ቴዎድሮስ ቢጎተጉቷትም፤ ታንጉት፤ ከሠፈር ጠባቂው ቀድማ ከአጠገባቸው ቁማ ታያለች። የጋረድ አዲስ ጀግንነት እንዳስገረማቸው ተፊታቸው ያስታውቃል። በአድናቆት ይሁን በንዴት ራሳቸውን ይነቀንቃሉ። እርሷንም ደንቋታል። በዚያ መዓት መካከል ግን ገብርዬንም ትፈልጋለች።

አለቃውን ተከትሎ እንደ ናዳ እየፈሰሰ የሚወርደው የጋረድ ወታደር፤ ከቴዎድሮስ ሠፈር ሲደርስ እንደ ቅጠል ይረፈፈፋል። የተረፈው ተመልሶ ጥቂት ፋታ ካገኘ በኋላ አሁንም እንደገና ወደታች ይጎርፋል። ሊታጨድ፤ ሊመተር። «አባቱ ባዩለት ይህንንስ» ሲሉ ቴዎድሮስ የተናገሩት ከራሳቸው ጋር ቢሆንም ድምፃቸው ከታንጉት ጆሮ ደረሰ። መሬት ቁና ሆና፤ ሕዝበ - አዳር እርስ በርሱ ተባልቶ የሚጫረስ እስኪመስል ሲፋጅ፤ የጣዕር ድምፅ፤ የፈረስ ኮቴ፤ የጎራዴ ፍጭት፤ «ስለ ነፍስ ውሃ!» የሚል የቁስለኛ ጩኸት አየሩን ሲሞላው፤ በቴዎድሮስ ዘመቻ ለመጀመሪያ ጊዜ ድሉ ከየት በኩል እንደሚውል የሚያጠራጥር መስሎ ታየ። እርግጥ በአብዛኛው የሚረግፈው የማይመለስ ዐይነት ነበር። ቴዎድሮስ በመገረም አስተአሉና የውጊያውን ስልት ለመቀየር በእጃቸው ዘርግተው ወደፊት ነጠቅ አሉ። በዚህ ጊዜ ነበር ጋረድ ሌላውን ተዋጊ ጥሶ ጦሩን እየሰበቀ ወደ ቴዎድሮስ የገሠገሠው። ቴዎድሮስ ከታጠቅ ፈረሳቸው ላይ እንደ ተቀመጡ፤ ከፊል ሠራዊታቸው በጎን በኩል ታጥፎ የጋረድን ጦር ከጀርባ ችምር እንዲያጠቃ እያመለከቱ ያደፋፈሩ ስለነበር፤ የጋረድን አመጣጥ በውል አልተከታተሉትም ነበር። አንድ ሠላሳ ክንድ ከሚሆን ቅርበት ላይ ሲደርሱ፤ ጋረድ ልጓምሙን እንደ መልቀቅ አድርጎ በቀኝ እጁ ሽጉጥ ሲያነጣጥርባቸው፤ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ፈረሱን እመር አድርጎ ከቴዎድሮስ ፊት ተደቅኖ በሽጉጥ ቀለበው። ጋረድ ከፈረሱ ላይ ክንብል ብሎ ሲወድቅ ከኋላው ይከተለው የነበረው በእናቱ በኩል የአጎቱ ልጅ ዐልፎ መጥቶ ጦሩን ሲለጋ፤ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ፤ «እ! እ!» ብሎ ሲጮህና ቴዎድሮስ ዘወር ሲሉ አንድ ሆነ። በደረቱ የገባ ጦር በጀርባው ዘልቆ ነበር። ቴዎድሮስ ወደ ቁስለኛው በማተኮር ጊዜ አላጠፉም። የጋረድ አጎት ልጅ ፈረሱን አዞሮ ከመመለሱ በፊት በአንድ ጥይት አጉነው ጣሉት። ከዚህ በኋላ የውጊያው መልክ ባንዳፍታ ተለወጠ።

የጋረድን መውደቅ ሲመለከት፤ ሠራዊቱ ባንድ ጊዜ ተበታትኖ ሸሸት ጀመረ። ጋረድን ከወደቀበት ማንሣት ቀርቶ መሞት አለመሞቱን ስንኳ ለማወቅ የቃጣ አልነበረም።

አሁን የውጊያው ውጤት እንደ ለየለት ታንጉት ዐውቃ፤ እየሮጠች ወደፊት ስትሔድ፤ ቴዎድሮስ፤ ከደረቱ ላይ ጦሩ እንደ ተሰካ ሊቀ መኳስ ዮሐንስን ተሸክመውት ሲመጡ፤ መኻል መንገድ ላይ ተገናኙ። «ይኸውልሽ!» አሉ ቀስ ብለው ከጭናቸው ላይ አስደግፈውት እየተቀመጡ። «እስቲ ውሃ!» አሉ ወዲያውኑ።

መሰባሰብ ጀምረው ከነበሩት መካከል አንዱ እርኮት ሰጣቸውና ሲያስጎነጩት ሕቅታው አለፈች።

«እዛዲያስ? እንግዲህ ማን ቀረኝ?» ሲሉ ወደ ታንጉት እየተመለከቱ ጠየቁ። ‹አንቺ ብቻ ነሽ› ያሉ መስሎ ተሰማት። አለሁልህ እንደ ማለትም ቃጣት። ወዲያው ግን፤ ልውጥውጥ ያለው መልካቸው ከቆመችበት ድርቅ አደረጋት።

«አይማረኝ፤ አንዱንም አትማሩልኝ?» ሲሉ በጩኸት አዘዙ። በብዙ ውጊያ ቴዎድሮስን ያየችው ታንጉት ጆሮዋን ማመን አቃታት።

ከዚህ በኋላ የሆነው እርድ እንጂ ውጊያ አልነበረም። የሰውን አንገት እንደ ቅጠል መጨፍጨፍ ነበር። ብርቱ ሩዋጭ፤ ወይም ጋላቢ ሆኖ የሚያመልጥ ካልሆነ በስተቀር ጥይት የሚያባክን አልነበረም። በኋላ እየደረሱ በሰይፍ መቀንጠስ፤ በጦር መሰቅሰቅ ብቻ ነው። የመላው ሠራዊቱ ወኔ ከጋረድ ጋር አብሮ የተቀጨ ይመስል፤ ቁሞ ለመከላከል መክቶ ለመዳን ወይም እየተጋደለ ለመውደቅ የሚሞክር አልነበረም። አውሬ እንደ መጣበት ከብት ደንብሮ ንብ እንደ ገባበት በረት ተተራምሶ፤ ጢስ እንዳፈነው ቀፎ ታምሶ፤ አብዛኛው አንገቱን አቀርቅሮ በነፍሴ አውጭኝ ወደ አልተወሰነ አግጣጫ ሲፈተለክ፤ የቀረው ደግሞ አንድ ዐይነት ምትሐት እንዳፈዘዘው፤ ወይም መንፍሱን እንደ ሰለበው እየተንበረከከ ምሕረት ይለምናል። ይማጠናል። ግን ማንም አልተማረም። ተንበርክኮ እጁን እንደ ዘርጋ የተሰየፈው ቁጥሩ አይታወቅም። አብዛኛው እግረኛ ያለቀው በሚሸሸው ፈረሰኛ እየተረገጠ ጭምር ነበር። ከቴዎድሮስ ማምለጥ ለሚሞክረው የጋረድ ወታደር፤ ሣር ቅጠሉ፤ ድንጋይ አፈሩ ቁስለኛው፤ ሬሳው ሁሉ አንድ ዐይነት ነበር፤ የተለየ አስተያየት የማይሰጠው። መተሳሰብና መተዛዘን ከወኔ ጋር አብሮ ጠፍቷል። በኋላም በእርካብ የተጎተተ፤ የተሰበረ ብዙ ሬሣና የፈረስ ጥንብ ከውልክፈት ገደል ሥር ተገኝቷል።

ፀሐይ ወደ ምዕራብ ማዘንበል ስትጀምር፤ የፍልሚያውም፤ የቅጣቱም የሽሽቱም ጉዳይ አበቃለት። ዐልፎ ዐልፎ ከሚሰማ የጣዕር ድምፅ በስተቀር የጉልቆ መሳፍርት ሕይወት የታመሰባት፤ የተቆላባት የደባርቅ መሬት ከምድኝ እንድ ወረደ ምታድ ረጋ፤ ቀዝቀዝ አለች።

ከአሸናፊው ወገን በጣም የደከመው ሰይፉን እየጠራረገ ወደ አፎቱ በመመለስ በየሥፍራው ዐረፍ ሲል ትንሽ ዐቅም የተረፈው፤ ከወገኑ በሕይወት የሚገኘውን ለማንሣት ፍተሻውን ቀጠለ።

«እኔ እንደሱ አይደለሁም። የአባቱ አጽምም ይወቅሰኛል» ሲሉ ቴዎድሮስ የጋረድን የአጎቱ ልጅ ሬሣ ተነሥቶ ከሊቀ መኳስ ዮሐንስ ጋር ደረስጌ እንዲቀበር አዘዙ። ቃሬዛው ሲዘጋጅ ገብርዬ ሌላ እሬሣ ታቅፎ መጣ። አያያዙ ሕፃን እሹሩሩ እንደሚል፤ አረማመዱ የእንቅልፍ ልብ ዐይነት ነበር። ቀስ አለና ዕቅፉን ከቴዎድሮስ አጠገብ ከመሬት ላይ አጋደመው።

«እሷም ተቀሰፈች» አለ በሰመመን አኳኋን።

«ማናት?» ሲሉ ጠየቁት ቴዎድሮስ።

«ያይኔ አበባ ናት» አለ ቴዎድሮስ አስቀድመው እንደማያውቋት ሁሉ። በዚህ ጊዜ ታንጉት እሪታዋን ለቀቀችው። «ወይኒ ያረፍንበት ባላገር ልጅ ነበረች» ሲል አከለበት።

ገብርዬ፤ ያይኔ አባባን ሬሣ ያገኘው በድንገት ነበር። ከጦር አለቆቹ የወደቀ ሲፈልግ የጋረድ ሠራዊት ወደ ኋላ ሲሸሽ፤ ጥሶት ካለፈበት የራሱ የደጀን ሠፈር አካባቢ የብዙ ሴቶች ሬሣ አገኘ። አብዛኞቹ በፈረስ ኮቴ ተረግጠው የሞቱ ነበሩ። በኀዘንና በሰቀቀን ተውጦ፤ ሳይታወቀው ማንን እንደሚፈልግ ሳያውቀው የሴቶቹን ሬሣ እያገላበጠ ይመለከት ገባ። በግንባርዋ የተደፋች አንዲት ጋሜ ልጅ ገልበጥ አድርጎ ሲያይ መብረቅ የመታው ያህል ሰውነቱን ነዘረው። ያይኔ አበባ ነበረች። ግን አላለቀሰም ዕንባው ደርቆ ነበር።

ጥቂት ቆይቶ ብርቱ ነፋስ የሚያወናጭፈው ዝናም ጣለ። እንደ አረንዛ በመስኩ ላይ ከተረፈረፈው ሕይወት የሌለው ገላ ላይ መርጋትና መድረቅ የጀመረው ደም፤ በዝናም ውሃ እየተበጠበጠ ቀጥኖ ከወገራ አፈር ጋር ተቀላቀለ።

ከላይ ጆቢራዎችና የስሜን ንስር አሞሮች ለድግስ እየተሽቀዳደሙ ማንዣበብ መሰባሰብ ጀመሩ።

ሠራዊቱ ጠለላ ፍለጋ ሲበታተን፤ ቴዎድሮስ ዝናሙ ሳይሰማቸ፤ መዝነሙ ሳይታወቃቸው፤ ከአንድ ቋጥኝ ላይ እንደ ተቀመጡ ዝም ብለው ቆዩ። በአጠገባቸው የቀሩት ጦር አበጋዞቻቸው ጥቂት ከጠበቋቸው በኋላ «ጥግ እንያዝ እንጂ አባ ታጠቅ?» አላቸ ገብርዬ። የሌሎቹ ጦር አለቆች ከተቀበሩበት መካከል ያይኔ አበባን

ቀብረው ተመልሰው፤ አሁን ታንጉት ከመንሰቅሰቅዋ በረድ ብሎላት በትካዜ ከወደ ዳር ተቀምጣለች። ንግግራቸው ይሰማታል።

ቴዎድሮስ ሐደውበት የነበርወ የመንፈስን ብቸኝነት እንደ ሰመመን መለስ አሉና፤ በፊታቸው ላይ የሚወርደውን የዝናም ውሃ በጨርቃቸው እየጠረጉ ዙሪያቸውን ተመለከቱ። «ለመሆኑ ያ - ሽባ ደብተራ አክሊሉ የምትሉት የት አባቱ ደረሰ?» ሲሉ ራሳቸውንም ጠየቁ።

መልስ የሰጠ አልነበረም፤ የሚያውቅም አልነበረምና።

ፊታቸውን ወደ ኋላ መልሰው አምባ ጊዮርጊስ ላይ ሠፈር ተደረገ። ታንጉት፤ ዱሮ በዚህ ቦታ ከፈጸመችውና በከንቱ ከተቀጨ የከንቱ ተስፋ ትዝታዋ ጋር፤ ያይኔ አበባ መቀጠፍ ተደምሮበት ከባድ ሰቀቀን ተጭኖዋት ነበር። ገብርዬ፤ ተገንዝቦ አልጠየቃትም። ቴዎድሮስ ግን፤ ራት ስታቀርብላቸው ከተዋበች በኋላ ለጊዘው ሌላ ቀራቢ የላቸውምና - «አንጓች ምነው ዐይንሽ ከፋብኝ?» ሲሉ ጠየቋት።

«ኧረ! ምነው እንዲህ ትላለህ አባ ታጠቅ?» አለች ታንጉት የምትመልሰው ጠፍቷት።

«ይህን ዕልቂት ስታዪ አንቺማ ምን ይፈረድብሻል? ግን አትፍረጂብኝ። ዓላማዬ ሲበላሽ፤ ሀገሬ እንደገና ተመልሳ ስትጠፋ፤ ያው አንድ ታልሆነች መጥፋቷ አይደለ? ዝም ብለህ ተመልከት ነው የምትይኝ? ይህንን አላደርገውም - ፈጽሞ?» አሉ በቁርጠኝነት። ታንጉት ፊታቸውን ስትመለከት፤ ቀድሞ ከምታውቀው ቁጣ ሌላ አንዳች ዐይነት ልዩ ፍርሃት አሳደረባት።

የጦር አበጋዞቻቸውም፤ ከተፈጥሮም ባይሆን በሁናቴ መለወጥ ምክንያት በቴዎድሮስ ባሕርይ ላይ የተከሠተውን ለውጥ ተገንዝበውት ነበር። ታንጉትን ይዘው ሌላ ምሽት ስለሚያገቡበት መንገድ መመካከር ጀመሩ። ታንጉት በመጀመሪያ አልተቀበለችውም። ወይም አላስደሰታትም። የምትሰጠው ምክንያት እንደ ተዋበች፤ ተዋበችን የሚተካላት ስለማይገኝ አገባም አላገባም ዋጋ የለውም የሚል ነው። ብቻዋን ሆና ከሐሳብዋ ጋር ስትወያይ ግን፤ ተኔ ሌላ እንዲቀርበው ስለማልፈልግ ይሆን? የሚል ጥርጣሬ ያድርባታል። አንዳች ዐይነት ቅናት እንደሚሰማት ይታወቃታል።

ከገብርዬ ጀምሮ ቅርብ የጦር አበጋዞቻቸው ግን፤ ሌላው ሁሉ ቢቀር የሚረቱበት አንድ ግልጽ ምክንያት ነበራቸው። ተዋበች በጠና ከታመሙና ከሞቱ እንሆ ሁለት ዓመት ዐልፏል። በዚህ ጊዜ ሁሉ ከሴት ጋር አልተገናኙም። ቁርባናቸውን ለተዋበች ያላቸውን ፍቅርና እምነት ያፈረሱ ስለሚመስላቸው

ወደፊትም እንደዚሁ ሊቀጥሉ ይችላሉ። ዛዲያ ቢበሳጩ፤ ቁጣ - ቁጣ ቢላቸው ምን ይፈረድባቸዋል? ሰው ናቸው፤ ወንድ ናቸው። ሌላ ምሽት እንዲያገቡ ከተደረገ ግን ከተዋበች ጋር የነበራቸው፤ የስሜትም ሆነ የሃይማኖት ቋጠሮ ይፈታል። ከዚያ በኋላ የሚሆነውን ማን ያውቃል? ትልልቆቹ የጦር አበጋዞች ከቴዎድሮስ ተደብቀው፤ ታንጉትን እንደ እኩያቸው አድርገው ስለዚህ ጉዳይ ሲያማክሩዋት፤ ስለ አባ ታጠቅ ስለኔ የሚያውቁት ነገር አለ የሚል ጥርጣሬ ብዙ ጊዜ ተሰምቷት ነእብር። ግን፤ ቴዎድሮስ ሳልሳደጉዋት - ከተዋበች ቀጥሎም ሌላ የሚቀርባቸው እንደሌለ አድርገው በመቁጠር ብቻ መሆኑን እያደር ተገነዘበች.......

......ጉዳዩ ቀላል አልነበረም። መጀመሪያ፤ ቴዎድሮስ አሁን ባሉበት ሁናቴ የምትስማማቸውን ፈልገው አፈላልገው ማግኘት ነበረባቸው። ቀጥሎ ደግሞ ቴዎድሮስን እሺ ማሰኘት ነበረባቸው። በሴት ወገን እንደዚሁ ያላነሰ ችግር ተከተለ።

ለቴዎድሮስ የተመረጠችው ምሽት፤ በያገሩ ያለው ዲቃላ ሳይቆጠር፤ በቤት የተወለደችውና በይፋ የታወቀችው፤ ጥሩ ወርቅ የምትባለው የደጃች ውቤ የመጨረሻ ልጅ ነበረች። ቤተ ዘመድ ቢስማማም፤ ጥሩ ወርቅ፤ አባቷ በአባ ታጠቅ ድል ሆነው ከተጋቡ ጊዜ አንሥቶ ደረስጌ ማርያም መቃብር ቤት ገብታ እመነኩሳለሁ ብላ ቆይታለች። የሴት ጉዳይ በሴት ይሻላል ተብሎ ታንጉት ከራስ እንግዳ ጋር ከደብረ ታቦር ደረስጌ ማርያም ሔዳ እንድትለምናት ተደረገ።

ጥሩ ወርቅ፤ ስለ ትዳር ቀርቶ ስለ ወንድና ስለ ሴት ሩካቤ ምኑንም የማታውቅ ገና ድንግል ነበረች። አባቷ፤ በቴዎድሮስ ድል ሆነው ሲጋዙ መቃብር ቤት ገብታ ስለ ተቀመጠች። በወሬ ስንኳ የምታውቅበት ምንም መንገድ አልነበረም። ሕይወቷን በዚሁ ዐይነት ለመጨረስ እንጂ ከደረስጌ ማርያም መቃብር ቤት የመውጣት ሐሳብም ፍላጎትም የላትም። ታንጉት እየተመላለሰች ስታወያያት ባንድ በኩል፤ በቴዎድሮስ ምሽትነት በማግባባቷ እንድ ቅናት ቢጤ፤ በጥሩ ወርቅ የዋህነት ደግሞ ለወደፊቱ ባልና ሚስቶች አዘኔታ አደረባት። ቴዎድሮስ ምናልባት የአካል እንጂ የመንፈስ እርካታ እንደማያገኙባት ተሰምቷት ነበር።

ምጥን ባለ ሥነ ሥርዓት የጋብቻ ተፈጸመ። ከዚህ ጋብቻ አንድ ጥሩ ውጤት ብቻ ተገኘ። አባ ታጠቅ «ዓለማየሁ» ብለው ስም ያወጡለትን ወንድ ልጅ ጥሩ ወርቅ በዓመቱ ወለደች። ከዚህ በተረፈ ግን፤ ጥሩ ወርቅ ከዕድሜ አለመብሰል ይሁን፤ ከራስዋ ሥነ ልቦናዊ ሁኔታ፤ ቴዎድሮስን ማሰሰት ማዝናናትና በቁጣም ሆነ በብስጭት የሚኮረኩር ስሜቱን ማርገብ ቀርቶ ጨርሶ ሊጣጣሙ የማይችሉ መሆናቸው በግልጽ እያስታወቀ ሔደ። ቴዎድሮስ ቢቸግራቸው ታንጉትን፤ ‹ትንሽማ እንደሆነ እባክሽ ምከሪያት። በዚህም በዚያም፤ ዓለማዬን የሚያደናቅፍብኝ፤

የሽፍታና የተንኮለኛ ነገር ሳያንሰኝ፤ እርሷ ደግሞ ስወጣ ስገባ ፊቷን ኮሶ እያስመሰለች፤ ልቤን የባሰ የምታጨልምብኝ ለምንድ ነው?› እስከማለት ደርሰው ነበር።

ታንጉት፤ ፈራ ተባ እያለች ነገሩን አነሣችለት። ያገኘችው መልስ እንደ ልጓም ባንድ ጊዜ ገታት። «እና ለቴዎድሮስ ጥሩ ሽምት አልሆነላትም ማለት ነው? ወንድ ልጅ ወለድኩለት፤ ሌላ ምን ፈለገ? የምራት ግሣጺ መሆኑ ነው ነው መስለኝ» ስትል ጥሩ ወርቅ በትዝብት ትኩር ብላ ተመለከተቻት። «ለመሆኑ ቴዎድሮስ ምንሽ ነ?» የጥሩ ወርቅ አጠያየቅ አንድ ዐይነት የጥርጣሬ አሽሙር ነበረ ነበረበት።

ታንጉት የምትመሰው አልነበራትም። በፊትም ቢሆን እስከዚህ አልተቀራረቡም ነበር። ከዚህ ጊዜ በኋላ ደግሞ ሕይወት፤ በአንድ አካባቢ እየበተታ መሔዱን ቀጠለ።

«እና ምን ይመስልሃል?» ስልት ታንጉት ገብርዬን ጠየቀችው። መልስ የምታገኝበት ይመስል ማንበብ የማትችለውን ደብዳቤ እያገላበጠች።

«እና ምናውቄ?» በማለት እንደዋዛ መለሰላት። ሐሳቡ በሌላ ጉዳይ ላይ ነበር። ቴዎድሮስን የተለያቸው ከፍተኛ ብስጭት ላይ እንዳሉ ነበር። በሸዋ፤ በወሎ በጎጃም፤ በትግሬ፤ ሽፍታ መነሳቱ ባያቋርጥም ከቆንስል ፐላውዴን፤ ከሊቀ እምኋስ ዮሐንስና ከተዋበች ሞት ወዲህ ብዙ ጊዜ ብቸኝነት ቢሰማቸውም፣ ጥሩ ወርቅ በማጽናናት ፈንታ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ብትሆንባቸውም፤ በተንሱበት ዓላማ ጨርሶ ተስፋ አልቆረጡም ነበር። ዐልፎ ዐልፎ ተስፋ የሚያሳድሩ ጭላንጭሎች ይታዩዋቸዋል። የየራሳቸውን ጉቶ መንግሥት ለመመሥረት ኢትዮጵያን የሚቦጫጭቋት መሳፍንትና መኳንንት ይዞት ጨርሶ ባይደመሰም፤ አንዳንዶቹ እንደ ገና ለመንቀሳቀስ ቢሞክሩም፤ በኢትዮጵያ ላይ አንድ መንግሥት ተቋቁሞ፤ ሕዝቡም አንድ ሀገር፣ አንድ መንግሥት እንዳለው ተቀብሏል። ከብዙ ክፍለ ዘመናት ቸልታና በስንፍና በኋላ፤ በሕዝቡ ዘንድ በመጠኑም ቢሆን የሥራ መንፈስ መቀስቀስ ጀምሯል። ቴዎድሮስን ዐልፎ ዐልፎ ፈገግ ከሚያሰኙዋቸው ነገሮ አንዱ፤ ይህንን የሚመለከት በጊዜው የሚሰማው የእረኛ ዘፈን ነበር።

«አሆሆሌሌ፣ አህያ መጣች ተጭና ቋንጣ፣

እጅ ንሡለት ገበሬ መጣ፣

«አሆሆሌሌ፣ አህያ መጣች ተጭና ዶሮ፣

የነጋዴው ነው ጊዜው ዘንድሮ።» ቴዎድሮስ ይህንን ዘፈን ሲሰሙ፣ በትካዜ ሐሳብ ላይ ቆየተውም ቢሆን ፊታቸውን ፈገግታ ለበስ ያደርገዋል። በጋፋት የተቋቋመው ማቅለጫም ቢሆን ዐፈሩን ወደ ብረት መለወጥ ጀምሮ ነበር። ኢትዮጵያን የሚተናኮልን እየቀጡ የሚመልሱበት የጦር መሣሪያ የሚያገኙበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። ከእንግሊዝ መንግሥት የጠየቁት ዕርዳታ ከመጣላቸው ደግሞ ብዙ ሐሳባቸው ሊሳካ ይችላል። ለዚሁም በጦር መሣሪያ ሥራ የሚዋረዱዋቸው፤ ወገናቸውን በልዩ ልዩ የጅ ጥበብ የሚያሠለጥኑላቸው ባለሙያዎች እንዲልኩላቸው ለንግሥት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ልከው መልሱን በመጠባበቅ ላይ ነበሩ። ደብዳቤውን ይዞ የሔደው፤ በማቹ ፕላውዴን የተተካው አዲሱ የንግሊዝ ቆንስል ካፒቴል ካሚሮን፤ ትዕቢቱና ኩራቱ ብዙ የሚያናድድ ሆኖ ቢያገኙትም፤ የጠየቁት እንደሚፈጸም የተስፋ ቃል ሰጥቷቸዋል። በዕለቱ የደረሰባቸው ወሬ ግን፣ ቆንስል ካሜሮን ወደ እንግሊዝ አገር በመሻገር ፈንታ በሱዳን አገር መቆየቱን የሚያስረዳ ነበር። ደባርቅ፤ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ በሱዳን አገር መቆየቱን የሚያረዳ ነበር። ደባርቅ፤ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ሲሞት፣ ጎንደር አንድ ባሕታዊ ይዞ መሸፈቱን ሲሰሙ እንደሆኑት ሁሉ ፊታቸው ባንድ ጊዜ ተለዋወጠ። ከውስጥ በንዴት ሲሰሙ እንደሆኑት ሁሉ ፊታችው ባንድ ጊዜ ተለዋወጠ። ከውስጥ በንዴት ግሎ በሚወጣው ትንፋሻቸው የተለበለቡ ይመስል፤ የአፍንጫቸው ቅጠሎች እንደ መርገብገብ አሉ። «ተጠላቶቼ ተቱርኮች ጋር ተቀምጧል ነው የምትሉኝ? ምን ሊሠራ? በኔና ባገሬ ላይ እየዶለቱ? እኔ የመይሳው ልጅ! እንተያያለን!» ሲሉ ተወራጩ። በቆዳቸው ተመሳሳይነት የነርሱንም አብረው የጠረጠሩዋቸው ይመስል፣ «የጋፋትን ልጆች» ለማጀመሪያ ጊዜ አመናጭቀው ተናገሩዋቸው። በቴዎድሮስ ቁጣና ብስጭት፤ ታማኝ የጦር አበጋዞቻቸውም ተሳቅቀው ዋሉ።

ገብርዬ፤ ቤት ገብቶ ይህንን ሊነግራት ሲል ነበር፤ ታንጉት የወይዘሮ ደብሬን ደብዳቤ ቀድማ የሰጠችው። ደብዳቤው፣ እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ የበረከት ሰላምታቸውን ከዘረዘረ በኋላ፣ «ዐይንሽን ለማየት በጣም ናፍቄአለሁ። ብርቱ ጉዳይ ነበረኝ። እኔ እንዳልመጣ ጤንነቱ አነሰኝ። ዕድሜዬም አሸንፈኝ። ብትመጭና ዐይንሽን ባየው ደስታውን አልችለውም ነበር። የምትመጭም ተሆነ ተጊዮርጊስ በፊት ብትደርሺ መልካም ነው» የሚል ነበር።

ታንጉት፣ ዐልፎ ዐልፎ እንድ ዋዛ ትዝ ቢሏትም ወይዘሮ ደብሬን በናፍቆት ስሜት ማሰብ፤ ስለ ደኅንነታቸው ማስላሰል ካቆመች ረጅም ጊዜ ዐልፏታል። ሁናቴያቸውን ለማወቅ ለመጨረሻ ጊዜ በጣም ተጨንቃ የነበረው፤ ገብርዬ ከጎንደር ዘመቻ እንደተመለሰ ነበር። ‹ወይዘሮ ደብሬን› አላገኘኻቸውም ማለት ነው?› ብላ ጠይቃው ነበር።

‹የት ብዬ ነው የማገኛቸው ታንጉት? ቤቱ ሁሉ ተቃጥሏል። የእሳቸውም መንደር እንደዚሁ በሙሉ። ያልተቃጠለውም ቢሆን ሰው አልነበረበትም።›

‹አታጠያይቅም ነበር?› አለችው በከባድ ቅሬታ።

‹ማን ተብሎ ነው የሚጠየቀው? እኛን ሲያዩ፣ ወይም የቴዎድሮስ ወታደር መጣ ሲባል፤ ሰዉ ገና ተሩቁ በርግጎ ይጠፋል!› አለ ገብርዬ ትዝታው ሳይቀር አስቅቆት ፊቱን በመጨፍገግ።

‹እና ምን የሆነ ይመስልሃል?› ስትል በድጋሚ ጠየቀችው።

‹ምናባቴን ዐውቄ ብለሽኝ? ደኅና ተሆኑ ወሬያቸውን እንሰማለ። ታለበለዚያም› በማለት ገብርዬ ንግግሩን ሳይጨርስ ተወው።

ሆን ብለው ቢያስጠያይቁም ከዚያ በኋላ ወሬያቸውን አልሰሙም። ከዚያም በቴዎድሮስ ዓላምና ሕይወት ላይ ሐሳብን አጥምደው የማይዙ፤ መንፈስን የሚያውኩ ሌሎች ሁናቴዎች በተከታይ ሲደርሱ የሁለቱ ወዳጅነት ባንድ በኩል ሲደበዝዝ፤ ታንጉት እየረሳቻቸው መሔድ ጀመረች። ባንድ በኩል ገብርዬ፣ በዘመቻ ወዲያ ወዲህ ሲል ወይም ስለ ቴዎድሮስ ዓላማ ከቴዎድሮስ ጋር በሐሳብ ሲወጣ ሲወርድ፣ ከልጅ ጋር ማጫወቱ፣ ከልጅ ጋር ዐይኑ መንከራተቱ ስለቀረ፣ በሌላ በኩል ራስዋ ተስፋ ስለ ቆረጠች፤ እንደወትሮው ስለ ልጅ ማሰቡንም ትታዋለች። የአምባ ጊዮርጊስ አዳር ስንኳ እንደ ሩቅ ዘመን ቅዠት መሰሎ ነው አንዳንድ ጊዜ በሐሳብዋ የሚታያት።

ከስንት ዓመት በኋላ፤ የወይዘሮ ደበሬ ደብዳቤ ድንገት ሲደርሳት ታንጉት እንደ መገረም እንደ መደንገጥም ተሰማት። ገብርዬ መጥቶ እስኪያነብላት ድረስ እንዲያውም መርዶ መስሏት ነበር። አሁን ደግሞ የባሰ ከነከናት። ‹ተጊዮርጊስ በፊት የኔን መድረስ የሚጠይቅ ምን ጉዳይ አጋጠማቸው? የኔ ጉዳይ ነው የርሳቸው? የጊዮርጊስ የሚጠይቅ ምን ጉዳይ ስለ አምባ ጊዮርጊስ ማስታወሳቸው ይሆን? ዛዲያ ስለሱ ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ? እንደገና ሞክሪ ሊሉኝ? አላደርገውም!› ሌላም ብዙ ሐሳብ መጣባት። መሔድ እንዳለበት ግን አላመናታችም።

«ዛዲያ እንግዲህ እንነሣ እንጂ። ይኸው ዛሬ ሥላሴ ናቸው። ብዙም ጊዜ የለን» አለችው ገብርዬን።

«እንዴት አገርን? እኔ እንደሆነ ተአባ ታጠቅ ፊት መራቅ አልችልም። አገሩ እንደሆነ በያለበት እያስቸገረ፣ እሱም በነገሩ ሁሉ እንደዚህ እያዘነ፣ እየተበሳጨ።»

«ዛዲያ ስንት ውለታ የዋሉልኝ ወዳጄ አደራ ብለው ሲልኩብኝ?»

«እንተዚ ብርቱ ጉዳይ ይመስልሻል?»

«ቢሆን ነው እንጂ! እኔ እንደሆነ አልቀርም።»

«እንዳልሽ፣ እንግዲህ መቸስ!» አለ ገብርዬ በቅሬታ ቃና። ታንጉት በሦስተኛው ቀን ወደ ጎንደር ተነሣች።

«ውይ ታንጉት! ሌላ ሰው መስለሽ የለ?» አሉ ወይዘሮ ደብሬ፣ የሰው ኮቴ እንደሰሙ እነ ምንም ወጥተው ከበሩ ላይ አላገላጠው እየሳሟት። በጣም የተለወጡት ግን ራሳቸው ነበሩ። ጸጉራቸው ጨርሶ ጥጥ ሆኗል። በሚሸሸ ሥጋቸውና በተጨማተረ ቆዳቸው ላይ ያ ደጓሳ አጥንታቸው እንደ አሮጌ ካብ ድንጋይ በየመጋጠሚያው አባጣ ጎርባጣ ሆኖ ወጥቷል። ዐይኖቻቸው ልመዋል። ያ ቀጥ ያለ ቁመናቸው ወደ ፊት ማዝመም ሐሩር እንደ ከረመበት ተክል ጠውልጓል። ግቢያቸው ጭምር ይህ የሕይወት ጥውለጋ የሰፈነበት ይመስላል። በተቃጠለው ቤት ምትክ መጠኑ አነስ ያለ ሌላ ቤት ያሠሩ ቢሆንም፤ የሕይወት ሞቅታ የለበትም። ግቢው ጭር ያለ ነው። ታንጉት የደከሙላት፣ ምሥጢሯን የተካፈሉላት ሁሉ መጣባትና ከባድ አዘኔታ ተሰማት። አንዲት ሠራተኛ ከወደ ጓዳ ጠርተው የቀርበውን ከመቅመሷ በፊት ማወቅ እንዳለባት ተሰማት። «ለመሆኑ ሰው ሁሉ የት ሔደ? ዕጣ ነፍዎን የቀሩ ይመስላል እኮ» አለች በማውጣጣት መልክ።

«ኧረ ባባጃሌው! ይልቅስ ጉሮሮሽን እህል አሳልፊበት። ተመንገድ ነው የገባሽው!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ እንጀራና ክክ ወጡን ወደርሷ በኩል እያሰናዱ። ዘያቸውን እንደ ተለመደው፤ ወይም አሁን ለርሷ ሲሉ ቢናገሩትም የወትሮ ቃናው የለም። «ስለ ሰው ምናስጨነቀሽ ልጄ?»

«ታለምክንያት ቤቱ ጭር አይልም። ሰው ሁሉ አይጠፋም። እና ምን ደረሰ?» ኮስተር ብላ ጠየቀች።

«በጎንደር ሁሉ የደረሰው ደረሰ! የጎንደር ሰው! ሳይቸግረው፣ የማያውቅበትን በቴዎድሮስ ላይልሸፍት ብሎ ተነሣ። ይኸው እንደ ሰማሽውና እንደምታውቂው ሆና!» አሉ ወይዘሮ ደብሬ በታከተ አንደበት።

ታንጉት፣ የነገሩ አዝማሚያ ከገባት በኋላ፣ ራስዋው እየጠየቀች ማውጣጣት እንዳለባት ተሰማት። «እሱማ ነው ለሱም ቢሆን.....» እንዴት እንደምትቀጥል ግራ ገባት።

አቡነ ሰላማ ቀጠሉላት። «በልጅ አልታደላችሁም መሰለኝ።»

«አንቺም፤ ገብርዬም ትፈልጉ ነበር?»

«እሱማ ምን ጥያቄ አለው አባቴ! ልጅ መውለድ ማን የማይፈልግ አለና!......» ለማለት ቃጣትና ምንኩስናቸው ታውሷት ራሷን ገታች።

«በብዙ መንገድ ሞክረሽም ነበር መሰለኝ» አሉ፥ የአቡነ ሰላማ አማርኛ በጣም እየተሻሻለ ሔዶ፣ አነጋገራቸው የአሸሙር ቃናም መያዝ ጀምሯል። ነገራቸው ቢገባትም አልመለሰችላቸውም። «አምባ ጊዮርጊስ ወይኒም አንቺማ መቸም መስሎች ነው......» አሁንም አቋርጠው ጠበቋት። ዝም አለች። «እና ምን ይመስልሻል?»

«ምኑ?» አለች ቁርጡን ለማወቅ።

«አንቺ መቸም ፍላጎሽን ነው ያየሽው። ግና፣ በጋብቻ እምነትም በሃይማኖትም፣ በደል መሥራትሽን አታውቂም? ገብርዬስ - ቢያውቅ ምን ይሰማዋል? የሰዉ ይቅርና ተእግዜብሔር ፍርድ ፊትስ እንዴት ትቆሚያለሽ?» አንደበታቸው የመንፈሳዊ ኃይልና ቁጣ ያዘ።

ታንጉት ተኮማትሮ ያነሰ እስኪመስላት ድረስ ሰውነቷ በፍሃት ተሸማቀቀ። ወይዘሮ ደብሬ እንድ ነገሩዋት፣ ጥርጣሬና ሥጋት ነበራት። እንደዚህ፣ አስፈሪና አስደንጋጭ ሁናቴ በግልጽ እንደሚያጋጥማት ግን አልገመተችውም ነበር። እንደ ወይኒው የተጠነሰሰ ሤራ ነው እንዳትል፣ ከአቡነ ሰላማ መንፈሳዊ ተግባርና አባትነት ጋር አልያያዝ አለባት። ቴዎድሮስ፣ በእርሳቸው ላይም ጀሮሽን ጣል አድርጊልኝ ቢሏትም ከሩቅ ከእስክንድርያ ተቀብተው የመጡት፤ የመላው ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባት የሆኑት ግርማ ሞገሳቸው የሚደብደው አቡን፣ በእርሷ ሕይወት ውስጥ ገብተ ተንኮል የሚጠነስሱ መሆናቸው አልመሰላት አለ። በዚህ ላይ ‹የአምባ ጊዮርጊስ ምሥጢር እንዴት ሊደርሳቸው ቻለ?› በወይዘሮ ደብሬ በኩል እንዳልሆነ በጣም እርግጠኛ ናት።

«ለመሆኑ እንዴት እንዴት?» ታንጉት በጥያቄ አቀራረብዋ ስታመናታ፣ አቡነ ሰላማ ሐሳብዋ ገብቷቸው መለሱላት።

«እኛ ሰዎች የምንሠራው ኃጢአት የሚገጥላቸው፣ የበቁ የዘጉ ባሕታውያን አሉ። ተኃጢአታችን እንድንታረም ተመጥፎ ጎዳናችን እንድንመለስ በማለት እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ አድሮ ያሳያቸዋል። የእነሱም ምክር፣ የነሱ ቃል መስማት ነው» አሏት።

አቡነ ሰላማም ሆነ የተባሉት ባሕታውያን ቃል ወይም ትዕዛዝ ምን እንደሚሆን ታንጉት ባታውቅም፣ እምቢ ለማለት እንደማትችልም ተሰማት። እንዳሉት ለሠራሁት ኃጢአት እንዲሆን የታዘዘልኝ እንደሆነስ የሚለው ሃይማኖታዊ

አስተሳሰብ ባንድ በኩል እንድ ወጥመድ ያዛት። በሌላው በኩል ደግሞ፣ የተጠየቀችውን ባትፈጽም፣ በሥጋዊው ረገድ ሊደርስ የሚችለው ሁናቴ ታያት። ተዋበች ቢኖሩ ኖሮ፤ ለተዋበች አማከራ፣ ተዋብች በተለመደ አቀራረባቸው ቴዎድሮስን አስረድተውና አሳምነው፣ ቴዎድሮስ በበኩላቸው ገብርዬን አግባብተው ጉዳዩ ምናልባት የተሻለ መልክ በያዘ ነበር። አሁን ቴዎድሮስ በሚገኙበት ለገብርዬ መናዘዙም የባሰ ነው። ተሌላ ወንድ፣ ልጅ አርግዤልህ ነበር ለማለት!?»

«አባቴ እንዳሉትም፣ ከውሰው ስሕተት ከብረት ዝገት አይጠፋምና፣ መስሎኝ አጥፍቼ ተሆነ፣ እንዲህ ብታረጊ ይበሉኝና መቸስ......» አለች ታንጉት ከጭንቀቷ የተነሣ በደከመ ድምፅ።

«እንደዚህ ነው እንጂ የክርስቲያን ተግባር! ግዴለሽም፣ ንስሐሽ እስከዚህ ከባድ አይሆንም። ለአንቺም፣ ለሀገሪቱም ቴዎድሮስ ለሚያስበው ነገርም፣ ይጠቅማል፣ ብሎ አንድ የክርስቶስ ወገን የጀመረው ሥራ አለ። በአንዳንድ ነገር ትረጅዋለሽ» አለና አቡነ ሰላማ፣ እንትሳለም መስቀላቸውን ዘረጉላት።

ሚስተር እስተርን ወደ ሀገሩ ለመመለስ ቀደም ሲል የነበረውን ሐሳብ ድንገት የለወጠ ይመስል፣ በእርሱ የሚመሩት ሚስዮናውያን ወደ ደብረ ታቦር ሔደው ሳይሰናበቱ፣ ወይም የስንብት ፈቃድ ለመጠየቅ ሌላ መልእክተኛ ሳይልኩ፣ ሚስዮናዊ ተግባራቸውን ችላ ብለው በጎንደር ከተማ መኖር ጀመሩ። ወንዶቹ በየመኳንንቱና በየወይዛዝርቱ ቤት እየተዘዋወሩ ውሎዋቸውን ያሳልፋሉ። ሴቶቹ ደግሞ በቤት ሥራ በእጅ ሙያ ጊዜውን ይገፋሉ። ሚስስ ሮዜንታል ጎንደር ከተማ መቀመጡን ባትጠላውም፣ በጠባይ ከማትስማማት ከሚስስ እስተርን ጋር በአንድ ግቢ ታግቶ መዋሉን ጠላችው። ከወንዶች ጋር ባንድነት በሚሆኑበት ጊዜ ስንኳ አንዳንድ ቃላት ከመለዋወጥ በስተቀር ሚስስ ሮዜንታልን ከቁም ነገር ጨዋታ አያስገቧትም። ከአጠገባቸው ተቀምጣ፣ በመካከላቸው የሌለች ይመስል፣ ሦስቱ ብቻ ይነጋገራሉ።

በዚህ ሁሉ ሚስስ ሮዜንታል ከሠፈር መዋሉን ቅብጥብጥ መንፈሷ ስላልቻለው ከእነርሱ ለመራቅ በየመንደሩ በየመስኩ እየተዘዋወረች ትውል ጀመር። «እንዲያው አንቺ መዞር አይታክትሽም ማለት ነው?» የሚለው የሚስስ እስተን አሽሙር እየተከተላት ከግቢ ትወጣና እግሩዋ ያደረሳትን አካባቢ ሁሉ ትቃኛለች፣ ትመለከታለች፣ ትጎበኛለች። በዚህ ዐይነት ስትዘዋወር ነበር፣ አንድ ቀን ያላሰበችው ትርዒት ያጋጥማት።

ዝምታና እርጋታ የሰፈነበት ቁርስ አብቅቶ ወንዶቹ እንደ ሔዱ፣ እርሷም ሚስስ እስተርንን የጎሪጥ እያየች መጥታ ወደ ደብረ ብርሃን ሥላሴ አግጣጫ ሔደች።

ከዚያም በዳገቱ ጥግ ስትዘዋወርን ከድንጋይ ላይ ቁጭ ብላ ከሥር እየተጠማዘዘ የሚወርደውን የአንገርብ ወንዝ፣ ከማዶ የአባይ ኪዳነ ምህርትን አምባ ስታስተውልም እያስተዋልችም ምኞቷን ስታልም ቆይታ ከቀትር አቅራቢያ ፀሐይዋ ስትበርታም፣ የጽዱ የወይራው የዝባው፣ የዋንዛው፣ በጠቅላላው ዕጸደ ልምላሜው ቀዝቃዝ፣ መዓዛው ዕውድ ወደሚያደርገው የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ገባችና ከአንዱ ትልቅ ዛፍ ሥር ግንዱን ተደግፋ ተቀመጠች። በአድያም ሰገድ ኢያሱ የተተከለው የደብረ ብርሃን ቤተ ክርሲያን ትላልቅ ከሚባሉት የጎንደር አድባራት አንዱ ነው። ግቢው ሰፊ፣ አጥሩ ሙሉ ግንብ ነው። ክብ ቅርጽ ካላቸው ከጎንደር ቤተ ክርስቲያናት ተለይቶ አራት ማዕዘን የሆነው የደብረ ብርሃን ሥላሴ ሕንፃ የተገነባው፣ በድንጋይና በጭቃ ሳይሆን እንደ ፋሲለደስና እንደ ሊሎቹ ግንቦች በልዩ ልዩ ኖራ ነው። ደጀ ሰላሙና በቅጽር ግቢው ውስጥ ያሉት ብዙዎቹ ውስጥም ፊታቸው የማይታይ የዘጉ ባሕታውያን እንደሚኖሩ ይነገራል። ሚስስ ሮዜንታል ከአገርዋ እንደ መጣች፣ እንደ ጎንደር ከተማ በውበትና በግርማ ሞገሱ አስደንቋት ነእብር። በዚያው መጠንም ከአረመኔና ከደንቆሮ ሕዝብ አገር መጥታ ራስዋ ለመደነቅና ለመከበር የነበራት ተስፋ ፀሀይ እንደ ነካው ጤዛ አርግፎባታል። አሁን ስለዚህ ሁሉ አልነበረም የምታስበው። ሐሳብዋ በአንድ ነገር ላይ አልረጋ እያለ ከአስቸገራት ውሎ አድሮዋል። አንድ ነገር ስታስብ ሌላ ይደረብባታል። በዚህም በዚያም በአብዛኛው የምታስበው ግን፣ ስለ ዕድል ዕጣዋ ስለ ምኞቷና ሕልሟ ነበር። አሁንም ሐሳብዋ በዚህ ዙሪያ እያንዣበበ ሳለ የደጀ ሰላሙ ትልቅ በር ሲጢጥ ሲል ተሰማት። የዛፉ ግንድ ጋርዶዋት ነበርና እንደ ዋዛ አንገቷን ሰገግ አድርጋ አየች። በሐሳብ ፍዝዝ ብሎ የነበረው ዐይንዋን ለማረጋገጥ በጣቷ ፈተግ አድርጋ አየች። የመጣው ሚስተር እስተርን ነበር። የቆዳ ኮረጆውን ይዟል። ከተቀመጠችበት ቀስ ብላ ተነሥታ እንዳታይ የማይታየው አንዱ ባሕታዊ አሉበት ከሚባለው መቃብር ቤት ውስጥ ገባ። ገረማት። ‹የበቁ ሆነው ትንቢት ሊጠይቋቸው ይሆን? የምን ትንቢት? ወደ እኛ ሃይማንቶ ያስገባቸው ካህን ይኖሩ ይሆን? ወይስ እኛ ሳናውቅ እርሱ ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ገባ? ይህ ከሆነ ለጉድ ነው። «ዐመድ በዱቄት ይሥቃል» እንደሚባለው ሚስስ እስተርን በእኔ ላይ ከንፈርዋን ስታጣምም የራስዋን ጉድ አላወቀች› ስትል አሰበች።

ወጥቶ መጨረሻውን እስከታይ በመጠበቅ ላይ እንዳለች ሳንቃው በድጋሚ ሲጢጥ አለ። ድምፁ ከመጠነኛ ደወል አያንስም ነበር። ‹አሁን ደሞ የኔው ባል ተብዬ አንዳይሆን!› የሚል ሐሳብ መጣባትና እንዳትታይ ተከለለች። የገብርዬ ሚስት ታንጉት ከደጀ ሰላሙ በር ላይ ሦስት ጊዜ ያህል ተሳለመችና ደንገጡሯ የመሰለቻትን የወይዘሮ ደብሬን ሠራተኛ አስከትላ ገባች። ከዚያም የቤተ ክርስቲያኑን

በራፍ በድጋሚ ሳመችና ሚስተር እስተርን ወደ ገባበት መቃብር ቤት ሔደች። ደንገጡርዋ ከውጭ ቀረች።

ሮዚንታል፤ ነገሩ ራስ የሚበጠብጥ ዕንቆቅልሽ ሆነባት። ‹ባሕታዊውን ለመጠየቅ ሁለቱም እንዳጋጣሚ መምጣታቸው ነው? ወይስ በቀጠሮ መገናኘታቸው? ምን የሚያገናኝ ጉዳይ አላቸውና? በአደባባይ፣ በቤተ መንግሥት ከመገናኘታቸውና የእግዜር ሰላምታ ከመሰጣጣታቸው በስተቀር እውቂያቸው እስከዚህም አይደለም። የአበሻ ሴቶች፣ ደግሞ ምናልባት ከውሽማ ሌላ ከባላቸው ደብቀው የሚፈጽሙት ምሥጢራዊ ጉዳይ የላቸውም።› ውሽማ የሚለው ቃል ሌላውን ሐሳብ አመጣበት። ‹ይኸ መጅ ፊት አንገቱን ደፍቶ አበሾች እንደሚሉት ያህያ ውሃ ጠጭ እንደሆነስ?› አለች ከራስዋ ጋር። የሁናቴው ሐሳባዊ ትርዒት ሣቅዋን አመጣባት። በዚያ ጨለማ መቃብር ቤት ውስጥ መነጽሩን አውልቆ ዕቃ እንደ ጠፋው ሰው ሲንደፋደፍ። ወይስ ከነመነጽሩ ይሆን? ግን ባሕታዊው ከውስጥ እያለ? አንድም ቀን ዐይኑን ሳይጥልባት፣ አሁን ከሐበሻ ጋር መወዳጀቱ ቅናት ቢጤ ሲያሳድርባትም በሌላ በኩል ደስ አላት። ከአረጋገጠች ሌላው ቢቀር በሁለት ሰው ላይ በቀኗን የምትወጣበት አገኘች ማለት ነው። ከንፈርዋን የምታጣጥምባትን ሚስስ እስተርን ከፈለገች እንደ አሻሮ ልትቆላት ገብርዬ ደግሞ ወይ የምትቀራረብበት፤ ታለበለዚያ መሣቂያ መሣለቂያ የምታደርግበት ይሆናል። ምን እንደሚሰሩ አይታ ለማረጋገጥ ግን ምንም መንገድ አጣች። መቃብር ቤቱ ደርቡም ምድር ቤቱም ለነፋስና ለብርሃን መግቢያ ተብለው የተሠሩ ሁለት ትንንሽ መስኮቶች አሉት። ግን የታንጉት ደንገጡ ደግሞ ከዚያው አጠገብ አለች።

ለጥቂት ተከታትለው የወጡት የቀትር ጀንበር ወደ ምዕራብ ማዘንበል ስትጀምር ነበር። ‹ምን ዐይነት ጉዳይ ወይም የፍቅር ጨዋታ ነው፣ ይህንን ያህል ጊዜ የሚቆይ?› ስትል የባሰውን ተገረመች። መጠበቁ እንደ ሳምንት፣ እንደ ወረ ረዘመባት።

ሚስስ ሮዜንታል፣ በየቀኑ ወደ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እየሔደች ከሳምንት በላይ ተጠባብቃ ምሥጢራዊን ያየች ለሦተኛ ጊዜ በተገናኙ ጊዜ ነበር። እንደ መጀመሪያው ጊዜ ሁሉ፣ በሁለተኛው ጊዜም የታንጉት ደንገጡር ከመቃብር ቤቱ አጠገብ ተቀምጣ እመቤቷን እየጠበቀች ስለ ቆየች በመስኮቶቹ በኩል ለመመራመር አላስቻላትም ነበር። በሦስተኛው ጊዜ እንደዚሁ አብራ መጥታ ከዚያው ሥፍራ ስትቀመጥ ሚስስ ሮዜንታል ልጅነቷን ከዚያ ሥፍራ እንድትርቅ ካላደረገች በስተቀር ሲገቡ ሲወጡም ዝም ብሎ ማየቱ ፋይዳ እንደሌለው ተስማት። እየተናደደች ዘዴ አሰበች።

«እንደምን ዋልሽ?» አለች እያመነታች ቀርባ።

«እግዜር ይመስገን?» ስትል መለሰች በሰላምታ አንገቷን ድፋ እያደረገችና ለመነሳት እየቃጣች።

«ከእመቤትሽ ከወይዘሮ ታንጉት ጋር መጥተሽ ነው?» ስትል ጠየቀቻትና፣ «ይኸውልሽ እኔም ታለቃዬ ከሚስተር እስተርን ጋር መጥቼ ነው» አለቻት። ልጅቷ መልስ አልሰጠቻትም። ሚስስ ሮዜንታል ልጅቷ እምቢ እንዳትላት ከመሥጋቷ ሌላ እስትረን ድንገት ወጥቶ እንዳያገኛቸው ተጨንቃ ነበር። ፈርታው ሳይሆን ምሥጢሩን ሳትደርስባት ነገሩ እንዳይበላሽባት ነው። «ምን ጉዳይ አላቸው እመቤትሽ?» ስትል እንደ ዋዛ ጠየቀች።

«የኔ እመቤት ስንኳ አይደሉም። የኔ እመቤት የቅርብ ወዳጅ ስለሆኑ ነው አብሬ የምመጣው። ዛዲያ ሰው መቸም ቤተስኪያን ይመጣል።

«ተዚህ ከመቃብሩ ቤት እንጂ። ደጋግመው መምጣታቸው አይደለ?»

«ምናባቴ ዐውቄ? ካለች በኋላ ደንገጡርዋ ሚስስ ሮዜንታልን በጥርጣሬ ተመለከተቻት።

ሁኔታዋ ገባትና ሚስስ ሮዜንታል ወዲያው ነገርዋን አስተካከለች።

ሁኔታዋ ገባትና ሚስስ ሮዜንታል ወዲያው ነገርዋን አስተካከለች።

«በዚህ የሚኖሩት ባሕታዊ ነገራቸው መሬት ጠብ አይልም አሉ። የኔ አለቃም እየመጣ ይጠይቃቸዋል።»

«እናንተም?» አለች ደንገጡርዋ በመገረም።

«እህሳ! እመቤትሽም የሚመጡት ለዚህ ነው?»

«መሆኑ ይሆናላ!»

«እኛማ ጧት የመጣን ውሃ ጥም መሞቴ ነው» ስትል ሮዜንታል ጥማቷን ለማሳወቅ ምራቋን ዋጥ ዋጥ አረገች። «አሁንስ ጉሮሮዬን የማረጥብበት አንድ ጉንጭ ውሃ ባገኘሁ።

ደንገጡርዋ ዝም አለቻት።

«አለቃዬ እንደሆነ ቶሎ አይወጣ። የሚጠጣ ውሃ የት የሚገኝ ይመስልሻል?

‹እህ?» አለች ደንገጡርዋ በመገረም። «ቤተልሔም እንደሆእን እንኳን ሴት ጨዋ አይገባበት። ተዚህ ከባሕታዊ ዘንድ እንዳላቸው መጠየቅ ነው እንጂ።»

«በጣም ስለምፈራቸው ተዚህስ አይሆንም።»

«ወይ ተዚያ መንደር» አለች ደንገጡርዋ፣ የደጀ ሰላሙን ውጪ በዐይንዋ እያመለከተች።

«መንደር ገብቶ መለመኑንም እኮ እፈራዋለሁ» አለችና ሚስስ ሮዜንታል በማሳዘን አስተያየት፣ «ሒደሽ ታመጭልኝ?» ስትል ለመነቻት።

«ኧረ!»

«በሞቴ! ምናለበት?»

«እሜቴ ሲወጡ ያጡኝ እንደሆነስ! ይቆጡኛል።»

«ግዴለሽም ይቆያሉ።»

«መጣሁ አሁን ጠብቂኝ ነው ያሉት፣ ይቆጡኛል፣»

«ግዴለሽም።»

«ተመመለስሽ በፊት ተመጡም ውሃ ልታመጣልኝ ለምኜ ልኬያት ነው እላቸዋለሁ።»

ደንገጡርዋ አሁንም አቅማማች።

«ተይ ጽደቂብኝ? ለጽድቅ እሆንሻለሁ።» ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች የመንግሥተ ሰማያት ነገር ከተነሣ፣ ሆዳቸው እንደማይጨክን ሚስስ ሮዜንታል ታውቅ ነበር።

«ዕቃ የታለ? በም አመጣልዎታለሁ?» እምቢታ ሳይሆን ሰበብ ፍልጋ ነበር።

«ባሮጌ ፋጋ የሚሰጥሽ ታጪያለሽ?»

«ጨካኝ ነሽ ልጄ!» አለቻት ሚስስ ሮዜንታል።

«እሺ» አለች በፈራ ተባ መንገድ እየጀመረች። «ግን ከወጡ አደራ ይንገሩልኝ። »

«ግዴለም አታስቢ፣ አትሩጭ እንቅፋት ደሞ እንዳይመታሽ?»

ደንገጡርዋ እግርዋ ከደጃ ሰላሙ እንደ ወጣ ሚስስ ሮዜንታል ወዲያው አጎንብሳ ወደ መቃብር ቤቱ ተጠጋችና ጆሮዋን ከምድር ቤቱ ትንሽ መስኮት ሥር ለጥፋ አዳመጠች። ከራዋ ልብ ትርታ በስተቀር ምንም ድምፅ አይሰማም። በዐይን አያለሁ ብሎ ከመታየት፣ ቀስ ብሎ ማዳመጥ የተሻለ ነበር። ግን አንዱንም ሳይትዘው ድነገጡርዋ እንዳትመለስባት ደግሞ ፈራሽ። በጎን በኩል አፍንጫዋን ብቅ አድርጋ ወደ ውስጥ ተመለከተች። በመስኮቱ በኩል የሚገባ የዛፍ ጥላ ያደበዘዘው ብርሃን ካረፈበት መኻል ወለል በስተቀር ክፍሉ በሙሉ ጨለማ ነው። ጥቂት ደፈር በማለት አሁንም ከጎን በኩል እንደ ተጠጋች አንገቷን የበለጠ ሰገግ አድርጋ ተመለከተች። ዐይንዋ ጨለማውን ሲለማመድ፤ የክፍሉ ግማሽ ያህል እስከ ጥጉ ድረስ ለይቶ ታያት። ምንም ነገር የለም። ከሌላው ጎን በኩል ሆና እንደዚሁ አደረገች። ያው ነው። ከእንግዲህ ያበጠው ይፈንዳ በማለት፣ መኻል ለመኻል አንገቷን ወደ ውስጥ ገባ አደረገች። የተዘጋ ቤት ትንፍግ ተቀበላት። የመቃብር ጉብታ ስንኳ የማይታይበት የተደለደለ ወና ቤት ነው። ዐልፎ ዐልፎ የደረቀ የሣርና ቅጠል ጉዝጓዝ ብቻ ይታያል። ከደርቡ መሆን አለባቸው አለች። የደረጃውና በሮቹ ከጀርባ በኩል ስለሆኑ ከየትኛው እንደ ገቡ አላየችም ነበር። ችግሩ የደርቡ መስኮት በጣም ከፍ ያለ ስለሆነ፣ ስንኳን ወደ ውስጥ ለማየት እጅ ተዘርግቶ አይደረስበትም ነበር። ለሣር መከደኛ የተሠራ መሰላል ቢጤ እንዳለ አካባቢውን ቃኝታ አጣች። አንድ ዕድልዋን ደረጃውን ወጥታ ገርበብ ባለው በር በኩል ለማየት መሞከር ነበር። ግን ደግሞ፣ ራስዋ መታየቷ የማይቀር ነው። በተለይም ክፍሉን ሁሉ ለማየት ከፈለገች። ለመቁረጥ ስታመነታ ዐይንዋ ከመቃብር ቤቱ አጠገብ ካለው የወይራ ዛፍ ላይ ዐረፈ። አጠር ያለ ሆኖ አንዱ ቅርንጫፍ ወደ ጎን በኩል ከደርቡ መስኮት አጠገብ ያለ ይደርሳል። ልጅቷ ቶሎ ካልመጣችባት ሌላ ዕድልዋ በዚህ መሞከር ነው።

ዛፍ መውጣት እስከዚህም አታውቅም ነበር። አሁን ግን፣ ጫማዋን አውልቃ በእህል እንደ ምንም ከአንዱ ቅርንጫፍ ወደ ሌላው እየተንጠላጠለች፤ ከአንዱ ባላ ወደ ሌላው እየተሸጋገረች፣ እየቧጠጠች እየተሳበች፣ ከአንድ ቤት ጣሪያ የማይበልጠውን ከፍታ ቁልቁል ስታየው እያስፈራትና ዐይንዋን እየጨፈነች፣ የማታውቀውን ችሎታ አግኝታ ያልነበራት ድፍረት አድሮባት፣ እንደ ምንም ከመስኮቱ አጠገብ ደረሰች የዛፉ ቅርንጫፍ ከመስኮቱ ከፍ ያለ ስለሆነ፣ የክፍሉ ውስጥ የሚታየው ከላይ ወደ ታች ነበር። ከጎን በኩል ብቅ እንዳለች ከአንዱ ጎን በኩል ባሕታዊ ገሚስ በግምጃ ተጋርዷል። ይህ ፊታችው የማይታይ የሚባሉት ባሕታዊ የሚከለሉበት እንደ ሆነ ገባት። እነእስተርንም ከዚያው ውስጥ ከሆነ ነገራቸውን የምታይበት ምንም መንገድ የለም። በበሩ ገብታ ዐይን አውጥታ መጋረጃውን ካልገለጠችው በስተቀር። ርቀት እንዳያይ ተጠንቅቃ ግንዱን ጭምድድ

አድርጋ ይዛ ተመለከተች። ከከፍታው የተነሣ በመስኮቱ የሚገባው ብርሃን ከምድር ቤቱ የተሻለ ከመሆኑ ሌላ፤ ብዙ ጧፍ ስለሚበራ እንደቤተ መቅደስ ልዩ ምሥጢራዊ ትርዒት ሰጥቶ በደንብ ይታያል። ታንጉትና ሚስተር እስተርን ትንሽ ተራርቀው ፊት ለፊት ተቀምጠዋል። ታንጉት የምትቋጭ ይመስል ጣቶቿ ከኩታዋ ጋር ይጫወታሉ። ድምፅዋ አይሰማ እንጂ ከንፈርዋ በንግግር ይንቀሳቀሳል። ሚስተር እስተርን ጀሮውን አስደግፎ ይጽፋል። ጽሑፉን አቁሞ ይመለከታል። እጁን እያወዛወዘ ከንፈሩን በንግግር ይንቀሳቀሳል። ሚስስ ሮዜንታል፣ ከዛፍ ላይ መሆንዋንና የመሬቱንም ርቀት ለጊዜው ረስታ ፍዝዝ ብላ አስተዋለች። ይኸው ሁናቴ ብቻ ቀጠለ። ምን ሊሆን ይችላል? ከውስጥ ባሕታዊው የሚናገሩትን እየጻፈላት ነው? ታዲያ የእርሷ ንግግር ምንድ ነው? ስሟን፤ የተወለደችበትን ቀን ሌላውን፣ ሌላውንም እየነገረች ኮከቧን እየቆጠሩላትና ልፋፈ ጽድቅ እየጻፈላት ነው? ምንም - ሊገባት አልቻለም። ምሥጢሩን ለማወቅ ጹሑፉን ማየት አለባት።

ከሁለት ቀን ደፈጣ በኋላ ነበር፣ በማረፊያ ቤታቸው ብቻዋን ሆና የሚስተር እስተርንን ኮሮጆ ማገላበጥ የቻለችው። ከኮሮጀው ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚይዘው መጽሐፍ ቅዱስ፣ አንድ ትልቅ የማስታወሻ ደብተሩን፣ መድኃኒቶች፣ አንዳንድ ጊዜ ደረቅ ምግቦች ነበር። አሁን ግን የተጻፈበት መዓት ወረቀት ታጭቆበታል። በመጀመሪያ ዐለፍ ዐለፍ አድርጋ፣ እያርም አጋጣሚ እየጠበቀች በዝርዝር አነበበች። ከትውልዱ እስከ ተግባሩ የቴዎድሮስ ታሪክና በቴዎድሮስ ምክንያት ሚስዮኖች የደረሰባቸውን ሥቃይና የሚቀበሉትን መሥዕዋትነት የሚዘረዝር ነበር።

ሚስስ ሮዜንታል፣ ያገኘውን ምሥጢር ምን እንደምታደርግበት በመጅመሪያ የተወሰነ ሐሳብ አልነበራትም። እንዲያውም ፈጽሞ ያልገመተችው በመሆኑ፣ «ለዚህ ነው ያ ሁሉ ልፋቴ?» በማለት ከቅሬታ ጋር አቃልላው ነበር። እርግጥ፣ እውነትም ይሁን ሐሰትም እስተርን በቴዎድሮስ ላይ እንደዚያ መጻፉ ቢያስገርማትም፣ ጥሩ ወርቅን በማግባታቸው ብስጭት አደረባቸው ሲባል በሰማች ጊዜ እንደ ሆነችው ሁሉ አሁንም ያደረባት፣ ‹እሰዬ ይበልህ› የሚል የእርካታና የአዘኔታ ቅልቅል ስሜት ነብር። ይህ ስለ ቴዎድሮስ ያላት የተምታታ ስሜቷ እስከ ቁርጠኛው ጊዜ አብሮዋት ቆየ።

ሚስተር እስተርን ረዘም ላለ ጊዜ ችላ ብሎት የቆየውን ያህል፣ ወደ አውሮፓ የመሔዳችውን ጉዳይ ለመጨረሻ ጊዜ በመወሰን፣ ቴዎድሮስ ጎንደር መግባት የጠሉ ይመስል ወልቃይት ጠገዴ ዘምተው ሲመለሱ አጨናቅር ግርጌ እንደ ሠፈሩ፣ የሥራ ጓደኞቹን ይዞ ለስንብት ቀረበ ፡

ቴዎድሮስ፣ ለሚስዮኖች፣ በተለይም ለእነስተርን ማኅበር፣ ፍቅር ቀርቶ ደኅና አመለካከት ባይኖራቸውም፣ በቅርብ አሰፍስፎ ከሚገኘው ከቱርክ ጠላትነት አንጻር ከአውሮፓ ጋር ያላቸው ግንኙነት ቆንስል ካሜሮን እንደ ጀመረው፣ ጨርሶ እንዳይበላሽባቸው በማሰብ፣ ስሜታቸውን ገትተው፣ ትዕግሥታቸውን ጨምቀው፣ ‹እና ቆርጣችሁ መሔዳችሁ ነው? መቸስ ምን ይደረግ?› በማለት ካነጋገሩዋቸው በኋላ፣ ማምሻውን ግሩም የመሸኛ ግብዣ አደረጉላቸው። የእነስተርንን መሶብ ከራሳቸው መሶብ አስጠግተው፣ ለማጉረስም እየቃጣቸው፣ ‹ብሉልኝ ጠጡልኝ ኧረ እባካችሁ! አልጣፈጣችሁም መሰለኝ ልበል?› እያሉ ጋብዙዋቸው። እንጀራውን እያስተካከለች ወጡን እያወጣች፣ የመጠጡን ብርሌና መለኪያ እያነሣች የምታስተናግደው ከደብረ ታቦር ይዘዋት የመጡት ዕቁባታቸው ናት የምትባለው እሸት ቆንጆ ነበረች። ጥሩ ወርቅ ከቴዎድሮስ ጋር መጓዝ ከተወች ቆይታለች።

ሚስስ ሮዜንታል ከምግቡ ጨርሶ ሥራ ሳትፈታ፣ ከመጠጡ ግን ጥቂት እየቀነሰች፣ ዐይንዋ የሚንከራተተው በቴዎድሮስና ዕቁባቱ ናት በተባለችው በአስተናጋጅዋ ላይ ሲያርፍ የሮዜንታል ፊት ድንገት በርበሬ ዐይን በአስተናጋጅዋ ላይ ሲያርፍ ለራስዋ ነበር የሚሰማት - እንደ ማቃጠል ሲላት። ቴዎድሮስ ዐይናቸው የትም ላይ ያረፈ ይምሰል እንጂ እንደ ሐሳባቸው ሌላ ላይ ያተኮረ ነበር። ከዓለማቸውና ከምኞታቸው ላይ።

«እና አሁንም የሆነ እንደሆነ አገሬንም ወገኔንም እንዳያችሁት ለሌለው ክፋት የለንም። ምን ቆርጦን። እኛው ራሳችን መላው ጠፍቶን እንዲህ ደካማ ሆነን አንጂ እንዳያችሁት ለምለም ሀገር፣ ሀብታም ሀገር አለችኝ። ምን አስኪዶን ሌላ ዘንዳ? እኔም እንደ ሆንኩ ያገሬን ችግር በተወጣሁት መጀመሪያ። ታዲያ እንደ ቱርክ የመሰለ ጠላት ሊወረን አጥር እየነቀለ ሲያስቸግር፣ እናንተ የሠለጠናችሁት እርዱኝ ነው የምንለው። እንደምትሉት እናንተ በመንግሥታችሁ ጉዳይ የማትገቡ ቢሆንም እንድታስረዱልኝ ነው በመንግሥታችሁ ጉዳይ የማትገቡ ቢሆንም እንድታስረዱልኝ ነው የምጠይቃችሁ። አስቀይሜያችሁ ተሆነም ይቅር መባባል የክርስቲያን ወግ ነው» ብለው ሐሳባቸውን ከገለጡ በኋላ፣ «እስቲ መባባል ግብዣውን፣ ወደ ሌላው እየተዘዋወረ በሚስስ ሮዜንታል ላይ ከአንዱ ተጋባዥ፣ ወደ ሌላው እየተዘዋወረ በሚስስ ሮዜንታል ላይ ለቅጽበት ሲያርፍ፣ የጎረሰችው እንደ ማነቅ፣ የተጎነጨችው እንደ ትንታ ይላታል። አንገቷን ሰበር ታደርጋለች።

ግብዣው ካበቃ በኋላ ስጦታ መጣ።

«እስካሁን ያላችሁም ወይም አጥታችሁታል ብዬ ሳይሆን አገሬን፣ ይቺን ወዳጅ ያጣች አገሬን በግድ እንድታስታውሷት፣ እንዲያውም ሲመችም ከአጠገቡ አንድ

ነገር ሲያይ፣ የዚያ ነገር ምክንያት ትዝ እንደሚለው ላገሬ ማስታወሻ ይሁናችሁ ብዬ ነው» በማለት ለቄስ እስተርንና ለቄስ ሮዜንታል በከፊይ ተደጉዞ በጨርቅ የተጠለፈ ወንጌል፣ ስንክሳርና ድርሳነ ሚካኤል ከአንዳንድ የብር የእጅ መስቀል ጋር አበረከቱላቸው። ለሴቶቹ ደግሞ አንዳንድ በውስጡ የወርቅ አምባር ያለበት ኅብረ ቀለም የአለላ ሙዳይ ሰጡዋቸው።

ሚስስ ሮዜንታል ሙዳዩን ተቀብላ ከፊት አድርጋ በማየት ከአንገቷ ቀና እንዳለች ለማመስገን ጎንበስ ብላ የቴዎድሮስን ፊት ስትመለከት ዐይንዋ እንደ መርገብገብ፣ ከንፈርዋ እንደ መንቀጥቀጥ አለባት።

ቴዎድሮስ፣ ‹ይች ኮስማና ሴትዮ ሞቅ ብሏታል?› ሲሉ አሰቡና የዉት። ሮዜንታል፣ ከመጠጡ ሞቅታ ጋር በከፍተኛ የምርጫ ማዕበል ውስጥ ነበረች። ለመጨረሻ ዕድሌን ልሞክር ወይስ ዝም ብዬ ወደ ሀገሬ ልመለስና በጥፍልና በሹራብ ሥራ ሕይወቴን ልግፋው? ሌሊቱንም ከራስዋ ጋር ስትታገል አደረችበት።

በበነጋው ጧት፣ እልፍኝ አስከልካይ ገብቶ ሚስስ ሮዜንታል ለመግባት ፈቃድ በመጠየቅ ውጭ የምትገኝ መሆኗን ሲነግራቸው፣ ቴዎድሮስ ዳዊት በመድገም ላይ ነበሩ።

«ጸሎቴንም አታስጨርሱኝ ማለት ነው» አሉ ዐይናቸውን አፍጥጠው በዳዊት መካከል እልባቱን እያስቀመጡ።

«ምን ላድርግ ካልቀረብኩ ሙቼ እገኛለሁ ብለው አስቸገሩ። ትናንት ደሞ ፍቅር ስላሳዩዋቸው ብዬ ነው መንገደኞችን» አለ በመጨነቅ። ከእነጋረድና ከአክሊሉ ጋር በጠፋው የተተካው እልፍኝ አስከልካይ አፈላልገው ያመጡትን የሥጋ ዘመዳችው ቢሆንም ግና ልብ ለልብ አልተገናኙም ነበር።

«ትናንት ጋብዤ አሰናብቻቸው የለም? አሁን ምን አመጣት?»

«ኧረ እኔ እንጃ!»

«እስካሁን ካልጠበቃት ባልዋ ጋር ተጣልተው ተሆነ፣ እንዲያውም ትናንት ሞቅ ያላት መስሎኛል፣ ያው በቅርብ የሚያውቋቸው አባ ሰላማ ያስማዋቸው። እኔ የንሥሐ አባት፣ የጋብቻቸው ሽማግሌ አይደለሁም።

«የለም። ስለርስዎ ላገርም ጉዳይ አለኝ ነው የምትለው»

«ደሞ ምን ታሰማኝ ይሆን ፈጣሪዬ? እሺ ትግባ» ሲሉ እጃቸውን አወናጨፉ።

«እህ ወይዘሮ ሮዜንታል ምን ችግር አገኘሽ?» ሲሉ ቴዎድሮስ ጠየቁ ገብታ እጅ እንደ ነሣች። በጥልፍ የተንቆጠቆጠ ባለጥለት ቀሚስና ኩታ ለባሳ ጸጉርዋን ቀጭን ሹርባ ተሠርታ ነበር። ግራ ተጋብተው ትኩር ብለው ተመለከቱዋት። የአውሮፓውያን ሴቶች ለዘወትርም ሆነ ለክት እንደ ኢትዮጵያውያን መልበስ ከጀመሩ የቆየ ቢሆንም፣ በጠጉር አሠራራቸው ግን ከአንዳንዶቹ የጋፋት ሴቶች በስተቀር ገና አልተቀላቀሉም ነበር። ወይ ከምከሞ ይቆረጡታል። ወይ ደሞ ዝርማኔው እንዳይነካ ከፈለጉ በወፍራሙ ይጎነጉኑታል እንጂ! በቀጭኑ ተሠርተውት አያውቁም። ምናልባት ሞክረውት ከቆዳቸውና ከጸጉራቸው ቀለም ጋር ስለማይስማማ ምናልባት ሞክርውት ከቆዳቸውና ከጸጉራቸው ቀለም ጋር ስለማይስማማ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ አውሮፓዊ መታወቂያቸውን ጨርሶ ላለመተው ሊሆን ይችላል። የጋፋት ሴቶች ስንኳ ቀጭኑን ሹሩባ አይደፍሩትም ነበር። «እሺ ወይዘሮ ሮዜንታል ምን ችግር አጋጠመሽ?» አሉ ቴዎድሮስ መልስ ሳትሰጥ በመዘግየቷ በመገረም እየተመለከቱ።

«ኧረ እኔ የራሴ ችግር የለብኝም ጌቶች።»

«እህሳ?»

«በርስዎ ላይ ክፋት ስለማልፈልግ ነው።» ሮዜንታል ለማቀፍ ወይም ለመታቀፍ የምትፈልግ ይመስል፣ እንደ ቆመች ሁለት እጅዋን ወደ ፊት ዘረጋች።

ለማየት ወይም ለመታየት ያፈረች ይመስል፤ ፊቷን ከሁለት እጅዋ ሽፍና ስትቀመጥ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ጠበቁዋት። «እሺ በጄ?» አሏት በመደፋፈር አኳኋን።

«በድፍረት ወይም በሌላ እንዳይተረጉሙብኝ» አለች ፊቷን በእጅዋ እንደ ጋረደች።

«ምኑን?»

«የመጣሁበትን ምክንያት ነዋ!»

«እሱማ የኔን ክፋት ባለመፈለግሽ መሆኑን ነግረሽኛል። ‹ሞትና መርዶ ዘወትር አዲስ ነው› እንደሚሉት እየሆነ ነው እንጂ፣ ሕይወቴ በሙሉ በክፋት ባሕር ከተዋጠ ቆይቶ የለ? አንቺ የመጣሽልኝ አዲስ መርዶ ደግሞ ምንድን ነው?»

«እርስዎን ለማሳዘን አይደለም?»

«ተንጠፍጥፎ አልቋል። አዘኔታም የለኝ። እንግዲህ ተጥፍሬ አይወጣ! ይልቅስ የምትነግሪኝ ታለ ንገሪኝ» አሉ ቴዎድሮስ ወደ ትዕዛዝ ባዘነበለ ኮስታራ አነጋገር።

«ሚ - ሚስተር - ሚስተር እስተርን» እንደ ምጥ ከተጨነቀችበት በኋላ ታፍኖ እንደቆየ እስትንፋስ በጩኸት ገንፍሎ ወጣ። «ሚስተር እስተርን በርስዎ ላይ ብዙ መጥፎ ነገር ጽፏል።»

«ምን?» ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት እንደ መነሣት ቃጣቸው።

«አዎ! በመጽሐፍ የሚታተም በጋዜጣ የሚወጣ በአውሮፓ ስለ እርስዎና ስለ ሀገርዎ ብዙ ነገር ጽፎ ይዟል» አለች እጅዋን እያፋተገች ዕንባ ያቀረሩ በሚመስሉ ዐይኖቿ ቀና ብላ እየተመለከተቻቸው።

ቴዎድሮስ፣ እንደ ወንጭፍ ተፈናጥረው ተነሡና አንፈራጠው ከፊቷ ቆሙ። በጥፊ የሚያላጉዋት ስለመሰላት፣ ጎንደር ከተማ ድረስ የሚሰማ ነጋሪት እስኪመለስላት ድረስ ልብዋ በጭንቀት እየጎሸመ፣ እንደ ፍቅር እንቅፋት ጥፊውን በጉጉት ጠበቀች። ‹ይምቱኝ! ይግረፉኝ! ይርገጡ። እያለች በሆድዋ፡ ምን ዐይነት ደስታ እንደሚሰጣት አላወቀችም። የምታውቀው ስሜቷ መፈልጉን ብቻ ነው። የጠበቀችው ግን አልሆነም። ቴዎድሮስ ድንገት ተወራጭተው እንደ ተነሡ ሁሉ፣ ድንገት ዘወር ብለው ከወንበራቸው ላይ ተቀመጡና ሥቃይ ድካምና፣ ትከታ በሚያስተጋባ አኳኋን በሰፊው ተነፈሱ። «ውጭልኝ! ሒጂ ከፊቴ!» አሉ በድንገት በከፍተኛ ድምፅ። ለቅጽበት ያህል መንቀሳቀስ አልቻለችም። መብረቅ እንደ መታው ደርቃ ነበር። «ውጭልኝኮ ነው የምልሽ» አሉ ደግመው።

ሳይታወቃት ዐይንዋ በእንባ ተጋርዶ እየተደናበረች ስትወጣ፣ «ሁላችሁም ያው አንድ ናችሁ። ማንኛችሁ ይታመኑና» የሚል ድምፅ ተከተላት።

መንገዱ፣ ጊዜው አካባቢው ሳይታወቅ በደመ ነፍስ ጎንደር ከተማ ከማረፊያ ቤታቸው ደረሰች።

«እሺ፣ ለዚህ ሁሉ ምን መልስ አለህ» ሲሉ እስተርን ጠየቁት። ፈራጅ እንዳይሏቸው ከተቀመጡበት ተነሥተው፣ ተፈራጅም እንዳትሆኑ ከጎኑ ሳይሰለፉ። ከአጨናቅር ጥግ ካረፉበት ውጭ ሙሉ የፍርድ ችሎት ተዘርግቷል። ችሎቱ አንድ ቀንና ሌሊት ሙሉ መሰናዶ የተነገረበት ነበር......

ሮዜንታልን ከድንኳናቸው ከአስወጡ በኋላ፣ ማንንም ሳያማክሩ ከጉዳዩ ጋር ብዙ ታገሉ። የሐሳብ የስሜት የእምነት ትግል ነበር። አንድ ጊዜ ረጋ ብለው ያስላስላሉ።

«ጠላት ከማብዛ፣ ቅያሜ ከማፈራ፣ ሰምቼ እንዳልሰማ ዝም ብዬ ልተወው? በአንዳች ምክንያት ልታጣላኝ ዐውቃ ውሸቷን እንደሆነስ? ግን የምትዋሽበት ምን ምክንያት ይኖራል?»

ወዲያው መልሶ የእንግሊዝና የፈረንሳይ መሪዎች ከላኩላቸው ንቀት መሰል ደብዳቤና ከካሜሮን በከሰላ መክረም ጋር በደሉ በአንድነት ተደምሮ ይሰማቸውና ንዴታቸው ሐሳባቸውን ያሸንፈዋል። «አሆሆ! ጥቁር ጠይም ሲባል ኽረ እንዲያው እንደነሱ ያልገረጣው ሁላ ሰው አይመስላቸውም? ኢትዮጵያዊው ምን እንደሆነ አያቁም? ንቀት የሚችል፣ ውርደት የሚሸከም አህያ አደረጉት? እኔስ ምን አሰልኩዋቸው? ወይኔ መይሳው!» በማለት ድንኳኑ እስኪጠባቸው ድረስ ይንጎራደዳሉ፣ ይንቆራጠጣሉ።

ወዲያው ቀጥሎ ተዋበች ትታወሳቸዋለች። እንዲህ በሚሆኑበት ጊዜ «ምነው የኔ ጌታ እስቲ ቻል አርገው። ነገርኮ እንደ ውሃ ሙላት ያልፋል - ረጋ ብለው ከጠበቁት» ስትል የምታባብላቸው በሐሳባቸው ይመጣል።

«ምነው ፈጣሪዬ? እባክህ ትዕግሥቱን ስጠኝ ወይ ተዋበችን መልስልኝ» ሲሉ በምሬት ይጸልያሉ። በዚህ ሁናቴ ረዘም ያለ ጊዜ አሳልፈው፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመጨረሻ ሲወስኑ፣ ወታደር ተልኮ እነ እስተርንና እነ ሮዜንታል ተይዘው ከነጓዛቸው እንዲመጡ ተደረገ።

ጓዙ በንቅስ ተፈትሾ፣ የተባለው ጽሑፍ ከተገኘና ፍሬ ሐሳቡ በሳሙኤል ተተርጉሞ ከተገመገመ በኋላ የፍርዱ ችሎት የተሠየመው......

«እኮ በል መልስ ስጥ! ስድብ ስትለቀልቅ ኑረህ አሁን ምን አፍህን ይዘጋሃል?» የጽሑፉ ይዘት እንደ ተናገራቸው፣ በንዴት ክፉኛ እርር ያሉ ቢሆንም፣ በጥርሳቸው ከንፈራቸውን ነክሰው የችሎት ላይ ትዕግሥት ለማሳየት ሞከሩ።

«ምንም መልስ የለኝ» አለ አንድ ጊዜ በዓረብ አገር በአጋጣሚ እንዳመለጠው ሁሉ፣ አሁንም በተአምር ወልቆ ይወድቅ ይመስል የታሰረበትን እጅ ሙቅ በንቀት በጎሪጥ እየተመለከተ።

«አበጀሁ፣ እንኳን ተሳደብኩ ማለትህ ነው?»

«ታሪክ ነው የጻፍኩት። በሠለጠነው ዓለም ይኸ ደሞ የተለመደ።»

«እኛ ግን አውሬዎች፤ አረመኔዎች! እንዲህ አርጎም ታሪክ፣ እንዲህ አርጎም ሥልጣኔ! ያክሱም ጊዜ እናንተ የምትኖሩት እንደ ፋሮ ገና ጉድጓድ ውስጥ ነበር። ለመሆኑ እናት አለህ?»

«የለኝም።»

«ከእበት እንደሚፈለፈል ትል እንዲሁ ነው የተገኘሁ በለኛ!»

እስተርን የአሽሙር አነጋገራቸውን ቢሰማውም ያልሰማ መስሎ በኩራት፤ «ማለቴ ነፍስ ሳላውቅ በሕፃንነቴ ነው የሞተችው» አለ።

«በሰማይ ነፍሷን ይማርና የኔም እናት ሞታለች። ዛዲያ አንተ የናትን ፍቅር፣ የናትን ጣም፣ የናትን ክብር ያላወቅህ እንደሆነ የሰው እናት መስደብ ይገባሃል?»

«እኔ አልተሳደብኩም» አለ እስተርን ድርቅ ባለ አነጋገር።

«ቅቤ ዕይቀባሃት ነዋ!» ቴዎድሮስ ሳያስቡት አነጋገራቸው ወደ ጩኸት ከፍ አለ። «እኮ የምትሸጥ ደሃ ነበረች። ዘርዋ እንደዚህ ነው። ይኸን ሁሉ ምን አመጣው? ድህነት ነውር ነው? ኃጢአትስ የዓመል ድህነት። የገሌ ልጅ ነው፣ ዛሬ እንዲህ ነው ማለትስ ምን ዋጋ አለው? ሁሉም እኩል የግዜር ፍጡር ነው። ቁም ነገሩ ዘር መቁጠሩ ሳይሆን ሙያ መሥራት ነው። የኔ እናትም ባተሌም ብትሆን እኔን በፍቅርና እብምግባር አሳምራ አሳድጋኛለች። አባቴንስ ቢሆን፤ ሌላ ልጅ ነበረችው ይባላል - ምንትሴ ይኸን ሁሉ ምን አመጣው? አዋልደሃል።»

«ስለዚህምኮ ነው አልተሳደብኩም ያልኩ!» ሲል እስተርን ቀበል አደረገ በመርታት ስሜት።

«ቀጣፊ!» ሲሉ ጮሁበት። «ባንተ ቤት ነገር መገልበጥህ ነው። አዎ! እኔ ከመሳፍንት ከመኳንንት፣ ባለመወለዴ፣ የተራ ሰው ዘር በመሆኑእ አላፍርበትም። እናቴም በድህነቷ ብትቸገርበትም አታፍርም ነበር። ሌላውም ቢሆን የቤተሰቤ የግል ጉዳይ ነው። ያንተ ሐሳብ ግን እንደ ውርደት፣ መጥፎ ነገር አድርገህ ባለም ፊት ለማሰደብና ለማስፌዝ ነበር። ስለኔ እስከዚህም ግሌለኝም። ነገር ግን በዐጸደ መቃብር ያረፈችው እናቴ ለምን በክፉ ትነሣ? ለምን ትሰደብ? አየህ፣ ባገርና በናት ዋዛ ፈዛዛ የለም። ለምን መሰለህ ሀገር በእናት የምትመሰለው? እናት ሀገሬ የሚባለው? እናቴ ዓለሜ ኢትዮጵያ የምንለው? ሁለቱም የፍቅራችን፣ የህልውናችን መገኛ ስለሆኑ ነው። ስለይህም እናቴን ብቻ ሳይሆን፣ እናት ሀገሬን ጭምር እንደ ሰደብክ ነው የምቆጥረው። ሐሳብክም ይኸው ነበር። ባለም ፊት ወገኔን፣ ሀገሬን ለማዋረድ ለማንቋሸሽ።

«እኔ አላልኩም - እርስዎ ይላሉ» አለ እስተርን በተበተ ድፍረት።»

«ኧረ ይኸ ዐመዳም ነጫጭባ።» ቴዎድሮስ ከንዴታቸው ብዛት ሥሥ ከንፈራቸ እንደ መንቀጥቀጥ አለ። «ተዚሁ ተፊት ለፊቴ እናትህን አንተው ሰደብክ ይለኛል?»

«እኔንስ ቢሆን ለምን ይሰድቡኛል?»

አጠያየቁ አስገርሞአቸው መለስ አሉ። «እሱስ እውነትህን ነው። ጥፋተኛው እኔ ነኝ። ታንተ ጋር አፍ መካፈቴ! አዎ! ዐመዳም ጀርባውን ገሽልጥልኝና ሁሉንም ቆራጣ ውሰዱዋቸውና ቀፍድዱዋቸው። የባለጌ ምሱ አለንጋ ነው» አሉና ሲገረፍ ለማየት ያልፈልጉ ይመስል ወደ ድንኳናቸው ገቡ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ እልፍኝ አስከልካይ ገባና፣ «ሮዜንታል የሚባሉት ሴትዮ አሁንም ገብተው ማነጋገር ይፈልጋሉ» አላቸው።

«ምን ቀራት ደሞ አሁን?»

‹እኔንጃ አባ ታጠቅ።»

«ትግባ።»

«እኔ ለርስዎ ስም ባሰብኩ ምንድን ነው ጥፋቱ?» አለች ገብታ እጅ ከነሣች በኋላ፣ ዕንባ እየተናነቃት ሰውነቷ እየተንዘፈዘፈ። በቴዎድሮስ ጥፊ መመታት ፈልጋ የነበረችውን ያህል አሁን ደግሞ ዐይኗን ጨፍና ባታየውም የእስተርን መገረፍ እንዳንድ ነገር አንቀጥቅጧታል።

«አንቺማ መስሎ ይሆናል። ባገራችን አንድ የምስሌ አነጋገር አለ። ‹በሌለሁበት ከሰደበኝ ይልቅ፣ ስድቤን አምጥቶ የነገረኝ የባሰውን ሰደበኝ› ይባላል» አሏት አሁን ትንሽ በረድ ብለው። «እና አሁንም አንቺ ባትነግሪኝ ኖሮ መቸ ዐውቀው ነበር? የውጭ አገር ሰው የሚያስገርፍ፣ የሚያስር ተብዬስ መቸ በክፉ እነሣ ነበረ? መቸም ለመልካም ስም ባልታደል።»

«እና ደግ የሠራሁ መስሎኝ - ም - ምናልባት ተሳሳት መታሰር አለብኝ?» ድምፅዋ እየተቆራረጠባት። ተበጣጠሰባት።

«ምን ይደረግ ብለሽ ወይዘሮ ሮዜንታል» አሉ ቴዎድሮስ በማጽናናት ዐይነት። «ደግሞስ አንቺን ነጻ ብተውሽ ባልየውን አስሮ ከምሽቱ ነጠለው ተብዬ በሌላ ይተርጎምብኝ? መቸም እናንተ መሔጃችሁ አይታወቅም።

ጉዳዩ ማብቃቱን ቴዎድሮስ በእጅ ውዝዋዜ አመልክተው፤ እልፍኝ አስከልካዩ ወደ ውጭ ሲመራር፣ ‹እንኳን መነጠል ሚስት ነጠቁ፣ ቢባልስ ምን ነበረበት› አለች በሆድዋ።

እልፍኝ አስከልካዩ ወዲያው ተመልሶ መጣን፣ «ሰውየውንስ ምን እናርገው ይላሉ?» ሲል ቴዎድሮስን ጠየቃቸው።

«የምን ሰውየ?»

«ከቤታቸው ውስጥ አብሮ የተገኘው የኛው አገር ሰው ነዋ!»

ቴዎድሮስ፣ ከፈረንጆቹ ጋር አንድ ኢትዮጵያዊ አብሮ መያዙ ተነግሮዋቸው ነበር። ሻሽ ጠምጥሞ ፊቱን እስከ አንጫው ድረስ በነጠላው፣ ሸፍኖ እንደ ታሰረ ከወደኋላው በኩል ቆሞም አይተውታል። ግን ሐሳባቸውና ስሜታቸውን በእስተርንና በሚስዮኖቹ ጉዳይ ላይ ተጠምዶ ስለ ነበር፣ ከመካከላቸው አብሮ ስለ ተገኘው አንድ ኢትዮጵያዊ ሊያገናዝቡ፣ ሊያተኩሩ አልቻሉም። ደግሞም በውጭ አገር ሰዎች መንደር ኢትዮጵያዊ መኖር አዲስ ነገር አልነበረም። አሽከር ያለው አለ። ገረድ ያለው አለ። ዐልፎ ዐልፎም የአማርኛና የግዕዝ አስተማሪ በአጠገባቸው የሚያኖሩ ነበሩ። ቴዎድሮስ፣ ጠምጣሚውን ሰውዬ በዚሁ ዐይነት ገምተው ችላ አሉት። በኋላም በእስተርን ላይ ግርፋት አዘው ሲመለሱ ንዴትም ኀዘንም ከተቀላቀለበት ስሜታቸው የተነሣ ፈጽሞ ረስተውት ነበር። አሁን የእፍልኝ አስከልካዩ እንደገና ሲያስታውሳቸው አንዳች ዐይነት ጥርጣሬ ከነከናቸውና ማንነቱን ለማወቅ አብረውት ወጡ።

ፈረንጆቹ ወደ ሚታሰሩበት ተወስደው ካህን ቢጤው ግን፣ በወታደሮች ዕይተጠበቀ ተሸፋፍኖ እንደ ቆመ ነበር። ቀረብ ብለው ከእግር እስከ ራሱ ከተመለከቱት በኋላ፣ «የምን ሙሽራ መሆን ነው? እስቲ ግለጠው እስቲ» አሉት አንዱ ወታደር።

‹አንተ ጉደኛ ነህ?› አሉ ቴዎድሮስ ዐይናቸውን ፍጥጥ አርገው ከቁታ ይልቅ በመገረም እያስተዋሉት። «በሉ እግሩን ጭምር ቀፍድዳችሁ በሚገባ ጠብቁት። እኔ አስቀድሜ ሳላበርደው ገብርዬ ደግሞ እንዳያየው አይምረውም።» በጊዜው ገብርዬ ወደ ሌላ ዘመቻ ሔዶ ነበር።

ደብተራ አክሊሉ ግን እስከዚህም የመረብትበት ሁናቴ አላሳየም።

ባልና ሚስቶቹ ፈረንጆች፣ ሚስተር እስተርንና ሚስስ እስተርን ሚስተር ሮዜንታልና ሚስስ ሮዜንታል አራቱም በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲኖሩ ከአጥር ግቢው እንዳይወጡ፣ ጧትና ማታ ለመናፈስ ወደ ጉሮ ብቅ ከማለት በቀር በግቢው እንዳይዘዋወሩ ከመደረጋቸው በቀር፣ እስረኝነታቸ ሌላ ስቃይ አልነበረበትም። እጇ ሙቅ ወልቆላቸዋል። ምግብ የምታበስልና የምታቀርብ አገልጋይ ተመድባላቸዋለች። የእህል ችግር የለም። በሌላ ጎጆ የሚኖሩት ወታድሮች፣ ግቢውን ሌት ተቀን ጠንቅቀው ከመጠበቅና ሁናቴያቸውን ለማየት እየገቡ፤ «እንዴት ዋላችሁ? አደራችሁ?» ከማለት በስተቀር አያስቸግሩዋቸውም ነበር። ሚስተር

እገርንም ቢሆን፣ ከግርፋቱ ቁስል በጥቂት ቀን ውስጥ ተሽሎት እንደ ልቡ ወዲያ ወዲህ ማለት ችሏል።

ነገር ግን፣ በእስረኞቹ መካከል የነበረው ግንኙነት ስሜት እንደ ክራር ከቀን ወደ ቀን እየተወጠረ ሄደ። የእስተርን ሰባራ ስንጥሩን ያለ ማቋረጥ ማነብነብ ሚስተር ሮዜንታልን ያበሽቀዋል። የሚስተር ሮዜንታልም፣ ዝም ብሎ መተከዝ እስተርንን ያነጫንጨዋል። ሚስስ ሮዜንታል፤ ከጧት እስከ ማታ ከእጅዋ የማይለየውን የሚስስ እስተርን የሹራብና የጥልፍ ሥራ ያለ ማቋረጥ ማየቱ፣ መንጭቀሽ እሳት ውስጥ ጨምሪው ያሰኛታል። ሚስስ እስተርን በበኩልዋ፣ የሚስስ ሮዜንታል ዐሥር ጊዜ መቀመጥ፣ መነሣት፣ ወደ በሩ መውጣት፣ በክፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ማለትና መቁነጥነጥ ይረብሻታል።

«ምናለ ዐረፍ ብትዬ? ከቂትሽ ላይ እሾህ ተሰክቷል?» ስትል ትጮኻለች።

«አንቺስ ምናለ የሎንደን ሳሎንሽን የምታጌጪ መምሰሉን ብትተይው?» ስትል በተመሳሳይ ጩኸት ትመልስላታለች።

«እንዳንቺ ሥራ ከመፍታት ሳይሻል ይቀራል?»

« ‹ሥራ ያጣች አሮጊት መነኩሴ ቆቧን ቀዳ ትሰፋለች እንደሚሉት ሐበሾች።»

«አሮጊት አይደልሁም።»

«የለም ልጃገረድ ነሽ እንግዲያው።»

ይፋጠጣሉ።

ሚስተር እስተርን ለሚያነበንበው ነገር፣ ሚስተር ሮዜንታል መልስ ሳይሰጥ ዝም ያለ እንደሆነ፣ «ምን ይዘጋሃል?» ሲል ይደነፋል።

«አንተስ ምን ያንጣጣሃል?! ለዚህ ያበቃኸኝ መች አነሰህ?»

«እኔ ነኝ ያሰርኩህ?»

«አንተው ነህ ምክንያቱ!»

«እውነቱን ታሪክ ነው የጻፍኩት። ደግሞ አስቀድሜ አማክሬሃለሁ! ለዚህ ወፈፌ ጠበቃ ቁምለታ! አንተም ከእርሱ አትሻል።»

«ወፈፌ ነኝ እኔ?»

«የምንጣጣ ፍየል ምላስ ነኝ እኔ ታዲያ?»

ጥርስ ይጋጠጣሉ።

ብዙ ዓመታት በሰላምና በስምምነት ኑረው፣ አሁን ምን እንደነካቸው ምክንያቱን ራሳቸውም ሊረዱ አልቻሉም። ምናልባትም ካለፈቃዳቸው በአንድ ጣሪያ ሥርና በአንድ ግድግዳ ክልል ውስጥ በአንድነት እንዲኖር በመደረጋቸው፣ በፊት የየራሳቸው ጓዳ ይችለው የነበረው ዐመላቸውን ስላወጣው ሊሆን ይችላል። ወይም እስረኝነቱ ሆደ ባሻ አድርጓቸው ይሆናል።

ውጥረቱ እጅግ የሚብስበት ቀንና ሁናቴም አለ።

ማታ መብራት ጠፍቶ ባልና ሚስቶቹ በየጥንዳቸው ሲጋደሙ፣ እይቀኑን ብሽቀት በአንዳች ዐይነት ለማካካስም ይሁን ከልብ በመነጨ ፍቅር ከአንዱ በኩል የወሲብ ስሜት የመፈጸም ፍላጎት ይነሣሣል። የሚስዮን ባሕል ነውና ማፈር መጨነቅ አለ። ግን መሆኑ አይቀርም። ልዩ አተነፋፈስ ልዩ እንቅስቃሴ ሲሰማ ደግሞ ከሌላው ጥንድ ጆሮውን አቅንቶ የሚያዳምጥ፣ የሰው ስሜት ውስብስብ ነውና ሌላም ሌላም የሚያስብ ይኖራል። ምናልባትም ጥርሱን እያፋጨ። ከዚያኛው ጥንድ ቢሆን፣ የሚያዳምጠው ወይም ሌላ ሌላ ነገር የሚያስብ ከአጠገቡ እንዳለ ስለሚሰማው፤ የወሲብ ክንዋኔው በዚያው ላይ ብቻ ያተኮረ ወይም የረጋ ስላልሆነ ብስጭትና ሠቀቀን የተቀላቀለበት ይሆናል። ጧት ታዲያ ሲተያዩ ዐይንህ ላፈር መሆን ነው።

ቴዎድሮስ፣ የእስተርንን ጽሑፍ ምሥጢር እንዴት አገኙት? የሚለው ጥያቄ ሲነሣም እንደዚሁ ነው።

«የጻፍኩት ለብቻዬ፣ ያስቀመጥኩት ከቤቴ፣ እኮ እንዴት ዐውቄ?» ሲል ደጋግሞ እስተርን ይጠይቃል።

«መቸም በቅርብ ያለሁት እኔ ነኝና ጠርጥረኸኝ ከሆነ እሱው እንዳወቀ ይፍረድብኝ» ስትል ሚስስ እስተርን የሹራብ ሥራዋን ሳታቋርጥ፤ ክፍሉን በሙሉ በመቃኘት ትቀበላለች።

«ዛዲያ ማንን ማለትሽ ነው?» ሲል ሚስተር ሮዜንታል እጁን ይቀስራል።

«እኔ እንጃ።»

«እኔ ማንን አልኩ?»

ሁሉም ዐይናቸውን ያጉረጠርጣሉ። ሚስስ ሮዜንታል ግን፣ ከውስጥ ጥርሷን ትበላለች። ይህ ጥያቄ በተለየ አቀራረብ ብዙ ጊዜ ከተደጋገመ በኋላ፣ አንድ ቀን ሚስስ ሮዜንታል መቻል አቃታትና አፈረጠችው።

«እኔ ነኝ! እኔ ነኝ የተናገርኩት» ስትል ሮዜንታል ጮኸች፤ ሚስተር እስተርን ለስንተኛ ጊዜ ከቁርስ በፊት በቁርስ ፈንታ ላቀረበው ጥያቄ። ጆሮዋቸውን ማመን አቅቷቸው ሦስቱም ፍጥጥ አድርገው ተመለከቷት።

«አዎ! እኔ ነኝ። የምታደርጉትን ማድረግ ትችላላችሁ። ከሚያቋርጥ ንዝንዛችሁ አይብስም» አለች በሚንጨረጨር ድምፅ።

ከረጅም ጊዜ ዝምታ በኋላ፤ «ግን ለምንድ እቴ?» ስትል እንደ ወስፌ በሰላ የአሽሙር ለዘብታ ሚስስ እስተርን ጠየቀቻት።

«እንጃ! እንጃ!» አለች ሚስስ ሮዜንታል አሁንም በጩኸት። ከዚያም ሳይታወቃት ዕንባዋ ባራት መሥመር ይወርድ ጀመር። በዕንባዋ መጋረጃ ውስጥም፤ በንኖ የሚጠፋው ሁሉ ምኞቷ፣ ጭጋግ ለመሰለው የሚስዮናዊ ሕይወትና በመጨረሻም ከእነርሱ ጋር አብሮ ለእስረኝነት የዳረጋት የዕድልዋ መጨረሻ ታያት።

«አዎ! ጉድህን ያወጣሁት እኔ ነኝ» አለች እንደገና ሚስስ ሮዜንታል፣ ከሐሳብዋ ትርዒትዋ ስትመለስ በሚስተር እስተርን ላይ ዐይንዋን አፍጥጣ። ተበዳይ እርሷ እንደ ሆነች ያህል ፍልሚያ የምትጠየቅ ትመስል ነበር።

ሚስስ እስተርን፣ ከሥር የሚፈላ ድፍድፍ የሚደገፋው የማሠሮ ክዳን ደረቷ ከፍና ዝቅ እያለ፤ ጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ተመለከተቻትና ድንገት ተወርውራ ጉብ አለችባት።

ጠባቂዎቹ ጩኸት ሲሰሙ እየተሯሯጡ ገቡ።

«እኒህ ፈረንጆች አበዱ?» አለ አንደኛው የመገረም ሣቅ እየመጣበት።

# ምዕራፍ ስድስት

## ታንጉት፣ ሥጋት የተሰማት እያደር ቀስ በቀስ ነበር።

አቡነ ሰላማ የጠየቁትን ሥርየት ፈጽማ ደብረ ታቦር ከተመለሰች ከጥቂት ወራት በኋላ በድፍን ጎንድር የታወቁ የነእብሩት ወይዘሮ ደብሬ ሳሙና በር አጠገብ

ከፈፉ ውስጥ ሞተው መገኘታቸውን ወሬ ሰማች። ማን እንደሆነ ባይታወቅም፣ በጎራዴ ወግቶ የገደላቸው ሰው ነው ይባላል። ወሬውን ቀድመው ያገኙት የዓለሜና የእንግዳ ሚስቶች ሲሆኑ የነገሩዋትም እነርሱው ነበሩ። ከወይዘሮ ደብሬ ጋር የነበራትን ወዳጅነት እያወቁ ቤተ ክርስቲያን ላይ እንደ ዋዛ በድንገት የነገሩዋት፣ በአደባባይ እሪታዋን ስትለቀው በሆዳቸው ለመሣለቅ መሆኑ ገባትና እንደ ምንም ችላው ቤቷ ደረሰች። ከዚያም ሁለት ቀን ሙሉ ብቻዋን እያለቀሰች እርሟን አወጣች።

የመጨረሻ ስንብታቸው ሁናቴ ታወሳት። ‹እኔ ነኝ ተዚህ ሁሉ ጣጣ ያስገባሁሽ። ላንቺ ነው እንጂ የምሠጋው እኔማ ተንግዲህ ወዲህ ብመንን ለነፍሴ እሆናለሁ እንጂ ምኑ እንዳይቀርብኝ? በኔ ላይ እንደሆነ ያሰቡትን ይሥሩ› እያሉ ከሆዳቸው ሊያስገቡዋት የፈለጉ ይመስል፤ ችምቅ አድርገው ዐቅፈው እየተንሰቀሰቁ አልቅሰው ነበር። ያን ጊዜ ልብ ባትለውም አሁን እንደገና ስታስታውሰው አንድ ዐይነት ከባድ ፍርሃት አድሮባቸው ሳይሆን አይቀርም ነበር። ምን ነበር ያስፈራቸው? ከዚያን ጊዜ ፍርሃታቸው ከአሁን አሟሟታቸው ጋር ዝምድና አለው ይሆን? ጎንደር ሔዳ ለመላቀስና በዚያም አሟሟታቸውን በትክክል ለማወቅ ሐሳብ መጥቶባት ነበር። ነገር ግን የምታላቅሰው ሁነኛ ዘምድ በቅርብ እንደሌለና ቴዎድሮስ በጎንደር አካባቢ እያለ ለገብርዬ ሳትነግር መሔዷ ግድ እንዳልሆነነ ስትገነዘብ መልሳ ተወችው። ኀዘንዋና ሐሳብዋን በሆድዋ ቀብራ ዝም አለች።

ከጥቂት ወራት በኋላ የፈላሻ ሚሲዮናውያን መታሰር ወሬ መጣ። ስለ ታሰሩበት ምክንያት መጀመሪያ የተረጋገጠ ነገር አልነበረም። የተምታታ ነበር። አንዱ ‹ቴዎድሮስን በአደባባይ ስለዘለፉዋቸው ነው› ይላል። ሌላው፣ ‹ብዙ የብራና መጻሕፍትና የብር መስቀል ደብቀው ይዘው ወደ ሀገራቸው ሲሔዱ ተያዙ› ይላል። ‹በአርማጭሆ በኩል ከቱርኮች ጋር ሲላላኩ ስለተገኙ ነው› የሚልም አለ። ያምሆነ ይህ ታንጉት ለእስረኞች ትንሽ አዘኔታ ቢሰማትም ጉዳዩን ከራስዋ ጋር አላያያዘችውም ነበር። ቴዎድሮስ ምሕረታቸው አጠር፣ ቁጣቸው ከረር፣ ቅጣታቸው ከበድ እያለ ሔዶ ነበርና፣ ‹አሁንስ ፈረንጆቹም ደረሳቸው?› በሚል ትዝብት ወሬውን እንደ ገለልተኛ አስተናገደችው።

ቆይቶ ወሬው እየተጣራ ሔዶ ከሚስዮናውያኑ አንዱ እስተርን የተባለውን የቴዎድሮስን ታሪክ አራክሶ መጻፍ ተረጋገጠ።

አሁን ባያስደነግጣትም ከነከናት። ከእናትዋ እንደ ሰማችው ስለ ቴዎድሮስን ዘርና አስተዳደግ እርሷም ነግራው ነበር። ‹ዛዲያ ከነገረችው ምኑ ነው ያስቆጣው?› ለመታዘብ ያህል፣ ጥጥ እያበዛተች ወይም እየፈልተለች ጉዳዩኑ እንደዋዛ

ስታብላላው ሕሊናዋን የሚፈታተኑ ብዙ ሐሳቦች ይመጡባታል። ስለ ትውልዱና ስለ አስተዳደጉ ለእስተርን የነገረችው ከእናቷ የሰማችውን ቢሆንም ቴዎድሮስ ራሱ ለሰው ከአጫወተውና ከሚያጫውተው የተለየ አልነበረም። በተራ ዘርነቱም በድህነቱም አያፍርበትም። አንዳንድ ቅሬታ ቢኖራትም ቴዎድሮስን ታደንቀዋለች። ትመካበታለች። እንደሚያስብላትም ታውቃለች። ታዲያ አቡነ ሰላማ መጀመሪያ ሲጠይቋት እንደ ፈራችው ሳይሆን፣ እስተርን እንዳለው ታሪኩን አሳምሮ የሚጽፍለት ከሆነ፣ ቴዎድሮስም እውነተኛ ታሪኩ መታወቁን የማያፍርበት ከሆነ በማለት ነበር የነገረችው። ግናስ ደግሞ? ብላ ራስዋን ትጠይቅና፣ ሕፃን ሳለች እናትዋ የነገረቻት ሁሉ ሲታወቅላት ራስዋን ትጠራጠራለች።

እናትዋ ካለርስዋ ያልወለደች፣ የህልውናዋን ዓላማና ፍቅርዋን ሁሉ ላንዲት ልጅዋ የስጠች፣ ደግነቷና ከፍቅርዋ ጋር የተፈጸመባትን በደል ዘወትር እየተሰማት የጠወለገች ባልቴት ነበረች። ሸክላ ስትሠራ የዋለችበትን እጅዋን ከተጣጠበች በኋላ፣ የሕፃን ፊትዋን እየጠራረገችላት። ‹ራበሽ ያይኔ ዓለም? አይዞሽ። አሁን ምሳ ይደርሳል። እስተዚያ ቆሎ ቆርጥሚ። መአስ ምን ይደረግ? ባይልልን ነው። ግና ዘራችን ባይወደድ፣ ዝምድናችን ባይፈለግ ምን ተዳችን! ሠርቶ ማደር አያቅተን› ትላት ነበር።

ታንጉት አባትዋን አታውቀውም። ጭልጋ ደሶ ሲመለስ ሽፍታ አደጋ ጥሎበት የሞተው ገና አንድ ዓመት ሳይሞላት ነበር። እሷም ገና ሳትወለድ አንሥቶ በበሽታ ከመደብ ላይ የዋሉት ሴት አያትዋም የሚኖሩት በእናትዋ የሸክላ ሥራ ነበር። ግን ምንም ቢሆን ጉሮሮዋቸው ተዘግቶ አድሮ አያውቅም።

ታንጉት ሰባት ዓመት ገደማ ሲሆናት እናትዋን በሸክላው ሥራ ለመርዳት ፈልጋ ነበር። አላፈቀደችላትም። ‹ይህንንስ ሙያ እጅሽ አይነካውም። እኔ ቁሜ እየሔድኩ። ባይሆን እንደ ዕድልሽ ሌላ ሌላውን ትደርሽበት ይሆናል› በማለት ከለከለቻት። ምክንያቱን ሳትነግራት ታንጉትም ሳይገባት ቀየች።

ዐሥር ዓመትዋ ገደማ አያትዋ እንደ ሞቱ፣ በዚያን ጊዜ በቋራ የታወቀ ጎበዝ የነበረ የዛሬው ቴዎድሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ መጥቶ ዳቦ ቆሎ ከሰጣት ከንስት ጊዜ በኋላ እንደገና ቀን ብቻውን መጣና ከእናቷ ጋር ብዙ ተነጋገሩ።

ከደጃች ጥግ የተቀመጠችው የታንጉት፤ ካሣ እንደሚለምን ዐይነት አንገቱን ደፍቶና ቀስ ብሎ የሚናገረው ባይሰማትም፣ እናትዋ ራስዋን በእምቢታና በምሬት እየነቀነቀች መልስ የምትሰጠው ከፍ ባለ ድምፅ ነበር። ‹ፈጥሞ የማይሆን ነገር ነው! ዱሮ ዱሮ ቀረ።

‹የናቴ አጥንትም ይረግመኛል።›

‹እኔ በሕይወት እስካለሁ ምንም ችግር የለብኝም።›

‹እናቴ በሰማይ በምድር ቃል ይዛኛለች። ተዚያ አልወጣም። ምንም ቢሆን።›

‹አንተ ምን አጠፋህ? ባባትህ ጉዳይ አትጠየቅበት! ግና የናቴ ቃል ቢሆን።›

‹አንተ ምን አጠፋህ? ባባትህ ጉዳይ አተጠየቅበት! ግና የናቴ ቃል ደግሞ ቃል ነው።›

ተሰነባብተው ሲሔዱ የተጣሉ አይመስሉም ነበር። በመካከላቸው አንድ ከባድ ጉዳይ እንዳለ ታንጉት ተሰምቷት ነበር። ከዚህ በኋላም፣ እህልና ከብት የያዙ ሰዎች ሲመጡ እናትዋ አልቀበልም እያለች ብዙ ጊዜ ትመልስላቸው ነበር።

ታንጉት ምሥጢሩ የገባት ቆይቶ፣ ቆይቶ ነው።

እናትዋ በድንተገኛ በሽታ ሞታ ታንጉት ከዘመድ ቤት ተቀምጣ ሳለች ሰዎች መጥተው፣ ከዘመዶቿ ጋር ተነግረው ወደ ካሣ ሠፈር ይዘዋት ሔዱ። ያን ጊዜ ስሙ በድፍን ቋራ የተጠራ ሆኖ ነበር።

በካሣ፣ በኋላም በቴዎድሮስ ቤት ያደገችውና የኖረችው በፍቅርና በንክብካቤ ተይዛ ነው። የቂም ጠባሳ የሚተው በደል ተፈጽሞባታ አያውቅም። ስታጠፋ ካሣ ቢቆጥትም ቢቀጣትም እንደ ባዕድ ሳይሆን እንደ እኅት እንደ ልጅ ነበር። ሚቿ ተዋበችም እንደ ልጅ ነበር የምታያት። በኋላም ገብርዬን እንድታገባ ስትደረግ በመጀመሪያ ፈቃድዋን ተጠይቃ ነበር።

የለም። በጊዜው፣ እየታወቀ ሆነ ብላ ቴዎድሮስን ለመጉዳት ያደረገችውስ አልነበረም።

«ወዳጃችን የቴዎድሮስን ታሪክ አሳምሮ ሊጽፍ ተነሥቷልና፣ ለኃጢአትሽም ሥርየት በምታውቂው ነገር ሁሉ እርጅው» ብለው አቡነ ሰላማ ጠየቋት። ‹እሺ› አለች። በጊዜው እምቢ ለማለት የማትችልበት የራስዋ ምክንያት ቢኖራትም ከመሠረቱ አቡነ ሰላማ ጋር በቅርብ እንድትወዳጅ አንዳንድ የማይጠይቋትንም ነገር እየፈጸመች እየጋበዘችና እያስተናገደች የሚሠሩትንና በቤታቸው የሚሆን ነገር ሁሉ እንድትነግረው ያዘዛት ራሱ ቴዎድሮስ ነበር። ምናልባት ከጀመሪያ ባትቀርባቸው ኖሮ ይህ ሁላ ሊደርስ አይችልም ነበር ይሆናል። ቴዎድሮስ አቡነ ሰላማን እንደሚጠረጥራቸው ገብቷታል። ከዚያ በፊት ያገኘችውንና ጠቃሚ የመሰላትን ሁሉ ስትነግረው ኑራለች። አቡነ ሰላማ በመጨረሻ የጠየቋትን መንገር ነበረባት?

ስለ ነገረችው መነሻ የሆነው ጥፋቷን ይምራት ኖሮ ይሆን? ሌላው ቢቀር ለሚስተር እስተርን ከነገረችው ብዙውን የማታውቅ መስላ ማስቀረት አትችልም ነበር? ምናልባት የአያትዋ ቃሉ - ግዝት የእናትዋ ምሬት በስውር ሕሊናዋ ከተቀበረበት ወጥቶ ለመቀበል ወይም ለመጉዳት ጭምር አድርጋው እንደሆነስ?

ቴዎድሮስ ቢሆን እሱ ጭምር አድርጋው ለሚያጠፋ የነገረበት ማን መሆኑን ከሌላ ዘንድ ሲሰማ፣ በቅንነት ወይም በጭንቀት ያደረገችው መሆኑን መች በቀላሉ ያምናታል? በማቶች ፍላጎት የተቀበረውን ራሱም ደብቆ የያዘውን ምሥጢር ያምታውቅ መሆንዋን የሚያውቅ አይመስልም። ወይም እያወቀ የማያውቅ መስሎ ሊሆን ይችላል።

ያም ሆነ ይህ ነገሩ ሲወጣ፣ ‹የአያትሽን ቂም በቀል በእኔና በሚች እናቴ ስም መጥፋት መወጣትሽ ነው?› ብሎ በንዴት ቃል ሲቃጠል ታያት። የፍቅሩን የደግነቱንና የርኅራኄውን ያህል በተለይ አሁን አሁን ምሬቱን ቁጣው ደግሞ፣ ራሱንም ሌላውንም የሚያቃጥል እሳት ነበልባል መሆኑን ታውቃለች።

ታንጉት አሁን እንደገና መለስ ብላ ስታስበው ሌላም የሚነከንክናት እንቆቅልሽ አለ። ፈቃዳቸውን እንድትፈጽም የሚያደርጉበት ሰበብ ቢኖርም አቡነ ሰላማ ስለ ቴዎድሮስ ዘር፣ ዘመድና አስተዳደግ ከሌላው ሰው ሁሉ የበለጠ እርስዋ የውስጡን የምታውቅ አድርገው ለምን ጠየቋት? በአም ቀራቢ ናት ብለው በአጋጣሚ ነው? ወይንስ ሌላውንም ምሥጢር በማወቃቸው? ከሆነስ እንዴት ዐወቁ? እርሷ እንደምታውቀው በሕይወት ያሉት ምሥጢሩ ባለቤቶች እርሷ ቴዎድሮስ መሆን አለባቸው። እንዲያው ምናልባት አባቱ ዐውቀው፣ እሱም ከአባቱ ሰምቶ ከሆነ ሌላው ጋረድ ነበር። በሕይወት ሳለ ሌላ ስሜቱን ቢገልጽም ይህንን ግን የሚያውቅ መስሎ አይታይም ነበር። ከሞተ ስንት ዓመት ሆኖታል። ደግሞስ ካልጠፋ ሥፍራ ከፈረንጁ ጋር ደብረ ብርሃን ሥላሴ መቃብር ቤት መገናኘታቸውን የመረጡት ለምን ነበር? የሚፈሩት ነገር ቢኖር ነው? ሌላ ምክንያት አላቸው? ወይስ ይኸውም እንዳጋጣሚ ቤተ ክርስቲያን ከመሳለም ጋር ያመቻል ብለው ነው?

ታንጉት ይህንን ሁሉ ስታሰላስል ጭንቀት እያረገዘች ሔደች በምክርና በሐሳብ የሚያገላግላት የቅርብ ሁነኛ አላገኘችም። ለዚህ ጊዜ የምትሆናት ተዋበች ነበረች። ታንጉት በኋላ - በኋላ የሚገባውን ክብርና ሞገስ የነጠቀቻት ይመስል፣ ቅናት ቢጤ ቢሰማትም ብዙ ምሥሪር ይካፈሉ ነበር። ተዋበች ስንኳን ቴዎድሮስ ላሳደጋት ለቴዎድሮስ ባለሟል ለገብርዬ ሚስ ቀርቶ ማንንም በፍቅር የሚይዝ ሰፊ ሆድ ሰፍሳፋ አንጀት፣ ንጹሕ፣ ልብ ነበራት። በየዋህነት ያደረገችው መሆኑን ትረዳለች ምሥጢርዋን እንደ ራስዋ ትጠብቅላት ነበር። ቴዎድሮስንም ልታሳምንላት

የምትችለው እርሷ ብቻ ነበረች። ብታስብም የምታምነውና የምትተማመንበት ሌላ ሰው ግን አጣች። ቴዎድሮስ ከነሠራዊታቸው እስረኞቹን ይዘው ወደ ደብረ ታቦር የተመለሱት፣ ታንጉት በዚህ ዐይነት የሐሳብ ባህር ውስጥ በመዋኘት ላይ እንዳለች ነበር።

የቴዎድሮስ መቃብር ቀደም ብሎ እንደ ተማሰ፤ ከሠፈር ቀርቶ የነበረውና የደብረ ታቦር ነዋሪ ሕዝብ፤ ሊቀበላቸው በአደባባዩና በመምጫቸው መንገድ ግራና ቀኝ ተሰባሰበ። ወትሮም ቢሆን ዘመቻ ቆይተው ወደ ሠፈር ሲመለሱ፣ ሰው ወጥቶ በሆታና በጭፈራ መቀበሉ የተለመደ ነበር።

አሁን ደግሞ ፈረንጆቹን እስረኞች ይዘው መምጣታቸው ሲሰማ የሚስዮናውያኑ ጋር ቅያሜ የነበራቸውና አሁን አንጀታቸው ቅቤ የጠጣው ‹የጋፋት ልጆች፤› የጋፋት መንደርና የአካባቢው ሰው ሁሉ ቀስቅሰው ይዘው ስለመጡ፤ ከወትሮው የተለየ ብዛት ነበረው። ሠፈር የቀሩት የጦር አለቆችና የጦር አለቆች ሚስቶች ሌሎችም የታወቁ ካህናትና ወይዛዝርት ከቤተ መንግሥት ፊት ለፊት በሚገኘው አደባባይ ላይ እንደየማዕረጋቸው ቦታ ቦታችውን ይጠብቃሉ።

ሠራዊቱ ገና ብቅ ሲል፤ እልልታው እንደ ዓውሎ ነፋስ ከሩቅ እያረገበ መጣ። ጭብጨባው፣ ሆታው አስተጋባ።

ከፊት የቀደሙት ቃፊር ፈረሰኞች ነበሩ። ቀጥሎ ብዛት ያለው እግረኛ ጦር ተከተለ። ከዘመቻ መልስ ወይም በረጅም ጉዞ የደከመው እየተንጠባጠበ እንዳይቀር በጣም ሲደክምም ለማረፍ እንዲያመች ተብሎ፣ እግረኛው ሠራዊት ከቴዎድሮስና ከጦር አለቆቻቸው ቀድሞ እንዲጓዝ ይደረጋል። አሁንም እንደዚሁ ነበር። በአደባባዩ የተሰበሰበው ሕዝብ በድፍንና በአንድነት የዕልልታና የጭብጨባ አቀባበል ያድርግ እንጂ፣ እያንዳንዱ ደግሞ በግል በዐይኑ የማይፈልገው ነበር።

የዘመተ ባል፣ ወንድም ዘመድ ወዳጅ በደኅና መመለሱን ለማረጋገጥ። ለሐሳብዋ ጭንቀት መልስ የምታገኝበት ይምሰል፣ የታንጉት ዐይን የሚፈልገው ጭንቀት መልስ የምታገኝበት ይመስል፣ የታንጉት ዐይን የሚፈልገው ደግሞ ፈረንጆቹን እስረኞች ነበር። ከእግረኛው ሠራዊት ቀጥለው መጡ። ግራና ቀኝ ፊትና ኋላ ነፍጥ በያዙ ወታደሮች ከመከበባቸው በስተቀር እጃቸውንም ሆነ እግራቸውን አልታሰሩም። ሁሉም የሚጓዙት በከብት ነበር። ነገር ግን የእስረኛ ወግ የውስጥ ስሜታቸውን በሚንጸባረቅ ሰውነታቸው ጠውለግለግ ያለ ይመስላል። ያሰራቸው፣ ወይም የተሰበሰበው ሰው ሲያሾፍባቸው መልሰው ለማሾፍ ይመስል ግንባራቸውን አኮማትረው ከንፈራቸውን እየለጠጡና እያንጋደዱ ግራና ቀኝ ሕዝቡን በክፉ ዐይን ይመለከቱታል። ዐይን ሰውን የሚገድል ቢሆን ኖሮ፤ በዚያ አደባባይ ስንቱ

በተረፈረፈ ነበር። በተለይ ሚስስ ሮዜንታል ደረቷን ገፋ፣ አንገቷን ቀና አድርጋ አቀማመጧን እንደምታስተካክል አሁን - አሁንም ራሷን እየሰበቀች ግራና ቀኝ ስትገላመጥ በእስረኝነት የምትጓዝ ሳይሆን፣ በአንድ ከፍተኛ ዙፋን ላይ ተቀምጣ ሕዝቡን የምትዳኝ ታስመስለው ነበር፤

ከአጠገብዋ ሲደርሱ የታንጉት ልብ በኃይል ይመታ ጀመር። ዐይንዋ እንደ ችካል፤ በተለይ ከእስተርን ላይ ተተክሎ አብሮ ተጓዘ። እስረኞቹ ከቆመችበት ፊት ለፊት ደርሰው ከእስተርን ጋር ዐይን ለዐይን ሲወጋጉ። ራስዋ ራስዋን እስክትታዘበው ልብዋ ስንጥቅ አለባት። ሰላምታ በመስጠት አኳኋን አንገቱን ላመል ያህል ቀልበስ አረገ። ዐይኑ በእርሷ ላይ ብዙ አልቆየም ነበር። ለታንጉት ግን ዝንተ ዓለም መስሎ ተሰማት። ከዐለፉ በኋላ ስንኳ ከጀርባው በኩል ስትመለከተው ዐይኑ እንደ ተተከለባት ሆኖ ይታያት ነበር። ምናልባት ሌላው ሰው የተለየ አስተያየት አላስተዋለበትም ይሆናል። ታንጉት ግን ዕድላቸውን በቅርብ ጊዜ እንደምትጋራ በመንፈስ የነገራት ይመስል የአዘኔታ ወይም የክስ አስተያየት የነበበችበት መሰላት። ታንጉት ያልተገነዘበችው ከእስተርን ጋር ዐይን ለዐይን ሲገጣጠሙ ሚስስ ሮዜንታል አይታ በፌዝ ፈገግ ማለቷ ነበር።

የታንጉት ዐይነ ሕሊና ከእስተርን ጋር አብሮ ሔዶ ስለ ነበር ቴዎድሮስ ከጦር አለቆቻቸው ጋር በአጠገብዋ ሲያልፉ፣ ገብርዬ ከፈገግታ፣ ጋር ጠቀስ ሲያደጋት አስተውላ አላየችም። በገመድና በጠፍር በመቀናጆ ወይም በነጠላ ታሥረው በእግራቸው እየተጓዙ የመጡት፣ በዘመቻ የተማረኩትና በሌላም ወንጀል የተያዙት ኢትዮጵያውያን እስረኖች ነበሩ። ከእነዚህም እስረኞች መካከል ታንጉት በሚገባ ያላየችው፣ ማልባት ዐይንዋ ዐርፎበትም ቢሆን ያላስታወሰችው አንድ ሰው ነበር። ከሚስዮኖቹ ቤት አብሮ የተያዘው ደብተራ አክሊሉ። ልም ዐይኑን አጨንቁሮ ከግር እስከ ራስዋ ከመረመራትና ከገመገማት በኋላ ንቀትም፣ ፌዝም አዘኔታም በተቀላቀለበት ዛቻ ራሱን ላይና ታች እያወዛወዘ ዐለፋት።

የታንጉት ሐሳብ፤ እንደ መጅ የሚመላለሰው በጥቂት ጥያቄዎች ላይ ነበር። ‹እስተርን ተናግሮባት ይሆን?› ምን ምን አለችኝ ብሎ? እስከ አሁን ካላተናገረስ ወደ ፊት ሲያስጨንቁት ማውጣቱ ይቀራል? ቴዎድሮስስ ምን ያደርጋት ይሆን? ታንጉት እነዚህን ጥያቄዎች መልሳ መልሳ በአእምሮዋ ውስጥ እያማሰለች፤ እንደ ተለመደው ቴዎድሮስን ተከትላ ወደ አዳራሹ በመግባት ፈንታ ደንገጡርዋ በለጡ በመገረም እየተከተለቻት ሳይታወቃት ወደ ቤትዋ አመራች። የታወሳት ከረጅም ጊዜ በኋላ ነበር። ግብር ከገባ በኋላ ደግሞ፤ አዳራሽ መግባት የባሰውን መጋለጥና የቴዎድሮስን ቁጣ መጋበዝ ሆኖ ተሰማትና እንድያውን ቀረች።

«ምን ሆነሻል ታንጉት? አሞሻል?» ስል ገብርዬ ጠየቃት። ከግብር ተመልሶ ቤት ገብቶ ከተሳሳሙ በኋላ።

«ደኅና ነኝ!» አለች ቅዝዝ ባለ አነጋገር።

«ዛዲያ ምነው?»

«ምኑ?»

«አዳራሽ ያልነበርሽው!»

«ታንጉት መልስ ስትፈልግ፤ «ቴዎድሮስ ‹የት ሔደች?› ብሎ ስላንቺ ጠይቆ ነበር» አላት አከታትሎ።

«ለቅጽበት ዐይን ከው አለች። «ምነው በደኅና?»

«እህ! ሲያጣሽ ጊዜ ነዋ! ታውቂው የለ የሱን ነገር። እንኳ ሁነኛ ቀራቢውን ሌላውንም ቢሆን ዐይኑን ያስተውላል።»

«አይ! ድንገት ‹አምሟት ይሆን?› ብሎ ጠየቀና ‹ኧረ አደባባይ አሁን ነበረች› ሲባል ጊዜ ‹ትጠብቅሃለች፣ ቶሎ ሒድላት› ብሎ ቀለደብኝና መልሶ ተወው።

«እንግዲያው አልተቆጣማ» ስትል መልሳ ጠየቀች፤ በሥጋትና በተስፋ መኻል እየዋለች።

«ምን አስቆጣው! አንቺ ግብር ስለ ቀረብሽ? ብቻ ካለወትሮሽ።»

«የማታው ጀንበር ግንባር ግንባሬን ስለ መታው በውሃ ላቀዘቀዘው ብዬ መጣሁና በኋላ ጥሼ እንዳልገባ ደግሞ» ትከሻዋን ነቅነቅ አደረገች። «የሚጠጣ ላምጣልህ?»

«መጠጥስ ጠጥቻለሁ። ግን ያንቺን እጅ ደግሞ ናፍቄአለሁ።»

«ፈረንጅ እስረኞችንም አመጣችኋቸው» አለች ታንጉት ጠጁን ቀምሳ ስትሰጠው ፍንጭ ፍለጋ።

«ዛዲያ የት እንተዋቸው?»

«የማታማልዷቸውና አገራቸው የማይሔዱ?»

«አይይ! አባ ታጠቅ አምርሮባቸዋል።»

«እስተዚህ መጥፎ ሥራ ሠርተዋል?»

«ሲሰድብ ማን ደስ ይለዋል? በተለይም አባ ታጠቅ!»

«ምን ብለው ተሳደቡ?»

«ዘሩ እንዲህ ነው አስተዳደጉ እንግዲህ ነው፣ ዐመሉ እንዲህ ነው፣ ልትደግመው ማንቆርቆሪያውን እያመጣች።

«ይኸን ሁሉ ምን አመጣው? አገርን ከመምራት ችሎታውና ከበጎ ተፈጥሮው ጋርስ ምን አገናኘው?»

«እና በጣም ተናዱዋል ማለት ነው» አለች ታንጉት ለሦስተኛ ጊዜ።

«በፈረንጆቹ ላይ ስንኳ አሁን ትንሽ በረድ ያለለት ይመስላል። እንዲያውም ዛሬ አብረውን አዳራሽ ግብር እንዲበሉ ተደርጓል። ዛዲያ ምን እያለ ቀለደባቸው መሰለሽ? የተራበውን መንገደኛ ታሪክ አወጋላቸው። ‹አንድ የራበው መንገደኛ ከባቄላ አዝመራ እሸት ደረሰና ባለቤቱ የግዜር መንገደኛ ብሎ ጋበዘው። ያን መንገደኛ ከረሃቡ የተነሣ መጀመሪያ እንደ ከብት ከነቆረፈዱ ጎለጎሉ። ሆዱ ትንሽ ጋብ ሲል እየፈለፈለ መብላት ጀመረ። አንድያውን ጥጋብ ሲሰማ ደግሞ የውስጡን ሽፋን እየላጠ መዘባነኑን ሲጀምር ባለቤቱ ሰውዬ ‹ብል በቃህ፣ እህል አታበላሽ ሲል አሰናበተው› ሲል ነገራቸውን ‹እናንተም መጀመሪያ እንደ መጣችህ ትሕትና አሳያችሁ። ቀጥላችሁ ትንሽ ጠገብ ስትሉ በሀገሬ ጉዳይ እየገባችሁ መፈትፈት ሞከራችሁ። አሁን ደሞ ይባስ ብላችሁ እኔን በማዋረድ ያገሬን ክብር ለመግፈፍ ቃጣችሁ› አላቸው፤ እንደ መሣቅም እያለ። ብቻ እኔ የምፈራው......»

«እህ?»

«ሰውየውን አያርገኝ?»

«ማን ሰውዬ?»

«አባ ታጠቅ እኮ በፈረንጆቹ ሳይሆን የባሰ የተናደደው እኔን የሚጠላ እኔ መጉዳት የፈለገ አንድ ያገሬ ክፉ ሰው መኖር አለበት የነገራቸው ብሎ ነው። ያንን ማግኘት ነው የሚፈልገው።»

«ዛዲያ የሚያገኘው ይመስልሃል?»

«ይዋል ይደር እንጂ የት ይቀራል ብለሽ? አባ ታጠቅን ታውቂዋለሽ። ያሰበውን ካላደረሰ እንደማይተው።

«ምን ሊያረገው ነው ቢያገኘው?»

«አሆሆ! ትጠይቂያለሽ? አባ ታጠቅ ባገሩ ክብርና በናቱ አጥንት ከማለ ስታውቂው!»

ታንጉት፣ የጉዳዩን ከባድነት ቢታወቃትም በውሃ ጥም የሚሠቃይ መንገደኛ በጠራ የቢጋ ወራት ድንገት ዝናም ይጥላል፣ ወይም ጭው ባለ ደረቅ በረሃ ምንጭ ይገኛል፤ ብሎ የእሳቤውን እውነት በተስፋ እንደሚሸፈን ሁሉ ከጭንቀቷ የተነሳ የጠበቀችው መልስ ጭንቀቷን የሚያቃልል ዐይነት ነበር። የገብርዬ አነጋገር ግን በጭንቀቷ ላይ የባሰውን በድንጋጤ መታት። ሳይታወቃት የቴዎድሮስን ቅጣት የምትከላከል ይመስል ሰውነቷ ሲነዝር፣ የያዘችው ማንቆርቆሪያ ከእጅዋ ወድቆ ሲደፋ የተረጫጨው ጠጅ የገብርዬን ልብስ አርከፈከፈከፈው።

«ውይ!» አለች በድንጋጤ ባንና እንደገና በመደንገጥ። ገብርዬ በበኩሉ ያልተለመደ ተግባርዋ አስደንግጦት ኩታውን እያራገፈ ብድግ ብሎ በሁለት ክንድዋን ድግፍ አድርጋት። «ምን ሆንሽብኝ ዛሬ ታንጉት?» ታንጉት ልጅ ለመውለድ ባላት ብርቱ ጉጉት ተዚህም ተዚያም ስትል ያልሆነ መድኃኒት ትወስዳለች የሚል ሥጋት አለው።

«ደኅና ነኝ። እንዳልኩህ ፀሐይ ነው» አለች በእጅዋ ግንባርዋን እያሻሸች።

«ተይ! ሌላ እንዳይሆን» አላት ዘለፍለፍ ያለ ሰውነቷን ደግፎ ወደ አልጋው እየወሰዳት።

«ደሞ ምን በሽታ አለብኝ ልትል ነው!» አለች ከድንጋጤዋ መለስ ብላ በቀልድ ቁጣ ዐይነት።

«ኧረ! ኧረ! አንቺ ጤና ሁኚልኝ እንጂ ምን ገዶኝ?» ጨርቅ ቢጤ በውሃ ነክሮ ከግንባርዋ ላይ አደረገላት።

«ደኅና ነኝ እኮ አልኩህ! የፀሐዩ ትኩሳት ነው። አሁን ይሻለኛል» አለች ታንጉት ከራስዋ አጉልነት ዐልፎ ዐልፎ ገብርዬ ሐሳብ ላይ በመጣልዋ እያዘነች አቃልላ በመናገር።

ገብርዬ ግን፤ ታንጉት ደኅና እንቅልፍ የወሰዳት ከመሰለው በኋላ ከቤቱ ታዛ ተቀምጦ ማሰቡ አልቀረም።

ገና በቋራ በረሃ ሳሉ፤ ቴዎድሮስ ያሳየው ሕልም ያመለከተው ዓላማ የፈነተቀበት ተስፋ፣ ያሳደረበት እምነት እያማረ፣ እየሠመረ ሲመጣ ቆይቶ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቴዎድሮስን እንዳስከፋውና እንዳሳዘነው ሁሉ፤ ገብርዬንም ግን እያሰኘው ሔዷል። በየጊዜው ያልታሰበ አዲስ ሁናቴ ይፈጠራል። የሰዎች ዓመል እንደዚሁ

እየተለዋወጠ አስቸግሯል። የታመነው ይከዳል። የተሾመው ክብር ማዕረግ የተሰጠው ይሸፍታል። ብርቱ ባለጋራ የነበራት፣ ተመሳጥረው ተሻርከው ይገኛል። ወዳጆች በድንገት ይጣላሉ። የታሰበው የማይነካበት ያልታሰበው የሚሆንበት ጊዜ ሆኗል። ይህ ጠቅላላ ግልብጥብጦሽ፤ ከአሁን ከታንጉት ሁናቴ እንዲሁ ብቻ ሐሳብ ያዘው።

ሐሳብ እንዲቀለው ወይም ሐሳቡን እያብላላ ወደ መስከ ሲናፈስ ቆይቶ ሲመለስ ግን ታንጉት እንድ ወትሮዋ ነቃ ብላ፤ የራቱ ድግስ ቤቱን ሲያውደው አገኘ።

ደስ አለው። ራት ተበልቶ የመኝታ ሰዓት እስኪደርስ ጊዜው ተንተተበት።

ገብርዬ ወደ መጀመሪያ ገደማ ላይ እንደ መገረም አለው። ገበታ ተነሥቶ የምሽቱ ጣጣና ጉዳይ አልቆ ሠራተኞች ወደ የማደሪያቸው ተሠርማርተው ገብርዬና ታንጉት በእልፍኝ ውስጥ ብቻቸውን ከትልቁ የጠፍር አልጋቸው ላይ ተኝተው ነበር። ዕንቅልፍ ገና አልወሰዳቸውም። በተለይ ለገብርዬ የዕንቅልፍ ሰዓት አልነበረም። የበላውና የጠጣው ሰውነቱን ተስማምቶታል። ስሜቱን አሙቆታል። በዚህ ላይ የብዙ ወራት ናፍቆቱ አለ። ገብርዬ ዘመቻ ሲሔድ እንደ ቆራቢ የተፈጥሮ ፍላጎቱ አከፋይ እንደ ሆነ ባይመስልም፤ ከታንጉት ጋር እስኪገናኝ ሁልጊዜ እንደጓጓ ነው። እንደ አዲስ ፍቅረኛ ገላዋን ከዕቅፉ ውስጥ ለማስገባት ይቸኩላል። ወዝዋን ይጠማዋል። እርሷም እንደዚሁ ነው የምትጠብቀውና የምትቀበለው። አሁንም በዚያው ዐይነት ስሜት ያሻሻታል። ይዳብሳታል። ሳም፤ ዕቅፍ ጭምቅ ያደርጋታል። ነገር ግን ታንጉት የፍላጎቱ ፍጻሜ የስሜቱ አስተናጋጅ እንጂ እንደ ወትሮው እኩል ተካፋይ አለመሆንዋ ያስታውቅ ነበር። ድም ሆኖ ሲቀርባት ነበልባል ሆኖ ትቀበለው የነበረውን ያህል፤ አሁን ታዛዥ ገላ ብቻ ሆነችበት።

«ምን ይሻላል ታንጉት» ሲል ጠየቃት የስሜት እሳቷን አለማቀጣጠል በሁለመናው ሞክሮ ሲያቅተው፣ ስሜቱ ድንገት እንደ መቀዝቀዝ ሰውነቱ እንደ መሸማቀቅ እያለበት።

«ምን አጠፋሁ» ታንጉት ቅር ልታሰኘው አስባ አልነበረም። ራስዋም ቢሆን መደሰቱን አትጠላውም ነበር። ነገር ግን ‹ልብ ካላየ ዐይን አያይም እንዲሉ፤ ሐሳብዋ በጭንቀት የተንጠለጠለው ወደ ፊት ከሚጠብቃት ዕድል ላይ ስለሆነ፤ ለፍቅር ጨዋታ ስሜቷ ሊነሣሣ አልቻለም። ሁናቴዋ እንደ ፈትል እንደ ስፌት እንደ ምግብ ዝግጅት የማይቀር ተግባር የማከናወን ዐይነት ነበር። ገብርዬ መገንዘብ አላቃተውም።

«ተለወጥሽብኝ!» አላት።

«ምን ሁኘ?» ስታነጋግረው ስንኳ አእምሮዋ የሚያውጠነጥነው ሌላውን ጉዳይ ነበር።

«እኔ እንጃ!» በጣም ቀዘቀዝሽብኝ!» አሁንም በዳበሳ ሊያሟሙቃት ሞከረ።

«ትኩሳታሟን አግኝተህ ይሆናል!» ታንጉት ሐሳብዋ በጭንቀትና በንዴት መካከል ተወጥሮ ስለ ነበር የተናገረችው ሳታስበው በድንገት ነበር።

«ምን?» እንደዚህ ስትናገረው የመጀመሪያ ጊዜ ነበር ገብርዬም ንዴት ብልጭ አለበት።

መልስ አልሰጠችውም።

«እህ ‹ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች› እንደሚባለው ከመንደር አውደልዳይና ጋለሞታ ጋር እየዋልሽ ዐመል አወጣሽ?»

ይህንን ሁሉ ጣጣ ያመጣባት ገብርዬ ይመስል ጭንቀቷ ወደ ንዴት ተለወጠ። «ጋለሞታ? እንዲያ እንጂ። ይኸው ነበር የቀረኝ!» ከተጋደመችበት ወደ ዳር ፈቀቅ አለች።

«አንቺው ትያለሽ፤ እኔ አልወጣኝም!» ገብርዬ መገረሙና መናደዱ ባሰበት።

«እኮ እኔ ጋለሞታ?» እንደ ማልቀስ ቃጣት።

ገብርዬ ጥርሱን አፋጨና መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ።

«እህ? ጋለሞታ?» እርሷም በንዴት ጥርሷን አፋጨች።

«እሁንስ እንዲያውም ምላስሽ ከጋለሞታ ከረፋ!» አለ ገብርዬ ከተጋደመበት በመወራጨት ዐይነት እንደ መቀመጥ እያለ።

«ከርፋታም? እኔ ነኝ ከርፋታም?»

ግብርዬ በጥፊ ሊመታት ከቃጣ በኋላ እጁን ሰብሰብ አደረገ። «ወይ ጀርሽ ደንቁሯል ወይ ጠበል ሒጂ!»

ታንጉት፤ በነገርዋ ሁሉ ክል እንዳልሆነች በአንድ በኩል ይሰማታል፤ ሁለቱም በክንዳቸው ላይ የተደገፈው ቀና በማለት ለአንዳፍታ ተፋጠጡ።

ሲተያዩ ገብርዬ ምንም እንዳልበደላት ይታወቃታል። ግን የምትናገረውን መቆጣጠር አልቻለችም። «እኮ እኔ ጋለሞታ?» እኔ ደንቆሮ!» አለች በጩኸት።

«ታልሽ አዎ! ነሽ! አላት ገብርዬ በብሽቀት።

«አዎ ነሽ!?» ታንጉት መልሶ እንዲያስተባብልላት የፈለገች መሰለች። የሚመልስላት ግራ ገብቶት ተወው።

« ‹አቶ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ› አሉ። ተዚህ ሁሉ ሒጂልኝ። በቃሽኝ ብትል አይቀልም?» አለችው ታንጉት ጠብ የመፈለግዋ ስሜት እየገፋት።

«ግድ ያለህ የለ?»

«ኧረ በስማም በይ ሴትዮ!»

»ሴትዮ አትበለኝ! ስም አለኝ! ወይስ ስሜንም አስጠፉህ?»

«እነማን?» አለ በመገረም ዐይነት።

«እነማን ብዬ ስንቱን ልቁጠርልህ? በየምትዞርበት የምትገልበውን ቀሚስ ራስህ ነህ የምታውቀው!!»

ገብርዬ በንዴቱ ላይ ሣቅ መጣበትና ከት አለ። ‹አዲስ ሁናቴ ያሳየችው በቅናት ምክንያት ከሆነ መቸስ ምን ይደረጋል? እንዳመጣጡ መቻል ነው እንጂ!› የሚል ሐሳብ መጣበት። ከዚያ በፊትም ዐልፎ ዐልፎ የቅናት እሳት እየተጫተባት የተቆጣችበት የተብሰከሰከችበት ጊዜ አለ። ታዲያ የፍቅር ጨዋታው ዕቅፉቱ ማባበሉ ዳበሳው ወዲያው ይመልሳት ነበር። በአነጋገርም እንደዚህ ሆና አታውቅም ነበር።

‹ከመካንነቷ ጋር ዕድሜዋ እየጨመረ ገላዋ እየላላ ሲሔድ የበለጠ እየተሰማት ይሆን? ወይስ የተገላቢጦሽ የራስዋን ጉድ ለመሸፈን ሰበብ መፈለጓ ይሆን? ራሱ ከስንት አንድ ጊዜ በርሷ ላይ እንደሚሔድ ምናልባት ታንጉት በድንገት ተወሳልታ ሊሆን ይችላል። ግን ለብዙ ዓመታት በሚያውቀው ጠባይዋ ታንጉት እስከዚህ ትከፋለች ወይም ይህንን የመሰለ ተንኮል ታሰባለች› ብሎ መገመት አስቸገረው።

«ሲሉ ሰምታ፣ ዶሮ ሞተች ከጢስ ገብታ አሉ› አለ ገብርዬ እንደ ዋዛ።

«እንዴት? ለወግ ለማዕረግ የማትበቂ ምናምንቴ ነሽ ማለትህ ነው?» ስትል እንደገና ተወራጨች በስሜቷ ከቴዎድሮስ ጋር የተፋጠጠች ይመስል።

«የለም። ዘመቻ ባደከመው እንደኔ ባለ ሽማግሌ፤ ምን ይቀናል ማለቴ ነው» ሲል መለሰላት ነገሩን ለማብረድ። «አጉል ላለመጠራጠር ደግሞ ቀርቦ ዕርፍ ማለት» ሲል አከለ።

«እንዲያ ነው!» አለች ታንጉት በማሽሟጠጥ።

«ወትሮውንም ቢሆን እኔ እምቢ አላልኩ።»

«እኔ ነኝ ዛዲያ?»

«እምቢ ባትይም ፈቃደኛነትሽን ወይም መፈለግሽን አላሳየሽም ነበር።»

«እህህ!» አለች ታንጉት በምጸት አነጋገር። «የሰው ኃጢአትና ኩነኔ ማን አከብጅ አለኝና!» - ‹አንተም ቴዎድሮስ አንድ ናችሁ› አለች በሆድዋ።

«እንዴት?»

«ቆረቡ የተባሉትን ባሎች ጉድ እያየነው።»

«እነማንን ልትይ ነው?» ገብርዬ ቁጣውን ለቅጽበት እንደ መርሳት ብሎ በጓደኞቹ ላይ የሚወራውን ሐሜት ለማወቅ ፈለገ።

«ምን ስም አስቆጠረኝ!»

«ውሸት!»

«ምን አስዋሸኝ! ዙፋን መጋራት የቀራቸው የደብረ ታቦር ቅምጦች ይመሰክሩታ?» አለች ፍርጥም አድርጋ ፍርሃቷን በዚህ በቀሏ የምትወጣው ይመስል።

«ምን?» አለ ገብርዬ እንደገና በጩኸት። የነገሩዋ ዳር ዳርታ ወዲያው ታይቶታል። «አባ ታጠቅን ማለትሽ ነው?» አለ ጥርሱን ቅርጭም አድርጎ።

«አልወጣኝም።»

«ነው እንጂ! የተንኮለኛው ነገረኛው ምላስ ሁሉ የተነሣበት በሱ ላይ ነው።»

«እና እኔ ተንኮለኛ!» አለች ታንጉት ቀበል አድርጋ።

«የሚሉትን ሰምተሽ ይሆናል ማለቴ እንጂ አንቺን አላልኩም። እሱስ ቢሆን በሰው ሚስት ላይ አልተገኘ? ደግሞም ተዋበች ተሞተች በኋላ ቁርባኑን አፈረሰ አይባልም። ተጥሩ ወርቅ እስታልቆረበ ድረስ። ምኑ ተመችቶትስ ይቁረብ?»

«ወትሮውም እንዳይሆን እንዳይሆን ነው፣ የተፈጥሮ ዓመል ሰበብ ነው የሚፈልገው» ታንጉት የድፍረት ድንበር መዝለልቃ ገና ተናግራ ሳትጨርስ ነበር የታወቃት። ግን እንደ እሳት እራት ጭልጥ ብላ ገባችበት።

የድፍርት አነጋገርዋ የሚያስከትለውን ውጤት ለማሰላሰል ገብርዬ ፋታ አልሰጣትም። በጦር እንደ ተወጋ ያህል «እ!» ብሎ ሲጮህና በቃሪያ ጥፊ ሲለጋት አንድ ሆነ። ከድንጋጤዋ የተነሣ አልጮኸችም። ድርቅ እንዳለች ቀረች። ገርብዬም ቢሆን መዳፉ ከጉንጭዋ ጋር እንደ ተላተመ፤ ድንገት እሳት ውስጥ የገባ ያህል ድንጋጤ መላ ሰውነቱን ነዘረው።

ከዚያ በፊትም ቢሆን ስታጠፋ ወይም ስታናድደው በምር ቀጥቷታል። እንደ ልጅ በቁንጥጫና በበለቅ ቢጤ እንጂ የቃሪያ ጥፊ ቀርቶ ደንደን ያለ በትር አሳርፎባት አያውቅም ነበር።

ታንጉት በአንዳች የስሜት እንቆቅልሽ አዲስ ዐይነት የድፍረት አነጋገር እንዳመጣች ሁሉ የገብርዬም የቅጣት ልማዱ የተለወጠበት ሳያስበው ነበር። ወዲያው ጥፊው ባረፈበት በኩል በአፍንጫዋና በከንፈርዋ በጋጠሚያ ደም ሲመነጭ ማየት አላስቻለው አለና፣ ፈትቶ ከራስጌው አጠገብ አስቀምጦት የነበረው ድጉን እንድትጠርግበት ሰጥቷት ከቤት ወጣ። ከታዛው ሥር የቤቱን ግድግዳ ተደግፎ ሐሳቡ በንዴትና በጸጸት መካከል እየተንገላታ በዚያ ዐደረ።

ወደ ማታ ገዳማ፤ ጥጥ ስታባዝት የነበረችው የታንጉት ደንገጡ እየተቻኮለች ገባችና፤ «መጡ! መጡ! አለች።

«እነማን?» ስትል ታንጉት በቅሬታ ጠየቀች።

እንግዳ እንዲመጣባት ያልፈለገችበት ምክንያት ነበራት። ጧት ገብርዬ ውጭ ዐድሮ በባዶ አፉ ወደ አደባባይ እንደ ሔደ ነበር። ትንሽ በተረጋጋ መንፈስ ማታ የሠራችው ጥፋት እየታወቃት የሔደው። ለፍቅር ጨዋታው ሰውነቷ ሊሟሟቅላት ባይችል በነበረባት ሐሳብ ሊፈረድባት አይገባም። ስሜቷ አልታዘዝ ካላት ምንም ማድረግ አትችልም ነበር። ግን ገብርዬን በነገር መጠዝጠዝዋ ምን ይባላል? ገብርዬ አልበደላትም። የጭንቀቷ ምንጭ ሌላ ነው። ጉዳዩን ጨርሶ በማያውቀውና በማያገባው በገብርዬ ላይ ብስጭትዋን መወጣት ‹አህያውን ፈርቶ መደላድሉን› እንደሚባለው ዐይነት መሆኑ ነው። ችግሩ፤ አግባብ አለመሆኑ በወቅቱ አልታያትም ነበር። ለጊዜው የተሰማት በቅርብ ባገኘው በገብርዬ ላይ ብስጭትዋን ለመወጣት መሞከርዋ ነበር።

በበነጋው፣ ወደ ኋላ ተመልሳ ጎዘንና ጸጸት ተሰማትና የፈሰሰ ውሃ እንደማይታፈስ ሁሉ፤ እንደገና ሆድዋ ልትውጠው ባትችልም ገብርዬ ማምሻውን ሲመጣ ማታ በአነጋገርም ላደረገችው ጥፋት እንዳይቀየማት ለመለመን፤ ስሜቷ በፈቀደላት መጠንማ በፍቅር ጨዋታ ለማስደስት ወስና ውላ ነበር።

መካሻ ይሆን መስሏትም የሚወደውን የቋንጣ ወጥ ራስዋ በጥንቃቄ ክሽን አድርጋ ሠርታለች። የሚያመሻሽ እንግዳ ይዞ ከመጣ ግን ለምትፈልገው የርጋታና የግል ጭውውት ሁናቴው ላያመቻት ነው። ‹የዛሬን እንግዳ ባይጎትትብኝ ምን ነበረበት› እያለች በሆድዋ አጉመተመተች።

‹አባ ታጠቅና ገብርዬ ናቸው!› በማለት ደንገጡርዋ ስትመልስላት፤ ታንጉት ድንገት በመብረቅ እንደ ተመታ ነገር ድርቅ አለች። ልብዋ የተተረተረ መሰላት። ቴዎድሮስ ከገብርዬ ሆነ ከሌሎች ባለሟሎቻቸው ቤት ዐልፎ ዐልፎ መሔዳቸው የተለመደ ቢሆንም አስቀድሞ ያሳውቃሉ። ለባለሟሎቻቸው ‹ነገ ታንተ ቤት ነው ምሳዬ› ሲሉ ይናገራሉ። ሚስቶቻቸውን ‹እስቲ ዛሬ ራቴን አብይኝ?› ሲሉ በቀልድ መልክ ይጠይቃሉ፤ ወይም ደግሞ ‹ራቴን የምበላው ተናንተ ዘንዳ ነው› በማለት ይልካሉ።

ከባለሟሎቻቸው ቤት ሔደው መጋበዝ የሚፈልጉት ደስ ባላቸው ጥቂት መዝናናት በፈለጉ ጊጌ ነው። በእንደዚህ ያለ ጊዜ ጨዋታቸውና ቀልዳቸው ሲያስደስት ሌላ ነው።

አሁን ድንገት መምጣታቸው ግን፤ ለፈራችው ነገር መሆን አለበት። ቁጣቸው እንደ ወላፈን ሲጋረፍ ተሰማት። ለሚወርድባት መዓት እንደ መዘጋጀት ገላዋን ኩምትር፤ ጥርሷን ቅርጭም አደረገች። በጭንቀት ብዙ ጊዜ ከማማጡ እንደዚህ በቶሎ ለቁርጠኛው መቅብረ፤ እንደ መገላገል ሳይሆንላት ይቀራል? ታንጉት ዐይንዋን ከደን አድርጋ በአፍንጫዋ በሰፊው ተነፈሰች። «ኧረ ድግስም አብሮ አለ?» የሚለው የደንገጡሩዋ ድምፅ የተሰማት እንደ ሰመመን በሩቅ ነበር።

«ምን?» ስት ታንጉት ጠየቀች፤ ድንገት በመባነን ዐይነት።

«አዎ! መሶብም፤ ገምቦም የተሸከሙ ሰዎች ይታዩኛል።

ታንጉት ራስዋው ለማረጋገጥ ወደ በራፍ ወጣችና ተመለከተች። መቀመጫዎቹን በጥድፊያ ስታሰናዳ አእሮዋ ልዩ ልዩ መላ ምቶች ያተራምስ ገባ። የትናንት ማታውን ገብርዬ ነግሮት፤ ‹አንቺም መጥፎ አትናገሪ። አንተም አትምታት› ብሎ ሊያስታርቀን ይሆን? ዕድሜ ልኩን ደብቆት የኖረውን ምሥጢር ለባለሟሎቹ በይፉ ሊገልጸው ይሆን? ባለሟሎቹ ካወቁትማ ወዲያው ለድፍን ኢትዮጵያ ይደርሳል። ከዚያ በኋላ ታንጉት በአዲስ ዐይን የምትታይ ትሆናለች። ዛዲያ ይህስ መሆኑ ከሌላው ሥጋቷ ያድናታል? የቴዎድሮስን ጠባይ ስለምታውቀው ያጠራጥራል። ቴዎድሮስ ካልመሰለው ለማንም አይመለስም። የሚያድናት ከሆነ

የገብርዬ ሚሽት መሆንዋ ብቻ ይብቃት ነበር። ታንጕት ስለ አመጣጣቸው ደግ ደጉን ለማሰብ ትፈልግ እንጂ ከሥጋቱም አልወጣችም።

ቴዎድሮስ እንደሆኑ አንዳንድ ጊዜ የሚሠሩት ሁሉ ፈጽሞ ያልታሰበና የማይመስል ነገር ነው። ለምሳሌ፤ አንድ ጊዜ ጥቂት ወስላቶች ተሰባስቡና ፊታቸው ቀርበው እጅ በመንሣት ‹ሁሉም በየሙያው እየገባ ይኑር በልው ዐውጀዋልና እኛም በሙያችን አንድንተዳደር› በለው ይለምናሉ። ‹ሙያችሁ ምንድን ነው?› ብለው ይጠይቋቸዋል። ‹ሙያችንማ፤ ቤት መሰርሰር ጎተራ መስበር ከብት መንዳት ነበር። ሌላ ሙያ አናውቅም› ሲሉ ይመልሱላቸዋል። ቴዎድሮስም የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው፤ ፈገግታ በማሳየት፣ ‹መልካም ነው። ግን እናንተ ብቻ አትመስሉኝኝ በዚህ ሙያ የምትኖሩት። አነሳችሁብኝ። ስለዚህ ሁላችሁም ተሰብስባችሁ ብትመጡ መልካም ነው› በማለት እንዲመለሱ የሚያደርግ የጉርሻ መላሻ አቅምሰው ያሰናብቷቸዋል። እውነት መስሏቸው ተፈላልገው በብዛት ተንጋግተው ሲመጡላቸው ግን ዋጋቸውን ሰጧቸው። በአንጻሩ ደግሞ በምትዋብ ላይ የፈረዱትን ታንጕት ታውቃለች። ማንነቷን በኋላ ታንጕት እንዳጣራችው የደጃማች ኃሉ ልጅ የሆነችው ምንትዋብ በልቅሶ ላይ ያወረደችውን ዘለፋ፤ ዐይንዋን ሳታሽ እንደገና በቴዎድሮስ ፊት ድግመው ምሕረት ተደርጎላት ቀለብ ተሠፍሮላት ቀለቧን እየበላች አሁንም እንደ ጥላ በመከተል የስድብና የዘለፋ ግጥሟን እንዳወረደችባት ትገኛለች። እስከ አሁን ዝንቧን እሽ አልተባለችም።

የታንጕት ጉዳይ ከምንታዋብ የተለዬ መሆኑ ይታወአቃል። ‹ዛዲያ ምንትዋብ የተበደለች መሆንዋ ታውቆላት፤ ከሙሉ ምሕረት ጋር ቀለብ እንደ ተሰፈረላት ሁሉ እሷን ደግሞ የተገላቢጦሽ እንደ ፍታት እንደ ተዝካር በድግስ ሊፈርድባት ሊቀጣት እንደ ሆነስ ማን ያውቃል? እንግዲህ ያጠበው ይፈንዳ!› ታንጕት በሆድዋ ጥርሷን ቅርጭም እንዳደረገች።

የቴዎድሮስ ድንገተኛ ጉብኝት ገብርዬንም በአእምሮ ውስጥ ጥያቄ አሳድሮበት ነበር። ‹ትናንት ማታ በጥፊ ከፉኛ እንደ መታት ሰምቶ ሁናቴዋን ለማወቅ ይሆን? ቴዎድሮስ በየቦታው የሚሆኑትን ዝርዝር ነገሮች ሁናቴዋን ለማወቅ ይሆን? ቴዎድሮስ በየቦታው የሚሆኑትን ዝርዝር ነገሮች ሁሉ የሚያገኙበት መንገድ አለው። ደንገጡሩዋም ቢሆን ለእመቤትዋ ማድላቷ አይቀርምና ነገሩ እንዲደርስ አድርጋ ሊሆን ይችላል።› ብቻ ‹ገብርዬ ዛሬ ካንተ ጎጆ ነው የምናመሸው› ሲሉት የቁጣ ሁናቴ አልታየባቸውም ነበርና ብዙም አልተጨነቀም።

የቴዎድሮስ ምክንያት ግን፤ ከዚህ ሁሉ ጨርሶ የተለየ ነበር። እንዲያውም አንዳች ልዩ ምክንያት አልነበራቸውም። በአቅራቢያ ከሆነ ውሎ ማደር

አያስችላቸውምና ደብረ ታቦር እንደገቡ ጧት፤ ወደ ጋፋት ገሥግሠው እንደ ሔዱ ያጋጠማቸው የሥራ ውጤት ለብዙ ወራት ተጭኖዋቸው የቆየውን የቅሬታ፤ የኀዘንና የብስጭት ሸክም በመጠኑ የሚያቃልል ሆኖ አገኙት። የብረት ማቅለጫ ገንዳዎች በየመጠናቸው ተሠርተው አልቀው አንዳንዶቹ እየተቀለጠባቸው ነው። የብረት ዐፈሩ ከሩቅና ከቅርብ እየተፈለገ መጥቶ በዐይነቱ ተቀምጧል። የቅርጽ ማውጫው የሸክላ ዐፈር እንደዚሁ ዐይነት በዐይነቱ ተቆልሏል። የመጀመሪያው ዋና ችግር የቀለጠውን ብረት ሳይፈረካከስ መያዝ የሚችል ቅርጽ ማውጫ ሸክላ ማግኘቱ ነበር። በአገር የታወቀ ሸክላ ሠሮዎች ዕርዳታ ጭምር ተጠይቆ ከብዙ ጥረት በኋላ ተሳክቶላቸው መድፍ የሚመሳሰሉ ሁለት መጠነኛ ቅርጾች ለማውጣት ችለዋል።

መተኮስ አለመተኮሳቸው አልተሞከተም። ግን አስቸጋሪው ሥራ ዋናውን ቅርጽ ማውጣቱ እንጂ፤ ባሩዱን መለኮሻውን ተስፈጣሪውን እርሳስ ማሟት የሚያቅት እንደማይሆን የጋፋት ሰዎች ለቴዎድሮስ ነግረዋቸዋል። አሁንም የአንድ መጠነኛ መድፍ ማውጫ በመሥራት ላይ ነበሩ።

ቴዎድሮስ አነስተኞቹን የመድፍ ምስል ቅርጾች እንደ ሕፃን ጉንጭ በጉጉት በስስት ዐይነት ደባበሷቸው። የብረቱን ዐፈር እንደሚያስጎመዥ ውብ እህል ደጋግመው በመዝገን፤ ማየት ብቻ ሳይሆን እንደማሸተት አደረጉት። ከዚያም በመለበድና በመተኮስ ላይ ያለውን ትልቁን ቅርጽ ማውጫ፤ የአናጢውን የሸመናውን የማረሻ የማጭድ የመጥረቢያና የሌላም የብረታ ብረት መሥሪያውን ክፍል እየተዘዋወሩ ሲመለከቱ መንፈሳቸው እንደገና ተስፋ ዘራ። በሰቀቀን ጠውልጎ የነበረው ስሜታቸው እንደ መለምለም አለ። ማን ያውቃል? ዕድሜም ሰላማዊ ፋታም ካገኙ ያለሙት ሁሉ እንደ ጨለመባቸው፤ ያሰቡት ሁሉ እንደ ራቀባቸው አይቀር ይሆናል። ከሌሊት በኋላ ንጋት ይከተላል። ፈተና እንደ ምንም ይታለፋል፤ እስኪያልፍ ግን ያለፋል ያማቅቃል።

«ወትሮውንም ቢሆን በተቻለ መጠን ትረዱኛላችሁ ብዬ እምነት የጣልኩባቸው ቢሆንም» አሉ ቴዎድሮስ ጉብኝቱን ከጨረሱ በኋላ ስሜት ለመበርበር ባደረገው ድምፅ «ሠርታችሁ የቆያችሁት እጅግ አርጎ ነው ያስደስተኝ። እነዚያ የፈላሻ ሚስዮኖችማ የሠሩኝን ሰምታችሁ ይሆናል። የጃቸውን ይስጣቸው እንጂ እኔ ሌላ ምን እላለሁ መቸስ? ተልብ ለናንተም ደግሞ ውለታችሁን በገንዘብ ከፍዬ አልጨርሰውም። ለውነተኛ ውለታ እሱ ምንድን ነው? አላቂ ጠፊ። እና አሁንም የሆነ እንደሆነ የምከፍላችሁ ዋናው ዋጋችሁ የልቤን ፍቅር ነው። በተረፈ ግን የሚያስፈልጋችሁ ነገር ቢኖር እንዲረዳችሁ በማለት ያህል - » ብለው እጃቸውን እንደ መዘርጋት ሲያደርጉ አብሮዋቸው የሚዘዋወረው ግምጃ ቤታቸው ጠገራ ብር

የተቋጠረበትን ከረጢት አቀረበላቸው። ሳይቆጥሩ እጃቸው እንደ ገመረ፤ «ለጋፋት ልጆቻቸው አደሉ።

እያንዳንዱ ምናልባት ከሌላው የበለጠ ደርሶት ይሆናል። ግን ቴዎድሮስ አቆነጣጠራቸውንና አሰጣጣቸውን እንደ ዕጣ ስላስመሰሉት፤ ሁሉም በደስታ ፈካ እንጂ ቅር የተሰኘ አልነበረም። «የጋፋት ልጆች» ሕፃናት ሳይቀር አንዳንድ ጠገራ ብር ተሰጣቸው።

ከዚህ ዐይነት የረካ መንፈስ ወደ ደብረ ታቦር ሲመለሱ ነበር፤ ከገብርዬ ቤት የማምሸት ሐሳብ የመጣባቸው። ቤት ሲገቡ ጥሩ ወርቅ በተለመደ ጭፍግግ ሁናቴዋ ደኅና ፈካ ያለ ስሜታቸውን መልሳ ታጠወልግባቸው ይሆናል። ወደ አንደኛዋ እቁባታቸው መሔዱንም አልወደዱትም። በጋፋት ያዩትን ተስፋ ማርከስ መስሎ ተሰማቸው። ግድ ሆኖባቸው በግላቸው ለግላቸው የሚፈጽሙበትን ተግባር፣ ትልቅ ለሆነው ዓላማቸው ማሳረጊያ ማድረግ ቀፈፋቸው።

በዚህ ላይ እንዳስተዋሉት የገብርዬ ሁናቴ ደስ አላላቸውም ነበር። የራሳቸው ስሜት በእርካታ የፈካውን ያህል፤ ብዙ ዕንቅልፍ ሳይተኛ ከቤቱ ውጭ ያደረው የገብርዬ ፊት፤ ሐሳብ ወይም ትካዜ ቢጤ ያጠላበት ይመስላል። ሲያጫውቱት ቢያመሹ መልካም ነው። ከኅልማሳነት እስከ ሙሉ ዕድሜ፤ በደስታ፣ በመከራ፤ በድል፤ በፈተና ከታንጉትና ከገብርዬ የቀረበ ማንስ አላቸው?

«አንጓች፣ አንቺ ጉራዲቴ፣ እንዴት ሰነበትሽ? አሁንማ ኮራ ኮራ አልሽ መሰለኝ። እልፍኝ አልወጣም ማለትሽ ነው?» ታንጉት ጉልበታቸውን እንደ መሳም ቀና አድርገው ሁለት ጉንጩዋን አገላብጠው እየሳሙ።

ለደግ መምጣታችወን ገና ከሩቁ በፈገግታቸው ገምታ ነበር። አሁን አረጋገጠች። ከልጅነቷ ጀመሮ፤ «ጎራዲት! የኔ ጎራዲት» እያሉ የሚጠሩዋት በተዘናኑ ጊዜ ነው፤ ሊያቆላምጡዋት ሲፈልጉ። እስከዚህ ጎራዳም ባትሆን ለቀልድ ለቁልምጫ ያወጡላት ስም ስለሆነ ትወደዋለች።

«እግዜር ይመስገን አባ ታጠቅ። አንተስ ደኅና ነህ?» አለች ታንጉት ጭንቀቷን ድንገት ሲለቃት ገጿ ላይ ፈገግታ ተተክቶበት። ልጅ ሆናማ ጎራዲት በለው ሲጠሩዋት የኮረኮሩዋት ይመስል ሣቅ ይመጣበት ነበር።

«እንደ ጠየቅሽኝ!» አሉ በቀልድ ኩርፊያ። «ለመሆኑ ትናንት የት ጠፋሽ?»

«የት ጠፋሁ አባ ታጠቅ?» ስትል ተዝናንታ መልሳ ጠየቀች።

«ገበታ ላይ መች ነበርሽ?»

«አዎ! ወደ ቤት መጣሁ።»

«አሃ! ከሌሎች ሴቶች ጋር ባንድ መሶብ ለመቀመጥ የጎራዳ ኩራት ተሰማሽ? ቆንጆ አገኘሁ ብለህ አንተ ትሆናለህ የምታኩራራት» አሉት ገብርዬን።

«ኧረ እኔስ ፀሐይ ራሴን ስላመመኝ ነው» አለች።

«ዘመቻ ለዘመቻ ያልተንከራተትሽውን ያህል! እውነትም አዘባነሃታል ገብርዬ! ምን ማዘባነን! አበላሽተሃታል እንጂ!»

«ምን አለበት ዛዲያ!» አለች እየተደፋፈረች ሔዳ።

«እንዴት አንቺ ጎራዳ?»

«የምታመንበት ጌታ፤ የምኮራበት ባል ቢኖረኝ ነዋ!»

«አየህልኝ ይቺ ያረብ ምላጭ ሁለታችንንም ባንድነት ስትሞሽልቀን!» አሉ ቴዎድሮስ በመሣቅ።

«ደሞም፤ ‹አፍንጫ ቢገተር እንደ መግላሊት፤ በደም ይበልጡሻል እነጎራዲት› ተብሏል» አለች ታንጉት የበለጠ እየተደፋፈረች። አባ ታጠቅ ከት ብለው ሣቁባት። የውስት ስሜቷ ፈነደቀ። ‹ምነው ዛዲያ ሁልጊዜ እንደዚህ ቢሆን ምን ነበረበት! ያ ነበልባል ቁጣው ከየት ይሆን የሚመጣው› ስትል አሰበች። ራሷም ቢሆን ትናንት ምሽትና ዛሬም ሌላ ስሜት እንደ ነበረባት ለጊዜው ተዘነጋት።

እንደ ወግ፤ እንደ ሥርዓቱ ለእራት የቀረበው ድግስ ቴዎድሮስ አሲዘውት የመጡት ድግስ ነበር።

«ለእኔ ግን፤ እስቲ ያንቺን እህል ልቅመሰው። ዘበናይ መሆን ጀምረውሽ ወንድሜን ጎድተሽው ይሆናልኮ» አሉ አባ ታጠቅ በቀልድ። «አይ! እጅሽን አሁንም ደጎና ነው። አልተበላሽም» በማለት አመሰገኑዋት፤ ቁንጣውን ወጥ አንድ ሁለት ጊዜ ከጎረሱና የታንጉትን ቤት ጠላ ከተጐነጩ በኋላ።

«አጉርሽኝ እንጂ! ገብርዬም አጉርሸው! ወገኛ! መታፈሩ ነው? በይ ድገሚኝ እንዳንጣላ» ሲሏት ሳይታወቅ እንደ መንደንገጥ ልብዋ መታ አደረገ። ወዲያው ግን መልሳ ተረጋጋች። የተለመደ ዘዬ ነው።

የተዝናናው ጭውውት ከእራት በኋላም ቀጠለ። ቀልድ፤ ተረብ፤ የቀድሞ ትዝታ፤ የአንዳንድ ሰዎች አስቂኝ አድራጎት የፈሪዎችና የጀግኖች ታሪክ።

ነገር ግን በጭውውቱ መካከል ዐልፎ ዐልፎ ቴዎድሮስ የረሱት ነገር ትዝ ያላቸው፤ አዲስ ሐሳብ የመጣባቸው ወይም ከሐሳባቸው ጋር የሚግገቱ በሚመስል አኳኋን፤ ላንዳፍታ በዝምታ ዓለም ጭልጥ ይሉና በአብዛኛው አድማጭ እንጂ ተካፋይ ሳትሆን፤ ትንሽ ፈቀቅ ብላ የተቀመጠችውን ታንጉትን ትኩር ብለው ይመለከታሉ። ብሩህ ዐይኖቻቸው የጧፉን መብራት ሲያንጸባርቁ ወደ ሰው ውስጥ ሠርጸው የሚገቡ ይመስላሉ።

አሁን ግን ታንጉት አላስፈሩዋትም። የሚመራመሩ፣ ምሥሪር የሚፈልጉ ዐይነት እንጂ ቁጣ የሚፈነጥቁ አልነበሩም።

ሆኖም ጥርጣሬ እንደገና መጣበት። ‹ምሥጢሬን ለማውጣት ከሐሳቡ ጋር እየተሟገተ ይሆን? ነገሩን ሲሰሙ ሰዎች ሁሉ እንዴት እንደሚደነቁ በተለይም የእነ እንግዳና የእነ ዓለሜ ሚስቶች ከላይ ከንፈራቸውን እየመጠጡ በሆዳቸው እንዴት እንደሚሣለቁ ታያት። ከውስጥ ስሜቷ ዘገነናት። አልወጣችውም።›

«ምን ትፈልጊያለሽ ጎራዲት?» ሲሉ ድንገት ጠየቋት።

ሳታስበው ለመጣባት ጥያቄ መስል ጠፋት። «ምን ደሞ ያስፈልገኛል?» ስትል መልሳ ጠየቀች። «ሁሉም ነገር ሞልቷል።»

«የሴት ጣጣ ማለቴ አይደለም። ገብርዬ ለዚህ ከሰነፈማ ለጉድ ነው። ላንቺ ለራስሽ ደስ የሚሽል ነገር» አሏት። ዝም ስትልባቸው ጥቂት አሰቡና «ያቺን ነገር ይዘሃታል?» ሲሉ የግምጃ ቤት ባለሟላቸውን ጠየቁት።

«ምኑዋን አባ ታጠቅ?»

«ከአገው ንጉሤ ጓዝ ውስጥ ያገኘናት መስቀል።»

«ኧረ አልያዝኳትም! እንደ ታዘዝኩት አስቀምጫታለሁ እንጂ!»

«እስቲ ሮጥ ብለህ አምጣት» ሲሉ አዘዙት..... «የምትወጂያት ግሩም ጌጥ ናት» አሏት ታንጉትን.......

«ግሩም አይደለችም?» አሉ ቴዎድሮስ በመጠየቅ ሳይሆን በማድነቅ አኳኋን፤ ከግምጃ ቤት ባለሟላቸው የተቀበሉትን በከፋይ ጨርቅ የተጠቀለለ መስቀል፤ ገላልጠው በሐብሉ አንጠልጥለው እያሳዩ።

ታንጉት ልብዋ ስንጥቅ አለ።

ሐብሉ እንደ ሸረሪት ድር በረቂቁ የተሠራ ነው። መስቀሉ ከአናቱ ላይ አንድ፤ ከጎንና ከጎኑ ሁለት፤ ከመካከሉ ላይ እንደዚሁ አንድ፤ በጧፍ እንደ ኮከብ የሚያንጸባርቅ አራት ቀይ ፈርጦች አሉት። ‹እንደዚህ ያለ መስቀል የሚሠራ አንጥረኛ በድፍን ጎንደሮች መኖሩ ያጠራጥራል። የባሕር ማዶ ሥራ መሆን አለበት› ስትል ታንጉት አሰበች።

«ተየት አባቱ ነጥቆት ይሆን?» ሲል ገብዬ በመገረም አኳኋን ጠየቀ።

«ፈረሠዮቹ የላኩለት ስጦታ ወይም ያገር መግዣ ዋጋ ይሆናላ! አሁን ማ ይሙት ይኸ ለወንድ ልጅ የሚላክ ገጸ በረከት ነው? ግና እንግዲያው በሴት ጌጥ ሀገሬን እንዲሸጥላቸው ነዋ?» አሉ ከምሬት ሣቅ ጋር።

መስቀሉን ሲሰጧት እጃቸውን ዘርግተው ታንጉትም ለመቀበል ብድግ እንዳለች፤ «እንዲያውም አንተ አጥልቅላት!» አሉት ገብርዬ ሐሳባቸውን ቀይረው?።

«ባንተ ስጦታ?»

ምኑ ነው የኔ የብቻዬ የሚሆነው? የራሴን ገንዘብ አውጥቼ አላሠራሁላት! አብረን በዘመትንበት የተማረከ ነው።»

ይልቅስ እንኳ! እሷም ደስ የሚላት ታንተ ሲሆን ነው። የኔ እጅማ ለማንስ አይደል የሚሰጥ? ባሌ ገብርዬ የሰጠኝ እያለች ትኩራራበት እንጂ! አይደል ጎራዴት? ዋ! ዛዲያ ወንድሜን በሚገባ ተንከባክበሽ ያኸው። ዋ!» አሉ በቀልድ ዛቻ።

ሐብሉ ተጠልቆላት ጥቂት በመሸኮርመም ዐይነት ጉልበቱን እንደምሳም አድርጋ ቀና ስትል፤ «እህ! የአባ ታጠቅን ጫማ አስትሚም ይልቅስ! አባ ታጠቅ ስላለ፤ እውነት እኔ የሰጠሁሽ መሰለሽ ጅሌ?» አላት።

«አትስሚው» ሲሉ ቴዎድሮስ ለጠቅ አደረጉ። «ዛዲያ በይ ተነሽ እንጂ!» አሉ ታንጉት በዚያው እንደ ተደፋች ስትቆይ ጊዜ ትንሽ እንደ መገረም እየቃጣቸው።

በዚያች ቅጽበት ግን፤ ታንጉት ከራስዋ ጋር በመሟገት ላይ ነበረች። ‹እንደ አለቃና ጭፍራ ሳይሆን፤ እንደ ወንድማማች ወይም እንደ እኩል ጓደኞች በገብርዬና በቴዎድሮስ መካከል ያለው ፍቅርና መተሳሰብ፤ ሁለቱም ለእርስዋ ያሳዩት ፍቅርና ይህ ነው የማይባል ልግሥና፤ እንደ ልዩ በጥልቅ ነካው። አንጀትዋን በላው። ሣቂ፤ አልቅሽ የሚያሰኝ አንድ ልዩ ሲቃ መላ ሰውነቷን ወረራት። አንዳች ጠጣር ነገር እንደ ተሰነቀረባት ያህል ጉሮሮዋን ተናነቃት። በዚህ ስሜቷ መካከል - አሁን መንፈሱ ተረጋግቶና ተዝናንቶ ሳለ፤ ባለማወቅ የሠራሁትን ተናዝዞለት ምሕረት ብጠይቅ - «መቸስ ምን ይደረግ የኔ እኅት፤ እንግዲህ የፈሰሰ ውሃ

አይታፈስ፤ ያለፈ ዐለፈ፤ ለወደፊቱ ግና ከቶ እንዳይደግምሽ» በማለት ሳይምረኝ ይቀራል?› የሚል ሐሳብ መጣባት።

ፍርሃትዋ ደግሞ እዚያው በዚያው ተናነቃት። ‹በይቅርታ ፈንታ ያ ቁጣ ድንገት ቢፈነዳስ?› የሚል ፍርሃት። የዚች ወቅት ፍቅርና ደስታ ወደ አስፈሪ ጭንቀትና ሰቀቃ ትለወጣለች። በፈገግታ ተውጠው በነበሩ ፊቶቹ የቁጣ እሳት ይተፋሉ።

ፍርሃትዋ ተስፋዋን የሸፈነባት። ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሰፈነውን ውብ መንፈስ ድንገት መነጠቁ አሳሳት። አንሰፈሰፋት።

እንደ ብዙ ሰዓት ለረዘመ አፍታ አምጣ፤ እንደ አሁኑ በመሰለ ደኅና አጋጣሚ ሌላ ጊዜ ለመሞከር በመወሰን፤ ካጎነበሰችበት ቀና ስትል ዐይኖቿ ዕንባ አቀርዝዘው ነበር።

«በሉ እንግዲህ፤ ተበላሁ ተጠጣሁ ልሒድ እንጂ!» አሉ ቴዎድሮስ በአቆላማጭ ፈገግታ ታንጉትን እየተመለከቱ፤ «ሌላ ዘንዳ አመሸህ ብላ ጥሩ ወርቅ ደግሞ ፊቷን ኮሶ አስመስላ ትጠብቀኛለች። ሌላ ሐሳብ ያለኝ ይመስላታል።»

ታንጉት ያንን የመሰለ ሌላ ዕድል ሳያጋጥማት ቀረ።

ቆንስል ካሜሮን በምድረ ሱዳን በቱርኮች መኻል ከርሞ፤ በመጨረሻ እንድ ዋዛ መመለሱ፤ በቴዎድሮስ መንፈስ ላይ ተጨማሪ ማዕበል አስነሣ።

ቆንስል ካሜሮን፤ ያን ያህል ጊዜ ቆይቶ በመተማ በኩል ተመልሶ ወደ ደብረ ታቦር ወይም እሳቸው ወደ አሉበት ቦታ ቀጥታ በመምጣት ፈንታ፤ ጎንደር ገብቶ ከአቡነ ሰላማ ጋር መሰንበቱን ቴዎድሮስ ሲሰሙ፤ ቀደም ሲል ከደረሳቸው ወሬ ጋር ጥርጣሬያቸው ይበልጥ ተጠናከረ። የረባ መልስ ይዞ ቢመታ ኖሮ፤ ከእጁ አውሎ አያሳድረውም ነበር። የደብዳቤያቸው መልስ ለጊዜው ባይደርስለት ስንኳ፤ በጎ ፈቃድና ቅን ሐሳብ ካለው ቀርቦ ምክንያቱን ለማስረዳት ችላ አይደለም ነበር። ቴዎድሮስ ሆዳቸውን እየቆረጠው ቆዩና ደብረ ታቦር መጥቶ እጅ የሚነሣ መሆኑን በመግለስና ፈቃድ በመጠየቅ አስቀድሞ ሰው ሲልክ ከሚሠፍሩበት ድረስ መጥቶ እንዲገናኛቸው አስታውቀው ወደ ጎጃም ተሻገሩ። በሽፍታ የሚታወከውን አገር በማርጋት ፈንታ፤ ቁም ነገር ያልተሠራላቸውን አንድ የውጭ ቆንስል በሥነ ሥርዓትና በክብር ለመቀበል ሲሉ ደብረ ታቦር ተቀምጠው የሚጠብቁት ምክንያት አልታያቸውም።

ዳሞት ላይ ሠፍረው ሳሉ ደረሰባቸው።

ቴዎድሮስ፤ ከድንኳኑ ሠፈር ዳርቻ ላይ ተቀምጠው በጦር ዛቢያቸው ላመል ያህል ዐልፎ ዐልፎ መሬት እየቆረቆሩ፤ ወደ ተራራው የሚያዘልቀውን መተላለፊያ ባሻገር ይመለከታሉ። ዐሥር ሺህ የሚሆነው ሠራዊት በሠፈሩ ተበታትኖ በጠቡድኑ ተከማችቶ የዕለት ተግባሩ ብቻ የሚከናወን ይመስል እንጂ፤ በአብዛኛው ነቅቶ የሚጠብቀው ካሚሮን ሲደርስ የሚፈሰውን ሁናቴ ነበር።

የረፋድ መንገድ ርቀት ላይ ሠፍሮ ማደሩ ወሬ ደርሷል። ቴዎድሮስ እየጠበቁት ናቸው። አልባሌ ለብሰው አልባሌ መስለው ብቻቸውን እንደዚህ የሚቀጡትም ከባድ ሐሳብና ትካዜ ሲጫናቸው መሆኑን ብዙው ሠራዊት አሳምሮ ያውቃል።

ደማቅ ቀይ የሆነው የአቡነ ሰላማ ጃንጥላ፤ ከሩቅ ብቅ ሲል የሁሉም ዐይን ወደዚያው አተኮረ። ቴዎድሮስ ግን፤ ለማየት የተጠየፉ ይመስል ከተቀመጡትበ ብግድ ብለው ወደ ድንኳናቸው ገቡ። ራስ እንግዳ ሰዎቹን ለመቀበል ወደ ኋላ ቀርተው ከውጭ ጠበቁ።

ጓዝ ተራግፎ፤ መንገደኞቹ እህል ውሃ ቀርበላቸው ጥቂት ከዐረፉ በኋላ፤ ቴዎዶስ ሊቀበሉዋቸው ወጡ። ሠራዊቱ ዙሪያውን ሰብሰብ አለ። ቴዎድሮስ አንገታቸውን ቀልበስ ቀና አደረጉ። «ደኅና ከረማችሁ? ደኅና መጣችሁ? ጉዞዋችሁ ደኅና ነበር? ችግር አላጋጠማችሁም?» በማለት በተቻላቸው መጠን ፈገግታ እያሳዩ የሰላምታ ጥያቄ አቀረቡላቸው። በሕሊናቸው ግን፤ ቀደም ሲል ስለ ካሜሮን አድሮባቸው የነበረው የአመለካከትና የግምት ስሜት አሁን እንደ ቁርጠት እያመማቸው ነበር……

ቴዎድሮስ፤ አቡነ ሰላማን በአንዳች ዐይነት ጥርጣሬ እንደ ተጠየፉ ሁሉ፤ በቆንስል ካሜሮን ላይ ቅሬታ ያደረገባቸው የሹመት ደብዳቤውን ይዞ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፊታቸው ሲቀርብ ነበር። ቴዎድሮስ ከትሕትናቸው ጋር በራሳቸው፤ በኢትዮጵያዊነታቸው ኩራት ይሰማቸዋል። ቆንስል ካሜሮን ደግሞ በራስ መተማመን ከመኩራት ዐልፎ በራሱና በዘሩ፤ ሌላውን ሁሉ ከሰማይ ላይ ሆኖ ቁልቁል የሚመከት ሆኖ ቀረበባቸው። ማራቅ ሳይፈልጉ ሁናቴው ገፈተራቸው። አሁንም አቀራረቡ አልተለወጠም ነበር። የበፊቱን ስሜት ቀሰቀሰባቸው………

ካፒቴን ካሜሮን ቀደም ሲል በቆንስል፤ የሠራ ሰው ስለ ነበር ችሎታው ባያንስም «በካፊር» ጦርነት የተካፈለ ከሁለት መቶ ማይልስ የበለጠ በጠላት እጅ የተያዘ አገር በማቋረጥ ጀብዱ መፈጸሙ የታወቀለት፤ በጄኔራል ዊልያም የጦር ክፍል ያገለገለ መኮንን በመሆኑ፤ በራሱና በእንግሊዝ ዜግነቱ ግብዝነት ቢጤ የሚሰማው ነበር። ይህንን ስሜቱን በቴዎድሮስ ፊት ስንኳን ለመደበቅ አልሞከረም።

አረመኔ አገር ለመግባት የተጸየፈ ይመስል ምጽዋ ደርሶ ብዙ ወራት ከቆየ በኋላ እንደዚሁ ጎንደር ያሰኘውን ያህል ከርሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቴዎድሮስ ፊት ሲቀርብ ሁናቴም ይኸንኑ የሚገልጽ ነበር።

«በግዛትዋ ፀሐይ ከማትጠልቀው ከታላቅዋ ብሪታንያና ከታላቅዋ ቪክቶሪያ በአበሻ ተሹሜ የመጣሁት አዲስ ቆንስል ነኝ» አለ በመጠኑ ወገቡን፤ ሰበር አድርጎ እጅ በመንሳት ደብዳቤውን እያቀረበ። ሳሙኤል አስተረጎመለት።

«እኛኮ ሀገራችንን የምንጠራት ኢትዮጵያ ብለን ነው። ይህን የቱርክን አጠራር ምናለ ብትተውት» ሲሉ ቴዎድሮስ ኮስተር ብለው አስተዋሉት።

«ይኸ ደግሞ ከታላቅዋ ብሪታንያ ታላቅ ንግሥት ቪክቶሪያ የተላከልዎ ስጦታ ነው» አለ ካሜሮን በኋላ በአሽከር አሲዞት ያመጣውን ዕቃ እየዘረጋ። ራሳቸው በእጃቸው የሚቀበሉት መስሎት ነበር።

ላጋፋሪው እንዲሰጠው በእጃቸው እያመለከቱ፤ ‹ምነው ትልቅ ትልቅ ማለት አበዛብኝ ይኸ ሰው!› አሉ በአጠገባቸው ለነበሩት።

«ታላቋ ንግሥት የላኩት ስጦታ ቢታይልኝ መልካም ፈቃድዎ ሆኖ» አለ ቆንስል ካሜሮን እንደ ወጋግራ ተገትሮ።

የተሸፈነበት ሐር ተገልጦ በየተራ እየወጣ ታዬ። አንድ ሽጉጥ አንድ፤ ጎራዴ፤ አንድ የፋርስ ምንጣፍ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር።

‹እንደ ልጅ መጫወቻ የምወድ መስልኩዋቸው› ለማለት ቃጣቸውና ንዴታቸውን ዋጥ አድርገው፤ ‹መቸም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ባገሬ ሞልቶ ተፍፏል። ምሥጢሩን አይረዳውም ወይም የሚሰብከውን ራሱ አይፈጽመውም እንጂ፤ ያገሬ ቄስ በየጎጡ ዘወትር እንዳነበበው ነው። ምንጣፍም ቢሆን የዓረብ ነጋዴ ያመጣዋል። እኔ የፈለግሁት ይህንን መሥራት የሚያስተሩልኝ ዐዋቂዎች ነበር» አሉ ወደ ሽጉጡና ወደ ጎራዴው እያመለከቱ። «ለሁሉም ለስጦታው አመሰግናለሁ። በተረፈ ደብዳቤው የሚለውን እንስማው።»

አማርኛ የሚሞክረው ሙሴ ባርዴልና እንግሊዝኛ የሚችለው አቶ ሳሙኤል ተጋግዘው በመተርጎም እንደ ነገሩዋቸው የሁለቱ አገሮች መልካም ወዳጅነትና ግንኙነት እንዲኖራቸው የታላቋ ብሪታኒያ ፍላጎት መሆኑን፤ መልእክተኛዋ በኢትዮጵያ የከበሬታና የወዳጅነት አስተነጋገድ እንደሚደረግለት የቪክቶሪያ መንግሥት ተስፋ መሆኑን ከመግለጽና በመጨረሻም ለቴዎድሮስ ረጅም ዕድሜና

መልካም ጤንነት ከመመኘት በስተቀር ሌላ፤ ይህ ነው ተብሎ የሚቁም ፍሬ ነገር አልነበረበትም።

«በመተሳሰብና መረዳዳት ከሌለበት በባዶው ወዳጅነት - ወዳጅነት ማለት ብቻ ምን ፋይዳ አለውና? ሕዝቤን እንዳስተምርበትና አገሬን እንዳለማ በባለሙያ ዐዋቂዎች እባካችሁ አግዙኝ! ብዬ ለላክሁት መልሱ የታለ ብለህ ጠይቀው» አሉ ቴዎድሮስ። ደብዳቤው የተላከው ገና ፕላውዴን እንደ ሞተ ከመርዶው ጋር ነበር።

«እንግዲህ ያለው ነገር በኛ አገር ደንብ፤ ለፓርላማ ቀርቦ ተመክሮበት ነው የሚወሰነው» የሚል መልስ አገኙ።

«ከስንት ዓመት በላይ ባንድ ጉዳይ?»

«ክርክሩ ጊዜ ይወስዳል» ተባለ።

«ዛዲያ ነገር መቁረጥ ካልቻሉ ጠላ እየጠጡ የሚጨዋጫሁበት የኛው ሰንበቴ ይሻላል በሉኛ።»

«የሕዝብ ተወካዮች ስለሆኑ መቸም መብታችው መከበር አለበት።»

«ሌሎቹንስ ሕዝቦች ስለ መብታቸው ታማክሯቸዋላችሁ?»

ቆንስል ካሜሮን ጥያቄው ያልገባው መሆኑን በማመልከት ራሱን አነቃነቃ።

«ማለቴ ሠራዊታችሁ፤ ነጋዴዎቻችሁ፤ ሚሲዮናዎቻችሁ፤ ጊገቡ ሕንዶችን፤ ዓረቦችን፤ ተዚህ በእኛው አካባቢ አፍሪካ የትምትሉዋቸውን ምክር ትጠይቋቸላችሁ ወይ ማለቴ ነው።»

«እሱማ መቸም ለማሠልተንና ለማስተማር ባለብን ኃላፊነት።»

«ይህንን ኃላፊነት ማን ሰጣችሁ?»

ቆንስል ካሜሮን ጥያቄውን ጥቂት አሰበበት። በዲፕሎማሲ አነጋገር ለመጥለፍ የቀረበ መሆኑ ገብቶታል።

«አንድ እረኛ ከብቶቹን ማሠማራት እንዳለበት ሁሉ፤ ገናና የሠለጠነ መንግሥት ኃላፊነቱ እንደዚሁ ይሰማልዋ በራሱ።»

«ሰዎቹን ከብት አልካቸው? ከአረመኔነትም አውርደህ? ምድረ ማህራጃና ሸክ ተወዝሮ እየተሰደበ አገሩን ቢያስወስድ ለነገሩ እኔ ምን አስጨነቀኝ። ይኸንን እንተወው። እንደምትሉት ሕዝቤን የማሠልጠን ፍላጎት ታልችሁ እኔ ሠራዊታችሁ

አልፈልግም። ሰባኪዎቻችሁንም አልሻም። ወገኔን የምታስተምሩልኝ ሙያ ዐዋቂዎች እርዱኝ ነው ያልኳችሁ የነበር። ቅንነት ካለ ዛዲያ ይኸ ምን ይገዳል?»

«የታላቋ ቪክቶሪያ መንግሥት የተቻለውን ሁሉ ከማድረግ አይቦዝንም።»

ቴዎድሮስ ኮስተርተር አሉ፡ « ‹ታላቅ› ማለቴ ምናለ ቢቀር። እንዲያውም ግብዝነት ሆኖ ነው የሚቆጠርበት። ደሞም ሁሉም ለየራሱ ትልቅ ነው። ራሱን በራሱ የሚያዋርድ ብቻ ነው ትንሽ። አሁን ይህን ጉዳይ እንተወውና የጠየኩት፤ ርዳታ መቸ ይደርስልኛል? ብለህ ጠይቀው» አሉት አስተርጓሚውን፤ ሳሙኤልን።

«በጊዜው» ሲል ካሜሮን ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ መለሰ።

«ምነው መይሳው! ምን ዐይነት አጉል መልስ ነው። ይህማ የዛሬ ዐሥር ዓመትም ይሆናል። ያኔ ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ መሆኑ ነው።

ወገኔ በተሎ ተምሮ ካልጠነከረ፤ ሀገሬን ያሰፈሰባት ጣላት መች ፋታ የሚሰጥ ሆኖ! ይዋል ይደር አያሰኝም ብለው።»

«ይህንኑ አሳውቃለሁ ለመንግሥቴ» ሲል ካሜሮን መለሰ።

«እንዴት አርገህ ነው የምታሳውቀው? መቸም ባሞራ አትልከው። ያሰብኩትን አንተ ካነሳህ ዘንድ እኔ የምፈልገው መልእክት ይዘህ ሒደህ ለመንግሥት እንድታደርስልኝ ነው። አዎ፤ ላመጣህልኝ መልእክት መልስና ለስጦታው ምስጋና እንደዚህም የሚላኩልኝ ሰዎች ጉዳይ አጣዳፊ መሆኑን ለንግሥት አጽፍላቸዋለሁ።

«አንተ አድርጌ ራሴ እሔዳለሁ ጃንሆይ? መንግሥቴ የላከኝ ከዚህ ሁኜ የቆንስላ ሥራ እንድሠራ እንጂ!» አለና ‹ለእርስዎ እንድላላክ አይደለም› ሲል ያሰበውን አቋርጦ ተወው።

«የቆንስል ሥራ በሁለታችን መካከል ወዳጅነት ማበጀት ማለት አይደለም? ወይስ ሌላ ሥራ አለሁ?» ሲሉ በጥርጣሬ አመለካከት ጠየቁት።

«እሱማ ነው!»

«ዛዲያ ወዳጅነታችንን የምታጠነክረው የኔን መልእክት ስታደርስልኝ ነው፤ ነው የምለው። ታለበዚያ እንዲሁ ተዚህ መቆየታትህ ምንም ጠቀሜታ የለውም» አሉት። እንድትቆይም አልፈልግም ማለታቸው ጭምር መሆኑ ካሜሮን ተሰማው።

ካሜሮን ቆንስልነት ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጥቱ በፊት ቤተ መሳሕፍት ሔዶ፤ ሰዎች ጠይቆ ስለ ኢትዮጵያና ቴዎድሮስ ስለሚባለው መሪ የቻለውን ያህል

ለመረዳት ሞክሮ ነበር። ካገኘው መረጃ የቀረጸው አስተሳሰብ ግን ከአጋጠመው ፈጽሞ የተለየ ነበር። እርግጥ የአክሱም ዘመነ መንግሥት፤ የአክሱም ሥልጣኔ የሚገባ ነበር። ይህ ግን፤ ያለፈና ያለቀለት ፍራሹ ብቻ የቀረ ታሪክ ነው። የጥንት መንግሥት የጥንት ሥልጣኔ በሶርያም በኤፍራጥስ ጤግሮስም፤ በካርቴጅም በግብጽም ሞልቷል። ኢትዮጵያን ከዚህ ሁሉ ልዩ የሚያደግ ምክንያት አልታየውም። ጉቶ ግዛት አቋቁመው ሲዋጉ ከኖሩት መኳንንት መካከል አይለው የወጡት ቢሆኑም ከብዙዎቹ የዐረብ ሼኮች፤ የአፍሪካ የጎሳ መሪዎች የተለዩ ሊሆኑ መቻላቸውን ካሜሮን ፈጽሞ አልገመተም ነበር። በዚህ ፈንታ ብዙዎች የአፍሪካና የእስያ የሕዝብ መሪ ነን ባዮቹ አሻንጉሊት እንዳየ ሕፃን ለመንጠቅ የሚከጅሉትን ስጦታ እንደ ቀላል ነገር የሚቆጥር ያም ሆኖ ለይሉኝታው ያህል፤ ምስጋናውን የሚገልጽ ኃይሉ ለእንግሊዝ ጦር ኃያል ይደግፈኝ ከሚል ይልቅ፤ ወገኑን በዘመናዊ ዕውቀት የሚያስተምሩለት ባለሙያዎች ዕርዳታ የሚጠይቅ በዓለም ዙሪያ የተዘረጋው የታላቋ ብሪታኒያ ግዛተ - አጼ እሱንም እንዳይጨፈልቀው ከሚጨነቅና ከሚለማመጥ ይልቅ በሠለጠነ መንግሥት እኩልነት ከሚያምን አፍሪካዊ መሪ አጋጠመው። ካሜሮን ያላሰበውና የማይፈልገውም ነገር ስላጋጠመው ደስ አላሰኘውም ነበር። ፕላውዴን በምን ዐይነት አቀራረብ ተስማምቶ እንደኖረ ሊገባው አልቻለም። ‹ታላቋ ብሪታኒያ ዜግነቱን ክብር ጥቂት በመሠዋት ይሆን› ሲል አሰቦ ነበር። ግን ወደደም ጠላ፤ ለጊዜው ፈቃድ ፈጻሚ ከመምሰል በቀር፤ ሦርስት ራሱን ቴዎድሮስን ሊጋፈጥ እንደማይችል ስላወቀ በሆዱ ጥርሱን ነክሶ በእሽታ እጅ ነሥቶ ተለያየ።

ቴዎድሮስ፤ የካሜሮን ሁናቴ ስላልጣማቸው፤ ‹ባገሩ ቅኝ ግዛት ስፋት፤ እንደ ፍየል ወጠጤ ልቡ ያበጠበት ትዕቢት ሳይሆን አይቀርም› ሲሉ ለባለሚሎቻቸው ቢናገሩም እንደ እንግድነቱ በወግ በሥርዓቱ ለማስተናገድ ያሰቡትን እንዲፈጽምላቸው ለማባበል ሲሉ ማምሻውን ሁለት ሽህር፤ ዐሥር ሙክት ሦስት ገንቦ ጠጅ አምስት ማድጋ ጠላ ከድንኳኑ ድረስ እንዲላክ አዘዙት።

ካሜሮን የቴዎድሮስን መልእክት ይዞ በመተማ በኩል የሔደው ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር። ከአንድ ዓመት በላይ ቆይቶ ምንም የረባ ነገር ሳይዝ እንደ መጣ ተሰምቶዋቸዋል። ግን ንዴታቸውን ውጠው በርጋታ ለመቀበል ሞከሩ።

ሁናቴው እንደዚህ በረድ እንዳለ መቀጠል ሲችል አቡነ ሰላማ ሆን ብለው የፈልጉ ወይም የታዘዙ ይመስል እሳቱን ለኮሱ። ቴዎድሮስ የሰላምታ ጥየቃቸውን ጨርሰው ከመቀመጣቸው በፊት ለመሳለም መስቀላቸውን ቀስረው ቀረቡ። ቴዎድሮስ ወደዚያ ወደዚህም ዘወር እያሉ ያላዩ ለመምሰል ሞከሩ። አቡኑ ግን

አልተበገሩም። እጃቸውን እንደቀሰሩ ትንሽ ቆይተው፤ «መስቀል ይሳለሙ እንጂ! እግዜር ይፍታ!» አሉ እጃቸውን አስጠግተውና ጮህ ብለው።

ቴዎድሮስ ደረታቸውን ገፋ በእጃቸው የጨበጡትን የጦር ዘንግ ረገጥ፤ መላ ሰውነታቸውን ቀጥ፤ ፈርጠም አድርገው አቡኑን ትኩር ብለው ተመለከቱዋቸው።

«የክርስቶስን መስቀል ይሳለሙ እንጂ» አሉ አሁንም ሙዝዝ ብለው። ቆንስል ካሜሮን ከወደ ኋላቸው ቆሟል።

«ጧት ተሳልሜያለሁ አባቴ!» አሉ ቴዎድሮስ የፌዝ ፈገግታ እያሳዩ።

«የክርስቶስ መስቀል መሳለም ደግሞ በቃኝ ያባላል? ሲሆንማ እንደዚህ እንደምንተነፈው አየር ዘወትር፤ በአገኘው ቁጥር ስንቀበለው ጸጋውን ያጎናጽፈናል እንጂ። ደሞም የአቡን ቡራኬ.....» ሲሉ አንጠልጥለው በመኩራራት ደመደሙ።

ቴዎድሮስ፤ አገጫቸውን በመዳፋቸው ዐቅፈው እንደ መሣቅ ቃጣቸው። «ለመሆኑ መስቀል አዘውትሮ በመሳም ይጸደቃል?»

«እህ? መቸም - መቸም» አሉ አቡነ ሰላማ ትንሽ በመናደድ አቆብቁበ የሚያዳምጣቸው የቴዎድሮስ ታማኝ ሠራዊት እንደማይወዳቸ በማወቅ፤ «መስቀሉን መሳለም ማለት ከኃጢአታችን ቀንሰን፣ ንስሐ አግኝተን፤ ምሕረቱን ገበየን ማለት ነው።»

«ነው? ነው ብለው ያምናሉ?» ሲሉ ቴዎድሮስ ፍርጥም አድርገው ጠየቁ።

«ምን ጥርጣሬ አለበት።»

«እንግዲያማ የስዎን መስቀል በመሳም ተሆነ፤ የጎንደር ሴት ኧረ ሌላውም ሁሉ እኔና ሠራዊቴ መቸም መቸም ሙብለጥ ሰለማንችል በከንቱ ነው የምንለፋው። የገነት ሥራ ሞቶ ነው የሚቀየን» አሉ ቴዎድሮስ የፌዝ ሣቅ እየቃጣቸው።

«የሱ ቤት ለፍጥረት ሁሉ ይበቃል። የጠፉትን በጎች ፈልጉ ነው የተባልነው» አሉ አባ ሰላማ በመርታት አኳኋን።

«ስለዚህ ነዋ፤ እልፍኝዎ ለጎንደር ጋለሞታ ሰፊ የሆነው» አሉና ቴዎድሮስ ኩታቸውን እንደ ማጣፋት አደረጉ። ሠራዊቱ አሽሙሩ ገብቶት እንደ መውካካት አለ። «ኧረ! ለነገሩማ ምን አግብቶኝ? ለሁሉም የጁን ይሰጠው እንጂ! የርስዎ ሥራ ሌላ፤ የኔ ጉዳይ ሌላ። ስላነሡብኝ ብቻ ነው። አሁን ዕረፍ ይበሉ። በመንገድ ላይ ነው የቆያችሁት።»

ቴዎድሮስ እንደ ቆሙ ቢሆንም አጋፋሪው አቡነ ሰላማን ወደ መቀመጫቸው ሲመራቸው ዘርፋፋ ካባቸውን ሰባስበው ተቀመጡ።

በጥያቄ መልክ የቴዎድሮስ አስተያየት በቆንስል ካሜሮን ላይ ሲያርፍ ቀረብ ብሎ እንደገና እጅ ነሣ። ብልጭልጭ ቁልፍ የሜዳይና በሐር ጉንጉን የተንቆጠቆጠ ሰማያዊ የማዕረግ ልብሱን፤ ሁለት ክንድ በሚለካ የእግንሊዝ ጎራዴ አጅቦታል። ከተንቆጠቆጠው አለባበሱ ጋር ከወገቡ ላይ ትንሽ ሰብር ያለ እጅ አነሣሡ፤ በቴዎድሮስ ፊት ልቆ ጎልቶ ለመታየት መፈለጉ በልግጽ ያስታውቅ ነበር።

ከሠራዊቱ መካከል አንዳንዱ በማሽዒጠጥ ከንፈሩን ለጠጠ። ሌላው በመገረም በእጁ አገጩንና ጭንቅላቱን ያዘ።

«ከታላቋ ንግሥተ ነገሥት የተላከ የመልካም ምኞት ሰላምታዬን አቀርባለሁ» አለ።

«የንግሥትህን ሰላምታ በከበሬታ እንቀበላለን» አሉ ቴዎድሮስ አሁንም በተረጋጋ ሁናቴ፤ «እና ዋና መልክቱ ይኸው ብቻ ነው?»

«ገጸ በረከት አምጥቻለሁ።»

«ቁም ነገሩ አላቂ ጠፊ ስጦታ ብቻ አይደለም። ሌላስ?»

ቆንስል ካሜሮን እያቅማማ እያመነታ፤ «መቸም መቸም» አለ።

«የለም ቆንስል ደበስበስ አታድርገው ጉዳዩን። ሌላ መልክት አለህ ወይ?» ሲሉ ኮስተር ብለው ጠየቁ።

«ለጊዜው ይኸው ነው።»

«እንዴት? የደብዳቤ መልስስ?»

«ይመጣል ጃንሆይ።»

«እኔ በከበሬታ በደብዳቤ ለላኩለት መልክት ያመጣልኝ የቃል ሰላምታ ብቻ ነው ማለት ነው?»

«ለጊዜው አዎ!»

«ለምን?»

«ስላልደረሰ ነው።»

«የደብዳቤው መልስ ካልደረሰ የቃሉ ሰላምታ እንዴት ሊደርስ ቻለ? ሁለቱም በሰው ነው የሚመጣው። ወይንስ የቃሉን ሰላምታ ወይስ ይኸኛውን በአክናፍ የሚበሩ መላእክት አበቀሉህ?»

ካሜሮን የሚመልሰውን ጥቂት ሲያስብ፤ እንደ ተረታ በመቁጠር ሠራዊት ጥቂት እንደ ማውካካት አለበት።

«መቸም በመንግሥታት መካከል ለሚከናወን ጉዳይ በጽሑፍ የሠፈረ ነገር ሁሉ ብዙ ጥንቃቄና ምክክር ስለሚያስፈልገው ነው። የዘመናችን ዲፕሎማሲና ፖለቲካ በጣም ውስብስ ነው» አለ ከጥቂት ጊዜ በኋላ።

«ዲፕሎማሲና ፖለቲካ የምትለውን ቋንቋ እንደ ደብተራ ትብትብ አቡሻክር አታስመስለው ቆንስል ካሜሮን! የኔ ጥያቄ ምሥጢር ፈቺ አያስፈልገው ነበር። ወዳጅን ከጠላት ለመለየት ወዳጅ የጠየቀውን ዕርዳታ እሺ ወይም እምቢ ለማለት ካመት በላይ ምክክር ያስፈልገዋል? እንደዚህ በምክር ብቻ ዘመኑን ከፈጃችሁትም እንዴት ሁናችሁ ነው የሠለጠናችሁት?» ቴዎድሮስ እንደ መሣቅ ቃጣቸው። ከሠራዊቱ ዘንድ የመሣለቅ ሁካታ ተሰማ።

የቴዎድሮስ አጠያየቅ፤ ስለት፤ የሠራዊቱ ሥላቅ፤ የካሜሮንን የታላቋን ብሪታኒያ ዜግነት ኩራቱን ቆጠቆጠው። «ወዳጅነት ሲባል እንደዚህ በደፈናው አይሆን» አለ።

«እህሳ?» ሲሉ ቴዎድሮስ በመገረም ጠየቁት።

«ወዳጅነት የሚረጋገጥበት ብዙ መለኪያ አለው።»

«ምን ዐይነት መለኪያ?»

ካሜሮን መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ።

«የጥጥ፤ የጨው፤ የእህል ነጋዴ፤ ‹ያተርፈኛል ወይስ ያከስረኛል? ያዋጣኛል፤ አያዋጣኝም?› እያለ እንደሚለካበት ሚዛን? የእናንተ የሠለጠናችሁት ወዳጅነት፤ ንግድ መሰል መሆኑን ብሰማም አላመንኩም ነበር።»

የአሁን አነጋገር ካሜሮንን የባሰ ቆነጠጠው። «እንደሱ ማለቴ አይደለም» ሲል ኮስተር ብሎ ተናገረ።

«እህሳ?»

«በማለት፤ በሠለጠኑ መንግሥታት መካከል በሚደረግ ግንኙነት መከበር ያለእብት ደንብና ሥርዓት አለ» ሲል መለሰ፤ ነገሩን ሰሞኑን ከአባ ሰላማ ጋር ወደ ተመካከሩበት ለማምራት እንዲመቸው።

«እና፤ እና ያልሠለጠነው፤ ይህንን ደንብና ሥርዓት ለማክበር የበቃን አልሆነም ማለት ነው?» በማለት በሰላ ፌዝ ጠየቁት።

«ይኸ አልወጣኝም።»

«እህሳ?»

«ግናስ.....» ሲል አቋርጦ ተወው።

ምንም መሪ ያውም ያንድ ጎስቋላ ሕዝብ መሪ ቢሆንም፣ በአንድ ጥቁር አፍሪካዊ ፊት እንደዚህ እንደሚሽቆጠቆጥ መደረጉ፤ በሰላ አንደበት መጠየቁ፤ ጭርንቁስ በለበሰ ሠራዊት ፊት መሣለቂያ መሆኑ ግብዝነቱን ቢያፈላበትም ነገርን በልስላሴ መያዝ የሚጠይቀው የዲፕሎማሲ ሙያው ሳብ አደረገው። የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ፖሊሲ፤ ያልሠለጠኑ ሕዝቦች መሪዎችን ከባላባቱ አንሥቶ በከበሬታ መሸንገል እንደሚያስፈልግ ያስጠነቅቃል። ነገር ግን ቴዎድሮስ በአገሩ አባባል፤ ‹ሱሪው እስኪጠበው ትልቅነት እየተሰማው ነው› ሲል አሰበ።

«ግናስ ምን?» ሲሉ ቴዎድሮስ እንደገና በጥያቄ አፋጠጡት።

«ጥቃቅን ጉድለቶች ግንኙነቱን ሊያበላሹት ይችላሉ። ካልታረሙ።»

«ለምሳሌ?» ሲሉ አሁንም በመኮሳተር ጠየቁት። ነገሩ አንዳች አዝማሚያ እንዳለው ገብቶዋቸዋል። ካልደረሱበት ደግሞ አይተዉትም።

«እኮ ጨርሰው እንጂ!»

ያበጠው ይፈንዳ በሚል ስሜት፤ ደረቱን ነፋ አንገቱን ቀን አደርገ።

«ለምሳሌ የፈላሻ ሚስዮናውያንን ማሰርዎ መልካም አይደለም።»

«ቴዎድሮስ መላ ሰውነታችን ነዘራቸው። ጥርሳቸውን ቅርጭም አድርገ ለቅጽበት አሳለፉት። «እንዴት?» ሲሉ በተገታ አንደበት ጠየቁ።

«ማለት አገር ለማሠልጠን፤ ሕዝብ ለመርዳት የመጡ የውጭ አገር ሰዎችን አስሮ ማንገላታት የታላቋ እንግሊዝ መንግሥት በደግ አይመለከተውም። ወሬው በሞላ አውሮፓ ተዳርሷል።

ቴዎድሮስ፤ የጦር ዛቢያቸውን ርግጥ አድርገው በመደገፍ በግራሜ ትዝብት ትኩር ብለው ተመለከቱት። «አንድ ዓመት ሙሉ የኔ ደብዳቤ የት እንደ ደረሰ ሳይታወቅ አሁን ከጥቂት ወር በፊት የሆነው እንዴት ከእንግሊዝ መንግሥት ጆሮ ደረሰና፤ እንዲህ ያለ ስሜት ፈጠረ? ይህም አዲስ ተአምር ነው» ሲሉ ሠራዊታችን ተመለከቱ።

«ወሬኮ ከደብዳቤ ይፈጥናል።»

«ይኸስ እውነትህን ነው። ወሬኛው ከልቡ ስለሚፈጥንበት። ይህንን እንለፈውና ወንጀለኛ ጥፋቱን ወስላታ ባስር ብቀጣ በናንተ በሠለጠናችሁት ዐይን ጥፋቲ ተምን ላይ ነው?» ሲሉ ጠየቁ። በቴዎድሮስ ለዘብ ያለ አነጋገር ካሜሮን እየተደፋፈረ ሔደ። ግምቱ ትክክል ቢሆን ነው። የድንቁርና ድፍረት የሚያሳዩ ሰዎች እንደ አንዳንድ አውሬ ዐይነት የፍርሃት ጀርባ ከሰጡዋቸው ዘለው ጉብ ይላሉ። ፊት ለፊት ሲፋጠጡዋቸው ግን ያፈገፍጋሉ፤ ወይም ባሉበት ቀጥ ይላሉ ሲባል ሰምቶ ነበር።

አሁንም የቴዎድሮስን ሁናቴ ተረጎመው። «በሰለጠኑ ሕዝቦች ዘንድ ምንም ሰው ጥፋት ሥራ ቢባል ተመስክሮበት ሳይፈረድበት አይታሰርምም። በተለይ ደግሞ የሌላ ሀገር ዜጎች ከፍተኛ ጥንቃቄና ከበሬታ ሊደረግላቸው ይገባል። እንዳገሬው ሰው መታየት የለባቸውም። ጥቃቅን ጉድለቶች የመንግሥታትን ግንኙነት ሊያበላሹ ይቻላሉ ያልኩት ሰለዚህ ነበር። በሚስዮናውያኑ መታሰር የእንግሊዝ መንግሥት እንዳይከፋ በጣም ነው የምሠጋው» አለ ካሚሮን እንደ መንጎራደድ እየቃጠው።

ሁናቴው ቴዎድሮስን ከማናደድ ይበልጥ አስገረማቸው። «እሱ አላካቸው። ለመሆኑ፤ ስለዚህ ቀጣፊ ወንጌል ሰባኪ ነን ባዮች የንግሊዝ መንግሥት ምን አገባውና ነው የሚከፋው?» ሲሉ ጠየቁ።

«ሁለቱ የእንግሊዝ ዝርያ አለባቸው። ሌሎቹም ያው የአውሮፓ ነጮች ናቸው።»

«አሃ!» አሉ በመገረም ሣቅ፤ « ‹ዘመድ ተዘመዱ አህያ ታመዱ› እንደሚባለው መሆኑ ነው? ፈረንጆች እንደዚህ መሆናችሁን የታባቱ ዐወቅሁና?»

«የቆዳ ቀለም መሳሳብ ሳይሆን፤ በዓለም ዙሪያ የተዘረጋው ታላቁ የእንግሊዝ ግዛት - ዐጼ በብዙ የዓለም ክፍሎች የሚፈጸመው ድርጊት ሁሉ ያሳስበዋል። ታላቅነት ኃላፊነት አብሮ ጥሎበታል።»

ቴዎድሮስ ንዴት እንቅ አደረጋቸውና እንደ ምንም አመቁት። «እሺ በጄ! ግሩም ነው። ኃይለኛ ከተባለ የትም አገር ገብቶ እንዳሻው ሊሆን ይችላል ማለት ነው።»

ካሜሮን ለመመለስ ተግ ሲል ቀደም ብለው ያቀዱት ይመስል አቡነ ሰላማ ለጠቅ በለው ተናገሩ። «መቸም እንደዚህ ያለው ትልቅ ኃላፊነት ከራሱ ከባለቤቱ ሳይሆን ከላይ ከእግዚባሔርም በአደራ የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በሌሎች አገሮች ምዕመናን ላይ ሥልጣነ - ሰማያት ቢሰጣት ነው እንደ ድንበር የማይከልላት።

ቴዎድሮስ አላስጨረሱዋቸውም። ግን ደግሞ ንዴት እንዳቃጠላቸ በጨኸት አልገነፈሉም። «አባቴ! ልበልዎ? አዎ ይባላሉ። ግን ስለ ክርስትናና መንፈሳዊ ሥራ አሁን በድንገት ከሚያነሡ ሌላ ሌላ ጉዳይዎን ቢሠሩ ይሻላል። እስቲ ልጠይቅዎ! የእርስዎ የመንፈስ አባትና እንደፈረደብን የእኛም የመንፈስ አባት የሆኑት፤ የእስክንድርያው ፓትርያርክ መጥተው፤ በመንፈሳዊ አባታቸው እንዲያ በክብርና በፍቅር ተቀብለን ሃይማኖታዊ ድጋፋችውን ስንጠይቅ፤ እሳቸው ምን ነበር አጥብቀው የያዙት ነበር? ስለ ቱርክ ፓሻ ትልቅነትና በጎ ሐሳብ አልነበረም? አዎ! ይኸው በሰልፍ ወጥቶ በየደረሱበት ያጀባችው ሠራዊቴ ይመስክር። አሁን ደሞ ለንግሊዝ መንግሥት የታላቅነት ኃላፊነት። ለንስቱ ነው የሚያድሩ አባቴ? መቼስ አባቴ ልበልዎት እንጂ። ትናንት ክርስቲያን ሆነው ለእስላሙ ቱርክ ፓሻ። ዛሬ ደግሞ እንደኛም ባይጠቁር አፍሪካዊ ሆነው ላውሮፓ። በእምነት ሳይሆን በትልቅነት ብቻ? ሌላውን ስንኳ እንተወው። የግልዎ ጠባይ ተሆነ መቸስ ምናረጋለሁ። በሀገሬና በመንግሥቴ ጉዳይ ግን ባይገቡ ይበጃል።» ወደ ቆንስል ካሜሮን ዘወር አሉ። «አንተን ልጠይቅህ እስቲ መልስልኝ?»

«መመለስ የችለው ተሆነ ምንተዳዬ?»

«አንተ ላመጣኸው ጉዳይ መስል መስተት አለብህ እንጂ። ያፍህ ወለምታ ተሆእም ስሕተህን ታምናለህ። አይደለም ወንዶሞች?»ሲሉ በዙሪያቸው የቆሙትን በአስተያየት ጠየቁ። ብዙ ጭንቅላቶች በአዎንታ መልስ ተነቃነቁ።

ካሜሮን፤ ምን ቸገረኝ በማለት አኳኋን ትከሻውን ሰበቅ አደረገ።

«እሺ» አሉ ቴዎድሮስ አሁንም በትዝብት እያስተዋሉ። «ላንድ አገር ባዳ የሆኑ ሰዎች ቢያጠፉም መታሰር መቀጣት የለባቸውም ብላሃል።»

«ጥፋታቸው ካልተረጋገጠ በስተቀር» ሲል ካሜሮን ለማስተካከል ቃጣ።

«እሱ ይሁንልህ። ዛዲያ ገናና ትልቅ የምትለው ያንተ መንግሥት ያንተም ብቻ ሳይሆን የፈረንሳይም የሠለጠኑ የ ትላቸው ያውሮፓ መንግሥታትም ድንበራቸውን ዐልፈው ባሕርና ውቅያኖስ አቋርጠው ሌላውን ዐቅም የሌለውን ሕዝብ የሚያሥሩት የሚያንገላቱት የሚረግጡት የሚጨፈጭፉት ምን ባጠፉ ነው? ቢያጠፉስ በሰው አገር እነሱን ምን ዶላቸውና ነው? በራሱ አገር በራሱ ልማድ ሥራት ይተዳደራል እንጂ።» ካሜሮን ወዲያው ስላልመለሰላቸው «እኮ አስረዳኝ እንጂ» ሲሉ አፋጠጡት።

ካሜሮን አሁንም ትከሻውን ሰበቅ አደረገና። «መቸም እንዳልኩት ታላላቅ መንግሥታትና የሠለጠኑ ሕዝቦች ኃላፊነት አለባቸው።»

«ማን ሰጣቸው ይህ ኃላፊነት?»

«የሥነ ምግባራቸው ከፍተኛነት፤ የዕውቀታቸው ጥልቀት፤ ትልቅነታቸውም ጭምር ራሳቸው በራሳቸው ኃላፊነት እንዲሰማቸው ያደርጋቸዋል።

«ተሰማይ ቤት ተሰጣቸው አለማለትህ ባይሆን ተእነአባ ትሻላለህ» ሲሉ ቴዎድሮስ አቡነ ሰላማ ፊታቸውን ጭፍግግ አደረጉ። «ዛዲያ ይህ ኃላፊነት ለመርገጥ ለመግደል ለመዝረፍ አገር ለመውሰድ ጭምር ነው?» በማለት ቆንስል ካሜሮንን እንደገና ጠየቁት።

ሠራዊቱና ዙሪያውን የቆሙት ባለሟሎቻቸው ቃላቱን የሚቀበሉ ይመስል አመለካከታቸው ከአንዱ ወደ ሌላው እያቀያየሩ ነገሩን በትኩረት ይከታተላሉ።

«መቸም አንዳንድ ጊዜ» አለ ቆንስል ካሜሮን ጉዳዩን በጥልቅ ያሰበበት ይመስል ግንባሩን ሽብሽብ አድርጎ። ‹ያልሠለጠነ ደንቆሮ ሕዝብ የሚጠቅመውና የሚጎዳውን አያውቅም። ሕፃን እሳት ልጨብጥ ይላል። አንበሳ ገደል ይገባል። ወይም የአውሬ ምግብ ይሆናል። ከሌለው። እና ከብት ለመግራት አውሬ ለማልመድ እንደሚደረገ ሁሉ› ሲል የተመኘውን ወደ ጎን ትቶ፤ «ለእነርሱ የወደፊት ደኅንነት ሲባል፤ አንዳንድ ጊዜ ታዲያ ኮስተር መረር ማት ያስፈልግ ይሆናል። መጨከን ሳይሆን.....»

«ምን!» ቴዎድሮስ ንግግሩን ማስጨረሱ አላስችላቸው አለ። ራሳቸውን ገታ አድርገው ነገሩ እንደ ተአምር በአስገርሞዋቸው፤ አገጫቸውን በመዳፋቸው ደገፍ አድርገው ለጥቂት ጊዜ በሐሳብ ተመሰጡ። ሲያስቡትም ነገሩ የባሰውን እርር ቅጥል አደረጋቸው። አባቴስ ይህን ነገር ይሰማሙበታል?» ሲሉ አቡነ ሰላማን ጠየቁ። አቡነ ሰላማ መልስ አልሰጧቸውም። «እንዲህ ያለው የሥልጣኔ አስተያየት ባፍንጫዬ ይውጣ።» ቴዎድሮስ ጣቸውን በካሜሮን ላይ ቀሰሩ። «እድነናንተ ያልሠለጠነው ወገኔም እንደ ከብት ነው ማለት ነው? አይደለም?» ሲሉ ጠየቁት።

«እንደዚህ ማለቴ አይደለም» ሲል መለሰ።

«ነው እንጂ! ስም ባትጠራ በደፈና ብለኸው የለ? ለካስ በወዳጅነት ወገኔን በሙያ ለማሠልጠን ርዱኝ ብዬ ለላኩት ደብዳቤ መልስ በማምጣት ፈንታ፤ በጠላቶቼ መኻል ከርመህ ባዶ እጅህን የተመለስከው እንደትሉት በኃይል እየረገጣችሁ ለማሠልጠን እንዲመቻችሁ ኑሯል? እኔ የዋሁ ይህን መቸ ዐውቄ? በሉ እሱን ውሰዱና ቀፍድዱልኝ» ብለው ከማዘዛቸው በካሜሮን የትዕቢት አነጋገር ከመሪው ጋር አብሮ ሲበሽቅ የቆየው ወታደር ከመቅጽበት የፊጥኝ ቀፍድዶ ያዘው።

«በምን ጥፋቴ ነው የምታሰረው?» ካሜሮን የፍርሃት ጀርባ ከማሳየት አሁንም ፊት ለፊት መፋጠጡ ቴዎድሮስን እንዲያፈገፍግ የሚያደርግ ዘዴ መስሎ ተሰማው። «ደግሞም የታላቋ ብሪታንያ መልክተኛ ነኝ» አለ።

«ትፋትህ? አንድ ሀገሬን፤ ወገኔን ጭምር በማዋረድ ተሳድበሃል። ሁለት ከጠላቶቻቸው ጋር በመሆን ሀገሬንና ወገኔን የሚጎዳ ዱለታ ስታደርግ ከርመሃል። ወይስ ሰልጥነናል የሚሉት ነጮች በጥፋት አይተየቁም? ወደዳችሁም ጠላችሁም ባገሬ ደንብ ትጠየቁበታላችሁ። የታላቋ እንግሊዝ መልክተኛ ስለ መሆንህ ግን ሁሉም ለራሱ ታላቅ ነው። ‹እሳት ቢያንቀላፉ ገላብ ጎበኘው› አሉ፤ ውሰዱልኝ ከፊቴ!» ሲሉ አዘዙ።

ወታደሮች ቆንስል ካሜሮንን እየገፉፉ ገለል ሲያደርጉት አቡነ ሰላማ የሚባርኩ ይመስል፤ መስቀል የጨበጡበትን እጃቸውን አሁንም ዘርግተው ተነሡ። «ጃንሆይ፤ ጥፋትም ካለ በይቅርታ፤ አለመግባባትም ከሆነ በመነጋገርና በመመካከር እንዲያልፋት በስመ እግዚአብሔር እለምንዎታለሁ። ቁጣ ለድምር ለሰማይ ቤትም እንደማይበጅ በመጽሐፍ ተጠቅሷል። እና አሁንም።»

«አባቴ መጽሐፉን ያውቁታል?» አሉ ቴዎድሮስ በፌዝ።

አቡነ ሰላማ ያልሰሙ በመምሰል «ይቅርታ ተባባሉ ይቅር መባባሉ ነው ደጉ ነገር።»

«ተጎንደር እልፍኝዎ ክህነት ለመስጠት ስንኳ አሞኛል ደክሞኛል የሚሉት ሰውዬ፤ ያለወትሮዎ እየተጎተቱ የመጡት ለዚህ ኑሯል? ገባኝ።»

«ቅድም መስቀል ላስላምዎት ብል እምቢ አሉ። አሁን ደግሞ ታረቁ ተስማሙ..... የለም እንዲህ አይሁኑ ጃንሆይ። ታለበለዚያማ ሰው የሚለው» አቡነ ሰላማ ድፍረትን ከቆንስል ካሜሮን መቅዳት ሞክረው መጨረስ አቃታቸው።

«ምን? ሰው ምንድን ነው የሚለው? ይናገሩት እንጂ! ለነገሩ ባገሬ በወገኔ በኔ ላይ ከሚዶልቱት መካከል ዋናው እርሶ አይደሉ? እንኳን እርስዎ የርስዎ መንፈሳዊ አባት የተባሉት አቡነ ቄርሎስ ሳይቀሩ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ስለ ሰይድ ፓሻ አይደል ዘወትር የሚያስቡ የነበሩት? ልጅም የሚወታው ባባቱ ነው። ስለይህም ወደ ግንዱ፤ ሀገር ወደ ማሻሻጡ ሲያደሉ አይደንቀኝም።»

እንደ ቆንስል ካሜሮን ሳይን፤ በአሁነኛው የከረረ የንግግር ልውውጥ ሠራዊቱ እንደ መደናገጥ አለ። ምንም ብዙ ቢወራባቸውም፤ ከጥንት ሲያያዝ የመጣ ታሪክ መንፈሳዊ አባት ተብለዋልና፤ ኃይለ ቃል ሲሰነዘርባቸው ማየትና መስማት ትንሽ የሚሰቀጥጥ ለጆሮ የሚከብድ ሆነበት። ሁናቴ ይህንን የተገነዘቡት አቡነ ሰላማ ድፍረት አገኙ።

«እኔ እንደሆነ ገና ለገና ቁጣ፤ ግዞት ወይም እስራት ፈርቸ ከመንፈሳዊ ሥራዬ ከቶ ዝንፍ አልልም። ሥጋዬን እንጂ ነፍሴን ቅንጣት እንደማይነካት ዐውቃለሁ። ሥጋዬ ለኔ ምኔ ነው? ይልቅስ እርስዎን ገዝቸ ከኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን እንዳልነጥልዎ ምክሬን ቢሰሙ ይሻላል።»

«ወይኔ መይሳው! ለማስፈራራትም ተባቃን?» አሉ አባ ታጠቅ ከቁጣ ይልቅ በመገረም ራሳቸውን እየነቀነቁ። «እኔስ ተዛሬ ነገ ይሻልዎታል ብዬ ችየዎ ነበር። እኔ ሞኙ ጠላቴን በጉያዬ አስቀምጬ። አገር በግዝት የምሸጥ ከመሰልዎ ያገኙታል። እሱን እሥሩልኝ!» ሲሉ ድንገት አዘዙ። በካሜሮን ላይ የተረባረበውን ያህል በቅርብ የነበረው ወታደር አሁን እንደ ማመንታት አለ።

«ወቸው ጉድ!» ቴዎድሮስ የምሬት ሣቅ ከጀላቸው። «የፈሪን መንደር አህያ ይወረዋል እንዲሉ፤ የስንቱ የጎንደር.....» ሊናገሩት የቃጡትን ቃል መልሰው ተዉት። «ስንት ወይዘሮ የተሳለመውን የሰዒድ ፓሻን ባለሟል ክንድ መያዝ ፈራችሁ? ሲሉ ጥቂቶች ወታደሮች ብዙም ሳይንገላቱ ክብብ አድርገው ያዟቸው።

«ገዝቻለሁ! ገዝቻለሁ! ‹እጁን የሚያሳርብኝ በሰማይ በምድር ውገዝ እከመ አርዮስ› ገዝቻለሁ! እንዳትነኩኝ ገዝቻችኋለሁ! ቴዎድሮስንም አውግዤአለሁ!» አሉ አቡነ ሰላማ፤ ሳይስቡት ድንገት በመታሰራቸው ከተለመደው አነጋገራቸው በላይ ቢጮሁም እንደ ዕብድ አስመሰላቸው እንጂ ለጊዜው ሰሚ አላገኙም።

ማምሻውን ሰፈሩ ርጭ ያለ ጸጥታ ሰፈነበት። ብዙው ሠራዊት ግን በደረሰው ሁናቴ አንዳች የሐሳብ ሸክም ስለ ተጫነበት ተዝናንቶ ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚጨዋወት አልነበረም። ከፊሉ በየማደሪያ ተጋድሞ ዕድሉን ያነብበት ይመስል ከዋክብት ይቆጥራል ሌላዉ ከእሳት ዳር ተቀምጦ ከነበልባሉ ከፍሙ ጋር የዝምታ

ውይይት የሚያደርግ ይመስላል። በዚህ ጸጥታ በዋጠው ጨለማ ሲያተምምና ሲያንጎራጉር የሚሰማው የቴዎድሮስ በገና ብቻ ነበረ።

የተቃኘ ደረቅ ጅማት ሳይሆን ሕይወት እንዳለ ፍጡር እያነባ የሚያንጎራጉር ሆድ እያባባ.....

# ሦስተኛ መጽሐፍ

# አባ ታጠቅ

የቋጥኙ ላይ እሬሳ

የዚያ አምበሳ

የካሣ

በመቶ ዓመቱ ቢያገሳ

ስንቱን

ስንቱን ቀሰቀሰውሳ።

(ሰይፉ መታፈሪያ፤)

(‹የተሰፋ እግር ብረት›)

# ምዕራፍ ሰባት

ዐቀበት ሲወጣ ወደ ኋሊት እየሳበ ጊዜ የመውሰዱን ቁልቁለት ሲወርድ ደግሞ ሳይወዱ የማንደርድሩን ያህል፤ ቴዎድሮስ ማዕከላዊ መንግሥት ለመመሥረትና ለማጽናት አገር ለማደላደል በሠራዊትም፤ በቤተ ክርስቲያንም አዲስ ሥርዓት ለመዘርጋት ሕዝብ ለማረጋጋት አዲስ ዐይነት ተስፋና ሕይወት ለማሳየት ከዐሥር ዓመት በላይ የፈጀባቸው የተግባር ሕንፃ መፈራረስ ሲጀምር እንደ ናዳ ተከታትሎ ለመውረድ ጊዜ አልወሰደበትም።

ዳሞት ላይ ቆንስል ካሜሮን አቡነ ሰላማን አስረው ከተመለሱ ወዲህ ድደግሞ የፍራሽ ናዳው ፋታ የማይሰጥ ሆነ። ቴዎድሮስ ያላሰቡት የመጀመሪያው ናዳ የወረደው ደብረ ታቦር በገቡበት ዕለት ነበር። መሽታ ቤቶች በበዙበትና ነጋዴውም ወታደሩም በሚሠማራበት አካባቢ ማምሻውን ከባድ አምባጓሮ ተፈጥሮ ከዱላ ዐልፎ የተጧጧፈ ተኩስ ቀለጠ። በግርግሩ መኻል ከአንዱ በተነሣው እሳት ሳቢያ ብዙ ቤቶች ተቃጠሉ። በዚህ ምሽት ደብረ ታቦር የጠፋው ንብረት የሞተውና የቆሰለው ሰው ከዚያ በፊት የማይታወቅ ዐይነት ነበር። የደብረ ታቦር ነዋሪ መዓት የመጣ መሰለው። አንዱም የተረጋገጠ መነሻ አላገኘም። የሚያወራው በወሬ ወሬ የሰውማውን ብቻ ነው።

ምናልባትም ግዝቱ ተሰምቷቸው የአቡነ ሰላማን እስራት በሚቃመውና ቴዎድሮስን በሚደግፉ መካከል እንደ ዋዛ የተነሳው ክርክር በሞቅታ ኃይል ወደ ተካረረ አምባጓሮ አምርቶ ሊሆን ይችላል። በሴት ምክንያት በወታደሮች ወይም በወታደሮችና በነጋዴዎች ምክንያት የተፈጠረ የቅናት ጠብ ወደ ሌሎቹ ተጋብቶ ይሆናል። ምናልባትም ደግሞ የአቡነ ሰላማን ግዝት አምነው የተቀበሉ የክርስቲያኖች ባደረባቸው ስሜት ቀደም ሲል በእስር ላይ የቆዩት የፈላሻ ሚስዮናውያን በኋላም ቆንስል ካሜሮን በገንዘብም በስብከትም ያዘጋጁዋቸው ሆን ብለው የጠነሰሱት ሤራ ሊሆን ይችላል። ወይ እንዳጋጣሚ ሁሉም ተደማምሮ ይሆናል።

ያም ሆነ ይህ ብዙው ሰዋስቦም ሳያስብም ፈልጎም ሳይፈልግም ከሥረ መሠረቱ እንደ ተናጋ ሕፃን የቴዎድሮስ ደጋፊና ተቃዋሚ በሚሆን ከሁለት እየተሰነጠቀ መጣ። ትንሽ አምባጓሮ በተነሳ ቁጥር ከሁለት ተከፍሎ ከተጨፋጨፈ በኋላ ተቃዋሚው ወገን የገደለውን ገድሎ፤ የሞተበትን ትቶ ከደብረ ታቦር እየኮበለለ ሲወጣ ያኛው እየተከተለ ሲያሳድድ፤ በመካከሉ የአቅራቢያውና የአካባቢው ገበሬ፤

መንገድ መርተሃል፤ አስጠግተሃል እየተባለ አብሮ ሲመታ፤ ግጭቱ ጥፋቱ፤ ምሬቱ ከቀን ቀን እየተስፋፋና እየከፋ ሔደ።

የልብ ልብ እየተሰማው፤ በስሜንና በምሥራቅ ከወሎ፤ በምዕራብና በደቡብ ከጐጃም የሚመጣው ሽፍታም በሰላም ሊቆጣጠሩት የሚችሉትን ግዛት እያጠበበው ስለ ሔደ፤ ሠራዊቱ በዚያው መጠን ቀለብ ሲያስጥርበት ወደ ዘረፋ ማዘንበሉ አሳሰበው።

ሠራዊቲታቸውም ሆነ አገር ያላወቀው ነጋዴ፤ ከደብረ ታቦር እንዳይወጣ ቴዎድሮስ በጥብቅ የደነገቱት ዘረፋውን፤ የወታደራቸውን ከዳትም ለመግታት ነበር። በየኬላውም ተቆጣጣሪ ዘብ ተደረገ። ግን አልሆነም።

ደብረ ታቦር ዙሪያውን አጥር እንደሌለው ሁሉ፤ በየምሽቱ የሚከዳውን ወይም ጨለማ ተገን አድርጎ ለመረበሽ ተሾልኮ የሚገባውን ማገድ አልተቻለም። እንዲያውም በተቆጣጣሪ ዘብና በእምቢተኛ መካከል ያለ ማቋረጥ የሚደረገው ግጭት የደብረ ታቦርን ከተማና አካባቢውን ጸጥታ ነሣው። መርዶ፤ ቀብር፤ ኀዘን፤ ለቅሶ፤ የዘወትር ኑሮና ትርዒት ሆነ። የቴዎድሮስ ብስጭት በዚያው መጠን እያከለ ሔደ።

አንዳንድ ሰዎች በድፍን ግምት የተስፋ ተስፋ እንዳደረጉት ራሳም የተባለው ሰው ከእንግሊዝ መንግሥት ተልኮ መምጣትም፤ በቴዎድሮስ ላይ የተሻለ ሁናቴ አላስከተለም። ራሳም ያመጣላቸውን የሩቅን አቅርቦና አጉልቶ የሚያሳይ መነጽር ስጦታ የወደዱለት ከመሆኑ በቀር ደህና የትሕትና አቀራረብ ዐዋቂ ስለ ነበር፤ ቴዎድሮስ ከሌሎቹ የተሻለ አክብሮት አሳይተውት ነበር። ዐልፎ ዐልፎም በኁልቱ መካከል ልዩ መተሳሰብ የታየበ ጊዜ ነበር። ነገር ግን ቀደም ሲል ለጠየቁት የባለሙያ እርዳታ «ይመጣሉ ግዴሎትም» ከሚል የተስፋ ቃል በስተቀር የሚፈልጉትን የተረጋገጠ መልስ ሊሰጣቸው ስላልቻለ እንደ ሌሎቹ በመጨረሻ እሱም ታሰረ።

የውጭ አገር መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ ስላላቸው ዓላማ የቴዎድሮስን ጥንካሬ የሚያጠናክር ሌላም ተጨማሪ ወሬ ደረሳቸው። ይኸውም ከእስክንድርያ እስከ ምድረ ሱዳን የምድር ባቡር ዝርጊያ መጀመሩ ነበር። ቴዎድሮስ፤ ለዚህ የባቡር ሐዲድ ራሳምን ደጋግመው ጠይቀውታል።

«ወንድሜ ራሳም፣ ይህንን የባቡር ሐዲድ ምን ልታረጉበት ነው?»

«ንግድ ይስፋፋበታል። ሰው ይመላለስበታል። ይጠቅማል እንጂ ምን ጉዳት አለበት?»

«መጥቀሙንማ መቸ አጣሁት፤ ጥቅሙ ለሌላ መሆኑን እንጂ!»

«ሌላ ምንም ስውር ዓላማ የለበትም!!»

«አገሬን ለመውረር ሠራዊት የምታጓጉዝበት መሆኑን መቸ አጣሁት። አንተማ ዛዲያ ይኸንን አምነህ ልትነግረኝ ኑሮዋልን? እንዲያው ለነገሩ ተሰይድ ፓሻ የኔ ወዳጅነት አይሻላችሁም ነበር? ግን እናንተ የምትፈልጉት ወዳጅ ብቻ ሳይሆን አሽከር ጭምር የሚሆናችሁን መሰለኝ። እኛ ሁለቱንስ አንሆናችሁም። አሽከርነቱን እናውቅበታል። አይሆንልን..... ይሁንና፣ ከሌሎች ሕዝቦች እንደ ለመዳችሁት ወገኔ በቀላሉ የሚበገርበላችሁ ይመስላችኋል? ተሆነ እናያለና!» ይሉታል በምጸት።

ራሳም፣ ጥርጣሬያቸውንና ሥጋታቸውን ሊያስተባብል ይሞክራል። ቴዎድሮስ ሳይቀበሉትም፤ በብርቱ ሳይከራከሩበትም በሆዳቸው የቋጠሩትን ቋጥረው ነገሩ የተዉት ይመስላሉ።

ግን ዓላማቸውን ባዶ ሕልም ብቻ በማድረግ፣ መገንባት የጀመሩትን በመናድ፣ በውስጥ አንድ አካል መሆን የያዘችውን ኢትዮጵያን ለመንገነጣጠል ከተንሡት ዓመፀኞች ጋር፣ ከውጭ እንደ ሕንድ፣ እንደ አፍሪቃ፣ ኢትዮጵያን ለመግዛት ከሚመጡ ወራሪዎች ጋር፣ የመጨረሻ ጦርነት ማድረጋቸው እንደማይቀር ስለሚሰማቸው የሚያዋጣ እንደ መሰላቸው መዘጋጀታቸውን ከጀመሩት ቆይተዋል።

የዝግጅታቸው አንዱ ክፍል መቅደላ ነበር።

የሰብል ዐይነት ሁሉ በአንድነት እንደሚወቃበት የአንድ ጐጥ የጋራ አውድማ ሁሉ፣ ወሎዬው፣ ትግሬው፣ አማራው፣ ኦሮሞው፣ ከዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ ሲገናኝ፣ ሲጣላ፣ ሲፋለም፣ ሲዳቀል፣ ሲቀላቀል ኖሮበታል። ለዚህም ዋናው መናኸሪያ በአድላ ደላንታ የሚገኘው የመቅደላ አምባ ነው።

ለምሽግነት የሰጠ አማካይነቱ ያመቸ በመሆኑም ጦርነት ያሰበ መኮንንና አዲስ የተነሣ ሽፍታ ተሽቀዳድሞ መያዝ የሚፈልገው የመቅደላን አምባ ነበር።

ቴዎድሮስ ወደ ወሎና ሸዋ ሲዘምቱና ሲመለሱ፣ ወይዘሮ ወርቂት ሠራዊት አንሥቶ አፍላ ጉልበት የተሰማው ሽፍታ መሸጉበት እያገኙ ደጋግመው ከአስለቀቁ በኋላ፣ በመጨረሻ ጠባቂ ወታደር በማስፈር፣ ቤትም፣ ክትርም አሠርተውበት ነበር። እየቆየም፣ ዓላማቸው ከቀን ወደ ቀን እየተሰናከለ ሲሔድ፤ ከቋራ እስከ አንኮበር ሲያንከራትታቸው ለኖረው ሕልማቸው የመጨረሻ መናኸሪያ መቅደላ

አምባ እንዲሆን የወሰኑ ይመስል፣ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የታሪክ ቅርሶችና የክብር ዕቃዎች እየተሰበሰቡ በዚያ እንዲቀመጡ ማድረግ ጀምረው ነበር።

እንደ ጎንደር ከተማ፣ ደብረ ታቦርም በአሉባልታ በወሬ በሤራ መበከል ከዚያ ወዲያ እያስጠላቸው ሔድዋል። ልጃቸው ዓለማየሁ በዚህ በሽታ መካከል እንዲያድግ አይፈልጉም።

ከሁሉ በፊት ግን፣ የጋፋቱ ሥራ መጠናቀቅ ነበረበት።

ቴዎድሮስ ሐሳባቸውን እያውጠነጠኑ፣ ምሬታቸውን እያብሰለሰሉ፣ ብቻቸወን በየመስኩ፣ በየዱር ይዘዋወራሉ። ዛፉን፣ ዝግባው፣ ዋርካው፣ ጥዱን፣ ወይራውን፣ በስስት እየተመለከቱ፣ ቁጥቋጦውን እያሰሱ፣ አበባውን እያደነቁ፣ ለዚህ እህል ለዚያ እህል፣ ለግጦሽ ለመስክ የሚሆነውን መሬት ያስተውላሉ፣ ወይም ደግሞ ከአንድ ቦታ ላይ ይቀመጡና ከሩቅ፣ ከአድማስ ጀምሮ እስከ አጠገባቸው መስክ ድረስ ዐይናቸው የሚደርስበትን ሁሉ ይቃኛሉ። ከሰማዩ ጋር የተጋጠመ የሚመስል ተራራውን፣ ከሥሩ የተጋደመ ረባዳውን፣ ከአንድ በኩል የተንጣለለ ሜዳ ሌላውንም ሁሉ በተራ በተራ ያዳርሱና ያስተውሉና ፍዝዝ ቅዝዝ ይላሉ። አገር፣ እናት ሀገር እትብት፣ ሕይወት የሆነች አገ ልትገዛ? ልትወሰድ? ላትኖር፤ ላንኖር?

መንፈሳቸውን ሰቀቀን ተጭኖት፣ ወደ ቤት ወይም ወደ ድንኳናቸው ሲመለሱ ጥቂትም የሚያጽናናችው ልጃቸው አለማየሁ ነበር።

«አባዬ!» ይላቸዋል፣ ጉልበታቸውን ተደግፎ በመቀመጥ።

«ወዬ ዓለሜ!»

«እስቲ ተረት አጫውተኝ!»

«ምን ዐይነት ተረተ ልጅ ዓለም?»

«የጦርነት! ደስ ደስ የሚል!» ከዕድሜው በላይ ንቁ የሆነው ዓለማሁ የአራዊትም ይሁን የሰው አብዛኛውን ጊዜ መስማት የሚወደው የውጊያ ታሪክ ነው።

«ጦርነት ምን ያረግልሃል። ጦርነት መጥፎ ነው» ይሉታል ጉንጬን በቁልምጫ ቆንጠጥ እያደረጉ።

«ዛዲያ አንተ ሁልጊዜ ለምን ውጊያ ትሔዳለህ?» ሲል ይጠይቃቸዋል።

«ወድጅን መስለህ? ‹በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል› ስለ ሀገርና አንድነት፣ ስለ ምኞታቸውና ስለ ሥጋታቸው ሊያወያዩትና ሊረዳላቸው ከሚችለው ዕድሜው

ገና ባለመድረሱ፤ ግን የልጅነት ፍላጐቱን ለመፈጸም ሳይሠቅቅ የሚያስደንቀውን፣ ሳያስፈራ የሚያስገርመውን፣ ጀግንነት ጋር ርጎራጌ፣ ከድፍረት ጋር ብልሃት የሚያሳየውን በሐሳባቸው እየመረጡ ያጫውቱታል። ግን የልጅ ፍቅርና የልጅ ጨዋታ ብቻቸውን፣ የሕይወታቸውን ባዶ እየሆነ መሔድ፤ ሊተካላቸውና ሌላ ፍላጐታቸውን ሊያሟላላቸው አልቻለም። ተፈጥሮዋቸው እጅግ ሠፊና ውስብስብ ሰብአዊ ግንኙነቶችን ይፈልጋል። ዓለማየሁ በመጠኑም ቢሆን ልባቸውን ለተወሰነ ጊዜ የሚያቅላቸውን ያህል፣ ይህንን ውብ ልጅ ያገኙባት እናት፤ ጥሩ ወርቅ ደግሞ፤ ከዕለት ልባቸው የፍቅር ውርጭ የምታስመታ ሆነች።

የፍቅር ፍላጐታቸውን በማርካት ረገድ፣ ወትሮም እምብዛም የነበረችውን ያህል ዓለማየሁን ከወለደች በኋላ ደግሞ ግዴታውን ተወጥታ ያበቃች ይመስል የሚስትነት፣ የሴትነት ድርሻዋን እርግፍ አድርጋ ተወችው።

አንድ ቀን ቴዎድሮስ፣ ውጭ ውለው እልፍኝ ሲገቡ ጥሩ ወርቅ የልጃገረድ ሱሪ ታጥቃ ቆየቻቸው። እንዳጋጣሚ ፈቅደው ነበርና በትዝብትና በመገረም እየተመለከቱ «ምነው? መንገደኛ ነሽ እንዴ? ሲሉ ጠየቋት።

«ባልሆንስ ምነው? ነውር አለብት?» ስትል መለሰችላቸው።

«ኧረ አልወጣኝም» አሉ ቴዎድሮስ ስሜታቸውን ውዋጥ አድርገው.... ከተዋበች ጋር ከቆረቡ ወዲህ ያን ዕለት ለመጀመሪያ ጊዜ፤ ከጋብቻ ውጭ ሌላ ሴት ዘንድ ሔዱ። የሚፈልጉትን ያንድ ለአንድ ፍቅር ለማግኘት ባለመቻላቸው እያደር ሌሎች ዕቁባቶች አስቀመጡ። ከአንድ ሁለት መለኪያ የሚያልፍ ከነበረው መጠናቸው በላይ አረቄ መጠጣት ጀመሩ። ጥሩ ወርቅም፤ አንድ ዐይነት መከላከያ ጋሻ ያበጀች ይመስል ሱሪ መታጠቋን ቀጠለችበት።

ቴዎድሮስ እንደ ዓለማቸው ሁሉ የግል ሕይወታቸውንም ጭጋግ አለበሰው። የዓለማየሁ ማጽናናት ማጫወት የመንፈሳቸውን ሸክም ሊያቃልል የማይችል እየሆነ ሔደ።

እንዲያውም ዓለማየሁ ነፍስ እያወቀ ሲሔድ፤ የአባቱ ሐሳብና ሠቀቀን በሊጋ ሕይወቱ ላይ የተጫነ ይመስል፤ ወይም ደግሞ እንደ አባቱ ደብረ ታቦርን መጽየፍ የጀመረ ይመስል፤ እንደ ዕድሜ እኩያዎቹ ብዙ መዘዋወሩንና መጫወቱን ተወው። በገጽታው ላይ ከልጅ ፍንደቃ ይልቅ፣ ሐሳብ እንደሚያመዝንበት ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ አስተውለዋል። ይህም ሆኖ፣ ውጭ ውለው ሲመለሱ፣ የውስጥ ስሜቱን እንደ ምንም በፈገግታ አልብሶ ከበር ላይ ይቀባላቸው ነበር። አንድ ቀን ይህንንም አስታጐለ።

«ምን ሆንክ የኔ አካል?» ጐንበስ ብለው ጉንጩን እየደባበሱ ጠየቁት።

«ምንም አልሆንኩ አባዬ!» ዓለማየሁ ፊቱን ለማሳየት ያልፈለገ ይመስል አንገቱን ቀና አላደረገም።

«ዛጊያ እንደ ሽማግሌ ብቻህን ምን አፍዝዞ አስቀመጠህ? በል ተነሥ?»

ተነሥቶ ፊቱን ሲያስተውሉት፤ አንድ ነገር እንዳገኘው እርግጠኛ ሆኑ። ዕንባው የደረቀበት በሁለት ጉንጮቹ ላይ ጥድ ትልም ሠርቶ ነበር።

«እናትህ መታችህ? በማለት እንደገና ጠየቁት፣ በማቆላመጥ አኳኋን እጁን ጨብጠው ወደ እልፍኝ ሲያመሩ።

«ኧረ አልነካችኝም!»

«ዛዲያ ከልጆች ጋር ተደባደብክ?»

«ብደባብስ የኔ እጅ ጨብጧል?» ሲል ዓለማየሁ መለሰ በተወጠረ ፈገግታ።

«የኔ አንበሳ! ጎበዝ መሆንክ መቸ አጣሁት። ብዙ ሆነው ገጥመውህ እንደሆነ ብዬ ነው እንጂ።»

«ለምን ብዙ ቢሆኑስ እኔ እፈራቸዋለሁ?»

«ጎሽ ግልግል አንበሳዬ!»

«ለምን ሺህ አይሆኑም!» አለ በልጅነት ድፍረት።

«እሺ፣ የኔ አካል ዛዲያ ለምን አለቀስክ?» አሉት ቴዎድሮስ እልፍኝ ገብተው ከተቀመጡ በኋላ፣ በጉልበታቸው መኻል አጣብቀው እያቆላመጡ።

«አላለቃቀስኩምኮ አባዬ!» ከጣብቂያው ፈልቅቆ ለመውጣት በቀልድ መልክ ታገላቸው።

«ዛዲያ ይኸ ዕንባ ተየት መጣ?»

«እንዲያው ነው።»

«አንድ ነገር አግኝቶሃል?»

«ምንም አልሆንኩ እያልኩህ!»

«ውሸት!»

«እውነቴን ነው!»

«እስቲ ሙት በለኝ!» አሉት ቴዎዶስ በውሸት ፍጥጫ።

«ለምን ትሞታለህ አባዬ!»

«እውነቱን ተነገርከኝ፤ እንኳን ሞት ጉንፋንም ባጠገቤ ዝር አይል። እና፤ እስቲ ‹ምንም አልሆንኩ ሙት› በለኝ!» የዓለማየሁን ጉንጭ እንደ መቆንጠጥ አደረጉት። «በልኮ።» ዓለማየሁ እንዲመታው የዘረጉለትን እጃቸውን ጨብጦ ዝም አለ። ለመማል አለመፈለጉ ያስታውቅ ነበር።

«በል እንግዲያው የሆንከውን ንገረኝ።»

«እኔማ ምንም አልሆንኩ!»

«እዛዲያስ!»

የመጣበትን ልቅሶ ለመግታት ሰውነቱን ወጥሮ ከአቅማማና ከተጨነቀ በኋላ ተነፈሰው። «ሰዎች የሚጠሉህ ለምነው አባዬ?» ሲል በቦዘዙ ዐይኖቹ እየተመለከተ ጠየቃቸው።

«መቸም ሰው ሁሉን ሰው አይወድም። ሁሉ ሰው አይወድደውም። አንድተስ አንዳንድ ጊዜ የማትወደውን ልጅ አለ አይደለም? ግን ሰዎች እንደሚጠሉኝ በም አወክ የኔ አካል? ዛሬ ነው?»

ዓለማየሁ ጥቂት አመነታ።

‹ያባትክን ጥፋት ነጋ ጠባ እየሰማህ ስታነባ ኑረሃል ማለት ነው?› ብለው በልባቸው ቴዎድሮስ በአዘኔታ ከንፈራቸውን መጠጡ። ዕንባ ቀጠቀጣቸው። «እሺ ዛሬ ያስለቀሰህን ብቻ ንገረኝ። ታለበለዚያማ የመከረኛ አባትህን ስንቱን ጉድ ታወራው ብለው የኔ አካል። ፍርጃ ነው!»

ዓለማየሁ ያረፈበት ይመስል አንገቱን ጥቂት ደፋ አድርጎ በዕለቱ የደረሰበትን ነገራቸውን።

ከምሳ በኋላ ወደ መስክ ወጥተው ለመጫወት፣ ከሦስት ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ፈረንጆቹና ኢትዮጵያውያን ከሚጠበቁበት ሰፊ አጥር ግቢ አጠገብ ሲደርሱ ውሻ የሚከተላት አንዲት ሴት ያገኛሉ። ስንቅ አድርሳ መመለስዋ እንደሆነም እንጃ ገልገል ይዛለች። ሊተላለፉ ሲሉ ውሻው ያጉረመርምባቸዋል። አንደኛው ጓደኛቸው በትሩን ይቃጣበታል።

የሐር እጅ ጠባቡ የቀልም ድምቀት ዐይኑን ስቦትም ይሁን እንጃ፤ በትር የቃጣበትን ልጅ ትቶ ዓለማየሁን ለመንከስ ይሞክራል። ዛዲያ መቸም ዝም ብሎ አይነከስ! ወይ ሴትየዋ ውሻውን አልያዘችለት። ዓለማየሁ፣ በትሩን ዘርግቶ ከተከላከለ በኋላ በመጨረሻ አንድ ሁለት ጊዜ ይለምጠዋል።

ሴትዮዋ፣ ዓለማየሁ እንዲነክስ ትፈልግ የነበረ ይመስል፣ ውሻው ከዱላው ወደ ኋላ ሲያፈገፍግ ጩኸትዋን ትለቀዋለች። በእሪታ ሠማይና ምድሩን ታደባልቀዋለች። እርግማኑና ስድቡን ታወርድበታለ። አላፊ አግዳሚውም እየቆመ ለሴትየዋ ያግዛል። እስረኞቹም በአጥሩ ላይ ሆነው ከሴትየዋ ጋር በማበር ብዙ ይጨዋጨሁበታል።

በመካከሉ ጓደኞቹ ጥለውት ሲሮጡ ዓለማየሁ አንዳች ዐይነት እልህና ንዴት ድርቅ አድርጎ ይዞት፣ በመለፍለፉ እስኪ.ታክታቸው ድረስ ያስጨርሳቸዋል። «ግን ፊትኮ አላለቀስኩ፣ አባዬ!» አለ ዓለማየሁ የሆነውን ተናግሮ ሲያበቃ።

«ጎሽ የኔ ግልገል። ዛዲያ እንደ ሴት እንባ ልታያሳያቸው ኖሯል?» ሲሉ በማደፋፈር ፊቱን አባበሱት። «ምን ምን እያሉ እንደ ተሳደቡ እኮ አልነገርኩም?»

ዓለማየሁ መድገሙ ቀፍፎት፣ እባክህ ተወኝ በሚል አስተያየት ተማጠናቸው።

«ንገረኝ እንጂ ምን አሳፈረህ? በአደባባይ ተዘርቶ አገር ምድሩ የሰማውን?»

«ጨካኝ የጨካኝ ዘር አለችኝ» አለ ዓለማየሁ የልጅ መልኩን ጭፍግግ አድርጎ።

«ደሞስ ሌላ?»

«እንደ አባትህ አረመኔ ነፍሰ ገዳይ ነህ» አለችኝ።

ቴዎድሮስ በምሬት እንደ መሣቅ ብለው ራሳቸውን ነቀነቁ። «እሺ ሌሎቹስ ምን አሉኝ?»

«ተስረኞቹ አንዱ፣ ‹አትፍረዱበት ሰውነቱ ጠንክሮ እንደ አባቱ ጭከናውን በሰው ላይ እስቲፈጽም ድረስ በእንስሳ ድረስ በእንስሳ እየተለማመደ ነው› ሲል የነበሩት ሁላ ተሣሣቁብኝ። ሌላም ብለዋል።

ቴዎድሮስ፣ ቆዳቸውን ለመላጥ የፈለጉ እስኪመስል ድረስ በሐሳብና በጭንቀት ፊታቸውን በመዳፋቸው ፈተጉት። «እኔንስ መቸም እንዳሻቸው ያሉኝን ይበሉኝ። እንደ ሐሳቤ፣ እንደ ዓላማዬ የልቤን የሚያውቅ ይፍረደኝ፤ ይፍረድብኝ። እኔ እንደሆን ከዚህ በኋላ ምንም ግድ የለኝ። ግን አንተን ደሞ ምን አርግ ነው የሚሉ የኔ አካል? ለዐዋቂ ሰውም ቢሆን ያንዱ ጥፋት በዘር ወደ ሌላው ተላልፎ

አያስጠይቀውም። አያስወቅሰውም። ባገሬው አጉል ልማድ በደም ታልተፈለገ በስተቀር። ዛዲያ ገና እርም ያህል ሕፃን ቁም ስቅል ሲያሳዩ ሌላው ቢቀር ጡር አይፈሩም?» ከአደጋ የሚከልሉት ይመስል ጭምቅ አድርገው አቅፈውት ቆዩ። «ለመሆኑ ሴትየዋን ታውቃታለህ?» ሲሉ ጠየቁት - በመጨረሻ። በአሉታ መለሰላቸው። «እንግዲህ ያለች ናት?» እንደ መስለው የሁናቴዋን ገለጸላቸ።

«በሽተኛም ተሆነች እንዳሻት። ታልሆነችም የርሷ ስድብና ርግማን ለኔ ንስሐ ሆኖ ቢታዘዝልኝ ነው። አንተን ማስደንገጥዋ ጠላሁት። እንጂ የርሷንስ እችላለሁ፤ ሰሞኑን ደሞ መለስ ብላልኝ ሰንብታ ነበር። ድንገት ምን ነካት?» አሉ በመገረም።

«ማናት አባዬ?»

«ስምዋማ ምንትዋብ ትባላለች። ለምን እንደዚህ ሆነች ለሚለው ግን፣ ለልጅ የማይጥም ረጅም ታሪክ ነው። ምናልባት ስትደርስ ወደ ፊት ታውቀው ይሆናል።»

«ግን አባዬ....» ዓለማየሁ ጀመረና በፈራ ተባ አቋርጦ ተወው።

ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ስለ ዓላማቸው ከሚነገሩት ረቂቅ ጉዳይ ይልቅ፤ በሐሳቡ ጎልቶ የሚታየው ቀን የደረሰበትና ከብዙ ሰዎች የሚገነዘበው ክፉ አመለካከታቸው ነበር። በልጅ ምርጫው፤ «እኔና አንተ ለምን ሌላ አገር ሔደን ብቻችንን አንኖርም አባዬ?» ሲል ድንገት ጠየቃቸው።

«ደብረ ታቦር አስጠላህ?» አሉትና የሚያደርጉትን ግን ወዲያው በሆዳቸው ወሰኑ።

ወደ መቅደላ የሚሔደውና ከደብረ ታቦር የሚወጣው ሰው ሁሉ ለመነሣት እንዲዘጋጅ ቴዎድሮስ ባስታወቁበት ወቅት፣ ታንጉት ክፉኛ አምዋት ሰንብቶ ነበር። ገብርዬ ሲነግራት ቀስሮ በያዘ ውጋትዋና እንደ እሳት የሚጋረፍ በሚመስል ትኩሳትዋ መከካል፣ እንደ ምንም እያቃሰተች ተነሥታ ጓዝ ማሰናዳት ጀመረች።

«አሁን ዛዲያ ምን እያረግሽ ነው?» ሲል ገብርዬ ጠየቃት በመገረምና መደናገጥ።

«ሒዱ ተብሏል አላልከም?» ስትል መልሳ ጠየቀችው።

«ዛዲያ እንደዚህ ሆነሽ መንገድ ልትነሽ ኑሮዋል? ስለ ወደ ፊቱ ነገርኩሽ እንጂ!»

«ደኅና ነኝ። ምንም አልል» አለች ታንጉት፣ የመቅደላው ጉዞ የሥጋትዋ አንድ መገላገያ ሆኖ እየታያት የጊዜው ሕመምዋን ቻል አድርጋ።

የቴዎድሮስ ጥረት ሁሉ በዚህም በዚያም እየተበላሸባቸው፣ ሰቀቀናቸውና ብስጭታቸው በዚያው መጠን እየከፋ መሔዱን ታንጉት ስትመለከት፣ ጥፋትዋን ተናዝዛ ይቅርታ የማግኘቱን ሐሳብ ተስፋ ከቆረጠችበት ቆይታለች። ከሚስተር እስተርንም ሆነ ከሌላ ምሥጢሩ ወጥቶ፣ የቴዎድሮስ ቁጣ የሚሰነዘርባትን ቀን ነበር በጭንቀት የምትጠብቀው። ይህም ጭንቀት በጤንነትዋና በሰውነትዋ ላይ ለወጥ አስከትሎ ነበር። ያለ ወትሮዋ ብዙ ጊዜ ራስ ምታት ይነሣባት ጀምሩዋል። ጉንጭዋ ላይ በሚያምሩት ስርጉዶቿ ፈንታ የመጠውለግ መሥመሮች ጐልተው ይታያሉ። ትንሽ ትልቁ ነገር ብስክስክ ያደርጋታል። ደግነቱ ገብርዬ አብዛኛውን ለዘመቻ ስለሚንቀሳቀስ፣ ሁናቴዋ በሁለቱ ግንኙነት ላይ ስለሚያመጣው ለውጥ የመገንዘቢያ ርጋት አልነበረም።

ቴዎድሮስና ጥቂት የጦር አበጋዞቻቸው፣ ጋፋት ቀርተው ታንጉትና ሌሎቹ መቅደላ መቀመጣቸው ከፊት መራቅ ከልብ መራቅ ነውና ከልብ መራቅም፣ ከቁጣም ሆነ ከፍቅር ስሜት ራቅ ማለት ነውና፣ ምሥጢርዋ ተቀብሮ ከጊዜ በኋላ ተረስቶ እንዲቀር የሚያደርግ መልካም አጋጣሚ መሰላት። ሕመምዋ ብርቱ መሆኑ ቢሰማትም እንደ ምንም ቶሎ መራቁን መረጠች።

«አሆሆ! ኧረ ተይ! ስንኳን በከብት በቃሬዛም አትችይ!» አላት ገብርዬ በእጁ እንደ መከልከል እያደረገ።

«እችላለሁ አልኩህ!» ታንጉት ጓዝ ማሰናዳቱን በእልህ ተያያዘችው።

«ተይ ስልሽ? ተይ!» አለ ገብርዬ በቁጣ መልክ።

«አንተስ ያባ ታጠቅን ትእዛዝ ማለትህ ነው?» አለች ፍርጥም አድርጋ።

ገብርዬ፣ ምክንያቷን ሊገምት ባይችልም፣ ድርቅ ብላ መነሣትዋ ደስ አላለውም። «ተመንገድ ላይ አንድ ነገር ብትሆኚ፣ አባ ታጠቅ የሚወቅስ እኔን። እንዲያውም መታመምሽን አልነገርኩትም። ታንቺ ጋራ ተመጨቃጨቅ እንዲያውም አሁኑኑ እነግረዋለሁ። ራሱ ይወስናል።»

ቴዎድሮስ ማምሻውን ከገብርዬ ቤት መጥተው፣ ሁናቴዋን ከአዩና፣ ግንባርዋን በመዳፋቸው ዳሰስ ትኩሳትዋን ከገመቱ በኋላ፣ «ለመሆኑ መቸ ነው የጀመራት?» ሲሉ ጠየቁ።

«ሦስት ቀን ሆናት» አለ ገብርዬ።

«ዛዲያ ለምን አልነገርከኝም?»

«ባንተ ቤት እኔ ተጨማሪ ሐሳብ ውስጥ እንዳልገባ ብለህ ነው። አይደል? ደግ አላደረግህም።» ወደ ታንጉት ዘወር አሉ። «መንገዱን ስትድኚ ትደርሺበታለሽ። ነገ ጧት ግን፤ ተቻልሽ በከብት ታልቻልሽ በቃሬዛም ቢሆን፤ ጋፋት ሔደሽ ሐኪም ብላንክ አይቶ ያክምሻል።

የሕክምና ችሎታ ያለው ዶክተር ብላንክ፣ እስከ ጥቂት ውራት በፊት ድረስ ከሌሎቹ ፈረንጆች ጋር ደብረ ታቦር በእስር ላይ ነበር። የጋፋቱ ባለሙያ ሚስተር ዋልድሜየር፣ ከጥቂት ወራት በፊት ሚስቱ ወንጌለ በጣና ታማመችና፣ ዶክተር ብላንክ ጋፋት በአጠገብዋ ሆኖ እያከማት እንዲሰነብት ቴዎድሮስን ለመነ። ሊቀ መኳስ ቤል ከኢትዮጵያዊት ሚስቱ የወለዳትን ወንጌለን፣ ቴዎድሮስ ለዋልድሜየር ራሳቸው የዳሩለትና እንደ ልጃቸው የሚያይዋት ስለሆነች ያለ ማመንታት ፈቀዱለት። ዶክተር ብላንክ፣ ወንጌለን እያከመ ጋፋት ሲሰነብት፣ በብረት ማቅለጫው እሳትና በሌላም የሚደርሰውን የአደጋ ቁስል በማከም ረገድ ብዙ ስለረዳ በዚያው እንዲቆይ ተደረገ። በዚያው የጋፋት ሐኪም ሆነ። ቴዎድሮስም፤ የእስረኛነቱን ጉዳይ ትተው ‹ሀገራችሁ አለ እንደምትለው ትልቅ ቤት እሠራልህና ወገኔን ሁሉ ታክምልኛለህ። የኔንም ሰው ጥበቡን ታስተምርልኛለህ› ይሉት ነበር።

በበነጋው ጧት፤ ቴዎድሮስ እንደገና ወደ ገብርዬ ቤት መጥተው ታንጉትን በቃሬዛ አሸከመው ወደ ጋፋት መንገድ ሲጀምር፤ «ጥሩ ወርቅን ሸኝቼ እኔም እመጣለሁ» ብለውት ገብርዬን፣ ወደ ቤተ መንግሥት አመሩ።

ቴዎድሮስ፣ የጉዞውን መሰናዶ በአጠቃላይ ቃኘት አደረጉና ከቤቱ ግድግዳ ጥግ ከቋንጣ ወንበር ላይ ተቀምጠው ጥሩ ወርቅን በታከተ ትዝብት ተመለከቷት። ጥሩ ወርቅ እስከ ልብ አልማው የመንገድ ልብስዋን ለብሳ፣ ጸጉርዋን በሻሽ ዐሥራ፣ የኮርቻ በቅሎዋ ስትሰናዳ፤ ፊትዋን አኮሳትራ በንቀት ታስትውላለች። ትልልቁ ጓዝና የጭነት ከብቱ ቀደም ሲል ተነሥቶ ጉዞ ጀምሯል። የቀሩት የጥሩ ወርቅ ደንገጡሮችና አጃቢ ወታደሮች ብቻ ነበሩ። ሁሉም ነገር መዘጋጀቱን ባልደራሱ እጅ በመንሣት ሲያስታውቅ ጥሩ ወርቅ እንደ መነሣት ቃጣትና ቅሪ እንድትባል የምጠብቅ ይመልስ አመናታች።

ዓለማየሁ፣ በልጅ ባሕርይ እንደ ዋዛ ከወዲያ ወዲህ ይበል እንጂ ሐሳቡ በወላጆቹ መኻል ተንጠልጥሎበት ነበር። ነገሩ ትክክል ባይገባውም የማታ ክርክራቸውን ከሞላ ጐደል አዳምጧል። አሁንም በመካከላቸው ዝምታ የሰፈነበት ውጥረት ይሰማዋል። አንዳንድ ጊዜ ስንኳ ተሣሥቀው ሲለያዩ ቢያይ፣ ምንኛ ደስ ይለው እንደ ነበር ያስባል።

«ዛዲያ እህል ቀምሰሽ ብትነሽ አይሻልም?» የሚል የአባቱን ድምፅ ሲሰማ፣ ዓለማየሁ ዝም ብሎ ያዳምጥ ጀመር።

«አላሰኘኝም» ስትል ጥሩ ወርቅ መለሰች።

«ስላላሰኘሽ ሳይሆን፣ ለሆነለት መንገድ በባዶ ሆድ መጀመር ደግም አይደለ!»

«ሰዎቹ ይቁረሱ» አለች ጥሩ ወርቅ አሁንም እንደ ተኮሳተረች።

ቴዎድሮስ ግን፣ ይህንን ሐሳብ እንዳልሰማ ያህል ችላ ብለው ዐለፉት። ምክያቱም ደንገጡሮቹም ሆኑ አጃቢዎቹ ጥሩ ወርቅ ሳትቀምስ፣ ቆርሳችሁ ሒዱ ቢባሉ ፈቃደኛ አይሆኑም። አዲስ ነገር ይሆንባቸዋል። ከፊታቸው ራቅ ስትል፣ ሰዎቹም ለራሳቸው ወስፋት ሲሉ እህል እንዲቀምሱ ሲጠይቋት፣ እሺ ትል ይሆናል ብለው በመገመት ሁሉንም ባንድ ዐይነት በባዶ ሆድ መላኩ የተሻለ መሰላቸው።

«እሺ እንግዲያውስ፣ ፀሐይ ሳይበረታ በረሃውን እንድትሻገሩ ብትነሡ ይሻላል» አሉና ቴዎድሮስ ከተቀመጡበት ተነሡ።

ጥሩ ወርቅ ተነሣችና ክንድዋን ወደ ፊት ዘርግታ ‹ይኸው› አለች።

«ምኑ?» ሲሉ ጠየቁ ቴዎድሮስ የነገሩን አዝማሚያ ቢገባቸውም።

«የስረኛ፣ የግዞተኛ ወጉ ይሟላልኛ!»

ቴዎድሮስ እራሳቸውን ነቀነቁ። ዐይናቸውን እንደ መቆጥቆጥ አደረጋቸው። «ምነው ሁልጊዜ ክፉው ብቻ የሚታይሽ? ክፉ ክፉውን የምትናገሪ?»

«እኔ ምናልኩዎ። ከእስረኛ ጋራ አምባ የምጓዝ ተሆነም ማሰሪአው ለምን ይቀራል ብዬ ነው» አለች ጥሩ ወርቅ፤ ላመል ትከሻዋን ሰበቅ አድርጋ።

«ተዚህ ሥራችንን ስንጨርስ ሁላችንም እንመጣለን እያልኩሽ? ተተጋዝን ያው አብረን ነው።»

«ዓለማየሁ ለምን ተኔ ጋር አይሔድም ዛዲያ?» ስትል ፍርጥም አድርጋ ጠየቀች።

«ትናንት ማታኮ ተነጋግረንበታል እሱን፣ ሩ። ተኔ ጋር ቆይቶ እንመጣለን።

«ተዚህ ሁላ ናለ አገሬ ብገባ?»

«ታገርሽ አይደለም ያለሽው? መላ ኢትዮጵያ አገርሽ ማይዶል? ጎጥ ብቻ መመልከቱን ብንተወው ምናለበት?» አሉ ቴዎድሮስ በምክር ዐይነት።

«እኔ የምፈልገው ባባቴ መቃብር ላይ እየጸለይኩ የቀረኝን ዕድሜ ለመጨረስ ነው።»

«ግዴለሽም የትም ሆነሽ ብትጸልይላቸው ይደርሳቸዋል» አሉና ቴዎድሮስ፣ ‹ስሜንን ይዘሽ ልትሸፍችብኝ -› ሲሉ በሆዳቸው አሰቡ።

«እንግዲያው እሺ ተልጄ ጋር ልሒድ» ስትል ጥሩ ወርቅ እንደገና ጠየቀች።

«አብረን እንመጣለን ብዬሻለሁ።»

«ምን ይሠራል ተዚህ ቀርቶ?»

«ምናለ ባታደርቂኝ፣ ጥሩ? ወንድ ልጅ ታባቱ ጋር አይቀመጥም?» ቴዎድሮስ ጋር አይኖርም?» ድርቅ አለች ጥሩ ወርቅ።

ቴዎድሮስ፣ ትዕግሥታቸው እያለቀባቸው ሔደና፣ «ምን ሊማር? አሉባልታ? ነገር? የለም አልፈቅድም» አሉ በቁጣ።

የጥሩ ወርቅ የተለመደ እልህም አብሮ ጠጠረ። «ተዚህስ ምን ሊማር?»

«ሌላው ቢቀር፣ እኛን ለመግዛት የሚመኙት ፈረንጆች ኃይል ያገኙበት መሣሪያ ሲሠራ ቢመለከት ይሻለዋል። ታሉባልታ» አሉ ቴዎድሮስ ፍርጥም አርገው።

«የሚበጀውን እኔ ዐውቃለሁ።»

«ልጄን ከናቱ የሚለዩት በግድ ነዋ?» አለች ጥሩ ወርቅ እንደ ማልቀስም እንደ መጮህም እየቃጣት።

ቴዎድሮስ በሠቀቀን ራሳቸውን ነቀነቁ። ከንፈራቸውን እንደ መንከስ አደረጉ። «ምን ሆነሽ ነው ከቶ እኔን ክፉ ለማሰኘት የምትጥሪው ጥሩ ወርቅ? ምናለ ሐሳቤን ብትረጂልኝ?» በድንገት ወደ ዓለማየሁ ዘወር ብለው «እሺ መሔድ ትፈልጋለህ? ተኔ ጋር መቆየት?» ሲሉ ጠየቁት።

ዓለማየሁ በጭንቀት አመለካከት ዐይኑን በሁለት መካከል ካንከራተተ በኋላ፣ ለመቆየት መምረጡን በመግለጽ አኳኋን ወደ አባቱ ተጠጋ።

«ይኸው?» አሉ ቴዎድሮስ የዓለማየሁን ራስ እያሻሹ።

ጥሩ ወርቅ ፊቷን የባሰ በማጨፍገግ «ምን ቸገረኝ» አለችና ወደ በቅሎዋ አመራች።

«ሳማት እንጂ እኔ አካል!» አሉት ቴዎድሮስ ዓለማየሁን።

መንገደኞቹ ጉዞ ሲጀምሩ ግን፣ ቴዎድሮስ ሁናቴውን የበለጠ ለማብረድ ሲሉ ሐሳባቸውን በመቀየር፣ ከዓለማየሁ ጋር ሆነው የአንድ ሰዓት መንገድ ሸኙዋቸው።

እንዲሔዱ የታዘዘው ሠራዊት ተቃጠልሎ ወደ መቅደላ ወጣ። ኢትዮጵያውያን እስረኞችም በሙሉ ተላኩ። የቀሩት፣ ወደዚህም ወደዚያም በአፋጣኝ እንዲዘምቱ የሚደረቱት የጦር አበጋዞች ከተወሰነ ሠራዊት ጋር ለጋፋቱ ሥራ የሚያስፈልጉ ሰዎች፣ ፈረንጆቹ እስረኞች ብቻ ነበሩ።

መሻቹም፣ ጋለሞታውም፣ ነጋዴውም እያደር ገበያ ሲያጣ በየ አግጣጫው ተበታተነ። የእስረኛ ስንቅ አቀባዮችም አንዳንዶቹ ወደ መቅደላ ዘለቁ።

ሌሎቹ «እንግዲህ እንዳሻው እንጂ» እያሉ ወደ ትውልድ ሠፈራቸው አመሩ። ደብረ ታቦር ከተማና ጋፋትን ጨምሮ አካባቢው በአጭር ጊዜ ውስጥ ጸጥታና እርጋታ ሰፈነበት።

ቴዎድሮስ የፈለጉም ይህንኑ ነበር። በሐሜት በአሉባልታ፣ በወሬ በመሸታ አምባጓሮና በሌላም የማይረባ ነገር ሁሉ፣ በሐሳባቸው ሳይከፋፈልና በየዕለቱ ሳበጠበጥ የጋፋቱን ሥራ ለማከናወን ፋታ ሰጣቸው።

ከፈረንጆቹ እስረኞች ጋር ያላቸው ግንኙነትም፤ ወደ ዕርቅ ወይም ወደ ስምምነት ባያዘነብልም ከበፊቱ ረገብ አለ።

ሰንሰለቱ ወለቀላቸው። ዘብ በዐይነ ቁራኛ እየተከተላቸው አንዳንድ ጊዜ ከታሰሩበት ግቢ እየወቱ እንዲዘዋወሩ ተፈቀደላቸው። አንዳንዶቹን በተለይ ራሳምንና ካሜሮንን ቴዎድሮስ ወደ ጋፋት ይዘዋቸው ይሔዱና ሥራውን በማሳየት ምክርና አስተያየት ይጠይቃሉ። ቅሬታቸውን አብረው መግለጽ ግን ቴዎድሮስ አልተዉም። «ዛዲያ በዚህ ዐይነቱ ሥራ የበለጠ ሠልጥናችሁበታልና እርዱኝ ብላችሁ እምቢ አላችሁኝ፣ ያፋርደና!» ይላሉ።

«ኧረ እምቢ አላልነም» ሲል ራሳም ይመስላል።

«በጊዜው ደርሶኝ ታልጠቀመኝ ያፍ ደለላው ምን ይረባኝና። ባገሬ ላይ ክፉ ዐይናቸውን ለጣሉባት ጠላቶቼማ ይኸውና ተካይሮ እስተ ካርቱም ባብሩ የሚባል ፈጣን የሰውና የዕቃ ማመላለሻ እየተሠራችሁ ነው አለ። ወይ ነዶ!»

«በጊዜው ይደርሳል አባ ታጠቅ።»

«መቸ ነው የሚደርሰው? አገሬ ተተዋረደች በኋላ? ጅብ ተሔደ ውሻ ጮኸ» አሉ።

ሚስተር ራሳም ነገሩ እንዳይካረር በማለት ጭውውቱን ወደ ሌላ ጉዳይ ለመምራት ይሞክራል። ቴዎድሮስ ግን፣ መልሰው ወደዚያው ይስቡታል።

«አዬ አቶ ራሳም፣ ለምሳሌ፣ ያመጣሁልኝ የሩቁን አቅርቦ፣ ረቂቁን አጉልቶ የሚያሳየው መነጽር መልካም ነው። ዛዲያ፣ ዕውቀትና ኃይል ታላገኘሁ ጠላቴን በሩቅ ማየቱ ምን ይረባል? ለዚህ ነው ያመጣህልኝ? ወይስ አገርህ በጥበብ የደረሰችበትን እንዳደንቅበት? ግዴለም፣ ታሁን ቀደምም በሰው ርዳታ እንዳልኖርን ሁሉ አሁንም ራሳችን እንወጣዋለን» ይሉታል። አነጋገራቸው ግን፣ የቁጣ ኃይለ ቃል ሳይሆን፣ እንደ ተዳፈነ እሳት እንጀት አንጀታቸውን እያቃጠለ የሚወጣ ምሬት ነበር።

ይህም ሁሉ ሲሆን ስለ ፈረንጆች ጉዳዩ ቴዎድሮስ ከመጨረሻው ውሳኔ ላይ አልደረሱም። ባንድ በኩል ከእንግሊዝ ጋር ጠቡ ገፍቶ የሚመጣ ከሆነ በማለት ሐሳባቸው ያተኮረው በመድፎቹ ሥራ ላይ ነበር። በዐይነ ቁራኛ እየተጠበቁ እስከ ቆዩ ድረስ የእስረኞቹን ጉዳይ ምን ጊዜም ሊቆርጡት እንደሚችሉ ያውቁታል። በሌላ በኩል ደግሞ ራሳም ከሌሎች በተሻለ የአቀራረብ ችሎታው ዘወትር የሚነግራቸውን እየሰሙ ምናልባት የሚጠብቁት መልካም መልዕክት እንደሚመጣ ቅንጣት ተስፋ ማሳደራቸው አልቀረም።

ፈረንጆቹ እስረኞች በበኩላቸው ስለ ወደፊት ዕድላቸው ያስባሉ። ይወያያሉ። የሚያስደስተው መልካም መልዕክት ደርሶ ቴዎድሮስ በዕርቅና በሰላም ይለቃቸው ይሆን? ወይስ ቁጣው ጽዋውን ሞልቶ ሲፈስስ፣ አንድ ቀን ከዚህ ዓለም ያሰናብታቸው ይሆን? የእንግሊዝ ጦር መጥቶ ያስለቅሳቸዋል? ወይስ ከዚያ በፊት ቴዎድሮስ እልሁን ይወጣባቸዋል? በተለይ አብዛኛው ሠራዊት ኢትዮጵያን እስረኞችና ዋጋ ያለው ዕቃ ሁሉ ወደ መቅደላ ከተላኩ ወዲህ፣ ፈረንጅ እስረኞችም አንድ ቀን ወደ መቅደላ እንዲወጡ መደረጋቸው እንደማይቀር በመገመት በጣም ሐሳብ ይዟቸው ምን እንደሚሻል ነጋ ጠባ ይወያዩበት ገቡ።

ከመካከላቸው ሚስስ ሮዜንታል ብቻ የተለየ ሐሳብና ስሜት ታስታምማለች።

ራሳም፣ የአስተሳሰራቸን ታሪክ እንደሰማ አለዝቦ መክሮ ሊያቀራርባቸው ቢሞክርም፣ ሮዜንታል በፊት በስሜት እንዳልተዋሐደቻቸው ሁሉ አሁንም በአካል እንጂ በመንፈስ ልትቀላቀል አልቻለችም። በምክራቸው አትካፈልም። በሚመካከሩበት ጊዜ አጋጣሚ በመካከላቸው ብትገኝም፣ የምታስበው ስለ እስረኝነታቸው የጋራ ዕድል ሳይሆን ስለ ራስዋ ብቻ ነው።

ጥሩ ወርቅ መቅደላ ወጥተው ቴዎድሮስ ብቻቸውን መሆናቸው ታንጉት የምትባለው የገብርዬ ሚስ ታማ እየታከመች ጋፋት መቀመጥዋን ሮዜንታል ስትሰማ ደግሞ በብቸኛ ስሜቷ ላይ የተምታታና የተቀላቀለ ሐሳብ አደረባት። መቅደላ አምባ መጋዙ፣ እንደዚሁ ወደ አውሮፓ ከመሔድ የባሰ ሆኖ አልታያትም። እንዲያውም የተመኘችውን የማታገኝ ከሆነ፣ ሕይወትዋን በግዞት ማሳለፍ አንድ ስም ያለው ሰማዕትነት መስሎ ተሰማት። ከዚያ በፊት ግን አንድ የመጨረሻ ዕድል ለመሞከር ፈለገች።

ደብረ ብርሃን ሥላሴ መቃብር ቤት ለእስተርን እየነገረች ያጻፈችው ታንጉት የምትባለው የገብርዬ ሚስት ነበረች። ቴዎድሮስ አሳድጓታል ሲባል ሮዜንታል ትሰማለች። ታዲያ ስለ ቴዎድሮስ ከሌሎች የበለጠ ምሥጢር በም ዐወቀች? ግንኙነታችው ምንድን ነው? ማወቁ አንድ መላ ሊያገኝላት የሚችል መሰላት። በዚህ ላይ ቴዎድሮስ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፉት በጋፋት ነው። ጋፋት ሔዳ ለመሰንበት ቆርጣ ተነሣች።

አንድ ቀን ጧት አሞኛል ብላ ለቁርስ ሳትነሣ ቀረች። ምሳ ሳትበላ በዚያው ዋለች። ራትም እምቢ በዚያው ዋለች። ሌሊቱን ከእንቅልፍዋ በነቃች ቁጥር እያቃሰተች አደረች። በበነጋው የባሰባት መሰለች። ሚስተር ራሳምና ቆንስል ካሜሮን ደባብሰው አዩዋት። ከማቃሰትዋ በስተቀር ትኩሳት የለባትም። ግን ሁለቱን ቀን ከንጹሕ ውሃ በስተቀር ትኩሳት የለባትም። ግን ሁለቱን ቀን ከንጹሕ ውሃ በስተቀር እህል በአፍዋ አልዞረም። መቸም ሰው በጤናው እህል ስለማያስጠላው ሥጋት ገባቸው። በሦስተኛው ቀን ከረሃብ ድካምና ጥውለጋ ጋር፣ ዐይንዋን ስልምልም፣ ሰውነቱዋን ዝልፍልፍ ስታደረግባቸው እንደ መደናገጥ አሉ። «እ.....እ.....እባካችሁ ጋ.......ጋፋት ከዶክተር ብ - ብላንክ ዘንዳ .....» ስትል በሚያቃስት ድምፅ ተማጠነች።

ራሳም፣ ለምኖ ቴዎድሮስን አስፈቀደና ሮዜንታል በቃሬዛ ወደ ጋፍት ተወስዳ፣ ሰፋ ሰፋ ያሉ ክፍሎች ባሉት በሚስተር ዋልድሜየር ቤት በማረፍ ሕክምናዋን ቀጠለች።

የጋፋት የብረት ማቅለጫው የተተከለው ከወንዙ ዳር ሲሆን፣ መኖሪያ ቤቶቹ የተሠሩት ደግሞ ከዳገቱ አፋፍ በአንድነት ክምችት ብለው ነው። ጎጡ ዙሪያውን በግንብ ታጥሮ አንድ ትልቅ ግቢ ሆንዋል። ከዚህ ግቢ የሚኖረው ሁሉ ሳይገናኝ ስለማይውል ሮዜንታል ከታንጉት ጋር ለመገናኘት ብዙ ቀን አልፈጀባቸውም። የፈለገችውም ይኸንኑ ነበር።

ታንጉት፣ ሕመምዋ ተሽልዋት፣ ሰውነትዋ ጠንክሮ ወደ መቅደላ እስክትሔድ ለቴዎድሮስ ምግብ በማበሳሰል እየረዳች ከቤት ወጣ ገባ ማለት ጀምራ ነበር።

ዶክተር ብላንክ፤ የበሽታዋን ዐይነት ለይቶ ባይደርስበትም፣ ሮዜንታል እንደ መጣች ማምሻዋን እህል ቀመሰች። በበነጋው ከአልጋ ተነሣች። በሁለተኛው ቀን ከቤት ወጣች። በዚሁ ቀን ቴዎድሮስና የጋፋት ባለሙያዎች በአንድነት ምሳ ከሚበሉት ከግቢው መኻል ከሚገኘው የድንጋይ ቤት ውስጥ ታንጉትና ወንጌለን ምግብ ሲያሰናዱ አገኘቻቸው። ከዚያ በተቻለ መጠን ታንጉት አልለያት አለች።

ሮዜንታል፣ ምኞቷና ስሜቷ ብቻ እየገፋፉት፣ ነገሩን እንዴት እንደምታውጣጣ፣ ወይም የምትፈልገውን እንዴት በእርጋታ እንደምታገኝ አላወቀችበትም። ነገር ፍለጋ የመጣች ይመስል ከሥር - ከሥርዋ እየተከታተለች ታነበንባለች። ቴዎድሮስን የትና መች ተዋወቅሽው? ዝምድና አላችሁ እንዴ? ጠባዩን በቅርብ ታውቂዋለሽ? ምን ይወዳል? ምን ይጠላል? ታሁኑዋ ሚስቱ ጋር እንዴት ነው? ለምን መቅደላ ላካት? ዛዲያ ካለሴት ብቻውን ይኖራል? አንዳንዱ ጥያቄ ታንጉትን ያሥቃታል። አንዳንድ ጊዜ መልስ እየሰጠች አብዛኛውን ግን በአንድ ጆሮዋ የገባውን በሌላው እንደምታፈስሰው ያህል ችላ ሥራዋን ትቀጥላለች። ብዙ ጊዜ ሁለቱም በመገረም ይመለከቱዋታል።

ሮዜንታል በሁናቴያቸው እየበሸቀች ስትሔድ ጥያቄ ማነብነቡን ትታ ወደ አሽሙርና ሽሙጥ ገባች ስለ ሐበሻ ሕዝብ ክፋት፤ ስለ ቴዎድሮስ ጭካኔ ስለ ጦር አበጋዞቹ ትዕቢት ስለ ጋፋት ፈረንጆች ክዳት የሰማችውን የተሰማትን ሐሜትና አሉባልታ ታወርድ ጀመር። በስሜት ግፊት የምትናገረው እያሰበች አልነበረም። ታንጉትና ወንጌል ቋቅ እስኪላቸው ድረስ ታግሠዋት ቆዩ።

ተሲዓት ሲቃረብ፣ «ወይዘሮ ሮዜንታል በይ እንግዲህ ቤት ሔደሽ ብትቆይ ይሻላል» አለቻት ወንጌለ።

«ለምን?» ስትል ሮዜንታል በቁጣ መልክ ጠየቀች።

«እነ አባ ታጠቅ ለምሳ መምጫቸው ደርሷል» በማለት ታንጉት ለጠቅ አደረገች።

«ቢመጡስ?»

«ተዚህ መቆየት አይፈቀድልሽማ!» አለቻት ወንጌለ።

«እናንተ ትቆዩ የለም?» ሮዜንታል በማሽጓጠጥ ከንፈርዋን አጣመመች።

«እኛ ባለሟል ሠራተኞች ነን። አንቺ ለሕክምና ተፈቅዶልሽ ብትመጭም እስረኛ መሆንሽን አትርሺ» አለች ወንጌል፣ ፍርጥም ባለ አነጋገር።

ሮዜንታል፣ ከአጠገባቸው ለመገኘት የነበራት ፍላጐት በመታገዱ ብቻ ሳይታወቃት ንዴትዋ ወደ ቴዎድሮስ ተሸጋገረ። «እህ እስረኛ! ኧረ አንድ ደንቆሮ ጥቁር እንዴት ቢደፍር ነው፤ ነጭ አውሮፓውያንን ያሚያስረው! ነገ ዋጋውን ያገኝ የለ!» አለች።

«ጥቁርም ቢሆን ሰው ነው። ከአጠፋችሁ በሥልጣኑ ሊያስራችሁ የማይችልበት ምህኛት የለም። በዕውቀት በኩልም ተሆነ ተማገኛችሁም ቢበልጥ እንጂ አያንስም» ስትል ወንጌለን መለሰችላት።

«ነጭና ጥቁር እኩል ሰዎች? ጥቁር ተነጭ እኩል ቢሆን ነው እንግሊዝ ፈረንሣይ ፖርቱጋል የአፍሪካንና የእስያን ሕዝቦች ረግጠው ቀጥቅጠው የሚገዙት በይኛ!» ሮዜንታል በየጉድባው ኢትዮጵያዊ ወንድ ያላንከባለላት ይመስል፣ የመኳንንቱን ገላ በሕልሟ ያልዳሰሰችውን ያህል፣ ማግኘት ያልቻለችውን አሁን በማጥላላት ፌዝ ከት ከት ብላ ሣቀች።

«ያቅም ጉዳይ ነው እንጂ ሁሉም ያዳም ዘር ነው» አለቻት ወንጌለ አሁንም ፍርጥም አድርጋ።

«ውይ ረስቸ አንቺም ለካ አለሽበት። ዛዲያ ምን ታረጊ? ራስሽን አታጣጥይው መቸስ። ክፍቱ ተዚህም ተዚያም አለመሆንሽ ነው።»

«እኔ ባባቴም በናቴም አላፍርም።»

«ብታፍሪበትስ ምን ታረጊው ኖርዋል። መርጠሽ ፈልገሽ አልተረገዝሽ። ለመሆኑ ወፍጮ ላይ ነው?»

«ታንጉት የራስዋ እናት ዲቃለነት ትውስ ስሜቷን ነዝሮት ይሆናል። ወይም ደግሞ ሮዜንታል ከአጓጉል ጥያቄ ጀምሮ ያለማቋረጥ ስትወርደእው የቆየችው የስድብና የሽሙጥ መዓት፣ የትዕግሥት ጽዋዋን ሞልቶባት ይሆናል። የሁለቱን ምልልስ ስትከታተል እንደ ቆየች ሮዜንታልን አላስጨረሰቻትም። በጥፊ ሳታጐናት ሮዜንታል የኋሊት ተፈናጥራ ከግድግዳው ጋር ተላተመች። ከዚያም እሳት ድንገት እንደ ገረፋት ያህል፣ ፊቷን በሁለት እጅዋ በመሸፈት ለጥቂት ጊዜ እንደ በድን ደርቃ ቆየች። ታንጉትም ወንጌለም ካሉበት አልተንቀሳቀሱም።

«ለርሷ አግዘሽ ነው?» ስትል ሮዜንታል ጠየቀች፤ ፊቷን አሁንም እያሻሸች እንደ ጣዕር በሚመስል ድምፅ።

«ይኸ ምላሽን ገና ተሌላ ያደርስሻል!» አለች ታንጉት።

«ዋ! እኔ እሻልሽ ነበር! በማለት ሮዜንታል ዛተች።

«ምን?» ታንጉት ዐይንዋን እያጉረጠረጠች ተጠጋቻት።

«ልንገርሽ?» አለች ሮዜንታል ወንጌለ እንድትሰማው የማትፈልገውን ይመስል በሹክሹክታ፣ «አየሽ ሚስተር እስተርን ባይናገርምኮ የደብረ ብርሃን ሥላሴውን መቃብር ቤት ጉድ እኔም ዐውቄዋለውሁ። ዝም ብዬ ነው እንጂ!!»

ታንጉት ነፍስዋን አላወቀችም። ለቅጽበት ተወርውራ ሥጋ ስትከትፍበት የነበረውን ካራ መዝዛ ሔደችባት። የቴዎድሮስ ቁጣ የሚወርድባት ከሆነ፣ ሌላው ጉዷ ሳይወጣ በነፍሰ ገዳይነት ብትቀጣ ይሻላታል። እስተርን የማይናገር ከሆነ ለወንጌለ አብራ ገደለቻት ነው የሚባለው።

ሮዜንታል ወደ አንድ በኩል በመፈናጠር የመጀመሪያውን አምልጣ፣ ታንጉት ለሁለተኛ ጊዜ እጅዋን ዘርግታ ስትሰነዝርና ወንጌለ ለመገላገል መኻል ስትገባ አንድ ሆነ።

የወንጌለ ጩኸት በግቢው ሲያስተጋባ፣ መጀመሪያ ከደረሱት መካከል አንዱ ዶክተር ብላንክ ነበር። በአስቸኳይ የሕክምና ሥራውን ጀመረ።

ቴዎድሮስ ከብረት ማቅለጫው ምድጃ አጠገብ ወዲያ ወዲህ እያሉ ሥራውን በመከታተል ጧት ከደብረ ታቦር ይዘዋቸው የመጡትን ሚስተር ራሳምንና ቆንስል ካሜሮንንም በማሳየት ላይ እንዳሉ የአደጋው መልክት ደረሳቸው። ከግቢው ሲደርሱ ከዋልድሚየር ቤት በራፍ በርከት ያሉ ሰዎች ተከማችተው አገኙ። ከአንድ በኩል ሴቶቹ «የጋፋት ልጆች» ለፍልሚያ የተፋጠጡ ይመስል ተከማችተው ቆመዋል።

ቴዎድሮስ ውስጥ ገቡና ዶክተር ብላንክ ሕክምናውን እስኪጨርስ እየተንቆራጠጡ ጠበቁት። «ተክንድዋ ላይ መሆኑ በጀ። ደረቷን አልነካውም። በቶሎ የሚያድን ነው» አለ ዶክተር ብላንክ አስፈላጊውን ሕክምና በማድረግ ሻሹን አስሮ ሲጨርስ። ሁናቴያቸውን አይቶ ለማቃለል መሞከሩ ነበር። እንዲወጣ በእጃቸው አመለከቱት።

ቴዎድሮስ፣ ከአልጋው ጠርዝ ላይ ተቀመጡና፣ «ምንድን ነው የሆነው ወንጌለ?» ሲሉ ጠየቋት።

ሮዜንታል፣ - ከምግብ ቤቱ መጥታ በሆነ ባልሆነ ነገር ስትጨቀጭቃቸው ያንንም ያንንም ስታማ ማርፈድዋን ከዚያም እርሷን ከወፍጮ ላይ የተፈጠርሽ ነሽ ብላ ስትሰድባት ታንጉት በጥፊ የመታቻት መሆኑን ከተረከችላቸው በኋላ፣

«ሮዜንታል ምን እንዳለቻት አላውቅም። ታንጉት በካራው ልትወጋት ስትል ልገላግል ገባሁና ግን ታንጉት ዐውቃ አይደለም» ስትል ጨረሰች።

ቴዎድሮስ፤ ከጐጆው እንደ ወቱ እሳት የጐረሰ እሳት የለበሰ ዐይናቸው በቆንስል ካሜሮን በሚስተር ራሳም ላይ አፈጠጠ። ቀጥሎ ወደ ታንጉትና ወደ ሮዜንታል ተወረወረ።

ታንጉት፣ እጆቿን ከደረትዋ ላይ አጣፍታ ከወደ ዳር በመቆም፣ ሮዜንታል ምሥጢርዋን አውጥታ ቅጣቱ እስኪወርድባት ተስፋ ቆርጣ ትጠብቃለች።

ሮዜንታል ፈንጠር ብላ ከድንጋይ ላይ ደርቃ ተቀምጣለች። እንደ ሰውነቷ አስተሳሰቧም በድንጋጤ ደርቆባት ነበር። ካራው ከፊቷ ላይ ብልጭ ሲል የታያት የሞት ትርዒት አሁንም ሁለመናዋን እንዳፈዘዘው እንደ ቀሰፈው ነው። ከሞት ፍርሃት ጋር ስትጋፈጥ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር። አሁንም አሁንም እንደ ማንቀጥቀጥ ይላታል። በምላስዋ የምትመኘውን ለማግኘት ስትሞክር፣ ከናካቴው ሕይወትዋን ልታጣ እንደ ነበር ድንጋጤዋና ፍርሃትዋ ብልጭ አድርጎ አሳያት። ምኞት ሊደርስ የሚችለው ደግሞ በሕይወት ሲኖሩ ነው። አሁንም የቴዎድሮስን ቁጣ የሚነድ ፊት ስትመለከት፣ የምታውቀውን ብትናገር በቁጣ የሚነድ ፊት ስትመለከት፣ የምታውቀውን ብትናገር ምን እንደሚያስከትልባት መገመት ስላልቻለች ፈራች። ተሸማቀቀች።

በሰፈነው ውጥረት መካከል ሚስተር ራሳም ከተለመደ የአክብሮት አገላለጹ ጋር፣ «መቸም አባ ታጠቅ እንደሚያውቁት የዕለት ግጭት በወዳጆችም መካከል ቢሆን» እያለ ለማብረድ ቃጣ።

«በቃ!» አሉት ቴዎድሮስ እንደ ነጐድጓድ በሚያስተጋባ ድምፅ። አነጋገራቸው ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ደብረ ታቦር ለቀሩት እስረኞች፣ ጥረታቸውን ላልተረዱት የባሕር ማዶ ሰዎች ሁሉ ጭምር ነበር። «በቃችሁኝ እንጂ! ወዳጅነቴን ብትንቁት ቻልኩ። አሁን ደሞ የቀረኝን አንድ ሥራ ልታበላሹብኝ ተነሣችሁ?»

ዶክተር ብላንክ እንዳለው የወንጌለ ጉዳት ቀላል ቢሆንም በጋፋት ልጆችና በእስረኞች መካከል የቆየውን መቃቃር፣ የበለጠ አክርሮት ከሚበጠስበት ደረጃ መድረሱ በግልጽ ያስታውቅ ነበር።

«ደበ ታቦር ያሉትን ጨምራችሁ ቸንክሩና መቅደላ ውሰዱልኝ፣ አሁኑኑ» ሲሉ አዘዙ። ወዲያው ረገብ ባለ አንደበት «አትቀየመኝ አቶ ራሳም። ተኔ ጥፋት የለም፣ የተቻለኝን ያህል ችያለሁ» አሉት።

ራሳም ለመግታት ቢጎሸመውም፣ ቆንስል ካሜሮን ለመናገር ሰውነቱን ወደ ፊት አስቀደመ። «የማይቋቋሙትን ኃይል መጋፋት ብልህነት አይመስለኝም።»

«ግዴለህም የደንቆሮ ጅልነት ነው። ግን ደሞ ዛቻና ጉራ የዕብሪተኛ ብቻ ነው። አይመስልህም።» አሁን - አሁን የካሜሮን ትዕቢት ከሚያስቆጣቸው ይልቅ፣ ሳይታረም እንዳደገ ጎረምሳ ብልግና የሚያስገርማቸው እየሆነ ሔድዋል።

«ባዶ ዛቻ አይደለም። የታላቅዋ ብሪታንያ ኃይል ከእጥፍና አጥናፍ ተዘርግቶ የሚገኝ ግልጽ ሐቅ ነው። ይህንን መካድ አይቻልም።»

«ዛዲያ ይሁና! ማን ይፈራል ብለህ ነው? እኔ መይሳው? አልሰማህም፤ ትንሹ ዳዊት ጎልያድን በወንጭፍ? ምናለበት ታንተ የበለጠ ታሪክ ባላውቅም ትልቅ ነኝ ብሎ የተመካ ሁላ፣ ትልቅ ሆኖ እንደማይቀር ባለም ላይ የደረሰ ብዙ አለ። እናንተሳ ሮማውያን ገዝተዋችሁ አልነበረም? እነሱ ደከሙ፣ አሁን ደሞ ቱርክ ሊጫወቱባት ደርሷል። እና ትልቅ ነኝ ብሎ መንደንፋቱ ዋጋ የለውም፣ ወዳጄ!» ቴዎድሮስ ባለ ጉዳዩን በማሰናበት እንደ መራመድ ሲሉ አሁንም ቆንስል ካሜሮን ቀበል አደረገ።

«ግንኮ መታየት ያለባት ያለፈ ታሪክ ሳይሆን የዛሬው የኃይል ሁኔታ ነው። ይህ ነው ሐቁ!» አለ ግትር ብሎ።

« ‹የዛሬ የኃይል› በምትለው አላምን ብየሃለሁ። እኩልነት ያገሬ ነጻነትና ዕድገት ይህንን ነው እኔ የማምነው። ውሰዱልኝ እባካችሁ! ነገር ታክቶኛል።» ቴዎድሮስ ጠቋሚ ጣታቸውን ወደ ታንጉት በማመልከት «ካራ መማዘዝ ተጀመርሽ በርትተሻልና እንግዲህ አንቺም መቅደላሽን ውጭ» ካሉ በኋላ፣ ወደ ብረት ማቅለጫው ለመመለስ በሮዜንታል አጠገብ ሲያልፉ ጸጥ ባለው አካባቢ አንድ ድምፅ ሳሙና ዘወር አሉ። ሮዜንታል ምራቋን ጢቅ ያለችበትን አፍዋን እንዳሞጠሞጠች ዐይናቸው ያዛት። በመጠየፍ ፊታቸውን መፍግገው፣ «ባለጌ! ይሽ ኑሮዋል ሥልጣያኔያችሁ!» ብለው ሌላ ቃል ሳይጨምሩ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

በንዴት መልክ ወንድ በጥፊ ተማትተው ከንዳቸው ጨበጥ ሲያደርጉዋቸው ከደረት ላይ ወከክ እንደሚሉት የሀገርዋ ሴቶች ልማድ፣ ሮዜንታል ጨርሶ በታወከና በተበጠበጠ ስሜቷ፣ ለመጨረሻ ጊዜ አስተያዩታቸውን ለመሳብ ሳይታወቃት ያደረገችው ነበር። ስሕተትዋ እንደ ገባት፣ «ቴ - ቴዎድ» እንደ መጣራት ቃጣት። ያስጨረሳት አልነበረም። ወታደሮቹ ለጉዞ ወዲያው ሲያጣድፉዋቸው ዕንባ ዐይንዋን ሽፍን አደረገው።

ጓዙ ሁሉ ተጭኖ ታንጉት ከከብት ላይ ከመውጣታትዋ በፊት ገብርዬን ለመሰናበት ጉንጭዋን ሲስማት፣ ከአንገቱ ላይ ተጠምጥማ ተንሰቀሰቀች። ስንት ዘመቻ ሲሔድ፣ ስንት ጊዜ ሲለያዩ እንደዚህ ስትሆን አይቷት አያውቅም።

«ምነው ሆድ ባሰሽ? እኛም በቅርብ መምጣታችን አይቀር። የሚያስፈልግሽ ነገር ሲኖር ሰው ላኪ» አላት።

«እኔ ፈራሁ ገብርዬ» አለች ከአንገቱ ላይ እንደ ተጠመጠመች።

«ምን አስፈራሽ?»

«እኔ እንጃ!»

»ፈረንጆቹ አንድ ነገር እንዳያደርጉሽ ብለሽ ነው? በሮዜንታል ምህኛት? ግዴለሽም አይዞሽ። እነሱ የሚታሰሩት ለብቻቸው። እናንተ የምትኖሩት ሌላ ሥፍራ። ምን አገናኝቷችሁ። ደሞ ስንት የኛ ሠራዊት እያለ?» ሲል የፍርሃቷን ምንጭ ያወቀ በመሰለው መንገድ አበረታታት።

ታንጉት፣ እንደ ማንም ከአንገቱ ተላቅቃ እንባዋን እየጠራረገች ጭንቀቷን በቀልድ ለማመቅ፣ «እናንተ ግን ዋ» ስትል አስጠነቀቀች።

«ለምኑ?»

«ሚስቶቻችሁን ሁላ ልካችሁ የምትሠሩት ምን ይታወቃል?» አለች የሚተናነቃት ለቅሶ ከቀልድ ሣቅ ጋር ቀላቅላ።

«ሴት እንደሽከላ ጠፍጠፈን እንዳንሠራ ነው? ወይስ እንደ መና ከሰማይ ይወርድልናል ብለሽ?» ሲል መለሰላት።

ወደ መቅደላ ከሚወስደው ዋና መንገድ እስኪገቡ ድረስ ገብርዬ ቁሞ በዐይኑ ተከተላቸው። ካለወትሮው የተሰማት ጭንቀት፣ ሥጋት አሳድሮበትም ይሁን እንጃ እርሱንም ቀፍፎት ነበር።

ወራጅ ወንዝ፣ በመስከ፣ በሸለቆ በቁልቁለት፣ በገደል የተለያየ ሒደት እንዳለው ሁሉ ሕይወት በመቅደላ በተለያየ መልክ ይንቀሳቀሳል። ጊዜ ለንዳንዱን አንሳፍፎ ሌላውን አስጨንቆ ይፈስላል።

በመቅደላ አምባ ላይ ብዙ ዐይነት ነዋሪዎች አሉ። ሠፈራቸውም እንደ ዐይነታቸው የተለያየ ነው። ከአምባው አናት መኻል ላይ የቴዎድሮስ ዋናው ማረፊያ ቤት ዕቃ ቤት፣ የእህል ጐተራዎች አሉበት። በእነዚህ ዙሪያ ጠባቂዎች

የሚኖሩባቸው ጎጆዎች ተንጠባጥበዋል። ትንሽ ፈቀቅ ብሎ ከዳፋታው ጉብታ ላይ የአምባው አዛዥ ግቢና የሠራተኞች መኖሪያ መንደር ይገኛል። ከዚህ መንደር በስተምሥራቅ ከአምባው ልሙጥ ገደል በኩል፣ በአሻገር ከተንታ አሮሞች ጎጥ ትይዩ የእስረኞች ሰፈር ነው። በውስጥ በርከት ያሉ ቤቶች የሚገኙበት እያንዳንዱ ግቢ በጨፈቃና በእሾህ ጥቅጥቅ ብሎ የታጠረ ሲሆን፣ ከየአጥሩ ውጭ የተረኛው ዘብ ጎጆ አለ። በስተደቡብ የሰላምጌ መስክ፤ ወደ በሽሎና ወደ ጀንዳ ሸለቆ መረማመጃ መደብ መስሎ ተዘርግቷል። ቀደም ሲል በዚያው ከነበሩት ባላገሮች በስተቀር የእስረኞች ቤተ ሰቦችና አሽከሮች በኋላም ከደብረ ታቦር እንዲመጡ የተደረጉ ወታደሮች እያረሱ፣ ከብት እያረቡ ወይም ቀለብ እየሰፈሩላቸው የሚኖሩት በሰላምጌ ስለሆነ፣ ችምችም ያሉ መንደሮችና የተበታተኑ ጎጆዎች በብዛት ይገኙበታል።

ጠቅላላው የመቅደላ አምባ ክልል መውጫና መግቢያ ኬላዎች በታመኑ ወታደሮች ሌት ተቀን ይጠበቃል። የቀረው ለዝንጀሮ ስንኳ የሚያዳግት ገደልማ ስለሆነ ጠባቂ አያስፈልገውም ነበር።

በዚህ ክልል ውስጥ እያንዳንዱ ነዋሪ፣ እንደ ሕይወት ዕጣ ፈንታው የየዕለት ውሎውን ይገፋል።

ለእስረኛው፣ ጧት መዝጊያ ሲከፈትለት ወጥቶ መናፈስ አቅራቢ ካለው ስንቁን ተቀብለው ከሌለው በባዶ ሆዱ ምናልባት ድንገት ስለሚውርድለት ምሕረት በተስፋ ወይም ስለሚመጣበት የመጨረሻ ቅጣት በጭንቀት እያለመ መዋል ነው።

ለነውረኛው ዘብ፣ ስንቅ የመካፈል የመማለጃ ጥቅም የመቀበል እንዲያም ሲል የእስረኛ ሚስት ወይም ሌላ ሴት የማማገጥ ዕድል ነው።

ለሐቀኛው ዘብ፣ የጥበቃ ተግባሩን በሚገባ ሲፈጽም ከመዋሉ ሌላ፣ ሆደባሻው፣ ተስፋ ከመቁረጡ የተነሣ ነካ ያደረገውንና ሌላውንም እስረኛ ሁሉ እንደ ወዳጅ እንደ ንስሐ አባት የማጽናናት ጥረት ነው።

ለአምባው ነባር ገበሬ ከበሬው ጋር ማንጎራጎር ከሞፈር ጋር መታገል ላቡን ከጥቁር ዐፈር ጋር እያዋሐደ ቸር ቀን እንዲያመጣ ከመመኘቱ ጋር ማምሻውን ቤቱ ሲመለስ፣ በባለጌ ወታደር ሚስቱ ተደፍራም ጎተራው ተሟጦ እንዳይጠብቀው ሥጋት ነው።

ከባለሟሎቻቸው ተለይተው ለመጡት እንደ ታንጉት ላሉት ሴቶች ደግሞ ከአንድ ቤት ሌላ ቤት፣ እየተገናኙ ማውጋት መገባበዝ ማማት፣ በየራስ ቤት

መፍተል መስፋት እንዲያውም ሲል ልብ ከፈቀደ ወታደር ወይም ሎሌ ጋር የተፈጥሮ ፍላጎትን በስርቆት መውጣት ነው።

እነዚህ ሁሉ የአምባው ነዋሪዎች የጋራ ሕይወት ደግሞ አላቸው። እስረኛው ይሁን ባላገር ወታደርም ይሁን የመኰንን ሚስት ከመልከተኛ በስተቀር የውጭው እንደማይገባ ሁሉ እንደ ፈለጉ ከክልሉ መውጣት አይችሉም። እስረኞችም በየግቢያቸው ብቅ አይሉም። ታማኞቹ ዘበኞች አይችሉም ከጥበቃ ኬላቸው እምብዛም ርቀው አይሔዱም። ለሌሎቹ ነዋሪዎችም ከአንዱ ጉብታ ላይ ከተተከለው ከሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ደብር ከአንዱ ቅዳሜ ቅዳሜ ከሚለው ገበያ በስተቀር የተለያዩትን ሠራተኞች የሚያገናኝ ማኅበራዊ መድረክ አልነበረም። በአንድ ዐይነት አጋጣሚ ዘልሎ ወይም ተጠልፎ፣ ከአንዱ ወደ ሌላው ከሚገባው በስተቀር የእያንዳንዱ ኑሮ የሚታቀበው በተከለከለለት ሰፈር ውስጥ ብቻ ነው።

ምኒልክ ከከዳ፣ ወርቂትና የጦር አለቆቿ አምባውን ለመያዝ የተደጋገመ ሙከራ ከአደረጉ፣ የቴዎድሮስን የአንዲት ኢትዮጵያና የአንድ መንግሥት ሥልጣን የሚቃወሙት እየበረቱና እያየሉ ከሔዱ ወዲህ ደግሞ በአምባው ውስጥ ለመዘዋወርም ሆነ ክልሉን ለማለፍ ጥበቃውና ቁጥጥሩ በጣም እየጠነከረ ሔዶ ነበር።

የእንቅስቃሴ ግድብ ባለበት በዚህ መካከል ግን ወሬዎች እንደ ነፋስ ይዛመታሉ። አምባውን ያደርሳሉ፤ ከአንዱ ጉጆ ውስጥ የሆነውን ከመቅጽበት መላው ሠፈር ይሰማዋል። የአንዱ ሠፈር ዜና፣ ከፈረሰኛ በሚያስንቅ ፍጥነት ከወዲያኛው ማዶ ሠፈር ደርሶ ይገኛል። ከአምባው ውስጥ የሚወጣው ብቻ ሳይሆን ከአምባው ክልል ውጭ የሚመጣውም እንደዚሁ ነው። ኬላ አያግደውም። የመንገድ ርቀት አያዘገየውም።

ቴዎድሮስ፣ ጋፋት ላይና በየአካባቢው የሚሠሩትና የሚሆኑት ሁሉ በየቀንኑ ይመጣል። ይደርሳል። የእንግሊዝ ጦር ሊመጣ ነው፣ ምኒልክ አንኮበር ገብቶ ኃይሉን ያጠናክራል በዝብዝብ ካሣ እየበረታ መጥቷል፤ ጣሰው ጎበዜ በወርቂት ላይ አይሏል፤ ዳሞት ጨርሶ ለይቶለታል፣ ወሬ ያለ ማቋረጥ ይጉርፋል። መብረቅ እንደሚያወርደው፣ ነጐድጓድ እንደሚያጕደጕደው የነፋስ ሠረገላ እንደሚሸከመው በአንድ ዐይነት ሥውር ኃይል የሚንቀሳቀስ ነው የሚመስለው።

ግን ይህ ሁሉ፣ ሥውር ኃይል አልነበረበትም። የውጭ አገር እስረኞች በተለይ የቆንስል ካሜሮንን የራሳም ሥራ ውጤት ነው። ከወገን ተለይተው ከአገራቸው ርቀው በባዕድ ሕዝብ መካከል በእስር ላይ የሚገኙት የውጭ አገር ሰዎች፣ መልእክት የሚያስተላልፉበት፣ ወሬ የሚያገኙበት አውታር አበጅተው ነበር። ‹ውሻ

በቀደደው ጅብ ይገባል፥ እንደሚባለው ፈጣን የወሬ ቅብብሎች ወደ ቀረው አምባው ነዋሪም ተጋባ።

የወሬ ዘመቻውን ፈጣንነት የሚጠቀምበት እንዳለ ሁሉ የሚጎዳበትም አለ። በአምባው ምክትል አዛዥ ለመሞት የበቃው በወሬ ጠንቅ ነበር።

በመቅደላና በአካባቢው አንድ ሽፍታውና እንደ ወንበዴው ሁሉ፣ በዘመኑ ጅብ በጣም በርክቶና አስቸግሮ ነበር። የጅብ መንጋ በመስከ፣ እረኛ እያቸነፈ በረት እየሰበረ ከብት ከመፍጀት ዐልፎ ቤት እየገባ በሰውም ላይ ጉዳት ማድረስ ስለ ጀመረ፣ ሁሉም ቤቱን በመቀርቀሪያ ክርችም አድርጎ እየዘጋ ነበር የሚያድረው።

ከወንድነቱ ይልቅ በትዕቢቱ፣ ከአስተዳደር ችሎታው ይልቅ በጨካኝነቱ ከመስጠቱ ይልቅ በመንጠቁ የሚታወቀው የአምባው ምክትል ሹም የቀኛዝማች ቢሠውር ቤት አንድ ቀን በሚገባ ሳይዘጋ ቀርቶ ይሁን አይታወቅም፣ ሌሊት ባልና ሚስቱ እንደተኙ፣ ሕይወት ያለው ሸክም ተጫነባቸው። ብሩክታዊትን ከአውሬ እንዳዳነው ጊዮርጊስ በወንድነቱ የተማመነችው ሚስቱ ቀስ አድርጋ ጎንተል አደረገች። አጅሬ ቢሠውር ግን፣ እንቅልፍ የወሰደው ይመስል ትንፋሹን ውጦ ዝም አለ። ደግማ ጎነተለችው። ስንኳን ፎክሮ ከአውሬ ሊተናነቅላት ቀርቶ እንደ በድን ደርቆ ቀረ። ለሦስተኛ ጊዜ በጉንተላ ልትቀሰቅሰው ስትሞክር መልሶ ልምዝግ አደረጋትና ከሽረሪት ሐር በቀጠነ ድምፅ «ዝም ብለሽ ተኚ» አላት።

ባልና ሚስቱ በሌሊት ልብሳቸው እንደ ተሸፈኑ ከሥር አድፍጠው ሕይወት ያለው ግዙፍ ሸክም ላይ እየተገላበጠባቸው፣ መዳፍ በሚመስል ነገር እየደባበሳቸው በዐይናቸው እንቅልፍ ዝር ሳይል ጎህ ቀደደ። የንጋት ብርሃን በግድግዳው በበሩና መስኮቶቹ መጋጠሚያ ስንጥቅ በኩል ሠርጾ ገብቶ ዐይን መለየት ሲያስችል እንደ ታቦት በፍርሃትና በጭንቀት ተሸክመውት ያደሩት ሕያው ነገር ዱብ ብሎ ከላያቸው ላይ ወረደ። አምቀው የቆዩትን ትንፋሻቸውን በመጠኑ አቃልለው ፊታቸውን በከፊል ቀስ አድርገው ገልጠው፣ ሲያስጨንቃቸው ያደረውን ጉድ ተመለከቱ። ለመውጣት ፈልጎ የሚያነፈንፈው ጅብ ሲጮህ ዘሎ ጓዳ ውስጥ በመሸጎጥ የታወቀው የመንደሩ አውደልዳይ ወደል ውሻ ነበር!!

የሚስትዮዋ ሣቅ እንደ ፊኛ ፈነዳ። «አንቺ ነሽ እንጂ፣ እኔ በፊቱንም እሱ መሆኑን ዐውቄዋለሁ። አሁንም ከፈቸለት ይውጣ» አለ ቀኛዝማች ቢሠውር ነገሩን ያቃለለ በመምሰል።

የቢሠውር ሚስት በኋላ እየማለችና እየተገዘተች እንደ ተናገረችው ከሆነ ጧት ግብር ሲወጡ እንደ ዋዛ ያጫወቻት ለአንዲት የቅርብ ጓደኛዋ ብቻ ነበር።

ግን በአንድ ቀን ውሎ በመቅደላ አምባ ሙሉ ተዳረሰ። ማምሻውን የአምባው ዋና ሹም «ቀኛዝማች ጅብ እንቅልፍ ነሥቷችሁ አደረ ሁሉ። ዛሬማ ከቤት ሊያስወጣን እኮ ነው!» ሲሉ ከፌዝ ሣቅ ጋር አነሡበት።

በጥቂት ቀናት ውስጥ ስለ ባልና ሚስቱ አዳር ብዙ ዐይነት ገላጭ ታሪክ ታከለበት።

ወትሮውንም በጠባዩ ምክንያት የሰው ፍቅር የተነፈገው ቀኛዝማች ቢሠውር በቤተ ክርስቲያን በገበያ፣ ማኅበር በዝክር የሰው ፊት ማየት የማይችል ከመሆኑ ደረሰ። ጥርስ ሳይገለጥ ይሣቅበታል። ንግግር ሳይደረግ ቃላት ሳይሰሙ ይፌዝበታል። ምናልባት ሁናቴውን ያጎላው የራሱ የቢሠውር የኃፍረት ስሜት ይሆናል። ከእርሱ ፊት ሰዎች የተያዩ ከንፈራቸውን ላመል ያህል ሸርመም ያደረጉ በሹክሹክታ የተጨዋወቱ ሌላው ቀርቶ የአክብሮት ሰላምታ ያቀረቡለት እንደሆነ የተሣለቁበት በአንዳች ዐይነት ሥውር ዘዴ ያሽሟጠጡት ይመስለዋል። ይህ ሁሉ ሳይንሰው ማንም ሰው እንደ ጦር የሚፈራው የእረኛ ዘፈን ወዲያው ተከተለ።

«አሆ ለሌ አሆ ለሌ

አህያ መጣች ተጭና እንስራ፣

አሆ ለሌ አሆ ለሌ

አህያ መጣች ጢሻ ለጢሻ፣

ወንዱ ቢሠውር አዘለ ውሻ።

አሆ ለሌ አሆ ለሌ

አህያ መጣ.....»

እረኞች እስከዚህም ተዳፍረው ከፊት ለፊቱ ላይ ባይዘፍኑበትም ምሉበት አካባቢ፣ እንዳጋጣሚ ሲደርስ ገና በሩቅ ይሰማዋል። እረኛ ማሳደዱን መደባደቡ የባሰ መሳለቂያ እንደሚያደርገው ስለሚያውቅ ያልሰማ መስሎ ያልፋል። በኃፍረት ጦር የባሰውን የሚወጉት ለርሱ የሚያስቡ የሚመስሉት ናቸው። የታማኝነት ውለታ ማግኘት የፈልገ ሎሌ ለብቻው ጠጋ ብሎ፤ «ኧረ ዛሬ ጌቶች?....» ሲል የሰማውን ያቀብለዋል። ከሚስቱ በላይ በድብቅ የሚጐበኛት ገረድ፣ «ኧረ ምንድን ነው ነገሩ?» ስትል ከማድቤት ከጎረቤት ውሃ ስትቀዳ የሰማችውን ትነግረዋለች።

ቀኛዝማች ቢሠውር፣ በመቅደላ አምባ ክልል ነዋሪዎች በግልጽም ሆነ በሥውር የሚዘንብበት የፌዝ፣ የሐሜትና የሥላቅ ውርደት ከፉኛ ቢሰማውም የባሰ

ያስጨንቀው ወሬው ለቴዎድሮስ መድረሱ ነበር። ዋለም አደረ መድረሱ ደግሞ እንደማይቀር ይታወቀዋል። ፍርሃትና ፈሪን እንደ ዐይነ ምድር የሚጸየፉት ቴዎድሮስ ነገሩን በዋዛ አያፍሉትም። እስር ቤት ባይከቱት ስንኳ ወይ ያግዙታል። ታለዚያ አዋርደው ይሽሩታል። እስከ አሁንም የአምባው ምክት ሹም ሆኖ የቆየው በቴዎድሮስ ዐይን ግምት ውስጥ ገብቶ ሳይሆን የአምባው ዋና ሹም ራስ እንግዳ ስለሚደግፉትና በቴዎድሮስ ዘንዳም ተደማጭነት ስላላቸው ነበር።

ከውሻው ወሬ ወዲህ ግን፣ የእርሳቸውም አስተያየት የተለወጠበት ይመስላል። እንደ ሌሎቹ በገሃድ ባይሣለቁበትም ለማራቅ እንደ ፈለጉ ዐይነት በሁናቴያቸው ተቆጥበውበታል። ይህንን ሁሉ ሲያስብ የሚደርስበት አስከፊ ዕድል ይታየዋል። መዘባበቻ ከመሆን ዐልፎ የወደቀ ግንድ ምሣር ይበዛበታል ነውና ቁጭቱን ቂም በቀሉን የሚወጣበት ሁሉ አሰፍስፎ ይነሣበታል።

ይህ ከመሆኑ በፊት ነበር፤ ቀኛዝማች ቢሠውር ከቤቱ ወረድ ብሎ ከሚገኘ የዋርካ ዛፍ ላይ አንድ ቀን በጠፍር ተንጠልጥሎ የተገኘው።

አንድ ባላ ጉዳይ ከታንጉት ማረፊያ በኢት የመጣውም ቀኛዝማች ቢሠውር ሳይፈታ እንደ ዐርባውም ሳይለወጥለት ዐልፎ ስለ እርሱ መወራት እየቀረና እየተረሳ ከሔደ በኋላ ነበር።

ታንጉት ከታዛ ተቀምጣ ጥጥ ስትፈትል ከየት በኩል እንደ መታ ያላስተዋለችው አንድ ሰው ድንገት ከፊቷ አጠገብ ደርሶ ሰላምታ በማቅረብ እጅ ነሣ። የተለመደውን መልስ ሰጠችውና በመገረምና በመጠየቅ መልክ አስተዋለችው። የውጭ መንገደኛ በመቅደላ አምባ ውስጥ ስለማይተላለፍ ማረፊያ ወይም ማደሪያ የሚፈልግ አንግዳ ሊሆን አይችልም። አለባበሱና ሁናቴው ደግሞ ወታደር ቀመስ ይመስላል። እግረ መንገዱን እንዴት ሰነበታችሁ በማለት የሚጠጣ ውሃ ለመጠየቅ ሰው መምጣቱ አዲስ ነገር ባይሆንም ታንጉት ሰውየውን ከዚያ በፊት አይታው ስለሚታወቅ ጥቂት ግር አላትና በሆድዋ ራስዋን ጠየቀች።

«ደሞ ማን አባቱ ልኮብኝ ይሆን ፈጣሪዬ?»

ባል ወይም ውሽማ ዘመቻ ሲሔድ ካለበለዚያም ከአጠገብ ራቅ ሲል ራስ መጥቶ ወይም ሁነኛ ሰው ልኮ የፍቅር ርጥባን መለመን የተለመደ ነበር።

ገብርዬ ስለሚወደድ፣ ስለሚከበርና ስለሚፈራ እንደ ሌሎቹ ሴቶች ታንጉት ብዙ ባትደፈርም ዐልፎ ዐልፎ ሞካክረዋታል። ደጀጠኙና አላማኙ የበዛበት ግን ከመቅደላ አምባ ከመጣች በኋላ ነበር። እንደ ፈለጉ መውጣትና መግባት በመከልከሉ ምክንያት ከልብዋ ወይም ከወዳጅዋ የተለይች ሴት ድጋሚ የምታገኘው

ይመስል መቅደላ እንዲቆይ የተላከው ወንድ የሕይወቱ ፍጻሜ እንደ ተቃረበ ቆጥሮት ከጊዜ ጋር ለመሻማት የቆረጠ ይመስል ከተለመደው የኀብረተሰብ ሥነ ምግባር ውጭ የወሲብ ፍላጎት በረከተ። ባል ይኑራት አይኑራት ወንዱ አይቷት ደስ ያለችውን ሴት ዐይን ሳያሹ ሰው ልኮ መለመን የተዘወተረ ሆነ። ለመግደርደር ካልሆነ በቀር ከልብ ሳያንገራግሩ እሺ እያሉ ፈቃዱ መፈጸም እየተለመደ ሔደ። ነውር መባሉ ቀረ። በአንዳንድ አካባቢ እንዲያውም እያደር የአስረሽ ምችው መልክ ያዘ።

በዚህ ሁሉ መካከል ታንጉት የተላከባትንም ራሱ የመጣውንም እየገሠጸች እያስፈራራች ከመለሰች በኋላ እንዳትምል አንድ ጊዜ ብቻ ፈጽማዋለች። ለዚሁም ረዘም ላለ ጊዜ ከገብርዬ ብትለይም የተፈጥሮ ስሜቷ አሸንፏት ሳይኖ ልመናው በቅርብ ባልንጀራዋ በኩል መጥቶ እንደ ውጋት ነጋ ጠባ ፋታ ስለ ነሣት ነበር። ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ፤ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ቡና ሲጠጡ እንዲያው ሊገናኙ በቻሉ ቁጥር ሁሉ «ግዴለም ብዬ ቃል ገብቸለት አባይ ታደርጊያኝ ታንጉት? አሁን ማ ይሙት የቆረብሽ አትመስይም? አሁን ይኸ ሁሉ አንቺ ብቻ ጨዋ፣ ጥሩ ተብለሽ እኛን ልክስክሶች ወራዶች ለማለት ነው? ባሎቻችን ለእኛ ሲሉ ደብረ ታቦር ላይ እየጾሙ የሚጠብቁን መሰለሽ? ተይ ታንጉት። ኧረ እኅትሽን አታሳፍሪኝ? አታስቀይሚኝ! ደሞ ደስ የሚልሽ ሰው ነው። በኔ ይሁንብሽ» እያለች ብታስቸግራት ለመገላገል ያህል እሺ አለቻት።

ሰውዬው በተቀጠረ ቀን ሰዉም ከብቱም በየቤቱ ከተከተተ በኋላ ጨለማን ተገን አድርጎ መጣ። ባንጀራዋ እንደ ነገረቻትም ሰውየው መልኩም ቁመናውም ያማረ ነበር። ነገር ግን የአምባ ጊዮርጊሱ ድርጊት ጳጳት የደብረ ብርሃን ሥላሴ መቃብር ቤት ምሥጢር የመውጣቱ ሥጋት መንፈሷን አኮማትሮ እንደ ያዘው ስለ ነበር እንደ ዕዳ ተወጣችው እንጂ የፍቅር ጨዋታውን አልተደሰተችበትም። ሌላ ጊዜ ላትደግመው ወስናለች።

ሰውየውን እየተመለከተች ይኸ ትውሳ በሐሳብዋ ውልብ ሲል ንዴት ቆንጠጥ አደረጋት። ነገር ግን የመጣበትን ጉዳይ ሳታረጋግጥ እንግዳ ሰው በቁጣ መቀበል ነውር መሆን ተስማትና ገታ አደረገችው። በተዘዋሪ መንገድ እንደ ዋዛ መጠየቅ የጀመረችው ሰውየው በእንግድነቱ ዐረፍ እንዲል ተነግሮት ደንገጡርዋ በለጡ እንደ ታዘዘች እህል ውሃ አቅርባ ሁለት ሦስት ጊዜ ከጎረሰና ጠላውን አንድ ጊዜ ከተጎነጨ በኋላ ነበር።

«ተዚህ ነዋሪ ነህ?»

«አዎ! ይኸው ሁለት ዓመቴን ይዣለሁ። እስረኛ ጠባቂ ነኝ።»

«ታሁን ቀደም አይቸህ አላውቅም።»

«ተሠፈሬ ብዙ አልወጣ።»

«ዛዲያ ብዙም አልወጣ።»

«ተርስዎ ተልኬ።»

«ተኔ? ራሱ መምጣት አቅቶት የሚልክብኝ ሰው ደሞ ማነው?» አለች ታንጉት የተገረመች በመምሰል በሆድዋ ግን የጠረጠረችው ጉዳይ መሆኑን እያሰበች።

ሰውየው ከሚያላምጠው እህል ጋር ትንሽ አቅማማ። «አለቃ» ሲል መለሰ።

«አለቃ? አለቃ ምን ተስኖት?» ታንጉት የሥላሴ ደብር አለቃ ማለቱ መስሏት ነበር።

«የለም አለቃ አክሊሉ።»

«አክሊሉ? አክሊሉ?» ፊቷን ጨፍገግ አድርጋ ከራስዋ ጋር ተጠያየቀች። ደብተራ አክሊሉ መቅደላ አምባ የታሰረ መሆኑን ብታውቅም፣ ስለ ሰውየው መልእክት ያደረባት ግምት ሌላ ስለነበርና ‹አለቃ› የሚለው ማዕረግም ለጆሮዋ አዲስ ሰለሆነባት ለጊዜው ያልተያያዘላትም።

«ተፈረንጆቹ ጋር አብረው ተይዘው የታሰሩት» ሲል አረጋገጠላት።

«ደብተራ አክሊሉ? ካስበችው መልክት ጋር ስታጋጥመው የመገረምና የፌዝ ሣቅ መጣባት። ትክክለኛውን ምክንያት ባታውቅም ደብተራ አክሊሉ ከነገሩ ሁሉ ከጉርምስናው ጀምሮ በሴት እንደማይጠረጠር ጎንደር ሳለች ስምታ ነበር። «ወይ አይመነኩስ ወይ አያገባ እንዲሁ ባሕታዊ መሰል ነው» ነበር ወይዘሮ ደብሬ ያሏት። በጃጀ ስሜታቸው ድንግል ካልገሠሡኩ ብለው የተሞሸሩት ሽማግሌ በጫጉላ ቤት ስለሆኑት የሰማችው ድንገት ትዝ አላት። መቆየት ብዙ ጉድ ያሳያል ይባል የለ!

«አዎ እመቤቴ» ሲል መልክተኛው በድጋሚ አረጋገጠላት።

«እሺ ምን ብሎ?» አሁን ረጋ ማለት ጀመረች።

«እንዲረዱዋቸው ይፈልጋሉ።»

ባንድ በኩል የተጠየፈችው ጉዳይ ባለመሆኑ በሌላ በኩል ሣቅ ያመጣበት ፌዝ በመቀጨቱ ደስታውም ቅሬታም ተቀላቅሎ ተሰማት። በፌዝ አንቱታ «ምን እንድረዳቸው ነው? ስንቅ አጠራቸው?» ስትል ጠየቀች የወይኒው በደል ትዝታ የቀሰቀሰባትን ንዴት እንደ ምንም ቻል አድርጋ።

«ኧረ ሞልቷል።»

«እዛዲያስ?»

«ከ'ስር እንዲወጡ።»

«ምን?» ስትል እንደ መጮህ ቃጣት ጆሮዋ የሚሰማውን ማመን አቅቷት።

«ማለቴ እንዲያመልጡ።»

«በስማም ወልደ መንፈስ ቅዱስ! ጆሮ አይስማው ጉድ የለ።» ጅጆሮ ግንድዋን በሁለት መዳፍዋ ከደነች። «አንተ የታጠቅ ዘብ ሆነህ የታጠቅ እስረኛ እንዲያመልጥ ነው የምትለው?» ፊቷ ሁሉ ተለዋወጠ።

«ማለቴ እንዲወጡ» ሲል አነጋገሩን መልሶ አረመ።

ግን አላዳመጠችውም። መላ ሐሳብዋ ተመልሶ የሚያየውና የሚሰማው በእነ ደብተራ አክሊሉ ተንኮ ምክንያት ወይኒ በሰነበቱበት መንደር የተፈጸውን የግፍ ጭፍጨፋ ደባርቅ ላይ የደረሰውን ዕልቂት ነበር። ደባርቅ ላይ ሞታ መገኘቷን የሰማችው ያይኔ አበባ ሁለመናዋ መጣባት። «አሁን አገሬ ላሲዝህ?» አለች በጥያቄ ሳይሆን በቁርጠኝነት ዛቻ።

«ምን ይጠቅሞታል?» እርሷ ስትነድ ሰውየው የሚያደነዝዝ ዕፅ እንደ በላ ዐይነት የረጋ ውሃ መሰለ።

ሰውየው እንደ መደንገጥ ከንዴቷ መንጥቆ ወደ ሐሳብ አስገባት። ያ ከይሲ ያላንዳች ምክንያት ባጋጣሚ ብቻ እንደዚህ ያለ ድፍረት አልላከባትም። አንድ ነገር ቢጨብጥ ነው። ምን ነገር? የመከተኛውም ህልውና ለጊዜው ረስታ መልሱን ጠርጋ የምታወጣው ይመስል ግንባርዋን በጣትዋ ፈተገች። በዚህ ተማምኖ ይሆናል የምትለው አንዳችም ግምት አልመጣላት አለ። «ለመሆኑ እንዲህ ያለ ድፍረት ሐሳብ ይዘህ ስትመጣ ትንሽም አትፈራ?» ስትል በመገረም ዐይነት ጠየቀች።

«አይ እሱማ መቸስ ግና ጉዳዩ የሁላችሁም መሆኑን ንገር ስላሉኝ ነው እንጂ።
»

«የሁለታችን?»

«አዎ! እርሳቸው ከአምባው ቢወጡ ለርስዎም እንደሚበጅ ካለበለዚያ ግን......»

ታንጉት ሰውነቷን አንዳች ነገር ውርር አደረጋት። «ካለበለዚያስ? ጨርሰው እንጂ!»

«ዝርዝሩን አልነገሩኝም። ለሁሉም ዛሬ ማታ ራሳቸው የሚመጡ መሆናቸውን ንገር ብለው ነው የላኩኝ።»

«ምን?» ስትል አሁን እንደ መጮህ ቃጣት።

መልክተኛው የመጣበትን ጉዳይ የጨረሰ ይመስል ለመሔድ ተነሣ።

‹እስቲ ደጁን ርይገጣት! አንተም አስቀፍድጄ ነው የማሳድርህ» ስትል ዛተች። በሆድዋ ግን እንደማታደርገው ይሰማት ነበር። አንዳች ፍርሃት ተለቀቀባት።

መልክተኛው እንዳለው አክሊሉ የመጣው ምሽቱ ገፍቶ ሰዉም ከብቱም ለአዳሩ ከተከተተ በኋላ ነበር። ታንጉት ‹እስቲ አባቱ!› እያለች ደግማ ደጋግማ ራስዋን በራስዋ እያታለለች ብትቆይም፣ ደንገጡርዋን በለጡን አሰናብታ ብቻዋን ተቀመጠች።

ገርበብ ያለውን መዝጊያ ገፍቶ እንደ ጨለማው የጠቆረ በርኖስ ለብሶ አክሊሉ ሲገባ ሆን ብላ የጠበቀችው ይመስል ሳትደነግጥ እንደ ዋዛ ነበር የተመልከተችው። እርሱም እንደምትጠብቀው ያረጋገጠ ይመስል «እንደምን ሰነበታችሁ? ደኅና ከረምሽ ወይዘሮ ታንጉት?» የሚል ሰላምታ አቅርቦ ሳይጋበዝ ከአንዱ ቋንጣ ወንበር ላይ ተቀመጠ።

ሰላምታው መልስ ሳትሰጠው ረዘም ላለ ጊዜ ዝም ብለው ተፋጠጡ። «የመጣህበንት ተናገር እንጂ፣ የዐመጽ ሰይጣን!» አለች ታንጉት በመጨረሻ ቅርችም ባደረገችው ጥርሷ መካከል። በጥቁር በርኖስ ተጠቅልሎ በተለመደው ኩርምት ያለ አቀማመጡ የሚርገበገበው የጧፍ መብራት ሲያንጸባርቅበት በእርግጥም ሥጋ የለበሰ አንዳች ዐይነት ጥልማሞታም ጋኔን መሰላት።

«ለስድኮ አልመጣሁም» ሲል አክሊሉ መለሰ ከንፈሩ በበርኖሱ ክሳድ እንደ ሸፈነ።

«አትናገሩኝ ለማለትም በቃህ?» አለች በመዛት ዐይነት። «ያን ሁሉ ሠርተህ?»

«የኔ ጥፋት የተባለብኝ ከሌላው መች ይብስና።»

የአነጋገር ዳር ዳርታው ገባት፣ «ከማን?»

«ከአንቺው።»

«ምን?» መስማት ፈለገች። መስማቱንም ፈራችው።

«ይኸ ሁሉ ሕዝብ፣ ፈረንጁ ተዚህ ታስሮ የሚሠቃየው በማን ምህኛት ሆነና?»

«እኔ?» ስትል በማስተባበል ድርቅና ጠየቀች።

«ደብረ ብርሃን ሥላሴ መቃብር ቤት ይመስክር» አለ አክሊሉ በፌዝ ቃና።

«እህ! ፈረንጆች ነገሩን? ለምን ለአባ ታጠቅ አልነገሩትም ዛዲያ?» የታንጉት አነጋገር ጥያቄ ሳይሆን የጭንቀት ክርክር ቢጤ ነበር።

«ለዐይን ምስክር ምኑን ይነግሩኛል። የቴዎድሮስን ጉድ ስትዘከዝኪ ተዚያ ነበርኩ ከመቃብር ቤቱ። ለቴዎድሮስ አለመንገራቸውም የሆነ እንደሆነ እኔ ለምኛቸው ነው። ላንቺም ስል ለእኔም መንገድ አገኝበታለሁ ስል ነው። ተያይዞ መጥፋቱ ምን ፋይዳ አለው ብዬ!»

«ለተአምር ነው የእኛ አዛኝ ቅቤ አንጓች!» አለች ታንጉት እንደ እሳት በሚያቃጥል ብሽቀት።

«አልዋሽም፣ ላንቺ አዝኜ ሳይሆን ራስሽ ለራስሽ እንደምታዝኚ በማወቅ ነው።
»

«እንዴት?»

«ቴዎድሮስ ምስጢሩን ቢያውቅ እንዴት እንደሚሆን መቸም ታውቂያለሽ። ፈረንጆቹን ነጋ ጠባ ቁም ስቅል ያሳያቸው የነበረው ማን እንደ ነገራችሁ ንገሩኝ እያለ አይደል? በኔ ልመና ነው እምቢ ያሉት። ገብርዬም ቢሆን፣ አባ ጊዮርጊስ የሆነውን ቢሰማ ደስ ይለው መሰለሽ?» አለ አክሊሉ እንደ ዋዛ ቢያመስለውም አጠያየቁን ረገጥ አድርጎ።

«ምን ሆነ ደሞ?» ስትል ታንጉት ጠየቀች ምን ማለቱ እንደሆነ ግን ሆድዋ እያወቀ።

«እቴ ‹ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል› ተብሏል።»

አክሊሉ የማስጠንቀቂያ ውሉን ቋጥሮ፣ ታንጉትም የመፍቻው መልስ ጠፍቷት ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ። ዐልፎ ዐልፎ ከሚሰማው የአዕዋፍና የከብት ድምፅ በስተቀር ዙሪያውን እንደ ሸፈናቸው ጨላማ ጸጥታ ሰፍኗል። ታንጉት ግን ለገብርዬ ልጅ ለመውለድ ባደረባት ጉጉት ከስንት ዓመት በፊት የሆነው ነገር ወደ ፊት ከሚንበለበለው ከሚያቃጥለው የገብርዬና የቴዎድሮስ የቁጣ እሳት ጋር በሐሳብዋ ሲታያት፣ በአካልዋም በመንፈስዋም መላ ሰውነቷ ማዕበል እንደ መታው ጀልባ ተናጋ፤ ተናወጠ። «ዛዲያ ምናርጊ ነው የምትለኝ አሁን!» አለች ታንጉት ቆይታ - ቆይታ ጭንቀትና ሠቀቀን አንቆ ባስቀረው ደካማ ድምፅ።

«ብዙም አላስቸግርሽም እቴ ታንጉት። እንዲያውም አንቺን ራስሽን ላስቸግርሽ አልፈልግም። ቀላል ነገር የምጠይቅሽ። አገልጋይሽን ስጭኝ እንዳዛት፣ እንድገዛት። »

ጥያቄው ስላስገረማት አትኩራ ለመመልከት የፈለገች ይመስል ታንጉት ፊቷን ወደ ፊት ሰገግ አደረገች። «ምን ልታረጋት?» ስትል ጠየቀችው።

«አይዞሽ እቴ ታንጉት! የምነግራትን ታረገች ቀላል ነው። ቀና መንገድ። ይህንን አስጠንቂቅልኝ ብቻ። ታለበለዚያ ተመልሰን ሁለታችንም ጣጣ ውስጥ ነው የምንገባው። ተዚህ በተረፈ አልሸጣት አልለውጣት ሌላስ ምን እንዳላረጋት ብለሽ ነው?» ሲል ደብቆት የኖረውን ምሥጢሩን በሚያጋልጥ ፌዝ ፈገግ አለ። ታንጉት ሳትወድ ሣቅ መጣባት።

«ለመሆኑ፤ ለመሆኑ» አለች ታንጉት ባንድ በኩል አንድ ያልደረሰበት ምሥጢር በመኖሩ ራስዋን የምታታጽናናባት አንዳች ዐይነት አሸናፊነት እየተሰማት። በሌላው በኩል ያወቀውን ካወቀ ዕድላችን ተቆራኝቷልና ‹ያበጠው ይፈንዳ› በሚል ግዴለሽነት «የመቅደላውን እንዴት ሳትሰማው ቀረህ?»

«ተዚህም ጉድ ነበር? መስማት አላላስፈለገኝ አልሰማሁትም። ትልቁን ነገር ይዤ በትንሹ ምን አታከተኝ? ተዚህ የሚሠራው ተራ ነገር ነው። ደሞስ ምን ያስገርማል? እና በቅርጫ አባባላችን ‹ትልቁ መደብ የደረሰው፤ ሌላ ዕጣ አይጥልም። › ስለዚህም የምትዪውን አልተከታተልኩም፤ አልሰማሁ።» አክሊሉ በዚያ አስተያየቱ አጨንቁሮ ተመለከታት።

«አየ እንዲያው ነው እንጂ» አለች ታንጉት ያነሣችውን ጥያቄ በማቃለል።

አክሊሉ ጉዳያቸው እንዳለቀና ታንጉትም እንደ ተሳማምች በማስመሰል ለመሔድ ተነሣና፣ «እንግዲህ በጊዜ ወደ መቃብሬ ልመለ ተንኮለኛ ዘብ ፈትሾ እንዳያጣኝ። ሰበብ ነው የሚፈልገው። ልጅቷ ግን ከረፋዱ ላይ ጀምሮ ተሰናድታ ብትቆየኝ መልካም ነው። ጉዞዋችንን ነገ ፀሐይ ሳይጠልቅ ነው የምንጀምረው። ብዙ ጓዝ አያስፈልጋትም። አንድ አገልግል ቢጤ፣ ለቁስለኛ የሚሆን ምግብ የተገኘውን ዐይነት የሚያስቸግርሽ ተሆነ ተኔም እመጣዋለሁ። ተዚያ፣ ጋቢም ደግሞ ለርሷ የሚሆን ልብስም እንዲያው እንደ ሆነ ዐይነት» ሲል እንደ መሰናበት ዐይነት እጅ ነሣ።

«እስቲ ሌላ ነገርም ልጠይቅህ? እውነቱን የምትናገር ተሆነ?»ስትል ታንጉት የጀመረችውን ገፋችበት።

«የማውቀው ነገር ተሆነ።»

«ወይዘሮ ደብሬን ማን ነው የገደላቸው?» ታንጉት ስማቸውን ስትጠራ ሁናቴያቸውን ከዐይነ ሕሊናዋ ጽድቅ አለባትና እንደ መጋረድ ዐይነት መዳፏን ላይ ሸፈነች።

«ወሬውን ሰማሁ እንጂ እውነት የማውቀው ነገር የለኝም። እሳቸውን ምን ብዬ እጠናወታቸዋለሁ? ተሳቸው ነገር የለኝ። ነገሬ ተሌላ። ባንችም ላይ ቢሆንኮ ክፋት የለኝም። ነገሬ ተሌላ። እንዲያው መቋለፊያ ሆንሽ እንጂ።

«ዛዲያ ማን በክፉ ያስባቸዋል? እርሳቸው የሆነ እንደሆነ ለሰው ክፉ ማሰብ ቀርቶ የማስብበት ምህኛት አልነበረም።»

«ምሥጢርክን ስለሚያውቁብህ ነዋ!»

«ለኔስ የሚያውቁት ነገር አልነበረም። የተገናኙት ከአቡነ ሰላማ ጋር ነበር።»

«ያው ነው» አለች ታንጉት፣ ድርቅ ባለ አነጋገር።

«የምታምኝኝ ተሆነ ነገርኩሽ?»

«እምነት? እምነት አልከኝ ደብተራ አክሊሉ?» ለመሔድ መነሣቱን ስትመለከት «እህል ውሃ ሳትል» አለችው ታንጉት ልማድ ለመፈጸምም በፌዝም መልክ። ይህንን ስትናገር ድፍት የምታደርግ መርዝ ከምግብ ጋር አዘጋጅታ ብትጠብቅ ኖሮስ? አክሊሉ ከሞት የሚያስፈራራበት ምሥጢር አብሮ ይቀበር ነበር። ግን መቸም መሠሪ ነውና አስቀድሞ ካልተቀመሰለት ምግቡን አልጋበዝም ቢልስ? ደግሞስ እርሱ እንዳለው ፈረንጆቹ ማን እንደ ነገራቸው እሰከ አሁን ሳይገልሱ የቆዩን ስለ ለመናቸው ከሆነ ሲሞት ቢለፈልፉስ? ለሁሉም አክሊሉ እምቢ ማለት እንዳትችል አድርጎ ጉዳዩን አሣሥሮ ለመሔድ ከተነሣ በኋላ፤ መላ ማሰላሰሉ ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ ዐይነት መሆኑ ተሰማት።

«ግዴለም አትቸገሪ። እንደ ዱሮው በደኅና ጊዜ ትጋብዥኛለሽ። ለአሁን ግን፣ አገልጋይሽ የምነግራትን ሁሉ በትክክል እንድትፈጽም በሚገባ አስረጅልኝ። የሚበጀው ለሁለታችንም ነው።» አለና አክሊሉ በበርኖስ የተሸፋፈነ ሰውነቱን እያጥመለመለ ተሰናብቶ ወጣ።

አክሊሉ ላቀረበው ጥያቄ የተረጋገጠ መልስ ባያገኝም፣ ታንጉት የእሺታ ወይም የእምቢታ መልስ ባትሰጥም በሁለቱም ዘንድ ጉዳዩ እንዳለቀለት የተሰማቸው ይመስል በዝምታ ተለያዩ።

በበነጋው፣ ጀንበር በምዕራብ ማዘንበል እንደ ጀመረች አንዲት ልጅ እግር ሴት ፍትግ ስንዴ የያዘ ዕንቅብ በራስዋ ተሸክማ፣ ባንድ ትከሻዋ እንጀራ በሥጋ ወጥ ያለበት አገልግል አንግታ፣ በጀርባዋ ልብሳ ልብስ የተከተተበት ከረጢት አዝላ፣ በወረይሉ በኩል ወደ አለው የመቅደላ መውጫ በር መጣች።

«ተመለሽ የት ነው የምትሔጅው?» ሲል ዘቡ ደነፋ።

«ተባሌ ዘንድ ነዋ!» አለች ልጅ እግርዋ ሴት የደከማት መሆንዋን ለመግለጽ ዕንቅቡን ከራስዋ እያወረደች።

«የምን ባል?» ሲል ዘቡ ጠየቃት። መልካም ድግስ፣ እንደ ቀረበለተ እንግዳ ቁመናዋንና ልጅ እግርነቷን በፈገግታ እየተመለከተ።

«የምን ባል? የሕግ ባሌ ነዋ!»

«ዛዲያ እኔ ስለ ባልሽ ምን አስቸገረኝ እቱ? ወንድ እንደሆነ ሞልቷል። ተኔ ጀምሮ» ደረቱን ነፋ አድርጎ አስመረቃት።

«ያሳልፉኝ ይልቅስ?» አለች በተኮሳተረ አነጋገር።

«የት?» ብዙ ሊያሾፍባት ከጀለ።

«የት?» እንደ ተነገረችው ፍጥጥ አድርጋ ተመለከተችው። «ተባሌ ዘንዳ ነዋ! ከመሐመድ በሽር ወንበዴዎች ጋር ሲዋጋ ለቆሰለው የቴዎድሮስ ወታደር ስንቅ አታደርስሽም የምትለኝ ተሆነ ምን ቸገረኝ። ለራስ እነግራለሁ» አለችውና የምትመለስ ለማስመሰል ጓዟን ሰበሰበች።

«እቱ እስቲ ታገሺ፣ አትቆጭ» አለ ዘቡ ግራ ተጋብቶ። ታች - ታቹን በወረይሎች መንደር ከመሐመድ በሽር ጭፍሮች ጋር ሰሞኑን በተደረገው ውጊያ ብዙ ወታደር መሞቱን ሰምቷል። ብዙ ቁስለኛም ወደ መቅደላ አምባ ገብቶዋል። በየመንደሩም በየጎጡም የቀረ ሊኖር እንደሚችል ያውቃል። ግን ስንቅ ለመቀበል ወደ ውጭ የሚወጣ ሲያጋጥመው ገና የመጀመሪያ ጊዜ ነው። ውሳኔው አስቸገረው።

«ዛዲያ አሳልፈኛ!» አለችው አሁንም በተኮሳተረ አነጋገር።

«እሺ! እሺ! እቱ» የያዘችውን ምግብ በአፍንጫው እያነፈነፈ በአድናቆት ከንፈሩን መጠጠ። «እስቲ በደኅና ያገናኛችሁ። ታልሆነም መቸም አስተዛዛኝ እሆንሻለሁ» አለና አሳይቶ ሸኛት።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የወታደር ልብስ የለበሰ ኮሳሳ ቢጤ ሰው እየተጣደፈ ወደ ዘቡ በር መጣና፤ «አንተ የቴዎድሮስ ዘብ ነህ?» ሲል በቁጣ ጠየቀ።

«ብሆን ነው እንጂ ዛዲያ ተዚህ የምጠብቅው።»

«አንዲት ልጅ እግር ሴት በዚህ አልወጣችም?»

«ልጅ እግር ሴት? ሴት?» ዘቡ በድንገት ቢታወሰውም ጸጉሩን እያከከ የሚያስብ መስለ።

«ባል ባልዋማ እኔ ነበርኩ» ሲል ሰውየው ከት ብሎ ሣቀበት።

«የቴዎድሮስን ወታደር ሚሽት፣ ማንም ሽፍታ እያስኮበለለ ሲወስዳት ዝም ብላችሁ ታያላችሁ ማለት ነው? ወይ ነዶ!» ራሱን ነቀነቀ። «መቸስ ምናረጋለሁ ላለቃየ መንገር እጂ!» ወደ መጣበት የሚመለስ ይመስል ዞር አለ።

«እኛ መቸስ ምን ዐውቅን ብለህ ወንድም። እሷው እንደ ነገረችን ነው ያሳለፍናት። አሁንምኮ ፈጠን ብለህ ተሔድክ ትደርስበታለህ። ብዙ አትርቅም። አለና ዘቡ መንገዱን በእጁ አመለከተ።

«ለነገሩ ነው እንጂ የት አባትዋ ታመልጠኛለችና! እኔ አባ ድፋው ሱሪ አልታጠኩማ!» እያለ ሰውየው ቁልቁለቱን ተንደርድሮ ወረደ።

መተኪያ እስኪታጣ ድረስ እጥረት የደረሰ ያህል፣ ራሳቸው እንደ ተራ ሠራተኛ ድፍት ቀና የሚሉበት ጦር መሣሪያ ሥራ፣ በዓመት በዓልና በሰንበት ቀን የሚቆም ቢሆንም ቴዎድሮስ ግን ፈጽሞ ዐርፈው ውለው አያውቁም ነበር። ከጊዜና ከሥፍራ ጋር እሽቅድድም የገጠሙ ይመስል ያለማቋረጥ ይንቀሳቀሳሉ።

እየባሰበት የሔደው የሽፍታውም ነገር ፋታ የሚሰጥ አልነበረም። ከጋፋትና ከደብረ ታቦር ከግማሽ ቀን የማይርቅ መንገድ ድረስ እየመጣ ለመዝረፍ የደፈረ ሽፍታ ሞልቷል። አንዳንድ የአካባቢው መንደሮችም የቴዎድሮስን ወታደር ብቻውን ካገኙ እየገደሉ እስከ መደበቅ ደርሰዋል። ብዙ መንደር፣ ‹ወታደርዎ ዘረፈን በደለን› ሲል አቤቱታ ለማቅረብ ይመጣል። በዚህ ሁሉ መካከል ቴዎድሮስ በቀላሉ መንቀሳቀስ የሚችል መጠነኛ ሠራዊት አስከትለው ከጋፋት አራቱንም ማዕዘን መኀብኘት መፈተሽ የማያቋርጥ ተግባራቸው ሆነ።

በዚሁ ሁሉ ጉዞዋቸው ወትሮ ከተለመደውና ባለሟላቸው ከሚይዝላቸው ነፍጥ፣ ራሳቸውን ከሚታጠቁት ጎራዴና ሽጉት ጋራ ከእንግባቸው የማይለይ አዲስ መሳሪያ ነበራቸው። ይኸውም ራሳም ያመጣላቸው የሩቁን አቅርቦ የሚያሳይ

መነጽር ነው። ስጦታውን መጀመሪያ ሲያበረክትላቸው «ምነው የመይሳው ልጅ! ዐይነ በሽተኛ ነው አሏችሁ?» ያላጥላሉትን ያህል ከዚያ ጠቀሜታው ተነግሮዋቸው ከዐይናቸው ላይ ተክለው ወደ ማዶ ከተመለከቱ በኋላ «ምን ትቀልዱብኛላችሁ! ባይኔ የማየውን ተራራ ወደ ማዶ ጭጋግ ሲያለብሰው» ብለው ሊወረውሩት ያልቃጡትን ያህል ለተወሰነ ዒላማ ተስተካክሎ ካዩበት ራሳቸውም ማስተካከሉን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ የትም ሲሔዱ ከእጃቸው የማይለዩት ብርቅ ዕቃቸው አድርገውታል።

ለራሱ በግልጽ አልነገሩትም እንጂ፤ ከሌሎቹ የውጭ አገር እስረኞች የተለየ አስተያየት ለራሳም የሚያደርጉለት አንዱ ምክንያት ይህ መነጽር ነበር። እልፍኝ ተወዝፎ እንደሚውል የዐረብ ሺህ በመቁጠር፣ አበባ ምንጣፍ ካመጣላቸው ከቆንስል ካሜሮን የተሻለ አመለካከት ያለው ሆኖ አግኝተውታል።

በየደረሱበት ዙሪያውን የሚዳኝ ከፍታ ቦታ ይመርጡና መነጽራቸውን ይደግናሉ። የመነጽሩ ዲካ እስከ ደረሰላቸው አካባቢውን ሁሉ ይቃኙታል። መስኩን ዳገቱን ጉብታውን ሸንተረሩን ሸለቆውን ሁሉ ያማትራሉ። አትኩረው ያስተውላሉ። ከመነጽሩም ይሁን ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሣ፣ የሥጋት ስሜት አድሮባቸው የየዛፉ ቅርጽ የሣሩ ቀለም የኮረብታው አቀማመጥ የወንዙ ጠመዝማዛና ወልገድጋዳ መንገድ፣ ያገጠጠው ጥቁር ቋጥኝ ሳይቀር ሁሉ ነገር ወትሮ ያልነበረ አዲስና ብርቅ ሆኖ ይታያቸዋል።

መነጽሩ ከዐይናቸው እንደ ተከሉ በመገረምና በማድነቅ ፍዝዝ ብለው ይቆያሉ። «አንቺ ውብ አገር! ምናለ ልጆችሽ ብርቱና አንድ ብንሆን? ሌላውን ንቆ ዐይኑን ከሚጥልብሽ?» ይላሉ ከራሳቸው ጋር።

መነጽሩ ሌላም ሐሳብ ያመጣባቸዋል። «የሠለጠነው ሕዝብማ ይኸውና የሩቁን የሚያቀርብ መሣሪያ ፈጠረ። እኔ ግን፤ ቅርብ የነበረው ዓላማዬም እየራቀ ሔደብኝ! ምን ዐይነት እርግማን ነው?» መነጽሩን ወርውረው የሚያሰኝ ምሬት ይሰማቸዋል።

በዚህ ዐይነት አንድ ቀን ረፋዱ ላይ በሸሎ አፋፍ ደርሰው ከሸለቆው መዳፊያ ጠርዝ ላይ እንደ ቆሙ መነጽራቸውን ወደ ወንዙ መደብ ሲያነጣጥሩ በርከት ያሉ ሰዎች እንቅስቃሴ ተመለከቱ። ወንዙ ባሕር ቢጤ ሠርቶ የተንጣለለበት ስለሆነ ከመሠረቱ በዚህ መሻገሪያ ላይ ሰውም ከብትም ማየት አዲስ ነገር ባልሆነ ነበር። በሁለት ምክንያት ለቴዎድሮስ አዲስ ነገር መሰላቸው። የነጋዴው የሽፍታው የእረኛ መተላለፊያ ቢሆንም በተለይ ለነጋዴና ለእረኛ የመናኸሪያ ጊዜ አይደለም። በጠዋት ተነሥቶ ሲሔድ የዋለ ከቀትር በኋላ ዐረፍ ይልበታል። ወይም ደግሞ ራቅ ካለ

ሥፍራ የመጣ ለማደሪያ ማምሻውን ያርፍበታል። የተመለከቱት ከሁለቱም አልሆኑም።

እርግጠኛ አይሁኑ እንጂ፣ የተገነዘቡት ሌላ ነገር ብዙዎቹ ሰዎች ለመጠጣት ይሁን ለመለቃለቅ ወደ ወንዙ የሚገቡት በመነጣጠል ለየብቻቸው ሳይሆን፣ እንደ ታሰረ ጨረቃ ሁለት ሦስት በአንድነት መሆናቸውን ነበር። ብዙ ነገር ያዩትና የደረሰባቸው ቴዎድሮስ ወዲያው ጥርጣሬ አደረባቸው።

«ታች ተወንዙ ውረዱና ተዚያ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ይዛችሁ አምጡልኝ። ቢሸሹም ቢርቁም ተከትላችሁ» ሲሉ ያስከተሉትን ሠራዊት አለቃ አዘዙ።

«ምንድን ናቸው አባ ታጠቅ?» ሲል ጠይቀ በድንገት ሽፍታ ቢሆኑ ታች ወርዶ መዋጋት እየቀፈፈው።

«ምንስ ቢሆኑ፡ ሒድ አልኩህ! ተዚህ ታፍንጫዬ ሥር» አሉ ቴዎድሮስ የመነጽራቸውን ጭፍ እየጠቆሙ። «ጠላቴ ተሆነ ቢያመልጥህ ሙት የኔ ባለሟል አይደለህም። ወይስ ራሴው ልውረድ?» ሲሉ ዛቱ።

«ኧረ ግዴለም አባ ታጠቅ» አለና ሠራዊቱን ለማሰባሰብ ሔደ።

ቴዎድሮስ ጆሮዋቸውን አንቅተው ቢያዳምጡም አንዳች የጥይት ድምፅና የውጊያ ግርግር ሳይሰማ፣ ጀንበር ወደ ምዕራብ ዘቅዘቅ ማለት ስትጀምር ማራኪም ተማራኪም ባንድነት መጡ። የሔዱት ወታደሮች ኻያ ያህል ሲሆኑ፣ ተይዘው የመጡት ሰዎች ግን ወደ መቶ ይጠጋሉ። አብዛኞቹ ሴቶች ናቸው። ከወንዶቹ መከካለ ጎራዴና ነፍጥ የያዙት ከአምስት አይበልጡም።

ተይዘው የመጡትን ሰዎች ሁሉ፣ ዘብ ዙሪያቸውን ቁሞ ተከማችተው እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ ቴዎድሮስ ዙሪያውን ዐለፍ መለስ በማለት አስተዋሉዋቸው። «እሺ ምንድን ናቸው?» ሲሉ አለቃ አድርገው የላኩትን ጠየቁት።

«ነጋዴ ነን ነው የሚለው» ሲል የዘመቻው መሪ መለሰ፣ ከተቀመጡት ሰዎች መካከል አንዱን በእጁ እያመለከተ።

«ነጋዴ? እንዲህ አርጎም ንግድ የለ። በጥቂት አህያ፣ በአንድ በቅሎ በሦስት ኢጋሰስ መዓት ሴትና የቀረውን ወንድ እየነዳ ምን ይሆን የሚነግደው? ጨው ነው? እህል?» አሉና ቴዎድሮስ ዙሪያውን እየተመለከቱ ተወራጩ። ከወንዶቹ ፍርጥም ፍርጥም ያሉት ከሴቶቹ ልጅ እግሮቹ በጥንድ መታሰራቸው ምን ዐይነት ንግድ መሆኑን ያስታውቅ ነበር።

ከድንጋይ ላይ ቁጭ አሉና «እስቲ ነጋዴውን አምጣው» ሲሉ አዘዙ።

በአለባበሱ፣ ጥምጥም ኩታ፣ ከማደፋ የተነሣ ቀለሙ የማይለይ አብደላ ከኔ እጀ ጠባብ፣ ሱሪ፣ ድግ ሁሉንም ያቀላቀለ ጠና ያለ ሰው እየተገፈተረ ከቴዎድሮስ ፊት ተደፋ።

«እንዲህ መሆኑ ምንም አይረባህ። መሬትና ጫማ መሳምህ ለኔ ፋይዳ የለውም። ይልቅስ ለምንና የት እንደምትሔድ ንገረኝ» አሉት ቴዎድሮስ።

«ለንግድ፣ ለንግድ ነዋ አባ ታጠቅ» ሲል አሁንም ድፍት ቀና እያለ መለሰ።

«ከጥቂት ጭነት ስንቅ በቀር ሸቀጥ አላይም። ይኸን ሁላ ሴትና ወንድ ነው የምትነግደው ሸቀጥ? ‹ስንተዋወቅ አንተናነቅ› » አሉ። የባርያን ንግድ ተከለከልኩ ስንት ዓመት ሆነው? ባርያ የሸጠ፣ የገዛ አይቀጡ ቅጣት እንደምቀጣው ታውቅ የለ?»

«ባርያ ኮ አልያዝኩም አባ ታጠቅ፣ እግዜር ምስክሬ ነው» በምሕረት ልመና አሁንም ደፋ ቀና አለ።

«የግዜርን ስም በሐሰት አታንሣው» አሉ ቴዎድሮስ በቁጣ። «ዛዲያ እነዚህ የታሰሩት ሁሉ ምን መሆናቸው ነው? አንስሶች?» መለስ ብለው የምሬትና የፌዝ ሣቅ ቃጣቸው።

«ኢየሩሳሌም ስለምንሔድ መተማ ድረስ አሻግረን ብለውኝ ነው።»

«እግር ተወርች ታስረው?»

«ሽፍታው እያደባ አንዳንዱን ነጥቆ እየወሰደ ስላስቸገረን ነው አባ ታጠቅ።»

«ስሜን አትጥራ ቀጣፊ! መዋሸትስ ቢሉህ እንዲህ ነው?»

«ኧረ እውነቴን ነው!» አሁንም መሬት ሳመ።

«እንግዲያው እሺ ይጠየቁ።»

ሰዎች እየተመሩ ቀረቡ።

«አሁን በእስላም ተይዛለች። ተባብረን እናስለቅቃት ብላቸው ክርስቲያን ነን የሚሉት ያውሮፓ መንግሥት ችላ አሉ። ዛዲያ እናንተ እየሩሳሌም መሔድ ለምን ፈለጋችሁ?» አሉ ቴዎድሮስ ሰዎቹ ለነገሩ እንግዶች መሆናቸው ከአስተያየታቸው ያስታውቅ ነበር።

«ንገሩኝ እንጂ፣ ወይንስ አይደለም?»

«ተየቤታችን የተሠፈራችን፣ በማናውቃቸው ሰዎች እየታፈንን መነዳታችንን እንጂ፣ ኢየሩሳሌም የሚባለውን ነገር ዛሬ ገና መስማታችን ነው። ‹ጽድቁ ቀርቶ በውል በኮነነኝ› አሉ። ኢየሩሳሌም ቀርቶ ለቤታችን በበቃን» በማለት አንደኛው ስለ ሌሎቹ ተናገረ።

«ዛዲያ?» ሲሉ ቴዎድሮስ ፍርጥም ባለ አነጋገር ነጋዴ ነኝ ባዩን ጠየቁት። ድምፃቸው የተገታ ይሁን እንጂ እንደ መንቀጥቀጥ የሚሉት ከንፈሮቻቸው፣ በሰውየው ላይ እንደ ጦር የተተከሉ ዐይኖቻቸው የታፈነ ይመስል፣ ቁርጥ እያለ የሚወጣው ትንፋሻቸው ከውስጥ ከቁጣቸው እንደ እሳተ ገሞራ የሚፈላና የሚያቃጥላቸው መሆኑን ይገልጹ ነበር። በመገረም ዐይነት ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ተመለከቱት። «እኔን ጨካኝ ለማሰኘት ነው እንጂ ለንደዚህ ላለው ምንስ ቅጣት ይበቃዋል?» አሉ ከራሳቸው ጋር። «ወደዚያ ውሰድና ዐርባ ግረፈው።»

ሰውዬው እየተገፈተረ ሊወሰድ ሲል በሚያስደቅን ቅልጥፍና ተፈናጥሮ ከእግራቸው ሥር ሲንደፋደፍ ነበር ከጣቱ ላይ የሚያብለጨልጨውን የወርቅ ቀለበት ድንገት የተመለከቱት። አሠራሩ ልዩና ለብዙ ዓመታት በጣታቸው ላይ አድርገውት የኖረ ስለ ነበር ለመለየት ጊዜ አልወሰደባቸውም። «ቆይ ቆይ እስቲ! ተየት አመጣኸው ይኸውን ቀለበት?» ሲሉ በጃቸው እያመለከቱ ጠየቁት። የሚሰጠን መልስ ለመስማት ያህል እንጂ አሁን የሰውየውም መልክ በመጠኑ ትዝ ይላቸው ጀምሮ ነበር።

ሰውየው መልስ ለመስጠት አመነታ።

«ተናገር እንጂ በሰው ተነገድክ መቾም ሌላው ሕሊናህ አይከብደውምና ዘርፈኸው ነው? ሠርቀኸው?»

«ኧረ እርስዎ ነዎት የሰጡኝ ጃንሆይ» ሲል በፈራ ተባ መለሰ።

«የታ?»`

«ደብረ ታቦር፤ ፊታውራሪ ገብርዬ የሚባሉትን የጦር አዝማችዎንና ሚሽታቸውን ተጭልጋ ይዛቸው የጣመጣሁ ጊዜ!»

«አዎ! አሁን እውነትህን ነው!» አሉ ቴዎድሮስ በማስታወስ ዐይነት ራሳቸውን እየነቀነቁ።

ሰውየው ተደፋፍሮ፤ ለቴዎድሮስ ታማኝ በመሆን ምክንያት የጋረድና የአገው ንሱሡእ ሰዎች በየጊዜው ጉዳት ሊያደርሱበት መሞከራቸውን እያጋነነ መተረክ ጀመረ።

«ሌላ ሌላ መወሻከቱን ተወው» ሲሉ ቴዎድሮስ አቋረጡት። «ብቻ ያን ጊዜ ገብርዬን በደኅና ስታደርስልኝ መልካም ሥራ ሠርተህ ነበር። አሁን ዛዲያ ምን ሆንኩ ብለህ ነው፤ አገሬንና ወገኔን የሚጐዳ የጥፋት መንገድ የተከተልከው? መነገዱን፣ ማትረፉን የከለከለህ የለ?» ሲሉ በትዝብት ጠየቁት።

መልስ አልሰጠም።

«ወንጀልና ጥፋት ለመሥራት እንዲያመቻቸው፤ ‹ዐፈር ቁሉ፣ ድንጋይ ቀቅሉ› እያለ የሚያፋጥጥ መሪ መጣብን ተሚሉት ወስላቶች አንዱ መሆንህ አይደለም? እኔማ እንግዲያው ለሠራኸው መልካም ሥራ ውለታ የጣቴን ቀለበት ሰጥቼህ ነበር፣ ቀራጭ እንዳያስቸግርህ ይረዳሃል በማለት። አንተ ግን መልሰህ እጄን ነከስከው። እንዲያውስ ማን ያውቃል፣ ለበጎ ሥራ የሰጠሁህን ቀለበት ለባርያ ንግድ ኬላ ማለፊያ አድርገኸው ይሆናል። እሚገርም እኮ ነው?» ቴዎድሮስ ለጥቂት ጊዜ አሰብ አድርገው፣ «እንዲያው ስለ ቅጣቱ ሐሳቤን ቀይሬአለሁ። ሁለተኛ ወገኑን እያሰረ ባርያ አድርጎ እንዳይነዳበት ሁለት እጁን ቁረጥና በአንገቱ ላይ አንጠልጥለህ ልቀቀው። ለእንደዚህ ያለው ተዚህ ያነሰ ቅጣት አይገባውም»

ሲሉ አዘዙ።

አንዱ ወታደር የሰውየውን እጅ የኋሊት ጠምዝዞ ቀለበቱን ለማውለቅ ሲሞክር ተመለከቱና፣ «ተው! ምንም በተግባሩ ቢያረክሰው አንዴ የሰጠሁትንማ መልሼ አልወስደው። ታንጉት ላይ አንጠልጥሎ ያጊጥበት« በማለት ከለከሉት።

የታሰሩት ተፈትተው እህል ውሃ ሲሰጣቸው ሌሎቹ ለጥያቄ እንዲቀርብ ተደረገ። ሦስቱ ነፍጣቸውን አንድ አራቱ ጎራዴያቸውን ተገፍፈው ስለ ነበር ሁሉም ጀሌዎች ሆነዋል።

«እነዚህ መሣሪያ ይዘው ነበር» ሲል የተላኩትን ወታደሮች የመራው አለቃ በእጅ እየጠቆመ አመለከተ። አባ ታጠቅ ግን የሚናገረውንም ሆነ የሚያመለክተውን እምብዛም አይከታተሉም ነበር። ዐይናቸው ከአንድዋ ልጅ እግር ሴት ላይ ተተክሎ አስተያየታቸው ግን የጠፋባቸው አንድ ነገር የሚፈልግ ይመስላል። አቸፈር ዘመቻ መሔዱን ላፍታ ዘንግተው «ገብርዬ!» ሲሉ በመጥራት ዙሪያቸውን ቃኙ። ትዝ ሲላቸው ተዉትና «አንቺ የታንጉት ልጅ አይደለሽም?» ሲሉ በጥርጣሬ ጠየቋት።

«አዎ! አባ ታጠቅ።»

«ዛዲያ ተነዚህ ጋር ምን አብሮ አመጣሽ? መቅደላ አምባ ገብተው ነበር ማለት ነው ሲሉ በመገረም ጠየቋት።

«እሜቴ አዘውኝ እሳቸው ናቸው ያመጡኝ» አለች አንገቷን ወደ ጐን ጠምዘዝ አድርጋ ባለጥምጥሙን ሰውዬ እያመለከተች።

ማንነቱን ለማረጋገጥ ዐይናቸውን ላንዳፍታ በእርሱ ላይ ማሳረፍ ብቻ በቃቸው። መቆጣት ቀርቶ መናገር ታከታቸው። አገጫቸውን ከመዳፋቸው ላይ አስደግፈው ከፊታቸው የተደቀነባቸውን ትርዒት ማየት ያልፈለጉ ይመስል ዐይናቸውን ከደን አድርገው ባንድ እጃቸው ጭፍርር ያለ ቁንዳላቸውን እያፍተለተሉ ዝም ብለው ቆዩ። በአካቢያቸው የነበረውም ሁሉ የሠቀቀን ጣዕራቸው ተሰምቶ አብሮ በዝምታ ተኮማተረ። ጸጥ ረጭ አለ። «አሁንም አንተ ነህ?» አሉ ቆይተው ቆይተው ከሩቅ ዓለም የመጣ በሚመስል ድምፅ። ለሰውየው ሳይሆን ለራሳቸው ያቀረቡት የመገረም ዐይነት ጥያቄ ነበር።

መልስ አልሰጠም። ጨርሶ ተስፋ በመቁረጥ ላመል ያህል አንገቱን ቀልበስ አድርጎ፤ የሚሠነዘርበትን ሰይፍ የሚጠባበቅ ይምሰል እንጂ ብርኩ እንደ መንቀጥቀጥ ሲል ከሱሪው በላይ ያስታውቅ ነበር።

«ለመሆኑ ይኸ ሰይጣን ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ?» ሲሉ ቴዎድሮስ በዙሪያቸው የቆሙትን ጠየቁ። «ወይኒ ላይ ሕዝብ ያስጨረሰ ያስጨፈጨፈ ጋረድን በምኞት እንደ ፈረስ እያስጋለበ ደባርቅ ላይ ያንን ሁሉ ሕዝብ ያስጨረሰ ለጥፋት ለተንኮል የተፈጠረ....... እሱ ነው» ዛዲያ እንደዚህ ያለውን ተሰይጣን የከፋ ሰይጣን ተባብ የባሰ መርዘኛ ምናርገው ትሉኛላችሁ?»

የፍርድ ትችት ከዚህም ከዚያም ተሰነዘረ።

«ተሰቅሎ ሲሞት ይታየኛል።»

«እንደዚህ ያለው ግፈኛ አረመኔ በሰም ተነክሮ እንደ ጧፍ ይቃጠላል ይነድዳል።»

«በፍትሐ ነገሥት እንደ ተጣፈው በድንጋይ ተወግሮ ይሞታል።»

«ተመክዳት አንሥቶ እስተ ማሸፈትና እስተ መሸፈት ተዚያም አንሥቶ ሰው እስከ ማስገደል እስከ መግደል እስተ ማስፈጀት፣ የሰው ንብረት እስተ መዝረፍ፣ በአባ ታጠቅ ላይ እስተ መዋሸት ኧረ ምኑ ቅጡ! ስለይህም ሁላ በብሉይም በሐዲስም በኋላም በፍትሐ ነገሥት የተደነገጉትን ጥፋቶች ሁሉ ሠርቷል ፈጥሟልና በሁላውም በየተራ ሲቀጣ ይታየኛል።»

«ሐሳቡ ጥሩ ነው» አሉ ቴዎድሮስ በመገረም አኳኋን፤ «ግና የዘረዘርኳቸው ጥፋቶች በሞት የሚያስቀጡ ቢሆንስ? አንድ ሰው ስንት ጊዜ ይሞታል? አንዴ ከገደልከው በቃ አይደል?»

«አሃ! አሃ» ፍርድ ሰጭው ትንሽ ግራ ተጋባና ነቃ አለ። «የሞቱን ቅጣት አቆይቶ በሌላ በሌላ መቅጣት ነዋ!» ሲል አስተካከለ።

ቴዎድሮስ የብዙዎቹን ፍርድ ዝም ብለው አዳመጡና በተለይ የመጨረሻው ትንሽ ቢያስገርማቸውም የሁሉም ያላጠገባቸው መሆኑን በሚገልጽ አኳኋን ራሳቸውን ነቀነቁ። «አያችሁ? አሁን ይኸ ምኑ ይገደላል?» አሉ ዐይናቸውን በአክሊሉ ቁመና ላይ ተክለው። «ምናልባት አታውቁትም እንጂ የሞተ ሙት እኮ ነው። እንደ መቃብር ጋኔን ለመልከፍ ለማጥፋት ብቻ ነው እኩይ ትንፋሹን የሚተፋው። የቀትር ምታት ምኑ ይገደላል? ለእንደዚህ ያለው ለሥራው የሚተካከል ምንስ ያች ምንትዋብ የሚሏት አሚናና ይኸ ጋኔን እንዲህ እኔን ነክሰው አለቅም ያሉበት ምህኛት ነው። ያች እንኳን ተበደልኩ ብትልም ከፋትዋ ታፍ ልፍለፋዋ አያልፍም። ይኸ ግን....» የታከቱትን ያህል ባንድ ልባቸው......እባክህ አሉ ተዚህ ሁሉ ገላግለኝ› እያሉ በልባቸው እየተማጸኑ። «ወዲያው!» ድንገት እጃቸውን በማወራጨት።

«ምን ላድርግ ዛዲያ አባ ታጠቅ?» ሲል የወታደሮቹ አለቃ ጠየቀ።

ከመቅጽበት ይሠነዘራል ብሎ የጠበቀው ሰይፍ በመዘግየቱና ንግግር በመቀጠሉ አክሊሉ አንዳች ቅንጣት ተስፋ ዘርግቶበታል። «ይፈቀድልኝና ልናገር» አለ በለዘብታ አነጋገር።

«ምን? ደሞ አሁንም መርዝህን ልትረጭ?» አሉ ቴዎዶስ የሚተናነቅ ስሜት ያመቀው በሚመስል ድምፅ። «ኧረ ሰዎች አንድ በሉና ተፊቴ አስወግዱልኝ!» ማስወገድ የሚለው ቃል በመጨረሻ ቅጣትነቱ የገባቸው ወታደሮች ጉራዴ እየመዘዙ ነፍጥ እያጉረሱ አክሊሉን በማዳፋት ዘወር አድርገው ሲወስዱት ቴዎድሮስ አንድ የረሱት ነገር ትውስ እንዳላቸው ዐይነት፣ መዳፋቸውን ከግንባራቸው ለጠፉና «እስቲ እስቲ ቆዩ» ብለው ወደ እርሳቸው እንዲቀርብ አደረጉ። «ሰው ተሆንክ ለነገሩ ሰይጣንም ቢሆን ምሥጢሩን ይገልጣል ይላሉ፣ አንድ ነገር ብቻ ንገረኝ። ታንጉትን ምን አድርገሃት እንዴት ተመቅደላ እንደ ወጣህ ብቻ......»

አክሊሉ ተጠፋ አይቀር ይዞ ለመጥፋት ምሕረት የሚያገኝ ተሆነ መናገሩ ሊያሥምረው እንደሚችል ተስፋ በማድረግ አክሊሉ ቴዎድሮስን ከሰዎቹ መካከል ወደዳር እየመራ ሔደና ተረከላቸው።

ቴዎድሮስ ሲያዳምጡት ሕይወት ካለው ሰው አንደበት የሚወጣ ድምፅና ቃል አልመሰላቸው አለ። አክሊሉ የሠራውን የሆነውን ሁሉ ርቱዕ በሆነ አንደበት ይተርካል። ግን በአነጋገሩ የጸጸት ቀርቶ የጥላቻ ወይም የበቀል ስሜት የለውም። ሰው ይቆጣል፣ ሰው ይናደዳል፣ ሰው ያዝናል፣ በዚህም ስሜቱ የድርጊቶች ይፈጽማል። አክሊሉ የተረከላቸው ግን፣ እንደ ተመልካች በመሰለ የደመነፍስ ወይም የበድን አነጋገር ነእብር። ቴዎድሮስ ሁናቴው ከማስገረም ዐልፎ አጠይፎአቸው ወደ ሰዎቹ ይዘውት ተመለሱ።

«እንዳትገድሉት! ሙት ነው። ምኑ ይገደላል? በዚህ ላይ አሁን ላስበው በሕይወት ለሱ የሚበቃ ቅጣት ዐይነትም ያለ አይመስለኝም።»

ወታደሮቹ ምን እንደሚያደርጉ ግራ ተጋብተው ዝም ብለው ቆሙ። «እንዲያውም» አሉ ቴዎድሮስ አዲስ ሐሳብ እንደ መጣላቸው ለጠቅ አድርገው። «እንዲያውም እሱው ራሱ ይወስን። ገመድ ወይም መጫኛ ስጡት። አልሞትኩም ሕይወት አለኝ ልብ አለኝ፣ ሐሞት አለኝ ታለ ያሳየን። ቢሠውርን ታሪክ መቸም ሳትሰማው አልቀረህም» አሉ ወደ አክሊሉ አተኩረው። «ተሱ ብሰህ ታቃተህ ግን መቸስ ምን አደርጋለሁ? በድንህትህን ራስህ መሰርክህ ማለት ነው። አዎ፤ አልሆንለት ታለ በድኑን ነውና በቁሙ ቅበሩት።»

ቴዎድሮስ የፍርዳቸውን ውጤት ማየት ያልፈለጉ ወይም ሥፍራውን ድንገት የተጸየፉት ይመስል ወዲያው ዘወር ብለው መንገድ ጀመሩ።

«ሌሎቹንስ ምን እናርጋቸው» አሉ ቴዎድሮስ በታከተ አንደበት። ወደ ታንጉት አገልጋይ በእጃቸው እያመለከቱ፣ «አንቺ ደሞ ነይ እስቲ ነይ። ታሪኩን ልስማው» አሏት።

አክሊሉ ከተመረጠለት ዛፍ አግዳሚ ግንድ ላይ ገመዱን አስሮ ሸምቀቆውን እንደ ምንም ከአንገቱ አስገባ። ግን እግሩን ከተቆናጠጠበት ቅርንጫፍ ላይ መንቀል አቅቶት ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ በጣዕረ ሞተ ዐይነት ብዙ ተንዘፈዘፈ። በመጨረሻ በደመ ነፍስ ጅው ብሎ ሲወረወር ከሱሪው ሥር ርጥበት መታየቱ ማምሻውን በሠፈር ሲወራ ቴዎድሮስ አልሰሙም። ፍርድ እንደ ሰጡ የታንጉትንም ጉዳይ ለማጣራት ጥቂት ራሳቸውን ወደ መቅደላ ጉዞ ጀምረው ነበር።

ገብርዬ ከአቸፈር ዘመቻ ተመልሶ የአክሊሉን ፍጻሜ እንደ ሰማ በመገረም መልክ ለቴዎድሮስ አነሣባቸው። «እንዲያው ለመጨረሻ ጊዜ መልኩን ባይ ደስ ይለኝ ነበር» አለ።

«ሰይጣን ማየ ምኑ ደስ ያሠኛል ብለህ ገብርዬ?»

«እውነትም ሰይጣን። ያንን ሁሉ ጠባቂ ዐልፎ እንዴት ከመቅደላ መውጣትስ ቻለ? ሰይጣን ቢሆን ነው እንጂ» ገብርዬ በመገረም ራሱን ነቀነቀ።

ቴዎድሮስ በትካዜ ተውጠው ዝም ብለው ቆዩ። ቀደም ሲል ሊነግሩት ወስነው ነበር። ራሳቸው የተሳሳቁትን ያህል ገብርዬንም አብሮ ማሳቀቁ መልሶ ከበዳቸው።

«መቸም ጠባቂዎችን በገንዘብ አታልሎ መሆን አለበት» ሲል ገብርዬ ቀጠለ።

ቴዎድሮስ  በቅሬታም በማስተባበልም ዐይነት ራሳቸውን ነቀነቁ። «እውነቱን ማወቅ ትፈልጋለህ ገብርዬ?» ሲሉ ጠየቁት ዕዳውን መወጣት እንደማይቀርለት መርዶ ድንገት ቆርጠው።

ገብርዬ የቴዎድሮስን አጠያየቅ ግራ አጋብቶት በመገረም ተመለከታቸው።

«ጉዱ ተኛው ነው!» አሉት።

አሁንም ሊገባው አልቻለም።

«አዎ! ታንጉት ናት እንዲወጣ የረዳችው!» አሉና ቴዎድሮስ በሰፊው ተነፈሱ።

«ምን?» ሲል ጮኸ ገብርዬ። «ምን ነካት? ምን ሆንኩ ብላ? ኧረ ምን ነካኝ ብላ? እኮ ምን ነክቷት?» እያለ ከመደጋገም በቀር የሚናገረው ጠፋው።

«ማን ያውቃል ገብርዬ? ጊዜ ምሥጢሩን ይፍታልን እንጂ!» አሉት በማጽናናት፣ ትከሻውን ጨበጥ አድርገው።

«እ - እሷም?» ገብዬ አንዳች ስሜት እየተናነቀው መልሱን መስማት ያልፈለገ ይመስል ጥያቄውን አቋርጦ ተወው።

«እሷም ራሷ ጠፍታለች» አሉ ቴዎድሮስ በሐሳብ አንገታቸውን ደፋ አድርገው። ከራሳቸው ጋር የሚሚገቱ ይመስላሉ። በመጨረሻ ጉዳዩን ከሐሳባቸው ያሰናበቱ በሚያመስል መልክ አንድ እጃቸውን ወንጨፍ አደረጉ።

ከዚህ በኋላ እንደማይነካ ቅዱስ ታቦት ወይም ርኩስ ነገር ቆጥረው የተዉት ይመስል የታንጉትን ጉዳይ ሁለቱም ሌላ ጊዜ አላነሡትም።

«ሳብ! ሳብ! ጎበዝ በርታ! ኧረ ጎበዝ በርታ! ሳብ ሳብ! ባንድነት ሳብ! ጎበዝ ግፋ! ሳብ ጎበዝ!.....» እራፊ ጨርቅ ከራሱ ላይ አስሮ ነጠላውንና ድጉን ከወገቡ ላይ የጠፈረው ቀስቃሽ፣ ዳር ዳሩን እየተራወጠ ላንቃው እስኪዘጋ ድረስ ያበረታታል። ይዘልፋል። አንዳንዴም ለማስፈራራት ያህል አለንጋውን ወይም ዱላውን ያወዛውዛል።

ቴዎድሮስ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ከወደፊትም ከወደኋላም ከመኻል ገደማም እየተገኙ እንቅስቃሴ ይመራሉ። ይቆጣጠራሉ። መንኰራኵርን ገመድና መጫኛውን ይፈትሻሉ። የዛለ ሰውነት ሲያዩ «ምነዋ! እንዲህ አርገህ አትስበውም?» ብለው ራሳቸው ይገቡበታል። አነገብርዬ እነገልሞ እነዓለሜና ሌሎችም የጦር አበጋዞች «እኛ እየለን አባ ታጠቅ!» ሲሉ ተረባርበው ያስጥሉዋቸውል። ዓለማየሁ ከአጠገባቸው ቱስ - ቱስ ይላል። ከብት የተጫነለት ቢሆንም፣ የአባቱን ድካም ለመጋራት የፈለገ ይመስል ብዙውን ጊዜ የሚጓዘው በእግሩ ነው።

ጉዞው ከተጀመረ አንሥቶ ዘወትር ከፊት የሚቀድመው ሴባስቶጶል የተባለው ትልቁ መድፍ የተጫነበት ባላ አራት መንኰራኵር ሠረገላ ነበር። ለእጅ ጨበጣ እንዳይተርፍ ተመጥኖ በተደራረብ ገመድና መጫኛ ረድፍ ገብቶ የሴባስቶጶልን ሠረገላ አቀበት ከፊት ሆኖ የሚስበውና ከኋላ ሆኖ የሚገፋው ቁልቁለት ላይ ከኋላ እየተሳበ የሚገታው ሰው ከአምስት መቶ ይበልጣል። ሃምሳም መቶም ሰው እየተሳበ የሚገታው ሰው ከአምስት መቶ ይበልጣል። ሃምሳም መቶም ሰው የተሰለፈባቸው ሌሎቹ ሠረገላዎች በዚሁ ዐይነት ከኋላ ይከተላሉ። ከሠረገላዎቹ ሁሉ እህል የሚያዘጋጁ ሴቶች ዐይነት ከኋላ ይከተላሉ። ከሠረገላዎቹ ሁሉ ኋላ እህል የሚያዘጋጁ ሴቶች ለሥራ የደከሙ ሽማግሌዎችና በሽተኞች ይጓዛሉ።

ጎድጓዳው እየተሞላ ጉብታው እየተደለደለ በጠቅላላው ለመንኰራኵር የሚሆን መንገድ ቢጤ እየተሠራ ቆላ ሲወርድ ደጋ ሲወጣ ለነጠላ እግረኛ ጥቂት ቀናት ብቻ የሚወስደው፣ ከጋፋት እስከ መቅደላ ያለው መንገድ ብዙ ወራት ፈጀ። እልህ የሚያጋባ እልህ የሚያስጨርስ ጎታታ ጉዞ ነበር።

የእንግሊዝ ጦር ከምጽዋ ተነሥቶ ወደ መኻል በመገሥገሥ ላይ ነው። የገነቡት የኢትዮጵያ አንድነትም በየሥፍራው ተናግቶ የየራሳቸውን ብቸኛ ሥልጣን ያወጁ ክፍሎች ተነሥተዋል። የአንድ መንግሥት ግዛታቸው ከመጥበቡ የተነሣ ሽፍቶች ከሠፈራቸው አቅራቢያ አደጋ እስከ መጣል ደርሰዋል። በዚህ ሁሉ መካከል ለመጨረሻ ፍልሚያቸው ወደ መቅደላ የሚያደርጉት ጉዞ ዕረፍት ቀርቶ ፋታ የሚሰጥ አልነበረም።

ጤዛ መርገፍ ሳይጀምር ገና በጧቱ ሠፈር ይቀሰቀሳል። ቀድመው ተነሥተው «አስነሳሣ አንጂ» ብለው ትዕዛዝ የሚሰጡት ቴዎድሮስ ራሳቸው ናቸው። ከዚያም ፀሐይዋ እስከትበረታ እስከ ተሲአት ጉዞው ቀጥሎ እህል ለመቅመስ ያህል ያታረፋል። እንደገና ውጣ - ውረድ ሳብ - ጎትቱ እንደ ቀጠለ ውሎ ፀሐይ ስትጠልቅ ለአዳር ሠፈር ይደረጋል። በበነጋው እንደዚህ ይቀጥላል።

በዚህ ዐይነት የዘወትር ጉዞ እንደ ቀን እንደ ተበተ ጕረምሳ ደረቱን የገለበጠ በሚመስል ዳገት ላይ ሲለፉ ውለው ጀንበርዋ ወደ ምዕራብ ዘቅዘቅ ስትል ትልቁ ሠረገላ ከጉብታው አናት ላይ ወጣ። ግራና ቀኝ ጭልጥ ያለ ገደል ሆኖ ሠራዊቱ ከነሠረገላው እንደ ምንም እየተቧጠጠ የወጣው አቀበት የኮረብታው አናት ከአንድ ትልቅ አውድማ አይሰፋም። ትልቁ ሠረገላ በዚህ ጠባብ ሥፍራ ላይ ደርሶ ሲቆም ሌሎቹ ሠረገላዎች ከኋላ ከአቀበቱ ላይ ተሰልፉ። ከየመንኰራኩሩ ሥር ከተሻጠው ድንጋይና የግንድ ጉማጅ ጋር ደልዳላ መቆሚያ እስቲገኝ ቀኑን ሙሉ እየሳበ የመጣው ሠራዊት አሁንም ሠረገላዎቹን በመጫኛውና በገመዱ ገትሮ መያዝ ነበረበት።

ትልቁን ሠረገላ ከኮረብታው አናት ላይ ያደረሱት እፎይ ለማለት ያህል ጫን ጫን እየተነፈሱ ላባቸውን በጨርቃቸውና በእጃቸው ሊጠራርጉ፤ ከኋላቸው የተከተሉት እያቃሰቱ ተወጥረዋል። ቴዎድሮስ የኮረብታውን አናት ዙሪያ - ገብ ለቅጽበት ቃኙና ጥቂት አሰቡ። የኮረብታው ደልዳላ አናት ሁሉንም አጠቃልሎ ማሥፈር አይችልም። አብዛኛው ሠራዊትና ጓዝ ከነሠረገላዎቹ ከዳገቱ ጥግ ማሳደር ደግሞ አሥጊ ነው። ወንበዴዎች ጥግ ጥጉን መጥተው አደጋ ሊጥሉበት ይቻላሉ። ካሁን ቀደምም ሞክረውታል። ሰው ባይገድሉ የየመንኰራኩሩን ማስደገፊያ እየፈነቀኑ ቢለቁትስ? ስንት ዓመት የተደከመበት ሥራ መና ሆኖ ቀረ ማለት ነው። መድፍ ከሌለ ጀሌ ሆኖ እጅን መስጠት እንጂ የእንግሊዝን ጦር በምን ይፋለሙታል? የደከመው ሠራዊትም ቢሆን ከየመንኰራኩሩ ሥር እንደ ተኛ ሳይታወቀው በእንቅልፍ ልቡ ማስደገፊያውን ድንጋይና ግንድ ሊያንሸራትተው ራሱም ቢሆን እየተንከባለለ ገደል ሊገባ ይችላል።

እጅግ ደፋታ የሆነ አጭር ቁልቁለት ወረድ ብሎ ግን ለኮረብታው አናት እንጂ፣ ትከሻ የሆነ ሁሉንም ለማሥፈር የሚበቃ ደልዳላ ሥፍራ መኖሩን ቴዎድሮስ ተመለከቱ። ሠራዊቱ በድካም መዛሉን አላጡትም ነበር። የራሳችውም አካል ቢሆን በመዶሻ እንደ ተቀጠቀጠ ያህል ይሰማቸዋል። ግን፣ እንደ ምንም ከደልዳላው ሠፍሮ ማደሩን መረጡ። «እስቲ በሉ ጎበዝ ዳገቱን ዘንዳ ቁልቁል ተዚያች መድረስ አያቅተንም» አሉ በእጃቸው እያመለከቱ።

ሴባስቶጳል የተጫነበት ሠረገላ ከደፋታው ጫፍ ላይ እንደ ተጠጋ ከፊት ሆኖ ሲስብ የነበረው ሠራዊት ከወደ ኋላ ተዛወረና ገመድና መጫኛውን ስቦ ያዘ። ጥቂት ሰዎች መንኰራኩሩን ወድደ ፊት ገፉ አደረጉት መንኰራኩሩን የገፉት ሰዎች ይቻኩሉ ወይ ገመድና መጫኛውን የያዙት ሰዎች ጨርሰው ይዛሉ አይታወቅም ድንገት ድብልቅልቁ ወጣ። ሠረገላው እንደ ደነበረ ከብት ባልታሰበ ፍጥነት ተፈትልኮ ሲሽከረከር፤ ዳርና ዳሩን ይጠባበቁት የነበሩት ሰዎች ወደ ኋላ ተፈናጠሩ። ገመድና መጫኛቸውን ስበው የያዙት ሰዎች እየተጨዋጨዋሁ ለመግታት ቢሞክሩም ብዙዎቹ እየተንሸራተቱ አብረው ወረዱ። ጥቂቶቹም እየተደናቀፉ በመውደቅ መሬት ለመሬት ተጎተቱ።

«ጎበዝ ለቀቃችሁት? ገደል አስገባችሁት ጎበዝ!» ልጃቸው ውሃ እንደ ወሰደው ወይም ገደል እንደገባ ቴዎድሮስ እየተንደረደሩ ሔደው የሠረገላውን መንኰርኩር ተጋተሩት። እያላጋ ይዟቸው እየወረወረ ትግል ገጠሙት። ዓለማየሁ በልጅ እግሩ እየበረረ እንደ ልጅ እያለቀሰ ከኋላቸው ደረሰ። «አባዬ! አባዬ!» እያለ ጮኸ። ቴዎድሮስ ግን ከተያያዙት ትግል በቀር ምንም ነገር አይሰማቸውም፤ አይቻላቸውም ነበር። ያንን መድፍ፣ ባለ የሌለ ኃይላቸው ካላዳኑ አብረው ገደል ለመግባት የቆረጡ ይመስል፣ ከመንኰርኩሩ ጋር ትንቅንቃቸውን ቀጠሉ። ሲያላጋቸው ሲያሸንፋቸው «ወይኔ መይሳው!» እያሉ።

ሠራዊቱ ከድንገተኛ ድንጋጤው ብንን እያለ የአባ ታጠቅንና የሴባስቶጳልን የመጨረሻ ትግል ሲመለከት እንደ ጦር እየተወረወረ ገባ። ከቅጽበት አብዛኛው ሠራዊት ከሠረገላው ፊት ተጋፈጠ። ግማሹ እንቅፋት በማድረግ ሊማገድ ሲሞክር ከመሪውና ከመድፉ ጋር አብሮ ከፍጻሜው ለመድረስ የሚረባረብ መሰለ።

በሰው ኃይል ብቻ ሳይኖ እንዳጋጣሚ በትርምሱ መካከል የሠረገላው አንድ እግር ከተጠረገው ጒዳና ወጥቶ ከዛፍ ጋር ተናከሰና ተገታ። ተነፍቶ እንደ ተለቀቀ ፊኛ ሁሉም በኃይል ተነፈሰ። እፎይታው ግን ለአጭር ጊዜ ብቻ ነበር። በጫጫታው ተውጦ የቆየ የሥቃይ ድምፅ ወዲያው ከያለበት አስተጋባ። የሠረገላው መንኮራኩር መኻል አካላታቸውን የጨፈለቀው እያጣጣሩ ጨርሱን ይላሉ። እግራቸው ቋንጃቸው ክንዳቸው የደቀቀው ያቃስታሉ። ቴዎድሮስ ራሳቸው ከሚሽከረከረው መንኮራኩር ጋር ሲተናነቁ ሁለት እጃቸው ተገሽልጦ ልብሳቸው በደም ተነክሯል። ግን የራሳቸውን ቁስል በሻሽ ጠቅልለው እየመሩና ትዕዛዝ እየሰጡ ሠረገሎቹ ሁሉ ቀስ በቀስ ከደልዳላው ሥፍራ እንዲወርዱ ተደረገ።

ሠፈር ተተክሎ ቴዎድሮስ እየተዘዋወሩ ፈትሸውና ቁስለኞችን አበረታትተው ከትንሽ ድንኳናቸው በራፍ ከድንጋይ ላይ ዐረፍ ሲሉ ጀንበርዋ በምዕራብ አድማስ

መጥለቅ ጀምራ ነበር። አብሮ ወዲያ ወዲህ ሲል የቆየው ዓለማየሁ ከአጠገባቸው ተቀመጠ። ለጥቂት ጊዜ አባትና ልጅ ዝም ብለው ተያዩ። ዓለማየሁ በተለይ ትኩር ብሎ የሚያስተውለው እንደ ማሳ ትልም በፊታቸው ላይ ነበር። ድንገት ብድግ አለና በእጅጌው ይጠራርግላቸው ገባ።

«አይደክምህም አንተ የኔ አካል? ለምን ገብተህ ጋደም አትልም?» አሉት ኀዘን በተጫነው ቁልምጫ።

«አንተስ አይደክምህም አባዬ?»

«እኔማ ትልቅ ነኝ!»

«ትልቅ ብትሆን ዛዲያ ለምን በጣም ትለፋለህ?»

«አየ የልጅ ነገር! ምንላርግ ብለኸኝ አካሌ!»

«ቅድምኮ ሠረገላውን ሩጠህ ስትይዘውና ሲሸከረከርብህ በጣም ደንግጬ ነበር።»

«ደሞ የምን መደንገጥ አመጣህብም!» አሉ ቴዎድሮስ በፌዝ ቁጣ።

«እስቲ እጅህን አባዬ?» ሲል እንደ ገና ጠየቃቸው በሻሽ የተጠቀለለ መዳፋቸውን በጥንቃቄ እየነካ።

«ደኅና ነው።»

«ይኸ መድፍ ያንጊዜ አቃጠለህ። አሁን ደሞ.......» ሲል ዓለማየሁ ቅሬታውን አንጠልጥሎ ተወው።

ሲባስቶጳል ከቅርጽ ማውጫው ተሠርቶ በወጣ ጊዜ የደረሰባቸውን ማስታወሱ ነበር። ቅርጽ ማውጫው ሸክላ ተሰባብሮ በሴባስቶጳል ሙሉ አካል ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ዐይናቸው ሲያርፍ፣ ቴዎድሮስ በስሜት እጅግ ከመዋጣቸው የተነሣ ተንደርድረው ሳሙት። ግለቱ ጨርሶ አልነበረም ነበርና ትሸሽ አድርጎ ከንፈራቸውን አነፈረው። ሳምንት ሙሉ ደረቅ ምግብ መጉረስ አቅቷቸው ነበር።

«ይኸንን መድፍ አትጥላው የኔ አካል» አሉ ቴዎድሮስ የዓለማየሁ ሐሳብ ገብቷቸው። «የኢትዮጵያ ጠላቶች ሊያጠቅዋት የሚመጡት እንደዚህ ያለ መሣሪያ ኃይል ስላገኙ ነው። ለጀግንነቱ እንደሆነ፣ እነ ገብርዬን እነ ገልሞን እነ ዓለሜን ማን ያህላቸው ነበር? ሌሎቹ ቱርክ ሳይቀር ተራራ ተሻግሮ የሚጎዳ መሣሪያ ሲኖራቸው እኛ ከጥቂት ነፍጥ ከጎራዴና ዱላ ገና አልወጣነ ነገር። ደካማ ያደረገን ይኸ ነው።

ለደካማ ማን ይተኛለት ብለህ? አሁንም እነሆእ መጥተዋል። እስቲ እንተያያለን» ቴዎድሮስ የመጨረሻውን ቃል የተናገሩት በዛቻ ሳይሆን በጸጸት መልክ ነበር።

በሠፈሩ እሳት ተቀጣጥሎ ሁሉም በያለበት ወደራት ቢጤው መሰማራት ሲጀምር ምንትዋብ ባንድ እጅዋ መሶብ ወርቅ ከደረትዋ አስደግፋ ይዛ፣ በሌላ እጅዋ ቅል አንጠልጥላ፣ እየተጣደፈች መጣችና «እህል ቅመስ ይልቅስ!» አለቻቸው ቴዎድሮስን ትዕዛዝ ይሁ ግብዣ ባለየት ኮስታራ አነጋገር።

በድምፅዋ ዐውቀዋት «አሁንም አንቺው ነሽ?» ሲሉ ቀና ብለው በመገረም ተመለከቱዋት።

የሁለቱ ነገር ጠብ ይሁን ዕርቅ በቀል ይሁን ይቅርታ የማይለይ እየሆነ ከሔደ ሰንብቷል። ዱሮ በአሽሙርና በግጥም ያለማቋረጥ ትወርድባቸው ያልነበረውን ያህል አሁን - አሁን አንድ ጊዜ ስትዘልፍ፣ ሌላ ጊዜ ታሞግሳቸዋለች። አንድ ጊዜ ስትወቅስ፣ ሌላ ጊዜ ታደንቃቸዋለች። ቴዎስሮስም ቢሆኑ፣ የዘፈንና የልቅሶ ግጥምዋ እንደ ጦር ያልወጋቸውን ያህል፣ ዓላማቸውን ለማሰናከል ሌሎች ከሚፈጽሙባቸው በደል ጋር ሲያስተያዩት፣ የምንትዋብን ነገር እንደ ልጅ ልፍለፋ እየቆጠሩት ሔደዋል። ነገርዋ አንድ ውል ያልያዘ በመሆኑ፣ በቤተ ሰቦችዋ ብዙዎች ምክንያት አእምሮዋ እንደ ተነካ አድርገው የሚመለከቱዋትም ብዙዎች ናቸው። በተለይ አብዛኛው ሕዝብ ከደብረ ታቦር ከተነሣ በኋላ፣ ምንትዋብ ከቴዎድሮስና ከሠራዊቱ አካባቢ ባለመለየት በምታሳየው ሁናቴ፤ «አሁንማ ሊለይላት ነው!» መባል ጀምራለች። አንድ ጊዜ ምግብ ከሚያሰናዱት ሴቶች መኻል ገብታ ታተራምሳለች። በዚህ መካከል ግን፣ በጋፋትም ሆነ አሁን በጉዞ ላይ እንደ ሌሎቹ አጋዥ ሴቶች አካል ሆና መታየት ይዛለች። ደብረ ታቦር ላይ አንድ ጊዜ እስከነአባቱ ወርፋና ረግማ ያላስለቀሰችውን ያህል ዓለማየሁም ቀስ በቀስ እየተላመዳትና እየቀረባት ሔድዋል።

«ዝም ብሎ ማሰብ ወንዝ አያሻግርም ተብሏል። አሁን የእህል ውሃ ጊዜ ነው» አለ ምንትዋብ የጠየቋትን ሳትመልስ የያዘችውን ሞሰብ ወርቅ ከቴዎድሮስ ፊት እያስቀመጠች።

«ባያሰኘኝስ?» ሲሉ በቀልድ ፌዝ ጠየቋት»

«አይዞህ አትፍራ።»

«ምኑን?»

«መርዝ እንዳላደግብህ ብለህ እንደሆነ።»

»ማን ያውቃል?» አሏት አሁንም በቀልድ መልክ።

«እኔ ምንትዋብ! የሆነው ይሁን እንጂ በመርዝስ አልገልህም! ጭራሽ!»

»እህሳ?»

«በሌላውማ ውነድ ብሆን ነበራ!» ስትላቸ ቴዎድሮስ ፈገግ አሉና ሞሶበ ወርቁን ጠጋ አደረጉት።

«ግና እንደዚህ አለቅህም ብለሽ የትከተይኝ ለምንድ ነው?» ሲሉ ጠየቋት።

«የብደደልከኝን ስትውቀው ትጠይቀኛለህ? ጥላህ ሆኘ ገና እስከ መቃብር እከተልሃለሁ።

«በግል ፍላጎቴ አይደለ! ያገር ጉዳይ ሆኖብኝ ነው እንጂ» አሉና ቴዎድሮስ በቅሬታ ላፍታ ሐሳብ ያዛቸው «ጥላ? ጥል፤አ አልሽኝ? ጥላኮ የሚኖረው ብርሃን ሲኖር ነው። እኔ ግን ጀንበሬ እየጠለቀችብኝ ምን ጥላ አለኝ ብለሽ እንግዲህ! እስተነምሳሌው ‹ጥላ ቢስ› ይባል የለ?»

«እሳትም፣ መብራትምኮ ጥላ አለው» ስትል ላለመረታት ተከራከረች።

«ማን እንደ ጀንበር!» ቴዎድሮስ እንደ መተከዝ አሉና ለጠቅ አድርገ፣ «እና እስከ መቃብሬ ትከተይኛለሽ? ልታለቅሽብም ነው? ልታለቅሽልኝ?» ሲሉ ጠየቋት።

«እንደሆነው። መጀመሪያ እስቲ ለዚያው ያብቃህ!» አለች በቀልድ መልክ።

«ምን ብለሽ?

ጥያቄውን ያልሰማች በመምሰል፣ «ብላ አንተ ልጅ! እንዳባትህ ዝም ብለህ ቆዛሚ አትሁን» ስትል ቆሎ የያዘውን መሶበ ወርቅ ወደ ዓለማየሁ አስጠጋችለት።

«ንገሪኝ እንጂ!» አሏት በድጋሚ «እኔ ስሞት ምን ብለሽ እንደምታለቅሺ?»

«ሰው ሲሞት ምን ተብሎ እንደሚለቀስለት አስቀድሞ መስማት አለበት? አሆሆ! እንደዚህ ያለ ጉድ ሰምቸም አላአውቅ» አለች በውሸት መኮሳተር።

«ተሞትኩ በኋላማ ዛዲያ የታባቴን እሰማዋለሁ። ይልቅስ አሁን ንገሪኝ።»

«አሆ! ተልጅ ፊት ስለ ሞት አይወራም። ነውር ነው።»

»እንዳይፈራ ነው? የኔ አካል ሞት ትፈራለህ?» ሲሉ ዓለማየሁን ጠየቁት።

«ታንተ ጋራ ተሆንኩ አልፈራም!»

«እሰይ የኔ አምበሳ! ይኸውልሽ! በይ ንገሪኝ!» ለመሔድ ቃጣች።

«ቆይ ንገሪኝ እንጂ! በሕይወቴ እያለሁ እንዲያ እየወረድሽብም ተሞትኩ በኋላ ለምትይኝ እንዳልቆጣ ነው?»

«ብትቆጣ ማን ይፈራል?»

ቴዎድሮስ ሣቅ አሉ። «ደፋር ተሆንሽ ንገሪኝ!» የቴዎድሮስ ውትወታ ከሞቱ በኋላ የሚበሉትን ለማወቅ ጓጉተው ሳይሆን ከጥቂት ጊዜ በፊት በደረሰው አሰቃቂ አደጋ እጅግ የተጫናቸውን ስሜት ቀለል የሚያደርግ ሌላ ጭውውት ለማምጣት ያህል ነበር።

«ምን ቸገረኝ!» ላንዳፍታ አሰበችና አመጣችው።

«አባ ታጠቅ ብሎ ለምን ስም አወጣ

ፈረንጆች ሲመጡ ተሥራው ተታጣ?»

ቴዎድሮስ ሳያስቡት ከት ለው ሣቁ። «አሆሆ! ይህማ ሸሽህ ማለትሽ ነው!»

የቴዎድሮስን ድንገተኛ የሣቅ ድምፅ የሰሙ ሁሉ በመገረም ጆሮዎቻቸውን ቀና አደረጉ። ቶርነትና ድሉን አብረዋቸው ከተካፈሉት ባለሟሎቻቸው መካከል ብዙዎቹ በየራሳቸው ፈገግ አሉ። የዛሬን አያድርገውና ሕይወታቸውን በተስፋና በደስታ የሚያቀጣጥል ድምፅ ነበር። አሁንም ድጋሚ አልሰሙትም። ብልጭ እንዳለ ወዲያው መልሶ ድርግም አለ።

«ፈረንጆች ሲመጡ» የሚለው የምንትዋብ ቃል ሠቀቀናቸው ውስጥ መልሶ ዘፈቃቸ። የሀገራቸውን ቅዱስ መሬት ረግጦ ከረከሰው ጠላት ጋር የሚያደርጉት ፍልሚያ ከፊታቸው ድቅን አለ። ለዚያ ፍልሚያ በሚደረገው ጉዞም በዕለቱ እንደ ደረሰው አደጋ፣ ሁሉ ነገር ከነገ ወዲያ ከዚያ በስቲያ የሚጠብቃቸው ከባድ ትግል አሰባቸው...... «በዕለቱ አደጋ የሕይወቴ ፍጻሜ ቢሆን?» የሚለው ጥያቄ በአእምሮዋቸው የመጣው በዚህ ቅጽበት ነበር። ዓላማቸውን ሕልማቸውን፣ ሳያዩ ያልፉ ነበር። ለነገሩማ ሕልሜና ዓላማዬ ጨልሞብኝ የለ? ታቅሜ በላይ ተሆነብኝ መቸስ ምን አደርጋለሁ? አሉ ከሐሳባቸው ጋር። «እንደ እኔ ማለም፣ እንደኔ ማቀድ ብቻ ሳይሆን፣ ያቀደውን ለመጀመር የጀመረውን ለመጨረስ ጊዜውም ሁናቴውም የተሻለ ዕድል የሰጠው መሪ ያምጣልሽ አንጂ ሀገሬ!» ሲሉ ተመኙላት።

በዓላማቸው የተቆራኙዋቸው ሰዎች ዕድልስ? የእያንዳንዱን ለማየት ሞከሩ.... እንግዳ ሸምገል ብለዋል። በዚህ ላይ ብልጥም ወላዋይም ስለሆኑ ይዘልቁት ይሆናል። ዓለሜ ጀግናም ብልህም ነው። መንገዱን አያጣም ገልሞ በዘሩ

ምክንያትም በእልኸኝነቱ ትንሽ ገለልተኛ ስለሆነ፣ ከተከፋ ተመልሰው ጭልጋ በመውረድ የዱሮ ኑሮውን መቀጠል የሚችል ዐይነት ነው።

ከገብርዬ ላይ ሲደርሱ ከሁሉም የከበደ ሐሳብ ያዛቸው። ገብርዬ ጀግና ነው። ቅንጣት የማይጠረጠር ታማኛቸውም ነው። ራሳቸው ለዚህም ነበር ምሥጢሩን ሁሉ ሳይገልጹለት ታንጉትን ያጋቡት። ተዋበችን እንዳገኙ፣ የሚያምኑዋትን የሚተማመኑባትን ሚሽት የሰጡት መስሏቸው ነበር። በእርግጥም መልካም ሚሽት ሆናለት ነበር። በመካከላቸው ጥሩ ፍቅር እንደነበርም ተገንዝበዋል። ዛዲያ በዘርዋና በመካንነቷ ምክንያት ከጥፋት ላይ ወደቀች። የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ገልጸውለት ቢሆን ኖሮ ይሻል ነበር? ከራሳቸው ንዴት በተቀር ሠቀቀኑንና ኀዘኑን አይችለውም በማለት ነበር የተዉት። በነገሩት ብቻ ስንኳ ከፍተኛ ትካዜ እንዳደረበት ሰሞኑን ከሁናቴው አስተውለዋል። ፊታቸውን ለማየት ይመስል ግድ ካልሆነበት በስተቀር ከአጠገባቸው መገኘቱን እየተወው ነው። አሁን እንዳይነግሩት ጊዜው አለመሆኑ ተሰማቸው። በጦርነት ዋዜማ ላይ ለዘመቻው ይዘጋጅ? ወይስ ጸጸት ያስታምም? «አዎ! የሁላችን የግል ሕይወት በሀገራችን ሕይወት ላይ የተመሠረተ አይደለ?» ሲሉ ደመደሙ።

ሌሊቱ ገፋ። ሰዉም በያለበት እየተጋደመ የድካም እንቅልፍ ወሰደው። ዓለማየሁ ከአባቱ ጭን ላይ ደገፍ እንዳለ ሽልብ አደረገው። በየሥፍራው ሲነድ የነበረው እሳት፣ ማገዶው እያለቀና ቆስቋሽ እየጠፋ አካባቢውን ጨላማና ጸጥታ ነገሠበት። የጠፋ ሕልማቸውን ያመለጠ ዓላማቸውን የሚፈልጉ ይመስል አባ ታጠቅ ብቻ ከትንሽዋ ድንኳናቸው በራፍ ተቀምጠው ዐይናቸውን በጨለማው ላይ እንደ ተከሉ ቀሩ.....

**ተፈጸመ**

# ድኅረ ታሪክ

ገብርዬ፣ በወርቀ ዘቦ የነደደ ያንበሳ ቆዳ ለምድ ለብሶ አንፋሮ ደፍቶ ጣምራ ጦር ይዞ ወታደሩን እየመራ በቴዎድሮስ ፊት ሲያልፍ «ናማ እስቲ እንደዬ ገብርዬ» አሉት ቴዎድሮስ። ነጠል ብሎ ወደ ቆሙበት ሔደ።

በስንት መከራ ከጋፋት ከመጡት መድፎች ትልቁና ከፍተኛ ግምት ጥለውበት የነበረው ሴባስቶጶል ሁለት ጊዜ ከተተኮሰ በኋላ በሦስተኛው ፍርክስክሱ ወጥቶ ወድቋል። የቀሩት አነስተኞቹ የሚተኩሱት አለሎ ከዒላማው ሳይደርስ ከወደዚህ እየቀረ፣ በባዶ ሜዳ አቧራ ያስነሣል። የእንግሊዝ ጦር ታች አርጌ ላይ ሆኖ የሚተኩሰው ግን የቴዎድሮስን ሠፈር ያደባልቀዋል። ሬሳ በየቦታው ወድቋል። ቁስለኛ በያለበት። በሩቁ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሰውን መሣሪያ ስላልቻሉት ከእንግሊዝ ጦር መኻል ገብቶ ለመዋጋት ገብርዬ ሠራዊቱን እየመራ ወደ አርጌ መውረዱ ነበር። ክንዱን ይዘው ወደ ጐን ወሰዱትና አንጀት በሚበላ አዘኔታ ተመለከቱት። «እንግዲህ መቸም የምንሆነው አይታወቅምና ልሰናበትህ ብዬ ነው። ለመሆኑ ታንጉት የደረሰችበትን ታውቃለህ?» ሲሉ ድንገት ጠየቁት።

ባልሆነ ጊዜ ያልሆነ ጥያቄ ስለቀረበለት ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ «ምናባቷን ደሞ ዐውቄላት?» በማለት መለሰ።

«ዘጌ መቃብር ቤት ነው ያለችልህ። በደኅና ተተመለስክ እኔም ባልኖር ሔደህ አምጣት፣ ይበቃታል።»

«ምን ዕንቆቅልሽ ነው የምትነግረኝ አባ ታጠቅ?»

ምንም ዕንቆቅልሽ የለበትም። በቅጣት ነው ያጋዝኳት። ለምን አልነገርሽኝም ብለህ አትቀየመኝም። ሌላ ያልነገርኩህ ነገር አለ። ጥፋትዋ ከባድ ቢሆንም እኔም የበደልኩዋት መስሎ ቢሰማት ደግሞ አልፈርድባትም።

«ደሞ ምን ብደልካት? አቀማጠልካት እንጂ!»

ቴዎድሮስ ለጥቂት ጊዜ በትካዜ ተመስጠው ቆዩና «እኅቴ እኮ ናት!» አሉ በመጨረሻ።

«ምን?» የገብርዬ አነጋገር ከጥያቄ ይልቅ የግራሜና የድንጋጤ ዐይነት ነበር።

«አዎ! የእኅቴ ልጅ እኅቴ፣ አባቴ ለአደን ሲዘዋወሩ ወይኒ ላይ ከሌላ ሴት የወለዱዋት የእኅቴ ልጅ ናት። ለምን ደብቀኸኝ ኖርክ ብትለኝ፣ ለአባቴም ለእናቴም ስል ነው። አባቴ እናቴ እንዳትቀየም ብለው፣ ምናልባትም ከቅማንት በመውለዳቸው አፍረውበት ጭምር ሊሆን ይችላል፣ በድብቅ ይዘውት ኖሩ። እኅቴ በዚህ ተቀይማ የአባቴን አባትነት እስተ ሕይወቷ ፍጻሜ እምቢ ብላ ቀረች። ውርደትና ንቀት የማትወድ በጣም ኩሩ ነበረች። ሳይሆልኝ ቀረ እንጂ እኅትነቷ የሚያኮራ..... እኔንም አስማለችኝ። ታንጉት የልጅ ልጅ መሆንዋ እንዳላወጣ። ታንጉት ግን ሳመጣት ገና ልጅ ብትሆንም ሳታውቅ የምትቀር አትመስለኝም። ዛዲያ የቴዎድሮስ እኅት መባል

ትፈልግ ኖሮ ይሆናል። አሳደጋት ከመባል፣ እኅትነትዋን የደበቅሁት ምናልባት በቅማንትነትዋ ምህኛት መስሏት ይሆናል። የሰው አስተሳሰብ መቸም አስቸጋሪ ነው።» ከዚያም እስተርን የጻፈባቸውን ታሪክ በከፊል ታንጉት የነገረችው መሆንዋን ይህንን ደብተራ አክሊሉ አወጣብሻለሁ ብሎ በማስፈራራት ለማምለጥ እንድትረዳው ማድረጉን ተረኩለት። የአምባ ጊዮርጊስን ጉዳይ ግን አልነገሩትም። የዚያ ዐይነት ምሥጢሮች ተቀብረው መቅረታቸው የሚሻል መሆኑ ተሰማቸው።

«አንተስ ቢሆን ቅማንት እኅቴ ናት ብዬ ብድርልህ ደስ ይልህ ነበር?» ሲሉ በሁለቱም ላይ የተጫነው ትካዜ ለማቃለል ያህል በቀልድ መልክ ጠየቁት።

«ምነው ሌላው ሁላ ሴት እንደሷ ቅማንት በሆነ!» አለ ገብርዬ ለታንጉት ያለው ፍርቅና አድናቆት ድንገት ተቀስቅሶበት።

«አዎ! ለነገሩማ ቅማንት ሆነ ወይጦ ያው ሰው ነው። ተሰውነቱ ላይ ልዩ ምልክት የለበት። ብቻ ብዙው ሰው የዘመኑ ልማድ እስረኛ መሆኑ አልቀር ይላል እንጂ። አንዱ ልፍቴም ወገኔ ተንደዚህ ያለው ልማድ እንዲላቀቅ አልነበር።

«ተዚህ ውጊያ በኋላም ገና ብዙ እንሠራለን።» ገብርዬ ትካዜያቸውን አይቶ ለማበረታታ ያለው ነበር።

«ይመስልሃል ገብርዬ?» ሲሉ ትኩር አድርገው አስተዋሉት። «ያም ሆነ ይህ፣ ያለፈው ዐልፏል። ወንድምዋ ምን ያህል ይወዳት እንደነበረ ንገራት።» ጉንጩን አገላብጠው ሳሙትና ትከሻውን በመዳፋቸው ጠብ ጠብ አደረጉት። «በል ሒድ ይቅናህ!»

ቁልቁለቱን ሲወርድ ዕንባ ቸፍ ያለበት ዐይናቸው ተከተለው........



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ብርሃኑ ዘርይሁን በ1925 ዓ.ም በጎንደር ከተማ ተወለዱ፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቤተክርስትያን ትምህርት ተምረዋል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጎንደር ይገኝ በነበረው በቀድሞው ቀዳማዊ ሃይለሥላሴ ትምህርትቤት አጠናቀቁ፡፡ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በተግባረ እድ ትምህርት ቤት በሬዲዮ ቴክኒሺያንነት ሙያ ተመረቁ።

ሥራ የጀመሩትም በመምህርነት ነው። በወቅቱ በካርታ ሥራ ድርጅት ቴክኒሺያንነት ሙያ ሠርተዋል። ከዚያም የጦር ሚኒስቴር እየተባለ ይጠራ በነበረው የአሁኑ መከላከያ ሚኒስትር በአስተርጓሚነት አገልግሏል። ማስታወቂያ ሚኒስትር እንዲዛወሩ ከተደረገ በኋላ የኢትጵያ ድምጽ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነዋል። ከሶስት አመት በኋላ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነው የማይረሳ ተግባር አከናውነዋል።

ብርሃኑ ዘርይሁን የደረሱት ‹ሞረሽ› በ1972 ዓ.ም፤ ‹ጣጠኛው ተዋናይ›በ1975 ዓ.ም እና ‹አባደፋር› በ1977 ዓ.ም፤ የተባሉት ቴያትሮቻቸው ተወዳጅ ነበሩ።

ከጻፏቸው መጻሕፍት ውስጥም ‹የቴዎድሮሥ እንባ › በ1958 ዓ.ም፤ ‹የእንባ ደብዳቤዎች› በ1961 ዓ.ም እና የታንጉት ምሥጢር› በ1978 ዓ.ም፤ እንዲሁም ለረጅም ተከታታይ ጊዜያት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ሲተረኩ የነበሩት ‹የአብዮት ዋዜማ፤ የአብት መባቻና የአብዮት ማግስት› የተሰኙት ማጸሐፍት ይገኙበታለል።

ብርሃኑ ዘርይሁን ለሐገራቸው የስነ ጽሁፍ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አበርክተዋል። በቀዳሚዎቹ ዘመናት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበርን በሥራ አመራር አባልነት ካገለገሉት መካከል አንዱ ብርሃኑ ናቸው።

**ምንጭ:** የኢትዮዽያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ማእበል የአብዮቱ ዋዜማ(**ልብወለድ**)
2. የአብዮቱ መባቻ(**ልብወለድ**)
3. የእንባ ደብዳቤዎች(**ልብወለድ**)
4. የቴዎድሮስ ዕንባ(**ልብወለድ**)
5. ድል ከሞት በኋላ(**ልብወለድ**)
6. የበደል ፍጻሜ(**ልብወለድ**)
7. ጨረቃ ስትወጣ(**ልብወለድ**)
8. የአብዮት ማግስት(**ልብወለድ**)
9. የታንጉት ምስጢር(**ልብወለድ**)
10. ሞረሽ(**ተውኔት**)
11. ባልቻ አባነፍሶ(**ተውኔት**)
12. ጣጠኛው ተዋናይ(**ተውኔት**)
13. ብር አምባር ሰበረልዎ(**ልብወለድ**)
14. አማኑኤል ደርሶ መልስ(**ልብወለድ**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY